የቀይ ኮከብ ጉዞ

t.me/BooksandYou

ከበዓሉ ግርማ

t.me/pdfbookscloud

የቀይ ኮከብ ጥሪ

t.me/BooksandYou

ከጠዓሉ ገ/ማ

t.me/BooksandYou

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

© All Rights Reserved

መጀመሪያ እትም 1972 ዓ.ም

ሁለተኛ እትም 1999 ዓ.ም

ሦስተኛ እትም 2000 ዓ.ም

አራተኛ እትም 2010 ዓ.ም

በማንኩሳ ማተሚያ ቤት ታተመ

t.me/BooksandYou

ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ ልብወለድ ነው። በታሪኩ ውስጥ የተከሰቱት ባለታሪኮች (ገፀ - ባህርያት) ሁሉ ደራሲው የፈጠራቸው ናቸው። ባለ ታሪኮቹ በህይወት ከነበሩ፥ ወይም አሁን ካሉ ሰዎች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም። የስም ወይም የባህርይ ተመሳሳይነት ያለ ቢመስል፥ የአጋጣሚ ነገር መሆኑን አንባብያን በቅድሚያ እንዲረዱልኝ እወዳለሁ።

ደራሲው

ምእራፍ ፩

ሰአት እላፊ የተቃረበ ቢሆንም፥ አዲስ አበባ እንደ ወትሮዋ በሰልቹነት አዛግታ ከእንቅልፍ አዘቅት ውስጥ አልተጋደመችም። የውድቅቱ ጨለማ ሰላሙን አጥቶአል። በጅቦችና በመንደር ውሾች ህብረ-ጩኸት ፊንታ የሽጉጥ፥ የመትረየስና የዲሞትፎር ተኩስ ጨለማውን እየሰነጠቀ ያስተጋባል – እንቅልፍ ነስቶ ሆድ እያሸበረ። በየቤቱ እንቅልፍ ያልዞረበት አይን አፍጥጦ ጣራ ጣራውን ይዳስሳል። ባሩድ የሸተታት ሚዳቁዋ ይመስል የሁሉም ጆሮ ተስሎ ቁሞአል።

ወይዘሮ አምሳለ እንደ ልማዳቸው ምሽቱ ሳይገፋ በጊዜ፥ ሁለት ብርጭቆ የአጃ አጥሚታቸውን ጠጥተው፥ ለጋ ቅቤአቸውን በሰርናቸው እንቆርቁረውና እንደ ጨረቃ ክብ የሆነች ትንሽ ፊታቸውን በቀዝቃዛ ወተት ከወለወሉ በሁዋላ፥ ከፊታቸው ላይ ጤዛ መስሎ የሚያብረቀርቅ ቅባት ተቀብተው ሲያበቁ፥ ሻሻቸውን እስከ ጆሮ ግንዳቸው ድረስ ዠርገድ አድርገው አልጋ ላይ ከወጡ የቆዩ ቢሆንም፥ እንደ ፊርጥ በሚንቦገቦገው ትላልቅ አይናቸው እንቅልፍ የሚሉት ጣአመ ነገር ከቶውንም አልዞረም። እንደ ጉርድ በርሜል ከአልጋ ውስጥ ይገላበጣሉ።

አቶ ጉልላትም እንደ ባለቤታቸው እንደ ወይዘሮ አምሳለ እንቅልፍ አጥተው በመቸገር፥ ስንደዶ የመሰለ አፍንጫቸውን ከአንሶላው ብቅ አድርገው፥ ወርዝቶ የሚታየውን መላጣቸውን እያብለጨለጩ፥ እንደ ጉድጉዋድ ውኃ ወደ ውስጥ የራቁትን አይኖቻቸውን ብልጭ ድርግም ያደርጋሉ፤ ወፍራም ሰውነታቸው አባይ ይዞት እንደሚሄድ ግንድ ከአልጋው ውስጥ ይገላበጣል።

‹‹ራዲዮውን አጥፋው! ይህን ራዲዮ የት አባቴ ወስጄ ልጣለው!›› አሉ ወይዘሮ አምሳለ፥ ተበሳጭተው።

‹‹ምን አገኝብታለሁ ብለህ ነው ይህን ራዲዮ ጠዋት ማታ የምትጎረጉረው?››

t.me/BooksandYou

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹ወሬ—ስለ አገራችን የጊዜው ሁኔታ! የኛ ራዲዮ ጣቢያ እንደሆን ከስድብ ሌላ ወሬ የለው! ትክክለኛ ወሬ የሚገኘው ከቢቢሲ፥ ከጀርመን ራዲዮ ጣቢያ፥ ከዶቼቬሌ፥ ከቮይስ ኦፍ አሜሪካ፥ ከሞቃዲሾ ራዲዮ ጣቢያ ነው. . .››

‹‹ለወሬ የለው ፍሬ እቴ! ይልቅ አታደንቁረኝ — አጥፋው!›› አሉ ወይዘሮ አምሳለ።

አቶ ጉልላት ሳይወዱ በግድ ቀኑ ብለው ራዲዮኑን አጠፉ። ከውጭ ራዲዮ ጣቢያ መለየት ፈፅሞ ደስ አይላቸውም። ከጣቢያ ጣቢያ እያማረጡ እሱኑ ሲጎረጉሩ ነበር የሚውሉት።

ራዲዮው ዝም ሲልባቸው ጊዜ፥ አቶ ጉልላት ከሩቅና ከቅርብ የሚሰማውን ተኩስ የምን አይነት መሳሪያ እንደሆነ በልባቸው ይገምቱ ጀመር።

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ! — ሽጉጥ።

ካካካካ! ካካካካ! — መትረየስ።

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! — ዲሞትፎር።

‹‹የመላኩ ያለህ! ይሄኛውስ እዚሁ ቤታችን አጠገብ ነው! ለመሆኑ የውጭው በር በደንብ ተዘግቶአል?››

‹‹ሰንቴ ልንገር!››

‹‹አታመናጭቂኝ እንጂ! አሁንስ ከቀበሌ ተኩስ ባሰብኝ ምላስሽ! ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው ይላል አማራ – እ።››

‹‹ታዲያ ሰንቴ መልስ ልስጥህ?! ከተጠራጠሩ ሂዶ ማየት ነው! ደርቤ– ሰሙን ቁስ ይጥራው እቴ! በሄደ በስንት ጊዜው! ይህን ሰሞን ደሞ ዝም ብሎ አፌ ይገባል አሰር አሰር ጊዜ። – ስንታየሁ ነው በጊዜ በሩን የዘጋው›› አሉ፥ እየተመናጨቁ።

ደርቤ፥ ከህፃንነት ጀምሮ አቶ ጉልላት ቤት ውስጥ በአሽከርነት ሲያገለግል ከቆየ በሁዋላ፥ አብዮቱ ከፈነዳ ወዲህ በሰላም ከቤታቸው ወጥቶ፥ በአቶ ጉልላት አማላጅነት በማስታወቂያና መርህ ብሄር ሚኒስቴር ውስጥ ስራ ከያዘ ሁለት ዓመት አልፎት ነበር። ወይዘሮ አምሳለ ካዩት ሰንበት ብሎአል። ሰሞኑን ስሙ

እየመጣ ከአፋቸው ለምን እንደሚገባ ሊከሰትላቸው አልቻለም። ከቤታቸው ውስጥ በአሽከርነት በቆየበት ዘመን፥ በተፈጥሮአቸውና በታማኝነቱ በጣም ይወዱት ስለነበረ፥ በተቆጡና በተበሳጩ ቁጥር ወይም አንድ ነገር ባስቸኩዋይ በፈለጉ ቁጥር፥ በመጀመሪያ የሚታያቸውና ስሙ አፋቸው የሚገባው ደርቤ ነበር። በአሳባቸው ‹‹ለዚህ ይሆን?›› ብለው ዝም አሉ።

‹‹እህ... እንቅልፍ አጥተሽ ነው መሰለኝ የምትነጫነጪው...››

‹‹ኤዲያ! ሽዋዬ ይሙት – የሰውን ስሜት የማያውቅ ሰው ደስ አይለኝም። አውሬነት ነው›› አሉና ወይዘሮ አምሳለ፥ ተቆጥተው በመገላበጥ ጀርባቸውን አዞሩ።

አቶ ጉልላት የእሜቴን ስሜት አላጤኑም። እሳቸው ለራሳቸው ጆሮአቸው ቆሞ፥ ትናንሽ አይኖቻቸው ፈጥጠው፥ በሞራ ተሸፍኖ የደከመ ልባቸው ትር ትር እያለ፥ ከጨለማው በላይ ነግሶ የሚያስተጋባውን የተኩስ ጋጋታ በፍርሃት ያዳምጡ ነበር።

‹‹ልጆቹ ደህና እንደሆኑ እስቲ ስልክ ደውለሽ ጠይቂ!›› ብለው አዘዙ።

‹‹ስንቴ ልደውል?!››

‹‹ግድ የለሽም እንደ ገና ደውይ። የሚሰማኝ አጣሁ እንጂ እኔማ ሱቅ እንዳያድሩ ብዬ ነበር።››

‹‹ወይ አበሳዬ›› እያሉ ጉርድ በርሜል መሳይ ገላቸውን ጎትተው በመነሳት፥ ስልክ መደወል ጀመሩ። ከአጭር ቁመናቸው በላይ ጎልተው የሚታዩት ትላልቅ ጡቶቻቸው ነበሩ። እንደ ሱቅ በደረቴ የተሸከሙት ጡት የገዛ ጡታቸው አይመስልም፤ ሀፃናት የሚጫወቱበትን የገና ላስቲክ ነፍተው በለሊት ልብሳቸው ውስጥ የከተቱት እንጂ! ከብዙ ዘመን ሙከራ በሁዋላ በስንት መከራ ቀለሙ ደብዘዝ እንዲል የተደረገው ንቅላታቸው ከአጭር አንገታቸው ላይ ይታያል። ወደ ላይ ፍንድር ያለው ትልቅ ቂጣቸው፥ እንደ እርጉዝ ሴት ወደ ፊት ገፍቶ የተንጠለጠለው ሆዳቸውና ትንሽ ክብ ፊታቸው በአንድነት ሲታዩ፥ አሻንጉሊት ያስመስሉአቸዋል።

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹ተኝተዋል መሰለኝ ስልኩን አያነሱም። አሉ› ማዳመጫውን ከጆሮ ግንዳቸው ላይ አጣብቀው።

‹‹የምን እንቅልፍ – በዚህ ሁሉ ተኩስ መሀል? የለም አንድ ነገር ቢሆኑ ነው!››

ወይዘሮ አምሳለ ስልኩን ዘጉ። አቶ ጉልላት ከወገባቸው ቀና ብለው ተቀመጡና› ‹‹እዚያ ሱቅ እንዳያድሩ ብዬ ነበር – ›› ከማለታቸው› ወይዘሮ አምሳለ ለጥቀው› ‹‹ከሰመሀ አትነግራቸውም ኖሮአል? ለወጉ አባት ነህ። እኔን እንደሁ ከመጤፍም አይቆጥሩኝ።ሽረ – ኤዲያ! ባለጌን ካሳደገ የገደለ ይሻላል። ተሰማ እንደሆነ ጠጉሩን አሳፍሮ ጢሙን ማሳደግ ከጀመረ ወዲህ አንደኛውን መረን ወጥቶአል። ቁመቱ ረዝሞ ከመገርጀፉ የጢሙ ማስጠላት! እኔ ማዝነው በሂሩቴ ነው። እንደ አይን ጠፍታለች። ሽቶውን› ልብሱን› ጫማውን ከየት እንደምታመጣው አላውቅም። የት ውላ እንደምትመጣ የሚያውቅ የለም። ሲጠይቁዋት ‹‹አፋ!›› ብላ በሩን ወርውራ ትወጣለች። በር ዘግታ የምትንሾካሾከው ከወንድምዋና ጠርብ ጠርብ ከሚያካክሉ – ትከሻቸው ካበጠ – ማንንም ከመጤፍ ከማይቆጥሩ ያሳፈሩ ጎረምሶች ጋር ነው። እኔ አላውቅም። በነሱ ምክንያት ቆሽቴ የሚደብንበት ምክንያት የለም። የነሱ ነገር በቅቶኛል›› ብለው በረጅሙ ተነፈሱ – በአንድ አፍታ ለተሰማ ጢም ያላቸው ጥላቻ በልባቸው ውስጥ ነፍስ ዘርቶ እየተንቀሳቀሰ።

የተሰማ ቁመት መርዘምና የጢሙ መንገርገግ – ዳዋ እንደ በላው የሰነፍ ገበሬ ማሳ – በጣም ስለሚያስቆጣቸው› ‹‹ልጄ ነው›› ብለው ለሰው ማስተዋወቅ ከተው ውለው አድረዋል። ከታናሽ ወንድማቸው ከጌታቸው ጋር መታየትም ካቆሙ ዘመን የላቸውም–ከርሱ ጋር መታየት ያንን የሚጠሉትን አድሜ አስታውሶ ስለሚያሳጣቸው። የውስጥ አዋቂ! ወንድምም ሸብቶአል! ሲላቸው› ‹‹ያለ እድሜው ነው የሸበተው። አንድ ፍሬ ልጅ ነው እኮ። ሽበት የዘራችን ነው›› ይላሉ።

ስለ ራሳቸውም ቢሆን› ‹‹አህህ! እኔኮ ልጅ ነኝ። አንድ ፍሬ ልጅ ሁኜ ነው ያገባሁት› ገና በአስራ ሁለት አመቴ!›› እያሉ መኩነስነስ ስለሚያዘወትሩ

የአድሜ እኩዮቻቸው፥ ‹‹ማሚቱ መጣች!›› እያለ ስለሚያሾፉባቸውና፥ ወጣት ሴቶችም – ሊመስሉአቸው በሚጠጉዋቸው ጊዜ – ‹‹አማማ›› እያሉ ስለሚጠሩዋቸው፥ ዛፍ ያጣ ጉሬዛ ሆነው እያዘኑ ይበሳጫሉ – አድሜአቸው እንደ ጥላ እየኮበለለ ሲሄድ፥ ግንባራቸው ላይ በቀዝቃዛ ስውር እጁ አርሶ ያለፈውን ፈር አንድ በአንድ ቆጥረው የቀይ ኮከብ ጥሪ እየተመለከቱ።

አቶ ጉልላት ተክዘው እየተፈላሰፉ፥ ‹‹ውሉ ጠፍቶ ከስሩ የተናጋ ህይወት። ወልዶ አሳድጎ ባእድ መሆን። ከጊዜው ነው ከሌላ አይደለም›› አሉ፥ ለሚስታቸው ሳይሆን ለራሳቸው ጆሮ እያጉረመረሙ። ጥቂት አሰቡና፥ ‹‹ታዲያ አሁን ምን ይሻላል?›› ብለው ጠየቁ።

‹‹ምኑን?››

‹‹ልጆቹን ነዋ!››

‹‹የሚሻለውማ መተኛት ነው! ሌላ ምን ማድረግ ይቻላል?››

‹‹እስቲ ደሞ ጌታቸው ቤት ደውዪ። መቼም ይሄኔ እንደ ልማዱ ስክሮ ተኝቶ ይሆናል።

‹‹የሱ ስካር ምኑ ቅጡ። ደሞዙን ሁሉ አንድ ሳንቲም ሳያስቀር ይጠጣበታል። ሚስቱ በቁመናዋ መንምና እየሞተች ነው–በስጋት። ያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር–አሁን ደሞ ምን ብለውታል ልጁ–አምን መርሀ ብሄር ሚኒስቴር–ምን እንዳስነካው አላውቅም!›› ብለው የጌታቸውን መንማና ሰውነትና ሽበት፥ የሚስቱን ከሰውነት መውጣትና ዘወትር ማልቀስ በአይነ ህሊናቸው እየቀረፁ፥ ስልኩን ደውሉ። ስልኩን ያነሳችው የጌታቸው ባለቤት ትእግስት ነበረች። የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጡ በሁዋላ፥ ‹‹ምን ነው ይተናነቅሻል? ታለቅሺያለሽ እንዴ? ደህናም አይደላችሁ? ምን ሁናችሁአል?›› በማለት ጥያቄን በጥያቄ ላይ እየደራረቡ፥ ቁርጥ ቁርጥ ባለ ትንፋሽ ጠየቁዋት።

‹‹ደህና ነን። የለም አላለቀስኩም። አልቅሼ ምን ልሆን?›› ብላ በጎረና ድምፅ መልስ ስትሰጥ ትሰማለች–ትእግስት–እየተነፋነፈች።

‹‹የኢኮብን ትእግስት ነው የሰጠሽ ልጄ። ስምን መልአክ ያወጣዋል አሉ። ፊቴ ባትሆኝም እንባሽ ይታየኛል። ለመሆኑ ሰፊራችሁ እንዴት ነው?››

‹‹ተኩሱ ይቀልጣል። በጣም ያስፈራል። ሰግቼ ወደ እርስም ልያውል ስል ነው ለትንሽ የቀደሙኝ...››

‹‹እኛም ዘንድ ተኩሱ እንደ በረዶ ይወርዳል። ከመጣው መአት እግዜር ይሰውረን ማለት ነው እንጂ ተኩሱስ አይጣል ነው። ለመሆኑ ጌቱ እንዴት ነው?››

‹‹ተኝቶአል... እንቅልፍ አልወሰደውም... ግን መነሳት አይችልም– ልታነጋግሩት ፈልገሁ እንደሆን?››

‹‹ተኝቶ እየጠጣ ነው?››

‹‹ይመስለኛል።››

‹‹ለምን መጠጡን አትቀማውም?››

‹‹በምን አቅሜ? ይግደለኝ ብለሁ ነው?››

‹‹እርሱ የሞተ እንደሁ? ሁዋላ እንደ ጲላጦስ እጅ መታጠብ ይቻላል?›› አሉዋት፥ የስጋ ጉዳይ አላስችል ብሎአቸው። ወዲያውኑ መለስ ብለው፥ ትእግስትንም ላለማስቀየም፥ ‹‹ዳሩ ምን ታደርጊ ልጄ! አበሳ ነው። የሰው ነገር አይቀበል – ቢመክሩት አይሰማ! ጠርሙስን የሙጥኝ ብሎ መሞት – በቤታችን እንኩዋን የለ! ልክፍት ነው። እዚያ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ያቀመሱት ነገር ይኖራል። ለመሆኑ መቼ ነው የተኛው?››

‹‹ሶስት ቀን ሆኖታል። ስራም አይሄድ። ከመስሪያ ቤቱም ይደውላሉ። በር ዘግቶ ዝም ይላል...››

‹‹ያው እንደ ልማዱ ከጠርሙስ ጋር ሱባኤ ገብቶአል በይኛ! የተጠናወተው ሰይጣን አለ–ሌላም አይደል። ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም አሉ። ይኸው ነው መሞቻው›› አሉ፥ አዝነው ሆዳቸውን ባር ባር እያላቸው።

‹‹አባባ ደህና ናቸው?››

‹‹ደህና ነው፡፡›› አሉ፥ ተክዘው፡፡ ትንሽ ቆይተው፥ ‹‹ለመሆኑ ጤፍ አላችሁ?›› ብለው ጠየቁዋት፡፡ ትእግስት ዝም አለች፡፡ የዝምታዋ ትርጉም ገብቶአቸው፥ ‹‹ትንሽ ጤፍ አለኝ፡፡ ጠዋት እልክልሻለሁ፡፡ አይዞሽ፡፡ በይ ደህና እደሪ›› ብለው ስልኩን ዘጉ፡፡

የትካዜ ሽውታ ለጥቂት ጊዜ መታቸው፡፡ የጌታቸው ጠባይ ለእርሳቸውም ሆነ ለሚያውቁት ሁሉ እንግዳ ነገር ስላልነበረ ይህን ያህልም አልተጨነቁበትም፡፡ መጠጡን ለማስጣል መክረው፥ ወትውተው፥ አልቅሰው፥ ለአርባ አራቱ ታቦት ተስለው፥ በጎንም ብዙ ጊዜ አዋቂ ዘንድ ሂደው አስጠንቁለው፥ ደብተራም ክታብ አስፅፈው፥ ምንም አልይዝ ብሎአቸው ተስፋ የቆረጡለት ጉዳይ ስለሆነ እንደ ተከዙ አልቆዩም፡፡ የቀራቸው ነገር ቢኖር አንቀው ጠበል መውሰድ ብቻ ነበር. . . አሳቡን ከአእምሮአቸው አወጡና፥ ፈንደስ ፈንደስ እያሉ በታኮ ጫማቸው ሂደው ቁምሳጥናቸውን ከፍተው ትንሽ ብልቃጥ አወጡ፡፡ ሽቶ ከአንገታቸውና ከትላልቅ ጡቶቻቸው መካከል ካርከፈከፉ በሁዋላ፥ አንድ የተጠቀለለ ሻሽ መሳይ ነጭ ጨርቅ ይዘው እንደፍ እንደፍ እያሉ ወደ አልጋቸው በመመለስ፥ ትላልቅ ጡቶቻቸውን ወደ ባላቸው ደግነው ተጋደሙ፡፡

ወይዘሮ አምሳለ ምንም ቢሆን ያለ ረጅም ታኮ ጫማ አይሄዱም፡፡ ከረጅም ሹል ታኮ ጫማቸው የሚገላግላቸው መኝታ ብቻ ነው፡፡

አቶ ጉልላት መፈላሰፋቸውን በመቀጠል፥ ‹‹ልጆችን ከወላጆች፥ ዘመድን ከዘመድ፥ ጉዋደኛን ከጉዋደኛ፥ ጌታን ከሎሌ፥ አለቃን ከጭፍራ እንዲህ አድርጎ የሚለያይና የሚያናክስ ውሉ የጠፋ ጊዜ! ክፉ ጊዜ ላይ ነው ያለነው፡፡ ከስሩ የተናጋ ህይወት! ኑሮ አይደለም–ስንገነባው የኖርነው ህይወት ምስጥ እንደቦረቦረው ቤት ከፊታችን ተገርስሶ ሲወድቅ ማየቱ፡፡ ይባስ ብለው ደግሞ ነጋ ጠባ አድሃሪ! እያሉ የጨዋን ልጅ ቤተስኪያን የገባች ውሻ ባያደርጉ፡፡ አይ ጊዜ–አያመጣው የለ!. . .›› እያሉ ሲያጉተመትሙ፥ ባለቤታቸው አቁዋረጡዋቸውና፥ ‹‹ምንነው አርፈህ ብትተኛ! የምን ማነብነብ ነው?›› ብለው ጢጋ አሉአቸው–ሽቶአቸውን አስቀድመው፡፡

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ!

የቀይ ኮከብ ጥሪ

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ!

‹‹የመላኩ ያለህ! ዛሬስ አላሳደሩንም! ጥይቱስ አያልቅባቸውም እንዴ?››

‹‹ምነው አርፈህ ብትተኛ – ጉልላቴ›› ብለው አሁንም ጠጋ አሉ፥ ወይዘሮ አምሳለ።

አቶ ጉልላት የሽቶው መልእክት አልደረሳቸውም – ሀሳባቸውን በሙሉ የውጭው ተኩስና የውስጣቸው መፈላሰፍ ይዞታል።

‹‹እንዲያው!. . . አዬዬ! ጉድና ጅራት ከወደሁዋላ!›› አሉ። ‹‹እነዚያን መሳሪያዎች የለም እናስረክብ ስልሽ ቅበር ባትይኝ ምን ነበረበት!›› አሉ፥ እያቃሰቱ።

ወይዘሮ አምሳለ እንደ ቆሰሰ አውሬ ተቆጥተው ከተጋደሙበት ብድግ አሉ። የብስጭትና የማፈር ስሜት የሚፈራረቅበት መልክ ከኮብ ትንሽ ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር። ‹‹ተነስተህ ሄደህ አስረክባ! ማስረከብ ልማዳችሁ ነው!›› አሉ፥ ከጣራው በላይ በነገሰና ስልቱን በሳተ ድምፅ።

‹‹ምን የማስረከብ ልማድ ነው የምትይኝ!››

‹‹ሁሉን!›› አሉ፥ ሻሻቸውን እያስተካከሉ።

‹‹እኮ እኛ እኮማን ነን – ልማዳችሁ ነው ስትይ?››

‹‹ሁላችሁም! ሁላችሁም! ! አየነው ጉዱን እቴ!››

‹‹የቱን ጉድ?››

‹‹የወኔን መሞት ጉድ አልኩህ! ይገባህ እንደሆን? የሰው ስሜት የማይገባው ሰው በድን ነው። ወንዶች ስትባሉ ወኔ አልባ በድን ሁናችሁአል!››

‹‹የመሳሪያውን ነገር ስላነሳሁ አሁን ይህ ሁሉ ውርጅብኝ ያስፈልጋል?››

‹‹ሄደህ አስረክብ አልኩህ! ራስ ደጃዝማቹ ሁሉ አስረክበዋል – እጁን ጭምር። ከጦር ኃይሎች ከፓሊስ ሰራዊትና ከብሄራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ!››

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹አበድሽ እንዴ!››

‹‹ኦ ሆ ሆ ሆ! . . . ጉዱን አየነው እቴ! ራስ እገሌ–ደጃዝማች እገሌ – ጅኔራል – ክቡር አቶ እገሌ–ሰላሬ ስምንት ሰአት ጀምሮ አራተኛ ክፍለ ጦር ድረስ መጥተው እጃቸውን እንዲሰጡ፥ በተባለው ሰአት መጥተው እጃቸውን ባይሰጡ ቤት ንብረታቸው እንዲወረስ የተወሰነ መሆኑን እናስታውቃለን! ካደፈጠበት መጥቶ ‹‹መጣን፥ እዚህ ደርሰናል›› እያለ እጁን ያልሰጠ ማን ነበር?››

መድፉ ሳይተኮስ ቦምቡ ሳይፈነዱ
ያ ሁሉ መኩዋንንት እንደ በግ ተነዱ

‹‹አንተም ሂድ መሳሪያህን አስረክብ!››

‹‹አብደሻል መሰለኝ››

‹‹ሲያልፍም አይነካኝ!››

‹‹እንግዲያውስ በውድቅት ጨለማ ሙት ወቃሽ አትሁኝ!››

‹‹ሙት ወቃሽ አልከኝ? እውነትም ሙት ወቃሽ! የወንድ ያለህ ነው የምለው፥ አልገባህም እንጂ! አሀሀሀ! – ንጉሱን ከስልጣን ለማውረድ የወጣ አዋጅ! ቁጥር አንድ እዝባር ምን ነበር እቴ? ከዛሬ መስከረም ሁለት ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ጀምሮ ንጉሱ ከስልጣን ወርደዋል – ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ! ንጉሱ ተጎትቶ ሲሄድ አንዲት ውሻ ብቻ አስከትሎ–አየነው ጉዱን እቴ! ንጉሱ ከተነኩ ኢትዮጵያ የአምቡዋይ ካብ ትሆናለች – አገሪትዋ በደም ትዋኛለች–ምድር ቀውጢ ትሆናለች – ብርሃን ይጨልማል፤ ተብሎ እንዳልተፎከረ ሁሉ!! ‹‹ዋይ ዋይ ንጉሱ፥ ከእንግዲህ ቀረ በዘር መንገሱ::!!›› እየተባለ ሲዘፈን፥ ‹‹አቤት! አቤት! እግዚኦ›› ከማለት ሌላ ጣቱን እንኩዋን ያነሳ ወንድ አላየንም!››

‹‹በአማላጂትዋ ተይኝ ነው የምልሽ – አንቺ ሴት!››

‹‹የገጠርን መሬት የህዝብ ለማድረግ የወጣ አዋጅ!››

‹‹እብደት ነው የያዘሽ! ጨርሶ እብደት ነው!››

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹አሀሀሀ . . . ከሣሬ የካቲት ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. ጀምሮ የገጠር መሬት የሰፊው ህዝብ ሆኖአል – ጊዜያዊ ወታደራዊ አሰተዳደር ደርግ! ያን ጊዜ ማን ነበር እጁን ያነሳው?!! ዋይ ዋይ ባላባት፥ ከአንግዲህ ቀርቶአል ሳይሰሩ መብላት!! እየተባለ በየአደባባዩ ሙሾ ሲቀልጥስ? አየነው ጉዱን እቴ?››

‹‹ምንነው ብትተይኝ–አንቺ ሴት! ተይኝ ብዬሻለሁ ሁዋላ!››

‹‹ምን ሊኮን? ኤጭ - እቴ! የማንን ርስት ማን ሊነካ! – የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊበድ፥ ያውሬ መፈንጫ ይሆናል እንጂ! መሬት ከተነካ ኢትዮጵያ ጥይት ይዘራባታል፥ የደም ጎርፍ ያጥለቀልቃታል፥ ተብሎ እንዳልተደነፋ ሁሉ! የጥይት ፉጨትና የደም ጎርፍ ቀርቶ ብቅ ብሎ ያጉረመረመ ጉልተኛ – ሰንዝሮ አንገት ቀንጣሽ፥ ተኩሶ ክር በጣሽ፥ ነፍጠኛ፥ አላየንም እቴ!››

‹‹ዋ ብዬሻለሁ!››

‹‹ወንድ አላየንም ስልህ ከዚህ ሁሉ መኩዋንንት! !››

አቶ ጉልላት የባለቤታቸውን ንዝንዝ አልቻሉትም። ወፍራም ቦርጫቸው ተሸክመው ተጎትተው በመነሳት ከአልጋ ወረዱ – ጭልጭል በምትል አይናቸው ወይዘሮ አምሳለን የጎሪጥ አዩና በሀሳባቸው፥ ‹‹ውሉ ጠፍቶ ከስሩ የተናጋ ህይወት!›› እያሉ። እንደወፍራሞች የተንጠለጠለ የሁዋላ ሥጋ ይኸን ያህል የላቸውም። ሆኖም ሰላላ እግሮቻቸው ወፍራም ሰውነታቸውን ተሸክመው ለመቆም የሚችሉ አይመስልም። በግድ የታጠረው ወፍራም አንገታቸው ከጠባብ ትከሻቸው ላይ እንደ ጉቶ ጉች ብሎ ሲታይ ለሰውነታቸው ባእድ ነገር ይመስላል። የጊጃማቸውን ሱሪ አጥልቀው፥ ጋቢያቸውን ደርበው፥ መላጣቸውን እያብለጨለጩ ተጎትተው ሄደው ከመኝታ ቤቱ በር ሲደርሱ፥ ከፍተው ከመውጣታቸው በፊት መለስ ብለው፥ ‹‹ካንቺ ንትርክ፥ የቀበሌን ተኩስ ሳሉን ተኝቼ ባዳምጥ ይሻለል። መቼም የዘንድሮ ነገር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖአል›› አሉ፥ ረጋ ባለ ድምፅ።

ወይዘሮ አምሳለ ከተጋደመበት ብድግ ብለው ከአልጋው ላይ ጉርድ በርሜል መስለው በመቆለል ሻሻቸውን እየነቀነቁ፥ ‹‹ንቀት ነው! ይህ ሁሉ

ንቀት ነው! ምን ታደርግ! ትናንት እመቤትህ ነበርኩ – አምን፥ ዛሬማ መሬቴ ሁሉ ሄዶአል። ያ ለመግ ለማእረግ፥ ፓርላማ ለመመረጥና ክባ ለመልበስ – የተከበሩ አቶ ጉልላት ዋለልኝ የጢቾ ሀገዘብ እንደራሴ ለመባል ያበቃህ! መሬቴ ነበር! ምን ታደርግ! ንቀት ይነስህ? እመቤትህ – እኔ ላንተ እመቤትህ ነበርኩ! ወይ እኔይቱ! እኔ የሸዋሉል ልጅ! . . .›› በማለት ከመግንፈላቸው በፊት፥ ባለቤታቸው ጣልቃ ገቡና ነገሩን ለማብረድ ያህል እየተለሳለሱ፥ ‹‹እኔ እኮ የምትይው ነገር ሁሉ አይገባኝም። ይህ ሁሉ ጭቅጭቅ በስተርጅና! አሉአቸው።

‹‹የምትሄድበት ሄደህ አሮጊትህን ፊልግ። እኔ አሮጊት አይደለሁም። አይደለሁም ብዬሃለሁ። የለው ስሜት የማይገባው ሰው በድን ወይም አውሬ ነው። በድን ነህ! ይገባሃል? አምን – ምድረ መኩዋንንት በድን ከመሆኑ የተነሳ መሬቱን፥ መሳሪያውንና ቤት ንብረቱን ቀርቶ፥ አዋጅ ቢታወጅ ሚስቱንም ወስዶ ሳያስረክብ አይቀርም።››

‹‹ባማላጅትዋ! በማን እድላችን!›› አሉ፥ ፍርጥም ብለው።

‹‹ንቀት ነው እኮ እንዲህ የሚያናግርህ – ዛሬ ጊዜ ከድቶኝ ባዶ እጄን ብሆን! በአምሳለ ትሕሻ ከትቢያ የተነሳህ መሆንህን አትርሳ!. . .››

ወይዘሮ አምሳለ ቀጥሉ ምን እንደሚናገሩ ያውቃሉና፥ አቶ ጉልላት የተለመደውን ዘፈን ቁመው ከመሰማት መሄዳቸውን መርጠው በሩን ክፍተው ወጡ።

ወይዘሮ አምሳለ የሚናገሩት አብዛኛው እውነት ነበር። ስለ ራስ እውነት ሲነገር እንደ አሾህ ይወጋል፥ እንደ አባጨጉራዋ ይኮስኩሳልና፥ አቶ ጉልላት ስለ ራሳቸው የሚነገረውን ቆይተው ለመስማት አልወደዱም። አብዛኛው ሰው ስለ ራሱ በጣም የተሳሳተ ግምት ስላለውና ስለ ራሱ እውነትን ለመስማት ጆሮው ስለማይፈልግ የአቶ ጉልላት ‹ከእውነት መሸሽ› አያስደንቅም። ኢትዮጵያዊ ኩራት ይታያል ሁኔታውን የመንደር ጠበቃ እንደነበሩ ልባቸው ያውቃል። የተገናኙትም ለወይዘሮ አምሳለ ጥብቅና ቆመው – መሬታቸውን ለመቀራመት አሰፍስፈው ከነበሩት ከልኡላንና ከልእልታት፥ ከመሳፍንትና

ከመኮዋንንት፥ ከራሶችና ከደጃዝማችች ለማስጣል ላይ ታች እያሉ ግራና ቀኝ በሚመዋገቱበት ጊዜ ነበር።

አንድ ቀን እንደ አጋጣሚ ወይዘሮ አምላለ ከባህር ማዶ በመጣ ሀር ምንጣፍ ካጌጠች ድንክ አልጋቸው ላይ ተጋድመው ያላዘው የቤት አሽከር እግራቸውን አጥቦ ሲያበቃ – ጥበ ዐሀይ ከመሰለው ጭናቸው ድረስ ዘልቆ ሊያሻቸው ደረሱ – አቶ ጉልላት። ከዚያን ቀን ጀምሮ ከወይዘሮ አምላለ ቤት አልወጡም – ወይዘሮ አምላለ ጎረምሳ እያማረጡ ከቤት ውስጥ እንደ ሙሽራ ዘግተውበት በመቀለብና ሲሰለቻቸው በጠገበ አሽከር ማድር ግንዱን አስይዘው እንደ አሮጌ ቁና አውጥተው ከደጅ በመጣ በአገር የታወቁ እንደነበሩ ባይዘነጋም ቅሉ፥ አቶ ጉልላት ምን እንዳቀመሱዋቸው አይታወቅም – ጎረምሳ የማማረጡን ጉዳይ እርሙ፥ ብለው እርግፍ አድርገው ተውት። ይህ የሆነው ከሰላሳ አመት በፊት ነበር።

‹‹ያጣህ የነጣህ የመንደር ጠበቃ ነበርክ። ስንቱ ያገር መኩዋንንት አደግድጎ እንደ እመቤቴ ማርያም ሲማለደኝ ላንተ የተሸነፍኩ እለት ነው የተዋረድኩ. . . ተይ ነገር የበላ የመንደር ጠበቃ አያዋጣሽም ሲሉኝ አልሰማ ብዬ! . . . ቤቴ ስትገባ የምትለውጠው ሱሪ እንኩዋን አልነበረህም! . . . በኔ ሀብት ነው ሰው የሆንከው፤ ፍሪዳ አሳርጄ፥ ጠጅ አስጥቼ ደግሼ፥ ድፍን የጢቾን ህዝብ ግብር እያገባሁ ነበር ለእንደራሴነት ያበቃሁህ። ስንት ዘመን ሙሉ። ያሾመህስ ማን ሆነና ነው? እኔው አምላለ ነኝ። እነ አቶ መኮንን ሀብተወልድን አስተዋውቄ እኔው ነኝ ለፊውታራሪነት – ለዲሬክተርነት – ለረዳት ሚኒስትርነት ያበቃሁህ።››

አቶ ጉልላት ይህን ሁሉ ዛሬ ባይሰሙም ወይዘሮ አምላለ የሚናገሩት ሁሉ በትዝታ ከጆሮአቸው ውስጥ እያስተጋባ ከአንድ አሮጌ ሶፋ ላይ በጋቢያቸው እንደ አስክሬን ተሸብልለው ተኙ – ‹‹ከሰላሳ አመት ጋብቻ በሁዋላ ይህ ሁሉ ንትርክ! ከስሩ የተናጋ ህይወት!›› እያሉ ለጥቂት ጊዜ ሲያስቡ፥ በወይዘሮ አምላለ ጠባይ ክፍኛ መለወጥ ሲገረሙ ቆዩና፥ ‹‹እንደ አሮጌ ቁና ተጥዬ ጡረታ መውጣቴ ላይቀር የፊውታራሪነት ማእረጌ ይሰረዝልኝ ብዬ ማመልከቴ አሁን ምን ይባላል? አይ የሰው ነገር! ስንት ዘመን ደጅ እንዳልጠናሁበት ሁሉ! ለትንሽ ነው እኮ! ደጃዝማችንቱም ይኸኔ አያልፈኝም

ነበር – አብዮት የሚሉት ጣጣ ባይመጣ ኖሮ!›› በማለት ለመጀመርያ ጊዜ ክፉኛ ተቆጨ። ራሳቸውንም ታዘቡት። የህይወት ጥምባት ሽተታቸው። ክርፋት ክርፋት አላቸው። ሞገድ እያንገላታት መልህቁዋን የምትጥልበት ያጣች መርከብ ይመስል ልባቸው ተንሳፈፈ።

ሁለቱም እንቅልፍ ሊወስዳቸው አልቻለም – ወይዘሮ አምሳለ ተናቅሁ ብለው እየተብከነከኑ – የሽቶአቸው መአዛ ራሳቸውን መልሶ በማወድ እያስጠላቸው – አቶ ጉልላት የቀበሌ ተኩስ እያስበረገጋቸው። ሲያጉዋራ ዲሞትፎሩ–ሰማዩ–ተገምሶ የወደቀ ይመስል ነበር። እንኩዋን የተኛን የሞተን ከመቃብር የሚቀሰቅስ ያህል ነበር የጥይቱ ዶፍ።

አቶ ጉልላት ከወይዘሮ አምሳለ ተለይተው ብርድ ከፍርሃት ጋር ተዳምሮ እያንቀጠቀጣቸው፥ ተጨንቆ ግሎ ጭንቅላታቸው ውሉ በጠፋ አሳብ – ‹‹ነጭ ሽብር! ቀይ ሽብር! የመደብ ትግል! አድሃሪ፥ ተራማጅ ብሎ ነገር፥ ሽብር! ሽብር! ሽብር! የመደብ ትግል እያሉ አገር ባይበጠብጡ፥ የማንም አፈር ገፊ፥ የፊጫይና የእንጨት ሰባሪ ልጅ ሁላ ከመሬት ተነስቶ አገር ያቀና፥ ያስተዳድር ይመስል ከእንጨት ተመርጦ ለታቦት፥ ከሰው ታጭቶ ለሹመት መሆኑን እረስተው!. . .›› ‹‹ጨዋ የጨዋ ልጅ እንደ አውሬ እየታደነ. . . እህህ . . . የራሄል ጩኸት–የናቡከደነጾር ህልም–ሰምንተኛው ሽህ. . .››

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ! – ሽጉጥ።

ከስከስከስ–መትረየስ።

ዱዋ ዱዋ–ዲሞትፎር።

‹‹የመላኩ ያለህ! የሉቃስ ወንጌል ጨርሶት የለ? – ህዝብ በህዝብ ላይ፥ መንግስትም በመንግስት ላይ ይነሳል. . .ታላቅም የምድር መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ–ችነፈር ረሀብም ይሆናል. . .››

ኩዋ! ኩዋ! ሽጉጥ።

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ዲሞትፎር።

‹‹የመላኩ ያለህ! ምዕአት ለጨዋ ልጅ! አድሃሪ እያሉ! የናቡከደነፆር ህልም. . . የሸነላ እግር. . . የሸነላ እግር!›› እያሉ እንቅልፍ ሸለብ እንዳደረጋቸው ቀን በጥላቻ የሰሙዋቸው የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች መፈክሮች –

‹‹አድሃሪያን በሰፊ ህዝብ ክንድ ይደመሰሳሉ!

በአድሃርያን ላይ ቀይ ሽብር ይፋፋማል!

ዲሞን በዲሞትፎር!

ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታል!

ቀይ ሽብር የአብዮቱ አለኝታ ነው!

ነው! ነው! ነው!››

መጥተው በጆሮአቸው ውስጥ እንደ ምዕአት ደወል እያስተጋቡ፥ ሁሉም ግራ እጁን አንስቶ ወደ እርሳቸው ጥርሱን እንደ ሲኦል ጋሻ ጃግሬ አግጦ እያንቀጫቀጨ ሲጠጋቸው በአይነ ህሊናቸው እየታያቸው ወባ እንደ ያዘው ሰው ሰውነታቸው በሙሉ በላብ ተጠምቆ ሳለ፥ እየበረዳቸው በመባነን፡-

‹‹የመላኩ ያለህ! ጊዜ የማይወልደው ጉድ የለ! ጨዋ የጨዋ ልጅ ሞላጫ ድሀን ፊርቶ እየባነነ ሲያድር–እንደ ድኩላ ሰግቶ! ደሞ የቃላቱ ጋጋታ! ለጆሮ የማይጥም እንደ አባጨጉዋሬ የሚኮለኩለ – ሻካራ! ፊውዳሊዝም – ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም – ኢምፔሪያሊዝም–ፊውዶ ቡርዥዋ– አናርኮ – ፋሺስት – ትሮትስካይት – ቀኝ መንገደኛ – ፊዲስት – የመደብ ጠላት – አድሃሪ ብሎ ነገር! በማናውቀው ቁዋንቁዋ መቀባጠር – የባቤል ግንብ – ማን ምን እንደሚናገር ሲጠፋ ሁዋላ ሲናድ እንደ እንቢዋይ ካብ–››

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ!

ከከከከ! – ከከከከ!

ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ!

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹የመላኩ ያለህ! ዛራስ አምረዋል እነዚህ ቀበሌዎች። እህህ ሆሆሆ! ጉድ ነው ኮ! ኢድህ - ኢ.ህ.አ.ፓ-ኢ. ኤል. ኤፍ. ፒኤል. ኤፍ–አልዋህድ . ኢምፔሪያሊስቶች – አድሃሪ የአረብ ገዥ መደቦች – ቀኝ መንገደኞች – ጠባብ ብሄረተኞች – የብሄር ትምክህተኞች–ሰርጎ ገቦች–የተራማጅ ካባ ለቦሾች– የቀበሮ ባህታውያን–ቢሮክራቶች–አድሃሪዎች–ሰላም የሌለው ሰላም ላይሰጥ! ፈሪ ላመሉ ጥላውን ሲጠራጠር! የፈሪ ዱላ መብዛቱ? ‹‹እናሸንፋለን! እናሸንፋለን! ድንቄም ታሸንፋለች!

‹‹ደሞ አዲሶቹ አማልክት መብዛታቸው – ካርል ማርክስ–ኤንግልስ–ሌኒን! ያልተባረከ ትውልድ! አሸክላዎች! ከውኃ ላይ የሚሳፈፍ ኩበት – ከእበት ላይ የፈሉ ትሎች – አባይ እንደሚያገላብጠው ግንድ ማደሪያ የሌላቸው – ጉዶች – የምድር ጉዶች! ግና ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ፥ ቀድሞ ነበር እንጂ አልሞ መደቆስ! በፊት ቀረ። ያንን ሽማግሌ እግዜር ይይለትና! እሱም ዙፋኑም ላይተርፉ አሳልፎ ሲሰጠን– እንደ ይሁዳ። የይሁዳ አንበሳ– ትንቢት ነበር ለካ! ይዝፈኑብን – ይዝፈኑብን ጠዋት ማታ – የፍየል ወጠጤን – የፍየል ወጠጤ ትካሻው ያበጠ ልቡ ያበጠበት፥ እንዋጋ ብሎ ከነብር ላከበት። የማትረባ ፍየል ዘጠኝ ትወልዳለች፥ ልጆችዋም ያልቃሉ እስዋም ትሞታለች– አይ ጉድ! የጊዜ ነገር! ጊዜና ሽርሙጣን ያመነ – ጉም የዘገነ!!›› እያሉ ሲገላበጡ፥ እንቅልፍ ማጣቱ አይናቸውን እያቃጠላቸው – ሌሊቱ እየረዘመባቸው ይሄድ ነበር. . . .

ምእራፍ ፪

ለእነ አቶ ጉልላት ቀበሌ ተመራጮች ጊዜው ክንፍ አውጥቶ እንደ መብረር ያህል ነበር–ሲርጥ–ሴኮንዶች ደቂቃዎችን እየወለዱ፥ ደቂቃዎች ለአቶች እየተኩ ሲሄዱ። ወርዱ እስር ስፋቱ አስራ አምስት ሜትር በሆነው የቀበሌው አዳራሽ ውስጥ አስቸኩዋይ ስብሰባ ከጀመሩ ከአራት ሰአት በላይ ቢሆናቸው እንጂ አያንስም። ነገር ግን፥ የጊዜው ኮብልሎ መሄድ አልታወቃቸውም። የታወጀው ሰአት እላፊ የትና የት አልፎአል።

አስቸኩዋይ ስብሰባ የተደረገበት ዋና አላማ፥ በፊት የነበረውን የቀበሌውን የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ትጥቅ አስፈትቶ ከስልጣን በማውረድ ከቁጥጥር ስር ለማዋልና፥ በምትኩ ሌላ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ለመምረጥ ነበር። አባሎቹ በሙሉ (በግምት አንድ ስድሳ ይሆናሉ) ወደ ስብሰባው አዳራሽ ሊገቡ በመካከላቸውም ፍፁም የመግባባት መንፈስ ስለነበረ፥ የቀሞውን የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሳያስበው በድንገት ይዘው ትጥቅ ሰማስፈታትና ከቁጥጥር ስር ለማዋል ጊዜ አልፈጀባቸውም። ከፍርሃት የተነሳ እያንዳንዱ የቀበሌው ተመራጭ በሆዱ ይዞት የቆየው ጉዳይ ስለነበረ፥ ሁሉም ሲፈራ ሲቸር እንደ ምንም በመካከላቸው አንድ አይነት የመግባባት መንፈስ በሰረፀበት ጊዜ ላንዳፍታ እንኩን ያመነታ አልተገኘም፤ ያመነታ ተመታ፤ ያልጠረጠረ ተመነጠረ የጊዜው ሁኔታ፥ ይልቁንም ሊያነታርካቸው የቆየውና ጊዜ ፊጅቶ ያንን ያህል ያስመሻቸው፥ በምትኩ ሌላ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር የመምረጡ ጉዳይ ነበር።

እያንዳንዱ አባል ካለፈው መራራ ልምድ ባገኘው ትምህርት መሰረት ከሌላ የፍርሃት አዘቅት፥ ከሌላ የስጋት ኑሮ ወጥመድ ውስጥ ለመውደቅ እንዳልፈለገ ያስታውቃል። ስለሆነም፥ የፈጀውን ጊዜ ቢፈጅም ምርጫው በከፍተኛ ጥንቃቄ መካሄድ ነበረበት። የቸኮለ ማንም አልነበረም።

ለምን ተብሎ–ላለፉት ሶስት ወራት እስካለፉት ጥቂት ሰአቶች ድረስ፥ እያንዳንዱ የአብዮት ጥበቃ አባልም ሆነ የቀበሌው ሊቀመንበር፥ በቀድሞው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር አምባገነን ተፅዕኖ ስር በታላቅ ፍርሃትና ስጋት ያሳለፉት እያንዳንድዋ የመከራ ደቂቃ ከአእምሮው ውስጥ አልወጣችም።

ከመካከላቸው ያች የመከራ ደቂቃ ገና ያላለፍች እየመሰለው፥ ክፉኛ የሚዘገንነውም ነበር። በዚያች ቀውጢ ሰአት ከመካከላቸው ወጥመድ እንደገባች አይጥ ለመኖር እየቃተተ ሞት ላይቀር ለሀይወቱ እየሳሳ ሳይወድ በፍርሃት ለፈፀመው ድርጊት፥ ህሊናው ቆስሎ በመምገል ያልገለማው ማን ነበር? ማንም አልነበረም።

ከሊቀ መንበሩ ፊት ካለው ወደ አንድ ጎን ያጋደለ፥ ቀለሙ ይህ ነው ተብሎ ሊነገርለት ከማይችል አሮጌ ጠረጴዛ ላይ፥ አዲስ ክላሺን አጋድሞ፥ ከቀጭን ወገቡ ላይ፥ በግራ ጎኑ በኩል፥ ባለስውር ምላስ ኮልት ፴፰ ሽጉጥ ሽጦ የተቀመጠው የአስመራጭ ኮሚቴ ሊቀ መንበር፥ የተዘጋ ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠራረገና፥ ቀልተው በሚታዩት ትላልቅ አይኖቹ ሁሉንም አንድ በአንድ ካማተረ በሁዋላ፥ ‹‹ጉዋዶች፥ እስካሁን ሰፋ ያለ ዲሞክራሲያዊ ውይይት አካሂደናል። ለምርጫ በእናንተው ጠቁዋሚነት የቀረቡትም ስድስት ጉዋዶች ስለ አቁዋማቸው አንድ ባንድ ገልፀውልናል። ጊዜውም እየሄደ ነው። እንደምትሰሙት ሁሉ ከውጭ የመደብ ትግሉ እየተጡዋጡዋፈ ነው። ጭቁን ሁሉ በየቦታው ዘብ መቆም አለበት። በዚህ ወሳኝና መራራ የትግል ወቅት! ስለዚህ ወደ ምርጫው እንድናመራ ቤቱን እጠይቃለሁ›› አለ፥ ሳይታወቀው በአንድ እጁ ከፊቱ የተጋደመውን ‹‹ክላሺን›› እንደ ህፃን ልጅ እየደባበሰ ከግራና ከቀኙ ሁለት ሌሎች ሰዎች ተቀምጠዋል። አንዱ ግንባረ ፈጣጣ ሌላው ደግሞ አይነ ሸውራራ ብጤ ናቸው።

ቤቱ በሲጋራ ጢስ ታፍኖ ዛር የሚወርድበት የቃልቻ እልፍኝ አልመሰለም። ለላብ ተብሎ ከብብት ውስጥ የሚቀቡትም ቅባት ሆነ፥ ዒም ከተላጨ በሁዋላ የሚርከፈከፈው ሽቶ ክፍሉን አያውደውም። የኮሌታው ንጣት ከሩቅ አይን የሚስብ ሸሚዝ ከመሸጎርጎሩ የተነሳ የሚያጥወለውል ክራባት፥ ባለፊው ምሽት በኤምባሲ ኮክቴል የቦዘነ አይን የሚሸፍን ጥቁር የፀሀይ መነፅር አይታይም።

አይን የሚወጋው ደግሞ፥ ኖራው ለቆ ምርጉ ያፈጠጠው ግድግዳ ብርሃንዋ የደበዘዘና ከረጂም ገመድ እርቃንዋን የተንጠለጠለች ባለሸሪ ሻማ አምፑል፥ ክራባት ያላነቀው አንገት፥ ለብዙ ጊዜ ምላጭ ያልነካው ዒም ነበር።

አንዱ ከመካከላቸው ድምፁን ከፍ አድርጎ፥ ‹‹ለደንብ!›› በማለት እጁን አወጣ። ሁሉም መለስ ብለው ተመለከቱት። እያንዳንዱ አባል ለማን ድምፁን እንደሚሰጥ በጥሞና ያሰላስል ነበርና ጆሮ የሚሰነጥቀው ድምፁ አሸበራቸው። በድንገት ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ፥ ‹‹በቀድሞው ሊቀመንበርና በግብረ አበሮቹ ላይ አብዮታዊ ፍርድ ሳንሰጥ ወደ ምርጫው መሄድ የለብንም። አንገብጋቢው ጥያቄ ፍርዱ ነው እንጂ ምርጫው አይደለም›› አለና ተቀመጠ።

የአስመራጭ ኮሚቴው ሊቀ መንበር እንደመናደድ ብሎ፥ መጥረቢያ መሳይ ፊቱን በይበልጥ ሳለና፥ ‹‹የተሰነዘረው አሳብ ከደንብ ውጭ ነው›› አለ። ‹‹ምርጫው ወይስ ፍርዱ የትኛው ይቅደም? በሚለው አሳብ ቅድም ቤቱ በሰፊው ሲከራከርበት ከቆየ በሁዋላ፥ ምርጫው ይቅደም ተብሎ በአብዛኛው ድምፅ ያለቀለት ጉዳይ ነው። ስለዚህ፥ አሁን ቤቱን እንደ ገና የምጠይቀው ወደ ድምፅ መስጠቱ ስነ ስርአት እንድናመራ ነው። በተስማማነው መሰረት ድምፅ አሰጣጡ በምስጢር ይሆናል። አሁን ድምፅ የምትሰጡበትን ወረቀት ማደል እንጀምራለን።››

ያች ወሳኝ ሰአት በመድረስዋ ድምፅ ለመስጠት ተቻኩሎ በታደለው ወረቀት ላይ የተጠየቀውን ምልክት ያደረገ አልነበርም። ግማሹ ውሀ እንደምትጠጣ ዶሮ ወደ ላይ አንጋጦ፥ የተቀረው ደግሞ አሳብ እንደተጫነው ፊላስፋ አቀርቅሮ ያስብ ነበር። የትናንቱ ፍርሃትና ጭንቀት እያንዳንዱ አእምሮ ውስጥ ትኩስ ነበር። ግን የትናንቱ ጥፋት፤ ያለፈው የፍርሃትና የመከራ ሰአት እንዲደገም ዋስትናው ምንድር ነው? የሚልም ጥያቄ በአእምሮአቸው ውስጥ ሳይመላለስ አልቀረም። በትግል፥ ትግል ደግሞ ያለቆራጥነት አይሆንም የሚል መልስ ያገኙ ይመስላል። አብዛኛዎቹ ከታደላቸው ወረቀት ላይ ምልክት ማድረግ ጀመሩ። ለእርዳታ ወደ አስመራጭ ኮሚቴው ሊቀ መንበር የሄዱት ከእስር አይበልጡም ነበር።

ሁሉም ድምፅ የሰጠበትን ወረቀት መመለስ ጀመረ። በተጨማሪ ብቅ የሚል ሰው መጥፋቱን በማየት ሊቀመንበሩ ትንሽ ቆየና፥ ‹‹የምርጫውን ወረቀት ያልመለስ እንዳለ?›› ብሎ ፈገግ በማለት ጠየቀ። ሁሉም ተያዩ።

‹‹እኔ ገና ነኝ›› አለ፥ በድንገት ከመካከላቸው አንዱ።

‹‹ምንነው ጉዋድ?››

‹‹መቁረጥ አቃተኝ!››

‹‹ለምን?›› ብሎ ጠየቀ፥ ሊቀ መንበሩ እየሳቀ።

‹‹ድምፅ መስጠት እንደ ዋዛ የሚታይ አለመሆኑ ዛሬ ነው የተከሰተልኝ። እና ተጨነቅሁ›› አለ፥ ቁም ነገር በተመላበት ሁኔታ።

በአጋንታ ራሱን ያልነቀነቀ ሰው በቤቱ ውስጥ አልነበረም። ለማንኛውም ነገር መልስ የማያጣው ሊቀ መንበር፥ ከፊቱ ላይ የነበረውን ፊገግታ ሳያጨልም፥ ‹‹አዎን ጉዋድ፥ ድምፅ መስጠት አስቸጋሪ ነገር ነው። ጭንቀትህ የንቃት ምልክት ነው። ቢሆንም፥ ጊዜና ጠላት ቆመው አይጠብቁንም። ስለዚህ መቁረጥ ያስፈልጋል›› በማለት አበረታታው።

ጉዋዱ፥ በመረጠው እጩ ስም አኩዋያ ምልክቱን አድርጎ ወረቀቱን መለሰ። እንደ ድንጋይ ከብዶት የነበረው ልቡ ቆርጦ ውሳኔ ከሰጠ በሁዋላ ስለቀለለው፥ ከፊቱ ላይ የደስታ ስሜት በጉልህ ተፅፎ ይነበብ ነበር።

አስመራጭ ኮሚቴው ምልክት ተደርጎባቸው የተመለሱትን ወረቀቶች ገምግሞ የምርጫውን ውጤት ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። የቤቱ አባሎች የተጨነቁበትን የምርጫ ውጤት ለመስማት፥ ማን ይሆን? ማን ይሆን? እያሉ በጉጉት እንደሚጠባበቁት ሁሉ፥ የስድስቱም እጩዎች ልብ፥ ምንም እንኩዋ ሁሉም በንግግራቸው ወቅት የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ መመረጥ ከባድ ሀላፊነትንና መስዋእትነትን የሚጠይቅ መሆኑን ቢገነዘቡም፥ እኔ እሆን? እኔ እሆን? በማለት ልባቸው ድው፥ ድው፥ እያለ እንደ ከበሮ ይመታ ነበር። ስልጣን የማያጉዋጉዋው ሙት ብቻ ነው፥ እንዲሉ።

ሶስቱም አስመራጮች አፍ ለአፍ ገጥመው ለጥቂት ጊዜ በለሆሳስ ከተንሾካሾኩ በሁዋላ፥ ሊቀ መንበሩ በወረንጦ የማይለቀም ሽንጡን እያሳየ ብድግ ብሎ፥ ‹‹እሺ ጉዋዶች፥ ውጤቱን በናፍቆት የምትጠባበቁ ይመስለኛል- አይደለም እንዴ?›› ብሎ፥ የቤቱን ስሜት ለማጤን ያህል ንግግሩን ቆም አደረገ።

ፍሁም ወጥታ የሰፈነበት ቤት ከመሆኑ የተነሳ፥ ሥርጌ እንኩዋ ብትወድቅ ሳትሰማ አትቀርም። ከሁሉም ፊት ላይ ጉጉት የሚያንሀባርቅ ፈገግታ ይታያል። የሁሉም የልብ ትርታ ጨምሮ ነበር።

‹‹መቼም እንደምትሰሙ ውጭ የመደብ ትግሉ እየተጡዋጡዋፈ ነው። ለአድሃርያን ጨለማው የባሰ ጨለማ፥ ለጭቁኖች ግን ብርሃን ሆኖአል። የምትሰሙት ተኩስ ለአድሃርያን ግብአተ መሬትን፥ ለጭቁኖች ብሩህ ተስፋን የሚያበስር ነው። ቀይ ሽብር!! ቀይ ሽብር!! ለኛ!! ለጭቁን መደቦች ሁሉ፥ መለት አይደለም፥ አለኝታችን፥ የአብዮታችን ዋስትና እንጂ!››

ሁሉም ጆሮውን በማቆም ጉዋጉቶ የሚጠባበቀው የምርጫውን ውጤት ለመስማት እንደመሆኑ መጠን፥ ጉዋዱ እግረ-መንገድን የሚናገረውንም ሆነ፥ ከውጭ የሚቀልጠውን ተኩስ ከልብ ያጤነ አልነበረም።

‹‹እሺ እንግዲህ ጉዋዶች! ብዙ አዘገየሁአችሁ መሰለኝ። ዘጠኝ ድምፅ በማግኘት ሶስተኛ ተመራጭ በሆነው እንጀምር-››

ሁሉም አጉረምርመው፥ አቀማመጣቸውን በመለወጥ ከወንበሮቻቸው ላይ ተመቻቹ።

‹‹ጉዋድ ኡርጌ ደባላ ዘጠኝ ድምፅ በማግኘት ሶስተኛ ተመራጭ ሆኖአል!›› ጭብጨባው ቀለጠ። ኡርጌን ለማየት ሁሉም ወዲህና ወዲያ ያማትር ነበር።

‹‹መልካም ነው። አስራ አንድ ድምፅ በማግኘት ጉዋድ ላጲሶ ሊልጆሮ ሁለተኛ ተመራጭና የአብዮት ጥበቃ ምክትል ሊቀ መንበር!!››

ጭብጨባው የአስመራጭ ኮሚቴውን ሊቀ መንበር ድምፅ ውጦ አስተጋባ። ከላጲሶ ጎን የተቀመጡት ጉዋዶች እየተነሱ በጋለ ስሜት ይጨብጡት ነበር። ግን ጊዜ አላጠፉም። ሁሉም ወደየወንበሩ ተመልሶ ተቀመጠ። ቤቱ ፀጥ አለ። ከፍተኛ ውጥረት የተመላበት ዝምታ በአዳራሹ ውስጥ ሰፈነ። አንዳንዶቹ ሊተነፍሱ ይሰማ ነበር። ሊቀ መንበሩም ሲቃ ይዞት ባጭሩ ባጭሩ ሊተነፍስ ይታይ ነበር።

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹ሰላሳ ድምፅ በማግኘት የቀበሌያችን የአብሶት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ የተመረጠው ማን ይመስላችሁዋል?››

ከፍተኛ ማጉረምረም ሆነ።

‹‹ጉዋድ ደርቤ ጉተማ!!››

ቤቱ በጭብጨባ በሆታና በፉጨት ተናጋ። ጭብጨባው እንደ ክረምት ዝናብ ሳያባራ እየቀጠለ ሰብዙ ጊዜ ቆየ. . .

ደርቤ ምስጋና ለማቅረብ ወደ መድረኩ ሲሄድ፥ ከድንጋጤው ብዛት እግሮቹ ይማቱ ነበር። ሊቀ መንበሩ በጭብጨባ ተቀብሎት እጁን ጨብጦ አቅፎ ከሳመው በሁዋላ፥ ስሜቱ ገንፍሎ፥ ከጠረጴዛው ላይ ተጋድሞ የነበረውን ክላሺን አንስቶ ሰጠው።

ደርቤ ክላሺኑን ከራሱ በላይ ከፍ አድርጎ ለጉዋዶቹ ሲያሳይ፤ ሌላ ጭብጨባ፥ ሆታና ፉጨት እንደገና ከግድግዳ ግድግዳ እየተላተመ አስተጋባ።

ጣምራ ጣምራ የሆኑ የእንባ ዘለላዎች የደርቤን ጉንጮች አቁዋርጠው ይወርዱ ነበር። ከወንዳ ወንድ፥ ውብ፥ ቀይ ዳማ ፊቱ ላይ የደስታ ሳይሆን የመደነጋጥ ስሜት ይታያል። በረጂም ቁመናው ከመድረኩ ላይ ወጥቶ ሲቆም ከሰው በላይ ግዙፍ የሆነ መስሎ ይታይ ነበር።

ጭብጨባው ሲያባራ ጠብቆ፥ ሊቀ መንበሩ መናገር ጀመሩ ‹‹ጉዋዶች፥ በምርጫችሁ ሁላችሁም እንደተደሰታችሁ አምናለሁ። ጉዋድ ደርቤ ቅድም በንግግሩ እንደ ገለፀው ሁሉ፥ ከህፃንነት ጀምሮ እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ በሰው ቤት በአሽከርነት ሲያገለግል የቆየ ቢሆንም፥ ማታ ማታ በትግል እየተማረ አስራ ሁለተኛ ክፍል የደረሰ ታታሪ ወጣት ነው። ባሁኑ ጊዜ በንብረት ክፍል ፀሐፊነት በማስታወቂያና መርሀ ብሄር ሚኒስቴር ውስጥ በሰራ ላይ ይገኛል። የአእምሮ ብስለቱንና አስተዋይነቱን የተገነዘቡ ሀቀኛ ጉዋዶች መልምለውት በየካቲት ፳፯ ፖለቲካ ትምህርት ቤት የርእዮተ አለም ትምህርት ከመከታተሉም በላይ ለሚያከራ ጥረቱና ለመልካም ጠባዩ የምስጋና ወረቀት ከሽልማት ጋር አግኝቶአል። እኔ ከጠባዩ ውስጥ በጣም ጎልተው የሚታዩኝ ነገሮች ቢኖሩ ትህትናውና ለመማር ያለው ብርቱ ፍላጎቱ ናቸው።

‹‹የቀለመውን የርእዮተ አለም ትምህርት ከዘወትር አስተሳሰቡና ድርጊቱ ጋር የማዋሃድ፥ ማለትም ቲዎሪን ከተግባር ጋር አጣምሮ የመስራት ችሎታው የነአስ ከበርቴዎች ልክስክስ ጠባይ እንደ አጉል ጀብደኛነት፥ ወላዋይነትና ከእኔ በላይ አዋቂ ለአሳር ነው ባይነትና የመሳለሉትን ፍፁም አስወግዶ፥ ሀብቱ የሆነው ትህትናው ሳይለየው በሀቀኛነት ያለ ይሉኝታ የተጣለበትን ሀላፊነት በትግል የመወጣት ችሎታው ወደ ፊት በተግባር የሚታዩ ናቸው። ብዙዎቻችን ይህን የትግል ጎዳና ልንዘልቀው ቀርቶ ግማሽ መንገድም ለመሄድ አንችልም –

‹‹በአብዮታዊ ወኔ ታድመን፥ የወዛደሩን ርእዮተ አለም ቲዎሪ ከተግባር ጋር አጣምረን፥ በአብዮታዊ አስተሳሰብ አብዮታዊ ሀይወት መኖር እጅግ አስቸጋሪ ነው። ሰፈተናው ተስገብግበው የሚቀርቡት ብዙዎች፥ ፈተናውን አልፈው የሚገኙት ግን ጥቂቶች ናቸው። ስለሆነም ነው፥ ጉዋዶች፥ በጥራት እንጂ በብዛት የማናምነው። የደብተራ ጋጋታ ቅዳሴውን አያሳምርም። ደባትር እንደ አሸን ፈልተዋል – ማርክስና ሌኒንን የሚያነበንቡ – ምስጢሩ ሳይገባቸው – ተሳስተው የሚያሳስቱ፥ እንደ ጥንቱ ደብተራ ጠዋት በቀኝ እጃቸው እያማተቡ ቀኝ ግራ እጃቸውን እንደ ሰይፍ የሚመዙብን ደባትር ብዙ ናቸው። ውሀ ቢወቅጡት መልሶ እንቦጭ እንዲሉ! ተከናንበው ቢመጡ ገልጦ የሚያይ የአብዮት ብርሃን ፈንጥቆአል። የፈነጠቀው ብርሃን አሁን እርቃናችንን አውጥቶ ባያሳየን የጊዜ ጉዳይ ነው!››

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!

አብዮቱ!

ከሁሉም በላይ አብዮቱ!

አብዮቱ!

ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

አብዮቱ!

‹‹አሁን ለጉዋድ ደርቤ መድረኩን እለቃለሁ። አመሰግናለሁ።››

ጭብጨባው እንደ ገና አስተጋባ። የቀበሌ ዲሞትፎር ከውጭ ሲያገዛ ይሰማ ነበር።

ደርቤ ብርድ እንደያዘው ሰው መላ ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ነበር። መላረብ አውጥቶ እንባውን ጠረገ። ማሰብም የተሳነው ይመስላል። ‹‹ጉዋዶች!›› ብሎ ጀመረ በተሰባበረ ድምፅ – ‹‹በቀበሌው ነዋሪ ሰፊ ሀዘብ ስም የጣላችሁበኝ ሀላፊነት በጣም ከባድ ነው። ያለ እናንተ ትብብር. . እ. . እ. . . ትብብራችሁ እንደማይለየኝ አምናለሁ። የጭቁኖች ጉልበት ጥንካሬና ሃይል አንድነት ነው!››

አንደበቱ ቀስ በቀስ መፍታታት ሲጀምር ረጅም ቀይ ሳማ ፊቱ እየፈካ ይሄድ ነበር።

‹‹ፍፁም የሆነ ዲሞክራሲያዊ ውይይት በመካከላችን መኖር አለበት። የምንደርስባቸውን ማናቸውንም ውሳኔዎች በተግባር የምተረጉመው በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት መርህ መሰረት ይሆናል። ከዚህ ውጭ በግልፅነት የምንፈፅመው ምንም ነገር አይኖርም። ምናልባት የወዛደሩ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ እንዴት አድርጎ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር ሊኖር ይችላል? ብላችሁ የምታስቡ ትኖራላችሁ። የአብዮታችንን ሂደት ልየ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱ እና ዋነኛው የወዛደሩ ፓርቲ አለመኖር መሆኑ የታወቀ ጉዳይ ነው። እኔ በበኩሌ አሁን ያለው አብዮታዊ መንግስት አብዮታዊ እስከሆነ ድረስ አብዮታዊ አመራር የሚጠይቀውን ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ሊሰጠን ይችላል ብዬ አምናለሁ። አለበለዚያ በቡድኖችና በግለሰቦች እየተወናበድን አብዮቱን በገዛ እጃችን ከመቀልበስ ደረጃ ላይ እናደርሰለን ብዬ እሰጋለሁ። አዎን አብዮታችንና ለአብዮታችን ህልውና ስንል የምናካሂደው ቀይ ሽብር ደካማ ጎን አለው ቢባል፥ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር አለመኖር ነው።

‹‹የዚህ መሰረታዊ መርህ አለመጠናከር ለአድር ባዮችና ለጀብደኞች እንዲያም ሲል ለቀማኞች፥ ለሌሰኞችና ደም ለጠማቸው፥ አብዮትን የግል ቂም የመወጫ መሳሪያ ለማድረግና ሰውን በማሰቃየት ለሚደሰቱ፥ እንዲሁም

አብዮቱ ለህዝብ የመጣለት ሳይሆን የመጣበት ለሚያስመስሉ፥ ቀልባሽ ግለሰቦች ሁሉ በር ይከፍታል።

‹‹ይህ ሁኔታ በኛም ቀበሌ ሆነ በሌሎች ቀበሌዎች አልፎ አልፎ በገሃድ ተከስቶአል፥ እየተከሰተም ነው. . . ሆኖም፥ ሁኔታው አድሃሪያንና የኢምፔሪያሊስቶች ዜና ማሰራጫዎች አስር ጊዜ አጋንነው እንደሚያናፍሱት አይደለም። እርግጥ ስር ነቀል የሆነ አብዮት ሂደት ውስጥ ስህተት ይደርሳል። በተለይም፥ አሁን አብዮቱ ከደረሰበት የአድገት ደረጃ ሲገመገም፥ የተበሌ ማህበራት ድርጅት የልዩ ልዩ መደቦች ነፀብራቅ እንደ መሆኑ መጠን አንዳንድ ስህተቶች ቢደርሱ አያስገርምም። ባለማወቅ ስህተት የሚያደርሱት በመደባዊ ወገናዊነት አመለካከት ማረም፥ ሆን ብለው ስህተት በመፈፀም ከሰፊው ህዝብ ጋር ቅራኔ እንዲኖር የሚያደርጉት ግን ማስወገድ ይኖርብናል።

‹‹የነፍጠኛ ጠብመንጃ አፈሙዝ የስንቱን ጭቁን አርሶ አደር ቤት እንዳላፈረሰ ሁሉ፥ ዛሬ ደግሞ የቀበሌ ተመራጭ በአብዮት ስም ጠብመንጃ አንግቦ የፊውዳሊስቶችን ጠባይ ሲያንፀባርቅ፥ ማንፀባረቅም ብቻ ሳይሆን በተግባር ሲገለፅ፥ የሀቀኛ አብዮታውያን ልብ ይደማል። የቀድሞ ጭቃ ሹሞችን፥ ነፍጠኞችንና ምስለኔዎችን ጠባይ የሚያንፀባርቁ እየበዙ ሄደዋል። እንዲህ አይነቱን ዝንባሌ በቀበሌያችን አካባቢ ብቻ ሳይወሰን ወደ ሌሎች ቀበሌዎችም ተራምደን በቆራጥነት መታገል አለብን። ለጭቁን፥ ቆራጥነት የመደብ ባህርይው ነው። ያለ ትግል እግረ መቁን እንደማይበጥስ ያውቃል። ላንዲት አጭር ቆርቁዋዛ ህይወቱ አይሳሳም፣ በመስዋእትነቱ የሰፊውን ህዝብ ትግል አንድ እርምጃ ወደ ፊት እንደሚያራምድ ያውቃልና!. . .››

ደርቤ አሳቡንም ሆነ ሰውነቱን በሙሉ ከቁጥጥሩ ስር አውሎአል። ቤቱም አፉን ከፍቶ ያዳምጠው ነበር። ስለሆነም፥ በራሱ ላይ ያለው እምነት እየታደሰ ሲሄድ ይሰማው ነበር። ‹‹ጉዋዶች! ትግል–ትግል ስንል አላማውና ግቡ ምን እንደሆነ ማወቅ ይገባናል። የጭቁን መደቦች ትግል አይነተኛ አላማና ግብ የሰፊው ህዝብ ነፃነት እኩልነትና ፍትህ ነው። የጭቁኖች ደስታ ነው ግባችን። ስለሆነ፥ ሀቀኛ ተራማጆች የማንንም እንባ ማየት አይፈልጉም። ሜካኔ መሳሪያቸው አይደለም – ካልተገደዱ በቀር። አላማቸው የሰው ዘር ደስታ ነው። ሆኖም ይህንን የጭቁኖች ደስታ በምኞት ብቻ ለማስገኘት እንደማይችም

ያውቃሉ። የመደብ ሹም ሽረት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ያስተግል አይሆንም። ከለፌ ህዝብ ደስታ ፊት የሚጋረጡትን መደምሰስ ቢያስፈልግም፣ ለማስተማርና ወደ አብዮቱ ሰፈር ለመመለስ ቅድሚያ መስጠት አብዮታዊ ግዴታችን ነው። አሻፈረኝ ያለውን ግን ያለ ምንም ይሉኝታ ከመምታት ሌላ አማራጭ የለም። አብዮት ይሉኝታን አያውቅም። የመደብ ትግል የስጋ ዝምድናን፣ ወዳጅነትንና ጉዋደኛነትን አይመርጥም።››

በድንገት የንግግሩ ሂደት ውል ጠፋበት። ከምላሱ ላይ ተንጠልጥሎ የቀረው፣ ‹‹ያለ ምንም ይሉኝታ›› የሚሉት ቃላት ብቻ ነበሩ። ወደ ሌላ አሳብ ለማምራት ፈልጎ በመቸገር የተፈጨነቀ መሆኑ፣ ከፊቱ ላይ ያስታውቃል... አብዮት ይሉኝታን አያውቅም... ይሉኝታ... አቶ ጉልላት... ወይዘሮ አምሳለ... ሂሩት... ተሰማ – ከፊቱ መጥተው ተደቀኑ። የአቶ ጉልላት አውቶማቲክ መሳሪያዎች የተቀበሩበት ጉድጉዋድ ወለል ብሎ ታየው– መሳሪያውን ሲቀብሩ፣ ‹‹ጣሊያንን ያርበደበድነው ተቀብሮ በቆየ መሳሪያ ነው፣ ይህ መሳሪያ የሚያስፈልግበት ጊዜ ይመጣል– ሩቅ አይደለም›› ብለው አቶ ጉልላት የተናገሩት ሁሉ ጆሮው ውስጥ አስተጋባ... ሂሩት፣ የተከለከለች ፍሬ! የሚል አሳብ ላንዳፍታ ሽው ባለበት ጊዜ፣ ፀሀያማ ፈገግታዋ ልቡን በማሞቅ እንደ ፍም እሳት በሰሜቱ ሪመጥ ውስጥ! ፈገግታዋን ላይሳሞቅ... የማይጨበጥ ከንቱ ምኞት... የህልም እንጀራ... ሂሩት፣ የተከለከለች ፍሬ... የተገለበጠ ኮልባ የሚመስለው ባትዋን እያጠቡ መኖር ምንኛ ደስ ባለ ነበር! ከዚሁ አሳብ ጋር ተያይዞ ሂሩትና ተሰማ በር ዘግተው የሚያነቡት የዲሞክራሲያ ነምር... ያጎፈሩ ጎረምሶች ጋጋታ... የሙዚቃው ጫጫታ... የዳንኪራው፣ የጫቱ የሲጃራው ነገር ሁሉ ትዝ አለው። አብዮት ይሉኝታን አያውቅም። ሂሩት፣ የተከለከለች ፍሬ... ላንዳፍታ የህሊና ጭንቀት አደረበት...

በሁኔታው ግራ የተጋባው ቤት ምን ሆነ? በማለት ተገርሞ ይመለከተው ነበር።

‹‹ይቅርታ ጉዋዶች! አምን–ቅድም ጉዋዱ በትክክል እንዳስቀመጠው፣ ምን ብንለፈልፍ፣ ብዙ አብዮታዊ መርሆች ብንደረድር፣ ተግባር ያለ ቲዎሪ አውር ነው! ቲዎሪም ያለተግባር በድን ነው። ትልቁ ፈተና እዚህ ላይ ነው። ለዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እንታገላለን!››

‹‹በተግባር!››

‹‹ለዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እንታገላለን!››

‹‹በተግባር!››

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

ደርቤ በሰፊው ያሰበውን ንግግር ባጭሩ ገትቶ ከመድረኩ ሲወርድ አሳቡ ሁሉ ሌላ ቦታ ሂዶ ነበር። ያደረበት የህሊና ጭንቀት አልተለየውም። እና ከመስቀልኛ መንገድ ላይ ደርሶ በዚህ ወይስ በዚያ? በየትኛው ልሂድ? በማለት እንደተቸገረ መንገደኛ ያህል ነበር ጭንቀቱ። የሚጉዋዝበትን መንገድ ለመምረጥ አልቻለም። የገዛ ልቡ እንደ ድንጋይ ከበደው... ይቀልጥ የነበረው ጭብጨባ አልተሰማውም። በድኑን ነበር ጉዋዶች አንድ ባንድ እየመጡ የሚጨብጡት...

ደርቤ እንደተቀመጠና ቤቱም እንደተረጋጋ የቀበሌው ሊቀ መንበር ተነሳና፥ ‹‹አሁን፥ ባሳለፋችሁት ውሳኔ መሰረት ዋስይሁን፥ ከበደና ግብረ አበሮቹ ለአብዮታዊ ፍርድ ይቀርባሉ›› ከማለቱ ዲሞትፎር ጠብመንጃ ይዘው ካጠገቡ ቆመው የነበሩ ሁለት ጉዋዶች ከአዳራሹ እየተጣደፉ ወጡ።

ሁለት እጃቸውን ወደ ሁዋላ የፊጥኝ የታሰሩ ሶስት ሰዎችን አጅበው በሄዱበት ፍጥነት ተመልሰው መጡ። የቀድሞው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር፥ ዋስይሁን ከበደ፥ ከሁሉም ቀደም ብሎ አንገቱን ደፍቶ ባጭር ባጭሩ እየተራመደ ይሄድ ነበር። ፍርሃት የሚሉት ነገር ሲያልፍም የነካው አይመስልም። ‹‹ትናንት ያገበድዱልህ የነበሩት ሰዎች፥ ጊዜ ሲከዳ አይተው፥ በአያባባይ ስትሰቀል ቆመው ይስቃሉ›› የሚል አሳብ በአእምሮው ይመላለሳል። ‹‹ወይኔ ዋስይሁን! ... ላልቀድማቸው ለትንሽ ተቀደምክ!››

ሁሉም አይናቸውን ሞልተው ፊት ለፊት ሊያዩት አልሞከሩም። ትናንት ጠብመንጃውን እንግቶ ሽጉጡን አገንድሮ ያነጠ ደረቱን ነፍቶ ሰፊ ትከሻውን እየጋረጠና ትላልቅ አይኖቹን እያትረጠረጠ ባጠገባቸው ሲያልፍ ጥላው ሳይቀር ያስፈራቸው ነበር። እንዲህ እጆቹን የፊጥኝ ታስሮ አንገቱን ደፍቶ ግርማ ሞገሱ ተገፎ ጥላ ቢስ ሆኖ ሲመለከቱት አንዳንዶቹ ሳያዝኑለት አልቀሩም። ደፋርነቱና ጀግንነቱ ትዝ እያላቸው ውስጥ ውስጡን የሚያደንቁትም ነበሩ። ግን ምን ያደርጋል፤ ጭካኔውና አውሬነቱ በአሳባቸው እየመጣ ስለሚዘገንናቸው ልባቸው ርህራሄ ተሞልቶ ይቅርታ ሊያደርግለት አልቻለም። የሁሉም ፍርድ በያንዳንዱ ልብ ውስጥ አስቀድሞ የታወቀ ነበር – – የነብርን ጅራት አይይዙም፤ ከያዙም አይለቁም፥ እንዲሉ።

ዋስይሁን የቀበሌው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር በነበረበት ጊዜ – ነበር እንዲህ ቅርብ – ከግብረ አበሮቹ ጋር ሆኖ ያደረሰው ጥፋት በዝርዝር ተነበበ። ከጥፋቱ ውስጥ ጥቂቶቹ፥ ዝናሽ ተበደ የተባለችውን የአስራ ስድስት አመት ወጣት፥ አናርኪስት ነሽ ብሎ ከያዛት በሁዋላ፥ ቀይ ሽብር አፋፍሞብሻለሁ ብሎ በማስገደድ ክብረ–ንፅህናዋን ከመድፈሩም ሌላ፥ ታጋልጠኛለች ብሎ በመሰጋት የዲሞክራሲያ ልሳን አስታቅፎ በጭካኔ ገድሎ ሬሳዋን ከመንገድ ላይ ጥሎአል። ወይዘሮ አሰገደች ደምሴ የተባሉትን የቤት እመቤት፥ ባላቸውን ኢ.ዲ.ሀ. ነህ ብሎ ካሰረ በሁዋላ፥ በማስፈራራት እያስገደደ ዘወትር፥ ጠዋት፥ ቀን፥ ማታ ሳይቀር ደፍሮአል። ከታሰሩት ሴቶች ውስጥ ሽጋ ሽጋዎቹን እመረጠ ለምርመራ ነው በማለት ከቤቱ ድረስ እያስወሰደ ተራ በተራ እንደ አሻንጉሊት ተጫውቶባቸዋል። ወልደተንሳኤ የተባለውን የታወቀ ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ ሁለት ሽህ ብር ጉቦ ተቀብሎ ከታሰረበት አውጥቶ ለቆአል። በቀበሌው ውስጥ የሚገኙትን መጠጥ ቤቶች አንድ ባንድ እያስሰ ባለቤቶቹን በማስፈራራት ውስኪ በነፃ እየጠጣ ሳይከፍል ቀርቶአል። ከአንድ መስሪያ ቤት ብቻ አምስት ሰዎችን፥ (ሁለት ሴቶችና ሶስት ወንዶች) አናርክ ፋሽስት ናችሁ በሚል ሰበብ ጠዋት ረፋዱ ላይ በመያዝ ቀኑን ሙሉ በጭካኔ የአንዳንዶቹን አይን አውጥቶ፥ የሴቶችን ጡት ቆርጦ ካሰቃየ በሁዋላ፥ ከምሽቱ አንድ ሰአት ላይ ገድሎ ከወንዝ ውስጥ ጥሎአቸዋል... የሚሉ ነበሩ።

ውስኪ እየተንገዳገዱ በአምስቱ ሰዎች ላይ የፈፀመው ግፍ አንሶ፥ ይባስ ብሎ ማምሻውን ደግሞ የፈፀመው የጭካኔ አገዳደል ነበር፥ ሌሎቹን የአብዮት ጥበቃ አባሎች ከመጠን በላይ አስቆጥቶ ፍርሃታቸውን በማስወገድ እንዲተባበሩ ያደረጋቸው። አንድ ከመሳከላቸው ወኔ ይሆት፥ ‹‹ጎበዝ፥ ይህን በኛ ስም የሚፈፀመውን ግፍና ጭካኔ ዝም ብለን የምንመለከተው እስከመቼ ድረስ ነው? እኛስ ወንዶች አይደለንም ወይ?›› ባለ ጊዜ ነበር፥ ሁሉም ተግባብተው፥ ሆኖም አንዱ የሌላውን ልብ ካለማመኑ የተነሳ እርስ በርሳቸው በአይነ ቁራኛ እየተጠባበቁ በማድፈጥ፥ ከሰይጣናዊ ተልእኮ እስኪመለስ ድረስ ጠብቀው፥ እርሱንና ግበረ አበሮቹን ትጥቅ በማስፈታት የያዙአቸው።

ዋስይሁንም ቢሆን እሳት ከላሱ ግብረ አበሮቹ ጋር ሰይጣናዊ ተልእኮውን ፈፅሞ ወደ ቀበሌው በፍጥነት የተመለሰው አለምክንያት አልነበረም። ብልጥ በመሆኑ፥ ወደ ሁዋላ በቀሩት የአብዮት ጥበቃ አባሎች አይኑ-ውሀ ውስጥ ያነበበው ነገር ነበር። ተልእኮን ከፈፀመ በሁዋላ ከግብረ አበሮቹ ጋር በፍጥነት ወደ ቀበሌው የተመለሰው፥ በድርጊቱ ያልተባበሩትን የአብዮት ጥበቃ አባሎች ሁሉ ፀረ አብዮት ናቸው በማለት ይዞ ከጨረሳቸው በሁዋላ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ዞር ብሎ በአምስቱ ሰዎች ላይ የፈፀመውን ኢሰብአዊ ድርጊት በእነርሱ ላይ በማላከክ፥ ያለፈ ህይወቱን ምእራፍ የዘጋና ምንም ጥቁር ነጥብ የሌለበት ለማስመሰል ነበር።

የጊዜ ጉዳይ ነበር። ይኸኔ ያለፈ ህይወት ታሪኩ ተፍቆ ዱካው ጠፍቶ አዲስ የህይወት ምእራፍ የሚጀምርበት ጊዜ ነበር። ግን የዚያ ተስፋ ደብዛ አሁን ጠፍቶአል–ዳግመኛ ላይመጣ! ሁለት እጆቹን ወደ ሁዋላ የፊጥኝ ታስሮ ማምሻውን ሊፈርድባቸው የነበሩት ሰዎች ሊፈርዱበት ቁጭ ብለው በማየቱ፥ ‹‹የጊዜ ጉዳይ ነው! ሞኝ ነኝ – – ቂል!›› ብሎ በልቡ ጥርሱን ነክሶና አክ አንትፍ ብሎ የህይወቱን ምእራፍ ዘጋ። ከእንግዲህ ተስፋም ሆነ ፀፀት፥ ንዴትም ሆነ ቁጭት፥ ከልቡ ምንጭቅ ብለው ወጡ። ልቡ ባዶ፥ ሰውነቱ በድን ሆነ... ለሞት ሆነ ለህይወት፥ ለምንም ደንታ አልነበረውም...

ደርቤም እንደ ዋስይሁን ልቡ ባዶ፥ ሰውነቱ በድን ሆኖ ይመለከተው ነበር። ሆኖም አይን ቢያተኩር ልቡና ካልታከለበት እውር ነውና፥ ለደርቤ

ዋስይሁን ከሀኃው እንዳልነበር ነበር። የተጨነቀው የደርቤ ሀሊና ወደሌላ አለም ዘምቶ ነበረ... የተከለከለች ፍሬ ያስችበት አለም...

ሊቀመንበሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ «እሺ እንግዲህ ጉዋዶች፥ ዝርዝሩን ሰምታችሁዋል። አሁን ቤቱ ፍርዱን እንዲሰጥ እጠይቃለሁ» ባለበት ጊዜ ነበር፥ ደርቤ ጭልጥ ብሎ ከተጉዋዘበት የሀሊና ጭንቀት ጎዳና ወጥቶ አሁን ወዳለበት እውነታዊ አለም እንደ መባነን ብሎ የተመለሰው። ያሰበትን አካባቢ እውነታ ካጤነና ዋስይሁን ከተመለከተ በሁዋላ ነበር፥ «ዛሬ ላንተ የደረሰችው ፅዋ ነገ የማን ትሆን?» የሚል ሀሳብ በድንገት እንደ ጥንግ ተወርውሮ አእምሮውን የመታው። እና፥ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዚህ ቀደም የማያውቀው አንድ አይነት ፍርሃት መጥቶ ሰውነቱን እንደ ጉንዳን ወረረው - ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ወርዶ አሰመጠው። ከልቡ ጥልቀት ውስጥ ተዳፍኖ የኖረው ለሂሩት ጉልላት ያለው ሚስጢራዊ ስሜት፥ አሁን ካለበት እውነታ ጋር ባልተገናዘበ ሁኔታ ውሉ እንደጠፋ ልቃቂት ተወሳስቦ ሀሊናውን ከማስጨነቅ አልፎ አስደነገጠው። የገዛ እራሳችን ስሜት አንዳንዴ ምን ያህል እንደሚያስፈራን ለተከሰተለት ብርድ እንደያዘው ሰው መላው ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ። «እህ - ለካ እራሳችንንም መፍራት አለና! ስንቶቻችን በዚህ ፍርሃት ጥላ ስር እንኖር ይሆን?» በማለት ለአንድ አፍታ አሰበ።

«አብዮታዊ ቅጣት! አሁን!» በሚል ፍርድ ቤቱ በአንድነት አስተጋባ።

ሊቀ መንበሩ ከፍርዱ ይልቅ ለስነ ስርአቱ በይበልጥ የተቆረቆረ ይመስል፥ «አብዮታዊ ፍርድ አሁን! ማለት ብቻ አይበቃም» አሉ።

«ሁላችንም አንድ ባንድ እጃችንን በማውጣት በነፍስ ወከፍ ድምፅ መስጠት አለብን። የተለየ ሀሳብ ያለው ሰው ካለ፥ የተለየበት ምክንያት ተገልፆ ይመዘገብለታል። ስለዚህ «አብዮታዊ ፍርድ አሁን» የሚለውን አሳብ የምትደግፉ እጃችሁን አውጡ» ካለ በሁዋላ፥ እያንዳንዱ ሰው የሚሰጠውን ድምፅ ለመመዝገብ ሲዘጋጅ፥ ደርቤ ድምፁን ከፍ አድርጎ፥ «ጥያቄ አለኝ» በማለት እጁን አወጣ።

ሊቀ መንበሩ ቀና ብሎ፥ «እሺ፤ ጉዋድ ሊቀ መንበር፡ ጉዋዶች፥ አሁን የማቀርበውን ጥያቄ ቅድም ባለማንሳቴ ይቅርታ አጠይቃለሁ። የማቀርበው

ጥያቄ መጠየቅ ያለበት መሰረታዊ ጥያቄ ሆኖ ስለተሰማኝ ነው። ቤቱ የማቀርበውን ጥያቄ በስሜት ሳይሆን በጥሞና ተመልክቶ መልስ እንደሚሰጠኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ሊቀ መንበሩ ባሳሰበው መሠረት አሁን ድምፅ እንድንሰጥ የተጠየቅነው ለምን አላማ እንደሆነ ሰማወቅ ነው። የቀድሞው የስብሰባ ጥበቃ ሊቀ መንበርና ግብረ አበሮቹ ያደረሱት ጥፋት በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ቀርቦልናል። ስለቀረቡት ማስረጃዎች ተጠራጥሮ አሌ የሚል አባል በቤቱ ውስጥ ያለ አይመስለኝም። ጥያቄው... ጥያቄው፥ እኛ አሁን ጥፋታቸውን አገናዝበን ለፍርድ ለበላይ አካል ማለትም ለመንግስት እንድናቀርብ ነው? ወይስ እኛው ጥፋታቸውን መርምረን ፍርድም እንድንሰጥ ነው? ቤቱ መልስ እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ›› ብሎ ተቀመጠ።

‹‹ሰለ ደንብ›› አለ፥ ቅድምም ስለ ደንብ ብሎ ዘሎ የተነሳው ሰው። ቀጠለና፥ ‹‹ቅድም ስለምንከተለው ስነ ስርአት በድምፅ ደንግገናል። አሁን የሚቀረን ነገር ቢኖር፥ ፍርድ ሰጥተን፥ አሁኑኑ አብዮታዊ እርምጃ መውሰድ ነው!›› ብሎ ተቀመጠ።

‹‹ልክ ነው! ልክ ነው!›› ሲል ቤቱ አስተጋባ። ሊቀ መንበሩ ከቤቱ ዝንባሌ ጋር ያልተስማማ መሆኑን በመግለፅ፥ ‹‹ጉዋዶች፥ በእንደዚህ ያለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ቤቱ በክርክር ስነ ስርአት ቴክኒካዊ ደንብ መያዝ የለበትም። ዲሞክራሲ ሲባል ማንኛውንም ነገር በድምፅ ብልጫ መወሰን ሳይሆን፥ ነፃነትና እኩልነት በሰፈነበት ክርክር ከትክክለኛው ወይም ከሚዛናዊ ውሳኔ ላይ መድረስ ማለት ነው። ስለሆነም... ስለሆነም ቤቱ የቀረበውን መሰረታዊ ጥያቄ በጥሞና ተመልክቶ መልስ ሊሰጥበት ይገባል›› በማለት የደርቤን ጥያቄ የተቀበለ መሆኑን በግልፅ አረጋገጠ።

ከዚያ በሁዋላ፥ በቤቱ ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ ተፈጠረ። ጥያቄው በመሰረቱ የቀልባሽ ጥያቄ ነው፤ ቀበሌዎች የተሰጠውን መብት የሚገፍና ከጥያቄ ላይ የሚጥል አደገኛ ጥያቄ ነው፤ የቀኝ አድር ባይነት ጥያቄ ነው፤ ሰፊው የቀበሌያችን ነዋሪ ህዝብ ለማንኛውም ጉዳይ እኛ እንድንወክለው መርጦ የላከን ስለሆነ፥ የበላይ ነኝ ለሚል ለማንኛውም አካል ተጠያቂ አይደለንም፤ ስለሆነም የተሰነዘረው ጥያቄ የሰፊውን ህዝብ መሰረታዊ መብት ይፃረራልና ውድቅ መሆን አለበት፤ ሌሎች ቀበሌዎች ማንኛውንም ጉዳይ

ራሳቸው መርምረው ባለው ሁኔታ ካጣሩ በሁዋላ፥ ፍርድም ራሳቸው ይሰጣሉና የኛ ቀበሌ በተናጠል ታይቶ የተለየ አሰራር ሊፈጥር ወይም ሊከተል አይችልም. . . የሚሉ አሳቦች እኩል ተራ በተራ እየተሰነዘሩ ክርክሩ ተጋግሎ ቤቱ እንደ ቡርዥዋ ፓርላማ ሲንጫጫ ከቆየ በሁዋላ፥ ደርቤ እንደ ገና እጁን ስላወጣ መድረኩ ተሰጠው።

‹‹ጉዋድ ሊቀ መንበር፥ ጉዋዶች፥ ከቤቱ ብዙ አሳቦች ተሰንዝረዋል። ዞሮ ዞሮ የክርክራችን መነሻና መድረሻ የሚያተኩረው የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሠራር ይኑር ወይስ አይኑር በሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ነው። የሰፊው ህዝብ አብዮት ግቡን እንዳይመታ የሚፈልጉ አድሃሪዎችና በአብዮተኛነት ስም ከሰፊው ህዝብ ትከሻ ላይ ባቁዋራጭ ለመውጣት የሚፈልጉ የስልጣን ጥመኞች፥ ማእከላዊነት ጠፍቶ የስርአተ - አልበኛነት አሰራር እንዲነግስ የሚፈልጉ ለመሆናቸው እኔ በበኩሌ አልጠራጠርም. . .

‹‹ጉዋዶች፥ ባሁኑ ወቅት፥ በተለይ የስልጣን ጥም እንዳበደች ውሻ የሚያከለፈልፋቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ቀበሌዎችንን መሳሪያ ለማድረግ እንደሚፈልጉ ግልፅ ሆኖ እንዲታየን ያስፈልጋል። በስውር ዘዴያቸው በቀበሌዎች አካባቢ ስርአተ-አልበኛነት የሚነግስበትን ሁኔታ በመፍጠር አንድም አብዮቱን ለመቀልበስ፥ አለዚያም ባቅዋራጭ የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት በመፍጨርጨር ላይ ይገኛሉ። ቀበሌዎች የሰፊው ህዝብ አብዮት መሳሪያ እንጂ የግለሰቦችና የቡድኖች ስልጣን ጥም ማርኪያ እንዳይደሉ ከኔ የበለጠ እናንተ ታውቃላችሁ. . .

‹‹ጉዋዶች፥ ዋስይሁንና ግብረ አበሮቹን ከቁጥጥራችን ስር አውለን የፊጥኝ ታስረው ከፊታችን እንዲቆሙ ያደረግንበትን ምክንያት መለስ ብለን እንመልከት። ያንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች መሳሪያ በመሆን፥ በማን አለብኝነትና በአምባ-ገነንነት የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነትን አሰራር ደብዝ ከነአካቴው ስላጠፉ አይደለምን? እነርሱ ራሳቸው ጠርጥረው፥ እነሱው ይዘው እነሱው መርምረው፥ እነሱው ፍርድ ሰጥተው፥ እነሱው የፍርድ አስፈፃሚ በመሆናቸው አይደለምን? ታዲያ እኛ ደግሞ በተራችን ጠርጣሬ፥ መርማሪ ፍርድ ሰጭና አስፈፃሚ እንሁን ብለን ስንከራከር ራሳችንን በራሳችን መቃረን

አይሆንብንም - የለም ጉዋዶች፥ አዘማሚያችን ይህ አልመሰለኝም። እኔ እንደገባኝ ከሆነ ጭብጣችን፥ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ይኑር ነው!

‹‹ጉዋዶች፥ የዲሞክራሲዊ ማእከላዊነትን መርህ መሰረት በማድረግ የሚከተለውን አሳብ አቀርባለሁ። ቅድም ከተነበበልን ዝርዝር ዘገባ ላይ ሁላችንም በመፈረም ዋስይሁንና ግብረ አበሮቼን ለበላይ አካል፥ ለመንግስት አካልፊን መስጠት አለብን እንጂ እኛው ጠርጣሪ፥ እኛው መርማሪና ከሳሽ፥ እኛው ፍርድ ሰጭ መሆን የለብንም።››

አባድ ፀዮታ በቤቱ ላይ ወደቀ። ደርቤ ባቀረበው ክርክር ምክንያት አቁዋማቸውን የለወጡ ብዙዎች ቢኖሩም፥ አንዳንዶቹ፥ ‹‹ነገ በነፃ ተለቆ የተመለሰ እንደሆን የት ልንገባ? ምን ሊውጠን? የለም፥ አሁኑኑ ብረትን መቀጥቀጥ በግለቱ ወቅት እንዲሉ። አሁኑኑ አብዮዊ እርምጃ መውሰድ አለብን። ያልቀደመ ተቀደመ፥ ያልጠረጠረ ተመነጠረ›› የሚል የአስተሳሰብ አቅጣጫ በመከተል ለክርክር የሚያቅማሙም ነበሩ። በመጨረሻ ቤቱ በቀረቡት ሁለት አሳቦች ላይ ድምፅ እንዲሰጥ በተጠየቀበት ጊዜ፥ የደርቤ አሳብ ያላንዳች ተቃውሞ በሙሉ ድምፅ ተደግፎ በማለፉ ሊቀ መንበሩን ገረመው።

በዋስይሁንና በግብረ አበሮቹ ፊት ላይ ደካማ ፈገግታ መታየት ጀመረ። አንድ ሰአት? አንድ ሌሊት? አንድ ቀን? ሳምንት፥ ወር? ማን ያውቃል?

ይህችን የምታጉዋጉዋ አለም ሳይወድ በግድ ተሰናብቶ፥ ዳግመኛ ላይመለስ፥ አንደኛውን ለመሄድ የሚፈልግ ማን አለ ሰው ልብ ምን ቢሆን ፍፁም ተስፋ አይቆርጥም። ሙት ብቻ ነው ተስፋ የሌለው። ፈገግታቸው ጨመረ። ግን በአንባሩ፥ የደርቤ ልብ በአሳብ ባህር ውስጥ እየሰመጠ፥ ሀሊናው እየተጨነቀ፥ ፊቱ እንደ ክረምት ሰማይ ጭጋግ እየለበሰ ይሄድ ነበር. . .

‹‹ከሁሉም በላይ አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››

‹‹አብዮቱ!››



ምእራፍ ፫

ሂሩትም ሆነች ተሰማ ወይዘሮ አምሳለ ያደረጉትን የስልክ ጥሪ ሳይሰሙ ቀርተው አልነበረም-ዘም ያሉት።

ስልክ ደወለ። ሁለቱም ተያዩ። አንድ አይነት የመግባባት መንፈስ በመካከላቸው ተፈጥሮ ነበር። ሆኖም ሶስተኛው ወጣት ትላልቅ አይኖቹን በስልኩ ላይ ተክሎ ለማንሳት የሚያቅማማ መሆኑን በመገንዘብ፥ ‹‹እርሳው! አሮጊትዋ ናት›› አለች ሂሩት፤ ጥሬ እንደ ቃመች ዝንጀሮ የቀኝ ጉንጭዋን በጎረሰችው ጫት አሳብጣ። እጅዋም እግርዋም አያርፍም። ከሰፊው ክፍል ውስጥ አበባ ምንጣፍ ከወለሉ ላይ ዘርግተው መጅሊስ የገቡ ይመስል ሶስቱም ቁጭ ብለዋል። ሻይ በጀበና ቀርቦአል። ጫት ከያንዳንዱ ፊት ተከምሮአል። ሃድራው ወርዶአል።

ቤቱ ከመንገድ ራቅ ያለ በመሆኑ የአላፊው የአግዳሚው ጫጫታ አይሰማም። ተኩስ አልፎ አልፎ ከሩቅ እንደ ክረምት ሰማይ ያጉረመርማል። ቤቱ የከተማ ቦታንና ትርፍ ቤቶችን ከመንግስት ቁጥር ስር ያዋለው አዋጅ ከመታወጁ በፊት ትንሽ ቀደም ብሎ ወደ ክትፎ ቤት የተለወጠ ቢሆንም፥ በፊት በወር አምስት መቶ ብር ኪራይ የሚያስገኝ ቪላ ነበር። ወይዘሮ አምሳለ ቤቱ እንዳይወረስባቸው ደህና ጉቦ በመስጠት ትርፍ ቤት መባሉ ቀርቶ በድርጅትነት ስለተመዘገበ፥ ለማስመለል ያህል የክትፎ ንግድ ከፈቱበት እንጂ፥ ቤቱ ከሰዋራ ቦታ የተሰራ በመሆኑ ክትፎ ለመብላት ብቅ የሚልም ደንበኛ ብዙ አልነበረም።

አፍሮውን አንጨፍሮ እንቅልፉም ትላልቅ አይኖቹን የሚያንከባልለው ወጣት በሂሩት እንደዚህ አርግጠኛ ሆኖ መናገር መንፈሱ አልረካም - ‹‹ብሞን አወቅሽ አሮጊትዋ መሆናቸውን? ወይስ ጫቱ ወልይ አድርጎሻል?›› አላት፥ ኮስተር ብሎ ጫቱን እያኘከ።

በተሰማ ልብ ውስጥ ጥርጣሬና ፍርሃት አደረ። እናቱ የሚጠሉበትን የተንዥረገገ ጢሙን አንድ ባንድ እየመዘዘ ወደ ታች ይስብ ጀመር። ውጭ እንደ ዶፍ የሚወርደው ተኩስ መንፈሱን ማወክ ከጀመረው ቆይቶአል - ‹‹ሂሩቴ፥ ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል!›› አለ ተሰማ፥ አሳቡ ታውኮ።

ሃሩት ፍንክች አላለችም። ከፊትዋ ተከምሮ ከሚገኘው ጫት ውስጥ እንዱን ዘለላ አንስታ ቅንጥጥ ቅንጥጡን በረጃጁም ውብ ጣቶችዋ አንድ ባንደ እየቀነጫጨለች፥ «እርጊትዋ ስትደውል ስልኩ ከአምስት ጊዜ በላይ አይጮህም። ምንዘዜም፣ ለምሳሌ፥ ተፈራ አይታወትህም እንጂ፥ ከሶስት ጊዜ በላይ ስልክህ እይጮህም። የለምችን የስልክ ጥሪ አስተውሎ ማን እንደሆነ የማወቅ ጉዳይ ነው እንጂ ወልያነት አይደለም። ረክችሁ ጉዋደች?» አለች፥ ዘንሩላ፥ ጥቁር፥ ረጂም ጠጉርዋን፥ ጭንትላትዋን ወደ ቀኝ መታ በማድረግ ከፊትዋ ላይ ገለል እንዲል አድርጋ።

መሀል ለመሀል ተከፍሎ እየተዘናፈለ ከጠባብ ክብ ትከሻዋ ላይ የሚወርደው ጠጉርዋ ከጥቁሬቱ የተነሳ የኤሌክትሪኩን ብርሃን መልሶ ያንጸባርቃል። የእናትዋን አይን አንዳለ ወርሳለች። እንደ ፊርጥ ይንቦገቦጋል። ፊትዋ ግን እንደ እናትዋ ፊት ክብ አይደለም። ረዘም ብሎ ውሃ ልክ እየጠበቀ ያወርዳል። አፍንጫዋ እንደ አባትዋ አፍንጫ ሰንደዶ ሳይመስል፥ እንደ እናትዋም አፍንጫ ስልክክ ብሎ ተገትሮ ሳይወርድ፥ ራሱን ጠባይ ይዞ ጉርድ ያለ ነበር። የጉንጮችዋ አጥንቶች ከፍ ብለው እንደ አለት ድንጋይ የቆሙ ሲሆኑ፥ ወፋፍራም ከንፈሮችዋ በከንፈር ቀለም አጊጠው የፅጌረዳ እምቡጥ በመምሰል አይን ይሰባሉ። ፊገግ ስትል ትላልቅ ወልጋዳ ጥርሶችዋ ጠቅላላ ውበትዋን ለመቀነስ ከጀል ቢያደርጋቸውም፥ ሳቅ በምትልበት ጊዜ ስርጉድ የሚሰው ጉንጭዋ የሚፈጥረው መግነጢሳዊ ሃይል ልብ ስንጥቅ ያደርጋል።

«ሳይንሳዊ ሳይሆን ቁሞናዊ መልስ ነው።» አልረካሁም» አላት ተፈራ አረንጓዋሬ የጫት ቅጠል ጋር የሚነፃፀረውን የጥፍሮችዋን ቀይ ቀለም በአድናቆት እየተመለከተ።

«ስኔ እርካታ የሚያገኝ ወንድ የለም! እኔ ለወንዶች ምን ጊዜም የውሃ ፓምፕ ነኝ» አለችና፥ አንዲት ቀንበጥ ጫት በጥሳ ጎረሰች። ጉንጭዋ እያበጠ ይሄድ ነበር።

ተሰማ በሕህቱ አነጋገር እንደማፈር ብሎ፥ ሴታ ሴት ፊቱን ቅልስልስ አደረገ። ጢሙን የሚያላድገው ሴታ ሴት መልኩን ለመለውጥ ነበር። አነጋገርዋና አደራሳትዋ ሁል ጊዜም ቁጥብ ስሜቱን ገፍትሮ ያስደነግጠዋል።

‹‹አሁንም የሰነበርሺው ቀኖናዊ አስተያየት ነው። ሳይሽ አረካለሁ። ነፍሴም ቁምር ትረካለች›› አላት።

‹‹ዝጋ ባክህ! ለትዝታዊ ስሜት ደንታ የለኝም። ወንዶች ስትባሉ ውሾች ናችሁ!›› አለችው።

‹‹እሺ፥ ለማዳ ውሻሽ ነኝ!›› አላት።

ተሰማ ተበሳጭቶ፥ ‹‹አቁሙ ባካችሁን። የምትናገሩት ሁሉ ደስ አይለኝም፥›› ከማለቱ . . . .

ተፈራ አቁዋረጠውና፥ ‹‹ገርል ፍሬንድህ ስላልመጣች ነው ንግግራችን ያስጠላህ? እውነት ዛሬ እቴቱ የት ጠፋች?›› ብሎ ጠየቀው፥ እየቀለደ።

‹‹እቴቱ ገደል ትግባ! ለቀልድ ጊዜ የለኝም። ይህን ሁሉ ተኩስ እየሰማችሁ ስትቀልዱ ይገርመኛል›› አለ ተሰማ፥ ብስጭት ብሎ።

‹‹ማሙሽዬ፥ አይዞህ፥ ፈርተህ አትጨነቅ። የተኩስ ጋጋታ የመርበድበድና የመደናገጥ ምልክት ነው - ሌላ አይምሰልህ። የመፍረክረክ ምልክት ነው። የባሰ ለማፍረክረክ ቅስቀሳችንና ነጥሎ የመምታት ተግባራችን በይበልጥ መፋፋም አለበት። ቀበሌ ከተዘጋ ለኛ በሩ ይከፈታል›› አለችና፥ ጫትዋን እኝክ እኝክ አደረገች።

ስልኩ እንደ ገና ተደወለ። ሂሩት ስልኩ ስንት ጊዜ እንደሚጮህ በልብዋ መቁጠር ጀመረች፤ አንድ፥ ሁለት፥ ሶስት፥ አራት፥ አምስት. . . ‹‹አሁንም አሮጊትዋ ናት፤ ከመቼ ወዲህ ነው ደሞ ለኛ መጨነቅ የጀመረችው? ህይወትዋ ሁሉ መሬትዋ ነበር፤ እኛ በልብዋ ውስጥ ቦታም ሆነ ህልውና አልነበረንም. . . ትደውል አስር ጊዜ። አናነሳም። ትጨነቅ. . . የልጅ ፍቅር ምን እንደሆነ ይገባት እንደሆነ. . .››

ተሰማ ከሂሩት ጋር በአሳብ አልተስማማም። ሂሩት ስለ እናታቸው የተናገረችው ነገር ሀቅ ቢሆንም፥ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ በእናቱ ጭንቀት ላይ ሌላ ጭንቀት መጨመር የማያስፈልግ ጭካኔ ሆኖ ስለተሰማው፥ ‹‹እንደገና ብትደውል ስልኩን አነሳለሁ። ለምን እናስጨንቃታለን? አባታችንም ቢሆን በጣም ይሰጋል›› አለ፥ ኮስተር ብሎ ወደ ሂሩት እየተመለከተ።

ንቀት በተመላበት አይን መልሳ ተመለከተችውና፥ ‹‹ልብህ ሁልጊዜ ይሸራሞጣል! የሚሸረሙጥ ሰው አልወድም. . .›› ብላ ሳትጨርስ፥ ተፈራ ጣልቃ ገብቶ፥ ‹‹ሸርሙጣ በበዛበት በዚህ አለም አንድ ተጨማሪ ሸርሙጣ ምን ይጎዳል ብለሽ ነው?›› አላት፥ እየቀለደ።

‹‹ዝጋ! እናታችን የማይረሳ ትምህርት መማር አለባት። ትንሽ የማዘነው ለዚያ ቂል አባታችን ነው - በህይወት ውስጥ የሚንሳፈፍ ቂል ነው!›› አለችና እንደገና ጭንቅላትዋን ወደ ቀኝ መታ አደረገች።

‹‹ሂሩት ወለላዬ፥ እሺ እዘጋለሁ። ግን አሁን ከተደወለ ስልኩን ማንሳት አለብኝ። አንድ ጥሪ እየተጠባበቅሁ ነኝ›› አላት ተፈራ፥ እንደመለማመጥ ብሎ ቀያይ ትላልቅ አይኖቹን እያንከባለለ። ቀጠለና፥ ‹‹አልለማችሁ እንደሆነ ባሁኑ ሰአት በቀበሌያችን ውስጥ ምርጫ እየተካሄደ ነው። ውጤቱን በስልክ እነግርሃለሁ ያለኝ ሰው ስላለ ይህን ቁጥር ሰጥቼዋለሁ›› ከማለቱ፥ ተሰማ ችኩሉ፥ ‹‹የምን ምርጫ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹አዲስ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ለመምረጥ. . .››

‹‹አታደርገውም!›› አለች ሂሩት፥ እንደመሸበር ብላ። ቀጠለችና ‹‹ዋስይሁን ምን ሆነና? ብላ ጠየቀችው።

‹‹ዛሬ ወደ አንድ ሰአት ገደማ በቁጥጥር ስር አውለውታል. . .››

‹‹ደህና አደረጉ!›› ብላ ፍርድዋን ከሰጠች በሁዋላ፥ ቀጠል አድርጋ ‹‹አውሬ ነበር። በኛ እጅ ባለመጥፋቱ ይቆጨኛል። የጊዜ ጉዳይ ሆኖ ነው እንጂ ላእከ እሰራለታለሁ ብሎ ፎክሮ ነበር። እሱ ሞት ሲያንሰው ነው አለች፥ ባንድ ፊት በመያዙ ስትደሰት፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከመንገድ ላይ ተደፍቶ እንዲቀር ባለመደረጉ እየቆጫት። ወፍራም ከንፈረዋን ነከሰች።

‹‹የባሰ ቢመጣስ? አለ ተፈራ፥ ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁት ሰይጣን ይሻላል የሚለውን ጥቅስ እያሰበ።

‹‹እኛ ካንዱ የቀበሌ ተመራጭ ሌላው ይሻላል የሚል አቁዋም የለንም በሁለት ሰይጣን መካከል ምርጫ አናደርግም። እስከታገሉን ድረስ ሁሉም ጠላቶቻችን ናቸው›› አለች፥ ስሜትዋ ተጋግሎ።

‹‹ሂሩት ወለላዬ፥ እኔስ ዋስይሁን ቢኖር ይሻል ነበር እላለሁ። ለምን ብትይኝ፥ ድርጊቱ ሁሉ በቀበሌያችን ነዋሪዎች ዘንድ ለኛ ጥሩ ስሜት እያሳደረ ሂዶ ነበር። አንዳንድ ትበብርም ለማግኘት የቻልነው እሱ ህዝቡን በማነሳሳቱና በማስቀየቱ ምልክት ነው። የቀበሌው ህዝብ የሚያቅፈው ሰው ከመጣ ግን የባሰ ችግር ላይ እንወድቃለን። በዙሪያ መንገድ ዋስይሁን ከሰማይ ወረደልን አጋራችን ነበር›› አላት።

‹‹የቀበሌ ተመራጭ ብሎ አጋር እኔ አላውቅም!›› አለችና፥ ጫትዋን እንደገና እኽክ እኽክ አደረገች።

‹‹ከፖለቲካ አንፃር ስትመለከተው ማለቴ ነው. . .››

‹‹ተፈ ልክ ነው። ዋስይሁን ካደረሰብን ጉዳት በፖለቲካ አንፃር የሰጠን ጥቅም ያመዝናል›› አለ ተሰማ።

‹‹ዝጉ! ፍሬን ያዙ! ጠላት የማያደርሰውን ጥፋት ጠብቆ ከመጠቀም፥ በራሳችን ጥረት መተማመን ይሻላል። ትናንት ከዲሞክራሲ ያጠናነው ነገር ይኸው ነው። ጠላቶቻችንን ወደ ባሰ ጥፋት በመገፋፋት ከህዝቡ ጋር የባሰ ቅራኔ እንዲፈጥሩ ማድረግ የእኛን ጥረት፥ ብስለት፥ ፍጥነትና ድፍረት ነው እንጂ የሚጠይቀው፥ የእነሱን ሞኝነት ወይም ድክመት ብቻ አይደለም›› አለችና፥ ሲጃራ አውጥታ አቀጣጠለች።

‹‹የእነርሱ ድክመት ለእኛ ጥንካሬ አይሬዳም ነው የምትይው!›› አላት ተሰማ።

‹‹ዝጋ! ይልቅ ነገ በቀበሌያችን ቅስቀሳ ማድረግ የእኛ ተራ ነው። ተነገወዲያ ሰፊራችን ከምንጊዜውም ይበልጥ በአርማችን አሸበርቆ መገኘት አለበት። ቴስ - በበኩልህ ምን አድርገሃል?›› ብላ ጠየቀችውና ሰራስዋና ለእነርሱም ሻይ በትናንሽ ብርጭቆ ቀዳች።

‹‹እኔ የሚለቀሉትን አርማዎች ሁሉ አምጥቻለሁ. . .››

‹‹የሚበተኑትንስ ወረቀቶች?››

‹‹እሱንም ተረክቤአለሁ።››

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹ጥሩ። ትልቁ ሃይላችን የምንበትናቸው ዕሁፎች ናቸው። ቴፋ፥ ባንተስ በኩል?››

‹‹ሰሞኑን ላእከ በነገረን መሰረት ባንዳንድ ቤተሰቦች ውስጥ የኦሎታ ኮሚቴ አቁዋቁሜአለሁ። እሪታውና ኡኡታው ነገ ባይቀልጥ ምናለ በደኝ የገቢ ምንጫችንን ለማጠናከር በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚገኙት ሻይ ቤቶች እንዲወረሱ ሰፊ ቅስቀሳ. . . ሳካሄድ ነው የዋልኩት። በእድሮችም ውስጥ ሌሎች ጉዋዶች ሰፊ ቅስቀሳ እያካሄዱ ናቸው። ነገ በምንሰማራበት ቦታ ሁሉ የመከላከያ ጉዋዶች እንዲገኙ ነግሬአለሁ። የመዋቅራችን ሀዋስ የት እንዳለ ደርሶበታል የተባለው የጥበቃ አባል ማን እንደሆነም ጠቁሜአለሁ። ነገ ለጥብስ ሳያደርሱት አይቀሩም። ላእከ የዋዛ ሰው አይደለም!››

‹‹ኦኬ፥ ጥሩ ጥረት አድርጋችሁአል። ግን በቂ አይደለም። አብዮት የማያቁዋርጥ ሂደት ስለሆነ የማያቁዋርጥ ትግል ማካሄድ ይኖርብናል። ብቻችንን አይደለንም። መዋቅረችን ከላይ ከደርግ ጀምሮ ታች ድረስ የተዘረጋ ነው። በነገራችን ላይ ሳልረሳው. . . ቴፍ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ያሉትን ጉዋዶች አግኝተሀ አቁዋማችንን በይበልጥ በየፕሮግራሞቻቸው እንዲያንፀባርቁ እንድትነግራቸው ተብለሃል። እዚያ መስሪያ ቤት ውስጥ የተሰገሰጉትን አድርባዮች - ከአጎታችን ጭምር - አንድ ባንድ እንፋረዳቸዋለን። ለማንኛውም ነገር ላእከ ስጦታ ልኮላችሁአል›› ብላ ሲጃራዋን ቡልቅ እያደረገች ለማምጣት ተነሳች።

ተስተካክለው የተቀመጡት መጠነኛ ጡቶቿዋ፥ እንደ ሀረግ እየተመዘዘ የሚወርደው ቀጭን ሽንጥዋና ክብ ዳሌዋ ከመካከለኛ ቁመትዋ ጋር ተዳምሮ ስትታይ መግነጢሳዊ ስሜት አሳድራ ልብን በምጭት ታሞቃለች። ተፈራ ገበሬ ፊቱን ዘርግቶ ትላልቅ አይኖቹን እንደ አልቲት ከጆርባዋ ላይ ተጣብቆ ይከተላት ነበር - ያሳደረችበትን ስሜት ከሻሂው ጋር ፉት እያለ። በላይዋ ላይ የተለጠፈ የሚመስለው የለበሰችው ራንግለር ብሉ ጂንስ ሱሪ ከነኩቱ የገላዋን ቅርፅ እየቆጠረ ያሳያል. . . ተፈራ ተስማን ሀር ብሎ ላንዳፍታ ተመለከተውና የፍላጎቱ እንቅፋት ሆኖ ስለታየው በልቡ ጮላቻ አደረበት። የሰው ጉልቻ! ብሎ በልቡ ተሳደበ።

ሂሩት ሪፂም ሽንጥዋን እንደ ጦር እየሰበቀች ተመልሳ መጥታ ተቀመጠች። በፈጌርቅ የተወቀለለ ነገር ይዛለች። የተሰማና የተፈራ አይኖች ሪፂም ውብ ጣቶቹዋን በመከተል ከፈጌርቁ ላይ አርፈዋል። ፈጌርቁን ፈታታችና ሁለት ኦቶማቲክ ቢራታ ሽጉጥ ብቅ አደረገች። የሁለቱም ጎረምሶች አይኖች የባሰውኑ ፈጠጡ። አይኖቻቸውን ሰማመን አልቻሉም፤ ‹‹አኬ - ልጆች፥ ይህ ስጦታ ከበላይ አካል የመጣው ለእናንተ ነው›› ብላ፥ አስር አስር ጥይት ጨምራ ሰጠቻቸው።

የተሰማ ልብ እንደ መቆም አለች። ሁለቱም ሽጉጦቹን በፍቅር አይን አገላብጠው ተመለከቱ።

ተሰማ ከንፈሮቹን አሹሎ አፉዋጨና፥ ‹‹ይፂ . ሲስ ፥ ምናደርግበታለሁ? እንዴት እንደሚተኮስ እንኩዋን አላውቅም›› አለ፥ ሽጉጡን እየዳሰሰ፥ አይኖቹን አፍጥጦ።

‹‹ጂል! ራስህን ትጠብቅበታለሃ! የልጆች ጨዋታ ሽርተቴ በመጫወት ላይ ያለህ መሰለህ? ለጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት መፈክር አሸናፊነት የተሰለፍክ ታጋይ መሆንክን አትርሳ! ሁለታችሁም ዛሬ ልትኮሩ ይገባል፥ መሳሪያው የድርጅታችን ሙሉ አባል መሆናችሁን የሚያረጋግጥ ነው›› አለችና፥ ዊነስተን ሲጃራ አውጥታ ሰራስዋ አቀጣጥላ ስታበቃ ለሁለቱም አንዳንድ ሲጃራ ከክብሪት ጋር ወረወረችላቸው።

ተፈራ በስሜት ገንፍሎ፥ ‹‹ይህችን ምሽት ማክበር አለብን። እማማ ጭላጭ ውስኪ እንኩዋን ውጭ ትተው አይሄዱም እንዴ?›› ብሎ ጠየቀ።

ሂሩት ሲጃራዋን ማማ ማማ ስታደርግ ትንሽ ቆየችና፥ ባለ አንዳንድ መቶ ብር ኖት ከቦርሳዋ መገዛ በማውጣት፥ ‹‹ይህ ደግሞ በስራችሁ ወቅት የሚያጋጥማችሁን ወፌኪ እንዲሸፍን ነው›› ብላ ሰጠቻቸውና ተነስታ ሄዳ ግማሽ ጠርሙስ ሌቢል ውስኪ ከሶስት ብርጭቆዎች ጋር ይዛ መጥታ ቀዳችላቸው። ለራስዋም ቀዳችና፥ ‹‹ለጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት መፈክር አቸናፊነት!›› ብላ በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ አደረገችው።

የተሰማ ልብ በታላቅ ፍርሃት ተዋጠ። ሂሩት የሚያውቃት እህቱ መሆንዋን ለማመን አቃተው። ፊዕሞ የማያውቃት ባእድ መስላ ታየችው።

ቀዝቃዛ ላብ ጀርባውን አቁዋርጦ ሲወርድ ተሰማው። ሂሩት የወንድምዋ ስሜት አጨነቃትና፥ ‹‹ቴስ፣ ምን ሆነሃል? በመደሰት ፈንታ ያዘንክ ትመስላለህ አለችው።

‹‹እ. . . እኔ ይህ ሽጉጥ ምንም አያደርግልኝም. . .››

‹የሽርሙጣ ልብህ መሸረሙዋሞጥ ጀመረ እንግዲህ!››

‹‹መሸራሞጥ አይደለም፥ አልፈልገውም! እኔ በግድያ አላምንም...››

ሂሩት ተቆጥታ ከተቀመጠችበት ምንጭቅ ብላ ተነስታ ረጃጁም ጣቶችዋ አንቁዋቁዋች። ጫትዋን በንዴት እኝክ አደረገች። ከማንም የአምቢታ መልስ የመቀበል ልምድ ስለሌላት በወንድምዋ እጅግ ተናድዳ ነበር። ጭንቅላትዋ እንደ ልማድዋ ወደ ቀኝ መታ አደረገችና፥ ‹‹አምን፥ አንተ በግድያ አታምንም . . እ. . . ማሙዬ . . እ. . . የምትፈልገው ነገር ሁሉ እንደ መና ከሰማይ ይወርድልሃል. . .›› እያለች መጋጋል ስትጀምር፥ ተሰማም በበኩሉ ብልጣ ብሎበት፥ ‹‹በእሱም አላምንም!›› አላት፥ ሳይታወቀው ድምፁን ከፍ አድርጎ።

‹‹በየቱ ነው የማታምነው?

‹‹ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት በምትሉት ፈሊጥ. . .››

ሂሩት ስትናደድ ጎራዳ አፍንጫዋን ነፋ ነፋ እያደረገች ትላልቅ አይኖችዋን ጎልጉላ ስለምታወጣ ውበት ጨምራ ታፈዛለች።

‹‹ቴስ. . ባንዳ አትሁን። ላእከ እንዳይሰማህ ብቻ›› አለው ተፈራ።

‹‹ላእከ ገደል ሲገባ ይችላል! እሱን በመፍራት እንደ በግ ልነ አልችልም። አላምንበትም ነው የምልህ! ይገባሃል?›› አለውና ወደ እህቱ ዞ ብሎ፥ ‹‹ያልነቃ፥ ያልተደራጀና ያልታጠቀ ህዝብ ከመሬት ተነስቶ እንደ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ሊያቁዋቁም እንደሚችል እኔ አይገባኝም! ህዝባ ሆኖ ጊዜያዊ ነገር ሊገነኝም አይችልም!›› አለና በረጂሙ ተነፈሰ። ቀጠለ ‹የወሰድነው አቅዋም ሁሉ እያጠራጠረኝ ሄዶአል። እውነቴን ነው›› አ ፍርጥም ብሎ።

‹‹የባንዳምችን ስነ ጽሁፍ እያነበብክ ይሆናል!›› አለው ተፈራ።

‹‹ዝን ቱፍ! አንተ ምንም ነገር ሊገባህ አይችልም። በሀሊናህ ውስጥ የሚንጭ ነገር የለም። አንተ የሄሩቱ ጥላ ነህ! ሁሉን ነገር እንደ ቀልድ ነው የምትወስደው. . .››

‹‹አንተስ?›› አለችው እህቱ፥ ንቀት በተመላበት ሁኔታ።

‹‹እኔ አልቀልድም። ሳንዘገይ አቅዋማችንን ማስተካከል አለብን። እውነቴን ነው። አገራችን ስትወረር፥ ወታደሩ መሀል ገብታችሁ፥ የምታካሂዱት አድሃሪ ጦርነት ነውና አትዋጉ እያላችሁ ቅስቀሳ አካሂዱ. . .እ. . . የጭቁን ብዜረሰቦችን መብት እስከ መገንጠል ድረስ አሁንኑኑ እንደግፋለን በሉ፥ ወዛደሩ ምርቱን እንዲቀንስ ካገሪትዋ አቅም በላይ የሆነ የደመወዝ ጭማሪ እንዲጠይቅ አድርጉ፥ ወታደሩ እንዳይዋጋ ቅስቀሳ አካሂዱ፥ እየተባለ የሚሰጠን መመሪያ ሁሉ በኔ ግምት ትክክልና ሳይንሳዊ አይደለም. . .››

‹‹አላልኩም? የለየለት ባንዳ ሆኖአል እኮ!››

‹‹ባንዳነት አይደለም እባክህ! የሀሊና ጉዳይ ነው። ለሰፊው ህዝብ ነፃነት፥ እኩልነት፥ ለጭቁኖች መደብ አንድነትና ለሶሻሊዝም እንዋጋለን፥ ፋኖ ተነስ ተሰማራ፥ እንደ እነ ሆቺ ሚኒ እንደ እነ ቼ ጉቬራ! ብለን የተነሳን ወጣቶች ዛሬ ለስልጣን ብለን፥ ከዐረ ህገ-ብ፥ ዐረ - አንድነትና ፀረ - ሶሻያሊስት ሰፊር ገብተን መሰለፍ የለብንም። እዚህ አቅዋም ላይ ያደረሰን የስልጣን ጥያቄ ነው. . .››

‹‹ስልጣን ለፓርቲያችን ካልሆነ ለማን ሊሆን ነው ታዲያ? ለወታደር? ስንታገል የቆየነው ወታደር ስልጣን እንድይዝ ነው?›› ብሎ ተፈራ ጠየቀው።

‹‹እባክህን ተወኝ! ራሱን ፓርቲ ነኝ ብሎ የሰየመ ሁሉ ፓርቲ ሊሆን አይችልም። እነላእከ ቅዠት ነው። አላምንበትም ነው የምልህ!›› አለው፥ ፍርጥም ብሎ።

እህቱ በተጎለጎሉት ትላልቅ ውብ አይኖችዋ በንቀት ተመለከተችውና፥ ‹‹ማሙሽ. . እ. . .ብታምንበትም ባታምንበትም . . .እ. . . አንገትህ ድረስ ተዘፍቀህበታል። ከእንግዲህ መውጫ የለህም። ሁላችንም የለንም! ይህን በሚገባ ማወቅ አለብህ. . . ማሙሽ። ከሃዲዎች ምን እንደሚደረጉ

ታውቃለህ? የምታውቅ አይመስለኝም። በሁለት አሳት መሀል ያለን ሰዎች
ነን. . . ማሙሽ ወዲህም ብትል ወዲያ ወዲህ አሳቱ ይለበልብሃል. . .እ. . .
እውነታው ተከሰተልህ? ተጨባጭ ሁኔታ ይህ ነው. . . ማሙሽ. . .እ. . .
ገባህ?›› አለችውና ጣቶችዋን እንደ ገና አንቀዋቀዋች።

‹‹ንቃት. . .ድርጅት. . .ትጥቅ. . .እ. . . የለየለት ባንዳነት ነው! የደርግ
ቡችላ. . .ባንዳ. . .አድርባይ. . .ሆነሃል መሰለኝ ቱስ . . .ኤ?››

‹‹ዝጋ እባክህ! አንተ ደግሞ ቁም ነገር የለህም። የሚሉህን ብቻ ነው
መልሰህ እንደ ገደል ማሚቶ የምታስተጋባው! ከማያምኑበት ነገር ራስን
ማውጣት ራስ መራራ ትግልንና ቆራጥነትን ይጠይቃል። በፍርሃት ተውጠን
እንደ ከብት መነዳት የለብንም›› ብሎ ሲያበቃ ወደ ሂሩት መለስ ብሎ
‹‹እህት አለም! ሁሉን ነገር እንደ ልጆች ጨዋታ የምትመለከቺው አንቺ ነሽ
እንጂ እኔ አይደለሁም። ነገሩ አስጊ ነው። የድብብቆሽ ጨዋታ አይምሰልሽ›
አላት

‹‹እስከዛሬ የት ነበርክ?›› አለች ሂሩት ተቆጥታ ጫትዋን በሀይል
እያኘከች።

ስልክ ተደወለ። ሶስቱም ተያዩ። ክፍሉን ከባድ ፀጥታ ውጦት ነበርና
ስልኩ በድንገት ሲደውል በጣም ደንግጠው ነበር። ሂሩት ነፍስ ገዘታ
በመቻኮል ሂዳ ስልኩን አነሳች. . .

‹‹ተፈራ. . . ስልክ ይፈልግሃል›› ብላ ስልኩን ሰጠችው . . .
ሰአትዋን ተመለከተች። ተኩሱ ጨለማውን እየሰነጠቀ ይሰማል።

‹‹ሃሉ! ማን አልከኝ?. . . ደርቤ? . . . ደረቤ ማ?. . . ደርቤ ጉተማ
አይደረግም! እውነትክን ነው?. . . አይደረግም! . . .››

ሂሩት ተሰማ ደርቤ ጉተማ የሚል ስም ሲሰሙ ነቅተው ተፈራ በስልክ
የሚያደርገውን ንግግር ማዳመጥ ጀመሩ። ተፈራ በችኮላ ስልኩን ዘግቶ
የመገረምና የመደናገጥ ሁኔታ ከገፅታው ላይ እየታየ ‹‹ሰምታችሁአል ማ
የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ እንደ ተመረጠ?›› አለ።

‹‹ደርቤ ጉተማ ነው እንዳትለኝ!›› አለች ሂሩት፥ መልሱን ለመስማት ተቸኩላ።

‹‹ነው! ተአምር ነው. . .የማይታመን ተአምር ነው. . .››

‹‹አይደረግም!›› አሉ እህትና ወንድም በአንድት፥ ጆሮአቸውን ለማመን እየተቸገሩ።

‹‹የባሰ ቢመጣስ? ብዬ አልነበረም ቅድም። ታይቶኝ ነው መሰለኝ! የሚገርም ነው!›› አለ ተፈራ።

‹‹ማን ነው ለመሆኑ የደወለልህ?›› ብላ ጠየቀችው ሂሩት፥ ተጠራጥራ።

‹‹የኮድ ስሙን ብቻ ነው የማውቀው። መሪ ጌታ ይባላል። የኛ ሰው ነው›› አላት።

ሂሩት ተገርማ፥ ‹‹ጉድና ጅራት ከወደሁዋላ ትላለች እናቴ! ፊዕም የማይታሰብ ነገር ነው!›› አለች።

ተፈራ ትንቢት የመናገር ችሎታውን እንዲያደንቁለት በማሰብ፥ ‹‹የባሰ ቢመጣስ ብዬ አልነበረም?›› አለ፥ ፈገግ ብሎ።

‹‹ዝጋ! የቃምከው ጫት ገልያልህ ይሆናል! ጥያቄው አሁን ያንተ ወልያነት አይደለም። ማሰብ አለብን›› ብላ፥ ከንፈርዋን እየነከሰች ጣቶችዋን አንቁዋቁዋች። ጭንቅላትዋንም ወደ ቀኝ መታ አደረገች።

‹‹ሂሩት ወለላዬ፥ እውነትሽን ነው! ማሰብ አለብን። ውስጠ አዋቂ ጠላት ነው ኮ የተፈጠረብን። አደገኛ ነው። ደርቤ ስለኛ የማያውቀው ምን ነገር አለ? ሁሉንም ነገር ያውቃል። ከእድገት በህብረት ዘመቻ ተደብቀን እንደ ቀረን ያውቃል። የትግል መስመራችን ምን እንደሆነ ከሀ እስከ ፐ ያውቃል። በድርጊት ያረጋገጥነለት ጉዳይ ነው። ሌላ የማያውቀው ምን ነገር አለ? ጉድ ነው ኮ! ውስጠ አዋቂ አደገኛ ነው. . .››

‹‹ታዲያ ኮ ምን እናድርግ! ውስጠ አዋቂ መሆኑን ተገንዝበናል። እሱ እንዳረጀ ሽክላ መልሰን መላልሰን መዝፈን የለብንም። ምን እንደምናደርግ

እናስብ ነው የምላችሁ!›› አለች ሂሩት፥ ትእግስትዋ አልቆባት፥ ጭንቅላትዋን አስር አስረ ጊዜ ወደ ቀኝ መታ እያደረገች።

‹‹ይህች ጥሬ ካደረች አትቆረጠምም ይባላል! እኔ ሳይቆይ መመታት አለበት እላለሁ። ለመከላከያ ጉዋዶች አሁኑኑ ደውዬ ማስታወቅ አለብኝ!›› ብሎ ውስኪውን በአንድ ትንፋሽ በመጨለጥ ቁና ቁና እየተነፈሰ፥ ወደ ስልኩ ሊሄድ ሲል፥ ተሰማ ጢሙን አንድ ባንድ ስቦ ወደ ታች እየጎተተ፥ ‹‹ቆይ! ቆይ! አትቸኩል። የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ሲሉ አልሰማህም? ረጋ በል። አትቸኩል። የቸኮለ አፍስሶ ለቀመ እንዳይሆን› አለው፥ ረጋ ብሎ።

‹‹አደገኛነቱ አልተከሰተልህም መሰለኝ! ነገሩ፥ ወይ ከኛ ወይ ከሱ መሆኑ ገብቶሃል? ጊዜ ካጠፋን ጠፊዎቹ እኛ እንሆናለን! ይገባሀል?››

‹‹ይገባኛል!›› አለ ተሰማ፥ ረጋ ብሎ ጢሙን እየሳበ። ቀጠለና፥ ‹‹የሚገባኝ ሌላም ነገር አለ›› አላት።

ሂሩት ትእግስትዋን ጨርሳ፥ ‹‹እንደምን ያለ?›› ብላ አፈጠጠችበት።

አሁንም ረጋ ብሎ፥ ‹‹ደርቤ አብሮ አደግ ወንድማችን ነው። ወላጆቻችን ማታ ማታ እንዲማር አድርገው ከኛ ጋር አሳድገውታል፡ በአስታችን አማካይነት ስራም ስላስያዙት ባለውለታው መሆናቸውን ያውቃል። ደርቤ ውለታ የሚበላ ሰው አይደለም። ደርቤን ራሴን ያህል ነው የማውቀው፥ ራሴን አውቅ እንደሆነ፡፡ እና›› ከማለቱ፥ ሂሩት ነገሩን ካፉ ነጥቃ፥ ‹‹ዝጋ! መመታት አለበት!›› ብላ አፈጠጠችበት።

‹‹በአገራችን ውለታ እና ይሉኝታ የሚሉት ነገር አለ ለማለት ነው!››

‹‹የመደብ ትግሉስ!›› አለ ተፈራ።

‹‹የአብዛኞቻችን ንቃተ ህሊና፥ ማንኛውንም ነገር ከመደብ ትግል አንፃር ተመልክቶ ይሉኝታን፥ ውለታን፥ የስጋ ዝምድናንና ጉዋደኝነትን ጨርሶ ከመርሳት ደረጃ ላይ ገና. . ገና አልደረሰም. .››

‹‹ሰው እንዳስቀመጡት አይገኝም ትላለች እናቴ! ተለውጦ እንደሆነስ? ዛሬ ነጉቱ ተለውጦአል! ከራስ በላይ ነፋስ በማለት ሁሉም ለራሱ የሚሮጥበት፥

አድር ባይ የበዛበት ጊዜ ነው። በዚህ ሩጫ ውስጥ ይሉኝታን መፍራት፥ ውለታን መቁጠር የለም. . ተምኔታዊ አስተሳሰብክን አቁም! ዝጋ!›› አለችና ወደ ተፈራ ፊትዋን አዙራ፥ ‹‹ይልቅ ስልኩን ደውል›› ብላ ካዘዘችው በሁዋላ፥ ‹‹እኛን ከግል ጥቅሙ የሚያስቀድምበት ምክንያት አይታየኝም። አሁን ትልቁ አንገብጋቢ ጥያቄ. . .ከኛ ወይ ከአርሱ ነው። ወንድም አለም! በዚያ ላይ ደግሞ ደርቤ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ከፍተኛ ፍላጎት ያለው ሰው መሆኑን አውቃለሁ›› አለችው።

‹‹ባንቺ ምክንያት ይሆናል፥ ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ የሚጥረው. . .››

‹‹ምን ማለትህ ነው!›› አለች ሂሩት፥ በጣም ተቆጥታ።

ሰውነትዋ ሁሉ ይንቀጠቀጥ ነበር። አይኖችዋ ተጎልጉለው ወጥተዋል። የታችኛው ከንፈርዋን ጣል አድርጋለች።

‹‹ተሰማ እህቱ በጣም የተናደደች መሆንዋ ስለገባው፥ ‹‹ምን አስቆጣሽ!›› አላት።

‹‹እንጃልህ!›› አለችው።

‹‹እህት አለም፥ ደርቤ ይወድሻል። መውደድ ስል ያፈቅርሻል ማለቴ ነው. . .››

‹‹የውሻ ልጅ፥ የምን ፍቅር!›› አለ ተፈራ፥ ቅናት አድሮበት።

‹‹አቁም ብዬሃለሁ!›› አለችና ሲጃራዋን ቡልቅ አደረገች፥ ጢሱ እስኪያፍናት ድረስ።

ድምፅዋ ስልቱን አጥቶአል። ጉሮሮዋ ለመዘጋት ደርሶአል። ንዴት ይተናነቃት ነበር።

ተሰማ በዚያው አላበቃም። ‹‹አዎን፥ ያመልክብሽ ነበር። ከቤት ወጥተሽ እስክትመለሺ ትእግስቱን ጨርሶ ጌታውን እንደሚጠብቅ ውሻ ይንጎራደድ ነበር። እግርሽን ካጠበ በሁዋላ እንዴት አድርጎ እንደሚስመው ትዝ ይልሻል፥ እህት አለም?›› አላት።

ሂሩት ንዴትዋን ልትቆጣጠረው አልቻለችም። ተፈራ መካከላቸው ባይገ
ኖር ጥፍሮችዋን አሹላ ጉሮሮውን ልታንቀው ነበር።

ብርድ እንደ መታው ሰው እየተንቀጠቀጠች፥ ‹‹ሌላ የምታውቀው ምን ነገር አለ?›› ብላ ሊዘጋ በደረሰ ጉሮሮ ጠየቀችውና፥ ሲጃራ አውጥታ በማቀጣጠል ጢሱን ባንዳፍታ ጉም አስመሰለችው።

ተፈራ ግራ ገብቶት አፉን ከፍቶ ቀርቶአል። ተሰማ እህቱን ትኩር ብሎ ለረጅም ጊዜ ተመለከተ። የሚያውቃት እህቱ መስላ አልታየችውም። አንድ ነገር ለመደበቅ እንደምትሞክር ገባው። አንድ ነገር ሽፋፍና ለማለፍ ስትፈልግ ሁልጊዜ አስቀድማ የምትናደድ መሆንዋን ያውቃል።

‹‹ይሄው ነው። ሌላ የማውቀው የለም። ለማለት የፈለግሁት አደገኛ ሰው አይደለም፥ ስለዚህ አንችኩል ለማለት ነው›› አላት።

በረጅሙ ወደ ውጭ ተነፈሰችና፥ ‹‹የማይገባ ነገር አለ። አንድ ቀን ይገባህ ይሆናል። ወንድምና እህት ብንሆንም በብዙ መንገድ አንተዋወቅም›› ብላ ሲጃራዋን ማግ፥ ቡልቅ አደረገችና ወደ ተፈራ መለስ ብላ፥ ‹‹ለላእከ ደውለህ ንገረው። አስቸኩዋይ ነው በለው›› አለችና አዘዘችው።

እህትና ወንድም ልብ ለልብ ተራርቀው ተያዩ።

ተፈራ ስልኩን ደወለ . . .

ምእራፍ ፬

ከሶስት ዓመት በፊት ነበር። ከሂሩትና ከደርቤ ሌላ ቤት ውስጥ ማንም አልነበረም። ሂሩት፥ እንቅልፍ ባያወስዳትም በጠዋት መነሳት ስቃይ ስለሚሆንባት እንደ ልማድዋ ከመኝታዋ ውስጥ አድፍጣ ትገላበጣለች እናትዋ ጠዋት በማለዳ የማትነሳ ሴት ልጅ ስለማይወዱ አርፍዳ የመተኛት ልማድዋን እንድትተው ሁልጊዜ ይቆጡዋታል። እናትና ልጅ የአለቱን ንትርክ የሚጀምሩት በዚሁ ጉዳይ ላይ ነበር።

ደርቤ የቤት ፅዳት ስራውን ጀምሮ ትንበስ ቀና ይላል። ትንሽ ዳረብታ መስሎ የተቆለሰውን የቤተሰቡን ልብስ ማጠቡ፥ የጌቶችን ሸሚዞች መተኮስና ሱፍ ልብሳቸውን መጥረግ ስለነበረበት፥ የቤት ሽኮት ስራውን ቶሎ ለመጨረስ ይጣደፍ ነበር።

ባልና ሚስት በጠዋት ተያይዘው እንደሄዱ፥ ተለማ እግራቸውን ተከትሎ ነበር የወጣው፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪች በጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ በመዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ያውቅ ነበርና ወላጆቹ ከቤት እስኪወጡ ድረስ ትእግስቱ አልቆ ነበር።

አባቱ ለእንዳልካቸው ካቢኔ መቀትም ሆነ ብርድ ባይሰማቸውም፥ ተቃውሞ ለማሰማት የወጣ መሆኑን እናቱ ቢሰመሙ ከቤት እንደሚያባርሩት ያውቃል. . .

እናቱ የእንዳልክካቸው ካቢኔ ጉዳይ በተነሳ ቁጥር፥ እንደ እግር ውስጥ እሳት ነበር የሚያንገበግባቸው። ‹‹እና አክሊሉ መናጢ ድሀዎችን በመስበሰቡ አይደለም እንዴ አገር የተበላሸውና ይህ ጉድ ሁሉ የፈላው! እንዳልካቸው የህዘቡን ልብ ትርታ አዳምጦ፥ የመሳፍንቱን፥ የመኮዋንንቱንና የባላባቱን ልጅ በመብራት እየፈለገ ስለ ሾመላችሁ ምን አድርግ ነው የምትሉት! ዱሮውንስ ማን ሊያስተዳድረን ናሮአል! ደግሞ ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም ብሎ ነገር! የጨዋ ልጅ ጉልቻ አይባልም!›› ይሉና፥ ‹‹እኔ ለመኮንን ሀብተ ወልድ ነው እንጂ ለአክሊሉ ደንታ የሰኝም። ከሰው ዘር ጋር ሲሰራ አላየሁትም። ተምረዋል ኮሚባሉ ከድሀ ልጆች ጋር ሊልከሰከስ ናሮ ነው፥ ወታደሩ ገና አንጥስ ሲል ተልፈሰፍሶ ትንጥስ ብሎ የወደቃውን ድንቄም ትምህርት! ወቸ

ጉድ! ህዝብን ለማስተዳደር ትምህርት አያስፈልግም! ዘር፥ ሀረግ፥ ትውልድ ነው የስልጣን መሰረቱ። የጨዋ ልጅ የተናቀው፥ ባህል የተበላሸው፥ አገር የተናጋው የፈረንጅ ትምህርት ድህው ቤት ከገባ ወዲህ ነው። ጃንሆይም ቢመከሩ ቢዘከሩ አልሰሙም። ይሄው ከጎናቸው አገኙት. . .

‹‹የድህ ልጅ ውለታ ያውቃል ብለው ነው? ድህ ምን ጊዜም የበላበትን ወጭት ከመስበር አይመለስም። ዋ እቴ! እንዳልካቸውን ለቀቅ። የጨዋ ልጅ ቢገድለኝ ይሻለኛል፥ የድህ ልጅ ከሚያኖረኝ›› ብለው ነገራቸውን ይዚጋሉ።

ወይዘሮ አምሳለ እንደ ተመኙት በየካቲት የቦነነው አብዋራ እየረጋ ነበር። በእሳቸው እምነት እድሜ ለእንዳልካቸው፥ የመሳፍንቱ፥ የመኩዋንንቱና የባላባቱ ልጅ ስልጣን ተቆናጦአል። ለኢትዮጵያ ህዝብ መሰረታዊ ችግሮች ሁሉ ፍቱን መድሀኒት ይሆናል ተብሎ ከፍተኛ ተስፋ የተጣለበት የአዲሱ ህገ መግስት መርቀቅ ስራ ተፋፍሞአል። ምሁራን ተመርጠው፥ በሶስቱ ስልጣናት መከፋፈልና መገናኘት ስራ፥ ሀያ አራት ሰአት ሙሉ ጭንቅላታቸውን እያዞሩ ናቸው።

አዲሱ ህገ መንግስት ከውጣ የኢትዮጵያ ችግር አበቃ! አርቃቂዎቹም፥ ‹‹የአዲሱ ህገ መንግስት አባቶች›› በመባል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ተገቢውን ስፍራቸውን አገኙ! ህዝቡም ጥያቄው ሁለ ስለተመለሰለት ተደስቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ! ሌላ ምን ያስፈልጋል! ፋታ ፋታ ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ደግነቱ ቴሌቪዥኑ፥ ራዲዮውና ጋዜጦች ነጋ ጠባ ይህንኑ ነበር የሚያስተጋቡት ፋታ! ጥረታቸው ውጤት አልባ አልሆነም። ወታደሩ ወደ ጦር ሰፈሩ ተመለሰ፤ በምተኩ የብሄራዊ ፀጥታ ኮሚሽን ተቁዋቁሞአል። ሰፊው ሰራተኛ ሰላማዊ ሰልፍ ሲያደርግ ያቦነነው አብዋራ አይኑ ውስጥ ገብቶ እያለቀሰ ወደ የስራው ተመልሶአል። ሰይቼንቶ ነጂዎች እየዞሩ ሳንቲም መቃረም ጀምረዋል። ተከምሮ የከረመው የአዲስ አበባ ቆሻሻም እየተጠረገ ነው።

የገዥው መደብ ችግር የሰፊው ህዝብ ብሶት ገንፍሎ መውጣት ሳይሆን ለጊዜው ተደናግጦ ከስልጣን የወረደው የአክሊሉ ካቢኔ ተመልሶ የስልጣን ርካብ ለመርገጥ፥ ከእንዳልካቸው ካቢኔ ጋር ውስጥ ውስጡን የሚያደርገው ሽኩቻ ብቻ ነው። ንጉሱ አሮጌውንና አዲሱን ካቢኔ በማጋጨት ተአምራዊ

የፖለቲካ ስራቸውን ቀጥለዋል። ለጊዜው ተንገዳግዶ የነበረው ዙፋን ለሚቀጥለው ሶስት ሽህ ዘመን ቀና ብሎ የሚቆምበትን መሰረት እየጠገነ ነው።። አለም ለክፉ አትሰጥም ነበር!

‹‹ሎሚ ተራ ተራ›› የተባለው ዘፈን ተወዳጅነትን እያገኘ ቢሄድም፥ ‹‹ጉብልየን››፤ ‹‹እረ እየድማሙን››፤ ‹‹አንተዬን›› ገና ሊተካ አልቻለም. . .

ዝም ብሎ መጋደሙ ስልችት አላት - ሂሩትን። ረፈድ ብሎ ስለ ነበረ መኝታዋም ወበቃት። ከአልጋዋ ለመውረድ ስለ ሰነፈች ዝም ብላ በጀርባዋ ተጋድማ ቀረች። ቀና ብላ የምታነበው መፅሀፍ አነሳች። ‹‹ፍቅር እስከ መቃብር›› ነበር። አንድ ጊዜ አንብባዋለች። እንደ ገና ልታነበው ፈልጋ ነበር። ማንበብ ጀመረች - የራስጌዋን መብራት አብርታ። አሳብዋ እየባከነ ስላስቸገራት ማንበቡን ለመቀጠል አልቻለችም። መፅሀፉን ወረወረችና ተነስታ ቴፕ - ሪኮርደርዋን ከፈተች። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር፥ ቴፕ-ሪኮርደሩ የባትሪ ድንጋይ የሌለው መሆኑ ትዝ ያላት።

ጥላው የተነሳችው መኝታ ገሃነም መስሎ ስለታያት ሄዳ የመኝታ ቤትዋን መስኮት ከፈተች። የጠዋትዋ ፀሀይ ብርሃን መኝታ ቤትዋን አጥለቀለቀው። ውብ ቀን ነበር. . .

ሰማዩ ኩል መስሎ ተንጣሎአል። አንድ ደመና ስለማይታበት ሰማዩ ከወትሮው ወደ ላይ የራቀ ይመስላል። ንፁህ ቀዝቃዛ አየር ይነፍስ ነበር። የተረበሸው መንፈስዋ በቀኑ ውበትም በቀዝቃዛው አየር ምክንያት ረጋ ማለት ቢጀምርም፥ ያደረባት ጭንቀት ሙሉ በሙሉ አልተለያትም።

‹‹ምን ነካኝ?›› አለች፥ ብስጭት ብላ።

የሆነችውን ልታውቅ አልቻለችም። ቀዝቃዛውን አየር ወደ ሳንባዋ እየላበች፥ ዝም ብላ በመስኮት ወደ ውጭ ትመለከት ነበር። ሁለት ርግቦች ሲጫሩ አየች።

ከነጋ ቁርስ አላገኘችም፡ የምግብ ፍላጎት አልነበራትም፡ ግን ለውነትዋ አንድ ነገር እንደሚፈልግ ይሰማት ነበር። በስስ የሌሊት ልብስዋ ውስጥ እንደ

የቀይ ኮከብ ጥሪ

በረሃ ሎሚ ጉች ጉች ብለው የሚታዩትን ጡቶችዋን እያሻሸች፥ ሄዳ ፊትዋ በመስተዋት ተመለከተች።

ጥቁር የሀር ነዶ የመሰለው ጠጉርዋ አሻፈረኝ ብሎ በየአቅጣጫው ተበትኖአል። ልትዳኘው አልሞከረችም። እንደዚያው ተወችውና ጡቶችዋን ይዛ እያሻሸ ከመስተዋቱ ፊት ቆማ፥ መወዛወዝ ጀመረች። ወገብዋን እንደ እባብ ጥምልምል፥ እጥፍ፥ ዘርጋ ሳብ፥ ኩምትር፥ እያደረገች ስትወዛወዝ ከቆየች በሁዋላ ሮጣ ሄዳ አልጋዋ ላይ በመዘርጋት ስትንከባለል፥ በእግርዋ የራስጌዋን መብራት ገመድ ስለነካች፥ መብራቱ ከኮሞዲኖው ላይ ወድቆ ክሽ አለ።

ደርቤ የመኝታ ክፍልዋን በር ቀስ ብሎ አንኩዋኩዋ። ጡቶችዋን እንደ ያዘች መንከባለልዋን አቁማ፥ ‹‹ማን ነው?›› አለች።

‹‹ደርቤ ነኝ›› አላት።

‹‹ምን ትፈልጋለህ?››

‹‹አንድ ነገር ወድቆ የተሰበረ መስሎኝ ነው›› አላትና፥ ወደ ስራው ተመለሰ።

ሂሩት የመኝታ ክፍልዋን በር ከፈተችና ግራና ቀኝ ካማተረች በሁዋላ ‹‹ምን ነው ቤቱ ጭር አለ?›› አለች።

‹‹ማንም የለም። እሜቴ ጠዋት የወጡ ናቸው። ጌቶችም ስራ ሄደዋል። ተሰማና የቤት ሰራተኞችም ዛሬ የሚደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ ለማየት ሄደዋል›› አላት።

‹‹የምን ሰልፍ!›› አለች።

‹‹የእስላሞች ሰላማዊ ሰልፍ›› አላት፡

‹‹የክርስቲያን ደሴት በሆነች አገር!›› ብላ ሳቀች።

ደርቤ መልስ አልሰጣትም። የቤት ፅዳት ስራውን ገፍ ብሎ ቀጠለ። ሂሩት ገፍ ብላ ስትመለከተው ከቆየች በሁዋላ፥ ድንገተኛ አላብ መጠነኛ ራስዋን ልትቆጣጠር አልቻለችም።

‹‹ግባና የተሰበረውን የራስጌ መብራት አንሳ!›› አለችው::

የቤት ፅዳት ስራውን እርግፍ አድርጎ ትቶ የታዘዘውን ለማድረግ ሰተት ብሎ ወደ መኝታ ክፍልዋ ገባ:: በሩን ቆለፈች:: ልቡ ስንጥቅ አለ:

መኝታ ቤትዋ በጠረንዋ እውድ ብሎ ነበር:: በሀይል ወደ ውስጥ ተንፍሶ ጠረንዋን ወደ ሳንባው እያስገባ፤ ወድቆ የተሰበረውን የራስጌ መብራት ለማንሳት ጎንበስ ሲል፥ ‹‹ስምህ ያስጠላኛል!›› አለችው::

ዝም አለ:: የልቡ ትርታ እንደ ከበሮ የሚጮህ ስለ መሰለው አፈረ::

‹‹እሱን ተወውና እየኝ!›› አለችው::

ስራውን ትቶ መለስ አለ:: አይን ለአይን ተጋጠሙ:: ደርቤ አይኑን ሰበር አደረገ::

‹‹ከእግሬ ምናለህ!›› አለችው::

አንገቱን አቀርቅሮ፥ ‹‹ደስ ይሉኛል:: እግርሽን ማጠብ ደስታ ይሰጠኛል›› አላት፥ ሰውነቱ እየተንቀጠቀጠ::

‹‹ደስታ የሚሰጥህ ከሆነ ሳመው›› አለችና የጠዋት ጫማዋን አውልቃ ጣለች:: የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ዝም ብሎ ቆመ::

‹‹ታዲያስ?›› አለች::

ሄዶ ጥምጥም አለባት::

‹‹ንከሰኝ! ንከሰኝ! ›› አለች፥ በስሜት እየቃተተች:: ነከሳት::

‹‹በሀይል! በሀይል! ›› አለችው፥›› ሲዘጋ በደረሰ ድምፅ:: በሀይል ነከሳት::

የንክሻው ስሜት የሰጣት ደስታ ስለ ተሰማት ሲቃ የተመላበት ሳቅ እየተንከተከተች፥ ‹‹ጡቶቼን በሀይል ጨብጣቸው! ጭምቅ አድርገኝ!›› አለችው::

ባለ በሌለ ጉልበቱ ጭምቅ አድርጎ ያዛት:: ህሊናውን ስቶ ከአልጋው ላይ ይዞአት ወደቀ. . .

ከስቃዩ ከሚሰማት ደስታ ብዛት እያለቀሰች ትስቅ ነበር። የተነከሰችው የተቡዋጨረችው ቦታ ሁሉ እየቆጠቆጣት ስትስቅ ስታለቅስ ከቆየች በሁዋ ከላይዋ ገፍትራው ተነስታ፥ ‹‹ይህ በኔና ባንተ መካከል የሚቀር ምስጢ ነው!›› አለችው፥ አውሬ መስላ።

ጣአት መስላ ታየችው። እንደ ሰከረ ሰው ሰማይና ምድር ዞሮበታል መጥፎ ቅዠት ይሁን እውን ለይቶ ለማወቅ ተስኖታል።

‹‹እሺ›› ብሎአት፥ ከሰውነቱ ጋር ተዋህዶ በቀረው ጠረንዋ ሰክረ እየተንገዳገደ ወጣ. . .

እግሩ ከበሩ ከመውጣቱ በፊት ነበር፥ ሂሩት ዳግመኛ ላታየው የቆረጠችው። እንደ ንግስት ንብ የተገናኛት ሁሉ መጥፋት ነበረበት። ከማንም ወንድ ጋር ለሁለተኛ ጊዜ አትተኛም። ዞር ብላ አታያቸውም። ቅ አይልዋትም።

እስዋ ሲፈልጋት መኪና ውስጥም ሆነ በየትም ቦታ የምትጋደምላቸው ወንዶች፥ እንደ ርካሽ ሴት እየቆጠርዋት ሌላ ጊዜ ሲፈልግዋት ልትመጣላቸው ቀርቶ ዞር ብላም አታያቸውም። ስማቸውንም እንኩዋን አታስታውስም ታዲያ እልክ ይገባሉ።

ወንዶች እልክ ገብተው ሲሰቃዩላት ስታይ ልዩ ደስታ ይሰጣታል ሰውነቱዋን የወንዶች ማሰቃያ መሳሪያ አድርጋ ነበር የምትመለከተው።

ደርቤን፥ ‹‹ንከሰኝ፥ በሀይል ንከሰኝ፥ ቡዋጭረኝ፥ ጭምቅ አድርገኝ እያለች፥ የራስዋን ሰውነት ለማሰቃየት ለምን እንደፈለገች አልገባትም። ነገ ግን፥ የተነከሰችው ቦታ ሁሉ ሲቆጠቁጣት ከዚህ በፊት የማታውቀው ልዩ ደስታ ይሰማት ነበር። አይኖችዋን ጨፍና ስቃይዋን ስታዳምጥ ቆየች እንቅልፍ ሸለብ አደረጋት፤ ስትነቃ አሳብዋ በአንድ ነገር ፀንቶ ነበር። ደርቤ ቤት ውስጥ ልየታው አልፈለገችም. .

ሳምንታት አልፈው ወራት ተተኩ። ሂሩት ፊት ስለ ነሳችው ደርቤ ዘወትር ይጨነቅ ነበር። እስዋን ማየቱ ነበር ጭንቀቱ። ባያት ቁጥር ይደነግጣል። ያለ ልማዱ ፈዞ ይቀራል። የነገሩትንም ይረሳል።

እሱ ፈዞ ቆመ የሚተኩሰው ሽሚዝ ተቃጥሎ ሲጠስ፥ ወይዘሮ አምሳለ ደርሰው፥ ‹‹ጉድ ፈላ ሰምች! ምን ነካህ አንተ!›› ብለው አስደነገጡት።

ሲያየው የሚተኩሰው ነጭ ሽሚዝ ተቃጥሎ ከስሎአል።

‹‹ጉድ ነው! ጉድ ነው!›› ብለው ሽሚዙን ተመለከቱና፥ ‹‹ብትሸጥም ዋጋውን ልትመልስ አትችልም›› አሉ ተቆጥተው።

‹‹ሳላውቀው ካውያው ግሎብኝ ነው›› አላቸው ዋሸቶ።

‹‹የለም፥ ይህን ሰሞን ልብህን የሰለበው ነገር አለ። ቢጠሩህ አትሰማም፥ ቢነግሩህ አይገባህም፥ ሲበሉ የላኩህ ይመስል ነገር ትረሳለህ። ጎረመስክና ልብህ አበጠ መሰለኝ! እከክክ! ከመቼ ወዲህ አንተ! የሰም፥ ልብህ ሸፍቷል. .

.

‹‹እኩልነት! ነፃነት ሲሉ ሰምተህ ነው መሰለኝ! ድንቄም እኩልነት እቴ! ቀጥ ብለህ ትሰራ እንደሆን ስራ! አለበለዚያ ከቤቴ ውጣልኝ!›› ብለውት ሄዱ።

ማታ ራት ላይ ለባላቸው ደርቤ ስላደረሰው ጥፋት ሲነግሩዋቸው፥ አቶ ጉልላት፥ ‹‹አምን ፈዞአል። ከአይን የሚቀድም ተፈ ነበር። ምን እንደነካው እግዜር ይወቅ›› ብለው ዝም አሉ።

ሂሩት ትጠብቀው የነበረውን እድል ስላገኘች፥ ‹‹ማታ ማታ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ እያለ የሚያመሸው ሌላ ቦታ ነው ሲሉ ሰምቻለሁ። ከቦዘኔዎች ጋር አፍ ለአፍ ገጥሞ ነው የሚያመሸው አሉ›› ብላ ዋሸታ ነገረቻቸው።

‹‹ለዚህ ነዋ!›› አሉ ወይዘሮ አምሳለ።

‹‹ምን ለመሆን ፈልጎ?›› አሉ፥ አቶ ጉልላት እየተገረሙ።

‹‹ምን መሆን ፈልጎ! ያልጠረጠረ ተመነጠረ አሉ ልጄ! ወመኔው ሁሉ ልቡ መቼ ተኖ! አምላክ የሰጠውን፥ ሰው ሊወስድ የሚችል ይመስል - ድሀው ሁሉ ጥርሱን እየነከሰብን ነው። እንዲያውም ትናንት በመንገድ ሳልፍ፥ በረንዳ አዳሪዎች፥ (የተነቃነቀ ጥርስ ካልተነቀሰ ጤና አይገኝም፥ ሲሉ ሰምቻለሁ። ባዳ ምጊዜም ባዳ ነው። ይልቅ ጉድ ሳያደርገን ከቤታችን እናባረው›› አሉ።

ሂሩት የእናትዋን አሳብ በመደገፍ ‹‹እማዬ ልክ ናት:: አልነገርኩዋች
እንጂ ባለፈው ሳምንት ምን አደረገ መሰላችሁ? ተፈራ ሲጠይቀን መ
‹‹ሲጃራ ግዛልኝ›› ቢለው ‹‹እኔ አሽከርህ አይደለሁም›› አለው:: ‹
ተወው›› ሲለው የተናገረው አልበቃ ብሎት ‹‹እኔ ካንተ አንሼ አንተ
በልጠህ የምንታይበት ምክንያት ምንድነው? አንተም ሰው እኔም ሰ
አንበላለጥም:: ሱፍ ብትቀያይርና መኪና ብትነዳ ዋጋ የለውም!›› ብ
ትከሻውን አሳይቶ ሄደ›› አለች::

ኧረ! ለዚህም ደረሰ? ልቡ አብጦአል ብያለሁ:: ነፃነት! እኩል
የሚባሉትን ነገሮች ከሰሙ ወዲህ የድሆች ልብ ተነሰቶአል:: ድህ በህል
ቅቤ ባይጠጣ አመዱ ይውጠው ነበር አሉ! የለም፥ ይህን መርዝ ከዚህ
ካልነቀልን አይሆንም›› አሉ ወይዘሮ አምሳለ::

እዚህ ላይ ሂሩት አልዋሸችም:: ፈጥራ አልነበረም የተናገረችው:: ደ
የተፈራን አይን ማየት አይወድም:: ከሂሩት ጋር ባየው ቁጥር አይኑ
ይለብሳል::

ሂሩት፥ ‹‹መቼ ይህ ብቻ ሆነና!›› ብላ፥ ‹‹በቀደም እለት ደግሞ በላ
ሲመጣ ከበር አባረረው:: ዱላም ቃጥቶት ነበር›› አለች::

‹‹ይህችን ይወዳል! የራስ ደስሜን ልጅ! በምን ምክንያት በይ!›› ‹
አባትዋ ተቆጥተው::

‹‹እኔ ምናውቃለሁ!›› ብላ አንገትዋን ወደ ቀኝ መታ አደረገች::

‹‹ያስር መናጢ ልጅ! እዚህ ምን አይነት ሰው እንደሚመጣ የት አ
ያውቃልና ነው! ጥሩልኝ! አሉ፥ አባትዋ በቁጣ::

ደርቤ ተጠርቶ መጥቶ ሁለት እጆቹን ወደ ሁዋላ በማጣመር አቶ
ቆመ::

‹‹በምን ምክንያት ነው በል ሰዎች ሲመጡ አላስገባም እ
የምታስቸግረው! ያባትህ ቤት መሰለህ! በል ተናገር እስ!›› አሉት::

ደርቤ መልስ ለመስጠት አልተዘጋጀም። ሰሌላ ጉዳይ የተጠራ መስሉት ነበር። የተለንመ ይመስል ዝም ብሎ ቆመ። ሂሩት ከእናትዋ ጋር ተነስታ ወጣች።

‹‹ደሞ የጥጋብህ ብዛት መልስ ለመስጠትም ትሳራለህ – እ›› አሉትና፥ ሁልጊዜ ለጌጥ ከግድግዳ ላይ ተሰቅሎ የሚኖረውን አኮርባጅ አውርደው ባለ በሌለ ጉልበታቸው ይወርዱበት ጀመር።

ደርቤ ከቆመበት አልተንቃነቀም። አይኑን ከጣራ ላይ ሰቅሎ ግርፋቱን በዝምታ ይቀበል ነበር።

አቶ ጉልላት ብለው፥ ብለው ሲደክማቸው፥ አይኑን ጣራ ላይ ለቅሎ ስላዩት፥ ‹‹እግዜር ይይልህ ማለትህ ነው?›› ብለው እንደ ገና ይወርዱበት ጀመር።

ደርቤ ከቆመበት ንቅንቅ ሳይል አይኑን ወለሉ ላይ ተክሎ ግርፋቱን ሲቀበል፥ ‹‹አንተ መናጢ! መሬት ግባ ማለትህ አይደለም?›› ብለው በመጨረሻ ሀይላቸው በመጠቀም ሲወርዱበት፥ ቀና ብሎ፥ ‹‹ጌታዬ ቅጣቱንስ ልቀበል! ለአይኔ ማረፊያ ይስጡኝ ብቻ!›› አላቸው።

አነጋገሩ ልባቸውን ሰለ ነካቸው ተውት።

ደርቤ በልቡ፥ ‹‹ነገሩ ነው እንጂ ጨቤ ሰው አይጎዳም!›› እያለ ሂሩትን እያሰበ ወጣ። በሚገረፍበት ጊዜ ሁሉ ሂሩትን ነበር የሚያስበው።

አሳቡን የሚካፈለው ሰው አልነበረም። እናት፥ አባት፥ የስጋ ዘመድ፥ ወይም የልብ ጉዋደኛ አልነበረውም። ብቻውን ስቃዩን መሸከም ነበረበት። ብቸኝነት ተሰማው። ሀይወት ባዶ ሆኖ ታየው።

‹‹አታናግረኝም፥ አታየኝም፥ የለሁም፥ ለሰዋ እኔ ሀልውና የለኝም፥ እቃ ነኝ፥ ቤት ውስጥ ካሉት እቃዎች ውስጥ አንዱ ነኝ። ለሰዋ! ይሄው ነው የኔ ሀልውና! በኔ ልብ ውስጥ ግን እሰዋ አለች። ያቺ ቀውጢ ቀን – እምቢ ብያት ብውጣ ኖሮ ዛሬ አይኔና ልቤ ታውሮ ሀይወት አይጨልምብኝም ነበር። ግን ምን ላደርግ እችላለሁ? ስቃዬን በቋሜ ከመቀበል በስተቀር! ይሄው ነው እንግዲህ የኔ እጣ፥ ራሴን ብገድልስ? ምን ይቀርብኛል በዚህ አለም?

ከአሽከርነትና ከስቃይ ከመገላገል ሌላ! እና ይዤያት ወደ መቃብር ብወርድስ? አንጀቴን እንዳላረረችው አንጀትዋን በጥሼ. .



‹‹ግሩም ነው ከሚወድዋት ጋር ተያይዞ ወደ መቃብር መውረድ›› እያለ በማሰብ ገድሎአት ለመሞት ሲቆርጥ ሲል፥ ‹‹የለም መጀመሪያ ሰው መሆኔን ማወቅ አለባት። አሳያታለሁ! ሰው የማይሆን የለም!›› ብሎ ጋደም በማለት፥ ለህይወቱ እቅድ ያወጣ ጀመር።

አስቀድሞ ጭንቅላቱ ውስጥ የገባ ነገር ቢኖር እግሩ ወደ ወሰደው አገር ኮብልሎ መጥፋት ነበር።

ደርቤ ስለ ህይወቱ እቅድ በሚያወጣበት ወቅት አቶ ጉልላት በጠባዩ መለውጥ እየተገረሙ፥ ‹‹ያሳደግነው ልጅ ነው። ዝም ብለን ከቤት እናስወጣው ነው የምትይው›› አሉዋቸው ባለቤታቸውን።

‹‹አባብ አንገትህ ላይ ጠምጥመህ ኑር፥ አንተ ከፈለግህ! እኔ ከዛሬ ወዲህ በቅቶኛል›› አሉ፥ ቆጣ ብለው።

‹‹ጨንቆኝ ነው. . .››

‹‹ስለገረፍከው አዘንክለት መሰለኝ! አዛኝ ቅቤ አንጉዋች ይላሉ። ድሀን ልክ ካላስገቡት የሰው ልክ አያውቅም። የሚያዝንላቸውን አይወዱም። አንተ አዲስ ሆኖብህ እንደሆን ነው እንጂ ዘሮቼ ሲገርፉ ነው የኖሩት ወዳጄ! ያኔ አገርም ሰላም ነበር›› አሉ፥ ባለቤታቸውን በንቀት እየተመለከቱ።

‹‹የምልሽ አልገባሽም። ከኛው ጋር ይኑር ማለቴ አይደለም። ግን ውስጠ አዋቂ ነው። ጊዜውም አያስተማምንም። ወታደሩ እንደ ገና ማጉረምረም ጀምሮአል አሉ። አገሪትዋ ጤና የላትም። በሰላም እንሸኘው ማለቴ ነው›› አሉዋቸውና ትራሳቸውን አመቻቹ።

‹‹ደብድበህ አባረው ማን አለህ!››

‹‹ሰው የሚልሽን አትሰሚም! መሳሪያ እንደ ደበቅን ያውቃል። በሁዋላ አደገኛ ሰው ሊሆን ይችላል፥ አስቀይመን ካባረርነው። ስራ እናስይዘው ነው የምልሽ. . .››

«ከቻልክ እኔ ምን ችገረኝ። ከቤቴ ይውጣልኝ ብቻ!» አሉና መብራቱን አጠፉ።

ደርቤ የሂሩትን አይን እያየ ጠዋት ማታ ከመሰቃየት ኮብልሎ በመጥፋት ቆርጦ ነበር ያደረው። ሰው ዘንድ ያኖረውን አንድ መቶ ሃያ ብር ለመውሰድና በዚያው ለመኖፋት ጠዋት በማለዳ ተነስቶ ወጣ። ሰውዬው ገንዘቡን አጥፍቶት ስለ ነበረ ሊሰጠው አልቻለም። ገንዘቡን ለማግኘት ሳይወድ በግድ አንድ ሳምንት መጠበቅ ስለነበረበት ተመልሶ ቤት ከመግባት ሌላ ምርጫ አልነበረውም። ግን እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሳምንት አልቆየም። በሶስት ቀን ውስጥ ነበር አቶ ጉልላት ወስደው በማስታወቂያና መርሀ ብሄር ሚኒስቴር ውስጥ ያስቀጠሩት. . .

ደርቤ በጊዜያዊ ሰራተኝነት መቀጠሩን ካወቀበት ሰአት ጀምሮ ኪራይ ቤት ሊፈልግ ነበር የቆየው። ወይዘሮ አምሳለ ኪራይ ቤት የሚፈልግ መሆኑን እያወቁ ምንም አላሉትም። ስራ ባገኘ በሁለተኛው ቀን መጥቶ ሲሰናበታቸው፥ «ምነነው ልጄ! ባንወልድህም አሳድገንሃል። ላልጠፉ ቤት በኪራይ ቤት መኖር ምን አስየዘመኑ ልጆች ለሁሉም ነገር ትቸኩላላችሁ» ካሉ በሁዋላ፥ በነገራቸው አምኖ አሳቡን እንዳይለውጥ በማለት፥ ቶሎ ብለው፥ «ብል መቼም እንደ ፈቀድከው ይሁን። እየመጣህ ጠይቀን። ቤትህ ነው» አሉትና አፋቸውን ጮማ አድርገው፥ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ፥ ቅር ሳይላቸው ሸኙት።

ደርቤ ሂሩትን ሳያገኝ ለመሄድ አልፈለገም። ከተሰማ ጋር እንባ ቀረሽ መለያየት ካደረገ በሁዋላ፥ «አገር ለቅቄ እሄድ ይመስል ይህ ሁሉ መርበትበትና ሀዘን ለምንድር ነው?» በማለት ራሱን ታዘበ። ከሂሩት ለመየት ግኑ ጭንቅ መስሎ ታየው። እስዋን ባሰበ ቁጥር ተለይቶአት ከመሄድ ከእስዋ ጋር አንድ ጣራ ስር እየኖርኩ የቁም ስቃይ መቀበል ይሻለኝ ይሆን? በማለት ልቡ ሲከዳው ቢከፎልም በመሄዱ ቆርጦ ስለነበረ፥ ወደ ሁዋላ ለማለት አልቻለም።

ከሀፃንነት ጀምሮ ካደገበት ቤት ወጥቶ ብቻውን ወደማያውቀው ሰፊ አለም የመግባት አሳብም ሳይከብደው አልቀረም። ሆዱን ባር ባር፥ ልቡን ፍርሃት ፍርሃት ይለው ነበር።

‹‹ቀውጢ ቀን!›› አለ፥ ከሂሩት ጋር የተጋደመባትን ጥቂት ደቂቃዎች ካንጀቱ እየረገመ።

‹‹ህይወቴን የለወጡ ጥቂት ደቂቃዎች›› ብሎ አሰበና፥ ያን ቀን ሞቺ ባረፍኩት ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስብኝም ነበር›› በማለት እድሉን ከፉኛ ካማረረ በሁዋላ፥ ‹‹ያ ጭንዋ ባይለክፈኝ! እግዜር ይይላት!›› ብሎ ተራገመ።

‹‹ባትለክፈኝ! እንዲሁ በልቤ እየወደድኩዋት ብኖር፤ ቀዝቃዛ ህልማዊ አለም ዛሬ እንደተሰበረ መስተዋት ደቆ ከፊቴ አይፈስም ነበር. . . ያንን ቀዝቃዛ ፍቅር ጊዜ በሻረው ነበር. . . አሁን ግን ዘለአለም የማይድን የልብ ቁስል. . . የጥቂት ደቂቃዎች ቅርስ›› እያለ ሲያስብ ቆይቶ፥ ሂዶ የመኝታ ቤትዋን በር አንኩዋኩዋ።

በሩ አልተዘጋም ነበር። ገብቶ ዝም ብሎ ቆመ። ከመፅሄት ውስጥ ቀዳ ያውጣችውን ባለቀለም ስእል ግድግዳ ላይ በጥንቃቄ ስትሰቅል አገኛት። አይኑ እንደ ሀረግ የሚላበውን ዳሌዋን ተከትሉ ወደ ስእሉ አመራ። የንብ ንግስት ስእል ነበር የምትሰቅለው። ስእሉ ደስ አላለውም። ምን ውበት አይታበት ይሆን? ብሎ ተገረመ።

የሚላት ነገር ጠፍቶት የቀትር መጋኛ እንደ መታው ሰው ፈዞ ቆሞ ቀረ።

ስእሉን ሰቅላ ጨርሳ በልዩ ስሜት ስትመለከተው ቆየችና ዞር ስትል ደርቤን በማየትዋ ደንግጣ፥ ‹‹በጣም አስደነገጥከኝ። ምን ትፈልጋለህ?›› ብላ በቁጣ ቃል ጠየቀችው።

‹‹ልሰናበትሽ ነው የመጣሁት፤ አሁን መሄዴ ነው›› አላት፥ ስልቱን ባጣ ድምፅ።

‹እሺ! መሄድህ ነው?›› አለች፥ ያለምንም ስሜት።

‹‹አዎን›› ብሎ መለሰላት።

‹‹ኦኬ፥ ቻው›› አለችውና ጀርባዋን ሰጠችው።



Scanned with CamScanner

ምእራፍ ፭

ደርቤ ከሂሩት በተለየበት ቀን በቁጭት ለራሱ የገባውን ቃል አላጠፈም። አንድ አላማ ብቻ ነበረው—አንድ ቀን ሰው መሆን!

አንድ ቀን ሰው መሆን ምን ማለት እንደሆነ ጠለቅ ብሎ በመመርመር ትርጉሙን ለማወቅ የሞከረበት ጊዜ የለም። ለሱ ትርጉም አንድ ነገር ብቻ ነበር የሂሩትን ልብ የሚማርክ፥ አይንዋን የሚስብ ሰው መሆን! አንድ ቀን ሰው የመሆን ትርጉሙ ለሱ ባጭሩ ይሄው ነበር።

ሰው ከመሆን ደረጃ ላይ የሚያደርሰው መሰላል ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። ባጭር ጊዜ ውስጥ እንደ ምንም ብሎ ከስልጣን ኮርቻ ላይ ለመውጣት ነበር ቆርጦ የተነሳው። እንደ ምንምብሎ አንዴ ስልጣን ከተቆናጠጠ ሀብትና ክብር አብረው ይመጣሉ-አስተሳሰቡ ቀጥ ብሎ በቀላሉ የታለመ ነበር። እና፥ ከዚህ ግብ ለመድረስ ምን ቢያደርግ ምንም ግድ አልነበረውም። የሂሩትን ልብ ድል ለመምታት የሚረዳ ነገር ከሆነ - ከፉም ሆነ ደግ - አይኑን ሳያሽ ከማድረግ እንደማይቆጠብ ህሊናውን አዘጋጅቶ ነበር፥ ወደ ስራ አለም የተሰማራው።

ስራ እንደ ጀመረ ቁጭ ብሎ እያንዳንዱን ቀን በምን ሁኔታ እንደሚያሳልፍ ዝርዝር መርሀ ግብር አወጣ።

ጠዋት ከአስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ እስከ ሁለት ሰአት ድረስ ጥናት። ከሰባት ሰአት ተኩል ጀምሮ እስከ ስምንት ተኩል ጥናት. . .ከአስራ ሁለት ሰአት ጀምሮ እስከ ሁለት ሰአት ከምሽቱ፥ የማታ ትምህርት መከታተል፥ ከሶስት ሰአት እስከ እኩለ ለሊት የቤት መሰናዶ ካለ መጨረስና የእለቱን ጥናት መፈፀም።

ባወጣው እቅድ ዝንፍ አላለም። እያንዳንድዋን ቀን የሚያሳልፈው ባወጣው መርሀ ግብር መሰረት ነበር። ከቤቱ ወደ ስራው፥ ከስራው ወደ ማታ ትምህርት ቤት - ይሄው ነበር ኑሮው። ለመደሰት ጊዜ አልነበረውም። የሚዝናናው ምግቡን በሚያዘጋጀበትና ሳምንት መጨረሻ ላይ ፍልውሃ ወርዶ በሚታጠብበት ጊዜ ብቻ ነበር።

ከአለታት አንድ ቀን የሚሰራበት መምሪያ የአስተዳደር ሹም ከቢሮው ደረስ አስጠራውና፥ ብልጣ ብልጥ አይናቹን እያቁለጨለጨበት፥ ያዝ ቦሚያደርገው ምላሱ ‹‹ሰራውን ተላመድከው ወይ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ምንም አልል ጌታዬ›› ብሎ መለሰለት፥ እንደ ማለፊያ አሽከር ሁለት እጆቹን ወደ ሁዋላ አጣምሮ እየተሽቆጠቆጠ።

የአስተዳደር ሹሙ ጠረጴዛ እንደ ባህር ተንጣሎ ታየው። የክፍሉን ጠርዝ እየታከከ የሚዞረው ቀይ ምንጣፍ አይን ያሞቃል። የአስተዳደር ሹሙ ተነስቶ ብቅ ጥልቅ እያለ ወደ መስኮቱ ተጠግቶ ወደ ውጭ እያየ፥ ‹‹አምን፥ ጎበዝ ሰራተኛ መሆንክን አውቃለሁ። ስራህ ላይ አቀረቅረህ ከመዋል ሌላ እንደ ሌሎቹ በውይይት ክበብ ስትደነፋም አላይህም። ከሰው ጋርም አትጉተምተም። ጥሩ ይዘሃል›› ካለው በሁዋላ፥ ‹‹ጊዜያዊ ሰራተኛ ነህ? አይደለም?›› አለው፥ ያዝ ያዝ ቦሚያደርገው አንደበቱ።

‹‹አምን ጌታዬ።››

ሹሙ ብቅ ጥልቅ እያለ ወደ ጠረጴዛው ተመልሶ ቁጭ ካለ በሁዋላ፥ ‹‹በቅርቡ ቋሚ ሰራተኛ ትሆናለህ። አመልህን ካላመርክ እድገትም አይጠፋም›› አለው።

አንድ እግሩ አንካሳ ነበር። ደርቤን ትኩር ብሎ በብልጣ ብልጥ ትናንሽ አይኖቹ አጠናና፥ ‹‹ወይዘሮ አምሳለ ዘመዴ ናቸው። አቶ ጌታቸውም ጉዋደኛዬ ነው። ስራ የገባኸውም በኔ ብርታት ነው›› ብሎት፥ በእጁ ጠረጴዛውን እየመታ፥ ‹‹ታዲያ የምትረዳኝ ነገር አለ›› አለውና፥ ፈገግ ብሎ ጥርሱን አሳየው።

‹‹ደስ እያለኝ›› አለው፥ አንገቱን ደፍቶ።

እንደ ዥን ከተቀመጠበት ተነስቶ ብቅ ጥልቅ እያለ ወደ መስኮት ሄዶ ደርባውን ሰጥቶት ከቆመ በሁዋላ፥ ‹‹አምን፥ በውይይት ክበባችሁ ውስጥ ማን ምን እንደሚለኝ እንድትነግረኝ ነው የምፈልገው›› አለው።

በቅርብ የሚያውቁት ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ፥ አንካሳ ሆኖ የቀረው ሲዋጋ ቆስሎ ሳይሆን፥ የለው ሚስት ሊያማግጥ ባል ደርሶበት ሲያባርረው

ባጥር ሲዘል ወድቆ ተሰብሮ ነው ይላሉ። ሳይሆን አይቀርም። ከቢሮው
ላይ ደም የላሰች ውሻ መስለው፥ ያለ ምንም ስራ ሹራብ እየ
የሚቀመጡትን ፀሀፊዎች ልዩ ሙያ፥ አንድ ሁለት ጊዜ ሳይፈትን የቀጠረ
ጊዜ የለም። እንደ ንብ ከዚህም ከዚያም መቅሰም ይወዳል . . .

ደርቤ እጅ ነስቶ ወጣ።

በጥቂት ወራት ውስጥ ቋሚ ሰራተኛ ሆነ። የደረጃ እድገትና የደመ
ጭማሪም አገኘ። በሰባት የትምህርት አይነት ፈተናውን በሚገባ አ
የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ምስክር ወረቀት ስላገኘ በአዲስ አበባ ዮኒቨር
ማታ ማታ ትምህርቱን ለመቀጠል ሂዶ ተመዘገበ። የምስክር ወረቀት አም
የሰው ልኩ የሚታወቀው በምስክር ወረቀት የሆነበት ሀብረተሰብ! ያለ
ማንም ሰው ላይ ሆን! እያለ ነበር ሂዶ የተመዘገበው።

ግን በፊፀመው ሁሉ ሙሉ ደስታ አይሰማውም ነበር።

የመምሪያውን ያስተዳደር ሹም ለማጋለጥና ለማባረር ሽንጣቸ
ገትረው ይታገሉ የነበሩት የውይይት ክበብ አባሎች አንድም ሳይቀሩ ም
ወደ ክፍላተ ሀገር ሲዛወሩ፥ የተቀሩት ደግሞ ከደረጃቸው ዝቅ ብለው እንዲ
ተደርገው ወደ ሌሎች መምሪያዎች መባረራቸውን እያስታወሰ ው
ውስጡን ሁልጊዜ ሰለሚከነክነው የመንፈስ እረፍት ያጣ ነበር። ቢሆ
የተነሳበትን አላማ የሚያስተው ጉዳይ ሆኖ አላገኘውም። ሂሩት ክ
አልጠፋችም።

አሮጌው ስርአት ፈርሶ አዲሱ ስርአት በመገንባት ላይ ባለበት ወቅት
ቆሞ ማንን ይጠብቃል? የስልጣን ጉጉት ላላቸው ሁሉ በሩ ክፍት ሆኖ
የሻሞ ጊዜ ነው! ለግል ጥቅሙ የቆመው ሁሉ ምን ሊያደርግ
የሚውለው? አሰፍስፎ የተሰለፈው ለጥቅሙ ነው - ያለውን ሽሞ
መቀራመት። የወደቀ ፓምብ ዙሪያ እንደ ጅፌ አሞራ እያንጎበበ፥ እ
የቻለውን ያህል መቦጨቅ አይደል አላማቸው? የበይ ተመልካች ሆኖ
የሚያይ ካለ፥ እሱ አንድ ቀን ሰው ለመሆን የማይፈልግ ደካማ ነው . . .

ጊዜው ደግሞ ለደካሞች አመቺ አይደለም። ጊዜው ሲከፋ፥ ወደ
መግፋት የሚችሉ ብርቱዎች ብቻ ናቸው ይባል የለ! አሮጌው ስርአት

ጥምብ ወድቆ ማን ቆሞ ሊጠብቅ? የሀሊና ልቅሶ ቦታ የለውም። የማን ሀሊና ሊያለቅስ አየንና! በተራማጅ ቃላት ተሸፋፍኖ ይቅረብ እንጂ በመሰረቱ አብዛኛው የሚታገለው ለጥቅሙ ነው - ለስልጣን፥ ለአድገት፥ ለደመወዝ ጭማሪ። ጥምብ ወድቆ የለ! እንደ ጆፌ አሞራ ጠንካራው ደካማውን እየገፋ ለመቀጨት። በውይይት ከበቦች አካባቢ የሚታየው ስነ-ልቡናዊ ክስተት ይሄው ነው። ጠንካሮች ይናራሉ፥ ደካሞች ይወድቃሉ። ታዲያ እኔን ምን አስጨነቀኝ፥ በማለት ለድርጊቱ የሚያፅናና ምክንያት ለመፍጠር መሞከር ከጀመረ ውሉ ቢያድርም፥ ራሱን ሙሉ በሙሉ ለማሳመን እያቃተው ይቸገር ነበር።

አንድ አርብ ቀን፥ ከሰአት በሁዋላ - ቢሮው ሲገባ፥ ከሱ ቢሮ ለጥቃ የምትሰራው ፀሐፊ ሰአትዋን አየችና፥ ‹‹እንድ ደቂቃ ወደ ፊት ወይም ወደ ሁዋላ ዝንፍ አትልም። ሰአቴን የማስተካክለው ባንተ ሆኖአል›› አለችው፥ እየተቅለሰለሰች።

ሰላምታ ከመለዋወጥ ሌላ ተነጋግረው አያውቁም። ከነገርዋ ትዝ የሚለው ሽቶዋና ልብ ወለድ መፅሀፍ አዘውትራ የማንበብ ልምድዋ ነበር። በተለይም፥ የምትቀባው ሽቶ ክፍሉን እውድ ያደርጋል፡

ሰአቱን ተመለከተ። ለዘጠኝ ሩብ ጉዳይ ሆኖአል። ሁኔታውን በመከታተልዋ እየተገረመ፥ ‹‹ልማድ ሆኖብኝ ነው መሰለኝ›› አላት፥ የተሻለ መልስ ሊሰጣት ባለመቻሉ ቅር እያለው።

ማስቲካ እያኘከች መፅሀፍ ታነብ ነበር። የምታመነዥክ ፍየል መስላ ታየችው።

መስቲካዋን ቀጭ ቀጭ ቀጭ አደረገችና፥ ‹‹እንደማይህ መካኒካዊ ህይወት ነው የምትኖረው›› ብላው፥ የከንፈር ቀለምዋን ላሰችና፥ ‹‹ዛሬ ይዘገይ ይሆን? ወይስ ቀደም ብሎ ይመጣ ይሆን? እያልኩ ሁልጊዜ ከራሴ ጋር እወራረዳለሁ›› አለችው።

ቤትዋ በጣም ሩቅ ስለሆነ ለምሳ አትሄድም። ከፀሀፊ ደመወዝ ግማሹን ለሊያቺንቶ ላለማስረከብ ስትል ነበር ቢሮ ተጎልታ የምትውለው። የምታነበውን መፅሀፍ አጥፋ ማስቲካዋን ቀጭ ቀጭ አደረገችና፥ ፍንጭትዋን እያሳየችው፥ ‹‹ታዲያ ይሄውልህ፥ ስለ ጊዜም ማሰብ የጀመርኩ ባንተ ምክንያት

ነው። ጊዜ ያለ ነገር ነው። ስለ ጊዜ ማን ያስባል? እኔ ግን፥ ለካ የሰው ልጅ የጊዜ እስረኛ ነው ብዬ አሰብኩ። አይገርምህም? የሰው ልጅ በሙሉ የጊዜ እስረኛ መሆሉ ታየኝ። የጊዜ ባሮች ነን፥ አይደለንም ሁላችንም? ጊዜን ለመቆጣጠር የምንችል ይመስለናል። ግን እውነት ነው? አይደለም። ጊዜ ነው በሰው ልጅ ላይ ወላኝ ቁጥጥር ያለው። እና ሁላችንም የምናገለግለው ጊዜን ነው!›› አለች።

ደርቤ፥ ጊዜን ከዚህ አንፃር ተመልክቶ አያውቅም። ለሱ፥ ጊዜ፥ ነው የሚሆንበት ቀን ነው፤ ሌላ ትርጉም አይሰጠውም።

ዘንፋላ ጥቁር ጠጉርዋ ፊቱን አስታወሰው።

‹‹ለኔ ጊዜ መሳሪያ ነው። እንጠቀምበታለን ወይም እንጠቀምበት። እያንዳንዳችን ለጊዜ የምንሰጠው ትርጉም እንደ አመለካከታችን ይለያያል አላት።

‹‹እኔ ግን የጊዜ እስረኛ ነኝ ብዬ ነው የማምነው›› አለችና ፍንጭትዋን ብልጭ አደረገች።

ጠይምነትዋ ወደ ጥቁረት ያደላል። ፊትዋን ፈገግ ያደረገው የለበሰችው ነጭ ሹራብ ሳይሆን አይቀርም ብሉ ገመተ። አንገትዋ በጣም ረጅም መሆኑ ታየው። የጆሮዋንና ያንገትዋን ጌጣጌጦች ስለወደደ፥ ጥሩ ምርጫ አላት ብሉ ገመተ። ሰላነጋገረችው አቀረባት። እምነትም አደረበት። ለምን አልጠይቃትም ብሉ አሰበና ሲያቅማማ ከቆየ በሁዋላ፥ ‹‹አንድ ነገር ብጠይቅሽ እሺ ትይኛለሽ?›› አላት።

አቀርቅራ ዝም ብላ ቀረች። ዝምታ በመካከላቸው ሰፈነ። ሰው ሁሉ በጊዜ ሰንሰለት የፍጥኝ ታስሮ፥ የጊዜ እስረኛ ሆኖ ተሰልፎ በፊትዋ ሲያልፍ ታያት ልብዋ ትር ትር እያለ የምትሰጠውን መልስ ነበር የምታሰላስለው።

ምን የጠየኩዋት መስሉአት ይሆን ዝም ያለችው? ብሉ በማሰብ ‹‹ማለቴ፥ አንድ የምታጋርኝ እቃ አለ። ትረዲኝ እንደሆን በማለት ነው አላት።

በሳቅ ተንከተከተችና፥ ‹‹ለሴት ነው!›› አለችው።

ላያስበው፥ ‹‹ለእህቴ ነው። ስራ ከገባሁ ሰጦታ አብርክቼላት አላውቅም›› አላት።

ፍናት አልተጠራጠረችውም። ከሁሉም ይበልጥ የጊዜ ምርኮኛ መሆኑ ስለ ታያት አዘነችለት። ለቅዳሜ ቀጠሮ ሰጠችው። እንደ ገመተው ውድ እቃ ብትወድም፥ ምርጫዋ ግሩም ነበር።

መቼ በነጋ እያለ አድሮ፥ ፍናት ያጋዛችውን የወርቅ አምባር ይዞ በጠዋት ተነስቶ ሄደ። ሲደርስ ወይዘሮ አምሳለና ባለቤታቸው መንገድ ጀምረው ነበር። ተቻኩለው ነበሩና ከሰላምታ ሌላ ሊያነጋግሩት አልቻሉም። ደርቤ እጅ ነስቶ እንደ ቆመ፥ ወይዘሮ አምሳለ አለባበሱን አይተው፥ ‹‹የሰው ልጅ መሰልክ አይደል እንዴ!›› አሉት።

አዲስ ጥቁር ሱፍ ልብሱ ውሃ ሰማያዊ ሸሚዝ ከቀይ ክራባት ጋር ሰብሶ አሸብርቆአል። ጠጉሩንም ግሩም አድርጎ ተስተካክሎአል። ቆዳው ወደ ቅላት አድልቶአል።

ወይዘሮ አምሳለ ምን ለማለት እንደ ፈለጉ በትክክል ባይገባውም፥ ያሉት አጥንቱ ድረስ ዘልቆ ተሰማው።

ተሰማ ቤት አልነበረም። ያ ሁልጊዜ ሳል የሚያስቸግረው የድሮ ዘበኛ፥ እየሳለ፥ ተሰማ አለመኖሩን ከበር ላይ ነግሮታል። ተሰማ ጣፋጭ ቡጣም ሰለሚወድ ብዙ ‹‹ኬክ›› ይዛለት ነበር የመጣው። ተሰማ ጣፋጭ በልቶ አይጠግብም፡ ቅዋቅ እስኪለው ድረስ ሊያበላው አስቦ ነበር።

ደርቤ ኪሱ ውስጥ ያለው አምባር በልዩ ስሜት እየዳበሰ ወደ ቤት ገባ። ገረድዋ አዲስ ስለ ነበረች አላወቀችውም። ወይዘሮ አምሳለ ሲያነጋግሩት አይታ ስለ ነበረ በአክብሮት እጅ ነስታው ወደ ሳሉን አስገባችው። እጀ ሰባራ ያደርጉት የነበሩ አሮጌ ሶፋዎች የሉም። እንግዳ ቤቱ በአዲስ የቤት እቃዎችና ምንጣፍ ከመጠን በላይ አጊጦአል። በአሜቴ ሹል ታኮ ጫማ፥ ፈንጣጣ እንደ በላው ፊት የተጠቀጠቀው ጣውላ መልኩን አልለወጠም። እንደ በፊቱ ነበር። ጉልበቴን የበላ ጣውላ የሚል አሳብ መጣበት።

ያ የተገረፈበት አኮርባጅና ቤት በሚያፀዳበት ጊዜ ሁሉ እየወደ የሚያስቸግረው ባለ ሰገባ ጎራዴ እዚያው ግድግዳ ላይ እንደተሰቀሉ ነበሩ::

‹‹ሻይ ወይም ቡና?›› ስትለው ገረዲቱ፥ ስለ ሳሎኑ ያለውን ትዝታ አቁዋረጠና የጠየቀችውን ትቶ፥ ‹‹ሂሩትን ነበር የምፈልገው›› አላት::

ገረዲቱ በልብዋ፥ ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል. . . እስዋ ፈላጊዋ ብዙ እንደ ጳጉሜ ውሻ. . . ኤጭ. . . ግን ምን ብታቀምሳቸው ይሆን? ጠዋት ማታ እየመጡ ሂሩት. . .ሂሩት የሚሉኝ! እያለች በልብዋ ስትመናጨ ወጣች. . .

ሙዚቃ ይሰማዋል:: ከሂሩት መኝታ ቤት ይሆናል ብሎ አሰበ:: ያ የንብ ንግስት ስእል ትዝ አለው:: ሂሩት ብቅ አለች:: ከዳሌዋ ሰፋ፥ ከወገብዋ ሸንቀጥ፥ ከደረትዋ ኮራ ብላለች:: የንብ ንግስት መስላ ታየችው::

በመጀመሪያ ማን እንደሆነ አላወቀችውም:: በስዋ አይን ምንም ህልውና የሌለው መናፍስት እንደ ሆነ ያህል ሆኖ ነበር የተሰማው:: ማራኪ ውበትዋ ትዝ አለው:: ላንዳፍታ፥ ‹‹ንከሰኝ. . .ጭምቅ አድርገኝ . . .›› ያለችው ጆሮው ውስጥ ደወለ:: ግን ፈፅሞ የማታውቀው መስላ ፊቱ ቆማለች:: ግራ ገባው.

.

ከረጅም ዝምታ በሁዋላ ነበር፥ ‹‹ደርቤ ነህ እንዴ?›› በማለት ከገባበት የጭንቀት ማጥ ያወጣችው::

ረጅም መንገድ ተጉዞ የተመለሰ ያህል ሆኖ ነበር የተሰማው:: ለዚያ ጥቂት ሴኮንድ በመኳከላቸው የተፈጠረው ርቀት የማይለካ ነበር::

‹‹ሂሩት፥ ልጠይቅሽ ነው የመጣሁት!›› ካላት በሁዋላ፥ ትኩረትዋን ወደ በይበልጥ ለመሳብ ተቻኩሎ፥ ‹‹ተዳፈርክ ባትይኝ፥ ስጦታ ብጤ አምጥቼልሻለሁ›› አላትና ፥ አምባሩን ከኪሱ አውጥቶ ሰጣት::

ስሜት አልሰጣትም:: አምባሩ ያለበትን ትንሽ ሳጥን ከፍታ፥ ምን አይነ ስጦታ እንዳመጣላት ለማየት እንክዋን አልፈለገችም::

‹‹ምን አሳሰበህ›› ብላ ዝም አለች::

እወድሻለሁ. . . ያላንቺ ህይወት የለኝም. . . ሰው መሆንም አልችልም. . . ብዬ ልንገራት ይሆን? ስቃዬ ገብቶአት ልብዋ ይራራልኝ ይሆን? እያለ ተጨንቆ ሲያቅማማ ሁለት ወጣት ወንዶች ከጉዋዳ ብቅ አሉ።

ሁለቱም ክምር ፅሁፎች ተሸክመዋል። የፅሁፎቹ አርእስት በትላልቅ ፊደሎች በቀይ ቀለም የተፃፈ ስለ ነበረ ከሩቅ ይነበባል።

‹‹ዲሞክራሲያ›› ይል ነበር።

ከሂሩት በስተቀር ሌላ ሰው በቤቱ ውስጥ ይኖራል ብለው አልገመቱም። ደርቤን ሲያዩት በጣም ደነገጡ። ከሁለቱ አንደኛው ከድንጋጤው የተነሳ ሲርበተበት ፅሁፉ ከእጁ አምልጦ ወለሉ ላይ በመበተኑ አርእስቱ በይበልጥ ጎልቶ ይታይ ነበር። የተበተነበትን ፅሁፍ ለመሰብሰብ ሲርበተበት አዳልጦት ወደቀ።

ወጣቶቹ ቢደነግጡም ስሜት አልሰጠውም። አሳቡ ሌላ ቦታ ነበር።

ሂሩት ሰአትዋን ተመለከተችና ያለ ምንም ስሜት ወይም ማመንታት፥ ‹‹ደህና ሁን-ቻዎ!›› ከሁለቱ ወጣቶች ጋር ውልቅ አለች።

ያን ቀን ደርቤ ጤነኛ ሆኖ አልዋለም።

ወይዘሮ አምሳለ፥ ‹‹የሰው ልጅ መሰልክ አይደለም እንዴ!›› ያሉት ትዝ እያለው፥ ‹‹አዎን መልኬ እንጂ ሰው አልሆንኩም፥ አሽከር ምን ጊዜም አሽከር ነው - ሰው ሊሆን አይችልም! ገረድ ገረድ ናት፥ ጭሰኛም ጭሰኛ ነው - ሰዎች አይደሉም! በነሱ ቤት ሰው ማን ነው?. . .

‹‹ደግሞ የስዋ ይባስ! ስጦታዬን እንኩዋን አይታው ብታስደስተኝ ምን ነበረበት! ምን ይጎዳታል ጥሩ ነው ብትለኝ! ‹‹ምን አሳሰበህ›› ትበለኝ! ሌላ የማስበው ምን ነገር አለኝና ካለስዋ በስተቀር! ሌላ ምን ህይወት አለኝ!

‹‹ከህፃንነቴ ጀምሬ ምን ሳሱቡ፥ ምን ስመኝ ኖርኩና ነው ‹‹ምን አሳሰበህ›› የምትለኝ። ህልም ሆኖ በቀረ ኑሮ-የህፃንነቴ ህልም! ግን ለከፈችኝ። ይልከፋትና! ለክፋኝ ስታበቃ በአይንዋ እኔን ለማየት ልትፀየፈኝ!. . . እንደሌለሁ ልትቆጥረኝ!. . .ውሻ ልታደርገኝ. . .ከድሮ ጀምሮ ‹‹ወንድ ውሻ

ነው›› ስትል አልነበረም?. . . አዎን. . . አረጋገጥኩላት አይደለም?. . . ወ
ነኝ! እኔ ሰው አይደለሁም›› እያለ ነበር፥ ፀሀያማና ነፋሻ በሆነ ቀን፥ የሰ
ሁኔታ በየሰአቱ እንደሚለዋወጥ ሁሉ፥ ፊቱ በማይዛመዱ ጥላዎ
እየተዥጎረጎረ በብሩህ ተስሎ የጀመረው ቀን ጨልሞበት የዋለው...

‹‹የሰው ልጅ የእለትዋ ጀምበር ከምትወስንለት እድል ውጭ ሌላ ም
ህልውና አለው? ፍኖት እንዳለችው ሁሉም የጊዜ እስረኛ ነው! ግን ፍኖ
ምን አይነትዋ ገደብስ ኖራለች!›› እያለ ብቻውን እያወራ ሲሄድ ሁኔታውን
አለባበሱን የተመለከቱ መንገደኞች፥ የገጠር መሬትና ትርፍ ቤ
የተወሰደባቸው ቤተሰብ ልጅ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት ሳይወስዱ
አልቀሩም::

ወደቤቱ አልሄደም:: በቀጥታ ወደ ቡና ቤት ነበር ያመራው::

ህፃን ልጅ ተንጠራርቶ የማይደርስበት ቁምጣ ቀሚስ የለበሰች የቡና ቤ
አሻሻጭ ውስኪ እየደጋገመ ሲጨልጥ አይታ፥ ጎኑ ሻጥ አለችና፥ ‹‹ጀማሪ ነ
መሰለኝ!›› ብላው እንደ ቁብ ዶሮ አስካካች::

ጎኑ ሻጥ በማለትዋ አልከፋውም:: ‹‹በምን ተከሰተልሽ?›› አላት::

‹‹ከልምድ!›› አለችና እንደ ገና አስካክታ፥ ‹‹ምን ልውሰድ?›› ብ
ጠየቀችው::

‹‹የፈለግሺውን!›› አላትና፥ ውስኪን አንስቶ ባንድ ትንፋሽ ጨለጠ:: ትን
አንቆ ሊገድለው ነበር::

አሻሻጭዋ ውስኪዋን ከያዘች በሁዋላ አለባበሱን አይታ፥ ‹‹መጠጣት ነ
ከእንግዲህ ገንዘብ ለምናባቱ! መሬት፥ ቤት፥ ንብረት እያሉ ገንዘብ ማጠራቀ
እንደሆነ ቀርቶአል:: እንደ ልብ መብላት መጠጣት፥ ማጌጥ - የነገውን እግዜ
ያውቃል›› በማለት እንደ መትረየስ ተንጣጥታ፥ እንደ ገና አስካካችና፥ ‹‹ትናን
ለሳንቲም ይስገበገቡ የነበሩት ባለርስቶች፥ ቤት አከራዮችና ነጋዴዎች ዛ
የመቶ ብር ኖት ሲመነዝሩ አይናቸውን አያሹም! ውስኪ በመለኪያ ገዝተ
መጠጣት ትተዋል:: ጠርሙሱን ነው የሚያወርዱት:: ለምኑ ብለው. . .

‹‹መቸ በውስኪ ብቻ። ኧረ ኤዲያ! አዲስ የቤት እቃ ያልገዛ! አዲስ መኪና ያልለወጠ ማን አለ ብለህ! ድሮ ለነፉ ቀን ይሆንናል ብለው ያጠራቀሙትን ገንዘብ እያወጡ መመንዘር ነው!›› አለችው።

አመጣጡ ይልቅ መንጭጣትዋ አስከረው። ምላሱን እየገመደ፥ ‹‹ከእንግዲህ ደግ ቀን አይመጣም ብለው ነው!›› አላት።

‹‹ነገ የሚሆነውን ማን ያውቃል? ደግ ያፓኑ እለት ነው›› ብላ፥ የቡና ቤቱን ቦይ ጠርታ ውስኪ እንዲደግማት አዘዘችው።

‹‹ብሩህ ቀን፥ በተስፋ ያጌጠ ቀን መምጣት አለበት። ሰው ያለ ተስፋ አይኖርም። ለዚህ ነው ነገ የሚባል ነገር ያለው›› አላት፥ በግማሽ ልብ።

የተናገራቸው ቃላት ከመጠጡ ጋር ተደባልቀው ልቡን ሞቅ ቢያደርጉትም ሙሉ በሙሉ አላመነባቸውም። መጭው ቀን የብሩህ ተስፋ አብሳሪ ይሆን ዘንድ ምን ማድረግ እንደሚገባው ስላልተከሰተለት የተናገራቸው ቃላት ላንዳፍታ ፍሙው ሲከስሙ ተሰማው።

ሁኔታውን ስታጤን ቆየችና ከመሬት ተነስታ፥ ‹‹የፍቅርም ጀማሪ ነህ መሰለኝ!›› አለችውና፥ ‹‹በምን ተከሰተልሽ አትበለኝ። ወንዶች የሚያብላላቸውን ነገር ማወቅ ለሴቶች ቅላል ነው። እንዲያው ይገለፅልናል። ደግሞም ብዙ ልምድ አለኝ። ስንቱ መሰለህ እዚህ ችግሩን ይዞ የሚመጣው! አይ ፍቅር. . .›› ብላ ለመዝፈን ቃጣችና፥ ‹‹ፍቅር ያዘኝ ብለህ አትበል ደንበር ጉተር፥ እኛም አንድ ሰሞን እንዲህ አርጎን ነበር›› ብላ አሾክካች።

ቁስሉን ስለ ነካችበት ተናደ ከመንጭጣትዋ ማስካካትዋ ብሎ ለመሄድ ተነሳ። ብዙ ከመናገር ብዙ ብጠጣ ምን ነበረበት! በሰፈሰፋበት አፍ ይጠፋበት ብላ ሱሪውን ላታስወልቀው በመቅረትዋ እጅግ አድርጎ ቆጨት።

የደርቤ እግር እንደ ምላሱ ተሳስሮ ነበር። ቤቱ ሲደርስ በመጀመርያ የታየው ግድግዳ ላይ ያለው የፊት መስተዋት ነበር። ጠጋ ብሎ ፊቱን በመስተዋቱ ውስጥ ተመለከተ። ድነገት ብልጭ ስላለበት መስተዋቱን በቡጢ አለው። መስተዋቱ አንኳሽኳሽ ብሎ መሬት ላይ አልፈለሰም። ፍርክስክሱ አለው። መስተዋቱ አንኳሽኳሽ ብሎ መሬት ላይ አልፈለሰም። ፍርክስክሱ ወጥቶ ይታይ ነበር። የውስጡ ፍርክስክስነት ነፀብራቅ መሰሉ ታየው።

እንቅልፍ እምቢ አለው። አይኑን በከደነ ቁጥር ምድርና ሰማይ ይገለባበጥበታል። የተኛበትም አልጋ መሬት ለቆ ይንሳፈፋል። በሀይል ቢያፈጥም አልሆነለትም። መጠጡ ልቡ ላይ እየፈላ መጥቶ በድንገት እንደ እሳተ ጎሞራ ፈነዳ. . .

ሲፈራ ሲቸር አይኑን ከደነ። እንቅልፍ ወሰደው። ጠዋት ሲነቃ ራስ ምታት ይዞ ይወቅረው ነበር። አንጎሉ ከራስ ቅሉ የተላቀቀ ይመስል ቁጭ ጎንበስ ባለ ቁጥር ጭንቅላቱ ይንቦጫቦጭ ነበር። የአጅ ቁስል ቆጠቆጠው። አዲስ መስተዋት መግዛት አለብኝ ብሎ አሰበ. . .

ቢሮው ሲደርስ፥ ፍናት በአይንዋና፥ በቅንድብዋም ጭምር እየተናገረች ‹‹ምን ነው ዘገየህ ልጄ! የሞትክ መስሎኝ ነበር›› አለችው - በስሜት።

‹‹መካኒካዊ ህይወት ነው የምትኖረው›› ያለችውን እያስታወሱ ‹‹መኪናው አንዳንዴ ይቆማል›› አላት።

‹‹በዋድባም አንዳንዴ ይዘፈናል፥ ብትል ይሻል ነበር›› አለችና፥ ‹‹እህትህ አምባሩን ወደደችው?›› ብላ ጠየቀችው። ስታነብ የነበረውን መፅሀፍ ቀዋ አድርጋ።

ልብ ወለድ መፅሀፍ ከጠረጴዛዋ ላይ አይጠፋም። ሹራብ በማትሰራበት ጊዜ ሁሉ መፅሀፍ ማንበብ እንደምታዘወትር ያወቀው ካነጋገረችው ጊዜ ወዲህ ነበር።

በመስኮት ወደ ውጭ እያየ፥ ‹‹በጣም ነው ደስ ያላት›› አለ የሱ ባልሆ ድምፅ።

ፊቱ ላይ የሚመላለሰውን ያልተዛመደ ጥላ አይታ ፍንጭትዋን ዘ አደረገችና፥ ‹‹ታዲያ ለምን ከፋህ?›› አለችው።

ደርቤ ትናንት የለበሰውን ልብስ አልቀየረም። ሆኖም ልብሱና ሰማ ላልተጣጣሙላትም። አምባሩን የገዛው ለእህቱ እንዲልሆነ ተጠራጠረች።

የቀይ ...

‹‹የከፋኝ እመስላለሁ?›› አላት፥ ወደ ውስጥ ጠልቀው የማየት ችሎታ ያላቸው የሚመስሉትን እንቁ መሳይ ብልጣ ብልጥ ትናንሽ አይኖችዋን እየሸሸ::

ፍኖት፥ አንድ አመል ነበራት:: የጀመረችውን መፅሀፍ ሳትጨርስ መተው አትወድም:: የታሪኩን መጨረሻ ሳታውቅ ስትቀር ያበሳጫታል:: መፅሀፍ ማንበብ ስትጀምር የታሪኩ ፍፃሜ ምን እንደሆነ ለማወቅ ትቸኩላለች:: ያንድ ልብ - ወለድ ውበት ከታሪኩ አፈፃፀም ላይ ነው ብላ ስለምታምንና ፍፃሜውን ለማወቅ ስለምትቸኩል፥ ስለ መፅሀፉ ይዘትና አላማ እምብዛም ግድ አልነበራትም::

ምስጢሩን ለማወቅ ፈልጋ ልብዋ ቆመ:: ደርቤም ምስጢራዊ ሆነባት:: አምባሩ ለእህቱ ከሆነ ለምን ከፋው? ካልሆነስ ለማን ነበር የገዛው? ማን አባትዋ ናት የኔን ምርጫ የምትንቀው? ወይስ ማን አጋዛህ ብላ ስትጠይቀው በሞኝነት ነግሮአት ቀንታ ይሆን ያስቀየመችው? ታሪኩ ጣፈጣት:: የመጨረሻውን ለማወቅ ፈለገች::

በአይንዋ፥ በቅንድብዋ፥ በእጆችዋም ጭምር እየተናገረች፥ ‹‹ከእህትህ ጋር ኮከባችን ሳይገጥም ቀርቶ፥ ምርጫዬ ሳያስደስታት ቀረ መሰለኝ!›› አለችው - እያሾፈች::

ሂሩት፥ ‹‹ምን አሳሰበህ›› ያለችውን በማስታወስ ውስጥ ውስጡን እየበሸቀና በፍኖት ገደ-ቢስነት እየተናደደ፥ ‹‹በምርጫው በጣም ነው የተደሰተችው›› አላት፥ ቃላቱን እያኘከ::

የታሪኩ ፍፃሜ ምን እንደሚሆን ሳይገልፅ አንባቢን እየሳበ እንደሚሄድ ልብ - ወለድ አድርጋ አነበበችው:: አንዳንድ መፃህፍት ሲያስለችዋት ብዙ ምእራፎች ዘላ የመጨረሻውን ምእራፍ እንደምታነብ ሁሉ፥ የእውነቱን እንዲነግራት ፈልጋ፥ ‹‹እውነት እስዋ ማን ናት?›› ብላ ልትጠይቀው ነበር::

ላስቸክዋይ ጉዲይ ትፈለጋለህ ተብሎ ተጠርቶ ሄደ:: ታሪኩ ተንጠልጥሎ ስለቀረባት ተናዳ ጥርስዋን ነከሰች::

የአስተዳደር ሹም ጤነኛ ሆኖ አልጠበቀውም። ደርቤ ሲደርስ እሳት ለብሰ ጠረጴዛውን ይቡዋጥጥ ነበር። የሚተሳሰረው ምላሱ የባሰውኑ ተሳስሮ፣ ‹‹ስሞኑን ለምን ጠፋህ አንተ?›› አለው።

ውሸሞቹና ወሬ አቀባዮቹ ሲጠፉበት በራሱ ላይ እምነት እያጣ ይጨነቃል። አለም ሁሉ ያመፀበት ሰው ቀርቆ ሳር ሁሉ ስለሱ የሚዶልት ይመስለዋል። እንዲያው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቢሮውንም ማመን ትቶአል። የተደበቀ ‹‹ማይክሮፎን›› እንዳለ በማለት በር ዘግቶ ክፍሉን አንድ በአንድ ሳያስስ ቁጭ አይልም። ለሱ ብቻ የሚሰማው ድምፅ እየመጣበት መሄድ ከጀመረው ሰንበት ብሎአል።

‹‹የትም አልጠፋሁም። እዚሁ ነኝ›› አለው፣ ‹‹ጌታዬ›› የሚለውን ቃል ሳይጨምር።

እንደታፈነ ሰው ለትንፋሽ ታገለና፣ ‹‹ኮርተሃል-አይደለም!›› ብሎት ብቅ ጥልቅ እያለ ወደ መስኮቱ ሄዶ፣ ‹‹አንተም እንደ ሌሎቹ ያጎረሰህን እጅ ለመንከስ ተነስተሃል መሰለኝ! አትስረቅ፣ አትፍራ ነው ነገሩ። እግዜር ከኔ ጋር ነው፣ ማንም ሊነካኝ አይችልም! . . .

‹‹ግን ይህን ሰሞን ሁሉም አድፍጦ ነው የሚንሾካሾከው። አንድ ነገር በመጎንጎን ላይ ናቸው ማለት ነው። ዝም ሲሉ ደስ አይለኝም። ስለኔ ምን እንደሚያስቡ በየደቂቃው ማወቅ እፈልጋለሁ. . .

‹‹አየህ የናቴ ልጅ! እነሱ ጠጠር ብጤ ነው የሚወረውሩብኝ። እኔ ግን ቁዋጥኝ ነው የማወርድባቸው። ገባህ የናቴ ልጅ! የአስራ ሁለተኛ መልቀቂ ‹‹ሰርቲፊኬት›› አምጥተህ የለም? ጥሩ የእድገት ደረጃ ታስቦልሃል። ታታ ሰዎች ማደግ አለባቸው ብዬ ነው የማምነው። ለዚህ ነው የሚጠሉኝ. . .

‹‹ታዲያ የናቴ ልጅ የሚጠሉኝ እነማን መሰሉህ? የስራ ጠር የሆነ ሰነፎች ናቸው። እኔ ከዚህ ብሄድ ስራ አላጣም። እግሬን ስመው የሚቀበሉ ድርጅቶች ሞልተዋል። ግን እኔ-የናቴ ልጅ-ያቀናሁት ቤት ሲበላሽ እያየሁ ዝም ብዬ አልሄድም በማለት ነው የምታገለው። የህሊና ወቀሳ እንዲያድርብ አልፈልግም።

‹‹ገብቶሃል የናቴ ልጅ! ሰራሴ ብዬ አይምሰልህ። ለኔ እግዚር አለልኝ›› አለው በአይነ ህሊናው ከጫፉ የመስቀል ምልክት ያለበት ከሰሩ አንኳሴ የሆነ ዘንግ እየታየው።

‹‹ገብቶኛል›› አሰው ደርቤ ያደረበት ንዴት አፍኖ።

‹‹አምን የናቴ ልጅ። ሰአንበሳ አይመትሩም፥ ለብልህ አይነግሩም ይባላል። ራሱን የማይረዳ ሰው፥ እግዚርም አይረዳውም!›› ብሎ ደርቤን ሸኘውና ብላታ ‹‹ቻርሊ›› እዚህ የተረገመ መስሪያ ቤት ባያስገቡኝ ኖሮ፥ ይሽኔ የጠገበ ነጋዴ እሆን ነበር ብሎ ሲያስብ ያቀጣጠሩ ሁኔታ ትዝ አለው።

ብዙ ጊዜ ደጅ ሲጠና ቢቆይም ብላታ ‹‹ቻርሊ›› አይተው እንዳላዩት አድርገው ስለሚያልፉት፥ አንድ ቀን ተናደደና ብቅ ጥልቅ እያለ በመሮጥ ከዚሮአቸው ድረስ ተከትሎአቸው፥ ‹‹ድንጋይ እንኩዋን ውሀ ያናግራል! ምን ነው ዝም አሉኝ ጌታዬ›› ይላቸዋል።

ባጭር ቁመናቸው ወደ ላይ ተንጠራርተው፥ ‹‹እኔ ነኝ ድንጋይ አንተ!›› ይሉትና፥ ወደ ፔርሶኔሉ ዞር ብለው፥ ‹‹ይህን ሰው ከደመወዙ መቶ ብር ቅጣልኝ!›› ይሉታል።

‹‹ሽረ ጌታዬ ስራ ፈላጊ ነው›› ይላቸዋል፥ ፔርሶኔሉ. . .

‹‹አንግዲያውስ ዛሬውኑ ቀጥረህ ቅጣው!›› ብለው ቢሮአቸው ይገባሉ።

‹‹ሰንቱን አሳለፍነው!›› ብሎ ፈገግ አለ። ከብላታ ‹‹ቻርሊ›› በሁዋላ በየጊዜው የማስታወቂያ ሚኒስቴር ሚኒስትር ሆነው የመጡት እነዶክተር ‹‹ሽሌልስ›› እነ፥ ደጃች ‹‹ለጥ ይበሉ››፥ እነ ዶክተር ‹‹አማኑኤል›› አንድ በአንድ ትዝ አሉት. . .

ደርቤ ሂሩትን ካያት ቀን ጀምሮ ለራሱ አውጥቶ የነበረው መርህ ግብር መክተል ትቶአል። ጠዋትም ሆነ ከሰአት በሁዋላ፥ በተወሰነ ሰአት ስራ መግባቱንም አቁሞአል።

ፍናት በደርቤ መለወጥ እየተገረመች፥ ስለሱ የማወቅ ፍላጎትዋም እየጠነከረ ይሄድ ነበር። ጀምራ ያልጨረሰችው ልብ ወለድ ታሪክ ሆነባት።

በሳምንቱ መጨረሻ ላይ፥ አርብ ከሰአት በሁዋላ ጠበቀችውና፥ ‹‹ጌታህን ከዳህ አይደለም እንዴ? ወይስ እሱ ነው የከዳህ?›› አለችው፥ ደቃ የሚመስሉትን ትናንሽ ላቂታ አይኖችዋን እያቁለጨለጨችበት።

ባንዳፍታ አመዱ ቡን ብሎ፥ ‹‹የምን ጌታ?›› አላት።

‹‹ጌታ›› ስትል ቶሎ ጭንቅላቱ ውስጥ የገባው የአስተዳደሩ ሹም ነበር።

‹‹ጊዜን ማለቱ ነው›› አለችውና ፍንጭትዋን ብልጭ አደረገችበት።

ከባድ ሸክም ከጀርባው እንደ ወረደለት ሰው በረጅሙ ተነፈሰና፥ ‹‹አንቺስ - ከመፅሀፍ ጋር ተጣላሽ?›› አላት፥ ለለውጥ ያህል መፅሀፍ በእጅዋ አልነበረም።

‹‹የጀመርኩን ሳልጨርስ ሌላ መጀመር አስጠልቶኝ ነው. . . ሁለት መፅሀፍ ባንድ ጊዜ የማንበብ ልምድ የለኝም። ግን አንዱ ሲሰለቻቸው ወደ ሌላው እየዞሩ ባንድ ጊዜ ሁለት ሶስት መፃህፍት የሚያነቡ ሰዎች አሉ። እኔ እንደነሱ አይደለሁም፤ የጀመርኩትን ሳልጨርስ ወደ ሌላ መጋባት አልችልም›› አለችውና፥ ስትሻው የነበረው ዘዴ ድንገት ብልጭ ስላለላት ፊንድቃ፥ ‹‹ነገ ቲአትር ቤት አብረን ለምን አንገባም? ሁለት ቲኬት አለኝ። የማውቀው ደራሲ ነው። ቲአትሩን ለህዝብ ሲያቀርብ የመጀመሪያው ጊዜ ስለሆነ ያልጋበዘው ሰው የለም. . .›› ብላ ንግግርዋን ሳትጨርስ አቁዋረጣትና፥ ‹‹ሁሉን በነፃ ከጋበዘ ገንዘብ ከየት ሊያገኝ ነው ታዲያ?›› አላት፥ ስሜትዋ ተጋብቶበት።

‹‹እምአአላፍ ለገንዘብ አይጨነቅም። ከድርሰት ሌላ ህይወት የለውም›› አለችና፥ ስለ እምአአላፍ ያላትን ትዝታ አስታውሳ፥ ‹‹የማንበብ ፍቅር እንዲያድርብኝ ያደረገኝ እሱ ነው። ለማንኛውም ነገር ድርሰቱ ጥሩ ይሁን አይሁን አላውቅም። የኬክ ጣፋጭነት የሚታወቀው ሲቀምሱት ነው ይባላል። ድርሰቱ ጥሩም ባይሆን ጥረቱን እናደንቅለታለን። እምአአላፍ ስለ ድርሰቱ ማውራትና መስማት በጣም ይወዳል። ዘጠኝ ወር ተሸክማና አምጣ ስትወልድ፥ ገና የምጥ ስቃይ ሳያልፍላት ህፃኑን በፍቅር አይን እንደምታይ እናት አይነት ነው ስሜቱ። . . ከኔ ጋር ትመጣለህ? እዚሁ ማዘጋጃ ቤት ቲአትር አዳራሽ ነው በዘጠኝ ሰአት›› ብላ፥ ፍንጭትዋን ብልጭ፥ አይኖችዋን

ቁልጭልጭ፥ ቅንድብዋን ከፍ ዝቅ አድርጋ ስሜቱን ባንድ ጊዜ አተረማመሰችበት።

ደርቤ ቲአትር ቤት ገብቶ አያውቅም። ሰድርሰትም ደንታ አልነበረውም። ግን እምቢ ሊላት አልቻለም . . .

ቀደም ብሎ ሂዶ ከአዬ ምኒልክ ሀውልት አጠገብ ወደ ማዘጋጃ ቤቱ ቲአትር ቤት ከሚያስገባው በር ላይ ሲጠብቃት ቆየ። ፀሀያማ ቀን ነበር። የተነደፈ ጥጥ የሚመስሉ ስስ ደመናዎች ከጠራ ሰማይ ላይ ተንጣለው ይታያሉ።

ሂሩትን እያሰበ ቆሞ ሲተክዝ፥ ፍኖት ከሁዋላው መጥታ ማጅራቱን ነካ አደረገችው። ባንኖ ዞር አለ።

«ብዙ እንዳላስጠበቅሁህ ተስፋ አደርጋለሁ» አለች፥ ፍንጭትዋን ብልጭ አድርጋ።

ፊትዋ ላይ የሚታየው የጋለ ስሜት የፀሀያማው ቀን ነፀብራቅ ይመስላል። ሽቶዋ አፍንጫውን እውድ አደረገው።

ነጭ ሱሪና አንገቱ ክፍት የሆነ ስስ ጥቁር ሹራብ ለብሳለች። የጡት ማያዣዋ በትንሹ ብቅ ብሎ ተመልካችን ይጠቅሳል።

«ሁልጊዜ ሱሪ የምትለብሺው ለምንድር ነው?» ብሎ ጠየቃት። ቀሚስ ለብሳ አይቶአት አያውቅም።

«ያስጠላብኛል!» አለችው፥ ወደ ቲአትር ቤቱ አዳራሽ ማምራት እንደ ጀመሩ።

«ያምርብሻል» አላት፥ ከልቡ።

ለብዙ ጊዜ እንደሚያውቃት ሆኖ ነበር የሚያነጋግራት።

«ለመኪለከል ይረዳኛል ብዬ ነው ሱሪ የማዘወትረው። ወረሀ እግሬን ለመሸፈን ስል አይደለም» ብላ ፈገግ አለች።

«ከምንድር ነው የምትከላከይው?»

‹‹ቀሚስ ባዩ ቁጥር ለመግለብ ከሚፈልጉ ወንዶች›› ብላ በላት ተንከተከተች።

ቀልድዋ አልጣመውም። እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኖ ነበር የተሰማው።

ቲኬታቸውን አስቆርጠው መቀመጫ እንደ ያዙ ቃላትዋን አንድ በአንድ እየደገሙ ‹‹ቀሚስ ባዩ ቁጥር ለመግለብ ከሚፈልጉ ወንዶች ስትይ ምን ለግለት እንደ ፈለግሽ አልገባኝም?›› አላት፡ በቁም ነገር።

ስሜቱን አላጤነችም። መስቲካ ከቦርሳዋ አውጥታ ሰጠችውና ለራስዋም ወስዳ ሱካሩን ካጣጣመች በሁዋላ፡ ጠጉርዋን ከፊትዋ ላይ ለማሸሽ ጭንቅላትዋን ወደ ግራ መታ አድርጋ፡ ‹‹የኛ ወንድ ሴት ይዞ በውጣ ቁጥር በመጀመርያ የሚታየው አልጋ ብቻ ነው። የግብረ ስጋ ግንኙነት ብቻ ነው የሚታየው። ከግብረ ስጋ ውጭ በሴትና በወንድ መካከል ሌላ ግንኙነት ያለ አይመስለውም።

‹‹ከግብረ ስጋ ውጭ ሴት እንደ ጉዋደኛ የማትታይበት ምክንያት የለም። የተበላሸ ህብረተሰብ ነው። አየህ፡ ሴት የስሜት ማርኪያ መሳሪያ አይደለችም። እስዋም ሰው ናት። ከግብረ ስጋ ግንኙነት ውጭ ሴት ልጅ ከወንድ ጋር ለመፈፀል የምትፈልገው ስሜት፡ አመለካከትና አስተያየት አላት። የሚያሳዝነው ግን ወንድ ከሴት የሚፈልገው እንትንዋ ብቻ ነው። ወንዱ ውሸማ ነው እንጂ ጉዋደኛ አይፈልግም። ሳስበው አናደዳለሁ። እና ሱሪ ለብሼ እዞራለሁ. . .

‹‹አንድ ጊዜ የደረሰብኝን ልንገርህ። እዚሁ መስሪያ ቤት ነው። ሰውዬው በጣም ቀልደኛ ነው። ቀልዱን ያመጣ እንደሆን እፍ ያስክፍታል። ሀንዶችን ጉራጌዎችን፡ አረቦችን መስሎ ሲናገር ጥርስ አያስክድንም። ‹‹ኮሚክ›› ነው።

የሰዎችን አነጋገርና አካሄድ መቅዳት ሲችል ላየው መቼም ትንግርት ነው። በዚህ የተነሳ እወደው ነበር። አንድ ቀን፡ ‹‹ሁና ልጋብዝሽ›› አለኝ። እሺ አልኩት። ፍላሚንጎ ወስዶኝ ቡና እየጠጣን በቀልድ ልቤ እስኪፈርስ ድረስ እንዲሁ ሲያስቀኝ፡ ለምን ቀልድ ትወዳለህ? ብዬ ጠየቅሁት። (ያለሳቅ ህይወት ጣእም የለውም። እኛ ኢትዮጵውያን በራሳችን መሳቅ መልመድ አለብን። እነ

ግን ቀልድ የማይመው በሌላ ምክንያት ነው። ብችንቱም፣ ስራዬም፣ አካላቴም ስለሚያስጠላኝ ከዚህ ያመለጥኩኝ እየመሰለኝ ነው ቦቱ የማነቀው አለኝ።

..ምሽት ሁሉ ደስተኛ ይመስለኝ ነበር። ሰማንያውም ነገር ውና ከሰማን ዘጠኝ ብቱን ጓላይሽ። አለኝ። እሺ ብዬ ቤቱ ሄድን። ጥሩም የሆነ ቤት አለው። ቤቱን አንድ ባንድ አሳየኝ። መጨረሻ መኝታ ቤቱ ገባን

..ጥሩም መኝታ ቤት ነው። የጣራውን መብራት አጥፍቶ የራስጌውን መብራት አበራ። ሙዚቃ ከፈተና ሂዶ በሩን ቀልፍ አደረገ። ለምን በሩን ዘጋኸው? አልኩት። (እንድንተኛ ነዋ) አለኝና ኮቱን ማውለቅ ጀመረ። ትቀልዳለህ መሰለኝ! አልኩት። (ከልቤ ነው) አለኝና ወደ በሩ ዘሂድ በል እያን ያ ይተናነቀኝ ጀመር. . .

..ቁላው ልቤን ያቀልጠው ይመስል እየደባበሰ ሊስመኝም ሞከረ። ወዲያ ገፋሁትና፣ አውራ አትሁን። ጉዋደኛነትክን ፈልጌ ነው አልኩት። ሊገው አልቻለም። እንዴት ተናቅሁ! የሚል ስሜት ነበር ያደረበት. . .

..ደግሞ እሱ ባይሆን ኖሮ ሌላውማ በገድ ያንቀኝ ነበር። ይሆንን ነው ፍቅር የሚሉት!

..ያገራችን ወንድ ሲባል ሴቶችን ማነቅ፣ ማለቃየት፣ ትልቅ ቁም ነገር ይመስለዋል። ስለ ፍቅር በጣም የተሳሳተ ትርጉም ነው ያለን። አለችው።

..ሴቶቻችንስ ያው አይደሉም?.. አላት።

..ሴቶች አይንቁም። ከፈለጉ ያግባሉ። ሴቶች ካጠመዱት ወየመጅ ሆነች ሊያመልጡ አይችሉም። እርግጥ ..ውበታቸውን.. በመላሪያነት ይጠቀም ሴቶች ይበልጣሉ። ግን እንዳልከው ሴቶችም ያው ናቸው . . .

..ወንዶች ጋር ሲወጡ ቀጥሎ የሚሆነውን እያወቁ ነው። ሌላ ፍላጎት የላቸውም። ምክንያቱም ከወንዶች ጋር የሚካፈሉት ሌላ ነገር የላቸውም። ስለዚህ በሁለቱም በኩል ያለው ግንኙነት በግብረስጋ ግንኙነት ተወሰነ ይሸል። የሚያሳዝን ነው.. አንዳለችው መጋረጃው ተከፈተ።

የመድረኩ መብራትና ትእይንት ስለሳበው ደርቤ ፈዞ ቀረ። ሁኔታውን ስላየች፥ ‹‹መድረክ እኔንም ይስበኛል። የህይወት ቁንፅል ገፅታ ነው። ህይወት ራስዋ ሰፊ መድረክ ናት። ግን፥ የሚያሳዝነው የኛ ቲአትር ቤት መድረኮች ባዶ መሆናቸው ነው። ሁኔታው የህይወታችን ባዶነት ነፀብራቅ መስሎ ነው የሚታየኝ›› አለችው።

ቲአትሩ አልተጀመረም። መጋረጃው የተከፈተው ድምፃውያኑና ተወዛዋዦችን ለማቅረብ ነበር። ፍኖት አልተደሰተችም። ድምፃውያኑ ከጥሩንባ ጋር፥ ድምፃውያኑና ጥሩምባው ደግሞ ከተወዛዋዦች ጋር ሲፎካከሩ መስማትና ማየት አስጠላት። ኩዋስ አበደች ተብሎ ጥለዛ የሚቀልጥበት የልጆች ጨዋታ መሰሎ ነበር የሚታያት። የዘፈኑ መልእክትና የድምፃውያኑ ውዝዋዜ መቋነጥነጥና እጅ ማወናጨፍ ስላልተጣጣሙላት ተበሳጭታ ነበር። ቲአትር ያለ ኦርኬስትራ አጀብ ተመልካችን መሳብ የሚችልበት ጊዜ መቼ ይመጣ ይሆን? ብላ በልብዋ ተመኘች።

የሙዚቃው ክፍለ ጊዜ እንዳበቃ ፍኖት ጆሮዋን ኮረኮረችና፥ ‹‹ጥለዛው እንዴት ነበር?›› አለችው።

ደርቤ ፈዞ ቀርቶ ነበር። ከመድረኩ ላይ አይኑን አልነቀለም።

‹‹የምን ጥለዛ?›› አላት፥ በግማሽ ልብ።

‹‹ሙዚቃውን ማለቴ ነው›› አለችው።

‹‹ጥሩ ነበር›› አላት፥ ኮስተር ብሎ።

‹‹አንኩዋን ወደድከው። በሙዚቃና በቀለም አይነት መከራከር አይቻልም። የስሜት ጉዳይ ነው›› ብላ ዝም አለች።

ስለ ኪነት አንዳንድ ነገሮችን ለመገምገም እንዲችል ባደርገው ጥሩ ነበር ብላ በልብዋ አሰበች። መፅሀፍ እያነበብን ስላብ ለስላብ ለመለዋወጥ ብንችል እያለች ስታስብ ለደርቤ ያላት ስሜት ተማታባት። መጋረጃው ሲከፈት አልታወቃትም።

ቲያትሩ እንደ ተጀመረ እስከ ግማሽ ትእይንት ድረስ ደርቤ እንዲም ጥርሱን አልከደነም። እየተንከተከተ ይስቅ ነበር። ግን ከሁለተኛው ትእይንት ግማሽ ጀምሮ በተለይም ከሁለተኛው ትእይንት በሁዋላ እስከ ቲአትሩ ፍፁሜ ድረስ መሳቅ ቀርቶ ፈገግም አላለም።

ሀዘን ላይ የተቀመጠ ሰው መስሎ ነበር የቀረው። ብዙ ሰው ስላልነበረ የቲአትሩ አዳራሽ አይመስልም፡ ግን ደርቤ ያልበው ነበር። አስር አስር ጊዜ መሃረብ አውጥቶ ፊቱን እየጠረገ ቁና ቁና ይተነፍስ ነበር።

ቲአትሩ ስለ ቢሮ ተላላኪዎች ነበር።

ለፊ አዳራሽ ይታያል። የቢሮ በሮች ሁሉ ተዘግተዋል። በያንዳንዱ ቢሮ በር ላይ ተላላኪዎች ቆመዋል። በተለይም በአንዳንድ በሮች ላይ ሁለት ወይም ሶስት ተላላኪዎች ይታያሉ። ደወል ሲደወል ተንጋግተው ይሄዳሉ። ተንጋግተው ይመለሳሉ። ፋይል በብዛት ይገባል። ሲወጣ ግን አይታይም። በር በተከፈተ ቁጥር ጢስ ቡልቅ ቡልቅ እያለ ይወጣል።

ቢሮ እንደ ጣኦት እየታየ ይሰገድለታል። ባለስልጣን ብቅ ባለ ቁጥር እጅ መንሳትና ጋጋታ ይበዛል። ካፖርቱን፡ ቦርሳውን፡ ባርኔጣውን ተቀብሎ ለመሸከም ትንቅንቅ ይደረጋል፤ ሲወጣም እንደዚሁ. . .

ባለጉዳዮች ተኮልኩለው፡ ‹‹አቤት! አቤት!›› ይላሉ። እያለቀሱ ይሄዳሉ። ዘመናይ ሴቶችን ግን የሚለከል የለም። እንደ ልብ ገብተው ይወጣሉ። እያሽኮሩ። ብር እየቆጠሩ የሚመጡ ጭሰኞች ይገባሉ። ስጦታ የያዙ የውጭ አገር ነጋዴዎች እንደ ልባቸው ይገባሉ - ይወጣሉ።

ተላላኪዎች ቡና፡ ሻይ፡ ሲጃራ ለስላሳ መጠጥ፡ ውሃ፡ አምቦ ውሃ፡ ከማመላለስ ሌላ ስራ ሲሰሩ አይታዩም። ደወል. . .ደወል. . .ንቅናቄ. . .በያንዳንዱ ተላላኪና ባለ ጉዳይ ፊት ላይ የሚነበብ ስሜት. . .

እንደ ባህር ሞገድ ከፍ ዝቅ የሚል የህዝብ ድምፅ ማስተጋባት ይጀምራል—ጎህ ይቀዳል—ብርሃን ይወጣል. . .

ባለስልጣኖች ከቢሮአቸው እንደ አይጥ እየተሸሎከሎኩ ይወጣሉ-ይገባሉ-ይደናገጣሉ-ይርበተበታሉ-የሚይዙትንና የሚጨብጡትን ያጣሉ። ብርሃኑ እያየለ ይሄዳል-እየፈካ-እያጥለቀለቀ. . .

ባለስልጣኖች ሲገቡና ሲወጡ ተላላኪዎች እጅ አይነሱም። ከተቀመጡበት አይነሱም። ባለስልጣኖች፥ ‹‹ጉዋዶች! ጉዋዶች!›› እያሉ እጅ ይነሳሉ። በገቡና በወጡ ቁጥር የጋለ ሰላምታ ያቀርባሉ። የደመቀ ፈገግታ ያሳያሉ።

ደወል. . .ደወል. . . የተለመደው ማኪያቶ፥ ሻይ ቡና፥ አምቦ ውሃ. . . ደወሉ ጋብ ሲል ተላላኪዎቹ አለቆቻቸውን ባወጡላቸው ቅፅል ስም እየጠሩ እያንዳንዱ አለቃ በምን ሁኔታ እንዳደረ፥ ስብሰባ ላይ ነኝ በማለት በር ዘግቶ ምን በመስራት ላይ እንዳለ፥ አለቃና ፀሀፊ ምን በማድረግ ላይ እንዳሉ መግለፅ ይጀምራሉ።

ሆዱን እያከከ፥ ‹‹አለቃዬ የአራት ብር ከስድሳ ሳንቲም ሲጫራ በቀን ሲያጤስ እኔ ጥሬ አሮብኝ አካለሁ›› እያለ በመደጋገም የሚናገረው ቀዳሚ ተዋናይ፥ አለቃው ቢሮ ገብቶ ሌሎች ተላላኪዎች ስለሱ የሚሉትን ሊነግረው ሲጀምር ቀልዱ ይለወጣል። ደርቤም መሳቅ ያቆመው ከዚሁ በሁዋላ ነበር።

ሁለተኛው ክፍለ ትእይንት፥ በውይይት ክበብ ስብሰባ ላይ፥ ‹‹ማን ነው ይሁዳ? ጭቁን ሆኖ ለጥቅም ጭቁኖችን አሳልፎ የሸጠ? ማን ነው እሱ መደቡን የከዳ? በሚል ሀይለ ቃል ይጀምራል።

‹‹እና አድሃሪ ቢሮክራቶች ውይይት ክበቦችን እንደ ጦር ይፈራሉ። ውይይት ክበቦችን ለማፍረስ የማይሸርቡት ሴራ የለም። ታዲያ እኛ ነው መልሰው መሳሪያ የሚያደርጉት - በይሁዳዎች እየተጠቀሙ. . .

‹‹ለስልጣን የቁዋመጡት ቡድኖችም መሳሪያ ሊያደርጉን ይፈልጋሉ እርስ በርሳችን እየከፋፈሉን. . .

‹‹ለግል ጥቅም የሚያስፈሰፉት መሳሪያ ሊያደርጉን ይፈልጋሉ እድምተኞቻቸው እያደረጉን. . .

‹‹ግን፥ ውይይት ከጠቦች የሰፊው ጭቁን ሰራተኛ ብሄራዊ ትምህርት ቤቶች ናቸው። እንማራለን! ከትግል እላት ተፈትነን እንወጣለን! እናሸንፋለን! ይሁዳዎች ይወድማሉ!››

ደርቤ ዝም ይላል። ያልበዋል።

በቲአትሩ መጨረሻ ላይ፥ ቀዳሚው ተዋናይ እንደ ይሁዳ እየተቅበዘበዘ ሂዶ በገመድ ራሱን ሲሰቅልና አለቃውም እንደ ጲላጦስ እጁን ሲታጠብ መጋረጃው ይዘጋል. . .

የደርቤ ሰውነት ነፋስ እንደ መታው ቅጠል ይርገፈገፍ ነበር። ፍኖት ስለ ደርቤ ሁኔታ አላጤነችም። እምአእላፍ በቲአትሩ ምን መልእክት ለማስተላለፍ እንደ ፈለገ ነበር የምታሰላስለው።

ከቲአትር ቤቱ አዳራሽ ወጥተው ደረጃውን ከወረዱ በሁዋላ፥ እምአእላፍ ከመውጫ በር ወደ ቀኝ ሲል ካለው ቡና ቤት ባንኮኒ ላይ ተደግፎ ሻይ ሲጠጣ ፍኖት ስላየችው፥ ወደሱ ሄደችና፥ ‹‹እንኩዋን ደስ አለህ። ጥሩ ነበር›› አለችው።

‹‹ኤጭ!›› አላትና እጁን አወናጨፈ።

ደርቤን አስተዋወቀችው።

‹‹አ ያ ተጀምሮ ያላለቀ መፅሀፍ!›› አላት፥ መነፅሩን በጣቱ ካፍንጫው ላይ ወደ ላይ ገፋ አድርጎ።

ደርቤ አልገባውም። ያ ሁሉ ሀይለ ቃል ከዚህ ስንጥር መሳይ ሰው እንዴት ሊወጣ ይችላል? እያለ ነበር የሚያስበው።

እምአእላፍ አንድ ሀሙስ የቀረው ይመስላል፡ አንገቱ እንደ ሲባጎ ሊል ብላ ትታያለች። አንጀቱ ከጀርባው ጋር የተጣበቀ፥ ደረቱ የለመጡ ትከሻው የጎበጠ፥ ጠይም ፊቱ ጨጎጎት በሚመስል ጢም የተሸፈነ፥ ጠጉሩ ከመጠን በላይ ያጎፈረ ነበር። አይኖቹ ጥልቀት ካለው ጉድጉዋድ ውስጥ እንደሚታይ ውሀ ከመነፅሩ ሁዋላ ጭል ጭል እያሉ ይታያሉ። ከወሎ ረሀብ አልቂት አምልጦ ገና በማገገም ላይ ያለ መስሎ ታየው - ለደርቤ።

‹‹ምን አበሳጨህ?›› ብላ ጠየቀችው::

እምአእላፍ የሚያኝከውን ጫት አገላባትና፥ ‹‹የሚያበሳጭ ነገር ምናለ ብለሽ ነው! ተዋንያኑ ያለቦታው ይጮሃሉ:: እንደ ቦና ጥጃ መድረኩ ላይ ይቦርቃሉ - እንደ አይጥ ይሽሎኮሎካሉ!›› ካለ በሁዋላ፥ ግንባሩን ቁዋጥሮ፥ ‹‹የመብራቱ መዝጎርጎር ደሞ! የሸርሙጣ ቤት መብራት ያስመስሉታል! ሰው የወለደውን ልጅ ሲያንገላቱበት የሚከፋውን ያህል ነው የሚሰማኝ›› አላትና፥ እንደ ቆሎ በኪሱ ይዞት የሚዞረውን ጫት አውጥቶ ጎረሰ::

ፍኖት ፍንጭትዋን ብልጭ አድርጋ፥ ‹‹የኪነት ሰዎች ስትባሉ የሌላ ሰው ስራ አይጥማችሁም›› ብላ በአይንዋ ጭምር እየሳቀች፥ ‹‹ለዚህ ይሆናል የተበሳጨኸው!›› አለችው::

እምአእላፍ ጫቱን እኝክ እኝክ አደረገና፥ ‹‹ሀብረተሰቡም ስራችን አይጥመውም:: እኛ የኪነት ሰዎች እንቁ ነን እንላለን፤ የሚያየን የለም:: ማር ነን እንላለን፤ የሚልሰን የለም:: የወለድናቸውን ልጆች አይስሙልንም፥ እንዲያውም ያንገላቱብናል. . .

‹‹በዚያ ላይ የሚረዳን ድርጅት የለም:: አንድ ደራሲ ድርሰቱን ከመፃፉ አንስቶ እስከ ችርቻሮ ድረስ ያለውን ስራ የሚያካሂደው ራሱ ነው:: የቲአትር ድርሰት ፀሀፊም ሆነ የሰአሊ እድል ከደራስያን የተለየ አይደለም::

‹‹ይህ ሳያንስ፥ ሀብረተሰቡ፥ ነጋዴን መጫኛ ነካሽ፥ ሽማኔን ቁጢጥ በጣ፣ ገበሬን አፈር ገፊ - ባለእጆችን ጠይብ፥ ቡዳ ወዘተ እያለ እንደሚያራክሰው ሁሉ፥ የኪነት ሰዎችንም፥ አዝማሪ፥ ቀለም ቀቢ - ብራና አለስላሽ፥ መተተ፣ ደብተራ እያለ ዋጋ ሲያሳጣቸው ቆይቶአል::

‹‹ኪነት ክቡር ነገር ነው:: የሀብረተሰቡ አይንና መስተዋት፥ የዛሬው ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ - የነገውን በትክክል የሚጠቁም ክቡር ሙያ ነው በኪነት መደሀየት ማለት፥ የህልውና ድህነት ማለት ነው:: በኪነት ያበለ ስልጣኔ ባዶ ነው - ህይወት የለውም::

‹‹የኪነት ሰዎች አላማና ግብ፥ ሀቅ ነው:: ግን፥ ስንት የኪነት ሰዎ ናቸው ለሀቅ ቆመው ለመሞት፥ ለመራብ፥ ለመታረዝና መጠማት የተዘጋጁ

ህብረተሰቡ በንቀት አይን ቢመለከተንና ዋጋ ባይሰጠን አይገርመኝም። ሀቅን ያልጨበጠ ኪነት ዋጋም ሆነ ዘላቂነት የለውም። የታሪክ አተላና ዝቃጭ ሆኖ ይቀራል. . .

‹‹ለኪነት ዘላቂነትና ውበት የሚሰጠው ሀቅ ነው። ያለ ሀቅ ኪነት የለም። ኪነ ጥበባችን ድሀ ሆኖ የቆየው፥ ሀቅን ጨብጦ ባለመገኘቱ ነው። ይገባሽ እንደሆነ የምበሳጨው ለዚህ ነው. . .

‹‹ለሀቅ ስለ ሀቅ መፃፍ አልችልም። ቲአትሬን እንደተመልካች ሁኜ ሳየው ሊያስታውሰኝ ነበር። ለምንድር ነው የፃፍኩት? ብዬ ራሴን ስጠይቅ ነው የመጣችሁት። ቴአትሩን ያቀረብኩት የህብረተሰቡን ሀቅ ለማንፀባረቅ እንዳልነበረ ገባኝ። ለዝናና ለገንዘብ ሰል ነበር ማለት ነው። እና፥ ራሴን ታዘብኩት። ራሴን ጠላሁት›› አለና በረጅሙ ተነፈሰ።

ደርቤ የሚያስበው ስለ ሌላ ነገር ነበር። በድንገት፥ ‹‹ዋናው ተዋናይ ራሱን እንዲሰቅል ለምን አደረክ? አለው።

እምአእላፍ ፈገግ ሲል ደስ ይላል።

‹‹እኔ አይደለሁም እንዲሰቀል ያረኩት። ራሱ ነው›› አለው።

‹‹አንተ አይደለህም እንዴ ደራሲው?››

‹‹ነኝ። ግን የፈጠርኩዋቸው ገፀ ባህርያት ከተፈጠሩ በሁዋላ፥ የየራሳቸው ህልውና አላቸው።ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ይመሩኛል እንጂ እኔ እንደ አሻንጉሊት አልጫወትባቸውም። የኔ ሚና የነሱን አስተሳሰብ፥ ስሜት፥ ፍላጎትና ውሳኔ ተከትሎ መፃፍ ነው›› ብሎ ሲያበቃ ለጠቀና፥ ‹‹በመሞቱ አዘንክለት መሰለኝ›› አለው።

‹‹መደቡን የከዳው ባለማወቁ ነው። መሞት አልነበረበትም!›› አለ ደርቤ፥ በድንገት ድምፁን ከፍ አድርጎ።

ፍኖት ተገርማ ትኩር ብላ ተመለከተችው። የደም ስሮቹ ተገታትረው መልኩ ተለውጦ ነበር።

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹ምናስቆጣህ ጃል! እኔ አልገደልኩም። ሊሞትም አላማከረኝም። ለመሞት ፈለገ - ሞተ። የኔ ሚና የያንዳንዱን ሰው ሀቅ ማቅረብ ነው›› አለና፥ ጫት አውጥቶ ጎረሰ።

‹‹አንድ ነገር አስታውሰት ይሆናል የተቆጣው›› አለች ፍኖት፥ በጥርስዋም በአይንዋም እየሳቀች።

ደርቤ በቁጣ፥ ‹‹ምንም ያስታውሰኝ ምን መሞት አልነበረበትም!›› ካለ በሁዋላ፥ ወደ እምአእላፍ እያተኮረ፥ ‹‹ምን ለማስተማር ነው የፃፍከው?›› አለው።

‹‹ምንም። እኔ አስተማሪ አይደለሁም። ማስተማር የደራሲ ተግባር አይመስለኝም። የኔ ተግባር ሀቅንና ውበትን መሻት ነው›› አለው፥ ድርሰቱ ከተመልካቾች ውስጥ ያንዱን ስሜት በመንካቱ እየተደሰተ።

ደርቤ ትእግስቱን ጨርሶ ነበር። የተናደደው በእምአእላፍ ሳይሆን በራሱ ነበር። መሪ ተዋናዩ እንደ አበደ ውሻ እየተቅበዘበዘ ሂዶ ራሱን ሲሰቅል ባሳዙ እየታየው የመንፈስ እረፍት አጥቶ ነበር። ወደ ፍኖት መለስ ብሎ ‹‹እንሂድ!›› አላት።

እምአእላፍ ከደርቤ ለመለየት አልፈለገም ነበር። ‹‹ፍኖት እንዳልጨረሰችው መፅሀፍ ታየው ይሆናል፥ ለኔ ግን ደስ የሚያሰኝ ባህርይ ነው›› ብሎ አሰበ።

እምአእላፍ ፈገግ ብሎ፥ ‹‹የጀመርሺውን ጥሩ መፅሀፍ ሳትጨርሺ ለመ አላውስሺም። እና ስለ መፅሀፉ ሌላ ጊዜ ታጫውቺኛለሽ። እኔም ቸኩያለሁ ዛሬ ምርቅን ማለት አለብኝ። ቻው›› ብሎአቸው ጫቱን እያኘከ ተለያቸው።

ደርቤና ፍኖት ተያይዘው ወጡ።

አፄ ምኒልክ አደባባይ አካባቢ ከድሮ ማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት ፍኖት ቀበና ብላ ሴይቼንቶ ካስቆመች በሁዋላ፥ ‹‹አትሸኘኝም?›› ብላ ደርቤ ጠየቀችው።

ደርቤ ምንም ሳይናገር ተከትሎአት ሴይቼንቶ ላይ ተሳፈረ። የተሳፈሩበት ሴይቼንቶ በደጃች ውቤ ሰፈር፥ በአፍንጮ በር፥ በየካቲት ፲፱ ለደባይ፥ አድርጎ ወደ ቀበና በፍጥነት ሲበር፥ ደርቤ ዝም ብሎ ስለ መሪው ተዋናይ መስቀል ያስብ ነበር።

ያባቱ ሬሳ ከወደቀበት ጫካ እንዲመጣ ተደርጎ ጢቾ ከተማ ላይ በገበያ ቀን መስቀሉ ትዝ አለውና፥ ሰውነቱን ዘገነነው። አይኖቹ እንባ አቀረሩ። በዚያ ቀውጢ ዘመን ከባለርስት ጋር ለመብቱ ሲታገል በጥይት ተደብድቦ የወደቀው አባቱ ከመቃብሩ ቀና ብሎ ቢያየኝ ምን ይለኝ ይሆን? ደረቅ ጡቶችዋ ደም እስኪወጣቸው ድረስ እያጠባችኝ፥ እስዋ ቆሎ አሮባት አንጀትዋ ተጣብቆ የሞተችው እናቴስ ከድንጋይ ትራስ ላይ ቀና ብላ ብታየኝ ምን ትለኝ ይሆን? ብሎ አሰበ።

አባቴ ‹‹ወንበዴ ነው›› ተብሎ እንደ አውሬ ታድኖ ተገደለ። መብቴን አትንኩብኝ ስለማለት ሌላ ምን ሀጢአት ሰራ! ይገርማል! እኔም ወንበዴነቱን ለምኜና ተቀብዬ ነው እስከ ዛሬ የኖርኩት! አባቴ የሞተለትን አላማ የረገጥኩ ወንበዴ እኔ ነኝ። እስከ ዛሬ የት ነበርኩ? ሰው መሆን. . . አይ ሰው መሆን. . . ሞት ይገባኝ ነበር እንደ መሪው ተዋናይ. . . እያለ ሲያስብ የሴይቼንቶው መቆም አሳቡን አቋዋረጠው።

ከተሳፈሩበት ሴይቼንቶ ሲወርድ የተከሰተለት ነገር ቢኖር፥ ከአንግዲህ የተለወጠ ሰው መሆኑ ነበር። በዚያች ደቂቃ ብቻውን ለመሆን ተመኝቶ ነበር። ብቻውን ሆኖ ወደ ውስጡ በመመልከት ስለ ራሱ፥ ስላላለፈው ህይወት፥ ስለ ወደፊት ኑሮው ስለ ሂሩት ለማሰብ ፈልጎ ነበር።

መንገድ ላይ ተሰናብቶአት ሌላ ሴይቼንቶ ይዞ ለመመለስ ሲያስብ፥ ፍናት ቀድማው፥ ‹‹ቤቴ ቅርብ ነው። ሻይ ጠጥተህ ትሄዳለህ›› ብላው፥ ከሱ መልስ ሳትጠብቅ ወደ ቤትዋ ማምራት ጀመረች።

ተከትሎአት ሄደ።

ፍናት የምትኖርበት ቤት ከዋናው መንገድ ትንሽ ራቅ ያለ ነበር። ቤትዋ ራሱን የቻለ አጥር ግቢ ሆኖ፥ ከቤቱ ፊት ለፊት ያለው ትንሽ መስክ በልዩ ልዩ አይነት የፅጌረዳ ተክል አይን ይማርካል። ከወንፊት ሸሆ የተሰሩ ሁለት

የምፍ ጎጆዎች ከአበቦቹ መሀል ብቅ ብቅ ብለው ይታያሉ። ፍኖት አበቦችዋን በፍቅር አይን እየተመለከተች አልፋ ወደ ምፍ ጎጆዎቹ ሄደችና፥ ምርቹ እህልና ውሀ እንዳላቸው ካየች በሁዋላ፥ ‹‹ሀኒንና ጆኒን ላስተዋውቅህ›› አለችው ደርቤን።

ሀኒና ጆኒ የመስቀል ምፍ የሚመስሉ - ጀርባቸው ጥቁር ሀር፥ ልባቸው ወርቅማ የሆነ ውብ ነገሮች ነበሩ።

ፅጌረዳ አበባዎቹ ፈንድተው ውበታቸውን ወደ ውጭ ገልብጠው በማውጣት እዩኝ እዩኝ እያሉ ደስ የሚለውን መአዛቸውን ከቀዝቃዛው አየር ጋር ደባልቀው በመርጨት ይስባሉ።

ፍኖት በተመስጦ አበቦችዋን ከተመለከተች በሁዋላ፥ ‹‹ተፈጥሮ እንደ ሴት ናት። ሰውን የምትስብበት መንገድ አላት። ተፈጥሮ ውብ ሆና ውበትዋ ቆም ብለው የሚያደንቁና በውበትዋ የሚደሰቱ ጥቂቶች ናቸው። እና ተፈጥሮ ፍቅር የተነፈጋት ውብ ሴት ተመስላ ስለምትታየኝ፥ ታሳዝነኛለች እያለችው ቤት እንደ ገቡ፥ ‹‹መጣሁ›› ብላው ወደ ጉዋዳ ዘለቀች።

እንግዳ ቤትዋ መጠነኛ ሆና በቀይ ሶፋዎች፥ በሰማያዊ የመስኮት መጋረጃዎችና በሰማያዊ ምንጣፍ ያጌጠች ነበረች። ውድ በሆኑ የአበባ ማስቀመጫዎች የፈነዱ ፅጌረዳ አበባዎች ተሞልተው አይን ከሚያርፍባቸው አንዳንድ ስፍራዎች ተቀምጠዋል። ከከፍሉ ውስጥ እጅግ ጎልተው የሚታዩት ግን የመፃህፍት መደርደሪያዎች ነበሩ።

ከእቃዎች አቀማመጥ ጀምሮ በእንግዳ ቤቱ ውስጥ ለአይን የሚያስቀይም አንዳችም ነገር አይታይም። ሁሉም ነገር አይን የሚስብና የሚያስደስት የመንፈስ እረፍትንና ፀጥታ፥ የሚያረጋጋ ስሜት የሚሰጥ ነበር - እንደሰዋ።

ከጉዋዳ ብቅ እስክትል ጠበቃትና፥ ‹‹ብዙ ታነቢያለሽ!›› አላት።

ደስ የሚል ሽቶዋ አፍንጫውን አወደው።

‹‹ተፈጥሮን ከማድነቅ ሌላ ደስ የሚለኝ ነገር መፅሀፍ ማንበብ ነው፡ ደስታ ይሰጠኛል። ስለ ማንኛውም ነገር ደግሞ ትምህርት አገኝበታለሁ›› አለችው፥ መፃህፍዎችዋ በፍቅር አይን እየቃኘች። ‹‹እና፥ ቢሮ ገብቶ በቴሌፎ

እገልፉ እገሊትዬ እያሉ የባጡንና የቆጡን ሲቀባጥሩ ከመዋል መፅሀፍ ማንበብ ይሻላል›› አለች፥ ፍንጭትዋን ብልጭ አድርጋ በአይንዋ ጭምር እየሳቀች::

‹‹እና፡- መፅሀፍ ሕይወት ነው:: በኔ ግምት የመፅሀፍ መጥፎ የለውም:: እያንዳንዱ ደራሲ ለአንባብያን ለማስተላለፍ የሚፈልገው ከህይወት ያገኘው ልምድ አለው›› ብላ ተነሳችና፥ ከሻይ ጠረጴዛ ላይ ያለውን አበባ አስተካከለች::

‹‹እና፡- ማንበብ ብቻ ሳይሆን እኔም አንድ ቀን አንድ መፅሀፍ ለመድረስ ተስፋ አለኝ›› እንዳለች፥ ወጣት ቤት ገረድ ሻይና ትኩስ የዶሮ ወጥ ፍርፍር በትሪ ይዛ መጥታ ከፍናት ፊት አስቀመጠችውና ወጣች::

ገረዲትዋ የጣት ውሀ ይዛ ተመለሰች:: ደርቤ እጁን እየታጠቡ ‹‹የመፃህፍት ማንበብ ፍቅር እንዴት አደረብሽ?›› ብሎ ጠየቃት::

ፍናት ስለ ራስዋ መናገር አትወድም:: ደስ የሚላት ስለ ሌሎች ሰዎች ህይወትና ልምድ ማወቅ ነበር:: ስለ ሌሎች ሰዎች ህይወትና ልማድ ማዳመጥ አይሰለቻትም:: ደርቤ ስለ ራሱ እንዲናገር ለመገፋፋት ስትል ስለ ራስዋ መናገር እንዳለባት አሰበችና፥ ‹‹ታሪኩ ረጅም ነው›› ብላ ጀመረች::

‹‹የመፅሀፍ ማንበብ ፍቅር ያደረብኝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው:: በህፃንነቴ የመፅሀፍ ማንበብ እድል አልነበረኝም:: የሚያበረታታኝም አልነበረም:: ከድሀ ቤተሰብ ነው የወጣሁት:: በድሀ ቤተሰብ ውስጥ መፅሀፍ ማንበብ ቅንጦት ነው:: ዋናው ቁም ነገር የእለት ጉርስ ማባረር ነው. . .

‹‹መፅሀፍ ማንበብ ቀርቶ ትምህርቴንም አቅዋርጬ ቆሎ ስራ እንድይዝ ወላጆቼ ይገፋፉኝ ነበር:: ጥርሴን ነክሼ እንደ ምንም ንግድ ትምህርት ቤት ገባሁ:: እንደ ጉዋደኞቼ ልብስም ጫማም አልነበረኝም:: ያኔ፥ እንደ ጉዋደኞቼ አረጀ በሞትኩ እያልኩ እመኝ ነበር. . .

‹‹ከጉዋደኞቼ በታች ሆኜ ስታይ ስቃይ ይሰማኝ ነበር:: ስቃዩ ስለ በዛብኝ ትምህርቴን አቁዋርጬ ስራ ለመያዝ ቆረጥኩና እንደ ገና ላስብበት ለምን? ብዬ ራሴን ጠየኩ:: ስንትዋ የድሀ ልጅ እያጌጠች ትማር የለም! ከየት ነው ገንዘቡን የሚያመጡት? ከእናቶቻቸው የቆሎ ወይስ የጠላ ንግድ ትርፍ ነው?

አብዛኛዎቹ ጉዋደኞቼ ጌጥ የሚቀያይሩበትን ገንዘብ ከየት እንደሚያገኙ ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም. . .

‹‹በዚያ ስርአት ውስጥ እኔም ገባሁበት›› ብላ፥ ደርቤ ምግቡን ትቶ ዝም ብሎ የሚያዳምጣት መሆኑን በማየትዋ፥ ‹‹ብላ እንጂ›› አለችው።

ደርቤ ፍርፍሩን አፉን ሞልቶ ጎረሰ። ሻይውንም ተጎነጨ። ‹‹በሞቴ›› ብላ አጎረሰችው። ለራስዋም ጎረሰችና፥ ‹‹ታዲያ ይሄውልህ አንድ ሽማግሌ ነጋዴ አጋጠመኝ። ዘጠኝ ልጆች ነበሩት። ልጆቹ በእድሜ ከኔ ይበልጣሉ። አስቀያሚ ነበር። ግን ደግነቱ አይጣል ነው። ርህሩህ ነው። እንደ አባት ያፅናናኛል። የፈለኩትን ይገዛልኛ። ተወኝ። ስራዬ መሽቀርቀር ብቻ ሆነ።

‹‹ሽማግሌው ያለውጣት ሴቶች ሌላ እንደማይሄድና ከብዙ ኮረዳዎች አንድዋ እንደሆንኩ ያወኩ ከጊዜ በሁዋላ ነበር። አንድ ቀን፥ ለምን የልጅ ልጆችዎ ከሚሆኑ ሴቶች ጋር ይወጣሉ? ብዬ ጠየቅሁት። ‹‹የናንተ ወጣቶች ትኩስ ህይወት ያለመልመኝ እንደሆነ በማለት ነዋ! የህይወት እፍታዎች ናችሁ። በናንተ ትንፋሽ መታደስ አለብኝ። ለዚህ ነው›› አለኝ. . .

‹‹ከብረ ንፅህናዬን የሸጥኩት በመታለል ነበር። በህይወቴ እንደዚያን ቀን አልቅሼ አላውቅም። ራሴንም ለመግደል አስቤ ነበር። ድህነት የማያስራው ነገር የለም ብዬ ዝም አልኩ። እናቴ ታማ ሆስፒታል ተኝታ ነበር። ሶስት መቶ ብር ከፍዬ ከሆስፒታል ሳወጣት፥ ‹‹ገንዘቡን ከየት አመጣሽ?›› ብላ አልጠየቀችኝም። እኔም አልነገርካትም። ከሆስፒታል ስትወጣ ትኩር ብላ ተመልክታኝ ስታበቃ እንባዋን አፍስሳ ዝም አለችኝ. . .

‹‹ሽማግሌው እንደኔው በገንዘብ ከገዛት ልጃገረድ ጋር ሲታገል ልቡ ቆሞ መሞቱን ሰማሁ። ህይወቴን ያድስልኛል ብሎ ያሰበው ነገር ሲገድለው አዘንኩለት። ግን፥ ለጥልቅ ሀዘን ጊዜ አልነበረኝም። ከአንድ የባንክ ባለስልጣን ጋር ፍቅር ይዞኝ ነበር።

‹‹ቆንጆ ነው። ወጣት ነው። ሚስትና ልጆችም አሉት። ከሱ ጋር ስንወጣ ውስጤ ሁሉ እንደ ፅጌረዳ አበባ እየፈካ ይፈነዳ ነበር። ከሱ ጋር ስሆን ራሴን መቆጣጠር አልችልም ነበር። ከሱ ጋር ተጋብተን ስንኖር እየታየኝ ስለ

ወደፊት ህይወታችን ፕላን አወጣ ነበር። እሱም እንደዚሁ፥ ‹‹አንድ ቀን አብረን እንኖራለን›› እያለ ተስፋ ይሰጠኝ ነበር. . .

‹‹ከጊዜ በሁዋላ አብረን በወጣን ቁጥር ከወንዶች ጋር ስላለኝ ግንኙነት አጥብቆ ይጠይቀኝ ጀመር። ‹‹ከብርናሽን ማን ነው የወሰደው? ማን ነው የመጀመሪያው ፍቅርሽ? እንዴት ነበር የምትሆኑት? ትወጂው ነበር ወይ? ለምንድር ነበር የምትወጂው?›› እያለ ይወተውተኝ ጀመር. . .

‹‹ዝም ስለው ያኮርፋል። እንዳያኮርፈኝ ደግም አብሬያቸው ስለ ወጣሁት አንዳንድ ወንዶች ስነግረው ይናደዳል። ሊመታኝም ይቃጣዋል።

‹‹ስንተኛ ደግሞ ከማን ጋር ወጥተሽ ነበር። እያለ አውሬ ይሆንብኛል።

‹‹ከዚያ በሁዋላ ተፀፅቶ ማልቀስ ይጀምርና፥ ‹‹ሁለተኛ አይለምደኝም›› ብሎ ይቅርታ ይለምነኛል። ግን ሌላ ቀን ስንገናኝ ተመልሶ ያው ነው። ንዝንዙን አልቻልኩም። እርግፍ አድርጌ ተውኩት።

‹‹በዚህን ጊዜ ትምህርቴን ጨርሼ ነበር። ዲፕሎማ ማግኘቴ ለውዬውን አስረሳኝ። ከእንግዲህ ምን አለብኝ! ስራ ይገፍ ራሴንና እናቴን እረዳለሁ ብዬ በማሰብ አዲስ ተስፋ አደረብኝ። ግን፥ ስራ የማግኘቱ ጉዳይ እንዳሰብኩት ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም።

ገረዲቱ መጥታ ትሪውን አነሳች።

‹‹ስራ የጠየኩት አለቃ ሁሉ መጀመሪያ የሚያቀርብልኝ፥ ‹‹መቼ ይመችሻል?›› የሚል ጥያቄ ነበር። አይመቸኝም ብዬ መልስ የሰጠሁት አለቃ ሁለተኛ አያየኝም። ከኔ ሁዋላ መጥተው ስራ የሚያገኙ ሴቶች እያየሁ በእድሌ አዘንኔ ዝም እላለሁ። ተስፋ የሰጠሁትም አለቃ አብሬው እስከምወጣ ድረስ፥ ጫማዬ እስኪያልቅ ‹‹ታዲያስ?›› እያለ ያመላልሰኛል. . .

ገረዲቱ መጥታ እጃቸውን አስታጥባ ወጣች።

‹‹ስራ ማግኘት ነበረብኝ። እና ‹‹ታዲያስ?›› ከሚሉኝ የቢሮ አለቆች ጋር ከመውጣት ሌላ ምርጫ አልነበረኝም። አንዳንዶቹ እልም ያሉ አታላዮች ነበር።

ሌሎቹ፥ የማይሆንላቸውን ቃል ይገባሉ። በአንድ ምሽት ግንኙነት ሊጋብዟ የሚጠይቁኝም ነበሩ። አይ ያዲስ አበባ ወንድ!

‹‹ግን ምርጫ አልነበረኝም። ለመማር ራሴን መሸጥ፥ ስራ ለማግኘት ራሴን መሸጥ ነበረብኝ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነው ያንን የበሰበሰ ስርአት መጥላት የጀመርኩ. . . በዚያ በበሰበሰ ስርአት ለመዛወር ራስን መሸጥ፥ ለእድገት ራስን መሸጥ. . .

‹‹በመጨረሻ የሸፍን ጉዋደኛ ያዝኩና ይሄውልህ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ስራ አገኘልኝ።››

‹‹የኛ ሸፍ?›› አላት።

‹‹አዎን። የኛን ሸፍ ነው የምልህ።››

‹‹ሸፍም ቢሆን ጉዋደኛው ስራ ባስገባኝ በሁለተኛው ቀን ቢሮው አስጠርቶኝ ከምላሱ ጋር እየታገለ፥ ‹‹ታዲያስ መቼ ይመችሻል?›› አለኝ። ሙከራ ላይ ስለ ነበርኩ እምቢ ልለው አልቻልኩም። እንደ አባ ጨጉዋሬ ይኮሰኩሰኝ ነበር። በህይወቴ እንደሱ ወንድ ጠልቼ አላውቅም። ስድስት ወር ሳይሞላኝ ቁዋሚ ሠራተኛ አደረገኝ። ከዚያ ወዲያ አፍንጫህን ላስ አልኩት. .

.

‹‹ከዚያ በሁዋላ ምን ሊያደርገኝ አስቦ ነበር መሰለህ? ጆሮ ጠቢ። ቢሮው እየጠራ ማን ምን እንደሚለው ሳይጠይቀኝ ውሎ አያውቅም። በዚህም አልተሸነፍኩም። በስንት ሙከራ ነው የተወኝ። አሁን አያነጋግረኝም፥ እንደጠላቱ ነው የሚያየኝ. . .

‹‹ቁዋሚ ሰራተኛ ከሆንኩ በሁዋላ ነው ከእምአእላፍ ጋር የተዋወቅሁት። በፊትማ መቼ ጊዜ አግኝቼ። ሸፍ ብቅ ጥልቅ እያለ ጥዋት በማለዳ፥ ቀን ከምላ በሁዋላ፥ ማታ ከመሸ ከቤቴ አይለይም ነበር። ሁለተኛ ሚስቱ ነበርኩ። ጠጉሬን ለመስራት እንኩዋን ካላስፈቀድኩ አይሆንም. . .

‹‹ቁዋሚ ሰራተኛ ከሆንኩ በሁዋላ የነበርኩበትን ቤት ለቅቄ ወጣሁ። እንዳጋጣሚ እምአእላፍ ጎረቤቴ ነበር። ሁሉጊዜ ላየው መፅሀፍ ከእጁ አይለይም። ከጊዜ በሁዋላ ሰላም ሰላም መባባል ጀመርን። ቆይተን ከሰላምታም

አልፈን ስለ ስራችንም መወያየት ጀመርን። ትዝ ይለኛል፥ አንድ እሁድ ቀን ቤቱ ጋበዘኝ።

‹‹ቤቱ ከመፅሀፍ፥ ካንድ ወንበርና አልጋ በቀር ምንም የለውም። ሻይ አፍልቶ ጋበዘኝና፥ ‹‹መፅሀፍ ማንበብ ትወጃለሽ? ብሎ ጠየቀኝ። አንብቤ አላውቅም አልኩት። በዚህ አለም ላይ አንድ ደስታ አምልጦሻል ማለት ነው። ማንበብ አለብሽ›› አለኝና መፅሀፍ አዋሰኝ። በየቀኑ፥ ‹‹እንዴት ነው መፅሀፉ? አንብበሽ ጨረሺው?›› እያለ ስለሚወተውተኝ፥ በግድ አንብቤ መጨረስ ነበረብኝ። አንብቤ ከጨረስኩ በሁዋላ ስለ መፅሀፉ ብዙ ተወያየን።

Death in Venice የሚል መፅሀፍ ነበር። ደራሲውም ቶማስ ማን ይባላል። አንብቤ መጨረሴን እንጂ፥ ምኑም አልገባኝም ነበር። እምአእላፍ ስለ መፅሀፉ ካስረዳኝ በሁዋላ የድርሰቱ ውበት ታየኝ።

‹‹ሌላ መፅሀፍ አዋሰኝ። እንዲሁ እንዲሁ ስል ከመፅሀፍ ማንበብና ከእምአእላፍ ጋር ፍቅር ወደኩ። ታሪኩ ይሄው ነው›› አለችው።

‹‹አሁንም ትዋደዳላችሁ?›› ብሎ ጠየቃት።

‹‹አዎን፥ አሁንም እንዋደዳለን። ስለ ጋብቻ ተነጋግረን አናውቅም። ሁለት ሚስቶች ማግባት አልችልም ይለኛል - ድርሰትንና እኔን ማለቴ ነው። የሚለው ነገር ስለሚገባኝ አላስቸግረውም። እሱም አያስቸግረኝም።

‹‹አንዳዴ እሱን ለማስቀናት ሳይሆን፥ ታማኝነቴን ለመግለፅ፥ አብሬው ከወጣሁት ወንድ ጋር ምን ሳደርግ እንዳመሸሁ፥ ካንዳንዶቹም ጋር ፍቅር እንደ ያዘኝ ፍርጥ አድርጌ እነግረዋለሁ. . .

‹‹ከህይወት ልምድ ማግኘት ጥሩ ነው። ግን ሰውን ቶሎ ብለሽ የግል ንብረትሽ ለማድረግ አትሞክሪ። በሰዎች መካከል ዋናው ነገር መዋደድ ነው እንጂ ጋብቻ አይደለም። ጋብቻ አንዱ ሌላውን የግል ንብረት አድርጎ የሚይዝበት ተቋዋም ነው። አንድ አልጋ ላይ ጎን ለጎን መተኛት፥ አንድ ጣራ ስር መኖር ብቻ አይደለም፥ የፍቅር ትርጉሙ›› ይለኛል።

ከእምአእላፍ ጋር ስሆን ነፃነት ይሰማኛል። የሚሰማኝን ነገር ሁሉ እናገራለሁ። የምደብቀው ነገር የለኝም። እሱም አይደብቀኝም። ምንም

ሳይደብቅ ይነግረኛል። እንዲህ አይነቱ ሀቅ በስንት ባልና ሚስት መካከል ያለ ይመስልሃል? በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው ፍቅር ተሸፋፍኖ ኑሮ ነው።

‹‹በፊት በፊት ምናባቱ! እያልኩ እቀና ነበር። አሁን ግን ምንም ቢነግረኝ አልቀናም። የሱም ሆነ የኔ ስሜት ይገባኛል። ዋናው ነገር በመካከላችን ያለው ፍቅር ነው። እስክ ህይወቴ ፍፃሜ ድረስ እጠብቀዋለሁ›› አለችና፥ ፍቅሩ ያሞቃት ይመስል ፊትዋ በፈገግታዋ ብርሃን ተሞላ።

ደርቤ ሊገባው አልቻለም። በአላቡ ምን አይነት ፍቅር ነው? ብሉ ዝም አለ። በምትወደው ወንድ የማትቀና፥ በሚወዳት ሴት የማይቀና - ቅናት የሌለበት ፍቅር፥ ፍቅር ሳይሆን በሽታ ነው ብሎ አሰበ። በፍኖትና በአምአለላፍ መካከል ያለው ፍቅር ትርጉም ፈፅሞ ሊገባው ስላልቻለ፥ ራሱን ነቅንቆ፥ እነሱ ናቸው እብዶች ወይስ እኔ ነኝ ደንቆሮ? ብሎ አሰበ።

ፍኖትም በበኩልዋ ስለ ራስዋና በተለይም ከአምአለላፍ ጋር ስላላት ግንኙነት ለማንም ተናግራ ስለማታውቅ፥ ደርቤ ላይጠይቃት በውስጥዋ አምቃ ያኖረችውን ምስጢር ዝክዝክ አድርጋ በማውጣትዋ ‹‹ምን ነካኝ?›› በማለት ራስዋን ወደ መታዘብ አድልታ ነበር። የደርቤን ምስጢር ለማወቅ ያላት ጉጉት የራስዋን ምስጢር አውጥታ እንድትናገር የገፋፋት መሆኑን በተገነዘበች ጊዜ፥ በሰው ተፈጥሮ ከመገረም አልፋ በመፀፀት አልተቆጨችም ወይም በራስዋ አልተናደደችም። እፍ ያለች ሽርሙጣ ነች ብሎ ይገምተኝ ይሆናል፥ ግን ምን ቸገረኝ፥ ስለኔ የፈለገውን ቢያስብ፥ እኔነቴን እንደሆን የሚለውጥ ነገር የለም ብላ ዝም አለች።

‹‹በጣም ግልጽ ነሽ›› አላት።

‹‹አመሰግናለሁ ማለት ይገባኝ እንደሆን አላውቅም። ግልፅ መሆን ብሄራዊ ጠባያችን አይደለም። በልማዳችን ግልፅነት ከወራዳነትና ከአብደት ጋር የተያያዘ ጠባይ ነው። ለኔ ግን ግልፅ መሆን የአስተሳሰብ ነፃነት ምልክት ነው። ስድ አደግ ወይም እብድ ትለኝ ይሆናል፥ አላውቅም። ላንዱ እንደ ሱካር የሚጣፍጠው ሌላውን እንደ እሬት ሊመረው ይችላል። ግን ህይወቱ ነው›› አለችው።

‹‹ግልፅ ነሽ ስልሽ ለማመስገን ነው›› አላት።

‹‹አንተም እንደኔ ግልፅ ከሆንክ ያንን አምባር ለማን እንደ ገዛህ አስቲ እውነቱን ንገረኝ›› አለችው።

ሊዋሸት አልቻለም። ለምን ሊዋሸት እንዳልቻለ አልገባውም። ‹‹ብቻ እንዳልኩሽ ለእህቴ አልነበረም። አምባሩን የገዛሁት ለምወዳት ልጅ ነበር›› አላት።

‹‹ወደደችው? ምን አለች?›› ብላ ጠየቀችው፡

‹‹ምንም አላለችም›› አላት፥ ብስጭት ብሎ።

‹‹ለዚህ ነዋ ሰሞኑን የተለወጥከው! ማን ትባላለች—ብሞቴ?›› አለችው፥ ስሜትዋን ለመቆጣጠር እስከሚያቅታት ድረስ ለወሬ ጉዋጉታ።

‹‹ሂሩት ትባላለች›› አላት፥ ስምዋን መጥራት የሚሰጠው ስሜት ልቡን እያቀለጠው።

‹‹እሺ!›› አለችና ፍኖት፥ ወሬ ለመስማት ከወንበርዋ ላይ ተመቻችታ ተቀመጠች። ጥሩ መፅሀፍ ያገኘች ይመስል ልብዋ ቆሞ ነበር።

‹‹ስምዋ መጥራት እንኩዋን ደስታ ይሰጠኛል›› ካለ በሁዋላ፥ ራቅ ባለ ድምፅ፥ ‹‹ግን ሂሩት ለኔ የተከለከለች ፍሬ ናት›› አላት።

‹‹የተከለከለች ፍሬ›› ብሎ የተናገረው ቃል ደስ ብሎአት በጭንቅላትዋ ውስጥ ቀረፀችውና፥ ‹‹ለምን የተከለከለች ፍሬ ሆነችብህ ልጄ?›› ብላ ጠየቀችው። በፍጥነት አሳቡን በሙሉ አንብባ ለመጨረስ አሰፍስፋ።

‹‹ቤተሰቦችዋ ያሳደጉኝ ባሽከርነት ነው። ግን፥ ጥሎብኝ ከህፃንነቴ ጀምሬ አመልካት ነበር›› ብሎ ጀመረ።

‹‹የቤት አሽከሮች ሁለታችንንም እያያያዙ ሊያሳስሙን ትዝ ይለኛል። ከሰዋ በእድሜ ትንሽ የምበልጥ ብሆንም አብረን አፈር ፈጭተን ነው ያደግነው. . .

‹‹ቤተሰቦችዋ ለሽርሽር ይዘዋት ሲወጡ እስኪመለሱ ድረስ በር ላይ ቆሜ ነበር የምጠብቃቸው። ከሰዋ መለየት አይሆንልኝም ነበር። ትምህርት

ያስጀመሩዋት ቀን ያፈለስኩት እንባ ትዝ ይለኛል። ወጥታ እስክትገባ ድረስ በር በሩን እያየሁ ነበር የምውለው. . .

‹‹ነፍስ ማወቅ ከጀመርኩ በሁዋላ ነው በሁለታችን መካከል ያለው ልዩነት የታየኝና እሽከር መሆኔ የገባኝ። ግን የሚገርመው ነገር፥ ለሂሩት ያለኝ ምስጢራዊ ስሜት ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። የስዋ አሽከር መሆኔ የገባኝ እለት ያ ትርጉም ልሰጠው ያልቻልኩት ስሜት ልቤ ውስጥ ተዳፍኖ መሞት ነበረበት። ግን አልሆነም። አብሮኝ አደገ. . .

‹‹እንዲያውም እድሜ እየጨመርኩ በሄድኩ ቁጥርና የህልውና ልእልና የውበት ድባብ፥ ተፈጥሮ ተአምርዋን፥ ምስጢርዋንና ውበትዋ እስዋን ብቻ መርጣ የምትገልፅባት መስላ ትታየኝ ጀመር። ከስዋ ጋር የመጫወትና የመቦዋረቅ፥ የልጅነት ሱስ ቀስ በቀስ ወደ አምልኮ እየተለወጠ ሄደ. . .

‹‹እግዜርን እንወደዋለን፥ እናከብረዋለን፥ እናመልከዋለን አይደለም መንግስተ ሰማያቱንም እንወርሳለን ይባል የለም? ግን አናቅፈውም አናየውም፥ አንሰማውም። እንደዚያ አይነት ነው ለሂሩት ያለኝ ስሜት - ለስዋ ያለኝ አምልኮ›› ብሎ፥ ከሂሩት ጋር ላንዳፍታ ጋደም ባለበት ጊዜ አምልኮትና ፍቅር ጭንቅላቱ ውስጥ ተጋጭተው መብረቅ የፈጠሩበትን ቀን ዘከረ ‹‹አሁንማ ዞር ብላ እንኩዋን አታየኝም። መኖሬም ትዝ አይላት። አምባሩን ስሰጣት እግዜር ይስጥህ እንኩዋ አላላችም። ስቃይ ነው. . . ስቃይ ነው. . . ገሃነም ውስጥ ነው ያለሁት። ከዚህ የበለጠ ገሃነም ያለ አይመስለኝም›› አላት፥ በምሬት።

ፍኖት የምትለው ነገር ጠፍቶአት ስታስብ. . . ‹‹ለምን ልትረሳት አትሞክርም? በማይሆን ፍቅር ተጠምደህ ለምን ትሰቃያለህ?›› እንዳትይኝ እስዋን ለመርሳት ያልሞከርኩት ነገር የለም። ባይሆንልኝ ነው። ልረሳት አልቻልኩም። እስዋን ለመርሳት ከሴቶችም ጋር አዘውትሬ መውጣት ጀምሬ ነበር። አብሬያቸው ከምወጣው ሴቶች አንዳንዶቹ ሁኔታዬን እያዩ፥ ‹‹ከኛ ጋር ያለህ አይመስለንም፥ ከሌላ ሴት ጋር የምታወራው በኛ ቦታ ሌላ ሴት የምታ ትመስላለህ›› ይሉኛል።

‹‹እውነታችሁን ነው። ልብ ከሌለበት ቦታ አለሁ ማለት ያስቸግራል። ለላ ሌት ለቅሬ የምትታየኝ ሂሩት ናት›› አላት።

ሂሩትን ላስረሳው እኔ እንዴት አልችልም? እሰዋ ማን ናት? ይሄኔ ጭራቸውን በየመንገዱ ከሚቆሰና እንደ ባዶ ጣሳ ከሚንኩዋኩ እንደ ጃፓን እኖ ከሚያብለጨልጩ የአዲስ አበባ ልጃረገዶች አንድዋ ትሆናለች ብላ አስበችና፥ እንዲህ አይነቱ ሰይጣናዊ አሳብ ጭንቅላትዋ ውስጥ በመግባቱ ፊትዋን ታዝባ፥ ‹‹የፍቅር መድሀኒቱ ፍቅር ይመስለኝ ነበር። የሰው መድሀኒቱ ነው ነው ይሉ የለም? ሰው በሰው ይረሳል የሚል ግምት ነበረኝ። የህይወት ውነታ ሁልጊዜ መፅሀፍ ውስጥ እንደ ምናነበው አይደለም›› ብላ፥ አሳቡ ሙቶ ጭንቅላትዋ ውስጥ ስለ ገባ ብቻ በነገርዋ ላይ አከለችና፥ ‹‹የአብዮታችን ፅታ፥ ይዘትና ሂደት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እንደሚታየው እንዳይደለ ሉ›› አለችው።

ስላዘነችለት ይሁን ወይም ለሂሩት ያለውን ጠንካራ ፍቅር ለመጋራት ልጋ እንደሆነ ስሜትዋን ለይታ ባታውቀውም፥ ሂሩትን ላስረሳው እንዴት ንችልም? የሚለው አሳብ ከጭንቅላትዋ አልወጣ ስላለ ተበሳጭታ፥ ‹‹ሂሩትን •ትረሳበት መንገድ መፈለግ አለብን!›› አለችው፥ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ።

መፅሀፍ አንብባ ስትጨርስ ትዝ ከሚልዋት ገፀ ባህርያት ህይወት ኑ ገብታ በነሱ ቦታ በመሆን የምትጨነቀው አይነት ጭንቀት ነበር ሰማት።

‹‹ምን ዘዴ አለ ብለሽ?›› አላት፥ ተስፋ በሌለው ድምፅ።

‹‹እንዴት ዘዴ ይጠፋል!›› ብላ አሳብዋ በየአቅጣጫው ሲጋልብ ከቆየ ፦ላ፥ ‹‹ከአሽከሬ ጋር እንዴት አድርጌ እውጣለሁ ብላ ይሆናል ኮከራው! ሰው፥ ሰው መሆኑን ባታውቅ ነው። ድህነት ቅርስ ወይም ነይ የተደነገልን ህግ አይደለም›› አለችና ትዝ ስላላት፥ ‹‹ስለ ቤተሰብህ ገርከኝም። ለምንድን ነው አሽከር የሆንከው?›› ብላ ጠየቀችው። ሲያስብ ›› ‹‹ይህ አብዮት ባይመጣ ኖሮ ድህነት የአርባ ቀን እድል ነው የሚል ት ይዜ እሞት ነበር›› ብሎ ሲያበቃ፥ አይኑን ከፈነዳው ፅጌረዳ አበባ ላይ

አሳርፎ፥ ‹‹አየሽ፥ አባቴና እናቴ የሞቱት ጡት ጠብቼ ሳልጠግብ ነው። አባቴ እንዴት እንደ ሞተ ልንገርሽ. . .

‹‹የሞተበትን ምክንያት ያወኩት ካደኩ በሁዋላ ነው። አባቴ ጪሰኛ ነበር። ታዲያ በእጁ አብልቶ ያሳደገው ልክ እንደኔ የሚወደው አንድ ነጭ ሙክት ነበረው። ሰሞኑ የፋሲካ ሰሞን ነበረና ባለርስቱ ይመጣና ያንን ሙክት ካልወሰድኩ ይለዋል - አባቴን - አባቴ ደግሞ አልሰጥም ብሎ ድርቅ ይላል. .

.

‹‹አባቴ እልም ያለ ደረቅ፥ ጠምዛዛና አንዴ የተናገረውን ቃል፥ ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ቢል የማያጥፍ ሰው ነበር ይባላል። ካባቴ ድህነቱን ነው እንጂ ጠባዩን አልወረስኩም። ለዚህ ነው የማልቆርጠው. . .

‹‹ለማንኛውም ነገር፥ ሙክቱን ስጠኝ አልሰጥም ሲባባሉ፥ በመሃሉ ነገሩ ይከርና ባለርስቱ ተናዶ በጉን በሀይል ይነጥቅና ባሽከሮቹ እያስጎተተ መንገዱን ይቀጥላል። አባቴ ቤት ገብቶ ጣምራ ጦሩን ይዞ ሲገሰግስ ይደርስና፥ ባለ ርስቱን አንጀቱን ዘክዝኮ ጥሎ ጫካ ይገባል. . .

‹‹አባቴ ጫካ በገባ ማግስት የወንበዴ ቤተሰቦች በመባል ከኖርንበት መሬት ተነቅለን ተባረርን። ከስድስት ወር በሁዋላ አባቴ በነጭ ለባሾች ታድኖ ተገደለ። ሬሳው መጥቶ ጪቾ ላይ በገበያ ቀን ሲሰቀል ትዝ ይለኛል›› አላትና ይተናነቀው የነበረውን እንባውን ለመግታት መሀረም አውጥቶ አይኑን አፍንጫውን አባበሰ።

ፍኖት ግን ስሜትዋን ለመቆጣጠር ስላልቻለች ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች። ደርቤ ከመቀመጫው ተነስቶ ወደስዋ በመሄድ ትከሻዋን ይዞ ‹‹ምንም አይደለም፥ ያረጀ ታሪክ ነው›› እያለ ሲያባብላት፥ በድንገድ ለቅሶዋን አቁዋርጣ ከተቀመጠችበት ተነሳችና እቅፍ አድርጋ ግንባሩ ላይ ሳመችው።

የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት አቅፎአት ቆሞ ቀረ።

በረጠቡት አይኖችዋ ቀና ብላ እያየችው፥ ‹‹ደስ ትለኛለህ፤ እንደ ጥ መፅሀፍ ነህ፤ ህይወት ያለው መፅሀፍ ነህ። ከእንግዲህ ከጭንቅላቴ ውስ አትጠፋም›› አለችውና፥ አዲስ አላብ መጥቶ አእምሮዋ ውስጥ ስለገባ፥ ‹‹ለ

ለዚህ አብዮት መታገል አትጅምርም? ስቃይ፥ ግፍ፥ ፍቅር፥ ርሀራሄ፥ ትህትና ምን እንደሆነ የምታውቅ ይመስለኛል። እና ጥሩ አስተዋፅኦ ልታደርግ ትችላለህ። አይመስልህም?›› ብላ በአይኖችዋም ጭምር መላቅ ጀመረች።

ተገርሞ፥ ‹‹ምን ያደርግልኛል ብለሽ ነው? አላት።

‹‹አሳብክን ወደ ሌላ ነገር ሊመራ ይችል እንደሆን ብዬ ነው።››

‹‹ሂሩትን ሊያስረሳኝ ይችላል ብለሽ ነው? ትቀልጃለሽ መሰለኝ. . .››

‹‹ቀልዴን አይደለም። ያብዮትና ያገር ፍቅር ከማንኛውም ፍቅር ይበልጥ ጠንካራ ነው። እና፥ አንድ አብዮተኛ ሊኖረው የሚገባው ጠባይ ያለህ ይመስለኛል። ጊዜህን በከንቱ አታጥፋ። የቀይ ኮከብ ጥሪን ተቀበል። አንድ ቀን ለው ስትሆን ሂሩት ወዳንተ ትመጣ ይሆናል›› አለችውና፥ በአይንዋ ጭምር እየላቀች ፍንጭትዋን አሳየችው።

አንብባ ከጨረሰች በሁዋላ እንደ ዘጋችው መፅሀፍ አድርጋ አልቆጠረችውም። እንዲያውም የሚቀጥለው ታሪክ አካልና ደራሲ እንደሆነች ያህል ነበር የተሰማት። የመጀመርያዬ መፅሀፍ ብላ አሰበች። ታሪኩ እየተዘረጋ ሊሄድ በአይነ ህሊናዋ ታያትና ፈገግ አለች። ስሜትዋን ለመቆጣጠር አልቻለችም። ተጠመጠመችበትና ሳመችው።

ያን ሌሊት ደርቤ እንቅልፍ አልወሰደውም። ህይወቱ አንድ ወሳኝ ምእራፍ ላይ የደረሰ መሆኑ ቢሰማውም፥ ምን አቅጣጫ እንደሚይዝ ወይም ወዴት እንደሚያመራ ቁልጭ ብሎ አልታይ ስላለው ነበር እንቅልፍ እምቢ ያለው።

ስለ ሂሩት ባሰበ ቁጥር ስቃዩ ሆዱ ውስጥ እየተገላበጠ፥ የእምአእላፍ ቲአትር መሪ ተዋናይ ራሱን ሲሰቅል በታየው ቁጥር እየተናደደና ሰው አሆናለሁ ብሎ ‹‹የሽፎ›› መሳሪያ በመሆን በፈፀመው ሁሉ ራሱን መልሶ አየታዘበና በአድራጎቱ እያፈረ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ከፍናት ጋር ያሳለፈውን ጊዜ በማስታወስ ‹‹ምን አይነት ውብ ፍጡር ናት! ለካ በሰዎች መሃከል እንዲህ አይነት ፍቅርም አለ!›› በማለት እየተደሰተና ቃላትዋን ሁሉ በማስታወስ እያመነዠካቸው፥ ‹‹ለምን ለዚህ አብዮት መታገል አትጀምርም?. .

. ያብዮትና ያገር ፍቅር ከሁሉም ይብልጥ ጠንካራ ነው፡፡ ያለችው ጭንቅላቱ ውስጥ እንደ መረዋ እየደወለ፡ ቀይ ኮከብ እየታየው፡ ሰማዩ በቀይ ኮከብ አጊጦ እየታየው፡ እንዲሁ ሲገላበጥ ነበር ያነጋው፡፡

ጎህ ቀዶ ወፎች ዝማሬአቸውን ሲጀምሩ፡ እውነት ለምን አብዮቱን አላገለግልም? እንዳለ፡ አባቱ ወንበዴ ተብሎ ከተሰቀለበት ገመድ ተንጠልጥሎ ሳይሆን፡ በፍናት ፅጌረዳ አበባ ተክሎች መሃል ቆሞ ሲስቅ ታየው፡፡ ከዮት ይሆን የምጀምረው? ብሎ እንደ ጉልቻ የጋለውን ጭንቅላቱን ይዞ ሲያስብ ቆየ፡፡ የሰፈሩ ቀበሌ ታየው፡፡

ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ይዞት ሄደ፡፡

ምእራፍ ፮

ጌታቸው የሸዋሉል፥ የአጥንቱ መገጣጠሚያዎች እየተጋጨ እንዲሰነምሙት ወይም ዘይት አጥቶ እንደ ደረቀ መዝጊያ ሲጥ ሲጥ እያሉ እንዲያሳሙት የሚጠነቀቅ ይመስል እርምጃዎቹን እየቆጠረና እየተንሳፈፈ የሌሊት ልብሱን ለብሶ ብቅ ባለበት ጊዜ፥ ትእግስት ስልኩን ዘግታ ፊትዋን ያራሰውን እንባ ለመጥረግ ፋታ አላገኘችም ነበር።

ባልና ሚስት ከአንድ ባህር ይቀዳሉ እንዲሉ፥ እርሰዋም እንደ ባልዋ ለውነትዋ እንደ ጅማት ከርሮ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ ባዶ ስልቻ መሰላ ትታያለች። እንባ ባቀረሩት አይኖችዋ ያው እንደ ልማድዋ በእናትነት ርህራሄ ተመለከተችው። የለበሰው የሌሊት ልብስ፥ ሱሪው፥ ሸሚዝና ኮቱ፥ ከአንድ አይነት ጨርቅ የተሰፋ ሆኖ፥ ግራጫና ጥቁር ቀለማቸው ሽበት እንደ ጉድ ከፈላበት ሥጋ ፀጉሩ ጋር ይነፃፀራል። ቀይ ፊቱ ገርጥቶአል። ረጅም ቁመናው ጎብጦአል።

የሌሊት ልብሱ ግን እንደ ጨው ሙዋሸ ያለቀ ሰውነቱን ይባስ ብሎ ለጋለጠው፥ የደረቱ አጥንት ምርጊቱ እንደ ፈረስ ማገር ገጥጦና አፍጥጦ ይታይ ነበር።

እጆቹን ከፒጃማው ኪሶች ውስጥ ከትቶ፥ ንፋስ እንደ መታው ዛፍ እየተወላወለ፥ «እኔ ካንቺ. . . እ. . . ፍቅርና አክብሮት ነው እንጂ. . .እ. . . ርህራሄ አልፈልግም! እኔ ነኝ በዚህ አውር ደንቆሮ አለም የማዝነው። አለም እንዲያዝንልኝ ወይም ማንም በርህራሄ እንዲመለከተኝ አልፈልግም» አላት፥ ትናንሽ አይኖቹን ብልጥጥ አድርጎ። እልከኛ ልቡን በግራ እጁ መታ መታ እያደረገ ቀስ ብሎ የሚናገር ቢሆንም፥ ትእግስት ቃላቱ አላመለጥዋትም።

እንደ ተጋጠ አጥንት ያገጠጠው የትእግስት ፊት ከርህራሄ ሌላ ምንም አይፈነጥቅም ነበር። በምታለቅስበት ጊዜ እንኩዋን፥ እንባዋን በዝምታ ከማፍሰስ በቀር ስቃይ ከፊትዋ ላይ አይነበብም። ስሜትዋን የአእምሮዋ ተገዥ ከማድረግ ከፋኛ አምቃ ብትይዘውም ቅሉ፥ ዝምታዋና ፀጥታዋ የሰውን መንፈስ ከሚረጋጋት ይልቅ መንፈስ አውኮ ይረብሻል፣ እንደ እሳተ ገሞራ ድንጋት ትፈነዳ ይሆን? የሚል ስጋት ያሳድራል። በዚያ ላይ በጣም አይናፋር

በመሆንዋ፥ ቀና ብላ ሰውን በሙሉ አይንዋ አትመለከትም። ሆኖም፥ ህይወት የሌለውን ፈገግታዋን እያሳየች ላንዳፍታ ቀና ብላ ሰውን ስታይ፥ አይናትዋ ወደ ውስጥ ዘልቀው ያለውን ጉዞ መዝነው ሰመመልከት የሚችሉ ስለሚመስሉ፥ የመንፈስ እረፍት አጥቶ ውስጥ ውስጡን የማይቁነጠነጥ አልነበረም።

ትእግስት ለባልዋ መልስ አልሰጠችውም። ድሮ ቢሆን ግን ስንቱን በተናገረች ነበር። ድሮ. . .ድሮ. . .የጌታቸውን ጠባይ አርቃለሁ በማለት፥ ጥሬ ግራ ወጥታ ወርዳ በፍቼ አስፈራርታ፥ በፍቅር ደልላ፥ መክራ አስመክራ ለፍልፋና አልቅሳ ተስፋ ከመቁረጥዋ በፊት እንኩዋን ቱናግሮለት ሳይናገራትም፥ «ባንተ ምክንያት ነው ከሰውነት የወጣሁት. . . አንድ ቀን ሳልደሰት፥ እንደ እኩዮቼ ለብሼ ሳሳጌጥ፥ ከሰው በታች ሁኜ ወድቄ የቀረሁት ባንተ ምክንያት ነው እንጂ፥ የአግራ አጣቢ ልትሆን እንኩዋን የምትችል ሴት የለችም! ግን አንተ ምን ታደርግ! እድሌ ነው ከሰው በታች የጣለኝ እድል የጨርቅ አይነትና ጌጥ እንዳላማረጥኩ ሁሉ ዛሬ. . .ወች ጉድ. . .አሆሆ. . .የምለውጠው ጫማና ቀሚስ አጥቼ ከቤት ውስጥ ተዘግቼ. . .እ. . .የጉዋ ሚስት. . .እ. . . የጉዋዳ ሚስት ሁኜ. . . ሳሳፈጅ አርጅቼ ከሰውነት ወጥ የቀረሁት. . .» እያለች እንደ መትረየስ በመንጣት፥ ባንድ ፊት እልኩን ወ ከአለቆቹም ሆነ ከጭፍሮቹ ጋር በመስማማት እንዲሰራና መጠ እንዲተው፥ በአንፃሩም እንደ እቃ ሳይሆን እንደ ሚስቱ በአክብሮት እንዲደ በማሰብ የንትርክ ዶፍ ባወረደችበት ነበር! ዛሬ ግን፥ እርሱን ጠባይ አቀና ብሎ የሞከረ ሁሉ ራሱ ጎበጠ እንደ ቀረ በመገንዘብ፥ ንትርክዋን እርግ አድርጋ ትታ ራስዋን የእርሱ ፈቃድ ተገዥ በማድረግ ነገር አለሙን ከተ ብዙ ዘመን አልፎአታል።

የሚገርመው ነገር፥ ራስዋን የእርሱ ፈቃድ ተገዥ ማድረግ በጀመረች ጊዜ ነበር ጋብቻቸው ከባድ ፈተና ላይ የወደቀው። ጨቅጫቃና ነ በነበረችበት አፍላ ዘመን እንዳረጀ ሽክላ ደግሞ ደጋግሞ፥ «አትጨቃጭ ለምን እንደዚህ እንደምሆን ልትረዲልኝ አልቻልሽም!» እያለ ሚስቱ ማ ባለመረዳትዋ በመበሳጨት በስኳር ላይ ስኳር ሲጨምር እንዳልና በየምሽቱ ሰክሮ እየተንገዳገደ ሲገባ በመቆጣት ፈንታ፥ «ጌቱ፥ ደህና መ

ግባ፤ ርቦሃል? ራት ትፈልጋለህ? ያ የምትወደው ጥሩ ፍርፍር አለ። ስለምትለው፥ አልፎ አልፎም ሰይጣኑ መጥቶ በተኛ ቁጥር በመጨቅጨቅ ፈንታ ዘም ብላ ስለምትመለከተው፥ ለኔ ከአንግዲህ እከብሮትም ሆነ ፍቅር የላትም፤ ብኖርም፥ ብሞትም ለእኔ ደንታ አይኖራትም በሚል ግምት ጠዋት ማታ ተብከንክኖ እየተበሳጨ የባሰውኑ ጠጭ ሆኖ ነበር። ከጊዜ በሁዋላ፥ ባለቤቱ የፈቃዱ ፍፁም ተገዥ ብቻ ሳትሆን፥ የነፍሱን ጭንቀትና ማንነቱን እውቃ የተረዳችበት፤ ከዚህም የተነሳ የምታፈቅረውና የምታከብረው መሆንዋን ከተገነዘበበት ቀን ጀምሮ፥ በባልና ሚስት መካከል ፍፁም የመግባባት መንፈስ ሰፍኖ ይኖሩ ነበር። ችግሩ፥ ከሚስቱ ሌላ ማንነቱን የሚያውቅለት የለም። እና ለዚህ እውር ደንቆሮ ነው ለሚለው አለም እጅግ አድርጎ ያዝን ነበር።

ቆም ቀርቶ ከወራጅ ውሀ ውስጥ እንደ በቀለች ሰንበሌጥ መወላወሉን የቀጠለ መሆኑን በመመልከት፥ ‹‹ጌቱ፥ ቁጭ አትልም፥ እንዴ? ርቦህ እንደሆነ ፍርፍር አሙቄ ላቅርብልህ›› አለችው ለጀሮ ደስ በሚል ሙዚቃዊ ድምፅዋ። ለረማመድዋ ልክ እንደ ባልዋ ሬጋ ያለ ሊሆን፥ አነጋገርዋም ዝግ ብሎ ለዛ ያለው ነበር። ለውነትዋ መንምኖ፥ የከረረ ጅማት ብትመስልም ቅሉ፥ በዘመንዋ በአይኑ ያያት ሁሉ በልቡ እየተመኛት የሚራኮትባት የውበት ዳርቻ ነበረች። እውነትም በመጣትነት ዘመንዋ የውበት ዳርቻ እንደ ነበረች የለውነትዋ ቅርፅና የፊትዋ አወራረድ ይመሰክራል።

ሊጋራ አውጥቶ አቀጣጠለና፥ የሲጃራው ጫፍ ፍም መስሎ ቦግ እስኪል ደረስ ልምጥጥ አድርጎ ስቦ ጢሱን ወደ ላንባው ምሳ ሊያበቃ ቡልቅ ካደረገው በሁዋላ፥ ‹‹ፍርፍሩን ትተሽ የምጠጣውን ስፈጪኝ›› አላት፥ ትእዛዝ በተሞላበት አነጋገር። ምን ጊዜም ቢሆን፥ ፍላጎቱ ትንሽም ይሁን ትልቅ፥ ፊፅሞ እንደማይጣስ ወይም እንደ ማይሻር ጥብቅ ትእዛዝ ታይቶ መከበር ነበረበት። የትእግስት ሁኔታ ከወትሮው የተለወጠበት መሆኑን በመገንዘብና እንደ ሌላው ሁሉ እርስዋም መደንቆር ጀምራ ይሆን የሚል ግምት በመውሰድ፥ ‹‹ሰምተሽናል?›› አላት። ሲናገር ለው የሚሰማው አይመስለውም፤ በለምች ጀሮ መደንቆር እየተናደደ። አለም ጀሮውን ከፍቶ ለምን እንደማያዳምጠው ፊፅሞ ስለማይገባው እውር . . . ደንቆሮ አለም! እያለ ዘወትር ይናደዳል፤ ይሰላቻል፥ . . ይጠላል።

ቀኑን ሙሉ እህል ያልቀመሰ መሆኑን ስለምታውቅ፡ ‹‹ትንሽ ፍርፍር ብትቀምስ ምናለበት? አለችው፡ ግማሽ ጠርሙስ ውስኪ ከብርጭቆ ጋር ከክብ የሳሉን ጠረጴዛ ላይ እያኖረችለት።

‹‹ሴትዮ፡ ምን ነክቶሻል? የቀበሌ ተኩስ አሳብዶሻል መሰለኝ!›› አላት። ሰይጣኑ ሲነሳበት እህል አይቀምስም። ሰይጣኑ ሲነሳበት ከእህል ጋር ብቻ ሳይሆን የሚጣላው፡ ከራሱም፡ ከአለምም፡ ከሁሉም ጋር እንደመሆኑ መጠን ራሱንም፡ አለምንም፡ ሁሉንም ያኮርፋል። የማያኮርፈው ነገር ቢኖር ጠርሙሱን ብቻ ነበር። ከእህል ጋር እምብዛም አይፋቀሩም። ከራሱም አልፎ ምግብ ለሚወድ ሰው አክብሮት አልነበረውም። ‹‹ሆዳም ሰው አይታመንም›› ይላል።

እግሮቹን በሚገባ ከወለሉ ላይ ተክሎ ቀጥ ብሎ መቆም ስላቃተ እየተንገዳገደ ሂዶ ቁጭ አለ። የክፍሉን አብዛኛውን ቦታ ይዘው የሚታዩት ጌታቸው በኩራት፡ ‹‹በዚህ አለም ያሉኝ ቅርሶች›› የሚላቸው መፃህፍት ነበሩ ክፍሉ እንግዳ ቤት መምሰሉ ቀርቶ፡ ትንሽ ቤተ መፃህፍት መስሎ ይታ ነበር። ውስኪውን በሚንቀጠቀጥ እጁ ከብርጭቆው ወገብ ድረስ ቀድ በትንሽ አምቦ ውሀ በመብረዝ ፉት ካለ በሁዋላ፡ ‹‹እንቅልፍ እምቢ አለ እንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም። የሰላም እንቅልፍ የሚተኙ የታደሉ ናቸ አለ።

ብልጭ ሲልበት ለተከታታይ ቀኖች እንቅልፍ የሚሉት ነገር በአ አይዞርም። ያበሳጨውን ነገር መልሶ፡ ቀልሶ፡ ደግሞ ደጋግሞ እንዳረጀ በማንጎራጎር፡ ባንድ ጎኑ ተኝቶ ከውስኪው ጠርሙስ ጋር ግብግብ ይጀምራ ወይም ከእርሱ ወይም ከጠርሙሱ አንዳቸው ተሸንፈው እስኪወድቁ ድረስ.

‹‹እንደ ፍየል ጭራ ገበና የማይሸፍን. . .›› አለ።

ትእግስት አባባሉን ቢያንስ መቶ ጊዜ ሰምታ ነበረና፡ ከቁም አልቆጠረችውም። ያ በውጫዊ እርጋታ፡ ሰላምና ፀጥታ ታፍኖ ይኖር የ ውስጣዊ ውጥረትዋ እንደ እሳት ገሞራ ሊፈነዳ ፈልጎ እየተና አስቸግሮአት ነበረና፡ ትእግስት የወትሮዋ አልነበረችም። ይህ ነው፡ ወይ ው ብላ ትርጉም ልትሰጠው ያልቻለችው ፍርሃት አድሮባት ስለ ነበረ፡

በለማች ቁጥር ልብዋ እስኪሰዳት ድረስ እየደነገጠች ትበረግጋለች። ግን፥ ልብዋ ያለበሰውን ከመናገር ይልቅ አሳብዋን ለውጣ፥ ‹‹እትዬ ደውሰው ነበር›› አለችው።

‹‹ምናባትዋ ትፈልጋለች? እኔ መሬት አልሆንላት!›› አሉ፥ ጉሮሮው ውስጥ ቃላቱን እያፈኑ።

በእህቱ በወይዘሮ አምሳለ የሸዋሉልና በእርሱ መካከል የመግባባት መንፈስ ተፈጥሮ አያውቅም። ወይዘሮ አምሳለ ኩራቱን፥ ልበ ሙሉነቱን፥ ብልህነቱንና እንከን የማወጣለትን ችሎታውን በማድነቅ፥ ባይጠጣ ኖሮ በችሎታስ ከአግሩ እጣቢ የሚደርስ የለም›› እያሉ ቢያደንቁትም፥ ግትርነቱን ባስታወሱ ቁጥር ደግሞ፥ ‹‹እጁን አንዴ ከነከሰ አይለቅም፥ አውሬ ነው! የናት ሆድ ሻንጉርጉር ነው እቴ!›› በማለት፥ የእሱን ጥፋት፥ አውሬነት፥ ራስ ወዳድነት፥ ዘመድ መጥላትና ብቸኝነት፥ ከእርሳቸው ደግነት፥ የዘመድ መውደድና ቸርነት ጋር እያነፃፀሩ፥ ምላስ ስራ ሲፈታ ዘመድን ያማል እንዲሉ፥ ቡጭቅ አድርገው ያሙታል - ቤታቸው ለመጣው ሁሉ። ወሰፋቱ ተከፍቶ ትንሽ አህል በሚቀምስበት ጊዜ፥ በእጁ ከመብላት በሄደበት ሁሉ መልካም ጣት ያላቸው ሴቶች ቢያጎርሱት ይመርጥ ነበር። ‹‹እንደ እህቴ ጥሩ ፍርፍር የምትሰራና ጥሩ ጉርሻ የምታጎርስ ሴት በዚህ አለም የለችም!›› ይል ነበር፥ በእህቱ ሙያ ተኩራርቶ።

ከትእግስት መልስ ጠብቆ ሳያገኝ በመቅረቱ ደንግጦና፥ ‹‹እኔ መሬት አልሆንላት! ለምን ትደውላለች?›› አላት፥ አገጩን ወደ ውስጥ ቀብሮ።

እየደጋገመ እኔ መሬት አልሆንላት! ያለበትን ምክንያት ስለምታውቅ፥ እርሱም በልቡ ስለሚያውቅ፥ ትእግስት መልስ ለመስጠት አልፈለገችም ነበር። ከአባታቸው የወረሱትን ሰላሳ ጋሻ መሬት እኩል መካፈል ሲገባቸው፥ አልፎ አልፎ አህልና ጥራጥሬ አስጭነው ከቤቱ ድረስ ከመላክ ሌላ፥ ሽጦ ይጠጣበታል በሚል ሰበብ፥ ለመተዳደሪያ እንኩዋን ይሁነው ብለው አንድ ጋሻ መሬት አልሰጡትም። እሱም አልጠየቃቸውም። ለመሬት ደንታ አልነበረውም። ጭንቅላት ወይም ጉልበት ሰርቶ ካፈራው ሀብትና ክብር ሌላ፥ መወለድና ውርስ ላስገኘው ሀብትና ክብር ምንም አይነት ዋጋ ስለማይሰጥና

ስለሚንቅ፥ ከእማማና ከአባባበ በተወረሰ ሀብት በትእቢት ተወጥረው መሬት ለመርገጥ ይፀየፉ የነበሩ አንዳንደ እኩዮቹ ውስኪ ሲጋብዙት፥ ከንቀቱ የተነሳ ቢሞትም ግብዣቸውን አይቀበልም ነበር። ‹‹እናንተ ሚኒ ፋሽስቶች የምትጠጡት እኮ ውስኪ አይደለም - - የጭሰኞቻችሁን ደም ነው። ይህ የያዛችሁትም የሚገማ ቱባ ቱባ ብር ከሰውነታቸው የተቦጨቀ ስጋ ነው›› ይላቸው ነበር። በመወለድ፥ በአምቻ ጋብቻ ግንኙነት፥ በዘረኛነትና በሃይማኖት በኢኮኖሚ ይዘቱ ደግሞ በመሬት፥ በቤት ኪራይና በሽርክና ንግድ ላይ ተመስርቶ ሊኖረው የሀይለ ስላሴ መንግስት የነበረው ጥላቻና ንቀት ይህ ነው ተብሎ አይገመትም ነበር። ብርጭቆውን በጨበጠ ቁጥር፥ ‹‹ይህ የሸርሙጣ መንግስት›› ከማለት ተቆጥቦ አያውቅም።

ትእግስት ያደረባትን ፍርሃት ለመደበቅ አልቻለችም። ‹‹ጌቱ፥ አየሁ፥ እ. .መቸም እኔ ካንተ የበለጠ አላውቅም፥ ግን ጊዜው የተለወጠ ይመስለኛል. . .›› ብላ ለመናገር ከፈለገችው ነጥብ ላይ ሳትደርስ አቁዋረጣትና፥ ‹‹እኔ ግን አልተለወጥኩም። እኔን የሚለውጠኝ ነገር በዚህ አለም የለም። ቲጊ፥ ታውቂኝ የለም እንዴ?›› አላት፥ ልቡን በግራ እጁ መታ መታ እያደረገ። ሚስቱን በሙሉ ስምዋ ጠርቷት አያውቅም። ቲጊ ነበር የሚላት።

ረጋ ብላ በለዘበ አንደበትዋ፥ ‹‹አምን. . . አልተለወጥክም፥ ብቻ . . . ጠዋት ተነስተህ ስራ ብትገባ ይሻላል ብዬ ነው›› አለችው፥ አቀርቅራ መሬት መሬት እያየች።

‹‹የውይይት ክበብ አባሎች ስራውንም ስልጣኑንም ወስደውታል። እኔ ምን ላደርግ እዬዳለሁ? ስራም ስልጣንም የለኝም!›› አላት፥ አኩርፎ የተኛበትን ምክንያት በከፊል ገልፆ። በስልጣኑ ቀናተኛ ነበር። በምንም መንገድ ስልጣኑ ሲነካበት አይወድም። ይበሳጫል፥ ይቆጣል፥ ያኮርፋል፥ እና ይጠጣል። ስልጣኑ ሲነካ እንደ ነበር ተቆጥቶ ራሱን እስከ መጉዳት የሚደርሰው፥ መንማናና ደካማ በመሆኑ በስልጣን ጡንቻ ተጠቅሞ አካላዊ ጉድለቱን ለማካካስ ስልጣንን የእልሁ መወጣጫና የቂም በቀል መቅረፊያ መሳሪያ ለማድረግ ነው፥ በማለት ከበስተጀርባው የሚያሙት ቢኖሩም፥ እርሱ ግን በበኩሉ፥ ስልጣኔ ሲነካ ወይም እኔን ሳያማክሩኝ ከበስተጀርባዬ አንድ ነገር በክፍሌ ውስጥ ፈፅመው ሲገኙ የምናደደው ለስልጣን ስለ ስልጣን ብዬ ሳይሆን፥ አስተዳደራዊ ዘ

ስርአት ለምን ይጣሳል? ለምን ስርአት አይከበርም? በሚል እምነት ነው ይል ነበር–አዘዉትር።

‹‹እኔ እኮ የምናደደው›› ይላል አንዳንዴ፥ ‹‹ሰነ ስርአት እንዲከበር ከውይይት ከበብ አሳሉች ጋር ፊት ለፊት ስጋተር፥ የቅርብ አለቆቼ፥ የአብዮት ጊዜ ነው፤ ለፊውን ሕዝብ እኛ እናውቅልሃለን የምንልበት ጊዜ አልፎአል ወዘተ በማለት ከውይይት ከበቦች ጋር ቂጥ ለቂጥ ገጥመው እኔን ሲያጋልጡኝ ነው። እኔ ግን የውይይት ክበቦች በአስተዳደሩም፥ በፖሊሲውም በማንኛውም ነገር እጃቸውን እንዲያገቡ ማበረታታት ስርአት አልበኝነትን መጋበዝ ነው እላለሁ። ራሱን የሚያከብር አብዮታዊ መንግስት ተሹዋሚዎቹን አክብሮ ማስከበር አለበት፤ አለበለዚያ ተጠሪነታችን ለማን ነው? በማለት ዘወትር ይሰሳጫል፥ ይናደዳል፥ ያኮርፋል፥ ይጠጣል። ከሁሉም የባሰ አበሳጭቶ የሚያስጠላው ግን በእርሱ ግምት የበላዮቹ ብልጭ ሲልባቸው በድንገት ተነስተው የሚሰጡት ሱሪ በአንገት አውልቅ አይነት ትእዛዝ ነበር። በእቅድ. . . በፕላን. . . በጥናት. . . በምርምር. . . በጥራት. . . በጥልቀት. . . ወዘተ በሕርጋታና በዝግታ መስራት ነው የለመደው እሱ። ምንም እንኩዋ በጣም ፈጣን አእምሮ ቢኖረውም፥ ሲጨበጡም ሳይጨበጡም የሚችሉ፥ ሁሉም ነገሞ አጣዳፊ የሆኑ ብዙ ስራዎቸ ባንድ ጊዜ ሲታዘዝ የሚይዘውና ምጨብጠው እየጠፋው፥ ከመጠን በላይ ይናደድ፥ ይበሳጭ፥ ያኮርፉ፥ ይጠጣ ነበር። አንዳንዴ ሲብስበት ከአገሩ ወጥቶ ለመኮብለልም ነሽጥ ያደርገውና፥ ዶርጠ ለመነሳት ሆዱ እምቢ ሲለው ከዚች ከምወዳት ኢትዮጵያ ወጥቼ ስላም ነግኛቼ የመኖር ተስፋ ፈፅሞ አይታየኝም፥ ጭንቀቴም ሆነ መቃብሬ እዚሁ ንሆናሉ ይልና በውስጣዊ ቅራኔ ተወጥሮ ይናደዳል፥ ይበሳጫል፥ ያኮርፋል፥ ጎጠጣል።

‹‹ይገባኛል። ግን. . .›› አለች ትእግስት

‹‹ጡረታ መውጣት ነው። ሌላ ምን ይመጣል?›› አላት።

‹‹መታሰርምኮ አለ ጌቱ፥ ስንት ጠላቶችና ምቀኞች አሉብህ! ይህን ሆወቅህ በግርግር ጊዜ ዱላ ለምን ታቀብላቸዋለህ?››

‹‹እንደ ፍየል ጭራ ገበና ከማይደብቁ አለቆችም ጋር መስራት አልችልም፣ በጥፋታቸው የቀጣሁአቸው ሰራተኞች በየውይይት ክበቡ አድሃሪ ቢሮክራት እያሉ ሲጨፍሩብኝ ዞር ብሎ ከእነርሱ ጋር ከሚያቶከቱክ አለቃ ጋር መስራት አልፈልግም። ቢራ ካራጁ ጋር ይውላል ይባላል። ከፍየል ጭራ ጋር. . . ጭራውን ከሚቆላ አለቃ ጋር ለመስራት አልፈልግም። ገባሽ ቲጊ?. . .››

‹‹ገብቶኛል፥ እኔስ መቼ አጣሁት አለቃህን። ያህያ ውሀ ጠጪ ነው። በጥርሱ ቢስቅም ልቡ የሚገኝ ሰው አይደለም. . .››

‹‹ልብ ሰለሌለው ነው።››

‹‹እኔ አሁንም ጠዋት ተነስተህ ሥራ ግባ ነው የምለው። ለምቀኞች በገሃ እጅህ ዱላ ማቀበል ደግ አይደለም። ያጠፋሃል ብዬ ነው የምሰጋው. . .››

‹‹ምቀኝነትንና የግል ፍላጎትን ከመደብ ትግል ጋር እያስታከኩ ለማወናበድ የሚሞክሩ በዝተዋል። እኔ. . .እኔ ግን አልፈራም፥ አላጎብስም. . . ለማንም. . . ደግሞ አድሃሪ አይደለሁም። ስርአትና ዲስፕሊን ይከበር ማለት አድሃሪ አያሰኝም። እኔ አድሃሪ ነኝ እንዴ ቲጊ? አድሃሪ እመስላለሁ?››

‹‹ለምን እልህ ትገባለህ?›› አለችው።

ቂመኛ መሆኑን ታውቃለች። ስልጣኑን በመጋፋት ክብሩን ከነኩበት እጅግ አድርጎ የሚቆረቆርለትን ክብሩን ከነኩበት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ. . .ጊዜና ሁኔታን ጠብቆ ባለው ስልጣን በመጠቀም ሳይኮረኩም ወይም አፈር ድሜ ሳያገባ አይመለስም ነበር። በክብሩ በመጣ ጉዳይ እንኩዋን የለየላቸው ጠላቶቹን ቀርቶ ጉዋደኞችንና ወዳጆቹንም አይምርም ነበር። ስለሆነም፥ ከመወደድ ይልቅ፥ መከበርንና መፈራትን ስለሚመርጥ፥ ከጠላቶቹ ይበልጥ ወዳጆቹን የመጉዳት ዝንባሌ ነበረው፤ ቁንጥጫው የደረሳቸው ወዲያኛ ሁሉ፤ ‹‹ከጌታቸው የተጠጋ ወዳጅ፥ ከአጋም እንደተጠጋ ቁልቁዋል ሲያለቅስ ይኖራል›› ይሉት ነበር።

ውስኪውን አንስቶ ባንድ ትንፋሽ ጭልጥ አድርጎ ያለ ልማዱ። ውስኪ ሲጠጣ በርጋታ ቀስ ብሎ እያንዳንድዋን ብርጭቆ እየተንከባከበ ነበር

የሚጠጣው፥ ‹‹እኔ በእንግሊ ኮሙኒዝም አላምንም - በውይይት ክበቦች ባራክ ኮሙኒዝም›› አለ፥ የጨለጠው ውስኪ እየተናነቀው።

‹‹ጌቱ አንተ ምናገባህ? ብትተወው ምናለበት? ዝም ብለህ ስራህን በትሰራ. . .››

‹‹ለምኑን ደግሞ አብዮት ያላበደው ማንን መሰለሽ? ያ እኔ ስራ የለገባሁት. . . የእህቴ አሽከር የነበረው. . . ደርቤ። አብዶአል። ምናለኝ መሰለሽ? ልመክረው ፈልጌ ባስጠራው፥ ‹‹የቢሮክራቶች ዘመን እያከተመ ነው. . ይልቅ፥ ጋሼ. . . ከውይይት ክበቦች ጋር ቢተባበሩ ይሻላል›› ብሎኝ ወጣ።

‹‹እውነቱን ነው።››

‹‹አንቺንም ቀበሌ አነቃሽ መሰለኝ? ልክ አገባዋለሁ. . . ሁሉንም ልክ ገብቶዋለሁ. . . ስራና ዲስፕሊን መቅደም አለበት። አብዮት አትከባበሩ ይልም። እኔ የማዝነው ሀላፊዎች አድርገው አስቀምጠውን፥ ማንም ያዋርደን፥ አብዮት ነው እያሉ ዝም ብለው በሚመለከቱን ባለስልጣኖች ነው። ንደ ፍየል ጭራ ገበና የማይሸፍኑ የምላቸው ለዚህ ነው. . .ይገባሻል?››

‹‹አልህ ነው እኮ የሚያጠፋህ።››

‹‹ሲነኩኝ አልወድም። ታውቂ የለም። አትንኩኝ ነው የምለው። ይደለም?›› አላት እየተጨነቀ፥ የጠጣው ውስኪ እየተናነቀው። ያንን ደፋር ቡን እንደ ልማዱ በግራ እጁ መታ መታ እያደረገ፡- ቲጊ፥ እኔ እኮ ሚያመኝ ውስኪ አይደለም። ይህ እውር ደንቆሮ አለም ነው ሚያቅለሸልሸኝ፤ እውር ደንቆሮ አለም። ታውቂኝ የለም ቲጊ? ሲነኩኝ ንደማልወድ?››

‹‹አውቃለሁ።››

‹‹እኔ ምንድን ነኝ-ድንች ወይስ ድንጋይ?

‹‹አንተ ምን ቸገረህ?››

‹‹እኔ ከማን አንሳለሁ? እኔ!›› ብሎ ልቡን መታ መታ አደረገና፥ ‹‹በሀይለ ላሴ ጊዜ፥ ኮሙኒስት ነው እየተባልኩ የማንም ደንቆሮ ሽርሙጣ መጫወቻ

ሆኜ ኖርኩ። አሁን ደግሞ አድሃሪ ይሉኛል፣ እኔ አድሃሪ አይደለሁም፣ ስርአት ዲሲፕሊን ይኑር ነው የምለው። ይሄ ነው እኮ የሚያመጣ የሚያቅለሸልሸኝ›› አለና፥ ብርጭቆውን ሞልቶ ውስኪ ቀዳ። ቆየና፥ ‹‹ይሄ ሙያ ባልማር ኖሮ ይሻለኝ ነበር›› አለ፥ የጋዜጠኛነትን ትምህርት የመረጠበትን አለት በውስኪ ትንፋሹ እየተራገመ።

ጌታቸው ለስልጣን ያለውን ከፍተኛ ጉጉት ትእግስት ባትወድለትም፥ ስ ችሎታው እምነት ስላላት ሀዘኑ ሀዘንዋ እየሆነ፥ ቁጭቱና ጥቃቱ ቁጭትዋና ጥቃትዋ ሆኖ እየተሰማት፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ አሁን ካሁን ምን ያደርጉ ይሆን? ብላ በመስጋት ሰውነትዋ እያለቀ ይሄድ ነበር።

እዝን ብላ፥ ‹‹ምን አለ ስራ ብትገባ?›› አለችው። ‹‹ላንቺ ስል፥ እሺ›› አላት። ጉዋደኞቹ እንደ ድሮ ሳይለማመጡት በመቅረታቸው ውስጥ ውስጡን እየበሸቀ።

ትንሽ ሰጋ_ ፍርፍር አሙቃ አመጣችለት - ጥሬ ቲማቲም ከሱ አድርጋ። አንድ አራት ጊዜ ከጎረሰ በሁዋላ፥ ትኩስ ሻይ አመጣችለት። ግ ቢጠጣ ትኩስ ሻይ ሳይቀምስ አይተኛም። ሻይውን ጠጥቶ ሲያበቃ፥ ‹‹ቲማ እወድሻለሁ። ታውቂ የለም? አንቺ ሰው አይደለሽም። መልአክ ነሽ›› አላት ተነስቶ ከግንባርዋ ላይ ሳማት። በዚያው እየተንገዳገደ ወደ መኝታ ቤቱ ሄደ. . ትእግስት በአዲስ ተስፋ ልብዋ እያንሰራራ ተከተለችው። ‹‹እንቅልፍ. . . እንቅልፍ. . . የለላም እንቅልፍ. . . እሰራለታለሁ. . . እሰራላቸዋለሁ. . . እሰራለታለሁ. . . እና ሁሉም እንደ ትእግስት የሚሰማኝ እንደ እርሷ ማንነቴን የሚያውቅልኝ ቢሆን ይህ አለም. . . ይህ ደንቆሮ አውር አ ምንኛ ጣፋጭ ጣእም በኖረው ነበር›› አለ በሀሳቡ።

ከብዙ ወራት ጀምሮ ከአንድ አልጋ ላይ ከጎኑ ተኝታ የምታ መሆንዋን ረስቶ ይኖር ነበር። ዞሮ አቀፋት። አፀፋውን መለሰችለት. . .

ምእራፍ ፯

አቶ ጉልላት ዋለልኝ እንቅልፍ በአይናቸው ሳይዞር እንዳደሩ ያስታውቃሉ። ጠይም ፊታቸው ጠቁሮአል። እንደ ጉድጉዋድ ውሀ ወደ ውስጥ ርቀው ጭል ጭል እያሉ ዘወትር ውሀ የሚያቀሩ ትናንሽ ቀያይ አይኖቻቸው የባሰውኑ ቀልተዋል። ከአይኖቻቸው ስር ያሉት ቆዳዎች በእንቅልፍ እጦት ተሸብሽበው ተንጠልጥለዋል። ትከሻቸው ሚዛኑን አጥቶ ወደ ቀኝ ከማጋደሉም በላይ፥ ደረታቸው ወደ ውስጥ ሰምጦ፥ ጀርባቸው ጎብጦ ሊታዩ፥ እድሜ ሳይሆን መከራና አሳብ በአንድነት ተረባርበው የለመጡአቸው ይመስላሉ።

ወይዘሮ አምሳለ ትላልቅ ጡቶቻቸውን አስቀድመው ታኮዎቻቸው ቁዋ. . . ቁዋ. . . ቁዋ. . . እያሉ ከጉዋዳ ብቅ አሉ። ሁለንትናቸው ጡት ብቻ ሰለ ነበረ የቤት ሰራተኛ በሹክሹክታ ‹‹ሱቅ በደረቴ መጣች›› ይላሉ። ወይም ሊቆጡ ፡ ንዴታቸው አፍንጫቸው ስር ስለሆነ፥ በቀን ሽህ ጊዜ ይቆጣሉና፥ «እንግዲህ፥ ሱቅ በደረቴ ተነሳባት!›› እያሉ ይሳለቁባቸዋል።

አጭር ቁመናቸውን ለማካካስ ረጅም ሹል ታኮ ያለው ጫማ ስለሚያደርጉ ቁዋ፥ ቁዋ፥ ሲሉ የመጡት ወይዘሮ አምሳለ የሸዋሉል ለመሆናቸው ተወራርዶ የሚረታ የለም። ሹል ታኮ ጫማቸው የቤቱን ጣውላ ሁሉ ፈንጣጣ የበላው ፊት የሚገላግላቸው መኝታ ብቻ ነበር።

አቶ ጉልላት ወደ ሚስታቸው ሳይዞሩ፥ ‹‹እንደምን አደርሽ?›› አሉ፥ ምንም አይነት ስሜት ባልተቀላቀለበት ድምፅ። አይኖቻቸውን፥ ክፉኛ ካደባ ከአንድ ወራም ግራጫ ድመት ላይ ሊነቅሉ አልፈለጉም።

«የእግዜሩ ሰላምታ ጀርባ ሰጥቶ ሆነ እንዴ?›› አሉ ወይዘሮ አምሳሉ፥ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው። ድምፃቸው የወጣት፥ አረማመዳቸው የወጣት፥ አለባበሳቸውም ዘመናይ ነበር። ጉርድ ቀሚስ ያዘወትራሉ፥ እንደ ዘመኑ አረዳዎች አፈድስት ሱሪ ለመልበስ ባለመቻላቸው ፡ የጮማ ግንድ እያወጣ ወደ ፊት በገፋው ሆዳቸውና ወደ ላይ ፍንድር ብሎ ሊሄዱ እንደ በሬ ሻኛ የሚገለጠው ቂጣቸው ምክንያት፥ ውስጥ ውስጡን ይቆጫቸዋል። ላይ ላዩን ግን አፈድስት ሱሪ የለበሰች ሴት ሊያዩ ደስ አይላቸውም። ‹‹ድንቄም ሱሪ

ሰበሰች እቴ! ይህን ሱሪ ካገር የሚያጠፋ ነገር እንዴት ታጣ ጭነችሁ! ደ
አንዴ መሬት፥ አንዴ ትርፍ ቤት እያለ ጨዋውን ሁሉ ከሚያስጨንቅ ሰ
አዋጅ ቢያውጣ የስንትዋን አዳሜ ደጋን እግር በማጋለጥ የሚበጅ ነገር በሠ
ነበር!›› ይላሉ። ግን ክብደታቸውን ለመቀነስ ሳምንት ሁለት ሳምንት ከያ
በሁዋላ አልፎ አልፎ የገዙትን አፈ ድስት ሱሪ አጥልቀው ከመስተዋት ፊ
ደብረክ ደብረክ እያሉ ዳሌያቸውን፥ ሆዳቸውን፥ ቂጣቸውን ይመለከታ
በመስተዋቱ ውስጥ የሚያዩት የለውነታቸው ቅርፅ ደስ ስለማይላቸ
ብስጭት ብለው፥ ‹‹ሆድና ቂጥ ተቆርጦ አይጣል ነገር!›› ይሉና ሱሪ
አውልቀው ከዲላብ ውስጥ ይጥሉታል። ዛሬም ጠዋት ማለዳ ተነስተው እ
ተለመደው ያንን መክረኛ ሱሪ ሞክረው - ሆድና ቂጥ ተቆርጦ አይጣል ነገ
ያው እንደ ተለመደው አልሆን ብሉአቸው ስለቀረ፥ ከሌሊቱ እንቅልፍ ማ
ጋር ተዳምሮ አነጫንጮአቸዋል። ብልጭ ብሉባቸው፥ ‹‹ሽዋሉል ይመ
ጀርባህን ሰጥተኸኝ አትቁም ነው የምልህ!›› አሉ፥ ጆሮ በሚሰነጥቅ ድም
መልስ በማጣታቸው ያንኑ አጭር ወገባቸው ይዘው ንቅሳታም እግ
እንገታቸውን እንደ እስክስታ ወራጅ እንክት አድርገው - ‹‹አንተን ነው
የምናገረው!›› ብለው ጮሁ።

‹‹ሽ ሽ ሽ. . .›› አቶ ጉልላት አሁንም መሬት ይዞ እያደባ በ
ከሚሳበው ድመት ላይ አይናቸውን አልነቀሉም። የእርሳቸውም ልብ ከድመ
ጋር እያደባ መሳብ ጀምሮአል። ድመቱ ወደ ፊት በተሳበ ቁ
እርሳቸውም አብረው ለመገለል እየቃጣቸው በእግራቸው ጣት ቁመው ፤
ላይ እየተንጠራሩ፥ በዋጡት ትንፋሽ ሰውነታቸው እየተነፋ፥ ሰው ሰማ
ወይም ለመጡዋጠጥ የተዘጋጁ ይመስል የደም ስሮቻቸው አብጠ
የሚታዩትን እጆቻቸውን ዘርግተው -

‹‹ይችን ትወዳለች አምላለ!. . .››

ድመቱ እመር አለ። የወፍ ላባ ግራና ቀኝ ተበተነ። ጭርር-ጭርርብ
አረጭ - ‹‹ያዛት! ያዛት!›› አሉ አቶ ጉልላት እንደ ህፃን ልጅ እየጨፈሩ

‹‹ምንዋን ማን ያዛት?›› አሉ ወይዘሮ አምላለ በመገረም፥ ወሬ
እንዳያመልጣቸው ወደ ፊት ራመድ ራመድ በማለት - ቁዋ... ቁዋ... ቁዋ

አቶ ጉልላት መለስ ብለው፥ ‹‹ድመት ወፌትዋን - ያዛት። እመር ብሎ ጭጭ አደረጋት›› አሉ፥ አንድ ውስጣዊ ፍላጎት የተሙዋላላቸው ያህል ተደስተው. . .

ወይዘሮ አምሳለ ቀንድዋ እንደ ተመታች ላም ቀጥ አሉ። የመደንገጥና የመገረም መልክ ቀይ ዝብ ፊታቸው ላይ ይታያል። የብር አንክብል የሚመስሉትን ትላልቅ አይኖቻቸውን እያንከባለሉ፥ ‹‹አብደትም ይኸካህ ጀመር እንዴ?›› አሉ፥ በመገረም።

‹‹ግሩም ነው። በልቡ ሲላብ፥ ሲላብ፥ ሲያደፍጥ ቆይቶ - እመር ጭጭ ምንጭጭ! ግሩም ነው - አድፍጦ ሲያመች የልብን ማድረስ. . .››

‹‹እዬዬ! ዋእቴ! ልብ ከየት መጥቶ? የፈሰሰ ሀሞት፥ የተሰለበ ወኔ ብቻ!›› አሉና አቶ ጉልላትን በይበልጥ ወደ ነገር ለመጋበዝ ሲሉ ቀጥለው ደግሞ ‹‹አድፍጦ ቆይቶ ሲያመች የልብን ማድረስ›› ብሎ ነገር! ድንቄም! ምፅአት ደረስ ቢያደፍጡ ዋጋ የለውም. . .›› ብለው ሳይጨርሱ፥ አቶ ጉልላት አቀዋረጡዋቸውና፥ ‹‹ምን ነው በጠዋት ተነስተሽ ባትለከፊኝ!›› አሉ - ብስጭት ብለው።

ወይዘሮ አምሳለ በባላቸው መቆጣት በይበልጥ ተደፋፍረው አፋቸውን ማሞጥሞጥ ጀመሩ፥ ‹‹ማድፈጥ ብሎ ነገር! አዬ የኛ ደጃዝማቾች፥ የኛ ፊታውራሪዎች፥ የኛ ጄኔራሎች፥ የኛ ሚኒስትሮች፥ መሳፍንት፥ መኩዋንንት፥ ባለብዙ ሉሌ ባለትልቅ ዝና! የረገጡትን መሬት የሚያንቀጠቅጡ፥ እንኩዋን ተኩሰው በግርማ ሞገሳቸው ብቻ ሰራዊት የሚፈቱ፥ አየነው ጉዱን እቴ! ያገዳ አሞር! ያህያ ባል ከጅብ አያስጥልም!››

‹‹ተኝክ ነው የምልሽ! ይህን መርዝ የሚተፋ አፍሽን ብትዘጊ ምናለበት? የግታው መቼ አነሰኝና ነው!›› አቶ ጉልላት መማለድ ብቻ ነበር የቀራቸው። ኻ ሚለታቸው አንዴ አፋቸውን ከከፈቱና ሹል ከንፈራቸውን ማሞጥሞጥ ከጀመሩ ፊፅሞ እንደሚያቆሙ ያውቃሉና፥ አቶ ጉልላት ተስፋ ቆርጠው እጆቻቸውን እያወናጨፉና ራሳቸውን እየነቀነቁ ሄደው፥ ተሻሽቶ የቀለሙ ደብዛ ሲጠፋ ከደረሰው አሮጌ ሶፋ ላይ እግሮቻቸውን ሰብስበው ቁጭ አሉና፥

ሌትየሞን በቀያይ አይኖቻቸው እንደ ትንግርት ይመለከቱ ጀመር ፡ የወይዘ
አምሳለ ጠባይ ከፉኛ መለወጥ እጅግ እያስገረማቸው።

ወይዘሮ አምሳለም ትኩር ብለው ይመለከቱአቸው ነበር ፡ አንዱ የሌላ
ልብ ዘልቆ ለመመልከት የፈለገ ይመስላል።

ከአብዮቱ ፍንዳታ በፊት ወይዘሮ አምሳለ ለአቶ ጉልላት ቅንጣት ታ
ደንታ አልነበራቸውም። አቶ ጉልላት ቤት ውስጥ ከሚገኙት ቁሳቁሶች እ
አንዱ ነበሩ - ለወይዘሮ አምሳለ። ለባላቸው ቀርቶ ለልጆቻቸውም እንከ
አልነበራቸውም። ከአባታቸው ከጢቸው ባላባት ከፊውራሪ የሸዋሉል አ
የወረሱት ኩታ ገጠም የሆነ ውሀ ገብ ሰላሳ ጋሻ መሬት ዙሪያ ብቻ
የልባቸው እንዝርት ሲሽከረከር የኖረው። ከአትክልት ዘር ሎሚው - ትርጎ
- ብርቱካኑና ሙዙ፡ ከጥራጥሬው ሽምብራው - ባቄላው - አተሩና ም
ከእህል ዘር ገብሱ - ስንዴው - በቆሎው - ማሽላውና ጤፉ በዚያ ላይ ሽ
አገዳው - ቅቤው - ማርና ወተቱ። ቁጥር የሌለው ጭሰኛ ይህን ሁሉ ሲ
በያይነቱ በመኪና - በአህያ - በአጋሰስ እየጋዘ ሲያመጣ ብሩን ቀ
ጭነቱን አስመዝነው ማስገባቱና ያጎደለ ጭሰኛን መንቀሉ ነበር ት
ደስታቸው። በወቅቱ እንደ መስከረም ጮራ ብቅ ብለው በቅሉ እንደረ
ጣሳ መላ ሰውነቱ የተጨራመተው ከመሬት ጋር ከአባት የተወረሰው ጭ
ከደጃቸው ተኮልኩሎ፡ አደግድጎ ቁሞ ማየቱ፡ ማንም የማይሸረው ወሳኝ ፍ
በጭሰኞቹ ህይወት ላይ መፍረዱ፡ ምንኛ ደስ ይላቸው ነበር! የህይወታ
አለኝታ፡ የስሜታቸው አድማስ ይህ ነበር ለወይዘሮ አምሳለ የሸዋሉል
ደስ ማለቱ ያንን ትፍስህተ ገነት ራዲዮና ቴሌቪዥን በፕሮግራሞቻ
ጋዜጦች በአምዶቻቸው፡ አዝማሪዎች በዘፈኖቻቸው ሲያስተጋቡ ከ
ወዲህ ግን አዋጅ ከሌለ በስተቀር ወይዘሮ አምሳለ ራዲዮም ሆነ ቴሌ
አይከፍቱም። ‹‹የምን ማላዘን ነው!›› ብለው ይዘጋሉ።

ከአብዮቱ ፍንዳታ ወዲህ ለወይዘሮ አምሳለ ሁኔታው
ተለውጦባቸዋል። የወንድን እጅ አይቶ - ለዚያውም የጡረታ አበል -
ፈፅሞ ሊዋጥላቸው አልቻለም። ምሬት፡ ምሬት፡ ለህይወት ምሬት
ዘርቶ ከውስጣቸው የሚገላበጥ ጥላቻ። እንደ ጣእረ ሞት ጥርሶቹን
ያፈጠጠ ችግር! አለምን አስረስቶ ያኖራቸው የነበረው መሬት ሄዶአል -

ኩራታቸውንና ትምክህታቸውን ይዞ። ገና ለማኝ ሳያራ ከደጃቸው ተኮልኩሎና አዳፋ ነጠላውን አደግድጎ በመቆም ምድረ ግቢያአቸውን እንደ ችሎት ያጣብብ የነበረው ጭሰኛም ሄዶአል - አለማቸውን ይዞ። ከሁሉም ይባስ ብሎ እርጅና እንደ ሸባ ለማኝ እየተንፏዋቀቀ መጥቶ ያፈጥባቸዋል። ህይወታቸው፥ የምትንጠለጠልበት ችካል፥ ወይም መልህቅ ጥላ የምታርፍበት ወደብ ያጣች መርከብ ይመስል ነበር ውስጥ ውስጡን የሚዋልልባቸው። አቶ ጉልላትም ከጭሰኞቹ እንደ አንዱ መሆናቸው ቀርቶ ንቀት እያደረባቸው የሚሄዱ እየመሰላቸው፥ ወይዘሮ አምሳለ ጠዋት ማታ መብከንከን ከጀመሩ ሰንብተዋል።

ወይዘሮ አምሳለ ጉርዱ በርሜል የሚያስመስላቸውን ወገባቸውን ይዘው ፍንጭታቸውን በማሳየት ትንሽ ክብ ፊታቸውን ቁልጭልጭ ካደረጉ በሁዋላ፥ ትንፋሻቸውን በረጁሙ ወደ ውስጥ ስበው፥ ረጅም ታሪክ ለማሰማት መድረክ ላይ እንደ ወጣ ተዋናይ ተዘጋጁ - ለነገር። ከአጭር አንገታቸው ላይ ምን ጊዜም ቢሆን የአንገት ልብስ አይለይም - ንቅሳታቸውን ለመሸፈን። ሻሽ ግን እንደ ሴቱ ቢሞቱ አያስሩም - ጠጉሪቱ በመተኮሻ ብን ብላ ብታልቅም ቅሉ። ‹‹የአህያ ባሎች ከጅብ የማታስጥሉ። ገሃነም እስኪቀዘቅዝ ድረስ ብታደፍጡ ምን ሊመጣ? ምን ተአምር ሊፈጠር? ምን ተአምር ሊፈጠር? ወሬ አልለማህም መሰለኝ ስለ ማታው ተኩስ።

‹‹ልጆችን ከቤት እያስወጡ ይዘዋቸው ሲሄዱ ወጣ ብሎ የጠየቀ ማን ነው? አይ ጉድ! አይ ወኔ! ሴቶች ሱሪ በቀሚስ መልበስ የጀመሩት ያለምክንያት አይደለም - ትንቢት ሲናገሩ ነው መሰለኝ።››

አቶ ጉልላት፥ አበጀ እንደ ማለት ትከሻቸውን ሰብቀው፥ ‹‹ዱሮውንም አንቺው ታመጭው አንቺው ታሮጭው አሉ እስከነተረቱ። ልጅ ያሶካው ለራት አይበቃም ይባላል። መሬት ላራሹ! እንዳላልካቸው ይውረድ! ይሰቀል! ጉልቻ ቢለዋውጥ ወጥ አያጣፍጥም! ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት ይቁዋቁዋም! ዘውድ ይገርሰስ! እያሉ በመጮህ ይህ ጉድ፥ ይህ መአት እንዲመጣ ያደረጉት እነሱ አልነበሩም! ይበሉአቸው! ሰው የእጁን ዋጋ ላያጣ! በሰፈሩት ቁና መሰፈር ላይ ቀረ. . . ከእሳት ላይ የፈሉ ትሎች! ይብሉአቸው!›› ብለው ሳጨርሱ፥ ወይዘሮ አምሳለ አቁዋረጡአቸውና - ሻሽ አልባ ራሳቸውን እየነቀነቁ፥ ‹‹ኤዲያልኝ! ከናንተስ ወጣቱ ትውልድ ይሻላል - በሙቱ እቴ! ላመነበት እየሞተ ነው።

አላችሁ እንጂ እናንተ - ያላንዲት ጥይት ባዋድ ብቻ የተፈታችሁ› ብለው አቶ ጉልላቱትን ለማለቃየት ሹል፥ ስስ ከንፈራቸውን ማሞጥሞጥ፥ ሙሉ ጪረቃ መሳይ ክብ ፊታቸውን ፈካ ማድረግ፥ ትላልቅ አይናቻቸውን ማንከባለልና ጉርድ በርሜል የሚያስመስላቸውን ወገባቸውን ማገላበጥ ቀጠሉ።

አቶ ጉልላት እጆቻቸውን ተደግፈው አቀረቀሩ - ህይወትን ሳይሆን ሞትን በልባቸው እየተመኙ። የደም ብዛት በሽታቸው ሲቀሰቀስ ይሰማቸው ነበር. ራሳቸው ላይ ፈልቶ እያዞራቸው፥ ላብላብ ብሎአቸው እየወበቃቸው። አንጀታቸው አርር ድብን ብሎ ስቶማካቸው ሲነሳ የባሰውኑ ኩርምት አሉ። ያ መከረኛ ጉበታቸውም ተነሳባቸው፥ ‹‹ምን ነው ብትተይኝ! እኔ ለራሴ በጠዋት አፌን ደም ደም ብሎኛል›› በማለት አጉረመረሙ።

ወይዘሮ አምላለ አልራሩላቸውም፥ ‹‹የፈሰሰው ደም ከርፍቶህ ይሆናል!»

‹‹ብፈጠረሽ ብዬሻለሁ - አንቺ ሴት።››

‹‹ቆራጥ ጭቁን ሲጠጋው የአድሃሪ ልብ የአገዳ አጥር ይሆናል ብለው የለ?››

አቶ ጉልላት ቀና ብለው መላጣቸውን በማብለጭለጭ እንባ በሚያቀሩ ትናንሽ አይኖቻቸው ወይዘሮ አምላለን አማተሩ፥ ‹‹አሁን ይህ ሁሉ ውርጅባ እኔን ፈሪ ለማለት ነው? አይምሰልሽ፤ ሙያ በልብ፥ ጦርነት በዘዴ ነው። ራስን ከግንድ ጋር ማጋጨትም ጀግንነት አይደለም፥ ሞኝነት ነው። የተወረወረ ቅዝምዝም ጎንበስ ወይም ዞር ብሎ ማሳለፍን ይፈልጋል። ደራሽ ጎርፍ ጥቂት ድንጋይ ቢወረውሩበት አይታገድም። ይልቅ ሁሉን ጠራርጎ እንዳይሄድ ብልሃትን ይጠይቃል. .

‹‹ኡ ኡ እቴ ድንቄም የኛ ጥበበኛ!››

‹‹አድምጪኝ እንጂ! አገር ምን ጊዜም ቢሆን በጠብመንጃ አፈሙዝ አይገዛም። አገርን የሚገዛው ፖለቲካ ነው። ለፖለቲካ ደግሞ ጉልበት ሳይሆን ጥበብ ያስፈልጋል። የአሳት ራት መሆን ባሁኑ ጊዜ አያስፈልግም። አድፍጦ ማለፍና ሲያመች - ሁኔታው ሲመዋሳ - የልብን መስራት። ገሸሽ የተወረወረን ቅዝምዝም ጎንበስ ብሎ ያሳለፈ ፈሪ አይባልም!››

የቀይ ኮሰብ ...

‹‹ዋ እቴ! ማድፈጡ ነው የናንተ ፖለቲካ. . .! ወኔ የለንም-ድሮም ባዶ ጉራ ነበር ብትሉ ይሻላል። ገሃነም እስኪቀዘቅዝ ድረስ ቢያደፍጡ ዋጋ የለውም፣ ሰማነው ሀልም. . .››

‹‹አይመስልሽም። የጊዜ ጉዳይ ነው። አልቆለታል። በሰሜን በኩል ናቅፋ፥ ቃሮራ፥ ተሰነይ፥ አቆርዳት፥ ክረን ምፅዋም በከፊል ተይዞአል። አስመራ ብቻ ናት የቀረችው። እስዋም ተከባለች። የአስመራ ሕዝብ በችጋር እያለቀ ነው። ሰባት ፍሬ ኦቾሊኒ ተቆጥሮ በአስር ሳንቲም መሸመት ጀምሮአል። ቁልቁዋል ሆኖአል አሉ ምግባቸው። በምስራቅ በኩል ብትሄጂ ጎዴ፥ ቀበሪ ደሀር ፥ ዋርዴር፥ ደገሀቡር፥ ጂጂጋ እንኩዋን ሳይቀር-ምናለፋሽ ኦጋዴን ያሉ በሶማሌዎች ተይዞ የቀሩት ድሬዳዋና ሐረር ብቻ ናቸው። እዚህም ችጋር ገብቶአል። ከሱካር ድንች በቀር ህዝቡ የሚበላው አጥቶአል። በደቡብም፥ ባሌና ሲዳማ በጣም አጠራጣሪ ሁኔታ ላይ ደርሰዋል። እንደ ገና በሰሜን እነራስ መንገሻና እነ ጀኔራል ነጋ ከፍተኛ መሳሪያና ሰራዊት ይዘው ወደ ጎንደር እየገሰገሱ ናቸው አሉ። እዚህ አዲስ አበባም ውስጥ እንደምታዩው ትንቅንቁ እየከረረ አብዮተኞች ነን ባዮቹ በመፍረክረክ ላይ ናቸው። ህዝቡም ግራ እየተጋባ ነው። ገበሬው እህል አላወጣ፥ መኪና ነጂውም አልነቃነቅ ስላለ የሚላስ የሚቀመስ እየጠፋ ነው፣ ፈረንጆችም እንዳሉ ተገልብጠው መሄድ ስለ ጀመሩ ፋብሪካው ሁሉ በመለዋወጫ እቃዎች እጥረት ምክንያት መቆም ጀምሮአል። ምእራባውያን አገሮች ሁሉ ለደርጉ ተቃዋሚ ወገኖች የሞራል፥ የማቴሪያልና የገንዘብ ርዳታ እያጎረፉ ናቸው። በደርጉም ውስጥ ከፍተኛ አለመግባባትና መቃቃር ስለ ተፈጠረ ሰሞኑን አንድ ነገር ሳይሆን አይቀርም ይባላል። ህዝባዊ ጦር ብለው እዚህ ስጋ ሜዳ አግበስብሰው ያጎሩትንም ጀሌ ተቅማጥና ተስቦ ወርቶታል አሉ። እናት አገር ጥሪ ብሎ ነገር! የምን እናት አገር ቀረችና? አብዮት የሚሉት ጣጣ የእንቡዋይ ካብ አድርጎአታል። ብቻ ምናለፋሽ የጊዜ ጉዳይ ነው አልቆለታል።››

‹‹ኤድያ! የጊዜ ጉዳይ ብሎ ነገር!››

አቶ ጉልላት በሚስታቸው የፓለቲካ ድንቁርናና ቅጥ ያጣ ንትርክ ተናደው፥ ውጭ ወጥተው ንፁህ አየር ለመተንፈስ በማሰብ ተነስተው ወደ በሩ

ጎምለል እያሉ ሲሄዱ፥ ስልክ በመጮሁ አሳባቸውን ለውጠው ቆሙ። ወይዘሮ አምሳለ ነበሩ ስልኩን ያነሱት. . .

‹‹ማታ እንደዚያ ስልኩን ሳንጫርር የት ነበራችሁ? . . .እ. . . አዎን. . . እንቅልፍ ይንላችሁ እቴ! ሰው ይጨነቃል ብላችሁ አታስቡም የዘመኑ ልጆች. . . የራሳችሁን ፍላጎት ብቻ ማሳደድ ነው ስራችሁ. . . ባለጌን ካሳደ የገደለ ይሻላል. . .ሂሩቴ የት ናት?. . . ተኝታለች? . . . ደልቶአታል!. . . ምናልክ?. . . ምን. . . የኛ ደርቤ? . . . መቼ? ማታ? ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም አሉ. . . በል ተወው!›› ብለው ስልኩን በችኮላ ዘጉ።

አቶ ጉልላት በልጆቻቸው ደህና ማደር እፎይ ብለው እንዳሰቡት ውጭ ወጥተው ንፁህ አየር ለመተንፈስ ሲሄዱ ሲሉ፥ የቀድሞ አሽከራቸው ስም ተነስቶ ጆሮአቸውን ስለ ጨረፈው፥ ወይዘሮ አምሳለ ስልኩን እስኪዘጉ ድረስ ጠብቀው፥ ‹‹ደርቤ ምን ደረሰበት? አደጋ አጋጠመው እንዴ?›› በማለት ለወሬ ችኩለው ጠየቁ።

‹‹የጠሉት ሊወርስ፥ የፈሩት ሊደርስ. . .››

‹‹ምን ሆነ?››

‹‹ጉድና ጅራት ወደ ሁዋላ ነው አሉ. . .››

‹‹ምንነው የሆነውን ብትነግሪኝ?››

‹‹ጆሮ የማይሰማው የለ! የቀበሌአችን የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖልሃል - ደርቤ። የጉድ ማለቂያ የለውም። ሰው ኮ አይደለም፥ ጊዜውም አይደለም። እግዜሩ ነው የተጣላን። እግዜር ቢጣላን አይደለም ከአብራካችን ጉድ፥ በጉዋዳችን ጉድ የሚወጣው! የዛሬውስ የጉድ ጉድ ነው!›› በማለት ነገሩ ከመክበዱ የተነሳ ለመሸከም የተሳናቸው ይመስል ሂደው ቁጭ አሉ።

የአቶ ጉልላት ደካማ ልብ ጨርሳ ልትቆም ምንም ያህል አልቀራትም ነበር። እየተንገዳገዱ ሄደው ነበር ሶፋው ላይ የተቀመጡት።

‹‹ሰውን ማመን ቀብሮ አለች ቀበሮ፡ እንዳስቀመጡት የሚገኝ ድንጋይ ብቻ ነው። ተአምር ነው እቴ! መኖር ደጉ ብዙ ያሳያል። እነደርቤ መንግስት

ሊመሰርቱ ሳላይ እግዜር አይግደለኝ! መቼም እንደኛውን ለጉድ ጎልቶናል!›› ብለው እንደ ተኮረኮረ ሰው ከት ብለው ሳቁ።

ጌቶች ከድንጋጤያቸው ብዛት ነገር አለሙ ፈዋሞ በአእምሮአቸው ውስጥ አልገናዘብ ብሎ ነበር፡ ደርቤ ‹‹ጌቶች›› እያሰ የሚጠራቸው ትዝ ብሎአቸው፥ ‹‹ጌታ ይንሳው! የቁልቢው ገብርኤል እንዳለ›› አሉ በለሆሳስ። ከሁሉም ይበልጥ አንገብግቦ የሚቆጫቸው፥ ከወለዱአቸው ልጆች ይልቅ አርሱን አምነው ያንን ያህል መሳሪያ ከዚያ ትልቅ ጉድጉዋድ እንዲያቃብራቸው ማድረጋቸው ነበር። ደርቤ እንደዚያ ሰውነቱ በላብ ርሶ መሳሪያዎቹ የተቀበሩበትን ጉድጉዋድ በውድቅት ጨለማ ሲቆፍር፥ በአይነ ህሊናቸው ስለ መጣ - ‹‹መቃብሬን ኖሮአል ለካ የሚቆፍረው!›› አሉ በዝምታ። . . . መቃብር. . . ከርስ መቃብር. . . ሊውጣቸው አፉን ከፍቶ የሚያላጋ ጉድጉዋድ. . . ባዳን ያመነ ጉም የዘገነ አሉ በዝምታ. . . ጉም. . . ጥቁር ጉም. . . የሞት ጥላ. . . መአት. . . እንዲያው. . . አሰዋ ቅበረው ባትለኝ ኖሮ አሁን ይህ ሁሉ ጭንቀት. . . መከራ. . . መአት አይደርስብኝም ነበር፥ በማለት አሰቡና. . . ሌት የላከችው. . . ብለው በራሳቸውም ሆነ በባለቤታቸው ሞኝነት ውስጥ ውስጡን ተናደዱ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ እንደዚያ የሚያምኑት፥ ምንነው ከአብራኬ የወጡት ልጆች እንደ አርሱ ጨዋ፥ አስተዋይና ታታሪ በሆኑ እያሉ ከልጆቻቸው ጋር በማወዳደር ፊት ለፊት የሚናገሩለት፥ ማእድ ቀርቦ በተነሱ ቁጥር አንድ ቀን እንኩዋን አንጀት አርስ ጉርሻቸው ያልተለየው ሰው፥ ‹‹እንዴት በእኔ ላይ ክፉ ሊያስብ ይችላል? ሌላው እንኩዋን ቢቀር እጄ ይጥሰው የለ? ያሳረሰውን ጣት የሚነክስ አይነት ሰው አይደለም ደርቤ፥ አስተዋይ፥ ማተቡ እንደ ጅማት የከረረ ነው። ብለው በማሰብ ራሳቸውን ለማፅናናት ሞከሩ።

‹‹ምንነው አድፍጠህ ቀረህ? ከእንግዲህ ማድፈጥ ዋጋ የለውም ብዬሃለሁ! መላ ፍጠር’ይልቅ!

አቶ ጉልላት ቁና ተነፈሱና፥ ‹‹በፊት ነበር እንጂ አልም መደቆስ፥ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ›› አሉ። ‹‹ምን መላ አለ ብለሽ ነው ሂዲ ከማስረሽብ ሌላ?›› አሉ።

‹‹አንዴ የጊዜ ጉዳይ ነው አልቆለታል ትለኛለህ! መለስህ ደሞ አሁኑኑ ሄደን እናስረክብ ስትል ይገርመኛል-ባንድ ራስ ሁለት ምላስ እቴ!››

ባለቤታቸው ባሳደሩባቸው ትዝብት የአቶ ጉልላት ቅስም በእንጂ ተሰበረ። እፍረትም ተከናነቡ። ባልና ሚስትን የሚያስተዛዝብ ጊዜ. . . ክፉ. . . ቀውጢ. . . ጊዜ. . . ከስሩ የተናጋ ሀይወት. . . ብለው አሰቡና ‹‹ከመሞት መሰንበት ይሻላል ብዬ ነዋ!›› አሉ የተከናነቡትን የእፍረት ሽማ ሳያወልቁ።

‹‹ኧረ ኤዲያ! በትንሹ ተስፋው የሚያንሰራራ፥ በዚያው ልክ ደግሞ በትንሹ ተስፋ የሚቆርጥ ሰው ደስ አይለኝም። እንደፋቂ ቆሎጥ በትንሹም በትልቁም ተንጠ መሞት ምንድን ነው?››

‹‹ታዲያ ምን እናድርግ ነው የምትይው?››

‹‹ደርቤን ባንወልደውም ያሳደግነው ልጃችን ነው። የበደልነው ነገር የለም። ብሮህበትም ከልጆቼ ሰይቼ አይደለም። አስተምረን ስራ አሲዘን ሰው አድርገነዋል። ውለታውን አይረሳም። አስተዋይ ልጅ ነው። ታማኝ በመሆኑ ነው እኛም ያሳደግነው። ውለታውን ባለመርሳቱም ነው ተመላልሶ የሚጠይቀን። አምን. . . ታዲያ ጠርተን ስለ መሳሪያው ያሰውን ግምት በዘዴ ብንጠይቀው ክፉ አይደለም። ፊዕሞ እረስቶት ከሆነ ጥሩ። አውቆ ዝም የሚልም ከሆነ አሰይ ላሜ ወለደች!››

አቶ ጉልላት በባለቤታቸው አባባል አልረኩም። ጥበቡም አልታያቸውም። ‹‹በየገደሉ እየዞሩ መቀደስ የተኛውን ሰይጣን መቀስቀስ›› አሉ። ‹‹ራሳቸው ጠርተነው ሁዋላ ያፈሰን እንደሆንስ? ሰው አንዳክቀመጡት አይገኝ የምትዪው አንቺው አይደለሽ?›› አሉ።

‹‹አምን. . . ሰው እንዳስቀመጡት አይገኝም›› አሉ፥ ወይዘሮ እምሀ ባላቸውን የጎሪጥ እየተመለከቱ፥ ‹‹ሰውን ማመን ቀበሮ ነው። ቢሆንም ደፋርና ጢሰ መውጫ አያጣም ይላሉ። ጠርተነው መሞከር ነው። ጉዳዩን እርስ ቀድሞ ካነሳ፥ ዝም እንዲል መምከር፥ ከዚም ካለፈ አጥብቆ መለመን ነው። ባእድ ምን ጊዜም ባእድ ነውና. . . ከባእድ እየጎረሱ ወደ ዘመድ መሄ የተባለው በከንቱ አይደለም. . . መሳሪያው ከየተ እንደ ተገኘ ሳያሳውቅ አስ ራሱ ወስዶ እንዲረክብልን ማድረግ ነው። እምቢ ይለናል ብዬ አልገምትም

ውለታን የሚረሳ ልጅ አይደለም. . .›› ብለው አሳባቸውን ከጫፍ ሳያደርሱ አቶ ጉልላት፥ ‹‹አዬ፥ ተይው እባክሽ›› አሉዋቸው፥ ውለታ የሚሉት ነገር ቀርቶአል። ስንቱን ጠቁም ያሳሰረው ታማኝ አሽከር መሆኑን እያወቅሽ፥ ምነው እንዲህ የዋህ ትሆኝያለሽ? እነ ፊታውራሪ በላቸውን መሳሪያ ደብቀዋል ብሎ በመጠቆም ያሳሰራቸው የስንት ዘመን ታማኝ አሽከራቸው አይደለም እንዴ? ዛሬ አሽከር ቀርቶ የወለዱትም ልጅ እየጠቆመ የገዛ ወላጆቹን ማሳሰር ጀምሮአል። ማንም የሚታመንበት ጊዜ አይደለም። ክፉ ጊዜ ነው። ሂዶ ኮማሰረክብ ሌላ የተሻለ መንገድ እኔ አይታየኝም።››

‹‹ሂደህ ብታስረክብስ? ከመታሰር ለመዳን ምንም ዋስትና አለህ? እነሱ ደሞ ሞኝ አይምሰሉህ! ከዚህ ቀደም ካንድም ሁለት ጊዜ ቤትዎን. . . ጣራ ግድግዳው ሳይቀር ፈትሸን ያጣነው መሳሪያ አሁን ከየት ተገኘ? ብለው ቢጠይቁህ ምን መልስ ልትሰጥ ነው? ሆ. . . ሆ. . . ሆ. . . ከሰማይ ወረደ ልትላቸው ነው? የዋሁስ አንተ ነህ! ያልቦካ ፀሎት ከተጠናወተ ሰይጣን አያድንም አሉ። ይልቅ ጉዳዩን የሚያውቀው የኛ ጉድ ብቻ ስለሆነ በርሱ ላይ መበርታት ነው. . .

‹‹ድሮውኑ ቅበር ባትይኝኮ እንዲያው!››

‹‹ራስህ ሁኔታው አያሳልቃቸውም. . .የጊዜ ጉዳይ ነው. . . ልጅ ይሮጣል እንጂ አይቀድምም፥ እያልከኝ ነዋ! ኧረንሺ! ደሞ ወዴት ሸርተት ሸርተት!. . . ጣልያንን ያርበደበድነው ተደብቆ በቆየ መሳሪያ ነው ስትል የነበርከው አንተ አይደለህም?››

‹‹ተይኝ እባክሽ! ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም። አሁን ምን እናድርግ ነው የምትይው?››

ወይዘሮ አምሳለ በባላቸው መረታት ተደስተው፥ ንቅላታም አንገታቸውን አንደ እስክስታ ወራጅ አንዴ እንከት አደረጉ። ወዲያውም ከብ ፊታቸው ብሩህ ፈገግታ ተጎናፀፈ። ‹‹አየህ፥ ደርቤ ምናልባት ቢያንገራግረርም፥ ዛሬ ገንዘብ አፍ አለው። ስንቱ ነው በገንዘብ ሀይል ከሞት አፋፍ የተመለሰው። የኛም ገንዘብ አፍ አለው ይናገራል›› አሉ፥ ፍርጥም ብለው።

‹‹ጉበ እንስጠው ነው የምትይው?››

‹‹እንዘት አድርገን! ለገንዘብ የማይጉዋጉዋ ማን አለ? ዋ እቴ! ክርስቶሱ የተሸጠው ለገንዘብ ነው። ባለፈው ሰሞን መጥቶ እንደምንም አጣራቅግ መኪና መግዛት አለብኝ ሲል ነበር። መቼም ልቡ ካቅሙ በላይ ይንጠራራል።››

‹‹በጣም እንጂ፥ ራሱን ከፍ ለማድረግ ያለው ጉጉት አይጣል ነው. . .››

‹‹ለመኪና መግዣ ብለን. . . ካንገራገረ ማለቴ ነው. . . ትንሽ ካጎረሰነው አፋን ይዘጋል። ደሞም አትርሳ፥ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ሰርቶ የመኖር እድሉም በኛው እጅ ነው።››

አቶ ጉልላት ራሳቸውን በአሉታ ነቀነቁ። ‹‹አዬ፥ ያንን ወንድምህ እንደሆን የምታስቢው ከአይንሽ ጉድፍ እፍ ብሎ አያወጣልሽም!››

‹‹አይ፥ ለዚህ እንኩዋን እምቢ አይለኝም። ጥቃት ስለማይወድ ላመነበት ወደ ሁዋላ አይልም። ወሰኔን መሰለህ እንዴ? ያንበሳ ልብ ነው ኮ ያለው። ሆኖም እሱም እምቢ ቢል የአለቃ ተክሌ ልጅ. . . ያ አንከስ አንከስ የሚለው . . አዎን መሀሪ፥ እሱ አለልኝ አንጀት የሚያደርስ።››

‹‹መሀሪ ለኛ ሲል ነው እንጂ በዚያን ሰሞን መጥቶ ስለ ደህ ብጠይቀው፥ በፊት ጥሩ ልጅ ነበር. . . አሁን ግን በውይይት ከበብ ውስ ቀንደኛ ቀስቃሽ እየሆነ አስቸግሮአል ብሎኝ ነበር።››

‹‹አላልኩሽም? ይህ አብዮት የሚሉት ጣጣ ያልለወጠውና ያላሳበደ ማን አለ?››

ኩዋ! ኩዋ! ኩዋ! . . . የሽጉጥ ተኩስ።

ድዋ! ድዋ! ድዋ! . . . የዲሞትፎር ተኩስ።

አቶ ጉልላት ከተቀመጡበት ደንግጠው ተነስተው፥ ‹‹የመላኩ ያ ያደሩበት አንሶአቸው ደሞ ሊውሉበት ነው እንዴ?›› አሉ፥ በር እየተመለከቱ።

ወይዘሮ አምላለ ወደ መስኮቱ እየሮጡ፥ ‹‹ደርቤ! ስሙን ቄስ ይጥ እቴ! ማን ነሽ አንቺ!›› ብለው ተጣሩ።

ተኩሱ የተከፈተው ከቤታቸው አጠገብ ስለ ነበረ ሰው ሁሉ ሲሩዋሩዋጥ ይሰማቸዋል። ሁለት ሴቶች እየተቀባበሉ ጩኸታቸውን ያቀልጣሉ። የቤቱ አናር ግንብ፥ መዘጊያው የብረት በመሆኑ ከአውራው መንገድ ላይ ይካሄድ የነበረውን ትርኢት ከቤት ውስጥ ሆኖ በመስኮት ለማየት አይቻልም ነበር።

‹‹ብርሃኔ! ብርሃኔ!›› እያሉ ቢጮሁ፥ ገረድ የሚሉዋት ከቦታውም ስላልነበረች ‹‹ኧረ ልጆቼ የት ይሆኑ? ከትናንት ጀምሮ አላየሁዋቸውም። ወይኔ ልጆቼን! ልጆቼን!›› እያሉ ደረታቸውን ጥለው በር ከፍተው ወጡ - ወይዘሮ አምሳለ። አቶ ጉልላትም ተደናግጠው ተከትለዋቸው ወጡ።

ህዝብ መንገዱን ሞልቶ እንደ ጉንዳን ይተራመሳል፥ ‹‹አዬ ጉድ! ጉድ እኮ ነው!›› እያለ ከንፈሩን እየመጠጠ - ሁሉም።

አንዱ ድምፁን ከፍ አድርጎ ፥ ‹‹በዚያ በኩል ነው የሮጡት ቁልቁለቱን - በመንደር ውስጥ›› አለ፥ የሄዱበትን አቅጣጫ በጣቱ እያመለከተ። ባመለከተው አቅጣጫ የዲሞትፎርና የሽጉጥ ተኩስ ከሩቅ ይሰማል።

‹‹ልጄን! ልጄን! ልጄን! ለኔ ባደረገው! ለኔ ባደረገው!›› እያሉ ጠጉራቸውን ይነጫሉ - እናት!

‹‹ወንድሜን! ወንድሜን! ወንድሜን! እኔ ልደፋልህ! እኔ ልደፋልህ! እኔ ልደፋልህ!›› አያለች ደረትዋን ትደቃለች - እህት!

‹‹ሸበላዬ! ሸበላዬ! ለማን አደራ አልከን? ለማን አደራ አልከን?›› እያለች ፊትዋን ትነጫለች፥ አንዲት ህፃን ልጅ ያዘለች ወጣት ሴት - ሚስት!

‹‹አምቡላንስ ጥሩ! ትንፋሹ አለች። አምቡላንስ ጥሩ!›› እያለ አንድ ረጅም ቀይ ሰው እንደ ዮሀንስ መኖምቁ በምድረ በዳ ይጮሀል - የሚሰማው አጥቶ፡ አንዱ በሌላው ላይ እየተንጠራራ ወሬ ለማየት ወደ ፊት ይጋፋል።

ወይዘሮ አምላለ፥ አጭር ቁመናቸው ምንም ለማየት ስላላስቻላቸውና ከተራው ህዝብም መካከል ገብተው መጋፋት ስላስፀየፋቸው፥ ከዳር ቁመው፥ ‹‹ምንድን ነው እሱ? ማን ነው የተመታው?›› እያሉ ለወሬ ቸኩለው ከአጠገባቸው ያሉትን ሰዎች ይጠይቃሉ።

‹‹የአብዮት ጥበቃ አባል ነው የተመታው - የዚህ የቀበሌያችን የአብዮት ጥበቃ ምክትል ሊቀ መንበር ነው አሉ -›› ይላቸዋል፥ ገዳዮቹ ያመለጡበትን መንገደ ያመለክት የነበረው ሰው።

‹‹እነማን ናቸው ገዳዮቹ?

‹‹ሁለት ወጣቶች ናቸው። ባጠገቡ እንደማለፍ ብለው ነው ሳያውቀው በድንገት መለስ ብለው በሽጉጥ ከደረቱ ላይ መትተው የጣሉት። ከወደቀበት ሆኖ ብዙ ተኩሶባቸው ነበር - አመለጡት እንጂ. . . ከማለቱ፥ ህዝቡ እንደ ተደረመሰ ግድግዳ ወደ ሁዋላ በድንገት ፈልሶ ሲወድቅ በማየታቸው፥ የወይዘሮ አምሳለ ልብ በድንጋጤ ለሁለት ስንጥቅ ሲል ተሰማቸው። አቶ ጉልላት ምንም እንኩዋ ረጅም ባይባሉም፥ በጣቶቻቸው ቁመው ወደ ላይ በመንጠራራት መላጣቸውን እብለጨለጩ፥ የሚሆነውን ይመለከቱ ነበርና ከቆሙበት አልተነቃነቁም።

‹‹እባካችሁን ወደ ሁዋላ ፈቀቅ በሉ - አየር እንዲያገን፥ ትንፋሹ አለች ወደ ሁዋላ! ከወደቀው ሰው ዙሪያ ከቦ ወሬ ለማየት አሰፍስፎ የቆመውን ህዝብ ለማጋፈር ይሞክር ነበር አንዱ የአብዮት ጥበቃ አባል፥ በሰደፍ እስፈራራ። ‹‹ወደ ሁዋላ!›› በደረቱ ከወደቀው ጉዋድ ስር ደሙ እንደ ክረምት ምንጭ ፎልፎል ብሎ እየወጣ ከአሰፋልቱ መንገድ ላይ ኮለል ብሎ ሲወርድ ይታይ ነበር። ዲሞትፎር ጠብመንጃውን እንደ ጨበጠ ነበር የወደቀው። አቶ ጉልላት በይበልጥ ለማየት ተንጠራሩ. . . ጉዋዱ በደረቱ ተደፍቶ እንደ ተኛ በድንገት በሀይል ተነፈሰ። በመጨረሻ ሀይሉ በመጠቀም ጠብመንጃውን ተደግፎ ተነስቶ በጉልበቱ ተንበረከከ። ትንሽ ቆይቶ የበለጠ ግፊት በማድረግ በሁለት እግሮቹ ለመቆም ቻለ። እልልታው ቀለጠ።

ደሙ ከአፉ ቡልቅ ብሎ ወረደ። የሚያደርገው የመጨረሻ ጥረት በስቃይ ከተኮማተረው ጠይም ፊቱ ላይ ይነበብ ነበር። ጠብመንጃ የያዘ ቀኝ እጁን እንደ ሞዶሻ ቡጢ የጨበጠ ግራ እጁን ወደ ሰማይ አንስቶ ቆመ። ፍፁም ፀጥታ ሆነ። ሁሉም ምን ይከተል ይሆን? በማለት አፉን ከፍቶ ቆም እንደ ትንግርት ይመለከተዋል። ጉዋዱ፥ በደከመ ድምፅ፥ ‹‹የኢትዮጵያ ጭቁኖ አርማዬን አንሱ! ከሁሉም በላይ አብዮቱ!›› አለና፥ ከራሱ የደም ኩሬ ላይ ዘፍ ብሎ ወደቀ. . .

ምእራፍ ፰

የጠዋትዋ ጀንበር፡ ሸፍኖአት የነበረውን ግራጫው መጋረጃ በጨረሮችዋ ወስፌ ብስክስክ አድርጋ በመግፈፍ የተንጠለጠለችበትን ትልቅ ሰማይ በይበልጥ ድምቀት እየሰጠችው በሙሉ ግርማ ሞገስዋ መንጣለል ጀምራለች። ባለፈው ምሽት ተኩስ ምክንያት እንቅልፍ አጥቶ ያደረው የአዲስ አበባ ከተማ የተንጣለለችውን ጀምበር ብርሃን ተቀብሎ መልሶ በማንፀባረቅ ፈንታ፡ አቡዋራ ለብሶ የወትሮውን ድምቀት አጥቶ ያዛጋል። አየሩም ውጥረት የተሞላበት ይመስል ነበር።

የብረት ቆብ የደፉ ወታደሮች መትረየስ ከተደገነባቸው «ቋሚ ተጠሪ» የሚል ቅፅል ስም ከተሰጣቸው ጂፕ መኪናዎች ላይ ሆነው፡ በየባቡር መንገዱ እንደ ሸማኔ መዘውር ሽው ሽው እያሉ አላፊ አግዳሚውን በአስፈሪ አይኖቻቸው ያማትራሉ። አንዳንድ ድልድዮች - ራስ መኮንን ድልድይ - ፍንፍኔ - ቀበና - ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፡ እንዲሁም በአንዳንድ ታላላቅ ህንፃዎች-ብሄራዊ ባንክ - ባንኮ ዲሮማ - ቴሌኮሙኒኬሽን - መብራት ሀይል - ትምህርት ሚኒስቴር - ፍንፍኔ ህንፃ - አካባቢ መትረየስ የተጫኑ «ቋሚ ተጠሪዎች» ጥግ ጥግ ይዘው ቆመው ይታያሉ።

ቢሮክራሲው በቀይ ሽብር ተደናግጦ እንደ ሽባ ሆኖ ነበር። በየቢሮው ስልኩ ብቻ ነበር ስራ ያልፈታው። ከድንጋጤ የተነሳ ማኪያቶ አስታውሶ የሚያዝ እንኩዋን አልነበረም። በቀይ ሽብሩ መፋፋም የልብ ልብ የተሰማው የያንዳንዱ መስሪያ ቤት ሰራተኛም በየውይይት ክበቡ ተሰግስጎ፡ አልፎ አልፎ የስልጣን ጉጉት ባለከራቸውና እንዲሁም የደመወዝ ጭማሪ በጠማቸው ግለሰቦች ተወናብዶ እየተንገዳገደ፡ ከወሳኝ ደረጃ ላይ የደረሰውን የመደብ ትግል በማጡዋጡዋፍ ላይ ነበር።

በአንዳንድ ሰፈሮች - ኮልፌ - ሰንጋ ተራ - ልደታ - ዘበኛ ሠፈር - በላይ ዘለቀ መንገድ - እሪ በከንቱ - አዋሬ - የኢ.ህ.አ.ፓ. ቀይ እራፊ ጨርቆች አኮሬንቲ ገመዶች ላይ ተንጠልጥለው፡ የሙብራት ምሰሶዎች በኢ.ህ.አ.ፓ እና በኢ.አ.ወ.ሊ. ቁራጭ ወረቀቶች ተዥጎርጉረው የጠንቁዋይ ዘንግ መስለው ይታያሉ። ግን ቆሞ ወረቀቶቹን የሚያነብ አንድም ሰው አይታይም። ሁሉም

በአይኑ ጨርፎ በማየት እርስ በርሱ እየተንሾካሾከ ነበር የሚያልፋቸው። መኪናዎች ከመጠን በላይ በዘተው ቢታዩም የተለያየ አቅጣጫ ይዘው የሚሄዱ አይመስሉም - የኢ.ህ.አ.ፓ ቀይ እራፊ ጨርቅ በብዛት የት እንደ ተሰቀለ ወይም ሬሳ ከየትኛው ጥግ ወይም መስቀልኛ መንገድ ላይ እንደ ተጣለ ለማየት ተደናብረው ከወዲያ ወዲያ የሚራወጡ ይመስላሉ እንጂ . ያውም በጠፋ ቢንዚን። ከሁሉም አሽከርካሪዎች አይነ-ውሀ ውስጥ ከፍተኛ ድንጋጤ በጉልህ ተፅፎ ይነበባል።

በየመንገድ ሁሉ ብዙ ሰው ይታያል-ልደታ-ተክለ ሃይማኖት-ኮልፌ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ-አባ ኮራን ሰፈር-ገዳም ሰፈር-ሰባራ ባቡር- በላይ ዘለቀ መንገድ-ደጃች ውቤ ሰፈር አፍንጮ በር - ስድስት ኪሎ በአቶ ኢብሳ ወፍጮ ቤት አድርጎ-ግንፍሌ-እሪ በከንቱ-ጎላ ሰፈር - ሠራተኛ ሰፈር . አዋሬ - ካዛንችስ - ራስ ሙሉጌታ ሰፈር - ዶሮ ማነቂያ - ቀበና - የካ ሚካኤል - አራት ኪሎ - የሚታይበት ባንዲራ የሚያውለበልቡ፣ የሚያብለጨልጩ ሽንጣም የኤንባሲ መኪናዎች ስለ ነበሩ አንድም ላይቀር እንዳሉ ተገልብጠው የወጡ ይመስላሉ - ሰው በዳቦ ብቻ አይኖርም በወሬም ጭምር እንጂ እንዲሉ። አምን - የአዲስ አበባም ህዝብ እንዳለ ተገልብጦ የወጣ ያህል ነበር — ለወሬ። አልፎ አልፎ በአንዳንዱ አካባቢ የሽጉጥ ተኩስ ይሰማል - ነጭ ሽብር። አልፎ አልፎ ቀይ ሽብር የተፋፋመበት ትኩስ ሬሳ ከመንገድ ዳር ወድቆ ይታያል - ከደም ኩሬ ውስጥ በጀርባው ወይም በደረቱ ተጋድሞ። ልጆቻቸው ቤት ያላደሩ ወይም የታሰሩባቸው ቤተ ዘመዶች - እናት - አባት - ወንድም - እህት - አጎት - አክስት - . . . እብድ ሆነው ጨርቃቸውንና ደረታቸውን በመጣል ካንዱ የወደቀ ሬሳ ወደ ሌላው ተግተልትለው በመሮጥ እያገላበጡ ይመለከታሉ። ግን ያንዱን ጩኸት ሌላው አያዳምጥም፥ የራሱን ጉድ ለማየት ብቻ ነበር ሁሉም የሚሮጠው። ህዝቡ ይጎርፋል - ለወሬ። ባንድ ፊት ለወሬ ሞት ባይ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ለህይወት እየፈራ ማጅራቱን ማመን አቅቶት፥ ወደ ሁዋላ እየተገላመጠ፥ አንዱ የሌላውን ልብ ላያውቀው፥ በግ ከተኩላ እየሆነ፥ አንዱ የሌላውን ቦቃ የመደብ ደርን በመልክ አይቶ ላይለይ - ቦቃ ስለሌለው - ትከሻ ለትከሻ እየተጋፋ።

ከድል ሀውልት አንስቶ እስከ ራስ መኮንን ድልድይ ድረስ ያለው አውራ መንገድ በሀዝብ ተጨናንቆ መኪናዎች በቀንድ አውጣ ዝግታ ነበር የሚጉዋዙት። ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በዚያች የጠዋት ጀምበር፥ በዚያ ውጥረት በተሞላበት አየርና በአንዳድ ሰራኞች ላይ ባለፈው ለሊት በደረሰው አደጋ አንፃር ሲታይ፥ እንደ ስሙ ብርሃንም ሆነ ሰላም አልሰፈነበትም። ከባድ የሀዘን ማቅ ተከናነበ ይመስላል። የውጭው በር ተዘግቶአል። ሆኖም አንድም የሀትመት ወዛደር ወደ እለታዊ ስራ አልተሰማራም። ሁሉም በማተሚያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በቡድን በቡድን ሆነው ክብ እያበጁ አፍ ለአፍ ገጥመው በለሆሳስ እየተንሾካሾኩ በየሜዳው ፈሰው ነበር የሚታዩት። የአራት ኪሎ ሲንቢሮ ጋዜጠኛ ወንጭፍ አስበርግጎአት ከዛፍ ላይ ተንጠልጥላ አይንዋ ብልጥጥ እንደምታደርግ ጦጣ፥ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሰባተኛ ፎቅ ላይ ተሰቅለው የሰባች ልባቸው ትር ትር፥ ብልጣ ብልጥ አይናቸው ቁልጭ ቁልጭ እያለች በየመስኮቱ ስንጥር መሳይ አንገታቸውን ብቅ ብቅ አድርገው ሁኔታውን አቆልቁለው ይመለከታሉ. . . ‹‹የአራት ኪሎ ጋዜጠኞች ሁኔታዎችን ፊት ለፊት ሳይሆን የሚመለከቱት፥ አቆልቁለው ወይም አሻቅበው ነው›› የሚለውን አሉባልታ ለማረጋገጥ የተሰለፉ ይመስላል። እያንዳንዱ የማተሚያ ቤቱ ወዛደር እና በአራት ኪሎ መንገድ የሚያልፈውና የሚያገድመው. . . ‹‹አድር ባይ ጋዜጠኞች ይወድማሉ - ይጋለጣሉ - ይደመስሳሉ - መሀል ሰፋሪ ጋዜጠኞች የመደብ ጠላቶቻችን ናቸው - የቡርዥዋ ጋዜጠኞች ብእር በአብዮቱ ግለት ውስጥ ይነጥፋል›› የሚሉ መፈክሮች አንግቦ የሚሄዱ መስሎ በአሳብ ስለሚታያቸው፥ ያልተነገረ መፈክር አየሩን ሰንጥቆ እየመጣ ከአብዛኛው አራት ኪሎ ጋዜጠኛ ጆሮ ውስጥ ያስተጋባል። በ፪፻፹፰ቱ ቀበሌዎች የተለያዩ ዝግጅቶችና ድርጊቶች ይከናወኑ ስለነበር፥ የእናት አገር ጥሪ - የዘማቾች ስንቅ ዝግጅት - የገንዘብ መዋጮ - የወዶ ዘማቾች ምልመላ - የሰለጠኑ የአብዮት ጥበቃ አባሎች ምረቃ - አታጠቅ ጦር ሰፈር የድንኳንና የቁሳቁስ አስባሰብ ስራ - የቅስቀሳና የሚጋለጥ ተግባር - አሰሳ - ብሎም በአናርኪቶች ጥይት ተመትተው የወደቁትን አንቂ ጉዋዶችና የአብዮት ጥበቃ አባሎች የቀብር ስርአት ለማዘጋጀት የሚደረገው ውጣ ውረድ ሩጫ - ዋይታና - ልቅሶ - በነጭ ጨርቅ ላይ በደማቅ ቀይ ቀለም የሚፃፉት መፈክሮች፥ ‹‹ታጋይ ቢሞት ትግሉ አይሞትም - የወደቀውን

ታጋይ እርማ አንስተን ለመራራው ትግል ወደፊት! አንድ ታጋይ ቢሞት በሽህ
ታጋዮች ይተካል - ያንድ ታጋይ የደም ጠብታ በሽህ አናርኪቶች ደም
ትመነዘራለች - የአድሃሪ ከበባ ይሰበራል - ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር
ይደመሰሳል›› እነዚህና እነዚህ የመሳሰሉ ሌሎች አጣዳፊና አንገብጋቢ
ተግባሮች በሚከናወኑበት በዚያን ወቅት፥ አንድም የአራት ኪሎም ሆነ የአቡኑ
ጴጥሮስ ጋዜጠኛ ብቅ ባለማለቱ፥ ጋዜጠኞችን፥ ‹‹አይናችሁ ላፈር
አድሃሪዎች፥ ሰላሪሞች - አነጠርሙስ አምላኩ - አናርኪስቶች›› እያለ
ከንፈሩን የማይነክሰባቸው ቀበሌ አልነበርም።

የአራት ኪሎና የአቡኑ ጴጥሮስ ጋዜጠኞች - ውስጠ አዋቂዎች የአሜሪ
ቡና ቤትና የጂማ ባር ጋዜጠኞች ይሉዋቸዋል - በየቀኑ በይፋ የሚሰ
የሚነበብና የሚታይ እንደመሆኑ መጠን፥ ማለትም ወሰል ብሎ የተጋለጠ ሌ
እንደ መሆኑ መጠን፥ ስራቸውና ስማቸው በማንም ዘንድ የሽቶ መአዛ አ
ሌለው ከማንም ይበልጥ አነርሱ ራሳቸው ያውቃሉና፥ ከየአቅጣጫው
ለሚደርስባቸው ዘለፋ፥ ግልምጫ፥ ሽሙጥና ስድብ፥ እርግማንና ውርጅ
እምብዛም አይጨነቁም። ‹‹የነኢ.ዲ.ህ. ቱልቱላ፥ አታሞ፥ ኮት ገልባጥ፥ ወሮ
ሰባሪ›› እያሉ ሲያንጓዋልሉአቸው እነኢ.ህ.አ.ፓ. ደግሞ፥ ‹‹አድርባዮች፥ በሁ
ቢላም - በሊታዎች፥ አሽቃባጮች፥ አጨብጫቢዎች፥ ጭራ ቆሊዎች›› በማ
ስድብ ናዳ ያወርዱባቸዋል። የቡርዥዋው አለም የህዝብ መገናኛ ዘዴ
አሰራር የተጠናወታቸው ቀኝ ክንፍ ቅብጥብጥ ንኡስ ክበርቲም
በበኩላቸው፥ በተለይም ጋዜጠኛ የጊዜውን ሁኔታ ተከትለው ናርባሱ ት
‹‹ማይማን፥ አወናባጆች፥ ደንፊዎች፥ እናንተ ብትጠፉ ሰላም ይኖር ነ
እናካሾች›› በማለት ያራክሱአቸዋል። በስራ የሚገናኙአቸው ግለሰቦችና መ
ቤቶች ደግሞ፥ በቅናት ይሁን በተንኮል ጠብ ያለሽ በዳቦ እያሉ በ
በአረፍተ ነገር እየተጣሉአቸው፥ ቆማጣን ቆማጣ ካላሉት ገብቶ ይፈተ
እንዲሉ፥ ‹‹ዘባራቂዎች›› ይሉአቸዋል። የግል ዝናን አጥብቀው የ
ግለሰቦች ደግሞ፥ ‹‹የኔ ወሬ ለምን ተቆራርጦ እንዲተላለፍ ተደረገ
ተጋንኖ አልተወራም፥ ለምን አርእስተ ዜና አልሆነም? እኔ ለቅስቀሳ ስ
እንጂ ለራሴ ዝና ብዬ አልተናገርኩምና አንድ ቀን ታሪክ ይፈርድባቸ
አሻጥረኞች! ያንን ሚኒስቴር የአብዮት ሰይፍ ገና አልዞረበትም መለሰኝ
ብቻ!›› በማለት ለማግባባትም፥ ለማስፈራራትም ይሞክሩአቸዋል። ሁ

ከከፍላተሀገር አስተዳዳሪዎች ጋር የነበራቸው ጭቅጭቅ ይህ ነው ተብሎ አይገመትም ነበር። ‹‹አዎን. . .ሲናንተ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ብቻ ናት! የጉዋዳ ጋቤጠኞች ነን ብትሉ አይሻልም? እናንተ መቼም የምታጎበጉቡት ለምትወዱትና ለምትፈሩት ብቻ ነው! ለአንድ ትንሽ ቀበሌ በራዲዮ ያን ሁሉ ለአት፥ በጋዜጣ ያን ሁሉ አምድ ስትሰጡ፥ ህዝብ በየለቱ ለሚፈፅመው ታሪካዊ ተግባር ዋጋ ስትነፍጉ ይገርማል። በተለይም ይህን ክፍለ ሀገር ፈፅሞ ረስታችሁታል። አውንም ከከፍለ ሀገሩ የተላለፈው ዜና ከፍተኛ አብዮታዊ መልእክት ስላለው፥ ያልተነገረ እንደሆነ ወዮላችሁ!›› በማለት እያስደነገጡ መግቢያ ያሳጡአቸዋል። በአብዮቱ ሰፊር ተሰልፈናል የሚሉት አንቂ ጉዋዶችም በበኩላቸው፥ የቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ቲዎሪ እንዲሁ በቀላሉ በተግባር ሊተረጎም የሚችል ይመስል፥ ትናንት ማርክሳዊ ሌኒናዊ ርእዮተ አለም ምን እንደሆነ ማወቅ ቀርቶ በጆሮአቸውም ሰምተው የማያውቁት ጋዜጠኞች ዛሬ ደግሞ ግንባር ቀደም ቀስቃሽ፥ አንቂና አደራጅ ሆነው እንዲገኙ በመመኘት፥ ‹‹አዎን ለሀይለ ስላሴ ቢሆን ኖር ስንት ከበሮ በደለቃችሁ ነበር! አስተምሩ ስትባሉ ግን ታወናብዳላችሁ። ትንሽ ድል ሲገኝ ትግሉ ሁሉ ያበቃ ይመስል አጉል እየደነፋችሁ ሰፊውን ህዝብ ከትግል ታዘናጋላችሁ። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ ቅስቀሳ እንድታካሂዱ ስትጠየቁ፥ የምትነዙት ውሸንብር ብቻ ነው። አዋቂ መሰላችሁ ለመታየት ፍሬ የሌለው የቃላት ጋጋታና ኩዋኩዋታ ታበዛላችሁ። ቴዎሪውን ሁሉ ከመፅሀፍ ገልብጣችሁ ሳታላምጡት እንዳለ ስለምትዘረግፉ፥ ህዝቡ ጋዜጣ ከማንበብ፥ ራዲዮ ከማዳመጥና ቴሌቪዝን ከማየት ወደ መቆጠብ ደረጃ ላይ ደርሶአል።

«እንዴ፥ የከሶ መድኃኒት ያሽራል ስለ ተባሉ፥ ሁሉም በአንድ ጊዜ አይጠጣም። መጠን አለው። ከልኩ ሲያልፍ መፈወሱ ቀርቶ መርዝ ይሆናል። በዚህ ላይ የአብዮቱ ሂደትና የሰፊው ህዝብ ትግል የደረሰበትን የእድገት ደረጃ በጊዜው በመገምገም በአገሪቱዋ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ አታካሂዱም። የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ ምን እንደሆነ አታውቁም። ስለሆነም ሕዝቡ ወቅታዊ መፈክሮችን አንግቦ እንዲነሳና በመፈክሩ ዙሪያ እንዲሰባሰብና እንዲሰለፍ አታደርጉም። ፕላን፥ እቅድ፥ መዋቅር የላችሁም። በጭፍን ነው የምትሰሩት። ግብታዊነት ያጠቃችሁአል። ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ሳይንስ እንደ መሆኑ መጠን ሳይንሳዊ ሂደትና ይዘት

አለው። ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ለምን ለማን እንዴት እንደሆነ ማወቅ፥ አውቆም መቼ ማጥቃት ወይም መሸሽ እንደሚያስፈልግ ታክቲክ መቀየስና ማቀድ አለ። ከነስተት ወደ ቅርፅ ከዚያም ወደ ይዘት በምንሸጋገርበት ጊዜ ሁሉ ወቅታዊ ፕላን፥ እቅድና መዋቅር ያስፈልጋል። ጊዜና ሁኔታ እንዲሁም አድማጭና አንባቢን ሳይመርጡ እንዲሁ የሚለፈፈውና የሚለቀለቀው ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ኢላማ አይመታም። ተደናቁሮ ማደናቆር፥ ግራ ተጋብቶ ግራ ማጋባት ሆናል። ደግነቱ ሰፊው ህዝብ በንቃቱ ከናንተ አልፎ ሄዶአል። ሊሆን ፕሮፓጋንዳውና ቅስቀሳው መቅደም፥ ይህም ባይሆን እኩል መራመድ ነበረበት። እናንተ ግን ወደ ሁዋላ ቀርታችሁአል። ብቻ . . .ዋናው ነገር . . .ይህን ሁሉ ለማድረግም ሆነ የተጣለባችሁን ከባድ ሀላፊነትን ለመወጣት በወዛደሩ ርእዮተ አለም ፅኑ እምነት እንዲኖር ያስፈልጋል። ስለሆነም፥ በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ድንፋታና ወላዋይነት ስፍራ የላቸውም። ባለሙያ ነን፥ ማን ይተካናል ብላችሁ የምትኩራሩ ካላችሁም ተሳስታችሁአል። ዛሬ አብዮቱ ያፈራቸው ህዝባውያን ጋዜጠኞች ከስር እያቆጠቆጡና እያበቡ ናቸው። በማለት፥ በየጊዜው ምክርና ተግሳፅ ስለሚያበዙባቸው ጋዜጠኞችም፥ ‹‹ሰራችን ከስድብ ሌላ ምስጋና የለውም (ስድብ ትርፉ) ምን ነው እኛም እንደ ሌሎቹ በአመት የማይታይ ፋይል እያገላበጥን ተጠርዞ የሚቀመጥ የአጭር፥ የመካከለኛና የረጂም ጊዜ እቅድና ፕላን እያወጣን በሰላም በኖርን - ጎመን በጤና እያልን›› እያሉ ስለሚበሳጩና ቆሽታቸው ስለሚደብን፥ እንደ ዶሮ ፊኛ ቶሎ ቶሎ ይጠማቸዋል. . .

የአድሃሪዎች የመጨረሻ ምሽግ ሆኖ የቆየችው የአዲስ አበባ ከተማ እንዲያ በመደብ ትግል ተጡዋጡፎ፥ ሲፍም፥ ሲግል፥ ሲነድ እሳቱ፥ የጋዜጠኞች አለመገኘት በሁሉም ዘንድ ጥፋቱ ከይቅርታ በላይ ሆኖ ነበር።

እፍኝ የማይሞሉ የአራት ኪሎና የአቡነ ጴጥሮስ ጋዜጠኞች ከየአቅጣጫው ሳያቁዋርጡ የሚጎርፉት የደደቢቶቹ ቀበሌዎችን፥ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን፥ የደርግ አባሎችን፥ የክፍለ ሀገር አስተዳዳሪዎችንና የተቀሩትን አያሌ የህዝባውያን ድርጅቶችን አንገብጋቢ ጥያቄዎች ተቀብለው (ያውም በሌላ መሳርያና የገንዘብ አቅም) ለማርካት የማይችሉ መሆናቸውን ደርቤ፥ የመስሪያ ቤቱ ባልደረባ እንደመሆኑ መጠን፥ በተጨባጭ ሁኔታ

ቢያውቅም፥ እርሱም ቢሆን የተመዋላ የጋዜጠኞች ቡድን ባስቸኩይ ወደ ቀበሌው እንዲላክለት ከጠየቁት ውስጥ አንዱ ነበር። የአርሱም ተስፋ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ከንቱ ሆኖ ቀረ፡ የተመዋላ ቡድን ቀርቶ አንድም ጋዜጠኛ ብቅ አላለለትም። ችግሩን ከአገሪትዋ አጠቃላይ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ፡ «አብዮቱ ድክመት ነው። ብቻውን ተነጥሎ የአብዮት ደሴት የሆነ መስሪያ ቤት የለም። ሆኖም. . .አምን. . .አሻጥረኛም አሉበት. . .እንደ ማንኛውም መስሪያ ቤት. . . የጊዜ ጉዳይ ነው. . .» ብሎ በማሰብ፥ ጋዜጠኞችን የማግኘት ተስፋውን ቆርጦ አጣዳፊ ስራዎቸ ላይ ማተኮር ሞከረ። ግን አልሆነለትም። ከፊቱ የተደቀኑት ስራዎች ሁሉም አንገብጋቢና አጣዳፊ ስለ ነበሩ የቱን ይዞ የቱን እንደሚተው ቸግሮት ነበር።

እንቅልፍ ያልሆረበት አይኑ በመስኮቱ ሾልካ የምትገባውን ጨረር ማየት ተስኖ ይጭበረበር ነበር። እንቅልፍ ሽለብ ሊያደርገው ሲል ነበር፥ ባለፈው ምሽት ከእርሱ ጋር የአብዮት ጥበቃ ምክትል ሊቀ መንበር ሆኖ የተመረጠው ላጲሶ ሶልጀሮ በአናርኪቶች ጥይት ተመትቶ የወደቀ መሆኑን የሰማው። «ለምን እርሱን ነጥሰው መቱ? በዚህ ቀበሌ የሚያውቀው ምን ነገር ቢኖር ይሆን? ወይስ የእርሱ ህይወት ያጠፋችው ጥይት ለኔ የታለመች ነበረች? ማን ያውቃል. . . ዛሬ. . . ምናልባት አሁን. . . በዚች ደቂቃና ስአት. . .ወይም ነገ. . . የእኔ. . . የአንዳችን. . . ወይም የሁላችን ተራ ሊሆን ይችላል። ሞልታ የፈሰሰችው የላጲሶ ፅዋ ለእኛም እየሞላች ነው. . . ግን ሞልታ ከመፍሰስዋ በፊት ምን ማድረግ አለብን? ምን፥ ምን!» እያለ በሚያስብበት ወቅት፥ የሞት ጥላ የተቃረበ መስሎ ስለተሰማው፥ ሰውነቱን ዘገነነው። እንደ ላጲሶ ከአውላላ መንገድ ላይ በድንገት ተመትቶ ሲወድቅ ላንዳፍታ በአይነ ህሊናው መጥቶ ስለ ታየው፥ «ሞትም አሰ ለካ!» ብሎ አሰበ። «የለም! መሞት የለብኝም. . .የለም. . . ለእርስዋ ስል. . . ለሌላ እንኩዋን ባይሆን. . . አምን. . . እያለብኩዋት ለመኖር. . . የህይወት ትርጉም ምንድን ነው? አሳብ. . . ትዝታ. . . ሌላ ምናስ እያለ፥ በልቡ ያደረው ምስጢራዊ ትዝታዋ ህይወትን የሙጥኝ እንዲል ሲገፋፋው፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ «ለምን? አሁን ለምን እዚህ ጣጣ ውስጥ ገባች? ህይወትን በጣም የምትወድ ተጫዋች. . . ሽቅርቅር. . . ነች። የተከለከለች የገነት ፍሬ. . . ግን ምን ላድርግ? እኮ ምን? እንዴት ነው እነርሱን አይናቸውን የማየው? ጣጣ ውስጥ ነው የገባሁት. . .»

እያለ የሀሳቡ ክር እንደ ተጎለጎለ ልቃቂት ሆኖበት ሲጨነቅ? ሁለት የአብዮት ጥበቃ አባሎች አንድ ሰው ይዘው ገቡ። ሰውየው ጋቢ የለበሱ ረጂም፣ ሪዛም፣ ጠጉራቸው ሸብቶ እንደ ጥጥ የነጣ፣ ፍርሃት አድሮባቸው መራመድ የተሳናቸው ሽማግሌ ናቸው።

ደርቤ ከነበረበት የአሳብ ጭንቀት አለም ወጥቶ አንዴ ወደ አብዮት ጥበቃ ጉዋዶች አንዴ ደግሞ ወደ ሽማግሌው ተመለከተ። ሽማግሌው መቆም የተሳናቸው መሆናቸውን በመገመት፣ ‹‹ይቀመጡ አባቴ›› አላቸውና፣ ወደ አብዮት ጥበቃ ጉዋዶች መለስ ብሎ፣ ‹‹ምንድን ናቸው?›› አለ።

አንደኛው የአብየት ጥበቃ ጉዋድ ተሽቀዳድሞ፣ ‹‹አሰሳ ስናደርግ የተቀበረ መሳሪያ ከጉዋዳቸው አግኝተን ነው እርሳቸውንም መሳሪያዎቹንም ይዘን የመጣነው›› ብሎ መለሰለት። ሲናገር ፈጠን ይል ነበር።

አንድ ዲሞትፎር ጠብመንጃ፣ አንድ ፍሻሌ ሽጉጥ ከቀይ ከፋይ ማህደሩ ጋር፣ እንዲሁም በጣልያን ጊዜ የተሰሩ አራት የእጅ ቦምቦች ከደርቤ ጠረጴዛ ላይ አኖረና፣ ‹‹እነዚህ መሳሪያዎች ዛሬ ጠዋት አሰሳ ባደረግንበት ጊዜ ከእርሳቸው ቤት ውስጥ ተቀብረው የተገኙ ናቸው›› አለው፣ የሚናገራቸውን ቃላት እንደ መትረየስ አከታትሎ እያንጣጣ።

የሽማግሌው ልብ ልትቆም ምንም አልቀራትም ነበር። ከጠይም ሪዛም ፊታቸው ላይ ታላቅ ፍርሃት በጉልህ ይነበባል። ፍርሃታቸው እንደ ተስቦ ተጋባበት - ደርቤን። ላንዳፍታ፣ ‹‹ለምን ይሆን የምንፈራው? ከምንወዳቸው ሰዎች አሳብና ትዝታ ላለመለየት ነው? ብንሞት ሌላ ምን እናጣለን?›› ብሎ አሰበና፣ ‹‹አባቴ፣ እነዚህ መሳሪያዎች ምን ያደርጉልኛ ብለው ነው መደበቅዎ?›› ብሎ ጠየቃቸው።

ሽማግሌው ደንግጠው ያረጁ አጥንቶቻቸውን እያንቁዋቁ ከተቀመጠበት ብድግ አሉ። ዝግ ብሎ ነበር እንኩዋን የጠየቃቸው። ምን እንዳስደነገጣቸው ግራ ገባው። ‹‹ድምጼ እንኩን ሰው አያስደነግጥም ነበር›› ብሎ አሰበና በፍርሃት ተውጠው ደንዝዘው ቆመው የቀሩትን ሽማግሌ፣ ‹‹መለስ አልሰጡኝም እኮ?›› አላቸው፣ በተጨማሪ እንዳያስደነግጣቸው ድምፁ የባሰውን ለስለስ አድርጎ።

‹‹ምንም፥ ምንም ልጄ. . .›› አሉት፥ ከንፈሮቻቸው እየተንቀጠቀጡ።

ያስደነገጣቸው ድምፁ ወይም ሁኔታው ሳይሆን ከድምፁ በስተሁዋላ ያለው የቀበሌዎች አስፈሪ ስልጣን መሆኑ በድንገት ስለተከሰተለት፥ እንደ መብሳጨት ብሎ በሀሳቡ፥ ‹‹የቀበሌ ነዋሪዎች በአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች ላይ ያላቸውን የፍራቻ አመለካከት መቼ ይሆን የሚለውጡት? አለ፡ ‹‹እኛ አውራ ወይም አረመኔ አይደለንም። የቆምነው ለሰፊው ህዝብ ደህንነት ነው። ግን እኮ የዚህ አደገኛ አመለካከት ምንጭ እኛው ነን። ፍርሃትን በሰው ልብ የሚለቀው በራሱ የማይተማመንና በሌሎቹም ላይ እምነት የሌለው ሰው ብቻ ነው። የለም - ህዝቡ በፍርሃት ተውጦ ያለ ምንም ጥያቄ ከሚታዘዘን ይልቅ በኛ ላይ እምነት አድሮበት አለኝታችን ናቸው ብሎ እንዲከተለን ማድረግ ያስፈልጋል። በፍርሃት ላይ የተመሰረተ መሪነት ዋጋም ዘላቂነትም የለውም። ትሁት መሆን ደካማነት አይደለም። አምን፥ በራሳቸው የሚተማኑ በጣም ትሁትና መንፈሰ ጠንካራ የሆኑት ሰዎች ናቸው የሰውን ልብ ለመግዛትና አለኝታ ለመሆን የበቁት። በራሱ የማይተማመን ብቻ ነው የሚያስፈራራውና የሚደነፋው። ‹‹ምንም ላያደርጉበት ለምን ደበቁ ታዲያ?›› ብሎ እንደ ገና ሸማግሌውን ጠየቃቸው፥ ድምፁ ለዘብ ፈገግታውን ፈላ ለማድረግ እየሞከረ።

‹‹ካልከሰ ልጄ፥ እንዲያው ወንድነት ይዞኝ ከመሳሪያ ላለመለየት ብዬ ነው እንጂ ለሌላ አይደለም። ወንድ ልጅ ያለመሳሪያ እንዴት ይኖራል ብዬ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ለነዚህ መሳሪያዎች የቆየ ትዝታ አለኝ። ባምስቱ የመከራ ዘመን በዱር በገደሉ እየተንከራተትኩ ተዋግቼባቸዋለሁ። ይህ የምታየው ዲሞትፎርና ፍሻሌ የምመካባቸው ክንዶቼ ነበሩ። ህይወቴ እያለች ለምን ልለያቸው ብዬ ነው። ስሞት ሬሳዬ በምን ታጅቦ ይሸኛል፤ ወንድ ልጅስ እንዴት ያለ መሳሪያ ይኖራል ብዬ ነው እንጂ ሌላ ምን ላደርግበት?›› ብሎው፥ የትዝታ ልጉዋም ስለሳባቸው አይኖቻቸውን ከመሳሪያዎቻቸው ላይ ጣል አደረጉ። ወዲያው ትዝታ ይዞአቸው ጭልጥ አለ፤ በአንድ አፍታ ፍርሃቱ ከልባቸው ውጦቶ እንደ በጋ ጉም መንምኖ ጠፋ። እንግዲህ ለሞትም ሆነ ለህይወት ደንታ አልነበራቸውም። ከትዝታቸው ጋር ወደ መቃብር መውረድ ጠረጡ። ‹‹ሌላ ምንስ ይዤ ልሄድ፥ ምንስ ቀረኝ?›› በማለት አለቡና ፈገግ አሉ።

ደርቤ በሽማግሌው አነጋገር ልቡ ስለተነካና ሀቀኛም መስለው ስለታዩ ለመሳሪያቸው ደረሰኝ ሰጥቶ ሊሸኛቸው ቆርጦ ትእዛዝ ለመስጠት ሲል ‹‹ጣሊያንን ያርበደበድነው በተደበቀ መሳሪያ ነው›› የሚል ቃል ኪዳሮዎ ውስጥ እንደ መረዋ ደውሎ ጥርጣሬ ስለቀሰቀሰበት፥ ‹‹አባቴ፥ መሬት ወይ ትርፍ ቤት ተወርሰዋል? ብሎ ጠየቃቸው፥ ሳያስበው ፈገግታውን አጨልሞ ድምፁን ከፍ አድርጎ::

‹‹የሞተላት ቀርቶ የገደላት በላ ሲሉ አልሰማህም ልጂ? መሬትም ቤትም የለኝም:: ያለኝ ትዝታ ብቻ ነው›› አሉት::

‹‹የታሰረ ወይም አብዮታዊ እርምጃ የተወሰደበት ዘመድስ?››

‹‹ዘመድ?››

‹‹አዎን ዘመድ. . .ልጅ?››

‹‹ያጣ የነጣ ሰው በዚህ አለም ምን ዘመድ አለው ብለህ ነው:: ልጅ የለኝም፤ መሀን ነኝ:: ዘመዶቼም ልጆቼም እነዚህ መሳሪያዎቼ ነበሩ:: ጠላቶች አሉኝ›› አሉት፥ ፍርጥም ብለው::

‹‹ማን ናቸው እነርሱ?›› ብሎ በመገረም ጠየቃቸው::

‹‹ጠላቶቼ? ሆዴና ትዝታዬ ናቸው!››

‹‹ብሉ አባቴ፥ ትንሽ ቢታገሱኝ ከጓዶች ጋር ተመካክሬ ውሳ እሰጥዎታለሁ›› ከማለቱ፥ ሲታገለውና ሲያስጨንቀው በቆየው ሃሳብ ሀሊናው ቆራጥ አቁዋም ሲወስድ ተሰማው::

ሽማግሌውን አንዱ የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ ይዞአቸው ሲወጣ ፈጠን እያለ ሲናገረው ሌላው አባል ወደ ሁዋላ ቀርቶ ‹‹ምን ሆነሃል?›› ደርቤን ጠየቀው::

‹‹ምን ሆኛለሁ?››

‹‹እኔ እንጃ! ግር ይልሃል - ከማታ ጀምሮ:: አንድ ነገር የሚያስ ትመስላለህ:: ሁላችንም የምንጠያየቀው ምን ሆኖአል? ምን ነካው ነው::››

ደርቤ ስሜቱን ደብቆ፥ ‹‹ምንም አልሆንኩም። የጣላችሁብኝ ሃላፊነት ከብዶኝ ነው የምጨነቀው። ሌላ የሚያስጨንቀኝ ነገር የለም›› ብሎ፥ በመዋሸቱ እየተፀፀተ፥ ቀጠለና፥ ‹‹ይልቅ የጉዋድ ላጲሶ ቀብር ጉዳይ ከምን ደረሰ?›› አለው። ምንም አይነት ጥርጣሬ ሳይፈጥር አርእስተ ነገሩን ከራሱ ወደ ሌላ ጉዳይ ለማዞር ሲመቸው ደስ አለው።

‹‹ሳጥኑ ተገዝቶአል። መኪና ተገኝቶአል። ጉንጉን አበባም ታዞአል። መፈክሮችም እየተዘጋጁ ናቸው። አስክሬኑ ቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ከሚገኘው ከአብዮታውያን መካነ መቃብር እንዲያርፍ ተፈቅዶአል። የቀብሩ ስነ ስርአት የሚፈፀመው በሰባት ሰአት ነው። አንተስ የምታደርገውን ንግግር አዘጋጅተሃል? ስለጋዜጠኞቹስ ምን አደረግህ?›› ብሎ ጠየቀው።

ደርቤ እራሱን ነቀነቀና እንቅልፍ አጥተው ያደሩትን አይኖቹን አሻሸ። በተዳከመው ሰውነቱ ዝሎ እንደ ድንጋይ ከበደው። ሰክሮ እንዳደረ ሰው አይኑ ቦዘ፥ ጭንቅላቱ ዝጎ ይዞርበት ነበር። ውሃ ያልነካው ቀይ ፊቱ በልዞአል። አህል ያልዞረበት አፉ አሻቦ መስሎአል። ክፉኛ ተንጠራርቶ አዛጋና፥ ‹‹ንግግሬን ለመፃፍ ጊዜ አላገኘሁም። ጊዜ ጠፋ። ድሮ ሰአቱ እንደ ቀን የሚረዝምብኝ ሰው፥ ዛሬ ቀኑ እንደ ሰአት እያጠረብኝ ተቸግሬአለሁ። ጋዜጠኞችንም ለማግኘት ብዙ ጊዜ ሞክሬ አልቻልኩም›› አለው።

‹‹እነሱ መቼ ይገኙና! ኢ.ድ.ሀ.ግ ኢ.ሀ.አ.ፓ. ብቻ ናቸው ያንን ቤት የሞሉት›› አለ ተናድዶ።

‹‹ከያይነቱ አለበት፤ ህዝባውያን ጋዜጠኞችም አሉ።››

‹‹እኔ እንጃ ብቻ፥ ግብግቦ አለ ቢሉዋቸው ኖሮ ሳይጠሩ ይመጡ ነበር። እኔ መቼ ሰማሁት። ሞኝ ሆነህ ነው እንጂ፥ አረቄም አለ ብትላቸው ኖሮ ያለ የሌለ መሳሪያቸውን ይዘው ነበር የሚመጡት። ገብተን ያንን ቤት አንድ ቀን ካልመነጠርነው አይሆንም።››

‹‹ምንጠራ እንዲህ በዋላ። ለምንጠራ ከመሮጥ በፊት ብዙ መማር አለብን። ምንጠራ ለምን? እንዴት? መቼ? ማንን? ከምንጠራ ሌላ ሊወሰድ የሚችል አማራጭ ርምጃ አለ ወይ? ለእነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ ተጨባጭ

መልስ ማግኘት ያስፈልጋል። አላማችን የአብዮቱን ሰፊር ማሰፋትና ማጠናከር መሆኑን መዘንጋት የለብንም›› አለው።

ጉዋድ ላጲሶ መገደሉን ከሰሙ ወዲህ የአብዮት ጥበቃ አባሉች ሁሉ በንዴት ገንፍለው ደሙን ለመበቀል ወኔያቸው የተቀለቀሰ መሆኑን ያረጋ ሳያጤን አልቀረም። እጅግ ያሳሰበው ጉዳይ ስለነበረ፥ ‹‹አየህ ጉዋድ›› አለ ‹‹የላጲሶ መመታት እንዳሰቆጣችሁ ይገባኛል። ግን ስሜታችንን መቆጣጠር ያለብን በተለይ በዚህን ጊዜ ነው። በስሜት ተነሳስተን በግብታዊነት የምንወስደው ርምጃ መናር የለበትም። ጠላቶቻችን የሚፈልጉት ይህንኑ ነው። ወጥመዳቸው ውስጥ መግባት የለብንም›› አለውና፥ እነዋሲሁንን ወስዳችሁ አስረከባችሁ ወይ ለመሆኑ?›› ብሎ ጠየቀ።

‹‹እንደኦታ። ጠዋት በማለዳ ነዋ›› አለው ፍርጥም ብሎ። ቀጠለና፥ ‹‹ብቻ ነገሩ ሁሉ ደስ አላለኝም›› ብሎ ራሱን ነቀነቀ።

‹‹ምኑ ነው ደስ ያላለህ?››

‹‹አንዳንድ የህዝብ ድርጅት ጉዋዶች የነዋስይሁንን መያዝ ሰምተው በጣም ተቆጥተዋል አሉ. . . ››

‹‹ለምን?››

‹‹እነዋስይሁን አብዮታዊ ናቸው። ትክክል ነው የሰሩት። አድሃሪያንንና አናርኪስቶችን መጨፍጨፍ ማስረጃ እያቀረቡ አይደለም. . . ይህ የአብዮት ጊዜ ነው. . . እንዲያውም ያሰራቸው ቀበሌ አድሃሪ. . . ቀልባሽ ነው በማለት ነዋ!››

‹‹ተዋቸው እባክህ! የቡድን ጉዳይ ነው። ቀበሌ የቡድኖች መሳሪያ. . . አምን የቡድኖች የስልጣን መወጣጫ አይደለም. . . ስልጣን የጠማቸው ግለሰቦች ናቸው እንዲህ የሚሉት. . . እናውቃለን እናደራጃለን እያሉ የራሳቸውን ቡድን በህዝብ ላይ የሚያደራጁ ካሉ ተሳስተዋል።››

‹‹ዋስይሁን ምናለ መሰለህ! ሆ. . .ሆ. . . ዛሬ ባልወጣ ምናለ በሉኝ! ከሁዋላዬ ማን እንዳለ ባታውቁ ነው! አልገባችሁም እንጂ እኔ የምታገለው ለአሸናፊው መስመር ነው። ለናንተ ይብላኝ ብቻ!›› አለ አሉ እየደነፋ። ‹‹በዛ

እጃችን ነው. . . ማታውኑ እርምጃ ብንወሰድበት ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስም ነበር. . .››

‹‹የወለድነው ርምጃ ትክክልና አብዮታዊ ነው። አንጠራጠር። አሸናፊውን መስመር የሚወስነው ሰፊው ህዝብ በትግሉ ነው›› አለውና፥ የጊዜውን መሮጥ ገምቶ፥ ከአንድ ሰአት በሁዋላ የቀበሌው የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች ሁሉ ተሰብስበው እንዲጠብቁት እንዲያደርግለት ነግሮት አሰናበተው። ጉዋዱ ፈጠን ፈጠን በሚል እርምጃው ወጣ።

የአብዮት ጥበቃው ጉዋዱ ከመውጣቱ፥ ልክ ወረፋ ሊጠብቁ የቆዩ ይመስል፥ ሁለት ፖሊታ አመላላሾች ተያይዘው ገቡ። አንደኛው ፖሊተኛ ኮማሰታወቂያና መርሃ ብሄር ሚኒስቴር ስለነበረ እጅ ከነሳው በሁዋላ በራሱማንዴው ደብተር ላይ ፈርሞ ፖሊታውን ተቀበለው። ደብዳቤው የተላከው ከሚሰራበት ክፍል በመሆኑም ለማንበብ ቸኩሎ ነበር። ‹‹የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆነው መመረጥዎን ሰምተናል። እንደሚያውቁት ያሉበት ክፍል ስራ ጊዜ የማይሰጥና በሀላፊነትም የሚያስጠይቅ ስለሆነ፥ በአስቸኳይ ወደ ስራዎ እንዲመለሱ እያስጠነቀቅን፥ በአርሰዎ ስራ ላይ አለመገኘት የተነሳ ስራው ተበድሎ ቢገኝ በሀላፊነት የሚጠየቁ መሆኑንና መስሪያ ቤቱም ባለበት አብዮታዊ ግዴታ መሰረት አስፈላጊውን ርምጃ ለመውሰድ የሚገደድ መሆኑን እናስታውቃለን. . .›› ከመስሪያ ቤቱ የተላከው ደብዳቤ ነበር።

ሳቅ ቃጥቶት ነበር። ግን ሊስቅ አልቻለም። ‹‹ከመቼው አፈጠናቸው?›› በማለት ራሱን በራሱ ጠየቀ። ‹‹አሁን የትኛው ስራ ይበደላል ብለው ነው? የትኛውስ ሃላፊት ነው የሚያስጠይቀኝ? በቀን የሁለት ሰአት ስራ እንኩዋን የሰኝም። ለዚያውም ቢሆን እኔም እንደነርሱ ሀሲና አለኝ። እንደ ሌሎቹ፥ ቀበሌ አሰራለሁ. . . የአብዮት ጥበቃ አባል ነኝ. . . አብዮታዊ ግዳጅ ላይ ነው ያለሁት እያልኩ በማስፈራራትና በማጭበርበር ከስራ እየቀረሁ ያልሰራሁበትን ደመወዝ ሰጡኝ አልል! ደብዳቤ ከመፃፍ ይልቅ ጠርተው ቢያነጋግሩኝ ምን ነበረበት? ቀልድና ተንኮል ነው!›› እያለ በአሳብ ባህር ሰምጦ ቆየና ሌሎቹንም ደብዳቤዎች ከሁለተኛው ፖሊተኛ ተቀብሎ አንድ በአንድ እየከፈተ ያነብ ጀመር። አምስቱም ደብዳቤዎች በእጅ የተፃፉ ሆነው፥ ከአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበርነት ባስቸኳይ ወርዶ ካልወጣ ውሎ ላያድር በሀይወቱ ላይ ርምጃ

የሚወሰድ መሆኑን የሚያስጠነቅቁ ዛቻዎች ነበሩ። ዛቻዎቹ ለቀልድ ያህል የተሰነዘሩ እንዳልነበሩ ስለገመተ ቀዝቃዛ ላብ በጀርባው ሲወርድ ተሰማው። የገዛ ህይወቱን ከአደጋ የማዳን ጥሬ ስሜት በመላ ለውነቱ ስለ ተሰራጨ ብርድ እንደ ያዘው ሰው ይንቀጠቀጥ ጀመር። በአሳቡ ግን፥ ‹‹የሰም፥ ፈተናው እዚህ ላይ ነው! የሰው ልኩ የሚታወቅበትና የሚለይበት ከዚህ ላይ ነው! ሞት ጥርሱን ቢያገጥ. . . ቢያንገራብብ እንደ ጥላ፥ ምኔን ወስዶ ምኔን ሊያስቀር? ለአንዲት አጭር ህይወት እንዲህ መጨረሻ የሌለው ጭንቀት! ምን ሊቀር ከትዝታ ሌላ? . . .›› እያለ ሊያዘግም፥ አጠገቡ የነበረው ስልክ ደወለ. . . ከመደንገጡ የተነሳ ከተቀመጠበት ሊነጥር ምንም አልቀረው ነበር።

ከድንጋጤው የተነሳ ስልኩን ለማንሳት ጊዜ ወሰደበት። እራሱን እየታዘዙ በሚንቀጠቀጥና በሚያልበው እጁ ስልኩን አነሳ። ‹‹ሃሎ. . . ማን ልበል? ማን. . . እሜቴ እንደምን አሉ?›› አለ፥ እየተገረመ። ወይዘሮ አምላለ ነበሩ። ለላምታው እጅግ ስለበዛበት የባሰውኑ ተደናገረ. . .

‹‹ለብርቱ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር። በምሳ ሰአት ልትመጣ ትችላለህ?

‹‹አዩ እሜቴ፥ ቀብር አለብኝ!››

‹‹አሁንስ መኪና እልክልሃለሁ. . .››

‹‹አሁንም ስብሰባ አለብኝ ከጥቂት ደቂቃ በሁዋላ. . .››

‹‹ማታስ?››

‹‹ማታ ማታ ውይይት አለብኝ። ዛሬ የሚመቸኝ አይመስለኝም። በስልክ ቢነግሩኝ. . .››

‹‹ጉዳዩ እንኩዋን በስልክ የሚነገር አይደለም። ከተመቸህ ብቅ በል. . . እ. . . መኪና እፈልጋለሁ ብለህ ነበር ጥሩ መኪና በጥሩ ዋጋ ተገኝቶልሃል። ገንዘብም ባይኖርህ እኔ ከፍዬልህ ቀስ ብለህ ትከፍለኛለህ! ሌላም ጉዳይ አለኝ። እንደ ምንም ብለህ ብቅ ብትል?››

‹‹ዛሬ ፊዕሞ አይመቸኝም እሜቴ. . . ››

‹‹ለመሆኑ ልጅ፥ ምን ወሰደ እዚያ ጣጣ ውስጥ ከተተህ? ጥንቁቅ ነበርክ እንኳ. . .››

የሚለጠውን መልስ እስኪፈልግ ጊዜ አልሰጡትም። ‹‹አዬ. . . ተሳስተሃል ልጅ። ሁላችንም እገዘነናል። ባታውቀው ነው እንጂ የእሳት ራት ነው ያደረጉህ። ሁዋላ አንድ ነገር ብትሆን ሀዘኑ ከኛ ራስ አይወርድም። መቼም የዘመኑ ልጆች የእሳት ራት ሆናችሁልል። አንተ ግን አስተዋይ፥ ጥንቁቅ ነበርክ እንኩዋ! መቼም በአናንተ ቤት ሁሉንም ነገር አውቀን ጨረስን ብላችሁልል። እስቲ ይሁን! ለማንኛውም ነገር እንደተመቸህ ብቅ በል፤ መኪናዋ እንዳታመልጥህ፥ ብዙ ሰው እየተሻማት ነው፥ ባለቤትዋም በእዳ ተይዞ ቡጧም የተቸገረ ስለሆነ ቶሎ ሊሸጣት ይፈልጋል። አራስህንም ጠብቅ፥ እግዜር ካንተ ጋር ይሁን›› ብለውት ስልኩን ዘጉ።

ወይዘሮ አምሳለ ስልክ የደወሉበትን ዋና ምክንያት ሳያውቅ አልቀረም። በላብ የተጠመቀው እጁ የባለውኑ እየተንቀጠቀጠ ስልኩን አስቀመጠ። የሰልክ ማስቀመጫው ውርጭ ውስጥ ያደረ መስሎ ነበር። ሁሉም ነገር በአንድ ጊዜ መጥቶ ከፉኛ ስለተጫነው ልቡም ሆነ ትከሻው ከጭንቱ ስር ሊሰምጡ ተሰማው። ካደገ ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ነገር ግን የያዘው አባዜ እስኪወጣለት ለማልቀስ እድል አላገኘም። ወዲያውኑ በሩ ተንኩዋኩዋ። ‹‹ለማልቀስ እንኩዋን ጊዜ የለም›› በማለት እድሉን ረገመና ፊቱን ቶሎ ጠራረገ። ብቻውን ሆኖ እስኪወጣለት ድረስ እንባውን በዝምታ ለማንባት ተመኝቶ ነበር። ባጭሩ የተቀጨው ስሜቱ እየተናነቀው ‹‹ይግቡ!›› አሉ።

የስብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ መመረጡን በጠዋት የሰሙ የመስሪያ ቤቱ ጋዜጠኞች ነበሩ። አራቱም በተራ አገላብጠው ከሳሙት በሁዋላ በመመረጡ የጋለ ደስታቸውን ገልጠውለት ወንበር ይዘው ቁጭ አሉ። ከዚህ ቀደም ለሰዓታት እንኩዋን ይኮሩበት የነበሩት ሰዎች አሁን እንዲያ ሊስሙት፥ የሚለው ነገር ጠፍቶት ባዶውን ወረቀት ሊያገላብጥ፥ የያዘውን እርሳስ በጥርሱ ሊነክስና ራሱን ሲያክ ከቆየ በሁዋላ፥ ‹‹እንኩዋን መጣችሁልኝ። ጋዜጠኞች ፈልጌ ነበር። ደህና እግር ጥሉአችሁልል›› አላቸው።

እነርሱ በቅርብ ባያውቁትም እርሱ አንድ በአንድ ያውቃቸዋል። ጠንካራ ከግንባሩ ሽሽት ያለው፥ ቀይ ፊቱና አይኖቹ በእረቂቁ የነበዙት ባለጎርናና ድምፁ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ በስካርና ከስራ በመቅረት፥ ስራ ሊገባም በሆነ ባልሆነው ከክፍል አለቆቹ ጋር አምባጉዋሮ እያነሳ በማስቸገር የታወቀ፥ የስራ ማህደሩ በቅጣትና በማስጠንቀቂያ የወፈረ ጋዜጠኛ ነበር። ከእርሱ ጎን የተቀመጠው ስፌድ ፊት ባለጎፈሬ አይነ ጮልጩዋላ ቀጭን ረጂም ወጣት፥ እንደሱው በስካሩ የታወቀ፥ በስንፍናውም ምክንያት ተክፍል አለቆቹ ጋር ዘወትር የሚጋጭ፥ ምላሱ ግን ሰው ቀርቶ ድንጋይ የሚያናግር ነበር። ለጥቂ የተቀመጠው ሶስተኛው ጋዜጠኛ፥ በሙያው እንክን የማይወጣለት ምስኪን ቢሆንም፥ በጠጭነቱና በሴት ማሳደድ ጠባዩ የተነሳ ገንዘብ ፈፅሞ የማይበቃው በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ገንዘብ ያልተበደረው ሰው የሌለ፥ በወር ውስጥ በሞዴል ፯ ሶስት አራት ጊዜ ካልተበደርኩ እያለ ሲለምኑት እየዞረ ስም የሚያጠፋ የለየለት አሉባልተኛ ከመሆኑም ሌላ፥ ካድሬ ሆኖለሁ፥ ትናንት ስጠጣ ያመሸሁት እገሌ እገሌ ከሚባሉ የደርግ አባሎች ጋር ነው. . . ነገ እንዲህ ሊሆን ነው. . . እገሌ ሊታሰር ነው. . . እያለ በማወናበድ የታወቀ ነበር። አራተኛው፥ ከጠጉሩ ላይ ሽበት ጣል ጣል ያለበት ጠይም ባለ ወርቅ ጥርሱ ከመለሳለሱ የተነሳ ሻንደረባ የሚመስለው ነባር ጋዜጠኛ፥ በሁሉም ዘንድ ይታወቅ የነበረው በጠጭነት ወይም በአመንዝራነት ሳይሆን፥ በመሰሪነቱ ነበር። በምንም ጉዳይ ላይ አቅዋም ወስዶ ሲከራከር ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም። ነባር ጋዜጠኛ ቢባልም በስሙ የቀረበ ፅሁፍ ለመሃላ ቢፈለግ አይገኝም። ነገር ግን፥ ዞር ብሎ የሚተክለውን የነገር ጩቤ ቶሎ የሚነቅል አልነበረም። ከመጠን በላይ የስልጣን ጉጉት ስለነበረውና የቅርብ አለቆቹን ጉድጉዋድ በሄደበት ሁሉ ስለሚቆፍር፥ አለቆቹ ሁሉ፥ በተለይም የውይይት መድረክ ተከፍቶ እርሱ ቀንደኛ ተሳታፊ ከሆነ ወዲህ፥ እንደጦር ይፈሩት ነበር።

ባለጎርናና ድምፁ ቀደም ብሎ፥ ‹‹ለምን ኖሮአል ጋዜጠኛ የፈለግከው?›› ብሎ ጠየቀው፥ ደርቤን።

‹‹የቀበሌያችን የአብዮት ጥበቃ ምክትል ሊቀ መንበር በአናርኪስቶች እጅ ስለተመታ ለእርሱ ነበር. . . እንደምታውቁት ለቀብሩ ብቻ ሳይሆን ለቅስቀሳም ይረዳል ብዬ ነው. . .››

ባለሰፌድ ፊት ጋዜጠኛ፥ ሹል አፉን አሹሉ፥ ትናንሽ አይኖቹን እንደ ጦጣ ብልጥጥ እያደረገ፥ ‹‹ታዲያ ችግሩ ምንድን ነው? አሁን ተመልሰን ፎቶግራፍ አንሺ፥ ፊልም አንሺና አንድ የዜና አገልግሎት ጋዜጠኛ እንልክልሃለን›› አለው፥ እርግጠኛ ሆኖ።

‹‹ቀጥሎ የተናገረው ለራሱ እድገትና ስልጣን መሰላል ለመዝርጋት ለስራ ጉዋደኞቹ ሁሉ የውድቀት ጉድጉዋድ ሲቆፍር የሚውለው ጋዜጠኛ ነበር። ‹‹ቢሮክራሲ እያለ በየት በኩል። ዙሪያውን ተብትበው ይዘውታል። የመጣንበት ዋና አላማም ቢሮክራሲውን በሚመለከት ጉዳይ ካንተ ጋር ለመነጋገር ነው። ከዚህ ቀደም ከዋስይሁን ጋር ጉዳዩን ጀምረነው ነበር። ጊዜ በማጣቱ ነው እንጂ ይሽኔ ጨርሶት ነበር›› አለው።

ሁልጊዜ በብድር የሚኖረው ጋዜጠኛ ለጠቀና፥ ‹‹ለዚህም ብቻ ሳይሆን ፈቃድህ ከሆነ የውይይት ክበባችን ሊቀ መንበር አድርገን ልናስመርጥህ በማሰብም ጭምር ነው። ያ መስሪያ ቤት መመንጠር እንዳለበት አንተ ከኛ የበለጠ ስለምታውቀው ከዋስይሁን የበለጠ ትረዳናለህ ብለን ነው። በአድሃሪ ቢሮክራቶች ተተብትበናል።. . .›› ብሎ ነገሩን ሳይጨርስ፥ ባለጎርናናው ድምፅ አቁዋረጠውና፥ ‹‹አዎን፥ ጉዋድ እውነቱን ነው። ሰርተን እንዳልሰራን አድርገው የግል ማህደራችንን እያበላሹ ይጫወቱብናል። ቢሮክራሲ ሽባ አድርጎ እስኪያስቀረን ድረስ ዝም ብለን መመልከት የለብንም። ‹‹አድሃሪ ቢሮክራሲ ይውደም›› የሚለውን መፈክር በተግባር ማሳየት አለብን። ‹‹የዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን›› የምንለው ለዚህ ነው. . .›› አለ።

ባለሰፌድ ፊት ጋዜጠኛ ቀጠለ፥ ‹‹ጉዋዱ የተናገረው ሀቅ ነው›› አለ። ‹‹ከኛ ጋር ቆመህ (ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን) ለሚለው መፈክራችን መታገል አለብህ። ዋስይሁን ከኛ ጋር ነበር። ሀቀኛ ጉዋዶች ሁሉ ከኛ ጋር መቆም አለባችሁ። እኛ የቆምነው ለሰፊው ህዝብ አብዮት ነው እንጂ

ለራሳችን ጥቅም አይደለም›› ብሎ ሽበት ጣል ጣል ያለበትን ጋዜጠኛ በአይኑ ጠቀሰው።

ሽበት ጣል ጣል ያለበት ጋዜጠኛ የጠነሰሰው ተንኮል ወደ ግቡ የተቃረበ መሆኑን በመገመት ፈገግ ብሎ ወረቅ ጥርሱን እያሳየ፥ ‹‹ከመስሪያ ቤታችን የሚጋለጡትንና ሊመነጠሩ የሚገባቸውን ሰዎች ስም ዝርዝር ይዘን መጥተናል›› አለና፥ በእጅ የተፃፈ ሁለት ሉክ ወረቀት አውጥቶ ለደርቤ ሰጠው። ቀጠለና፥ ‹‹እነዚህ ሰዎች ባስቸኩዋይ ካልተወገዱ ድርጅታችን በዚያ መስሪያ ቤት ውስጥ ፊፅሞ ሊጠናከር አይችልም። ከአንድ እስከ ስድስት ተራ ቁጥር የተመለከቱት አብዮታዊ ርምጃ ሊወሰድባቸው የሚገባቸው ናቸው። አንዱ ተልእኮአችን ይህ ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ ቅድም እንደተጠቆመው የውይይት ክበባችን ሊቀ መንበር ሆነህ እንድትመረጥ ለማድረግ ነው›› አለው።

ደርቤ ወረቀቱን አንድ በአንድ ተመለከተ። የአርባ ሰዎች ስም ሰፍሮበታል። በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ከነበሩት ባለስልጣኖች አንድም ሰው አልቀረም። የጌታቸው ሽዋሉል ስም በሁለተኛ ተራ ቁጥር ሰፍሮ ነበር። የፍናት ከበደ ስም ደግሞ ቀንደኛ የኢ.ህ.አ.ፓ. አባል ተብለው ኮሚጋለጡት ሰዎች ስም ዝርዝር ውስጥ ሰፍሮ በማየቱ እየተገረመ። ‹‹አድሃሪዎች አሻጥረኞች፥ የኢ.ዲ.ሀ. አባሎች የሀይለ ስላሴ ከበሮ ደላቂዎች፥ ከማለት ሌላ በነዚህ ሰዎች ላይ የምታቀርቡት ተጨባጭ ማስረጃ አላችሁ ወይ?›› ብሎ ጠየቃቸውና አራቱንም አንድ ባንድ ተመለከተ።

መላሪያቸው ሊያደርጉት እንደ ፈለጉ ገብቶታል። ንዴቱ እያየለ ሊሄድ እየተሰማው፥ ራሱን ለመቆጣጠር ከፉኛ ይታገል ነበር።

ባለጎርናናው ድምፅ ጋዜጠኛ ‹‹ጉዋድ›› አለው፥ ‹‹አድሃሪዎች እኮ ማስረጃ እየተው አይደለም አሻጥራቸውን የሚሸርቡት። (ፀሀዩ ንጉስ) ሲሉ ከረሙ ለእንዲህካቸው ደሞ ‹‹ቆታ ቆታ›› እያሉ ሲያወናብዱ የቆየ አድሃሪ ጋዜጠኞች ናቸው። አሁንም እንደ ልማዳቸው እያወናበዱ የአብዮታዊት ኢትዮጵያ ባለስልጣኖች ሆነዋል። በተለይም በአንድ ቁጥር ስሙ የሰፈረው ከአብዮቱ በፊት በርእስ አንቀፆቹ ምን ሲፅፍ እንደነበር ሁላችንም እናውቃለን። በሁለት

ቁጥር ስሙ የሰፈረው የለየለት አድሃሪ ደግሞ ቢሮክራሲውን ከማጠናከሩ የተነሳ እንኩዋን ያለቀጠሮ በቀጠሮ ቢሮው ሰው አያስገባም። ስንቱን ዘርዝረን ልንዘልቀው?›› ማስረጃ በመጠየቁ ቁጣ ቁጣ ብሎታል።

ደርቤ ያሰቡት አይነት ሰው አለመሆኑ ስለተከሰተላቸው አራቱም ተያዩ።

‹‹እርግጥ ነው. . . አድሃሪ ማስረጃ እየተወ አይደለም ፀረ-ህዝብ አሻጥሩን የሚፈጽመው።›› አለና፥ ለጥቂት ጊዜ ሲያስብ ቆይቶ፥ ‹‹እንደምታውቁት ለማጋለጥ የሚሮጠውም ሁሉ ሀቀኛ አብዮተኛ ነው ማለት አይደለም። የአብዮት ሂደት ውስብስብና ጠመዝማዛ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው። ግን. . .›› ብሎ ንግግሩን አቆመና ተራ በተራ ትኩር ብሎ ተመለከታቸው። ፊት ለፊት አይኑን የሚመለከት ከአራቱም ውስጥ አልነበረም። ገዝፀ የማይበቃውም፥ ባለሰፊዴ ፊቱም፥ ባለጎርናና ድምፁም ግንባር ላይ ላብ ተንቸርፍፎ ይታይ ነበር። ደርቤ፥ በአንድ ፊት አራቱንም እዚያው አቆይቶ ለመመርመር ልቡ እየከጀለ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ዋስይሁን በመታሰሩ ከአንድ ሀሁእ ድርጅት የተላኩ ሰላዮች ይሆኑ? አቅዋሜን ለማወቅ ይሆን የመጡት? አውቀውስ ምን ሊያደርጉኝ? እያለ ሲያሰላስል፥ ሽበት ጣል ጣል ያለበት ጋዜጠኛ፥ በፍርሃት ደርቆ ሊዘጋ የደረሰውን ጉሮሮውን እንደ ምንም አላቆ ሲያበቃ፥ ‹‹የለም ጉዋድ. . . ይህን ሊስት ያመጣነው ከመሬት ተነስተን ላይሆን ዋስይሁን ስለ ጠየቀን ነበር። ከአሉ ይልቅ አንተ የመሰሪያ ቤታቸንን ሁኔታ በይበልጥ ታውቀዋለህ. . .እ. . . ጊዜ ወስደህ ተመልከተው›› አለና፥ ወጣትነቱን በማየት ቀጥሎ፥ ‹‹በአብዮት ጊዜ ማመንታት አያስፈልግም። ለዘብተኛ ከአድሃሪ ተለይቶ አይታይም›› ብሎ፥ ፊጋ ቦግለት የወርቅ ጥርሱን አሳየው።

የዋስይሁን ስም ተደጋግሞ በመነሳቱ የደርቤ ጥርጣሬ ተጠናከረ። አቅዋማቸውም በይበልጥ ገባው።

‹‹ድርጅታዊ አምባገነንነት ካልከሰመና ቦታውን ለህብረት ካልለቀቀ፥ የጋራ ጠላቶቻችንን በአንድ ግንባር መዋጋት ቀርቶ የእርስ በርስ ሽኩቻ በተራማጆች መካከል ይሰፍናል፤ ህዝባውያን ድርጅቶችና ጦር ሀይሎች በድርጅት አኩያ ተከፋፍለው አብዮቱ ይደክማል። የተከፋፈለ ቤት አንድነት ሊቆም ስለማይችል

ለአብዮቱ ጠላቶች አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል፣ እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን፥ የሚለው መፈክርና የኢ.ህ.አ.ፓ. ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አሁን፥ የሚለው መፈክር በይዘትም ሆነ በአላማ የተሰያየ አይደሉም፤ ሁለቱም ስልጣን የጠማቸው የንኡስ ከበርቴዎች ጥያቄዎች ናቸው›› በማለት ክርክር ሊከፍት ከቃጣው በሁዋላ፥ የጊዜውን ሁኔታ በመገመት አላቡን ለወጠ። ‹‹ርምጃ ከመውሰድ በፊት ሁኔታዎችን በትክክል ለማገናዘብ መማከር ለዘብተኛ እያሰኝም። ቃታ ስበው ከተኮሱ በሁዋላ ጥያቄ የማቅረብ ሁኔታ እያከተመ ነው። በአብዮት ሂደት ውስጥ ጅብደኛነት ቦታ የለውም›› ብሎ ራሱን እያከሰ ሲያስብ ቆየና እንዲህ አላቸው፥ ‹‹እያንዳንዱ ዜጋ ፀረ-ህዝቦች የማጋለጥ ግዴታ አለበት። ሆኖም ጥቆማ ከማድረጉ በፊት ሁሉም የጣዛ ሀሊናውን መመርመር ይኖርበታል። የጠቋሚዎች ሀሊና እስካልጠራ ድረስ የማጋለጡና የምርመራው ተግባር ሁሉ የጠራ ሂደት አይኖውም። አብዮቱን ከስህተት ላይ ይጥላል። ለዚህም ነው የቀይ ኮከብን ጥሪ በሀቅ የተቀበሉ ታጋዮች ዛሬ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ አዝማሚያ የሚያሳዩት። ይህን አዝማሚያ የቀኝ ክንፍ አዝማሚያ. . . የፋሺስቶች አዝማሚያ በማለት ያልሆነ ትርጉም ሊሰጡት የሚሞክሩ አሉ። የጊዜ ጉዳይ ነው። እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል። ለማንኛውም ነገር ጉዳዩን ለማጣራት እሞክራለሁ። ሁቅ ተደብቃ አትቀርም›› ብሎ ሸኛቸው። እነርሱም በፍርሃት ተውጠው ነበሩና፥ ከደርቤ ቢሮ ቶሎ ወጥተው ለመሄድ አለመነቱም። አራቱም እያላባቸው እግሬ አውጭኝ አሉ።

መሳሪያ ቀቢረው የተያዙት ሽማግሌ ጉዳይ እና የወይዘሮ አምሳለ ጥሪ በደርቤ አእምሮ ውስጥ እየተመላለሱ ቢያስጨንቁትም፥ የአራቱ ጋዜጠኖች መምጣት በአንድ በኩል አይነ ጥላውን ቢይበልጥ ስለ ገለጠለት ተደስቶ ነበር። በላዲሶ ቀበር ስነ ስርአት ላይ የሚደርገው ንግግር ይዘት ጥርት ባለ ሁኔታ ቅደም ተከተሉን ይዞ በአእምሮው ውስጥ ተደረደረ. . . ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች በትግል የሚለው መፈክር ትርጉሙ ተከለተለት። ፈገግ አለ። ለጊዜው ያደረበት ድካም ሁሉ ለቀቀው። ሽማግሌው. . . ብሎ አለበና፥ የመሳሪያ ፍቅር አድሮባቸው በተመሳሳይ ሁኔታ መሳሪያ የደበቁትን ሁሉ እዲያገላቡ ተመክረው በነፃ እንዲለቀቁ ፅኑ ውሳኔ አደረገ። በውሳኔው በመደሰት ፈገግታ ጨመረ። ሰውነቱ በይበልጥ ቀለለው። ግን ፈገግታውና

ስሜቱ አብረውት አልቆዩም። የወይዘሮ አምላለን ጥሪ ሃሩትን እንዳሰታወሰ ፊቱ ላይ እየፈካ ይሄድ የነበረው ፈገግታው ተመልሶ መጨለም ሲጀምር፥ ፍኖት በሩን አንኩዋክታ ገባች። ደርቤ ፍኖትን በማየቱ ተደስቶ ከመቀመጫው ዘሎ በመነሳት ሮጦ ሂዶ ሊጨብጣት እጁን ዘረጋ። ጠጋ ብላ ጉንጩን ሳመችው። ‹‹ካታክልቱ ውስጥ የቀጠፍኩት ናት ብላ እምቡጥ ያልፈነዳ ፅጌ ረዳ አበባ ሰጠችውና፥ ‹‹የቀይ ኮከብ ጥሪ ስለ ደረሰህ እንኩዋን ደስ አለህ። መመረጥክን ቤት ደውለው ነው የነገሩኝ›› አለችው።

ሳቂታ ፊትዋ ጨልሞአል። ብሩህ ፈገግታዋ ጠፍቶአል።

‹‹የመመረጤ ወሬ ከመቼው ተነዛ?›› አላት። ምን እንደ ሆነች ባይገባውም የተለወጠች መሆንዋ ሳይሰማው አልቀረም።

‹‹አዲስ አበባ ካቅምዋ በላይ የሰፋች መንደር ናት። የተደረገ ነገር ቀርቶ የተተነፈሰም ነገር ሰው ጆሮ ሳይገባ ውሎ አያድርም›› አለችው።

ድምፅዋም እንደ ፊትዋ ህይወት አልነበረውም። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር ከላይ እስከ ታች ጥቁር መልበስዋ የታየውና፥ ‹‹ምንነው ጥቁር ለበሽ?›› ብሎ የጠየቃት።

ለጥቂት ሴኮንድ ያህል አመነታችና፥ ‹‹እምአእላፍ ሞቶ ነው›› አለችው? የራስዋ በሆነ የቀዘቀዘ ድምፅ።

ደርቤ ደንግጦ ራሱን ያዘ። የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ህይወት አልባ ሆኖ ደንዝዞ ቆሞ ቀርቶ ነበር።

‹‹ምንም አይደል። የፊለገው ነገር ነው። ስሜቱ ይገባኛል›› አለችው።

ፍኖት ባትናገር ኖሮ እንደ ደነዘዘ ይቀር ነበር። ‹‹ምን ሆኖ ነው የሞተው?›› አላት፥ እምአእላፍን መሞት ማመን እያቃተው።

‹‹ራሱን ነው የገደለው››

‹‹እንዴት?››

‹‹ተሰቅሎ።››

‹‹ፈፅሞ አላምንም። እምአእላፍ ሞቶአል ብዬ አላምንም...››

‹‹እኔም እንደሱ ነው የሚሰማኝ። የምንወደው ሰው ሲሞት ሙቶአል ብሎ ለማመን ያስቸግራል። እኔ አለ ነው የምለው። ምክንያቱም ካሳቢ አይጠፋም። ግን ትዝታው ብቻ ነው የቀረው›› አለችውና፥ መሀረም አውጥታ አይኖችዋን ጠረገች።

‹‹ግን ለምን? ለምን?›› አላት በደረቀ ጉሮሮ፥ እንደ ህፃን ፈገግታ ብልጭ ሲል ደስ ይል የነበረውን የእምአእላፍን ፈገግታ፥ ለዛና ቁም ነገር የተመላበት ቀልዱን፥ ለህይወትና ለሰው ልጅ የነበረውን የጋለ ፍቅር እያስታወስ።

‹‹ያንን ቲአትር ካሳየ ወዲህ ደስ ብሎት አያውቅም። ውስጥ ውስጡን የሚበላው ነገር ነበር›› አለችና፥ አይኖችዋንና አፍንጫዋን በመሀረም አደረቀች።

‹‹ክፍቶት አላየሁትም። ሁልጊዜ ሲስቅና ሲቀልድ ነው የማየው። ጫቱን በልቶ ‹‹ምርቅን›› ሲሰማው የሚያየው አስቂኝ የሆነውን የሰው ልጅ ጎን ነበር›› አላት።

‹‹አዎን፥ ግን እምአእላፍ ደስታውን ነው እንጂ ከሰው ጋር የሚካፈለው፥ ሀዘኑንና ብስጭቱን ከራሱ አሳልፎ ለማንም አይገልፅም ነበር።

‹‹ቢገልጽም የሚያስቅ መንገድ ፈልጎ ነበር። እያንዳንዳችን ሀዘናችን በጉያችን፤ ደስታችንን በጋራ፤ በዚች አሳዛኝ አለም ላይ ሀዘን መጨመር ምን ያደርጋል፤ ሁሉም በልቡ በቂ ሀዘን የተሸከመ ስለሆነ፤ እንዱ ከሌላው የሚፈልገው ደስታን ብቻ ነው፤ መሆንም አለበት። ይህችን አጭር ህይወት በደስታ ማሳለፍ ከፈለግን ይህችን ማርና እሬት የሆነች ህይወት›› ይል ነበር፥ ‹‹እና፥ የሚፅፈው ለሰው ልጅ ደስታን ለመፍጠር ነበር›› ብላ፥ ‹‹ነበር እንዲህ ቅርብ ናሮአል አሉ እቴጌ ጣይቱ›› አለችና፥ ተከዛ አንገትዋን ደፋች።

የደርቤ እንባ ኮለል ብሎ ወረደ። አይኔን የከፈተልኝን ወንድም አጣሁ ብሎ በማሰብ ሀዘኑ አጥንቱ ድረስ ዘልቆ ተሰማው። እንባውን በዝምታ እያወረደ፥ የእምአእላፍን ብዥ ያለ ገፅታ በእንባው ውስጥ አሻግሮ እያየ፥ ለምን ራሱን ይገድላል? ዝና ፈልጎ ነው? ወይስ መፃፍ አቅቶት? እያለ ሲያስብ ከቆየ

በሁዋላ፥ እምአሳፍ አንድ ቀን፥ ‹‹መፃፍ ያቃተው ደራሲና ጥይት የሌለው መሳሪያ አንድ ናቸው›› ያው ትዝ አለውና፥ ‹‹እንደሱ ያለ ሰው ለምንድን ነው ራሱን የሚገድለው? ለሰው ልጅ ፍፁም ፍቅር ያው ሰው እንዴት ራሱን ይጠላል? ተፈጥሮን የሚወድ. . . እ. . . እንዴት ሕይወትን ይከዳል?›› አላት፥ ብስጭት ብሎ። ከቦርሳዋ አንድ ደብዳቤ አውጥታ ሰጠችው። ደርቤ አይናቹን ጠራርጎ ደብዳቤውን ከፈተ። ደብዳቤው፥ ‹‹ፍኖትዬ - የኔ ፍቅር›› ብሎ ነበር የሚጀምረው።

‹‹መቼም ይቅርታ አታደርጊልኝም። ይቅርታ ታደርጊልናለሽ ብዬ አልጠብቅም። አድራጎቴ ከይቅርታ በላይ ነው። ህይወትን ያህል ውብ ነገር በገዛ ፈቃዱ ደህና ሁኝ ብሎ ለዘለአለም የሚሰናበት ሰው ይቅርታ ሊጠይቅም፥ ይቅርታ ሊደረግለትም አይችልም።

‹‹ግን ሊአል የተሻለ ቦታ ሳይሆን ይቀራል ብለሽ ነው! እስኮማየው ድረስ ቸኩያለሁ። መቼም ፈልጌ መንግስት ሰማያት አልሄድም። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ የሚሰለቸኝ ይመስለኛል. . .

ደርቤ ከደብዳቤው ላይ ቀና ብሎ ፈገግ አለ። በራሱ ላይ ሞት ፈርዶ መልሶ በራሱ የሚስቅ ሰው ይገርማል ብሎ አሰበና፥ ደብዳቤውን ማንበብ ቀጠለ።

‹‹ለማንኛውም ነገር ዘለአለማዊ ደስታ የሚሉት ነገር ያ አይመስለኝም። የፈጠራ ሀልም ነው።

‹‹ቸኩያለሁ። የምንጠለጠልበት ገመድ ተዘጋጅቶ ይጠብቀናል። ሸምቀቆው አፉን ከፍቶ ይታየኛል።

‹‹ፍኖትዬ፥ ለመኖር አልቻልኩም። ያለ ድርሰት ሌላ ህይወት የለኝም። ምኞቴ በድርሰት ለሰው ልጅ ደስታን ለማስገኘት ነበር። ግን ለሰው ልጅ ደስታ ለመስጠት አልቻልኩም። ራሴን አታልዬ፥ ሌሎችንም ማታለል ምን ፋይዳ አለው! በኔ ግምት በድርሰት ምንደኛ ወይም አድርባይ መሆን የሚቻል አይመስለኝም። ለስሜቱ ሀቀኛ ያልሆነ ደራሲ ለራሱም ሆነ ለሌላው ደስታ ሊሰጥ አይችልም።

‹‹ይህ ስሜት ያደረብኝ ቲአትሬን ካሳየሁ ወዲህ ነው። ከኔ የወጣ ወይም የኔ መስሎ አልታየኝም። ምክንያቱም ሀቅ አልነበረውም፣ ቢኖረውም ሀ የተድበሰበሰ ነበር። የስሜቴን ሀቅ ያንፀባርቃሉ የምላቸው ሌሎች ድርሰቶቼ ሳጥን ውስጥ ተቀልፈው ምስጥ እየበላቸው ነው። ከድርሰት ሌላ ህያውት የለኝምና በቋሚም ምስጥ እየበላን ነው ማለት ነው። ከዚህ የበለጠ ስቃይ ምናለ!

‹‹ግማሽ አካሌ በምስጥ ሲቦረቦር እያየሁ፥ አእምሮዬ ተጨንቆ የወለዳቸው ልጆቼ ለምፅ ያለባቸው ይመስል ብርሃን ተነፍጎአቸው በጭለማ ተውጠው ቀርተው እያየሁ ምኑን ናርኩት!

‹‹ፍናትዬ፥ የኢዮብ ትእግስት የለኝም። ቸኩያለሁ። አልነገርኩሽም እንጂ ህመሜም እየጠናብኝ ሄዶአል። በፊት በወር አንዴ፥ ያውም አልፎ አልፎ ይጥሰን የነበረው፥ በቅርቡ በሳምንት ሁለት ሶስት ጊዜ ይጥለኝ ጀምሮአል። እና የማስታወስ ችሎታዬ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል። ማስታወስ ከጠፋ ህይወት - ምን ህይወት አለ ብለሽ ነው? ያለፈው ህይወት ባሁኑ ውስጥ ከሌለ ወደ ፊት የሚባለው ነገር ትርጉም አልባ ይሆናል።

‹‹ፍናትዬ፥ አስለቅሁሽ መሰለኝ። ኑዛዜ መደርደሬ አይደለም። ልነግርሽ የፈለኩት ነገር ቢኖር፥ አንቺ አትገቢኝም ለማለት ነው። እርግጠኛ ነኝ የምልሽ ይገባሻል። ግን ልትረዲልኝ የምፈልገው አንድ ነገር አለ። እንዳንቺ የምትግባባኝ ሴት በህይወቴ አላጋጠመኝም። ግን ስቃይ ልሆንብሽ አልፈልግም። ለሰው ደስታን እንጂ ስቃይን አልመኝም። እኔ ፍቅርሽን ይዤ እሄዳለሁ። አንቺ ግን ትዝታዬን ይዘሽ አትቅሪ. . .

‹‹በነገራችን ላይ እንደኔ ስነ ፅሁፍ ሱስ አይሁንብሽ። ራስ ላይ ይወጣል፥ ያስከራል፥ ስቃይ፥ ለመመን ይሆናል። ቀስ በቀስ ፍፁም ተገሽሮ ያደርግሻል። እና፥ ከዚያ በሁዋላ አንቺን አያድረገኝ!

‹‹እንደ ቀናተኛ ወዳጅ ጠዋት ማታ ይነዘንዘሻል፤ ፋታ አይሰጥሽም። ስለምትወጂ ፋታ ማግኘት አትፈልጊም። የሚወዱዋት ሴት ስታኮርፍ፥ አልመጣ ስትል፥ ደም ከመጣችም በሁዋላ ስታኮርፍ፥ ስትነጫነጭ ቂይታ

በመጨረሻ ውበትዋን ከፍታ ስትሰጥና ልብ በደስታ ባህር ላይ ከሞገዱ ጋር እየተንሳና እየወደቀ በመንሳፈፍ ሲንገላታ-አቤት ደስ ማለቱ!

‹‹የደራሲ ህይወት - የሞትና የህይወት ባህር ላይ መንሳፈፍ - የባህሩ ሞገድ ተነስቶ በወደቀ ቁጥር አብራ የምትንገላታ ነፍስ-ባህሩን ተከትላ፥ ጥቁር አረንጉዋዴ ሜዳምቾን፥ ለጥ ያሉ ሜዳምቾን አሸቀማ በረሃምቾን እያቁዋረጠችና በልዩ ልዩ ምንጮች እየተመገበች፥ ባህሩ እየሰፋ - እየደፉ ሂዶ ውቅያኖስ እየሆነ - እሀ-ፍኖተዬ-በመጨረሻ - በመጨረሻ - አለም ኩሀ ናት!

‹‹ድርሰት ስቃይ ነው። ምጥ ነው። ግን ምጥ የራሱ ደስታና ውበት አለው። ወልዶ መሳሙ ደስ ይላል። ደራሲና ወላድ ይመሳሰላሉ። እኔ ግን ወልዶ ለመሳም አልታደልኩም። እንዳማጡ መቀጨት!

‹‹ግን ደስ ይላል። ደስ ይላል። በድርሰት ፍቅር የተለከፈ ደራሲ ከድርሰት ላንድ ደቂቃ እንኩዋን ተለይቶ ሲኖር አይችልም። በዚህም አልታደልኩም። ከፍቅሬ ጋር ቀኑን ሙሉ ውዬ ለማደር አልታደልኩም። የቢሮ እስረኛ፥ የድርሰት ፍቅረኛ፥ የሁለቱ ቁራኛ ሆኜ ለመኖር አልቻልኩም።

‹‹የመፍጠር ስራ የራሱ ኡደትና ስልት አለው። ደራሲ ፈጣሪ ነው። መፍጠር ያስደስታል። ደራሲ ያማልክትን ባህርይ ይጋራል። ይህን ባህርይ የሚጋራው የህብረተሰቡ ሻማ ሆኖ እያበራ በደስታ እየነደደና ራሱ በደስታው አላት ውስጥ እየተቃጠለ ነደ ሲያልቅ ብቻ ነው። ደራሲ ከፈጣሪነት ሰገነት መውረድ የለበትም።

‹‹ድርሰቶቼን ሁሉ ትቼልሻለሁ። ቀደም ብሎ ቤትሽ ያመጣሁአቸውም ለዚሁ ነው። ቤት ልለውጥ ነው ያልኩሽ ውሸቴን ነው። ግን አልዋሸሁም ለካ! ቤቱ መለወጡ አይደለም እንዴ?

‹‹ከመፃህፍት ሌላ ቅርስ የለኝም። ስለ ንብረት አስቤ አላውቅም። ደራሲ ማሰብ ያለበት ስለ ድርሰት ብቻ ነው። ፈጣሪ ምን ንብረት ያስፈልገዋል። አለም የራሱ ናት፤ የሰው ልጅ ገንዘቡ ነው ፍቅር ሙዚቃው ነው። ውበት ምግቡ ነው። ገንዘብ ትዝ አለኝ ስለ ሬሳ ሳጥን አሁን ሳስብ ነው። ሬሳዬ ካልጎማችሁ የትስ ብትጥሉኝ እኔ ምን ቸገረኝ። የሚቸገረው የሞተው ላይሆን ሀያው ነኝ እያለ ሞትን የሚጠብቀው ብቻ ነው።

‹‹ችኩያለሁ። ከሞት ጋር ቀጠሮ አለኝ፤ ይገርምሻል፥ ከቆረጡ ሞት እያስፈራም - ቢሆንም ከመሰናበቴ በፊት አንድ ቀልድ ልንገርሽ. . .

‹‹አንድ ገበሬ ከቆላ ወርዶ ወንዝ ዳር ያርሳል። ጉዋደኛው ከአፋፍ ላይ ሆኖ አያ አዝላጤ እያለ ይጠራዋል። ወይ! ይላል ስሙ ሲጠራ ሰምቶ። እናትህ ሞታለች፥ ይለዋል። ምን ሆና በል? ብሎ ይጠይቀዋል። መብረቅ መቶአት ነው! ሲል ይመልስለታል። እንዴት ትደነግጥ ጄል! አለው ይባላል።

‹‹ጥሩ ቀልድ አይደለም? ቻው፥ ፍኖትዬ። ደርቤን ሰላም በይልኝ፥ ለቀይ ኮከብ ጥሪ ታጠቅ በይው። ምስራቅ ቀይ ናት። የፀሀይ መውጫ ቀይ ነው፤ በደምህ በይበልጥ አቅላው በይው። ቻው!››

ደርቤ ደብዳቤውን አንብቦ ከጨረሰ በሁዋላ በእምቢታ ራሱን ነቅንቆ ሊያበቃ፥ ‹‹አሁንም አልገባኝም። ፊፅሞ ሊገባኝ አይችልም›› አላት።

‹‹የደረሰበት ሰው ብቻ ነው ስሜቱ በትክክል ሊገባው የሚችለው» አለችውና፥ ደብዳቤውን ተቀብላ በጥንቃቄ በማጠፍ ቦርሳዋ ውስጥ ከተተችው።

‹‹እና፥ ከዚህም ሌላ የሚጥል በሽታ ያለበት ሰው ብቻ ነው ጭንቀቱና ምሬቱ ሊሰማው የሚችለው›› አለችው በሀዘን፥ ረጂም አንገትዋን እንደ ባህር ማሽላ ዘልላ።

‹‹እና፥ ስሜቱ ይገባኛል። እምአእላፍ በዚህ አለም ላይ የሚጠላው አንድ ነገር ብቻ አለው ሳንሱር። የሳንሱር ነገር ሲነሳ ብቻ ነበር የሚናደደው። የሳንሱር ነገር ሲነሳ ከጥላቻው ብዛት ስሜቱ ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ ይሆንበት ነበር። ‹‹የወላጆች ቁጥጥር፥ የትምህርት ቤት ቁጥጥር፥ የመስሪያ ቤት ቁጥጥር፥ የሚስትና የቤተሰብ ቁጥጥር፥ የህብረተሰቡ ቁጥጥር መቼ ነው የሰው ልጅ የአስተሳሰብ ነፃነት የሚኖረው? ችግሩን በሙሉ አውርሶኝ ነው የሞተው። ከእንግዲህ የኔ ህይወት ተልእኮ እሱ የፃፋቸውን ድርሰቶች ማሳተም ነው›› አለች።

‹‹ለምን እሱ ሲያሳትማቸው አልሞከረም?››

‹‹እንደማይሆንለት ስለሚያውቅ።››

‹‹ለምን አይሆንለትም? ቲአትሩን አሳይቶ የለ?››

‹‹አየሁ፥ እሱ አብዛኛውን ጊዜ የሚፅፈው ስለ ፍትወት ነው። ‹‹የብልግና ውበት›› ይለዋል። ስለ ፍትወት ይፅፋል፥ ስለ ፍትወት ያዜማል። ለሱ ግብረ ስጋ የህይወት፥ የውበት፥ የሀሴት ምንጭ ነው. . .

‹‹ምን ይል ነበር መሰለህ? ‹‹ተፈጥሮ መፈንደቅ የምትጀምረው አበቦች ሲፈነዱ ነው። አበባ ፍትወት ነው፥ ውበት ነው። ገላቸው ፍትወት መንምዠት ሲጀምር ነው ውበት የሚጨምሩት፤ የደስታ ዜማ የሚያዜሙት። ወንድ ጡንቻው ሲያብጥ፥ ሴት እንጠንጠኔ ስታወጣ አቤት ማማራቸው! ጠረናቸው ከሩቅ ይጣራል፤ ትንፋሻቸው እንደ እሳት ምላስ ከሩቅ ይለበልባል። ፍትወት ያስፈነድቃቸዋል፥ ያስቦርቃቸዋል፥ ያቁነጠንጣቸዋል። ሰው ፍትወት ሲሳመሽ አቤት ማማሩ! ህይወት ያኔ ነው የምትጣፍጠው። አቤት ህይወት ስትጣፍጥ በወጣትነት ጊዜ! ሽማግሌ እንኩዋን ፍቅር ሲይዘው ይወራል። ፍተወት የህይወት፥ የደስታ የውበት ምንጭ ነው!›› ይል ነበር›› አለችና፥ እንባ ያቀረሩትን አይኖችዋን ጠረገች።

‹‹ታዲያ እንዲህ አይነቱ ፅሁፍ እንዳይታተም ምን ይከለክላል?›› አላት።

‹‹ህብረተሰቡ ግብረ ስጋን ያደርጋል›› እንጂ ስለ ግብረ ስጋ ማንበብና መስማት አይፈልግም። ለዚህ ነው›› አለችው፥ ብስጭት ብላ።

‹‹ማርና እሬት?›› አላት፥ የጀመረችውን ልብወለድ መፅሀፍ አስታውሶ።

ቶሎ ፅፋ ለመጨረስ ያሰበችው መፅሀፍ፥ ፍፃሜው እንደ በረሀ ኩሬ እየቀረባት በሄደ ቁጥር እየራቀ መሄዱን ላንዳፍታ በማጤን።

‹‹የቀንድ አውጣ ጉዞ ሆኖአል›› አለችው፥ የሀዘን የደስታ፥ የብስጭትና የተስፋ ጥላዎች ፊትዋ ላይ እየተመላለሱ።

እንደከረምት ሰማይ ፊትዋ ጠቆር፥ ፈካ፥ ብልጭ ድርግም ይላል።

‹‹በጣም እንደ ሰወጠሽ ይገባሻል?›› አላት፥ በፊት የሚያውቀውን ላቂታ ፊትዋንና አይንዋን በማስታወስ።

‹‹ጠባዬ እንደ መዕሀፉ ሂደት ይለዋወጣል። ፈቀቅ አልል ሲለኝና አንድ ቦታ ላይ ነክሶ ሲቆም፥ ህይወት ራሰዋ የቆመች ያህል ይሰማኛል። አላቡ በድንገት የራሱን መንገድ ቀይሶ መሄድ ሲጀምር ደግሞ ደስ ይለኛል። ህይወት ራሰዋ መፈንጠዝና መፈንደቅ ትጀምራለች። እንደ መዕሀፉ ሁኔታ ስሜቴ በቀን ብዙ ጊዜ ይለዋወጣል። የሚገርመው ነገር ብቸኝነት በጣም እያስፈለገኝ ሄዶአል። ጊዜዬን ለመፃፌ በቀር ለምንም ልሰጥ አልፈልግም። ጊዜን የሚሰርቅብኝ ሰው ደስ አይለኝም፣ ያለኝ ጊዜ አይበቃኝም። አየህ ድርሰት ንፁህ ስሜትክን፥ ጥሩ ጊዜህን ይጠይቃል። ለዚህ ነው የተሰወርኩ መሰለኝ። አየህ መፃፌ ይፈልገኛል›› አለች።

‹‹አምአለላፍ በሽታ ተጋብቶብሻል!››

‹‹የደራስያን በሽታ ይዞኛል። ግን ጥሩ በሽታ አይመስልህም? በሽታው እንደ ትኩስ ፍቅር ነው የሚጣፍጠው። አንዳንዴም ያበሳጫል። ሌሊት ግሩም መስሎ የሚታየው አሳብ በቀን ብርሃን እንደ ገና ሲመለከቱት የሚያስጠላበት ጊዜ አለ። ወረቀት ላይ ሲያሰፍሩት ባዶ የቃላት ኩዋኩዋታ ሆኖ ይገኛል። ግሩም ድንቅ አሳብ መስሎ ብቅ የሚለው ሁሉ ሀቅ ሆኖ አይገኝም። በቅርብ ሲያዩት ፕሮፓጋንዳ ወይም ስብከት ይሆናል። ይህ ሲሆን የተፃፈውን እንደ ገና መፃፍ አለ። መፃፍ እንደ ገና መፃፍ ምስጢሩ ሀቁ ቁልጭ ብሎ እስኪወጣ ድረስ። የደራሲ ረሃብና ጥማት፥ ውበትና ሀቅ ነው። ቀላል ስራ አይደለም። ያለ የሌለውን ሀይል የሚጠይቅ ትግል ነው - እና እንድንኖር የሚገፋፋኝን ያህል እየገደለኝም ነው። ‹‹ማርና አሬት ነው›› አለች፥ ሩቅ እየተመለከተችና ምላሰዋን አሹላ ጥርስዋን እየላሰች።

ጥርስዋን በምላሰዋ ስትልስ ከንፈርዋ ይረጥብና ደስ ይላል።

‹‹እንደ አብዮቱ ነው›› አላት።

‹‹አምን፥ እንደ አብዮቱ ነው›› ብላ መለሰችለት።

‹‹የቀይ ኮከብ ጥሪ! እናት ኢትዮጵያ ስትጠራኝ ይሰማኛል። ይህች ጉደኛ አገር ኮ ፍቅር ትጥላለች። በአፍሪቃ የክርስቲያን ደሴት ነበረች። ሁዋላ ደሞ የነፃነት ደሴት ሆና ቆየች። አሁን ያብዮት ደሴት ሆናለች። በቀይ ኮከብ እናስጌጣታለን። ለሮጌ ጨርቅዋን እናስጥላታለን። እምአለላፍ አንድ ቀን

‹‹ኢትዮጵያን በሚገባ የሚያውቅ ኢትዮጵያዊ፥ ኢትዮጵያ የሚወድ ኢትዮጵያን አብዮተኛ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያ አብዮት ያስፈልጋታል፥ ተሀድሶ ያስፈልጋታል፥ ያለኝ ትዝ ይለኛል አለች።

‹‹አብዮትም እንደ ድርሰት ንፁህ ስሜታችንንና ሙሉ ጊዜያችንን፥ የመፍጠር ችሎታችንን ይጠይቃል›› አላት፥ ስሜት እየተናነቀው።

ፍናት ትኩር ብላ እያየችው፥ ድንገት ፍንጭትዋን ብልጭ አድርጋ ምላስዋ በማሾል ጥርስዋን ላሰች። ከንፈሮችዋ ረጠቡ። በውስጥዋ መፈንደቅ የጀመረውን ስሜት በግድ ገታችና፥ ‹‹አብዮተኞችን ከዚህ አንፃር ለማየት ሞክሬ አላውቅም። ግሩም ነው›› አለችው።

‹‹መቼም መፅሀፍሽ ውስጥ እኔ አለሁበት አይደለም?››

‹‹ማን አለህ?››

‹‹እንዲሁ ይገባኛል። ሁሉጊዜ የምትጠይቂኝ ጥያቄዎች ይነግሩኛል። ጠያቂ፥ ጀሮና አይን ብቻ ሆነሻል።››

አባባሉ አስገርሞአት ፈገግ አለች። ፈገግታዋ ተጋባበት። ደስ አለው። የሚለማኝን ሁሉ ዝክዝክ አድርጌ ልነግራት ብችል ምን ነበረበት ብሎ ተመኘ። መፅሀፍዋ ትዝ አለውና ድንገተኛ ቅናት አደረበት። ምን ነው ባለቀላትና በተገላገለችው አለ። ለምን ያስቃያታል! የሚል አሳብ መጣበትና፥ እናቱን! አለ በልቡ።

‹‹ለምን እንዲህ ታየኛለህ?››

ጥያቄዋ አስፈራውና አይኑን ሰበረ።

‹‹ለምን ያስቃያታል እያልኩ በልቤ ስራገም ነበር።››

‹‹ማን?››

‹‹መፅሀፍሽ››

‹‹ለምን?››

‹‹በቃ አለ አይደል። ቅናት አሳደረብኝ።››

‹‹ለምን?››

‹‹መካከላችን የገባ ሰው መስሎ ስለታየኝ። እና ስለሚያሰቃይሽ።››

ውስጥዋ ይፈነድቅ የነበረው ስሜት ገንፍሎ ስለ ወጣ ዘላ ግንባሩን ሳመችው። ጉንጭዋን ሳማት። ላንዳፍታ አይኖቻቸው በቅርብ ተጋጨ። የእሳት ብልጭታ ተፈጠረ። እሱ ቀይ ኮከብ ታየው። እስዋ አዲስ ምእራፍ ታያት።

እየፈነደቀች፥ በጥርስዋም በአይንዋም ሳቀችና፥ ‹‹እምአእላፍ ሞተ። አዲስ ምእራፍ ተወለደ። እምቢ ብሎኝ የነበረውን አሳብ ፈታህልኝ›› አለችውና፥ እንደ ገና ግንባሩን ስማ እየሮጠች ስትወጣ ተከትሎ ደረሰባትና፥ ‹‹ቆይ እንጂ። ምን ነካሽ ቀብሩ መቼ ነው?›› አላት።

‹‹ውይ በሞትኩት! የመጣሁበትን ጉዳይ ረስቼው! አሁን ነው›› አለች፥ ባሳየችው ሁኔታ እንደማፈር ብላ።

‹‹አብሬሽ እመጣለሁ። ግን ሞቶአል ብዬ አላምንም።››

‹‹ደራሲ ይሞታል፥ ድርሰቱ ግን አይሞትም›› ብላ፤

‹‹ሌላም የምጠይቅህ ነገር ነበረኝ›› አለች።

‹‹ምን?››

‹‹ስለ ሂሩት።››

‹‹ጀመርሽ እንግዲህ!››

‹‹ምን?››

‹‹ያን መከረኛ ጥያቄሽን።››

ከት ብላ ሳቀች።

‹‹ሌላ ጊዜ ስለ እስዋ አጫውትሻለሁ። ለስዋ ያለኝ ፍቅርና ለቀይ ኮከብ ያለኝ ፍቅር እየተወሳሰበብኝ፥ እየተገመደብኝ ሄዶአል›› አላትና ‹‹አንዴ ቆይኝ›› ብሎአት ወደ ቢሮው ገባ።

ኮቱን ይዞ ሽጉጡን ጎኑ እየሻጠ ተመልሶ መጣና፥ ‹‹እምአእላፍን መሸኘት አለብኝ›› አላት።

‹‹ይኖራል። ከመቃብር በላይ ይኖራል። ለዘለአለም!›› ብላው ፊታቸውን ወደ መንገዱ መለሱ። እርስዋን ‹‹ማርና ሬት›› እየጠራት፥ እርሱን ቀይ ኮከብ እየጠራው. .

ምእራፍ ፱

ከማስታወቂያና መርሀ ብሄር ሚኒስቴር ሊጋለጡና ሊሙቱ ይገባቸዋል በማለት የመሰሪያ ቤቱን የአብዛኛዎቹን የመምሪያ ሀላፊዎች፥ የአንዳንዶቹን የጋዜጣና የራዲዮ ፕሮግራም ዋና አዘጋጆች እንዲሁም የአንዳንድ የጠቅላላ አገልግሎት ሀላፊዎችንና የፔርሶኔል ሹሞችን ስም ዝርዝር ይዘው የመጡት አራት ጋዜጠኞች ከደርቤ ቢሮ ወጥተው በቀጥታ ወደ ስራቸው አልተመለሱም። ተያይዘው በቀጥታ ያመሩት ወደ ሌላ ቀበሌ ነበር።

እግረ መንገዳቸውን ላንዳፍታ ቆም ያሉበት ጊዜ ቢኖር፥ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ለመግዛት ብቻ ነበር።

ጋዜጣውን ብዙ ህዝብ ይሸማ ስለነበረ በስንት ልመናና ግፊያ ለዚያው በሃያ አምስት ሳንቲም ከአንድ ጋዜጣ በላይ ለመግዛት አልቻሉም። የፊስጉት ዜና በመጀመሪያው ገፅ በሶስት አምድ፥ በሰፔ ኮር ፊደል፥ ‹‹የተጋለጡ አናርኪቶች በተራማጅ ሀይሎች ቁጥጥር ስር ዋሉ›› በሚል አርእስት ስር ተፅፎ ቦማየታቸው ተደስተው ፈገግታ በመለዋወጥ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

በአርእስቱ ስር የሰፈረው ፅሁፍ ይዘት፥ በተራማጅ ሀይሎች ቁጥጥር ስር የዋሉት ዘጠኝ አናርኪስቶች፥ ሶስት ሌቶችና ስድስት ወንዶች፥ ትናንት ጠዋት ከረፋዱ ላይ በቁጥጥር ስር ለማዋል የበቁት፥ የመሰሪያ ቤታቸው ስፊ ሰራተኛ ከሀቀኛ ታጋዮች ጋር በመተባበር ስላጋለጣቸው ነው የሚል ነበር. . .

ዘጠኙም ሰዎች በዋስይሁንና ግበረ አበሮቹ እጅ መራራ ፅዋቸውን ቀምሰው እንደ ውሻ ጥምብ ከወንዝ ውስጥ ማታውኑ ተጥለዋል። ‹‹ዋስይሁን ትንሽ ጊዜ ቢያገኝ ኖሮ እኛንም ከስንት የኢ.ዲ.ሀ. አባሎች፥ አናርኮ ፡ ፋሺስቶችና ተገንጣይ ቡድኖች ቅፅበታዊ በሆነ ፍጥነቱና ቆራጥነቱ በገላገለን ነበር›› በማለት አራቱም ጋዜጠኞች በመያዙ እየተቆጩና በደርቤ አቅዋምም እየተገረሙ ከቀበሌው ፅህፈት ቤት ደረሱ።

ከአዲስ አበባ ቀበሌዎች ሁሉ በቅድሚያ የታጠቀና አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት በተሸጋገረበት ወቅት የመጀመርያውን ጥይት በመተኮስ የህዝባዊ የቀይ ሽብርን ክስተት ያበሰረ፥ ስሙ ከሩቅ የሚያስፈራ ዝነኛ ቀበሌ

ነበር። አንዳድ በገሃነ ብቻ ከሩቅ የሚፈሩ እንጂ በመልክ ብዙም የማይታወቁ የሸዋ ክፍለ ሀገር የህዝብ ድርጅት ካድሬዎች፥ ማዶ ሆርበት ከማያውቀው ጉፈራአቸው ላይ ቁብ የምትል የማኦን አይነት ኮፍያ ብጤ ደፍተው፥ ጢሞቻቸውን አንሸራርገው፥ በተጨማደዱ ካኪ ኮቶች ላይ ሃንቸውን በሽጉጥ፥ ሽንጣቸውን በዝናር፥ ትከሻቸውን በክላሺን አስጊጠው፥ ሲጃራቸውን ቡልቅ እያደረጉ አዳዲስ ላንድሮቨር መኪናዎች ውስጥ አምስት ስድስት ሆነው በመታመቅ፥ ከቀበሌው ፅህፈት ቤት ወጣ ገባ ይሉ ነበር። ቦታው ከወትሮ ለየት ያለ ሽር ጉድ በዝቶበታል። አንድ አዲስ ክስተት ወይም እንግዳ ነገር የተፈጠረ ለመሆኑ እንኩዋን ለጋዜጠኞች ቀርቶ በቀበሌው አካባቢ ለሚያልፉትና ለሚያገድሙ መንገደኞችም ስውር አልነበረም። በአካባቢው የሚያስጨንቅ ውጥረት ሰፍኖ አየሩ ሁሉ ይከብዳል።

አራቱም ጋዜጠኞች መታወቂያዎቻቸውን አሳይተው ከራስ ጠራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ድረስ ከተፈተሹ በሁዋላ፥ ወደ ቀበሌው ፅህፈት ቤት ገብተው ትንፋሻቸውን ከመዋጣቸው በፊት፥ ጉዋድ ታደሰ ገብረ መድህን ይጠብቃችሁአል ስለተባሉ፥ ተቻኩለው ገቡ።

ቤቱ የተወረሰ ትልቅ ቪላ ሆኖ ክፍሎቹ ሁሉ ሰፋፊ ነበሩ። የገቡበት ቢሮም ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ስብሰባ ይካሄድበት እንደነበረ ያስታውቃል። የሲጃራ ጢስ ክፍሉን አፍኖታል። የሲጃራ መከስተሪያው ሁሉ የመስቀል ችቦ የነደደበት መስሎአል። ሆኖም እንደ ሌሎቹ ቀበሌዎች ቢሮ በአግዳሚ የእድር ወንበሮችና በማመልከቻ ፀሀፊዎች ወልጋዳ ጠረጴዛ አይነት ተሞልቶ አይን የሚገፈትር ሳይሆን፥ ከጥቁር ቆዳ በተሰሩ ሶፋዎች፥ በሞዝቮልድ ጠረጴዛና በቀይ ምንጣፍ አጊጦ አይን ይስብ ነበር።

ከፍሉ ውስጥ ሶስት ሰዎች ነበሩ። የቀበሌው ሊቀ መንበር ከትልቅ ጠረጴዛ ሁዋላ ተቀምጦ አንድ ወፍራም ፋይል በተመለጠ ያነብ ነበር። የቀበሌው ቤተኛ የነበረውና በእንግድነት መጥቶ ጋዜጠኞቹ እንዲገቡ የፈለገው ጉዋድ ታደሰ ገብረ መድህን የተባለው ሰው፥ ከቀበሌው ሊቀ መንበር ጠረጴዛ ፊት ለፊት አግሮቹን አጣምሮ ቁጭ ብሎ ነበር። ሳፈሬው በጥሩ ሁኔታ ተበጥሮ አምሮ ይታያል። ጠይም ፊቱ ያበራል። ትላልቅ ንፁህ አይኖቹ የማንንም ሰው ልብ ወደ ውስጥ ዘልቀው ለማየት የሚችሉ ይመስላሉ። ሪዙ በደንብ ተከርክሞ

የከንፈሮቹን ግራና ቀኝ በመያዝ አገጩ ድረስ ወርዶ ሲያበቃ ጫፉ ወደ ላይ ይቀለበላል። የማያርፉ ጣቶቹ ከሪዙ ጫፍ አይለዩም። ሪዙን መጎተት ያበዛል። ፈገግ ሲል ትላልቅ አይኖቹና ችርችም ብለው የታነፁት ነጫጭ ጥርሶቹ አብረው ለለሚስቁ፥ መልኩ ለክፉ አይሰጥም። አለባበሱም ቢሆን በጣም ይማርክ ነበር። ነጣ ያለ የሱፍ ልብስ፥ ቡና ቀለም ያለው ሸሚዝ ለብሶ ከልብሱ ጋር የሚስማማ ክራባት አስሮ ነበር። ከታደሰ ፊት ለፊት የቀበሌው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ከጎፈሬ ላይ ቁብ ያለች ቀይ ኮፍያ እስከ አይኑ ድረስ ደፍቶ፥ ክላሺኑን እንዳነገተ ቁጭ ብሎ ነበር። ካነገተው ክላሺን ይልቅ ጎልቶ የሚታየው ጉንጩ ላይ ያለው ትልቅ ጠባሳ ነበር።

ታደሰ ሪዙን እየሳቡ ‹‹ቁጭ በሉ እንጂ፥ ደሞ ጋዜጠኛ ብሉ ሰው አከባረ! ጠጣምች ናችሁ›› አለና፥ በቀልድ የተናገረ መሆኑን ለማሳወቅ ወፍራም ፈገግታ አሳያቸው። ቀጥሎ፥ ‹‹እህስ ጉዋዶች፥ አዲሱ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ምናላችሁ ታዲያ?›› ብሎ ጠየቃቸው።

አራቱም ጋዜጠኞች ተያዩ። ታደሰ የዚህኛው ቀበሌ ነዋሪ አልነበረም። በቀበሌው ውስጥ የተለየ ሀላፊነትም አልነበረውም። ሆኖም በቀበሌው ላይ ከፍተኛ ስልጣን ነበረው።

ታደሰ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ነበር። አንድ ቀን ከሆነለትም፥ በትርብ ቀን ውስጥ፥ የማስታወቂያና መርህ ብሄር ሚኒስቴርን አመራር ለመውሰድና ያንን አመፀኛ ቤት ለማስተካከል ከፍተኛ ጉጉት እንደነበረው ጋዜጠኞች ለለሚያውቁና፥ እርሱም ቢሆን፥ ‹‹ነገ ተነገወዲያ ተሹሜ ልመጣ ነው፥ ከእናንተ ጋር እጅና ጉዋንት በመሆን ነው ያንን አመፀኛ ቤት የማስተካከለው›› እያለ በየቀኑ ስለሚነግራቸው፥ ምናልባት ምኞቱ ተፈፅሞ ቋሚ ተጠሪ ወይም ሚኒስትር ሆኖ የመጣ እንደሆነ በማለት ለእርሱ ያላቸውን አክብሮትና አድናቆት በማያሻማ ሁኔታ ሊገልፁለት ይሞክሩ ነበር። አራቱም ተያይተው ዝም ሲሉ ጊዜ፥ ታደሰ ለማደፋፈር ያህል፥ ‹‹አይን አውጣ ጋዜጠኛ አይን ያፍራል እንዴ?›› አላቸው።

ሽበት ጣል ጣል ያለበት ባለ ወርቅ ጥርስ ጋዜጠኛ ቀደም ብሎ፥ ‹‹አዎን፥ ጉዋድ ጠዋት እንደ ደወልክልኝ ለነርሱም ነግሬ ሊስቱን ይዘን ሄደን ነበር. . .›› ከማለቱ፥ ታደሰ ተቻኩሎ፥ ‹‹ምናላችሁ ታዲያ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ከዚህ ሌላ ማስረጃ አላችሁ ወይ ብሎ ጠየቀን››

‹‹መቼ ይህ ብቻ!›› አለ ባለጎርናና ድምፁ ጋዜጠኛ፥ ‹‹ፀረ ህዝብ ሀይሎች ማስረጃ እያዝረከረኩ አሻጥራቸውን በገሃ እጃቸው ያጋልጡ ይመስል፥ ማስረጃ አምጡ ከማለቱም ሌላ፥ ምክርም ሊሰጠን ሞክሮ ነበር›› አለ፥ ለደርቤ ምን ያህል ንቀት እንዳደረበት ለማሳየት ፊቱን ኮሶ አስመሰሉ።

‹‹ምን ብሎ እባክህ?››

የቀበሌው ሊቀ መንበርና የአብዮት ጥበቃው ሊቀመንበር ደርቤ የሰጠውን ምክር ለመስማት በይበልጥ ጆሮዎቻቸውን ከፈቱ።

‹‹ርምጃ ከመውሰድ በፊት ሁኔታዎችን ማገናዘብ ያስፈልጋል፣. . .እ. . . ቃታ ከሳቡ በሁዋላ ጥያቄ ማቅረብ አክትሞአል. . . ሀሊናቸውን ያልመረመሩ ጠቁዋሚች አብዮቱን ከስህተት ላይ ይጥላሉ!›› እያለ ሊያስተምረን ነው የቆየው. . .

‹‹አላልኩዋችሁም!›› አለ ታደሰ ወደ ሊቀ መንበሩ ዙሮ። ቀጠለና፥ ‹‹በዬ ነበር። ፀረ-ቀይ ሽብር የሆኑ ለዘብተኛና ቀልባሾች በቀበሌ አመራር ውስጥ ሰርገው እየገቡ ነው። ወይም ሆን ተብሎ እየተተከሉ ናቸው። ይህን አደገኛ አዝማሚያ መታገል አለብን!›› አለና፥ በንዴት ሪዙን ጎንተል ካደረገ በሁዋላ፥ ‹‹አዎን. . . ኢ.ማ.ሌ.ድ.ሀ. ምናምን ማለት ጀምረዋል። እኛ የምናውቀው የማሌ ድርጅት የለም። የሁለት መስመር ትግል ሲካሄድ የቆየው በኛ ድርጅትና ከስረት በደረሰበት በኢ.ህ.አ.ፓ መካከል ብቻ ነው። ሌላ አናውቅም። አሸናፊው መስመር የኛ ብቻ ነው። ሌላ የለም። መኖር የለበትም። ኢ.ማ.ሌ.ድ.ሀ. ብሎ ነገር ደግሞ! የኛን ድርጅት ለማድከም የንኡስ ከበርቴ ጥርቃሞዎች የሚሸርቡት ሴራ ነው። ሌላ አይደለም!›› አለና በንዴት ጠረጴዛውን መታው።

ወዲያውኑ የቀበሌው አባል የሆነ አንድ ሰው በጥድፊያ በሩን አንኩዋኩቶ ዘው ብሎ ገባና ወደ ዋናው ሊቀ መንበር ጠጋ ብሎ በጆሮው አንድ ወረ ከነገረው በሁዋላ፥ አንድ ብጫ ማህደር በእጁ ሰጥቶት ተመልሶ ወጣ።

ሊቀ መንበሩ ጊዜ አላጠፋም። ማህደሩን ከፍቶ ውስጡ የነበረውን ወረቀት ቅንድቡን ከፍ ዝቅ እያደረገ ማንበብ ጀመረ።

ታደሰ ሪዙን እየጎነተለ ሲያስብ ቆየና፥ «ጥዋዶች፥ ባታውቁት ነው እንጂ በድርጅታችን ላይ አደገኛ አዝማሚያ ከየአቅጣጫው እየተፈጠረ ነው። የአገሪትዋ ኢኮኖሚ የወደቀው፥ አገራትዋ በሶስቱም ማእዘናት በወረራ የተናጋችው፥ የውስጥና የውጭ ጠላቶች የተነሱባት፥ በኛ ድርጅት ምክንያት ነው፥ ይባላል። ይህን ጥፋት ሁሉ ያመጡት እነርሱ ናቸው፤ ደርግ እንደ ጀመረው ብቻውን ቢጨርሰው ኖሮ ይህ ሁሉ ጣጣ አይደርስም ነበር እየተባለ በሰፊ መወራት ጀምሮአል። ይህ አደገኛ አዝማሚያ ዞሮ ዞሮ የሚያተኩረው በድርጅታችን ላይ ነው። ካልቀደምን መቀደም ይመጣል። ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ድርጅታችን የበላይነት እስካለው ድረስ፥ በተለይም ባሁኑ ወቅት፥ «ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን» የሚለውን መፈክራችንን በይበልጥ ከፍ አድርገን ማንሳት አለብን። በዚህ መፈክር ዙሪያ ሰፊውን ህዝብ አሰልፈን በመነሳት ካልመራነው ድርጅታችን አስጊ ሁኔታ ውስጥ ባይወድቅ ምናለ በሉኝ» አለ።

የቀበሌው ሊቀ መንበር፥ ቅንድቡን እንደ ልማዱ ከፍ ዝቅ እያደረገ በተመስጦ ያንብ ነበረና፥ ታደሰ የተናገረውን አልሰማም። ሌሎቹ ግን በአላቡ የተስማሙ መሆናቸውን በመግለፅ ራሳቸውን አስር አስር ጊዜ ይነቀንቁ ነበር። ወደ ጋዜጠኞቹ ዞር አሉና፥ «እምን. . ሕ. . . መፈክራችንን በይበልጥ ቦማስተጋባት ረገድ እናንተ ከፍተኛ ሚና ልትጫወቱ ትችላላችሁ። መፈክራችን መስሪያ ቤታችሁ ውስጥ በተለገሰን አድሃሪ ጋዜጠኞችና አድር ባይ ባለስልጣኖች መታፈን ጀምሮአል አሉ። ወቅታዊና አንገብጋቢ የሆነውን መፈክራችንን በሚቻላችሁ መንገድ ሁሉ በየቀዳዳው ማሾለክና ማስተጋባት የናንተ ታጋይ ጋዜጠኞች ታሪካዊ ሀላፊነትና ግዴታ ነው። የምላችሁ ነገር ገብቶአችሁ. . ያለ?. . . ጥሩ ነው. . . እኔም በቅርቡ ወደ እናንተ መስሪያ ቤት ሳልዛውር አልቀርም. . . አብረን እንታገላለን» አላቸውና ወደ ሊቀ

መንበሩ መለስ ብሎ፥ ‹‹አንተ ደግሞ ፋይል ማገላበጥ ብቻ ነው የምትወደው፥ ለመሆኑ አዳምጠኸኛል?. . .›› ከማለቱ፥ የቀበሌው ሊቀ መንበር ከሚያነበው ወረቀት ላይ ቀና ብሎ፥ ‹‹ይግረምህና የማነበው ደርቤ ትናንት ማታ ሲመረጥ የተናገረውንና ዛሬ ጠዋት አንድ የደርግ ተወካይ ስለ ዋስይሁን ድርጊት የለጠውን አስተያየት ሪፖርት ነው›› አለው።

‹‹ምናለ? ንገረን›› አለ ታደሰ፥ ሪዙን እየሳሳበ።

‹‹ደርቤ ሲመረጥ ምናለ መለስህ?›› የሚገርም ነው።

‹‹ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እንዲሰፍን በቀበሌያችን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ቀበሌዎች ላይ መዝመትና መታገል አለብን. . .ቀበሌዎች የአንድ ቡድን መሳሪያ መሆን የለባቸውም›› እያለ ሲፎክር ነበር አሉ. .››

‹‹አላልኩዋችሁም? የኛን ድርጅት ማለቱ ነው. . .››

‹‹መቼ በዚህ ብቻ ተወሰነና! ዛሬ – አሁን በቅርቡ - የቀበሌውን የአብዮት ጥበቃ አባሎች ሰብስቦ ‹‹ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን›› ከሚለው ከኢ.ህ.አ.ፓ. መፈክር በይዘትም ሆነ በአላማ ያልተለየ፤ ስልጣን የጠማቸው ንኡስ ከበርቴዎች ጥያቄ ስለሆነ አንቅረን መትፋት አለብን. . . እርግጥ የጭቆኖች ትግል ከዲሞክራሲያዊ መብት ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። ሆኖም የጭቁኖች ዲሚክራሲያዊ መብት የሚገኘው በስጦታ ሳይሆን በትግል ነው. . . ትግል ደግሞ ያለ ንቃት፥ ያለ ድርጅትና ያለ ትጥቅ ግቡን ሊመታ አይችልም። አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት በተሸጋገረበት ማግስት፥ ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን፥ በሚል መፈክር ስር ገና ያልነቃውን፥ ያልተደራጀውንና ያልታጠቀውን ጭቁን ወዛደርና ገበሬ ለማስለፍ መሞከር ላበጠና ያለ እኔ ማን አለ? ለሚል ድርጅት ስልጣን መጠየቅ ካልሆነ በቀር ሌላ ትርጉም የለውም። እኛ መስለፍ ያለብን፥ ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች በትግል፥ በሚለው መፈክር ስር ነው›› ፥ እያለ ከፍተኛ ቅስቀሳ ያካሄድ ነበር አሉ››

‹‹አላልኩዋችሁም? ቅደም ብዬ ነበር እኮ. . . አዝማሚያው አደገኛ ነው. . .››

‹‹ዋስይሁን ትናንት ማታ አብዮታዊ ርምጃ ስለ ወሰደባቸው ዜጣን አናርኪስቶች አንድ የደርግ ተወካይ ደግሞ እንባውን እያዘራ. . . ‹‹ሁኔታው አሳዛኝ መሆኑን ሁሉም ተገንዝቦታል. . . ነገሩ ያሳዝናል. . . ባሁኑ ጊዜ አገሪትዋ ያለችበትን ሁኔታ ሁላችንም የምናውቀው ነው. . . የሰፊው ህዝብ ወዳጅና ጠላት ማን እንደሆነ ገና አልለየም›› ሲል ነበር አሉ. . .››

‹‹ቀይ ሽብርና እንባ አብረው አይሄዱም። አዎን. . . ይህ ሁሉ የተፋፋመውን ቀይ ሽብር ለማኮላሸት የሚቀነባበር ሴራ ነው። ሌላ አይደለም። አሁን የሚያስፈልገው ፍጥነት፥ ፍጥነት ብቻ›› አለ ታደሰ ሪዙን ክፉኛ እየሳበታተሰ።

ባለ ጎርናናው ድምፅ ጋዜጠኛ በእጁ የያዘውን ጋዜጣ ተመለከተና ‹‹እንዴ! ምን የሚያሳዝን ነገር አለ? በመሰሪያ ቤቱ ስፊ ሰራተኛ ተጋልጠው ነው ርምጃ የተወሰደባቸው›› አለ።

የቀበሌው ሊቀ መንበር ራሱን እየነቀነቀ፥ ‹‹አዎን. . . ብቻ ሰራተኞቹ ለደርግ ተወገዩ፥ ‹‹እኛ አላጋለጥንም። ውሸት ነው›› ብለዋል አሉ›› አለና በረጅሙ ተነፈሰ።

ታደሰ በሁኔታው ተገርሞ ሪዙን እየሳበ፥ ‹‹አጋለጡ አላጋለጡ አሁን ጉዳዩ እሱ አይደለም። ማጋለጥ በድምፅ ብልጫ የሚደረግ መሰላቸው እንዴ? ዋስይሁን መፈታት አለበት። ቅድም በስብሰባ ላይ እንደተነጋገርነው፥ የዋስይሁን መፈታት ወይም አለመፈታት ለድርጅታችን ወሳኝ ጥያቄ ነው። በነፃ እንዲለቀቅ ጉዋዶች በመታገል ላይ ናቸው። ዋስይሁን ላይ አንድ ነገር የደረሰ እንደሆነ ድርጅታችን እስካሁን ከሀዝቡ ዘንድ ያተረፈውን እምነት ያጣል። የሚያስከትለው የፖለቲካ ሁኔታ ቀላል አይደለም። ሌላም ጉዳይ አለ›› ብሎ፥ ወደ ጋዜጠኞቹ መለስ በማለት፥ ‹‹ጉዋዶች እናንተ ልትሄዱ ትችላላችሁ። ድርጅታችሁ የጣለባችሁን ሀላፊነት አትርሱ። አንድ ነገር ቢደርስባችሁ ደውሉልኝ። ያንን ቤት የምናፀዳበት ቀን ተቃርቦአል። ስለጠየቃችሁኝ ትጥቅ ጉዳይም አልረሳሁም። ምናልባት ነገ ታገኙ ይሆናል። በርቱ!›› አላቸውና ተነስቶ እጃቸውን በጋለ ስሜት እየጨበጠ ሸኛቸው። አራቱም ጋዜጠኞች የበለጠ ሀይል እየተሰማቸው ነበር የወጡት።

ታደሰ ወደ ቀበሌው ሊቀ መንበር ጠጋ ብሎ፥ ድምፁን ዝቅ በማድረግ ‹‹ይሄ ደርቤ የምትሉን ለው አንድ ዘዴ ፈልጎ ከዚያ ማስወጣት፥ ካልተቻለም

ሌለ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። አዝማሚያው አደገኛ ነው›› አሰ፥ ፍርጥም ብሎ።

ኮፍያውን አይኑ ድረስ ደፍቶ ሲጻራ እያከታተለ የሚያጨሰው የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ለመጀመርያ ጊዜ እንደ ምንም አፉን አላቆ እያንዳንዱዋን ቃል እየቆጠረ፥ ‹‹አምን. . .እዚያ. . .እንትን. . . እንትን. . . ቀበሌ ውስጥ የኛም እንትን ጉዋደኞች አሉ። እንትን. . . ዘዴ ፈልገን. . . እንትን. . . እንትን. . . እንትን. . . እንዲጋለጥ. . . እንትን. . . እንትን. . . ለማድረግ ይቻላል›› አለ። ነገሩን እንትን. . . እያለ በመጎተት ትእግስታቸውን አስጨረሰ። በጣም አይነ አፋር ስለነበረና ለመናገርም ሲፈልግ ቃላት ስለማይያዙለት በርከት ያሉ ሰዎች ባሉበት መናገር አይወድም። በህፃንነቱ የወደቀ ቦምብ አግኝቶ ሲቀጠቅጥ ፈንድቶበት ነው ይባላል፥ ግራ እጁ ቆራጣ ነበር። በአንድ እጁ የተኮሳት ጥይት መሬት ጠብ ስለማትልና ርህራሄ የሚሉትን ነገር እስከነቃሉም ስለማያውቅ ከሩቅ የማይፈራው ሰው አልነበረም። መናገር ከመጥላቱ የተነሳ ብዙ ሰዎች ካሉበት ቦታ መገኘት ደስ አይለውም ነበር። በሰዎች መካከል ሲሆን ሰውነቱ ሁሉ ይወጣጠርና የሚያደርገው ነገር መላቅጡ ይጠፋዋል።

የቀበሌው ሊቀ መንበር ፊቱ የነበረውን ወረቀት በአይኑ ጨረፍ አደረገና፥ ‹‹ለማጋለጥ እንኩዋን ለጊዜው አመች ሁኔታ ያለ አይመስለኝም። በሪፖርቱ ላይ እንደ ተመለከተው በብዙ ድምፅ ነው የተመረጠው›› አለ።

ታደሰ እንደ መበሳጨት አለና፥ ‹‹ሌላውስ አማራጭ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ከላይ ድጋፍ ያለው ይመስለኛል። ባይኖረው መቼ ይደፍር ነበር?. . .››

‹‹ድጋፍ ቢኖረው ታዲያ ምን ይሁን! አንተ ደሞ ትገርመኛለህ! የኛ ጥይት ቦታ አለው አሉህ? ብሎ አመናጨቀው። ሶስቱም ተያዩና ፈገግ አሉ. .

ምእራፍ ፲

ወይዘሮ አምሳለ ለደርቤ ስልክ ደውለው፥ ዛሬ ፈፅሞ ስለማይመቸኝ ለመምጣት አልችልም ካላቸው ወዲህ፥ ተናቅሁ፥ ተደፈርኩ፥ እንዴት እንደ መናጢ ድሀ አይመቸኝም ብሎ መልስ ይሰጠኛል? በማለት ተናደው ነበር። ስልኩን ከዘጉ ጀምሮ እየደጋገሙ ‹‹ወቸ ጉድ! አንድ መናጢ ደሀ አይመቸኝም ይበለኝ! ዛሬ ነው የሞትኩት!›› በማለት በንዴት ጦፈው፥ ደርቤ ቤታቸው እንዲመጣ የፈለጉበትን ምክንያት ከነአካቴው ረስተው፥ ስለ ክብራቸው መደፈር ብቻ ውስጥ ውስጡን እንደ እሳት እየነደዱ ‹‹ጉድ! ጉድ! ጉድ! እያሉ፥ አንዳንዴም ‹‹ድሀ ከእድፍና ከብልግና ድሮውኑስ መቼ ይርቃል? የጨዋ ልጅ ይግደለኝ!›› በማለት እየተሳደቡ ነበር የቆዩት።

ወይዘሮ አምሳለ ‹‹ወቸ ጉድ!›› ባሉ ቁጥር፥ አቶ ጉልላት፥ እልሁና ንዴቱ ዞሮ ዞሮ እርሳቸው ላይ እንዳያርፍ በመፍራት፥ የሆነ ያልሆነ ምክንያት በመፍጠር ቁጭ ብድግ፥ ወጣ ገባ እያሉ፥ ቁርጠት እንደ ያዘው ሰው ሲንቆራጠጡ ቢቆዩም፥ ሊያመልጡ አልቻሉም። ገና ከደጅ ገባ ሲሉ፥ ወይዘሮ አምሳለ ሲብከነከኑ ቆይተው ነበርና፥ ‹‹ላንተ ስል ኮ ነው ይህን ውርደት የተከናነብኩት! ምን ነው አሁንስ ሞቴን ባቀረበው! እግዜሩም አልሰማ አለ!›› አሉዋቸው ምርር ብለው።

አቶ ጉልላት በመጡበት እግር ወደ ሁዋላ ለመመለስ አልቻሉም። በልባቸው፥ ‹‹አዬ አነሳዬ! አሁንስ የት አባቴ ልግባ?›› ብለው አሰቡና፥ ‹‹ምን አድርግ ነው የምትሪኝ የኔ እህት? ጊዜው ነው እንጂ ሰው ኮ አላዋረደንም›› አሉዋቸው፥ ነገሩን ለማብረድ ዘዴ እየፈለጉ።

‹‹ኤጭ! የምን ጊዜ ነው እሱ! ሰው ነው ጊዜን የሚቆጣጠረው። ሰው የለም!›› ብለው አመናጨቁአቸውና ቀጥለው፥ ‹‹መሬቴስ ይሂድ። ጦሌን ይዘ ነው የሄደው። ደግሞ ክብሬን ልገፈፍ?›› አሉዋቸው።

‹‹ሄደህ ተታኮስ ነው የምትይኝ? . .››

‹‹አዬ እቴ! ምን ወንድ አለና?››

‹‹ክብር የተገፈፈው መሬት የሄደ እለት ነው. . ››

‹‹ማን አስወሰደና?››

‹‹እኔው ነኛ የፈረደብኝ!››

‹‹ታዲያስ?››

‹‹በፈጠረሽ አምላክ ተይኝ! የባሰ ውርደት፤ ከውርደትም ግርፋትና ሞትም ሊከተል ይችላል. . .››

‹‹እኔ የሸዋሱል ልጅ!››

‹‹አዎን፥ በስልክ አክብሮ ዛሬ አይመቸኝም ያለሽ ሰው፥ ሊያስረንም የሚችል መሆኑን ዘነጋሽ መሰለኝ. . .››

‹‹ይሄው አይደል የቀረው? ምን ነው ሞቴን ባቀረበው! እንደዚያ በትህትና ስጠይቀው. . . ኤጭ!. . . ምን ነው ምላሴን በቆረጠው ኖሮ!. . .››

‹‹አይደለም። አሁንም የሚያዋጣው ትህትና ነው። ደግ አድርገሻል። አሁንም የሚያዋጣው ትህትናና ዘዴ ነው።››

‹‹ትንሽ ሰው መቼም ከፍ ላድርግህ፥ ላክብርህ ሲሉት፥ ከራስ ላይ ይወጣል።››

‹‹ግድ የለሽም አይወጣም። በዘዴ የተያዘ ማንኛውም ነገር ከልኩ አያልፍም።

ወይዘሮ አምሳለ በባላቸው አስተያየት ያልተስማሙ መሆናቸውን አመግለፅ ራሳቸውን እየነቀነቁ፥ ‹‹ከልኩ አያልፍም ሲባል ራስ ላይ እየወጣ ሂዶአል እቴ!›› ከማለታቸው፥ ልጃቸው ተሰማ በረጅም ቁመናው እየተንገላወደ ው ብሎ ገባ። ወይዘሮ አምሳለ ነገራቸውን አቁዋረጡና ተሰማን በትላልቅ አይናቸው ከላይ ወደ ታች፥ ከታች ወደ ላይ ከቃኙ በሁዋላ፥ ‹‹ ምን ነው ንዲህ ከሰውነት ወጣህ ልጄ? አመድ የነፋብህ መስለሃል። ይህን ጢምህን ግሞ ብትላጨው ምን አለበት ልጄ? የምን ማስቀየም ነው እሱ!›› አሉት፥ ጢሙ አለ ቅጥ ማደግ እንደ አዲስ ነገር ተበሳጭተው።

አቶ ጉልላት ግን በተሰማ መጎሳቆልና ከሰውነት መውጣት፥ እንዲሁም ካለ እድሜው በድንገት መገርጀፍ ቢገረሙም፥ ጭንቅላታቸውን የመታቸው ወይዘሮ አምላለ ያላጤኑት ሌላ ነገር ነበር።

‹‹የደነገጥክ ትመስላለህ። ምን ሆነሃል?›› ብለው ጠየቁት።

‹‹ ሂሩቴ ደህና አይደለችም እንዴ?›› አሉ ወይዘሮ አምላለ።

‹‹ደህና ናት›› አላቸው።

‹‹እኮ ምን ሆነሃል?›› ብለው እንደ ገና ጠየቁት፥ የተሰማን መንፈስ መሸበር እያጤኑ።

ተሰማ የሰውነትም ሆነ የመንፈስ እርጋታ አይታይበትም ነበር። እጁም እግሩም እረፍት አጥተው ይወራጫሉ። አልፎ አልፎ እንደመደንገጥ ያደርገውና ሰውነቱ ሽምቅቅ ይላል።

ወይዘሮ አምላለ፥ ጢሙን በጥላቻ አይን እየተመለከቱ፥ ‹‹ተናገር። ምን ይዘጋሃል?›› አሉት።

ተሰማ ሁለቱንም በአይን ጨረፍታ ተመለከተና አቀርቅሮ፥ ‹‹ስለ ደርቤ ጠዋት ደውዬ ነበር. . .›› አለ።

ወይዘሮ አምላለ፥ የደርቤ ስም እንደ ገና በመነሳቱ በአንድ ፊት እየተንገፈገፉ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ተሰማ ሊናገር ያሰበውን ለመስማት እየቸኮሉ፥ ‹‹አምን፥ ምን ተፈጠረ ታዲያ?›› ብለው አጣደፉት። እንዳቀረቀረ ቀርቶ፥ በጫማው ወለሉን እየፈተገ፥ ‹‹በሂሩት በእኔና በደርቤ መካከል አደገኛ ሁኔታ ተፈጥሮአል›› አላቸውና፥ ከባድ ሸክም ከትከሻው ላይ እንዳወረደ ሰው ቁና ተነፈሰ።

‹‹እንዴት ያለ አደጋ በል?›› አሉ አባትየው።

አሁንም እንዳቀረቀረ ወለሉን በጫማው በሀይል እየፈተገ፥ ‹‹እዚህ. . .ክ. . .ሊ. . .ህ. . .ስ. . .ፓ መሆናችንን ያውቃል›› አለ።

‹‹ኢ.ሀ.አ.ፓ.? እናንተ? የኔ ልጆች? ይህንኑ ነበር የፈራሁት!›› አሉ አቶ ጉልላት። ቀጠሉና፥ ‹‹ምን ቆርጦአችሁ ነው እዚያ ውስጥ የገባችሁት? አዬ ዘንድሮ! አዬ ዘንድሮ! ›› ብለው ራሳቸውን ይዘው አቀረቀሩ።

ወይዘሮ አምሳለ ከተቀመጡበት ተነስተው በሁለቱም እጆቻቸው ራሳቸውን ይዘው እየተንጎራደዱ፥ ‹‹ወይ ጉዴ! ወይ ጉዴ! ወይ ጉዴ!›› እያሉ ቅልጥ ያለ ሙሾ ማውረድ ጀመሩ።

አቶ ጉልላት የራሳቸውን ሀዘን፥ ብስጭትና ንዴት ትተው ተዱ እንጂ! ምን ነካሽ?›› እያሉ ግልግል ገቡ።

‹‹ጉልላቴ ተወኝ! ተወኝ! ተወኝ! ሂሩት፥ ሂሩቴ ልጄ! ይሄኔ በመንገድ ዳር ደፍተዋት ይሆናል፥ ደፍተዋት ይሆናል. . .››

‹‹የመላኩ ያለህ! አታሙዋርቺባት! ተይ ነው የምልሽ. . .››

‹‹እኔን. . . እኔን ያስቀድመኝ ልጄ! እናትሽ ትደፋልሽ ልጄ!›› አሉና፥ ወደ ተሰማ መለስ ብለው፥ ‹‹ምን በደልኩዋችሁ? ምን በደልኩዋችሁ?›› እያሉ ራሳቸውን ይዘው ጮሁበት።

ተሰማ በእናቱ ጩኸት ተሸማቅቆ የባሰውን አቀረቀረ። አንድ ወንድና አንዲት ሴት የቤት ሰራተኞች በወይዘሮ አምሳለ ጩኸት ተደናግጠው መጥተው ከበር ላይ ቆመው ነበር።

ነገሩ ባይገባቸውም በእሜቴ ልቅሶ ሆዳቸው ባብቶ አይኖቻቸው እንባ አቅርረው ነበር። አቶ ጉልላት በአንድ ፊት ባለቤታቸውን እያፅናኑ፥ ሰራተኞቹን፥ ‹‹ሽረ ምንም የለም። ደህና ነው። ብለው ወደ ስራቸው እንዲመለሱ አዘዙአቸው።

ሰራተኞቹ መሄዳቸውን ካረጋገጡ በሁዋላ ወደ ተሰማ ተመልሰው፥ ‹‹ለመሆኑ ሂሩቴ የት ናት?›› ብለው ጠየቁት።

‹‹ሱቅ ናት። እዚያ ትቼአት ነው የመጣሁት›› አላቸው፥ ቀና ብሎ።

ወይዘሮ አምሳለ ወዲያውኑ ስልክ ደወሉ። ከብዙ ጊዜ በሁዋላ ሱቁ ውስጥ የሚሰራው አሽከር ስልኩን አነሳ። ሂሩት አሁን በቅርቡ የውጣች መሆንዋን ነገራቸው።

‹‹ጉዋደኞችዋ ዘንድ ሄዳ እንደሆን?›› አሉ። ወይዘሮ አምሳለ እያከታተሉ ስልክ መደወል ጀመሩ። ዘመድ ቤት - የሂሩት ጉዋደኞች ቤት - አንድም አልቀራቸው። ሂሩት ያለችበትን ግን የሚያውቅ አልነበረም።

‹‹ጉልላቴ ዝም ትለኛለህ? ልጄን አጣሁዋት ኮ. . .›› አሉ ተስፋ ቆርጠው።

‹‹ምን ሆንሺብኝ?››

‹‹እንፈልጋት እንጂ!››

‹‹የት ብለን? አዲስ አበባ ሰፊ ነው. . .››

‹‹ሬሳ ወድቆአል በተባለበት ሁሉ. . .››

‹‹አታሙዋርቺባት ነው የምልሽ አንቺ ሴት! ዛሬ በቀኝ ጎንሽም አልተነሳሽም? ወች ጉድ!››

ተሰማ ከተቀመጠበት እየተነሳ ‹‹ባይሆን እኔ ዞር ዞር ብዬ ልፈልጋት›› ሲል አሳብ አቀረበ።

አቶ ጉልላት ተቆጥተው ‹‹አርፈህ ተቀመጥ! ከዛሬ ጀምሮ እግርህ ከዚህ ቤት ዝር እንዳይል! ዋ! ገብቶሃል? አደብ ግዛ። ከእንግዲህ ልጅነት የለም። እምቢ ያልክ እንደሆነ ካንተ ወይም ከኔ ይለይልናል። ልባርግ!›› አሉት።

አባቱ እንደዚያ ምርር ብለው ተናግረውት ስለማያውቁ ተሰማ ደነገጠ። እናቱም ለልጆቻቸው እንደዚያ ሲጨነቁና ሲያለቅሱ በማየቱ በአንድ ፊት ልቡ ተነክቶ ነበር። ስለሆነም ፈቃዳቸውን ከመፈፀም ሌላ አማራጭ እንደሌለው ታወቀው። ይሁን እጂ እህቱን ካለችበት ፈልጎ የማግኘቱ ጉዳይ ምን ያህል አስቸኳይ እንደሆነና ማምሻዋን ምን ለማድረግ እንዳቀደች ሊነግራቸው ፈልጎ ነበር። የወላጆቹን አሳዛኝ ሁኔታ በማየትና የተናገርኩ እንደ ሆን የባለውኑ ተደናግጠው አንድ ነገር ይሆናሉ፥ ወይም ሊፈልጉዋት ወዲህና ወዲያ ሲሉ

ላያስቡት በገዛ እጃቸው አጋልጠዋት ያርፋሉ ብሎ በመገመት ዝም አለ። ሆኖም አሳቡ ሁሉ ለሁለት ተከፍሎ ነበር።

‹‹ምን ነው አሁን እግር ጥሎአት ከተፍ ባለች!›› ብሎ በልቡ ተመኘ። አዎን፥ ሂሩት ብትመጣ ተሰማ የሚያደርገውን ያውቅ ነበር። በአሳቡ ፍፁም ቆርጦ ነበር። በደርቤ ላይ እምነት ስለነበረው፥ ሂሩት እንደ መጣች ደርቤን ባስቸኩዋይ ጠርቶ፥ ራሱንና እህቱን በማጋለጥ እጃቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ነበር ያቀደው።

ሂሩት ግን ቤት አልመጣችም። ጊዜው ደግሞ ይሮጥ ነበር። ሄጄ ልፈልጋት ይሆን? ወይስ እዚህ ልጠብቃት? እያለ ሲያመነታ ቆይቶ፥ ምናልባት ትመጣ ይሆናል፥ መምጣት አለባት፤ እራስዋን ለማጥመድና ከአደጋ ለማዳን ከዚህ የተሻለ ቦታ የለም፥ በማለት ቆረጠና ከቤት ሊቆያት ወሰነ።

ወይዘሮ አምላለ ጨኸታቸውን አቁመው ስሜታቸውን ገታ በማድረግ ሊያስቡ ቆዩና፥ ‹‹ በል ተሰማ አንተ ወደ መኝታ ቤትህ ሂድ። ከዚህ ቤት ዝር ማለት የለብህም›› ብለው ነገሩት። ከክፍሉ መውጣቱን እንደ ተመለከቱ ወደ ባላቸው መለስ ብለው፥ ‹‹ይህ መናጢ ሰው በሁላችንም ላይ መጣ አይደለም?›› አሉ።

ሚስታቸው አንድ ነገር እንዳሰቡ ገባቸውና፥ ‹‹አምን፥ ጉድ ነው! አጥፊያችንን ኖሮአል ለካ ያሳደግነው? እግዜርን ምን ብንበድለው ይሆን አስተምረን ያሳደግነውን ሰው እንዲያጠፋን የፈረደብን?›› አሉዋቸው፥ በሀዘን ተውጠው።

‹‹አይ፥ ይቅር ግድ የለም›› አሉ፥ ወይዘሮ አምላለ።

‹‹ምኑ?››

‹‹ምንም አይደለም።››

ወይዘሮ አምላለ ያሰቡትን ለመናገር አልፈለጉም። የሚቻል ቢሆን ኖሮ ቄንቅላታቸው ውስጥ የገባውን አሳብ ከራሳቸውም በደበቁ ነበር። አቶ ጉልላት የሚስታቸውን አይን ትኩር ብለው ቢመለከቱም፥ አሳባቸውን ለማወቅ አልቻሉም። በሚስታቸው ፊት ላይ ከዚህ ቀደም አይተውት የማያውቁት፥

ፍፁም እንግዳ የሆነ የጭካኔ መልክ ስለታያቸው ተጨንቀው፥ ‹‹ከጠዋቱ የተለየ ሌላ ምን አስበሻል?›› ብለው ጠየቁአቸው::

‹‹ምንም::››

ሁለቱም በዝምታ ተዋጡ::

አቶ ጉልላት የሚስታቸውን አሳብ ዘልቀው ለማወቅ አእምሮአቸውን ሲቡዋጥጡ ከቆዩ በሁዋላ፥ ‹‹ተይ አይሆንም ንገሪኝ:: ብንመካከርበት ይሻላል::

‹‹ምንድን ነው የምነግርህ? እኔም አላውቀውም›› አሉአቸውና ከት ብለው ሳቁ::

አቶ ጉልላት ቦሚስታቸው ሁኔታ አንድ አይነት ፍርሃት አደረባቸው::

ወይዘሮ አምላለ ደገሙና፥ ‹‹እኔም አላውቀውም›› ብለው በሳቅ ተንከተከቱ::

ደርቤ ሲመጣ. . . ትእግስት. . . ትእግስት. . .ነገም ይሁን ከነገ ወዲያ ሲመጣ. . . መቼም ገንዘብ የማይስበው የለም. . . መኪና ሊገዛ!. . . የጨዋ ልጅ ተዋርዶ መናጢ ድሀ በመኪና ሊኮፈስ. . . ሲመጣ በጥሩ እንጀራና ወጥ ጠቅልሎ የሚጎርሰው መርዝ ታያቸው::

እንደ ገና ከት ብለው ሳቁ::

ምእራፍ ፲፩

ተሰማ ለእናትና አባቱ ዋሽቶአል። ሂሩትና ተፈራ ሳይሆኑ በሌሊት የወጡት፥ እርሱ ራሱ ነበር ሳያዩት በጉዋሮ ዞሮ በጠዋት የጠፋው። ሌሊቱን በሙሉ እንቅልፍ አልወሰደውም። ሌሊቱ ከመጠን በላይ ረዝሞበት ነበር። የቀኑን ብርሃን ከማየትና ከእናትና አባቱ ጋር ከመሆን ሌላ የፈለገው ነገር አልነበረም።

ተፈራ ወደ ዞን አላፊው ስልክ ደውሎ ደርቤን በተቻለ ፍጥነት ማስወገድ አማራጭ የሌለው እርምጃ መሆኑን ጠቁሞ ካሳመነ ወዲህ፥ የተሰማ ጭንቀት የባሰውን አይሎ ነበር። የገቡበት ማጥ ምን እንደሆነ ሊገባው አልቻለም። የተከሰተለት ነገር ቢኖር፥ አስጊ ሁኔታ እየተፈጠረ መሄዱ ብቻ ነበር።

ሁኔታው ከዚህ አስጊ ደረጃ ላይ ይደርሳል ብሎ አላሰበም ነበር። ጨዋታ መስሎ ነበር የሚታየው። እና፥ ጨዋታ እስከሆነ ድረስ ግን ከአድሜ እኩዮቹ ጋር ገጥሞ መጫወቱ ባልከፋም ነበረ። ግን ጨዋታው መልኩን ለውጦ የምር እየሆነ መሄዱን ሲመለከት፥ ጎራውን ጠብቆ ባለበት ለመርጋት አልቻለም። ልቡ እየከዳው ይሄድ ነበር። በተለይም ተኩስ በሰማ ቁጥር ወኔው በይበልጥ እየከዳው ይሄድ ነበር። እንቅልፍ ሸለብ ባደረገው ቁጥር፥ ወኔው በይበልጥ እየከዳው ይሄድ ነበር። እንቅልፍ ሸለብ ባደረገው ቁጥር፥ ጥርሶቹን ያገጠጠ ጣአረ ሞት በህልሙ እየመጣበት ደንግጦ ይነቃል። ቃዥቶ በነቃ ቁጥር ተነስቶ ለመሮጥ ይፈልጋል። ሌሊቱ ደግሞ ባለበት የረጋ ይመስል አይነጋም። ጨለማ በብርሃን ላይ የሸፈቱ ያህል ሆኖ ነበር የሚታየው። እና የቀን ብርሃን እንደዚያ ናፍቆት አያውቅም።

እንቅልፍ የከለከለው ፍርሃቱ ብቻ አልነበረም። ሂሩትና ተፈራ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ የሚያደርጉት መዳራት ነበር። አንዳንዴ ግብ ግብ ይገጥማሉ። ይቀጥሉና እየተሳሳቁ መርዋሩዋጥ ይጀምራሉ። ቆይተው «ውዋጨርሺኝ እኮ!» – «ታዲያ ጠመዘዝከኛ» ይባባሉና ድምፃቸው ጭልጥ ብሎ ይጠፋል። ያኔ ተሰማ እየተናደደ ብቸኝነት እየተሰማውና ፍርሃትም እያደረበት፥ «ምን እያደረጉ ይሆን?» በማለት በቅናት እየደነ ማሰብ ይጀምራል። የተፈራ ስግብግብ ከንፈሩ የፅጌረዳ እምቡጥ መስሎ ካበጠው

ከንፈርዋ ላይ እንደ ሙጫ ተጣብቆ፥ ባለበው እጁ ሲያሻሻት ይታየዋል። አደነ ሀሊናውን ለመጨፈን በሞከረ ቁጥር የባሰውኑ ጎልተው በአሳቡ ይመጡበታል። እና፥ ከተጋደመበት ይገላበጣል።

በቅናት፥ በብቸኝነት፥ ትርጉም በሌለው ንዴትና በፍርሃት ሰውነቱ ተዳከሞ እንቅልፍ ሸለብ ያደርገዋል። ሂሩት ተፈራና እሱ ሆነው የኦ.ህ.አ.ፓን አርማ ኮሬንቱ ገመድ ላይ ሲሰቅሉ. . . ከላይ እስከ ታች ቀይ ልብስ በለበሱ የአብዮት ጥበቃ አባሎች ሲከበቡ. . . ከዚያ እርሱ አምልጦ ከንቱ ሩጫ እየሮጠ. . . እግሩ እየከዳው. . . እግሮቹ ተሳስረው እየወደቀ. . . ለመነሳት እየቡዋጠጠ. . . ባለበት ሲዳክር. . . እነርሱ ሲደርሱበት. . . ነበር ሌሊቱ የነጋው።

ረጂም ሌሊት ነበር። እና፥ ጨለማ ገፎ ሰማይና ምድር እንደ ተላቀቁ ነበር ተስማ ተነስቶ ለመሄድ የቆረጠው።

ሆኖም ወደ ቤት ስልክ ደውሎ ስለ ደርቤ የአብዮት ጥበቃ ሲቀ መንበር ሆኖ መመረጥ በተናገረ ጊዜ፥ ወይዘሮ አምላለ ስለ ሂሩት ሲጠይቁት፥ የለችም ብሎ መልስ የሰጠበት ምክንያት ለእርሱም ቢሆን አልገባውም። ከሂሩትና ከተፈራ ለመለየት በአሳቡ ቆርጦ ስለነበረ፥ ሂሩትን ያቀረበ እንደሆን ምናልባት ነገሩ ይወሳሰብኛ ይነቁበኛል ብሎ በመገመት ይሆናል። ለምን ስልክ ደውሎ ስለ ደርቤ መመረጥ እንደ ተናገረም ምክንያቱ ግልፅ አልሆነለትም። ቤት ሲደርስ ሊናገር ይችል ነበር። የፍርሃት ልጉዋሙን ስላላወለቀ፥ ያሰበውን ሊናገር አልቻለም። አእምሮው ትክክል አልነበረም። የፈለገው ከጥፋት አፋፍ ላይ ነንና መጥታችሁ አድኑን፥ ገደል ከመግባታችን በፊት ድረሱልን ለማለት ነበር። ግን አፍ አውጥቶ ለመናገር አልቻለም። በጉዋሮ ዞሮ ጭልጥ አለ። ቤት ከደረሰ በሁዋላ ነበር እህቱን ጥሎ መመጣቱ የቆጨው።

ሂሩትና ተፈራ ፈልገውት ካጡት በሁዋላ ነበር ሰግተው ስለ ተስማ መወያየት የጀመሩት። ተፈራ አላመነታም፥ «መክዳቱ ነው!» አላት።

ሂሩት እንደ ተፈራ እርግጠኛ ሆና ለመናገር አልፈለገችም።

«ሊሆን ይችላል» ብላ መለሰችለት።

‹‹ምን ሊሆን ይችላል ትያለሽ? ማታ ሲናገር የነበረውን አልሰማሽም? የደርግ ባንዳ ሆኖአል። መክዳቱ ነው። ባይከዳ ኖሮ ሹልክ ብሎ አይጠፋም ነበር።››

ሂሩት ትላልቅ አይኖችዋን እንደ ጡዋፍ እያንቦገቦጓች ዘንፋላ ጠጉሩዋን ከፊትዋ ላይ ለማራቅ ጭንቅላትዋን ወደ ቀኝ መታ እያደረገች፥ ‹‹ቢከዳ አይገርመኝም። ግን አንተ እንዳልከው በአቅዋም የተነሳ አይመስለኝም›› አለችው።

‹‹ፈርቶ ይሆናል!›› አላት።

‹‹ቢፈራም አይገርመኝም። ለህይወቱ የማይፈራ ማን አለ? ህይወት ውድ ናት። መኖር ራሱ ደስታ ነው።

‹‹ግን እኛ አለን፥ አልፈረጠጥንም!›› አላት።

‹‹አፋ! ተወኝ እባክህ! ህይወቱን የማይወድ የለም።››

‹‹አንቺ በተለይ. . .››

‹‹አዎን፥ እኔ በተለይ! ህይወትን እወዳለሁ። መኖር ራሱ ልዩ ደስታ ይለጠፍል። እያንዳንዱ ቀን ልዩ ጣእመ ዜማ ነው የሚያበስርልኝ። ሙዚቃ ነው፥ የማይጠገብ የህይወት ሙዚቃ ነው። የማይጠገብ የህይወት ሙዚቃ! ለዚህ ይሆናል አደጋ የሚባል ነገር መኖሩ የማይታወቀኝ። ግን አደገኛ ጨዋታ ላይ ነው ያለነው።››

‹‹እንኩዋን ዛደ ነው የምትይው?››

‹‹አፋ! አላልኩም!››

‹‹ታዲያ ምንድን ነው የምትይው? ሊገባኝ አልቻለም›› አላት ተበሳጭቶ።

‹‹እኔ የምለው፥ ምንድን ነው የምለው? አዎን፥ ከአደጋ ጋር ድብብቆሽ መጫወት ደስ ይላል። ደስ አይልም?›› ብላ ጠየቀችው።

ተፈጥሮዋ ሆኖ ከአንድ ቦታ እንኩዋን ረግታ መቀመጥ አትወድም። እጅዋንም፥ እግርዋንም፥ ሰውነትዋንም ማንቀሳቀስ ታዘወትራለች። ህይወትዋ በእንቅስቃሴ ስልት ላይ የተመሰረተ ይመስል ነበር። በአንድ አሳብም አትረጋም። አዲስ አሳብ ይስባታል፣ አዲስ ነገር ይማርካታል። ታዲያ ተፈራ ደስ አይለውም። ሁኔታዋ ሁሉ የመንፈስ እረፍት ይነሳዋል። ግን፥ ከአይኑ ሊለያት አይችልም። ሳይወድ ቀናተኛ አድርጋዋለች።

‹‹እኔ ደስ አይለኝም›› አላት።

‹‹እንግዲያውስ አንተም እንደ ወንድሜ ድንች ነህ! የልብ ትርታን ከፍ የማያደርግ ህይወት መኖር ትርጉሙ ምንድን ነው? ትርጉም የለውም። ስሜት የሌለበት ህይወት፥ ህይወት አይደለም። የልብ ትርታን ከፍ የሚያደርግ ስሜት ግን የህይወት ቅመም ነው›› አለችው፥ ጥፍሮችዋን ቀይ ቀለም እየቀባች። ቀጠለችና፥ ‹‹ከአደጋ ጋር ድብብቆሽ እየተጫወትን የምናደርገው ነገር ሁሉ፥ ወረቀት መበተኑ፥ አርማ መስቀሉ፥ መንገዶችና ግድግዳዎች ላይ መፃፍ የልብ ትርታን ከፍ ያደርጋል። እና ደስ ይላል!›› አለችው።

‹‹በፖለቲካ እሳት መጫወት!›› አላት ተገርሞ።

‹‹እሱም ህይወት ነው! በአደጋው መጠን የልብ ትርታ ከፍ ይላል። እና ለህይወት የበለጠ ውበትና ትርጉም ይሰጣል!››

‹‹ዋሣ መስሎሽ››

‹‹እኔ የማየው አደገኛነቱን ሳይሆን የሚያስከትለውን የልብ ትርታ ነው። ስሜት የማይሰጡ ተመሳሳይ ሰአቶች እግር በእግር እየተተኩ ቀኑ መሸቶ ሲነጋ ምን ህይወት ነው?››

ተናደደና፥ ‹‹ለብዙሀኑ እግር በእግር የሚተካ ተመሳሳይ ሰአት የሚባል ነገር የለም›› አላት። ‹‹እያንዳንዱዋ ደቂቃ ያለ ከፍተኛ የልብ ትርታ አታልፍም። የእለት ጉርስ ማግኘት ከፍተኛ ትርታን ይጠይቃል። ረሀብ ፋታ አይሰጥም። ለብዙሀኑ እያንዳንድዋ ደቂቃ ትርጉም አላት፤ የሞትና ሽረት ጉዳይ ናትና። ከሞት ጋር ነው እነርሱ ድብብቆሽ የሚጫወቱት። አንቺ ግን

የቡርሻዋ ኑሮ መኖር ሰልችቶሽ ነው ከአደጋ ጋር የድብብቆሽ ጨዋታ የምትፈልጊው።

ቁም ሳጥን ላይ ወዳለው ትልቅ መስተዋት ጠጋ ብላ ሁኔታዋን ከላይ እስከ ታች ድረስ በረጋ መንፈስ ተመለከተች። የለበሰችው ጥቁር ሸሚዝና ሱሪ የሰውነትዋን ቅርፅ አጉልቶ ያሳያል። እየተዘናፈለ ከኮብ ትከሻዋ ላይ የወደቀውን ጠጉርዋን ሰብስባ በቀይ ሻሽ ሸብ አደረገችው። ቀይ የከንፈር ቀለም ከቦርሳዋ አውጥታ በጥንቃቄ ተቀባች። ፈገግ አለች። ወደ ተፈራ መለስ ብላ፥ ‹‹እንግዲያውስ፥ ከብዙሀኑ አንድዋ ብሆን ምንኛ ደስ ባለኝ!›› አለችው።

‹‹አይመስለኝም! ከብዙሀኑ አንድዋ ብትሆኚ የተወለድሽበትን ቀን በየደቂቃው ትረግሚ ነበር!›› አላት።

‹‹የልብ ትርታዬን የሚጨምር ከሆነ ለምን አረግማለሁ›› አለችው። ‹‹ታዲያ የብዙሀኑ የኑሮ ውጣ ውረድ የልብ ትርታሽን እንደሚጨምር እያወቅሽ፥ ከአድገር በህብረት ዘመቻ ለምን ቀረሽ?››

‹‹አንተስ ለምን ቀረህ?›› አለች፥ ተቆጥታ።

‹‹አንቺ ስለቀረሽ። አሁንም እዚህ እላት ውስጥ የገባሁት ባንቺ ምክንያት ነው. . .››

‹‹በኔ አታሳብብ!››

‹‹ስራም ስላጣሁ ነው። መኖር አለብኝ፥ አይደለም? አላት አዝኖ።

‹‹እንደሱ በላ! ለምን በኔ ታሳብባለህ›› አለችው፥ ረጅም አንገትዋን እንደ እስክስታ ወራጅ እንክት አድርጋ።

ያባቱ መታሰር የንብረታቸው መወረስ፥ ስራ የማጣቱ በየመስሪያ ቤቱ ማመልከቻ ባገባ ቁጥር ያባቱን ስም ሲያዩ የፊታውራሪ ልጅ ነህ እንዴ! ወደ ፊት እናሳውቅሃለን ብለው ተስቦ የያዘው ይመስል እንዳይጋባባቸው ቶሎ ከቢሮአቸው እንዲወጣላቸው የሚጣደፉት ቢሮክራቶች ትዝ አሉት። እንጠራሃለን። እናሳውቅሃለን። አትመላለስ። ጠብቅ። ግን የሚራኝ የሚያሳውቀኝ የለም፥ ተስፋ የማያልቅ ተስፋ ብቻ! ቁምጥና ወይስ ለምፅ

አለብኝ? ያባቴን ስም ስጠራ አቤት ሲፈሩ! ውሾች! ወኔ-ቢስ ቢሮክራቶች! ስሜን ጠርቼ ያባቴን ስም ላልደግም! ይገርማል። በፊት ያባቴ ስም ለማንኛውም ቦታና ጊዜ የሚያገለግል የይለፍ ወረቀት ነበር። አሁን ግን ያደጋ ምልክት ነው። ቀይ መብራት-የጥፋት ደወል - እያለ ሲያስብ ቆየና፥ ‹‹ልጅ ባባቱ ሀጢአት ይቀጣል? ማን ያወጣው ሕግ ነው?›› አለት።

‹‹ልጅ ያባቱን ሀብት ይወርስ የለ!›› አለችው፥ ፀጉርዋን እያስተካከለች።

‹‹ምን ማለትሽ ነው?››

‹‹አትጨህ! የውርስ ጉዳይ ቢሆን ሽንጥህን ገትረህ ትከራከር ነበር። አይደለም? ዲቃላም ብትሆን ያባቴ ልጅ ነኝ ብለህ ምስክር ትፈልግ ነበር - ለመውረስ። አሁን ያባትህ ስም እንቅፋት ስለሆነብህ ያባቴ ልጅ አይደለሁም ብለህ ልትክድ ትፈልጋለህ። እና፥ ልጅ ባባቱ ሀጢአት ለምን ይቀጣል ትላለህ። ባባት ስም ስንነግድ ከኖርን ለምን ባባት ሀጢአት አንቀጣም፥ እ?››

‹‹ተሳስተሻል። ፍፁም ተሳስተሻል››

‹‹ኦፋ! እሱን ተወውና ይልቅ ስለ ተሰማ ለላእከ ምን ብዬ እንደማስረዳ ንገረኝ።››

‹‹ተሳስተሻል. . .››

‹‹ኦፋ! ምን ብዬ እንደማስረዳ ንገረኝ ነው ያልኩህ!››

‹‹ምን ምክንያት እንደምትሰፍኪ እኔ አላውቅም!››

‹‹ተቆጣህ እንዴ? አትቆጣ። ማታ ከፍተኛ ስራ ይጠብቀናል። ስፊራችንን ቀይ በቀይ ነው የምናደርገው. . .››

‹‹ምኑም ደስ አላለኝም።››

‹‹እኔ ግን ከደስታዬ ብዛት የልቤ ትርታ ጨምሮአል። ነገ ጠዋት የስራችንን ውጤት ስንመለከት ደግሞ የበለጠ ደስ ይሰናል። ይልቅ ወደ ሆነ እንሂድ። እንቅስቃሴ የህይወት ቅመም ነው›› ብላው ተያይዘው ወጡ።

ተፈራ ከሂሩት ጋር ወደ ዞን መሄድ ደስ አላለውም። የዞን አላፊውን ላእከን ማየት አይወድም። ላእከ ሂሩትን ባያት ቁጥር ልሀጨ ጠብ ሊል ይደርሳል። በዚህ ላይ ደግሞ በጉልበቱና በስልጣኑ ተመክቶ ሰውን ማሰቃየት ይወዳል። ከሁሉም በላይ ተፈራን የሚያሰቃየው ግን፥ ሂሩት ለህይወት ያላት ጉጉት ነበር። በምንም ነገር አትረካም። ስለሆነም፥ በርሷዋ የተነሳ ልቡ ሁሉጊዜ እንደተሰቀለ ይኖራል። ልቡን ሰቅላ የምታሰቃየውን ያህል ደግሞ ከአይኑ ሊለያት አይፈልግም። ከአርስዋ ተለይቶ ለመኖር እንደማይችል ልቡ ያውቃል። ያኔ ነፃ የትምህርት እድል እንዳገኘሁ ጨክኜ ጥያት ብሄድ ኖሮ ምን ነበረበት! በማለት አስበና መስላታ ልቡን ፈገመ።

አምን፥ ነፃ የትምህርት እድል አግኝቶ ወደ አሜሪካ ሊሄድ ሁሉን ነገር ከጨረሰ በሁዋላ የሂሩት ስለ ዘገየባት እርስዋን ጥሎ ብቻውን መሄዱን ጠልቶ ቀረ። በእርስዋ ምክንያት እድሉን ሲሰብር የመጀመሪያው ጊዜ አልነበርም። ከዚያም በፊት እርስዋን ጥሎ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መግባት ጨለማ መስሎ ስለታየው፥ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት መልቀቂያ ፈተናውን አውቆ የወደቀበትና ክፍል የደገመበትም ጊዜ ነበር። ‹‹ለምልኮት ነው ወይስ ፍቅር? የለም፥ ፍፁም ጅልነት ነው! ስሜቴ ሁሉ የዚች ውሻ ተገዥ ሆኖ እንዴት ይቅር? ነፃነቴን ማግኘት አለብኝ! ይባስ ብላ ደግሞ ወደ ገሃነም ስትመራኝ ዝም ብዬ እንደ በግ የምከተላት ለምን ይሆን?›› እያለ ሲያስብ፥ ሂሩት ሰይቺንቶ አስቁማ ሲሳፈሩ ሁሉ፥ እንደ ህልም ሆኖ ነበር የሚታየው. . .

ትንሽ መንገድ እንደ ተጉዋዙ ‹‹ምንነው ፈዘገክ?›› ብላ ጠየቀችው።

‹‹ከፈዘገኩ ዘመን የለኝም›› አላት።

‹‹አስቀየምኩህ መሰለኝ. . .እ. . .››

‹‹አንቺን መቀየም የሚችል ልብ ቢኖረኝማ እስካሁን ሰው እሆን ነበር›› አላት፥ ወደ ውጭ እየተመለከተ። አይኑ ግን ምንም አያይም ነበር።

‹‹አሁንስ ምንድን ነህ?››

‹‹ድንች። የድንች ገንፎ!››

መበሳጨቱ ስለገባት እጁን ፈልጋ ያዘችው። መለስ ብሎ ተመለከታት። አይኖቻቸው ተገናኙ። ፈገግታ ተለዋወጡ። እጅዋን ጠበቅ አድርጎ ያዘ።

ወደ ጆሮዋ ጠጋ ብሎ፥ ግሩም ጠረንዋ ህይወት ይሰጠው ዘንድ ወደ ውስጥ እየተነፈሰ ‹‹ጊዜያዊ ደስታ. . . እ. . . ከጊዜያዊ የልብ ትርታ የላቀ አላማ በኖረሽና የዘላለም ባርያሽ ሆኜ በቀረሁ፥ ከማለቱ የተሳፈሩበት መኪና በመንገድ ቆመ። ባለ ሰይቼንቶው በድንገት ፍሬን በመያዙ ፊት ለፊታቸው ካለው ወንበር ጋር ሊላተሙ ምንም አልቀራቸውም ነበር። ከፈለጉበት ስፍራ ደርሰው ስለነበረ ተያይዘው ወረዱ። ገበያው በመቀዝቀዙ ሰይቼንቶ ነጂው አሳቡ የባከነ ይመስላል። ከመንገድ ሌላ ህይወቷ የሌለው ይመስል ደግሞ፥ አይኑ ከመንገድ ለሌላ አይመለከትም። ሂሩት ብሽቅ ብላ ሳንቲሞቹን አፍንጫው ላይ ወረወችለት።

ከአውራ መንገድ እምብዛም ርቀው አልሄዱም። ኮረኮንች መንገድ ተከትሰው በእግር ትንሽ እንደተጉዋዙ፥ ሂሩት ወደ አንድ ተራ መሳይ ኪዮስክ ጠጋ ብላ፥ ‹‹ቅርንፉድ አለ?›› ብላ ጠየቀች።

‹‹ለምን የሚሆን?›› አላት ባለ ሱቁ።

‹‹ለጉትቻ›› አለችው።

ጠጉሩን ተላጭቶ የራስ ቅሉ የሚያብለጨልጨው ወጣት ባለ ኪዮስክ ወደ ተፈራ መለስ ብሎ፥ ‹‹ምን ልታዘዝ?›› አለው።

‹‹ክብረ ሰማይ›› ብሎ መለሰለት።

‹‹ክብረ ሰማይ ለምን?››

‹‹ለቂጥኝ››

ባለ ኪዮስኩ ማንነታቸውን በማወቁ ፈገግ ብሎ ግራና ቀኝ በመመልከት በአካባቢው ሰው አለመኖሩን ካረጋገጠ በሁዋላ፥ ከመስኮቱ ስር ያለችውን ትንሽ ስውር በር ቶሎ ከፍቶላቸው ሹልክ ሹልክ እያሉ ገቡ። ቡቱቶ የለበሱ ሶስት ጭቅቅታም ሰዎች በጀበና ሻይ ጥደው፥ ቁጭ ብለው ጫት ይቅማሉ። ቡቱቶውና ጭቅቅቱ የምድር ጎስቁዋላ ቢያስመስላቸውም ቅሉ፥ የሰውነታቸውን

መፈርጠምና ወጣት እድሜአቸውን ለመደበቅ አልቻለም። አቶማቲክ መሳሪዎች ከተቀመጡበት አርጌ ካሊም ስር ብቅ ብለው ይታዩ ነበር።

ሶስቱም ሂሩትን ከላይ እስከ ታች ድረስ በፈገግታ ተፈራን ደግሞ ኮስተር ብለው ተመለከቱ። ከሶስቱ አንደኛው ባለ ኪዮስኩን በአይኑ ጠቀሰው። ተራ የሽቀጣ ሽቀጥ መደርደሪያ መስሎ የሚታየውን ሳንቃ ወደ ጎን ገፋ አድረጎ ወደ ውስጥ እንዲዘልቁ ጋበዛቸው።

በስውሩ በር ተከታትለው ወደ ውስጥ ዘለቁ። የሚሄዱት አጎንብሰው ስለነበረ ቀና ሲሉ ያጋጠማቸው አይን በሚወጋ ሀይለኛ አምፑል የበራ ሰፊ ክፍል ነበር።

ክፍሉ በሲጃራ ጢስ ታፍኖአል። ሆኖም የሂሩትን አፍንጫ ያወደው ተራ የሲጃራ ጢስ ሽታ አልነበረም። የሀሺሽ ጢስ ሽታ ነበር።

በክፍሉ አራቱም ማእዘናት እንቅስቃሴ ይታያል። በአንደኛው ማእዘን ሌሎች ሁለት ወጣቶች መአት ገንዘብ ይቆጥራሉ። በሶስተኛው ማእዘን አንዲት ሴትና ወንድ የብዙ ሽጉጦችና አቶማቲክ መሳሪያዎች ቁጥር እያነበቡ ይመዘግባሉ። በአራተኛው ማእዘን ደግሞ በእድሜአቸው ጠና ያሉ ወጣቶች፥ የፍርሃት ሁኔታ የሚታይበትን አንድ ወጣት ከበው በመስቀለኛ ጥያቄ የሚያጣድፉት ይመስላሉ። የዞን አላፊው፥ ላእከ፥ ከክፍሉ መሀል ከትንሽ ጠረጴዛ ላይ አቀርቅሮ፥ የደረቀ ቅጠል መልክ ያለው ቀጭን ሲጃራ ከንፈሮቹ መሀከል ሰክቶ ይፅፋል። ከሰፊው ትከሻው ላይ እንደ ጉቶ ጉች ብሎ የሚታየው ትልቅ ጭንቅላቱ የበሬ ጭንቅላት እንጂ የተራ ሰው ጭንቅላት አይመስልም።

በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሁሉ በስ ተጠምደው ነበር። በስራው ያልተመሰጠ ወጣት አይታይም። እና፥ ሁሉም ደግሞ በሚሰሩት ስራ የተደሰቱ ይመስላሉ። ትኩስ ሃይላቸውና ጠንካራ መንፈሳቸው በክፍሉ ውስጥ እያስተጋባ የሰውን ልብ እንደ መግነጢስ ይጎትታል። ይህን ትኩስ ይሃይል. . . ይህን አስደናቂ የመፍጠር ችሎታ. . . ይህን ጠንካራ መንፈስ. . . ይህን ድርጅታዊ ዲስፕሊን. . . ውጣቱ ለገንቢ አላማ ቢያውሉት፥ ይህች አሳዛኝ አገር ምንኛ በታደለች ነበር! እያለ በአሳቡ ሲያወጣና ሲያወርድ የነበረው ተፈራ እንኩዋን

ሳይቀር፥ ከፍሉ ውስጥ በሚታየው መግነጢሳዊ እቅስቃሴ ልቡ ከመሳብ አላመለጠም። ሂሩትም በበኩልዋ የልብዋ ትርታ እየጨመረ ሲያስፈነድቃት ምንም አልቀረውም ነበር።

ላእከ ከጠረጴዛው ላይ ቀና ብሎ ተንጠራራና፥ ‹‹አ! እንቁጣጣሽ!›› አላት። እንቁጣጣሽ የሂሩት የኮድ ስም ነበር። ትኩር ብሎ በአድናቆት እየተመለከታት፥ ‹‹ውበትሽ በየቀኑ እየፈካ ይሄዳል›› አላት። ሲናገር ድምፁ እንደ ነጎድጓዱ ያስተጋባል።

‹‹አመሰግናለሁ። የልቤ ትርታ እየጨመረ ስለሚሄድ ይሆናል የምፈካው!›› አለች ሂሩት፥ ፈገግ ብላ።

‹‹እንደ ምሽት ፅጌረዳ!›› አላትና፥ ኩበት የመሰለውን ለምቦጩን በምላሱ ልሶ አረጠበ።

ላእከ ለሂሩት ውበት ያለውን አድናቆት ተፈራ አልወደደም። ባላበው እጁ ጎፈሬውን አከክ አከክ አድርጎ ዝም አለ። ላእከ ይባስ ብሎ እንደ ሂሩት ጥላ ያህል ቆጥሮት ምንም ግምት ወይም ትኩረት ሳይሰጠው በመቅረቱ ውስጡ በግኖ ነበር።

ላእከ አንድ ነገር ለማለት እንደ ፈለገ ያስታውቃል። ግን የሀሺሽ ጢስ በሰውነቱ ውስጥ እስካለ ድረስ አሳበ ብኩን በመሆኑ፥ ለማለት የፈለገው ነገር ቶሎ አይጨበጥለትም። ወዛም ጠይም ፊቱን አጨማዶ ሲያስብ ከቆየ በሁዋላ፥ ‹‹አ! ላጲሶ በጠዋት ለጥብስ ደርሶአል። ከኛም ወገን አንድ የመከላከያ ጉዋድ ቆስሎ ሊያዝ ነበር። ራሱን ገደለ። ይህንን ነው እኔ ዲሲፕሊን የምለው። ራሱን የገደለው እኛ እንድንኖር ነው። እና፥ እንኖራለን። መሞት ብቻ አይደለም። ለመኖር መግደልም አለ። ላጲሶ ባይሞት ኖሮ ይህ ህዋስ እስካሁን አይኖርም ነበር። ደግነቱ ላጲሶ ከያዘው ምስጢር ጋር ወደ መቃብሩ ወርዶአል›› አለና፥ ለመጨመር የፈለገው አላብ ስለ ጠፋው ፊቱን በትልቅ እጁ ማሻሸት ጀመረ።

የለበሰው ነጭ ሸሚዝ እጀ ጉርድ ስለነበረ፥ ፊቱን ሲያሻሽ ጡንቻው እንደ አሎሎ ሲንከባለል ይታያል። ሁኔታው ሁሉ በልቡ ፍርሃት ስለሚለቅበት፥ ተፈራ የባለውን ጠላው። ሂሩት በላእከ ጡንቻና ቆራጥነት፥ ባለው ስልጣንና

በሚታይበት ኩራት ተማርካ አፍዋን ከፍታ ሰለምትመለከተው፥ ተፈራ፥ ቅናትም አድርበት፥ ጥርሱን ይነክስ ነበር።

ሂሩት ጡንቸኛ ወንድ ስታይ ያምራታል። ቀጭን ወንድ ስታይ ያምራታል። ጠይም ወንድ ስታይ ያምራታል። ጥቁር ስታይ ያምራታል። ቀይ ወንድ ስታይ ያምራታል። ወንድ ሲባል እስዋን ለማስደሰት ብቻ የተፈጠረ ይመስላታል እና፥ በወንድ ገላ ትደሰታለች። ከተደሰተችበት በሁዋላ አትወደውም ትንቀዋለች።

‹‹ኦ! በነገራችን ላይ›› አለ ላእከ ‹‹ጥቆማችሁ ጥሩ ነበር። ለትግል ትከክለኛ ጥቆማ በጣም አስፈላጊ ነው። ሳልረሳ. . . ሳልረሳ. . . መሳሪያዎቹና ገንዘቡ ደርሶአችሁአል?›› ብሎ ጠየቀና እፀ ፋርሱን ወደ ውስጥ ማገ።

ተፈራ፥ ‹‹አዎን ደርሶናል›› ብሎ መለሰለት።

‹‹ምን ሆነሃል? ያዘንክ ወይም እኔ እንጂ፥ አንድ ነገር የምታስብ ትመስላለህ›› አለው።

‹‹አላዘንኩም፥ አሳብም የለብኝም!››

‹‹አዎን፥ በአብዮት ጊዜ ሀዘን የለም። ግኡ፥ አብዮት የጭቁኖች በአል ነው ሲል ጨርሶታል። ማሰብም ካንተ አይጠበቅም። ድርጅትህ የማሰቡን ተግባር ያከናውንልሃል። ካንተ የሚጠበቀው ድርጊት. . . ድርጊት. . . ድርጊት! ብቻ ነው›› አለውና፥ ቀጥሎ፥ ‹‹ታወላውላለህ መሰለኝ?›› ሲል ጠየቀው።

‹‹የመደቤ ልጉዋም እየሳበኝ ይሆናል›› አለው።

ላእከ ፈገግ ብሎ ወተት የመሰሉ ትላልቅ ጥርሶቹን እያሳየው፥ ‹‹አዎን፥ ግኡ እንዳለው፥ ከመደብ ውጭ ባህርይ ወይም ተፈጥሮ የሚሉት ነገር የለም። የሰው ተፈጥሮ እንደ ማንኛውም ነገር የሚመራው በዲያሌክቲካዊ ህግ ነው። የሰው ተፈጥሮ አንድ ቦታ ረግቶ የሚቀር ኩሬ አይደለም። እንደ ማንኛውም ነገር እየተለወጠ እያደገ የሚሄድ ነው። ንቃት፥ ዲሲፕሊን፥ ድርጊት - ከዚያ በሁዋላ ማወላወል የለም። ኦ! አሁን ትዝ አለኝ። ወንድምሽ የት አለ?›› ብሎ ሂሩትን ጠየቃት።

የተዘጋጀችበት ጥያቄ ነበርና፥ ‹‹በድንገት አሞት ተኝቶአል›› ብላ ፍንክች ሳትል መለሰችለት።

‹‹ይህ ድርጅት ለበሽተኞች ቦታና ጊዜ የለውም!›› ብሎ በነጎድጓዳዊ ድምፅ በመጮህ ጠረጴዛውን መዶሻ በሚመስለው እጁ አንዴ ሲመታ፥ ክፍሉ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ዞር ብለው ይመለከቱት ጀመር።

ሁሉም፥ ምን ይከተል ይሆን? በማለት ጆሮአቸውን አቁመውና አይናቸውን አፍጠው ይመለከቱት ስለነበረ፥ በተፈጠረው ሁኔታ ተጠቅሞ መልእክት ለማስተላለፍ በመፈለግ፥ ‹‹እኔ ለበሽተኞች፥ ለደካሞችና ለተሸናፊዎች ደንታ የለኝም!›› አላቸው። ‹‹የምናካሂደው የድኩማን ድርጅት አይደለም። ተጋድመን ህመማችንን የምናዳምጥበት ጊዜ ላይ አይደለም ያለነው! ያሮጊቶች ስሞታ አልፈልግም! ነፃ ርምጃ በተቃጣብን ባሁን ጊዜ፥ እያቃሰትን ከመታገል ሌላ ምርጫ የለንም። ይህ ለሁላችንም ግልፅ መሆን አለበት።››

ነጎድጓዳዊ ድምፁ አጉዋርቶ ዝም ሲል፥ ክፍሉ ፀጥ እረጭ ብሎ ቀረ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር ሁሉም ወደየስራው ተመልሶ ጎንበስ ቀና ማለት የጀመረው።

‹‹እንዲነሳ እንነግረዋለን›› አለ ተፈራ የሂሩትን ውሽት ደግፎ።

‹‹ንገሩት! መነሳት አለበት። እንዲያውም አሁን ትዝ አለኝ። ዛሬ ማታ ስራ አላችሁ አይደለም እንዴ?››

‹‹አዎን፥ ተዘጋጅተናል›› አለች ሂሩት።

‹‹ታዲያ ምናባቱ ሆኖ ነው የሚጋደመው? ወይስ ፈርቶ ነው? ለመሆኑ ስሙ ማን ነበር? የሰው ስም አይያዝልኝም! እና፥ ለፈሪ ሰው ደሞ አክብሮት ሆነ ርህራሄ የለኝም!›› አለና፥ አሁንም እፀ ፋርሱን ወደ ውስጥ ማገ።

ተፈራ፥ አዎን፥ ከእንቁጣጣሽ ሌላ ስም አይያዝልህም! ብሎ በልቡ ረገመው።

‹‹ብነገራችን ላይ፥ ማን ነው የምትሉት? ኦፋ! ይሄ የቀበሌያችሁ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ የተመረጠው? ስሙን አምጡልኝ!››

‹‹ደርቤ›› ብላ ነገረችው።

‹‹አዎን፥ ደርቤ። ማታ ነግራችሁኝ ስሙ ጠፋብኝ። የቤት አሽከራችሁ ነበር አላላችሁኝም እንዴ?››

‹‹አዎን፥ ነበር›› አለችው።

‹‹ጠባዩን፥ ደካማና ጠንካራ ጎኑን ታውቃላችሁ ማለት ነዋ! ለመሆኑ ምን አይነት ሰው ነው?››

‹‹በጣም ጥሩ ልጅ ነበር። አሁን አላውቅም። ታታሪ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ራሱን ከፍ ለማድረግ ይጥራል›› አለች ሂሩት።

‹‹ምን ለመሆን?›› ብሎ ጠየቃት።

‹‹እኔ እንጃ!›› ብላ ክብ ትከሻዋ እንደ እስክስታ ወራጅ መታ አደረገች።

‹‹ማወቅ አለብሽ። እኔ እንጃ ማለት መልስ አይደለም›› አላት።

‹‹ተሰማ እንደ ነገረን ከሆነ የሂሩትን ትኩረት ለመሳብ ብሎ ነው የሚንጠራራው!›› አለው ተፈራ።

‹‹ተሰማ እንደ ነገረን ከሆነ የሂሩት ትኩረት ለመሳብ ብሎ ነው የሚንጠራራው!›› አለው ተፈራ።

‹‹ኦ! ይሄማ ጥሩ ነው።››

‹‹ማ? እኔ?››

‹‹አዎን አንቺ!››

‹‹እንዴት አድርጌ?››

ላእከ ሀሺሹን ለመጨረሻ ጊዜ በረጅሙ ስቦ ጭሱን ዋጠ፥ ቆየ-ቆየ-ቆየ እና ወደ ውጭ ሲተነፍስ ትንሽ ጭስ እንኩዋን ካፉ አልወጣችም. . .

‹‹በውበትሽ ተጠቀሚ!›› አላት ሂሩትን፥ ‹‹የሴቶች ውበት ምን ጊዜም አደገኛ ወጥመድ ነው። በነገራችን ላይ፥ አንድ ጀሌ ቀርቶ ስንት ታላላቅ ሰዎችም በሴቶች ውበት ተጠምደው ጉድ ሆነዋል። የሴቶች ውበት በተለይም በኛ ህብረተሰብ ውስጥ ትልቅ የፖለቲካ መሳሪያ ሊሆን ይችላል። ግብረ ስጋ ርካሽና ጠቃሚ መሳሪያ ነው። እንዲያውም አሁን ሳስብ እንቁጣጣሽ በዚህ ረገድ ብዙ ጥቅም ልትሰጪን ትችያለሽ›› አለ ላእከ፥ በመጣለት አሳብ ተደስቶ።

ተፈራን ግን አሳቡ አቅለሽልሾት ቁዋቅ ሊለው ትንሽ ቀርቶት ነበር። በዚህ ላይ የወንድነት ወኔው ተቀስቅሶ ምንም ሳይፈራ፥ ‹‹ርካሽና ሰይጣናዊ አሳብ ነው!›› አለ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ። ቀጠለና እሳት ጉርሶ እሳት ለብሶ ‹‹እኔ እያለሁ ይህን አታደርግም! እንድታደርግም የሚያስገድዳት ሃይል የለም!›› አለ።

ላእከ የሚያስገድዳት ሃይል እንዳለ ሊያሳየው ፈልጎ ነበር። እንዲያውም ሂሩትን ሳብ አድርጎ ከተፈራ ፊት ሊስማት አስበና ተወው። ግን አሳቡን ጨርሶ ከአእምሮው ውስጥ አላወጣም። ለጊዜው በአሳቡ ውስጥ ቅድሚያን የያዘው የፖለቲካ ሁኔታ፥ ማምሻውን የሚፈፅሙት ከፍተኛ ግምት የተሰጠው የቅስቀሳ ተግባር ስለነበረ፥ ቆይ ሌላ ጊዜ እሰራልሃለሁ በማለት እልኩን ውጦ በልዝብ አንደበት፥ ‹‹ትወዳታለህ መሰለኝ?›› አለው።

‹‹የግል ጉዳዬ ነው!›› ብሎ መለሰለት።

የላእከ ስሮች ተገታተሩ። ሆኖም፥ ንዴቱን እንደ ምንም ውጦ፥ ‹‹ለከፍተኛ አላማ የተፈጥሮን ውበት መጠቀም ነውር አይደለም! ወይስ በአላማችን አታምንም ማለት ነው?›› አለው።

ላእከ ወዴት ሊመራው እንደ ፈለገ ስለ ገባው ተፈራ ገሞ ብሎ ቀረ።

‹‹አልመለስክልኝም እኮ!››

‹‹እኔ ያልኩት፥ እኔ. . .የምለው. . .እወዳታለሁ. . .እና።››

‹‹አዎን የምትለው ገብቶኛል። እኔም ትሸርሙጥ አላልኩም።›› በውበትዋ ተጠቅማ. . . ማን ነው ስሙ? አዎን፥ ደርቤን ታግባባውና ወደኛ ትሳበው ነው ያልኩት. . .››

‹‹ለምን አይደመስስም?›› አለው ተፈራ::

‹‹ከሞተ በህይወት ያለ ሰው ይጠቅማል ብዙ ነው:: ልንጠቀምበት እንችላለን. . .››

‹‹ግን መስመራችንን ያውቃል እኮ!›› አለች ሂሩት::

‹‹ውበት የማያሸንፈው ልብ የለም! ተፈራም እንቦሳ የሆነው በውበትሽ ተማርኮ ነው:: ፈገግ በይና እንኩዋን የደርቤን ልብ ሰራዊት ትፈቺያለሽ:: ዘዴ ፈልገሽ ቅረቢው:: ሳታውቂው ምርኮኛሽ ይሆናል:: ቀላል ነው! አላት::

ላእከ በደርቤ አሳቦ ስለ ራሱ ልብ መማረክ ነበር የሚናገረው:: ከነገ ጀምሮ፥ ሂሩት ከአጠገቡ ሳትለይ እንድትሰራ ለማድረግ የቆረጠው የጀመረውን አረፍተ ነገር ከመጨረሱ በፊት ነበር:: ስለተፈራ እንደ ሆነ ገሃነም አፉን ከፍቶ ሊጠብቀው ይችላል ብሎ በአሳቡ ቆረጠ::

ተፈራም በበኩሉ ከዚህ ሁሉ ጣጣ ለመውጣት በልቡ ቆርጦ እግሩ ካለበት ክፍል ውስጥ የሚወጣበትን ደቂቃ ነበር የሚጠብቀው:: እርግጠኛ ያልሆነበት ነገር ቢኖር የሂሩትን አቅዋም ነበር:: ሂሩት ግን፥ ልብዋ ቆሞ የምታሰላስለው ደርቤን የምታጠምድበትን መንገድ ነበር::

‹‹ቀላል ነው›› ብላ ፈገግ አለች::

ምእራፍ ፲፪

የኪነት ሰዎችን የመፍጠር ችሎታ እየኮረኮረ የሚቀሰቅሰው የአለቱ ሀምራዊ ሰአት ተቃርቦአለ። ፀሀይዋ አቆልቁላ ከወጨጫ ጋራ በስተጀርባ ለመደበቅ ትንሽ ቀርቶአታል። እያቆለቆለችና ክብ ፍም እየመሰለች በሄደች ቁጥር ሽቅብ የምትፈነጥቀው ብርሃን፥ ጥቁር ለማዩን የቀዘቀዘ የፍም ባህር የተንጣለለበት ስለመሰለው ነበር። ነገር ግን፥ የሀምራዊ ሰአቱን ውበት ቆሞ የሚያደንቅ አንድም የአዲስ አበባ ነዋሪ አልነበረም።

ግን፥ ለማዩ ለማንም ውበቱን አይነፍግም። የአዲስ አበባ ሰማይ ጠቁሮ ሲያኮርፍ፥ ጉም አልባ ሆኖ ባህር መስሎ ሲንጣለል፥ ነብር መስሎ ሲሸጎረጎርም፥ ወይም የጥጥ ንድፍ በሚመስሉ ስስ ጉሞች ተውቦ ከፀሀይዋ ጋር ሲስቅ፥ የሚያየው የለም። ዝም ብሎ ብቻውን ይቆጣል፥ ያኮርፋል፥ ፈገግ ይላል፥ ይስቃል፥ አይናፋር ይሆንና እንደ ቲማቲም ይቀላል - ያዲስ አበባ ሰማይ።

ድሮ ጭራ ሰጭራ ተያይዘው፥ ሰጉል ከሚወጠሩ እግረኞች ጋር እየተፋጠጡና እየተጋፉ መንገዶችንም ሞልተው፥ ተጣበው የሚያጣብቡት መኪናዎች፥ ለአይነት ካልሆነ በቀር አይታዩም። በመሆኑም፥ የአዲስ አበባ አውራ መንገዶች ባዶ ከመሆናቸው የተነሳ ስፋት የጨመሩ መስለው ይታዩ ነበር።

ቀይ ሽብር ተፋፍሞ የቀበሌ ዲሞትፎር በየአካባቢው እያጉዋራ የሰፈውን ጭቁን ህዝብ አመፅ ማስተጋባት ከመጀመሩ በፊት እስከ ሁለት ሰአት፥ ገበያ ከደራ ከዚያም በሁዋላ፥ በራቸውንና በመብራት ያሸበረቀ የእቃ መደርደሪያ መስኮታቸውን እንደ ሽርሙጣ ፊት ወለል አድርገው ይቆዩ የነበሩት ሱቆች በጊዜ ተዘግተው፥ ዋና ዋና መንገዶችን ጭር አድርገዋቸዋል።

ሜክሲኮ አደባባይ - አውሮራ - ሲዮኔ - ፍላሚንጎ - ጊኮክ - ሚኒ - ቲሩም - ፓርክ ሆቴል - መስቀል ተራራ - ቡና ቤቶች ፊት ለፊት በመኪና ውስጥ ተቀምጠው፥ ማኪያቶ - ቢራ - ውስኪ - ጀላቲ - የፓፓያ፥ የሙዝ ወይም የብርቱካን ጭማቂ፥ ወይም ግሪን ፋየር ይዘው ሰልምልም በሚሉ አይኖች እየተያዩና ጭን ለጭን እየተደባበሱ በጋለ ስሜት የሚቃጠሉ

ፍቅረኞች ዛሬ አይታዩም። እያንዣበበ የሚያስቸግረውም ለማኝ የለለት ጉርሱን በጊዜ የቃረመ ይመስል፥ ጅምበርዋን ጠብቆ በጊዜ ገብቶለል።

የፍራፍሬውን ጭማቂ - አረቄውን ጠጥተው - ጥራና ለብለብ ከትፎውን ከበሉ በሁዋላ፥ ስልምልም በሚሉ አይኖች እየተያዩ የጭን ዳበሳውና ጉንተላው በመድረስ የሚያርፉባቸው በጎጃም መንገድ ሰሜን - መርሀ ቤቴ - የድል በር፥ በመሀል አራዳ፥ ከፍለ ሰላም - ኦኤሲስ - ሐምሌ ፲፱ - ሸዋ - አብርሃ፥ በአዲስ ከተማ አካባቢ፥ ቃኘው ሻለቃ - አሰፋ ወሰን፥ አዲስ አበባ - አሰብ - ምእራብ - ለንጋ ተራ አካባቢ፥ አፍሪካ፥ በደብረዘይት መንገድ፥ መስከረም - አደይ - ወይን አዳራሽ - አደይ አበባ - ዳማ፥ በካዛንቺስ አካባቢ፥ መናኸሪያ - እንደራሴ፥ በአዋሬ አካባቢ፥ እንሳሮ - ቤል ኤር - ሆቴሎች በጊዜ የብረት መዝጊያቸውን ቀርቅረው ስለ ነበረ፥ በሞንቴ ካርሎ ራሲ ፍጥነት የሚገባና የሚወጣ መኪና አይታይም።

ባንዳንድ የማታ ትምህርት ቤቶች አካባቢ፥ እንዲሁም በሆስቴሎች አካባቢ . ስድስት ኪሎ - አራት ኪሎ ቺቺ አፓርታማ - የተወሰወሱ መኪናዎች ገትረው አስር አስር ጊዜ የእጅ ሰአታቸውን በማየት ትእግስት አጥተው መንገድ መንገዱን እየተመለከቱ ቀጠሮ የሰጡዋቸውን ፍቀረኞች የሚጠብቁ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች (የቀበሌ ዲሞትፎር ፍቅረኞች ላይ አዋጅ ያወጀ ይመስል) በየትም ስፍራ ለአይነት እንኳን አይታዩም ነበር።

በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ቁጥራቸው እስከ ሁለት መቶ ሽህ የሚገመቱት ሴተኛ አዳሪዎች ‹‹ሊቺንሳ›› በሌላቸው በስመ ልጃገረዶችና የቢሮ ሴቶች እያማረሩ፥ በጊዜ በራቸውን ባይዘጉም እንኩዋን፥ ገርበብ አድርገው ቡና እያንተከተኩና እጣን እያንቦገቦጉ የመሸበትን ሰካራም እግረ እንድትጥልላቸው አድባርዋን መለማመን ከጀመሩ ቆይተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በየአካባቢው እንደ ለንለለት በመያያዝ እንደ አሸን የፈሉት አረቄ ቤቶችም፥ መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ እንዲሉ፥ ቡና ቤት ወይም ግሮሰሪ ይሉዋል! በዚያን ሰአት እንደተለመደው የደራ ገበያ አልነበራቸውም። የባሰባቸው ሱሰኞች በቁመናቸው አንድ ሁለት ብለው፥

ከውድቅት በፊት አይኖቻቸውን አይተው የማያውቁትን ሚስቶቻቸውን ለማስደንገጥ ሮጠው ቤት ከገቡ ጊዜ አልነበራቸውም።

በተለይም፥ የአራት ኪሎ አካባቢ የተወረረ መንደር መስሎ ነበር። ከአንዳንድ የለየላቸው እብዶችና የአራት ኪሎን ሉካንዳ ቤቶች በደንበኛነት ከሚያዘወትሩ ውሾች በስተቀር ሌላ የሚታይ ፍጡር አልነበረም።

ጌታቸው የሸዋሉል በመንገድ ጭር ማለት እየተገረመና የአዲስ አበባን ወንዶች ፍርሃት በልቡ እየታዘበ፥ በቅሎ እንደረገጠችው ጣሳ በየቦታው የተኮረኮመችውን ፔጆ 404 መኪናውን በትምህርት ሚኒስቴር ወረድ ብሎ ከቀድሞ ፓርላማ አጠገብ፥ ከቅድስት ስላሴ ፊት ለፊት አቁሞ፥ ‹‹ሆራዬ›› ከሚላት፥ ‹‹ከእሜቴ›› ቡና ቤት እንደ ልማዱ ግትር ብሎ በቀስታ እየተራመደ ገባ። ለረጂም ጊዜ ከሚያውቀው ቀይ፥ ቀጭን፥ ራስ በራ ቦይ ሌላ ማንም አልነበረም። እሜቴም ገንዘብ ከሚቀበሉበት ወንበር ላይ ገና አልተሰየሙም።

ቦዩ ሳይጠይቅ ውስኪ ቀድቶ አቀረበለትና ይናገር ይሆን? በማለት ጆሮውን ጠጋ አደረገ።

‹‹ሰው ምን ነክቶታል?››

‹‹ቀይ ሽብር ነዋ! ዛሬ ዝር የሚል የለም›› አለ መልካሙ።

‹‹እንግዲያውስ ያበድኩት እኔ እሆናለሁ!›› አለ ጌታቸው፥ ቃላቱን እየቆጠረ። ‹‹የሚስት ቀሚስ ከቀይ ሽብር ያድን ይመስል!›› አለና ውስኪውን አንስቶ ተጎነጨ። አንድም ጋዜጠኛ ብቅ ባለማለቱ ተረገመና ሰአቱን ተመለከተ። ከምሽቱ አንድ ሰአት ሆኖ ነበር። ወዲያውኑ የፓርላማ ሰአት ደወለ። የአንጋፋ ጋዜጠኞች መድረሻ ሰአት መቃረቡን ገመተ።

የኤምባሲዎች ኮክቴል ግብዣ ካለ በቀር ‹‹ሆራችን›› የሚሉትን የእሜቴን ቡና ቤት ባንኮኒ ሳይሳለሙ ቤት አይገቡም። ቡና ቤቱን መርቀው የከፈቱ የአራት ኪሎ ጋዜጠኞችና የፓርላማ እንደራሴዎች ነበሩ ይባላል። ከቆርቁዋሪዎቹ አንዱ ጌታቸው ነበር። ‹‹ኮብላይ እንደ ጥላ›› አለና፥ ስለ ዘመኑ መሮጥ ላንዳፍታ አሰበ።

የተከበሩ የህዝብ እንደራሴዎች አነባላንዛራስ፥ እነግራዝማች እነቀኛዝማች፥ እነፊታውራሪ ከዚሁ ቡና ቤት ውስጥ በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተኮልኩለው ከሚጠጡት ውስኪ ውስጥ ጋዙን ለማውጣት በረጃጅም ማንኪያዎች እያማሰሉ በመጎንጨት፥ ስለ ባለርስትና ጭሰኛ ግንኙነት ሀግ ረቂቅ ክርክር እየገጠሙ ይፈጥሩት የነበረው ውካታ ትዝ አለው።

«የማንን መሬት ማን አስይዞ ሊበደርበት? ኧረ ኤዲያ! «ህጉ» የፀደቀ እንደሆነ ያፋጃል። ካልጠፋ መሬት ጭሰኛና ባለመሬት በህግ ተቆራኝታችሁ ተጋደሉ ነው። ለነገሩ. . . ይህንን የህግ ረቂቅ ያቀረቡልን ባለስልጣኖች የኢትዮጵያ መሬት ሰፊ ትምህርት ያደድባል እንዴ?»

«እኔስ ይህን አይደል የምለው? የህግ ረቂቁን ያቀረቡት ባለስልጣኖች የራሳቸውን አገር ትክክለኛ ሁኔታ አያውቁም። የጉብልዬን ዘፈን ከቅምጥ ኮረዳ ጋር ተኝቶ ማዳመጥ መሰላቸው እንዴ? አህ -ሀ -ኦ ሆ ሆ!. . . በአፅመ ርስትና በሚስት ቀልድ የታለና!»

«እንዲያ ነው 'ይ! ዛሬ ስንዝር የሰጡት ነገ ክንድ መጠየቁ ይቀራል? ካያት ከቅማያቴ የወረስኩትን አፅመ ርስት፥ ዛሬ አስይዞ ለመበደር መብት ያገኘ ጭሰኛ፥ ነገ የልብ ልብ አግኝቶ ልንቀልህ ቢለኝስ? ይቀራል ብላችሁ ነው ባያሌው ሞት? አይደረግም። እባብ ጭንቅላቱን ካልተመታ አደገኛ ነው። ዘር አባታቸው ይጥፋና፥ እዚህ አራት ኪሎ አካባቢ መሬት ላራሹ እያሉ መጥፎ ሙዋርት ማሰማት ከጀመሩ ቆይተዋል። የለም ንበዝ፥ የባለርስትና ጭሰኛን ግንኙነት የሚመለከት የህግ ረቂቅ ከመሬት ሳይነሳ ጭንቅላቱን ብለን መግደል፥ ፍታቱን ማጣደፍና፥ ግብለተ መሬቱን ቆሎ መፈፀም አለብን. . .»

እያማሰሉ የሚጠጡት ውስኪ ትዝ አለውና አንገሽግሾው፥ ጌታቸውን። ውስኪ ሲማሰል ደስ አይለውም። «አንተ ገና ወጣት የሆድ እቃህ ሁሉን ይችላል። የኛ ግን ስቶማኩም፥ ጉበቱም፥ ኩላሊቱም ተነክቶአል። በዚህ ላይ፥ የደም ብዛት፥ የደም ማነስ፥ ሪህ፥ ኧረ ስንቱ! ጨው፥ ቅመም፥ ቅቤ፥ በርበሬ፥ ሲጋ፥ መጠጥ፥ ሱካር ምን ያልተከለከልነው ነገር አለ ብለህ ነው? በጎመን ውሀ ነው የምንኖረው። በቁም ሞቶናልኮ እያለ ውስኪውን ለማለሳለስ እያማሰሉ ሲጠጡና ከየፋርማሲው እንደ ከረሜላ የሚገዙትን፥ የደም ብዛት፥ የጨጉዋራ፥

የሱካር፥ የጉበትና የኩላሊት መድሀኒት፥ ‹‹ግሩም የሆነ መድሀኒት አግኝቻለሁ። አንድ አርመን ነው የሰጠኝ። እስቲ ሞክረው›› ሲል አንዱ፥ ሌላው ደግሞ፥ ‹‹የሰም ጃል ምነ ነካህ? ያለ ፋርማሲስት የሰጠን መድሀኒት ይሻላል›› እየተባባሉ ኪኒኖችን እንደ ዋዛ ሲውጡ ላንዳፍታ ታዩት። እንደ ሀበሽ መድኃኒት እንደ ከረሜላ እየተቀባበለ የሚቅም ህዝብ ይኖር ይሆን? በማለት ሲገረም፥ ኤ. ቢ. ዋይልድ የተባለ ፈረንጅ እ.ኤ.አ. በ1880 ኢትዮጵያን በጎበኘበት ጊዜ፥ እንደ ኢትዮጵያውያን መድሀኒት የሚወድ ህዝብ አላየሁም. . .›› በማለት በትዝብት ያሰፈረው ፅሁፍ ወሰል ብሎ ታየው።

ዋይልድ ከመቃብሩ ተነስቶ ኢትዮጵያውያን መድሀኒት እንደ ከረሜላ እየተለዋወጡ ሲቅሙ ቢመለከት ምን ይል ይሆን? በማለት ረጂም የአሳብ ጉዞ ለመጀመር ሲያዘግም፥ መልካሙ አቁዋረጠውና፥ ‹‹ጋሼ ጌታቸው፥ ብር ሊወድቅብዎት ነው›› ብሎ በጣቱ ጠቆመው። ብር ሳይሆን የሎተሪ ቲኬት ነበር።

‹‹ሰድሳ ሽህ ብር ልጥል ነበር ጃል!›› አለው።

‹‹ዛሬ ነው እኮ የሚወጣው›› ሲለው፥ ጌታቸው የቲኬቱን ቁጥርና ሎተሪው የሚወጣበትን ቀን አገላብጦ ተመለከተና፥ ‹‹ልክ ነህ። የስድሳ ሽህ ብር ጌታ መሆን ነው ዛሬ!›› አለው።

መልካሙ ጠጋ ብሎ በስንት መከራ ካዳመጠው በሁዋላ፥ ‹‹ከትናንት ጀምሮ እጄን ይበላኛል›› አለና መዳፉን አከክ አከክ አድርጎ ሳመ።

‹‹እከክ እንዳይሆን?››

‹‹የለም እከክ አይደለም። ገንዘብ ላገኝ ስል ነው እጄን የሚበላኝ›› አለና፥ ትናንሽ አይኖቹ በተስፋ አበሩ፥ ‹‹እኔም ለገብርኤል ተስዬ በእርሱ ስም አንድ ቲኬት ገዝቻለሁ›› አለው።

ወዲያውኑ የቀበሌ ዲሞትፎር ተኩስ ሶስት ጊዜ አጉዋራ። ጌታቸው፥ ‹‹በለው!›› አለና፥ ‹‹ለምን በራስህ ስም አልገዛህም?›› ብሎ ጠየቀው።

መልካሙ በተኩሱ ደንግጦ አልሰማውም።

‹‹ምን አሉ?››

‹‹ለምን በገብርኤል ስም ገዛህ? ነው ያልኩህ።››

‹‹ገብርኤል ያውቃል ብዬ ነዋ! መቶዋን ብር ለሱ ተስያለሁ።››

‹‹አላሳነስክበትም? ከፍ ያለ ብር ለተሳለለት ሰው እድልህን አሳልፎ የለጠብህስ እንደሆን?

‹‹ይድረሰኝ እንጂ ምን ከፍቶኝ። ጃንጥላም እጫምራለሁ. . .››

‹‹ለንጋም አክልበት። ገብርኤል ባነስተኛ ጨረታ አይገደድም. . .››

‹‹እሪ በስመ አብ ይበሉ ጋሼ. . .››

‹‹በስመ አብ ብያለሁ። ግን ገብርኤል በስለት ተደልሎ አንድ ነገር ይስጠናል ብለህ አትጠብቅ። ከንቱ ነው›› አሰው።

‹‹በስመ አብ ይበሉ።››

‹‹ብያለሁ!›› ኢትዮጵያውያን ምድራዊ ባለስልጣኖችም ሆነ መላእክትን በጉቦ አባልገው የተመኙትን ለማግኘት ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ በአሳቡ ላንዳፍታ አጤነና ሲያበቃ፥ ውስኪውን ባንድ ትንፋሽ ጨልጦ ‹‹መላእክት በጉቦ የሚደለሉ የአጥቢያ ዳኞች አይደሉም። ብትሳልም ባትሳልም የእድልህን አታጣም›› አለው።

‹‹እግዜር አይሰጥም አይነሳም ነው የሚሉት?››

‹‹ሕለ! አዎን›› ብሎ፥ ነገሩን እዚያው ላይ ለማቆም አስቦ ነበር።

ነገር ግን፥ መልካሙ ቀጠለና፥ ‹‹ማንኛውም ነገር እግዜር ካልተጨመረበት አይሆንም›› አለና፥ ነገሩን በይበልጥ ለማብራራት አስቦ፥ ‹‹አይ ጋሼ ጌታቸው፥ አባቴና ጉዋደኛው፥ ፊታውራሪ ጉልላት ይባላሉ፥ አሁን እንኩዋን አቶ በሉኝ ብለዋል አሉ›› አለውና፥ ትዝ ብሎት፥ ‹‹ያውቁዋቸው የለም እንዴ? የጢቾ አንደራሴ በነበሩበት ጊዜ ከዚህ አይታጡም ነበር›› አለው።

‹‹አዎን አውቀዋለሁ። ከማወቅም የእህቴ ባል ነው. . .››

‹‹እውነትዎን ነው እንዴ? ይህን ሁሉ ዘመን ላላውቅ እንዴት ቀረሁ ይገርማል. . .››

‹‹መገረሙን ትተህ የጀመርከውን ታሪክ ንገረኝ›› አለው።

‹‹አዎን። ይሄውልዎ አባቴና እሳቸው አንድ መንደር ውስጥ ተወልደው አብረው ያደጉ ናቸው። አባቴ በጭስኛነት ማቆ ሲሞት፥ እርሳቸው ያው እንደሚያውቁት ባለብዙ መሬት ጌታ ሆነው፥ ስንት ወግና ማእረግ አይተው እዚህ ደርሰዋል። ታዲያ ይሄ የእግዚአብሔር ስራ አይደለም ብለው ነው›› ካለ በሁዋላ፥ ትንሽ ቆይቶ ‹‹የኔም አብሮ አደግ ጉዋደኛዬ ፊታውራሪ ቤት ይሰራ ነበር. . . ደርቤን ያውቁት የለም እንዴ. . .›› አስራ ሁለተኛን ጨርሶ ‹‹በናንተ መስሪያ ቤት ስራ ይዞ. . . ትናንት ማታ ደግሞ የአብዮት ጥበቃ ሲቀ መንበር ሆኖ ተመረጠ አሉ። እኔ ግን ይኸው ከዚሁ ቡና ቤት ውስጥ አረቄ ቀጂ. . . ብርጭቆ አጣቢ. . . ለስካራሞች አፋሽና አጎንባሽ ሆኜ ቀርቻለሁ›› አለው።

‹‹ደርቤን ታውቀዋለህ?››

‹‹አብሮ አደጌ ነው ስልዎት! የዛሬን አያድርገውና ከኔ የባሰ መናጢ ድሃ ነበር›› ብሎ፥ ስለ ደርቤ አባት አሟሟት በሰፊው አጫወተውና፥ ‹‹እናቱም በችግር ተቆራምደው ነው ሁዋላ በተስቦ የሞቱት፥ ካለው በሁዋላ፥ ‹‹የኔም ወላጆች በጭስኝነት ሲኖሩ፥ ሁዋላ ባለርስት ስለነቀላቸው ችግር በዛና እኔና ደርቤ ተመካክረን ወደ አዲስ አበባ ኮበለልን። እግዜሩም ጥሎ አልጣለን፥ አቶ ጉልላት የጢቾ እንደራሴ በመሆን ተመርጠው እንደ መጡ እንዳጋጣሚ አገኘናቸውና እኔን እዚህ እሜቴ ቡና ቤት ስራ ሲያስይዙኝ፥ ደርቤን ለአሽከርነት ወደ ቤት ይዘውት ሄዱ። ያባቴ ጉዋደኛ የጠቀሙኝ መስሎአቸው ነበር በተሻለ ደመወዝ ያስቀጠሩኝ. . .››

‹‹አሁን ከደርቤ ጋር ትገናኛላችሁ?››

‹‹አዎን ይጠይቀኛል። ኧረ ከመጠየቅም እዚህ እሜቴ ቤት ለምንሰራው ሰራተኞች በሳምንት ሁለት ጊዜ እየመጣ ንቃት ይሰጠን ነበር. . .››

‹‹ምን እያለ?››

የቀይ ኮከብ ጥሪ

«ሽረ ስንቱ ተወርቶ ጋሼ! ብቻ አጥብቆ የሚመክረን ስለ ዲሲፕሊን ነው። ያለ ወዛደራዊ ዲስፕሊን የሰፊው ጭቁን ህዝብ ድል አድራጊነት አስተማማኝ አይሆንም ይለናል። እንዲያውም አንድ ቀን ስለ ዲስፕሊን ሲያስተምረን፥ የአባቱን አሟሟት አንስቶ፥ (አባቴ በተጠናከረ ድርጅታዊ ዲስፕሊን የታቀፈ ቢሆን ኖሮ፥ ሀቀኛ ትግሉ በትንሽ ትንፋሽ እንደ ሻማ ጠፍቶ፥ እሱም እንደ ውሻ ጥንብ የትም ተጥሎ አይቀርም ነበር)፥ ያለን በጣም ትዝ ይለኛል. . .»

«የዲስፕሊን ትርጉም ገብቶሃላ?» አለው፥ የውይይት ክበብ ቀንደኛ ተናጋሪ እየሆነ መሄዱን በንዴት እያስታወሰ።

«በመጠኑ ገብቶኛል። ያው እንደሚያዩት እዚህ ቤት ውስጥ ያለን ሰራተኞች መብታችንን እያስከበርን ግዴታችንንም እንፈፅማለን። እንደ ሌሎች አሰሪያችንን አንቺስ ተነስተሽ ለምን ቡና አትቀጂም? እያልን አናስቸግርም። እንውረስ አንልም። ታዲያ እሜቴ የዲሲፕሊናችን ነገር ሲያስደስታቸው መብት የሚሉዋትን ቃል ጆሮአቸው መስማት አይወድም። ምን ያደርጋል አባክዎን! የአርባ ቀን እድሌ ቀጂና ብርጭቆ አጣቢ አድርጎ አስቀርቶኛል!»

ጌታቸው ዝም ብሎ ሊያልፈው አልፈለገም። ምንም ነገር ቢደርስባቸው፥ ክፉም ሆነ ደግ፥ የአርባ ቀን እድሌ ነው በሚል ጎታች አስተሳሰብ እየተመሩ ሁሉንም ነገር በመተው እጅና እግራቸውን አጣምረው ወደ ላይ በማንጋጠጥ ባዶውን ሰማይ የሚመለከቱትን ሰዎች በርቀት ስለሚንቃቸውና ስለሚያዝንላቸው፥ ካርል ማርክስ በትክክል እንዳለው፥ «ሃይማኖት ህዝብን አደንዛዥ እፅ ነው።» ገዥ መደቦች፥ ሰፊው ህዝብ መፅሀፍ ቅዱስን አቅፎ ወደ ላይ በማንጋጠጥ፥ ምንም ጠብ ላይልለት፥ ሰማይ ሰማዩን እየዳበሰ ምድራዊ ህይወቱን ችላ በማለት በዚያኛው ሀሳባዊ አለም ላይ ልቡን ሲያሳርፍ፥ እነርሱ አይናቸውን ከፍተው በዚህኛው አለም ብዝበዛቸውንና ጭቆናቸወን የሚያጠናክሩበት መሳሪያ ነው። በአገራችንም ቢሆን ነገስታቱ፥ መሳፍንቱና መኩዋንንቱ፥ እና፥ አንዳንድ ጳጳሳት በአንድነት ሆነው ሰፊውን ህዝብ አይኑን ጋርደው የኖሩት በሃይማኖት መጋረጃ ነው። ሚሲዮናውያን ወደ አፍሪቃና ወደ ሌሎችም አህጉራት ሰርገው ከገቡ በሁዋላ፥ አገሬዎቹን መሬት አልባ፥ እራሳቸውን ግን ባለመሬት በማድረግ ለቅኝ ግዛት በር

የከፈቱት፥ ሁዋላ ቀር የሆነውን ህዝብ መፅሀፍ ቅዱስ አስታቅፈው ምድሪቱን ትቶ ወደ ሰማይ እንዲያንጋጥጥ ለማድረግ በቻሉበት ጊዜ ነው። ስለሆነም፥ አምላክ ይህን ያደርግልኛል፥ ያህን ይሰማኛል፥ ይነሳኛል፥ ይነፍገኛል የሚል ጭፍን አስተሳሰብ ሰብአዊነተትን ያህል ከቡር ነገር ከመካድ ይቆጠራል። ይልቅስ ሰውን ሰው የሚያደርገው ስራው ነው፤ እንደ ሰው ልጆች ስርአት ማህበር ሁኔታ ገነትም ገሀነም ልትሆን ትችላለች፥ ብሎ በአጠቃላይ ሊያስረዳው ፈለገና፥ ‹‹ኤጭ - አሁን ምን ያደርጋል፥ እንደ ዮሀንስ መጥምቁ በምድረ በዳ መጮህ?›› ብሎ በማሰብ፥ እንዲያው ለነገሩ ያህል፥ ‹‹እግዜር ካለ በሰዎች ጉሮ ውስጥ ገብቶ የያንዳንዱን እድል አይወስንም። ከሰዎች መካከል እየመረጠ፥ አንዱን እድለ ስንኩል. . . ሌላውን እድለ ቀና፥ አንዱን ድሃ ሌላውን ጌታ፥ አንዱን ገዥ ሌላውን ተገዥ የሚያደርግ አምላክ ካለ ብትፋረደው ይሻላል እንጂ ልታመሰግነው አይገባም›› አለውና፥ ውስኪ እንዲጨምርለት አዘዘው።

‹‹በስመ አብ ይበሉ፥ ጋሼ።››

‹‹ብያለሁ።››

‹‹እርስዎ በምንም ነገር አያምኑም ማለት ነው?››

‹‹በራሴ አምናለሁ. . .››

‹‹እሺ በስመ አብ ይበሉ፥ ጋሼ. . .››

‹‹ብያለሁ።››

‹‹ጋሼ፥ ዛሬ ከመሬት ተነስቶ ደስ ደስ ይለኛል. . .››

‹‹ሎተሪ ይወጣልኛል ብለህ ይሆናል!››

‹‹ለዚያውም ሁለት እድል አለኝ. . .››

‹‹ምንና ምን?›

‹‹የኔ ያልወጣልኝ እንደሆነ የእርስዎ ሳይወጣ አይቀርም. . .››

‹‹ታዲያስ?››

‹‹ታዲያማ ስድሳ ሽህ ብር ከደረሰዎት ወፈር ያለ ጉርሻ አይነፍጉኝም ብዬ ነዋ! እንደሚወጣልዎት ታይቶኛል. . .››

‹‹እንዴት ታየህ?››

‹‹ቁልጭ ብሎ ነዋ የታየኝ! ቲኬትዋ ከኪስዎ ብቅ ያለችው ያለ ምክንያት አይደለም። ብቅ ሲያደርጉዋት ጊዜና ደግሞ ልቤ የደነገጠው መደንገጥ እንዲህ አይምሰልዎት! ጋሼ ጌታቸው፥ ቢደርስዎት ስንት ይሰጡኛል?››

‹‹ሽህ ብር›› አለው፥ ሳያስብ።

‹‹እኔ ደግሞ ለስላሴዎች የአስር ብር ግምጃና ጡዋፍ።

ከጥይት ቤት አካባቢ የሽጉጥና የዲሞትፎር ተኩስ አይሎ መሰማት እንደጀመረ ሀብቴ ይርጉ፥ ጉደታ ፈይሳ፥ ታቦር ይመርና ኢዮብ ገብረማርያም ተንጋግተው ገቡ። የአራት ኪሎና የአቡነ ጴጥሮስ አንጋፋ ጋዜጠኞች ነበሩ።

ጌታቸው ሁኔታቸውን ትመስላላችሁሳ!›› አላቸው።

አራቱም የሚለውን ለመስማት ጆሮአቸውን ጠጋ አድርገው ነበር።

ታቦር አሳቡንና ምላሱን አስተባብሮ ለመናገር እየተቸገረ፥ ‹‹እኛን የሚገድለን አረቄ ነው፥ ጥይት ሲያልፍም አይነካን›› አለው።

ታቦር ሰውነቱ አልቆ፥ ስለታም ጠይም ፊቱ አመዱ ወጥቶ በየቦታው የተኮረኮመች ሰይቸንቶ መስሎ ነበር።

ጉደታ ፈይሳ በጌታቸው ውስኪ እየቀና፥ ‹‹እኔ ብሞት ለቀባሪ አላስቸግርም፤ በጋዜጣ ወረቀት ጠቅልላችሁ ቅበሩኝ›› አለ፥ መልከ መልካም ቀይ ፊቱን እያብረቀረቀ።

ጉደታ ፈይሳ እድሜው ገፋ ያለ ቢሆንም፥ የወጣትነት መንፈስ ይታይበታል። ራሱን ትልቅ ጋዜጠኛ አድርጎ የሚቆጥር በመሆኑ፥ ኢዮብ ገብረማርያም ሁልጊዜ ስለሚናደድ፥ ‹‹. . .በጋዜጣ ወረቀት የሚጠቀለለው እቃ ብቻ ነው። ጋዜጠኛ አይደለም›› አለው፥ ምላሱን እየገመደ።

‹‹በሩን ዘግቶ የሚውል የዲስክ ጋዜጠኛ እዚህ ውስጥ ምን አገባው? ህዝባዊ ጋዜጠኞች ይናገሩ!›› አለውና፥ ኮት ብሎ ሳቀ። ጉደታ ራሱ ተናግሮ ራሱ ይስቃል።

‹‹ድንቄም ህዝባዊ ጋዜጠኛ!›› አለው ኢዮብ።

ታቦር አይኑን እያቁለጨለጨ፥ ‹‹የለም እኮ! እንዴ፥ እንዴ! ጉደታ እኮ ለመቃብሩ የጋዜጣን ወረቀት የመረጠው የራሳ ሳጥን ለመግዛት ስለማይችል ነው›› አለ።

‹‹የራሳ ሳጥን ፍጆታ በዝቶ ምርቱ ስለ ቀነሰ ዋጋውም ንሮአል!›› አለ ሀብቴ፥ ደረቅ ቀልዱን አክሎ።

‹‹እሱም የዋጋ ቁጥጥር . . . እንዲደረግበት ያስፈልጋል። አለበለዚያ. . . <u>መኖርም መሞትም ከአቅማችን በላይ ሊሆኑ ነው</u>. . .››

‹‹ለዚህ ነው እኮ፥ በጋዜጣ ወረቀት ጠቅልላችሁ ቅበሩኝ የምለው. . .››

ሀብቴ ወደ ላይ አንጋጦ ጣራ ጣራውን እየተመለከተና ቀይ ድዱን እያሳየ፥ ‹‹አትቸገሩ!›› አለ። ‹‹እኔ የራሳ ሳጥን በርካሽ የሚሸጥበት ሱቅ አይቻለሁ። በሩ ላይ ምን ተፅፎአል መሰላችሁ? ከፍ ብሎ በትልቁ፥ ‹‹ቀይ ሽብር እናፋፍማለን›› ይልና፥ ከስሩ ደግሞ፥ ‹‹በርካሽ ዋጋ የራሳ ሳጥን ይገኛል›› ይላል። ያለንግድ ሚኒስቴር ቁጥጥር ፍጆታንና ፍላጎትን ያስተካከለ ቤት. . ለማንኛውም ነገር አዳው ገብስ ነው›› ብሎ ወደ መልካሙ ዞረና፥ ‹‹ያንን መርዜን አቀብለኝ›› አለው።

መልካሙ ቢራ አውርዶ ሰጠው።

ጉደታና ታቦር ተያዩ። ታቦር ወደ ኢዮብ እየተመለከተ፥ ‹‹ዛሬ የተወለድኩበት ቀን ነው አላልከንም ነበር እንዴ? አንተን ተማምነን ነው እኮ የመጣነው›› አለው።

ደርግ ባወጣው መግለጫ የፍራንክ ቅጭልጭል በሚሰማበት ቦታ ሁሉ እየዞሩ በወሬ የሚነግዱትን ጋዜጠኞች በጥብቅ ካወገዘ ወዲህ፥ ታቦርና ጉደታ የሚተማመኑት በገዛ ኪሳቸው ሳይሆን በሌሎች ሰዎች ኪስ ሆኖአል። በፊት

ቢሆንም ናሮ፥ መደበኛ ስራችን ችላ ብለው በየቀኑ የሚቃርሙትን ወሬ ለቢ. ቢ. ሲ. ለርይተር፥ ለኤ. ኤፍ. ፒ፥ለዩ. ፒ. አይነ ለሌሎችም የምእራብ ዜና ምንጮች እየሸጡ በሚያገኙት ገንዘብ፥ በየምሽቱ አለማቸውን ይቀጪቱ ነበር። በተለይም ጉደታ - የዛሬን አያድርገውና. . .

«እኔ የምሸናው እኮ እንደናንተ ውሀ አይደለም፥ ንፁህ የእሜቴን ቤት ውስኪ ነው» እያለ ጉራውን የሚነዛበት ጊዜ ነበር። በሙያው አንፃር ቢሆን ከስራው ጉራው ይቀድማል። ሪፖርተሮች ወይም ሌሎች የውጭ ሰዎች የማይጥመው ፅሁፍ ሲያቀርቡለት፥ «እኛ ካየንላችሁ ይበቃል!» በማለት ነበር ከቢሮው የሚያባርራቸው። አንዳድ ሪፖርተሮች፥ «ለምን ዜናችን አልወጣልንም? አድልዎ ተደርጎብናል!» በማለት ሊከራከሩት ሲሞክሩ ሁልጊዜ የሚሰጣቸው መልስ፥ «እኛ በማይማን መካከል አድልዎ አናደርግም» የሚል ነበር። ከእርሱ እኩል ጋዜጠኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ አይመስለውም። «የጋዜጠኝነትን ሙያ ሀሁ ያስተማርነው ሁሉ ባቁዋራጭ ቀድሞን ሄደ» እያለ ዘውትር ይበሳጫል። ሆኖም፥ በብስጭት ምክንያት እንደ ሌሎቹ ራሱን ጥሎ አይጥልም። የጊዜውን የአለባበስ ሞድ እየተከተለ ይሽቀረቀራል። ሆዱንም ስለሚወድ ቡፌ የሚያቀርቡ ሆቴሎች ሊስት ከማስታወሻ ደብተሩ ውስጥ አይተፋም። ይበላል፥ ይጠጣል፥ ይሰበሳል። ለገንዘብ ደንታ የለውም። ሌቶችም በመልኩ ብቻ ሳይሆን በሌጋስነቱም ጭምር ስለሚወዱት ፈልገው ይጠጉታል። አባ መስጠት ታዲያ፥ በየእለቱ እንደ ሸሚዝ ለሚቀያይራቸው ሌቶች ሁሉ፥ ተበድሮም ተለክቶም ቢሆን የጠየቁትን ሳይፈፅምላቸው አያድርም። ስለሆነም፥ ከአቅም በላይ በሚኖረው ጉሮ ምክንያት የፈላበት እዳ ከራስ ጠጉሩ ቁጥር ልክ ነበር። ታዲያ ጉደታ ግድ አልነበረውም።

«ዘሬች አለም የምኖትረው አንዴ ነው። የሰው ችግር ደግሞ ለመጀመሪያው መቶ አመት ብቻ ነው» ስለሚል፥ የህይወት ኩርሲም ገጭቶት ራሱን ለመቆጣጠር ሙከራ የጀመረው ኢዮብ እየተናደደ. . . «አንተ እድሜህ ነው እንጂ የገፋው አሳብህና ሁኔታህ የጎረምላ ነው። አስተሳሰብህና ስውነትህ እኩል አልበሰሉም» ሲለው፥ «ልክ ብለሃል። እኔ እርጅናን እታገለዋለሁ። ፍፁም አላቀርበውም፥ የታባቱ! እንዳንተ እርጅና የተጫናቸውን ሰዎች ሳይ ያስጠላኛል። በቁም መበስበስ! ኤጭ! ይህ ህይወት የሚያስጠላኝ ለዚህ ነው።

ሁሉም ነገር በወጣትነት ዘመኑ ነው ደስ የሚለው። እርጅናህን አታጋላብኝ። እርጅና የወለቀ ጥርሱን፥ የሸበተ ፀጉሩን፥ የተጨማደደ ፊቱን፥ የጎበጠ ወገቡን ሊያሳየኝ እየተጎተተና እየተንቀጠቀጠ ቢመጣብኝም እኔ እሸሸዋለሁ። ላየው አልፈልግም፤ እርጅና ሌባ ነው!›› ብሎ ይመልስለታል።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መግቢያ ፈተና በወሰደበት ጊዜ በመላ ኢትዮጵያ ፈተናውን አብረውት ከወሰዱት ተማሪዎች መሃከል አንደኛ በመሆን የኢሉባቦርን ስም አስጠርቶ ነበር። ወላጆቹ ቀርተው የአገሩ ተወላጆች ያን ጊዜ ምን ያህል እንደ ኮሩበትና ሁሉም እንደ አቅማቸው ስጦታ አምጥተው እንዳበረከቱለት ባስታወሰ ቁጥር ልቡ በደስታ ይሞቅና አይኖቹ እንባ ያቀራሉ። መስክረም ጠብቶ ወደ ጄኔራል ዊንጌት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመግባት ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት በተነሳበት እለት፥ ከቤት ወጥቶ ያልሸኘው የጎረ ከተማ ነዋሪ ቢኖር ጥቂት ነበር። ብር አውጥቶ ያልሸጎጠለት፥ እንትፍ - ብሎ ይቅናህ - አድባርዋ ትከተልህ - ርጥብ ሳር ነጭቶ እግርህ እንደዚህ ርጥብ ይሁን ያላለው አልነበረም። የሸኙት ሁሉ የተስማሙበት ነገር ቢኖር፥ ኢዮብ አንድ ቀን ትልቅ ሰው ይሆናል። በሚል አሳብ ላይ ነበር። የወላጆቹን ኩራት፥ የዘመዶቹን ትምክህትና ህዝቡ ያሳደረበትን እምነት ለመጠበቅ ቆረጠ። ለራሱ በገባው ቃል መሰረት፥ ጄኔራል ዊንጌት ትምህርት ቤት በአምስት አመት በቆየበት ጊዜ፥ ከአንደኝነት ደረጃ አንድ ጊዜ እንኩዋን ዝቅ ብሎ አያውቅም። በተለይ በሂሳብ የክፍል ጉዋደኞቹ ቀርተው አስተማሪዎቹም ጭምር አልፎ አልፎ ለእርዳታ ይጠይቁት ስለነበረ፥ ‹‹ዳግማዊ አይንስታይን›› እየተባለ ይጠራ ነበር። ‹‹ይህን ጭንቅላት ይዘህ የሚያሳስብህ ነገር የለም። በሄድክበት ሁሉ ከፍተኛ እድል ይጠብቅሃል›› የማይለው አስተማሪ አልነበረም። የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪ የነበሩት እንግሊዛዊ አዛውንት በተለይ፥ ‹‹የዚች አሳዛኝና ውብ የሆነች አገር የወደፊት ተስፋ የሚሆኑት ወጣቶች ውስጥ አንተ አንዱ ነህ!›› እያሉ ያወድሱትና ያበረታቱት ስለነበር፥ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ እንግሊዝ አገር እንዲሄድ ታጨ። የወደፊት እድሉ እንደ ፅጌረዳ እምቡጥ ከፊቱ እየፈነዳና እየፈካ ሊሄድ ተሰማው። ጫማው - ካቦርቱ - ሱፍ ልብሱ፥ ባርኔጣው - ከራባቱ ሳይቀር ተገዛለት። ከራባቱ እንዴት እንደሚታሰር ለመማር የፈጀበትን ጊዜ ሲያስታውስ ይስቃል።

ከአዲስ አበባ ሲነሳ፥ ኦጥቂት እመታት በሁዋላ ሀሲም ሆኖ ከእንግሊዝ አገር እንደሚመሰስ ይታየው ነበር።

ከእንግሊዝ አገር ከምርጥ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ጋር የህክምናና ትምህርቱን ለሶስት አመት ያህል ከተከታተለ በሁዋላ፥ የእንግሊዝ አገር አየርና የእንግሊዝ ህዝብ የአውሬነት ጠባይ እያስጠላውና ብቸኝነትም እየተሰማው በትምህርቱ ላይ ማተኮር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሳነውና እየተበሳጨ ይሄድ ጀመር። ጉርምስናውም መጣ። ግን መፃህፍትን ከማገላበጥ ሌላ ሴቶችን እንዴት አድርጎ ለመቅረብና ለማግባባት እንደሚችል እንግዳ ነገር ሆኖበት ግራ እየገባው፥ ከኢትዮጵያ ይዞት የሄደው የአይናፋርነት ጠባይም ልጉዋም ሆኖበት አስቸገረው - ጉርምስና እየበጠበጠው - የሴት ፍላጎት በአይኑ እየዞረ ናላውን እየበጠበጠው፥ የእንግሊዞች ጠባይና የእንግሊዝ አገር የአየር ጠባይ አጥንቱ ድረስ ዘልቆ እየቀዘቀዘው የመንፈስ እረፍት ፈፅሞ ስላሳጣው፥ ቢራ ቤቶችን ማዘውተር ጀመረ።

ከጊዜ በሁዋላ ከነአካቴው ክፍል መግባቱንም ተወው። መፅሀፍ ማገላበጥና ማንበብ ቀርቶ ማየትም ፈፅሞ አስጠላው። ቢራ ቤት አምሽቶ በገባ ቁጥር ብቸኝነት እያጠቃው፥ ፍላጎቱ እየባሰ - ጉርምስናው እንደ ነበልባል እያቃጠለው - ያደገበት መንደር - ሜዳው - ሽንተረሩ - ጎረቤት - ጉዋደኞቹ - ወንዙ - ተራራው - ሽለቆው - አደይ አበባ - መስቀል - ዳቦ - ቡሄ - የቡሄ ዳቦ - ጅራፍ - ጢስ - የባህር ዛፍ ማገዶ - የጢስ ሽታ - ዶሮ ወጥ - ነጭ እንጀራ - ዳቦ - የቡሄ ዳቦ - መንገድ - ሜዳዎችን እያቁዋረጠ የሚሄድ የእግር መንገድ - እርሻዎችን እያቁዋረጠና እየተጠማዘዘ የሚሄድ እግር መንገድ - ዝሬ - አፈር መሳይ ገበሬ - በሬዎቹን ጠምዶ ‹‹አህ በሬ!›› ሲል - አፈር - የጥቁር አፈር ሽታ - ትዝ ትዝ አያለው - እየናፈቀው አዲስ አበባ - የአዲስ አበባ ሽታ - ሳዱላ - ዳሌዋ የሞላ - ጡቶችዋ ያጎጠጎጡ - አይኖችዋ ያጎረጡ - ጥርሶችዋ የነጡ - ከንፈሮችዋ ያበጡ - አንገትዋ እንደ ባህር ማሽላ የተዘለሰ - ደምግባትዋ ከሩቅ የሚጣራ - ስትስቅ የምታፈዝ - ቀና ስትል የምታደነዝዝ - ልጃገረድ - የልጃገረድ ጠረን - ደም ግባት - ወዝ - አካል - በአንዱ አንግሊዝ አገር ብርድና ዝናም - ዘወትር ዝናብ የሚያንጠባጥብ ጃንጥላ የድንች ጥብስ ሽታ - የክፍት ሰገራ ሽታ - ህንፃ - ሰማይ ጠቀስ ህንፃ ዝምታ

የቀይ ኮከብ ጥሪ

- ዝምታ - አውሬ - አውሬነት - ተናግሮ የማያናግር - ቢያናግሩት የማያሰማ - በየመንገዱ ጋዜጣ - በየአውቶቡሱ ጋዜጣ - በየባቡሩ ጋዜጣ - በየአውቶቡሱ ጋዜጣ - ጥቁር ሻንጥላ - ጥቁር የዝናብ ልብስ ነጭ ሸሚዝ - ቀይ አፍንጫ - ግራጫ የድመት አይን - በየቦታው - ኢዮብ ትዝታውን - ፍላጎቱን - ብስጭቱን ለመቁዋቁዋም አልቻለም። አንድ ምሽት ሰክሮ ገብቶ መፃህፍቱን ሁሉ ቀዳደደና ጣለ።

ከዚያ ብዙም አልቆየ። በእንግሊዝ አገር የሚገኘው የኢትዮጵያ ባለስልጣን ከጥቂት ወራት በሁዋላ ትመለሳለህ በሚል ተስፋ በኤርፕላን አሳፍሮ ወደ አዲስ አበባ ላከው።

ወራት አልፈው ወራት ተተኩ። ወደ እንግሊዝ አገር የመመለስ ተስፋው እየራቀ ደብዛው እየጠፋ ሄደ። በኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ሀኪሞች አንዱ የመሆን ተስፋው ማክተሙ በታወቀው ጊዜ ቅስሙ ተሰበረ። ብስጭቱን ለመርሳት ሲል ከቢራ ወደ ውስኪ - ከውስኪ ወደ ጂን - ከጂን ወደ ቀንዶ - ከቀንዶ ወደ ጠጅ ከሀኪምነት ወደ ጋዜጠኛነት ገባ . . .

ማስታወቂያ ሚኒስቴር በገባ በሁለተኛው መር አንድ ቀን ከአንድ ቡና ቤት ደጅ ቁጭ ብሎ ሲጠጣ አንዲት ዳሌዋ የሞላ - ጡቶችዋ ያጎጠጎጡ - ከንፈሮችዋ ያበጡ፥ አንገትዋን የደፋች ሴት ስታልፍ አየ። ቤትዋ ድረስ ተከትሎአት በመሄድ፥ አይን አውጥቶ ለጋብቻ ከጠየቃት በሁዋላ ነበር ሳምንት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ አግብቶአት ትዳር ለመመስረት የበቃው።

ጋብቻውም ቢሆንም አልሆነለትም። ሚስቱ ለቤተሰቡ የጉሮ ዋሰትና በማሰብ፥ ‹‹ለምን መሬት አንገዛም፥ ቤት አንሰራም፥ ገንዘብ ባንክ አናስቀምጥም? ደመወዝህን በሙሉ በየወሩ ለኔ ማስረከብ አለብህ እያለች፥ ነጋ ጠባ ስለምትጨቀጭቀውና በሽማግሌዎችም ፊት ቢያንስ በወር ሁለት ጊዜ ስለምትወቅሰው፥ አይንዋን ማየት ድረስ አስጠልቶት ነበር። እና፥ በዚህም የተነሳ ይጠጣል። ጠዋት በማለዳ ይወጣል - ሴሊት በውድቅት ይገባል - ከጭቅጭቅዋ ለመሸሽ ሲል. . .

ግን ሚስቱ ነጋ ጠባ ጭቅጭቅዋን አትተውም - በሌተኛ አዳሪነት ያሳለፈችው መራራ ዘመን ትዝ እያላት።

ባለቤቱ ከእርሱም አልፋ በየውድቅቱ ከቤት አምጥተው በድኑን ጥለውላት የሚሄዱትንም የአረቄ ጉደኞቹን ጭምር፥ ‹‹እናንተ ናችሁ እንዲህ የምታደርጉት፣ አጫራሾች! የምትጠጡት የልጆቿንና የኔን ደም ነው!›› እያለች፥ አኩርፋና ገላምጣ በስድብ ስለምትሸኛቸው፥ ምላስዋን በመፍራት ወደ ኢዮብ ቤት ብቅ ማለት ከተው ዘመን የለወም። እና፥ ይሄም እያበሳጨው ያስጣው ነበር - ጠዋት ማታ. . .

የቤተሰቡ ብዛት እየጨመረ ሲሄድ፥ መጀመሪያ ሁለት መኝታ ክፍል ያለው ቤት፥ ቀጥሎ ሶስት መኝታ ክፍል ያለው ቤት ሳይወድ በግድ እያስፈለገው፥ በፍላጎቱ መጠን የቤት ኪራይ እየጨመረበት፥ ኑሮው እየቆረቆዘ፥ ችግር ኪሱንና ጉዋዳውን እየዳበሰ፥ ችግሩ በልጆቹ ሰውነትና አለባበስ ላይ ከፉኛ እያንፀባረቀ፥ ደመወዙ በሞዴል ስድስት በቅድሚያ ተወስዶ እያለቀ፥ እድሉ በየወሩ መጨረሻ ላይ ደመወዝ መውሰድ ቀርቶ የደመወዝ መዘገብ መፈረም ብቻ እየሆነ፥ የጎረቤት ኪዮስክ ዱቤ እየተጫነው. . . በየአለቱ የሚፅፈውን ፅሁፍ በቤት ኪራይ ውድነትና በቤት አከራዮች ጭካኔ ላይ መመስረት ጀመረ። እንጨት ቆም ቆም - ማእዘን ሰካ ሰካ - ማገር መታ መታ - ጭቃ ለጠፍ ለጠፍ - ቀለም ቀባ ቀባ አድርገው ከሁለት ሙቶ እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር የወር ኪራይ መጠየቅ በወገን ላይ ይቅርታ የሌለው በደል መፈፀም ነው፥ እያለ ነጋ ጠባ ቢፅፍም ሰሚ አላገኘም። የቤት ኪራይ እየተወደደ ኢዮብም ርካሽ ቤት ፍለጋ ከተማ ዳር እየወጣ - በደብረ ዘይት መንገድ - በነፋስ ስልክ - በአስመራ መንገድ ኮላም በረት - በጉጃም መንገድ ከመርሀ ቤቴ ሆቴል አልፎ በመከራየት እየተንከራተተ ኑሮው እያዘቀጠ እንደ መሄዱ መጠን፥ በየጊዜው የሚፅፋቸውም ፅሁፎች በቁጭትና በንዴት፥ ተስፋ በመቁረጥና በብስጭት እየተሞሉ ሄዱ። በዚህን ጊዜ ነበር በጊዜው የነበሩት ባለስልጣኖች አደገና ኮሙኒስት ነው ብለው በማመን አላፊነት በሚጠይቅ ስራ ላይ እንዳይቀመጥ ያደረጉት።

እንዲሁም መጠጥ ቤቶች እየበዙ እንዳይሄዱ ቁጥጥር እንዲደረግ፥ መጠጥ ቤቶች ለህዝብ ክፍት የሚሆኑበት ሰአት እንዲወሰን ወጣቶች እንደ ልባቸው መጠጥ ቤት ዘው ብለው እንዳይገቡ እድሜያቸውን የሚያመለክት የመታውቂያ ካርድ እንዲይዙ ህግ እንዲወጣ፥ ከአገር ቤት ኮረዳዎችን

እያስኮበለሉ አምጥተው በሌተኛ አዳሪነት ርካሽ ሙያ የሚያስማሩት፥ የአልጋ ኪራይ የሚያስከፍሉና የኮቴ ዋጋ የሚጠይቁት ነጋዴዎችና ደላላዎች እየተያዙ በህግ እንዲቀጡ በፅሁፎቹ ሳያሳስብ ሳምንት አለፎ አያውቅም።

ሆኖም፥ በጊዜው በነበሩት ባለሥልጣኖች ዘንድ ፍፁም የኮሙኒስት ዝንባሌ ያለው መሆኑ የተረጋገጠው፥ አሜሪካኖችን ህገ መንግስት እየጠቀሰ በቪየትናም የሚያደርጉትን ወረራ ለሰላምና ለነፃነት፥ ለእኩልነትና ለወንድማማችነት ሲሉ እንዲያቆሙ በፅሁፍ ባሳሰበት እለት ነበር።

በጊዜው የማስታወቂያ ሚኒስትር የነበሩት ከቢሮአቸው ድረስ በእስቸኳይ አስጠርተውት ሲያበቁ፥ ምን ያህል ታግሰውት እንደኖሩ ካሳሰቡት በሁዋላ የፃፈው ፅሁፍ ያልታሰበበት፥ አላፊነት የማይሰማውና አላፊነትም ለመሸከም የማይበቃ መሆኑን በቁጣ ነገሩት።

‹‹የለም ኮ - እኔ - ጌታዬ በእውነቱ ለክፋት ብዬ አይደለም። እኔ አሳምራለሁ ብዬ ተሳስቼ ይሆናል።›› መቼም ሲናገር አሳቡን አሳክቶ መግለፅ አይሆንለትምና፥ ከርክር አይሉት ይቅርታ መደርደር ሲጀምሩ ‹‹አትንተባተብኝ ለበቃ!›› ብለው ከቢሮአቸው በግልምጫ አስወጡት።

ሚኒስትሩም ወዶ አልነበረም። በጠዋት ኢዮቤልዩ ቤተ መንግስት ተጠርቶ መሳፍንት፥ መኩንንትና ሌሎች ሚኒስትሮች ባሉበት ፅሁፉ የወጣበት ጋዜጣ፥ ‹‹የድሀ ልጅ! ይህን በጋዜጣችን ላይ እንድታወጣ ነው የሸምንህ?›› ከሚል ተግሳፅ ጋር ከአፍንጫው ላይ ተወርውሮ ነበር። ከዚያ በሁዋላ ነበር ሚኒስትሩ ወደ ቢሮው ተመልሶ፥ ‹‹የማስታወቂያ ሚኒስትር መሆን ከታች እሳት ከላይ እሳት የሚነድበት የቡሄ ደቦ መሆን ነው!›› በማለት ፅድቅ ቅኔ ተቀኝቶ ኢዮብን ከጋዜጠኝነት ስራው ያባረረው።

ኢዮብ ከሚኒስትሩ ቢሮ ወጥቶ በቀጥታ የሄደው ወደ ቢሮው አልነበረም። ወደ አቅራቢያው መጠጥ ቤት አመራ። መጠጣት ጀመረ። ከምሹቱ አራት ሰአት ሊሆን፥ መነሳትም መቀመጥም ስላቃተው፥ ሁኔታውን የተረዱት የቅርብ ጉዋደኞቹ የላንሳ ተሸከመው ወደ ቤቱ ወሰዱት።

‹‹ልጆቹስ? ልጆቹስ? አፈር በበላሁት፥ ልጆቹስ? የባለቤቱ ፊቼኽት ነበር።

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹የምን ልጆች?››

‹‹ጥዋት ትምህርት ቤት እንደሄዱ አልተመለሱም። ወይኔ ልጆቼ! ምነው አፈር በበላሁት!››

ከጥቂት መጨዋጨዋህ በሁዋላ ነበር ጉዋደኞቹ እንደ ምንም አስታግሰዋት ሲያበቁ፥ የሚማሩበትን ትምህርት ቤት እንድትነግራቸውና ሄደው ልጆቹን ለማምጣት የተስማሙት።

ከአንድ ሰአት በሁዋላ በብርድ የተቆራመዱ፥ በረሃብ የተቆሉ፥ ከንፈሮቻቸው እንደ ከብት የደረቁ፥ በፍርሃት የተዋጡ፥ የደነገጡ፥ የሚንቀጠቀጡ፥ ህፃናት ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዳመሹት ሁሉ፥ እጅ ለእጅ ተያይዘው የገቡት። ከፍርሃታቸው የተነሳ እናታቸውን እስኪያዩ ድረስ አልተላቀቁም። እናትዬውም እንደዚያ በፍርሃት ተውጠውና ተርበው እጅ ለእጅ ተያይዘው በተመለከተቻቸው ጊዜ እንባዋ ባንዳፍታ ደረቀ። ‹‹ምኑን እናት ሆንኩት? አፈር ይብላኝ። የማርያም ልጅ የተሰቀለው በሰው እጅ በመሆኑ እናቱ አልሸሸችም። መስቀሉ ስር ተንበርክካ አለቀሰች። እኔ ግን እያየሁ በገዛ እጄ ልጆቼን ከችግር መስቀል ላይ አልሰቅላቸውም። እኔ ብሰቀል ይሻላል ብላ እንደ ወትሮዋ ሳትስማቸው ውልቅ አለች። ጭለማ ክንፉን ዘርግቶ ጋረዳት. . .

የኢዮብ የስራ ጉዋደኞች በስካሩ እየተገረሙና እንደ ጥጥ ቦጭቀው እያሙት፥ ብርዱን እያማረሩ፥ ልጆቹን ከትምህርት ቤት - ከዘበኛ ቤት ውስጥ - አውጥተው ቤት ለማድረስ ስላጠፉት ጊዜ እየተቆጩ ወደ አቅራቢያው መጠጥ ቤት ተመለሱ። ከኢዮብ የባሱ ጠጪዎችና ሃላፊነት የማይሰማቸው ከመሃከላቸው ጠፍተው - እህቶቻቸው - ወንድሞቻቸው - እናቶቻቸው - ዘመድም ባይኖር ገረዶቻቸው ዘወትር እንቅልፍ አጥተው እየባነኑ የሚጠብቁዋቸው ይገኙ ነበር። አንዳንዶቹ፥ በተለይም እየሰከሩ ገብተው ሚስቶቻቸውን በመደብደብና በመሳሪያ በማስፈራራት ከቤት ያስወጡና ወጥተውም ስራ እንዳይዙ በማስፈራራት ከአገር ያባረሩ፥ ሌሎች ደግሞ ሰክረው ገብተው ሲጃራ አቀጣጥለው በመተኛት ተከራይተው የሚኖሩባቸውን ቤቶች በእሳት በማጋየት እዳ የሚገፈግፉ፥ ሌላው ደግሞ ከስካሩ የተነሳ ሁለት

አዳዲስ መኪናዎች ፈፅሞ ከጥቅም ውጭ ያደረገና ዳግመኛ መሪ ላለመፈለጥ እርም ብሎ የተወ - በያይነቱ ነበሩባቸው. . .

ጉዋደኞቹ አስተኝተውት ከሄዱ በግምት ከሁለት ሰአት በሁዋላ ኢዮብ ነቃ። ቤቱ ባዶ ነበር። እረጭ ብሎአል። በቀሉት አይኖቹ ክፍሉን አማተረ። ልጆቹ እድ ለእድ እንደ ተያያዙ ከሶፋው ላይ ኩርምት ብለው ተኝተዋል። አስታወሰ. . .

ክፍሎቹን ሁሉ አዳረሰ። ማንም አልነበረም። አወቀ። ወደ ጉዋዳ ዘው ብሎ ቢላዋ አነሳ። ወደ መኝታ ቤት ሄደ። ወደ ውስጥ በረጂሙ ተንፍሶ አይኖቹን ከደነ ‹‹አማምዬ ራበኝ!›› የመጨረሻ ልጁ ድምፅ ነበር። ቢላዋውን ጣለው። እና ዳግመኛ ላለመጠጣት ማለ. . .

ኢዮብ በአሳብ ጭልጥ ብሎ መሄዱን አጤነና፥ ‹‹ምን ሆነሃል?›› ብሎ ጠየቀው ጌታቸው።

ኢዮብ እንደ መባነን ብሎ፥ ‹‹ሆሆሆ . . . ስላሳለፍኩት ከንቱ ሃምሳ አመት ነበር የማስበው። ህይወት አጭር መሆንዋን ብዙ ከመኖር የተረዳሁ መሰለኝ›› አለው።

‹‹አዎን፥ በተለይ ህይወት በዚህ ሰሞን አጭር እየሆነች ሄዳለች!›› አለው ጌታቸው፥ ውጭ የሚጠፈውን ተኩስ እያዳመጠ።

‹‹ላጭር ህይወት!›› አለና፥ ኢዮብ ሻይውን አነሳ። ቀጠለና፥ ‹‹የተወለድኩበትን ከንቱ ቀን ለማክበር ነው የመጣሁ›› አለው።

ጌታቸው ሲያስብ ቆየና፥ ‹‹የከንቱም ከንቱ። የኛ ህይወት በየአለቱ እንደምናዘጋጀው ዜና ነው። ሲያልፍ ወዲያውኑ ይረሳል - እንደ ትናንቱ ዜና›› አለና፥ ወደ ሀብቱ መለስ ብሎ፥ ‹‹ዛሬ ምን ወሬ አለ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ለው ውሻ አልነከሰም። ከብርሃንና ሰላም ፎቅ ተወርውሮ ራሱን የገደለ ካቡነ ጴጥሮስ ህውልት ጋር የተጋጨ፥ የልጃገረድ ክብር በግድ የደፈረ የለም። የወሬ ድርቅ ሆኖአል!›› አለው፥ ወደ ላይ አንጋጦ ቀይ ድዱን እያሳየ።

‹‹አይ የቡርዥዋ ጋዜጠኛ አመለካከት! ይኸ ሁሉ የቀበሌ ተኩስ፥ ተልባ ሊቆላ ነው በለኛ! በምስራቅ፥ በደቡብ፥ በሰሜን የሚካሄደውስ ጦርነት?›› አለው።

‹‹ኦ. . . እሱ የመደብ ጦርነት ነው. . .››

ሀብቴ፥ ይርጉ የሚቀልድ መሆኑን ቢያውቅም፥ ‹‹የመደብ ጦርነት ወሬ አይሆንም ያለህ ማነው?›› አለው።

‹‹የለም፥ መራራ ትግል ነው ማለቴ ነው። መራራ ትግል ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ነው የሚያስፈልገው። ትግል ነው የሚያስፈልገው፥ ወሬ አይደለም። ገባህ? በቃ፥ ፖለቲካ አታናግረኝ፤ እኔ እኮ የምትከተለውን መስመር አላውቅም!›› ብሎ፥ ለመዝፈን እየቃጣው፥ ‹‹ባሉባልታ ወሬ መነገድ. . . በውሸት ተነስቶ መቀደድ፥ እንደ ጣቃ መቀርደድ፥ በሰፊው ህዝብ መቀለድ፥ ወሬውን ወዛ ወዛ ቀባ ቀባ ማድረግ፥ በጋዜጣ ላይ መባለግ፥ በቲሺ መረግረግ - አክትሞአል!›› አለ።

ጉደታ፥ በሀብቴ ደረቅ ቀልድ እንደ መብሸቅ ብሎ፥ ‹‹ቁም ነገሩ ያለው አመለካከታችንን ከመለወጥ ላይ ነው›› አለ። ‹‹ህዝባዊ ጋዜጠኞች ብንሆን ኖሮ ይህ ሁሉ የመደብ ትግል እየጦፈ ስለወሬ ድርቅ አናወራም ነበር! የህዝቡን አስተሳሰብ መምራት ሲኖርብን ጅራት ሆነን ቀርተናል!››

‹‹ማን ከለከለህ ታዲያ!›› አለው ጌታቸው፥ ብሽቅ ብሎ።

ታቦር ነፃ ውስኪውን ጨለጠና፥ ‹‹እንዴ፥ እንዴ፥ የመደብ ልጓም እየሳበው ነው!›› አለ።

‹‹. . . አመለካከት. . . ምናምን. . . እንደ ሸሚዝ የሚለውጥ አይደለም። . . አመለካከት ከእምነት ተነጥሎ ሊታይ አይችልም። እኔ የሚገርመኝ የብዙ ለዎች እምነት እንደ ላስቲክ ለመሳብና ለማጠር መቻሉ ነው። አድርባይነት በዝቶአል!›› አለ ኢዮብ፥ ወደ ጉደታ እየተመለከተ።

‹‹የጊዜው በሽታ ነው!›› አለ ጌታቸው፥ ባሳቡ የደርቤን በድንገት መለውዮ አሰታውሶ።

ጉደታ፥ ኢዮብን ለመቅጣት ነፃ ውስኪን በአንድ ትንፋሽ ፈጁለጠና፥ ‹‹ዱሩ፥ ያረጀ ውሻ አዲስ ፊሊጥ ሊማር አይችልም፡፡ አለው፡፡

‹‹የማያውቁትን አውቃለሁ በማለት ተደናግሮ ከማደናገር ያረጀ ውሻ መሆን ይሻላል. . . ወሬ ዓፍን አልዓፍን ሀዝቡ እንደሆነ ከጋዜጣና ከራድዮ ቀድሞ ሄዶአል. . . ወሬ የለም ሰንል ከወሎ ረሀብ አልተማርንም. . . ሴላ ዲምብልቢ ሊያስፈልገን ነው?››

‹‹የዴስክ ጋዜጠኛ በዝቶ ነው›› አለው ጉደታ፡፡

ጌታቸው ሁሉንም በንቀት እየተመለከተ፥ ‹‹በደፈናው ጋዜጠኞች የሉም ብንል ይሻላል፤ በጋዜጣ ላይ የሚፅፈው ሁሉ ጋዜጠኛ አይደለም›› አላቸው፡፡

‹‹እንዴ፥ እንዴ፥›› አለ ታቦር፥ ‹‹የራጉኤል ደብተሮች ያቀኑት ቤት መሆኑ ቀረ እንዴ? ወይስ ያጌጡት ብል ይሻል ኖሮአል? የጋዜጠኛ ወዳጅ ካለህ ጠላት አያስፈልግህም ያለው ማን ነበር?››

‹‹ፖለቲካ ባታናግሩኝ አሁንም የሌኒንን መፅሀፍ እየጠቃቀሱ የሚያነበንቡ ደብተራዎች በዝተዋል›› አለ ሀብቴ፥ እንደ ልማዱ ወይ ላይ አንጋጦ ቀይ ድዱን እያሳየ፡፡ ትርጉመ ቢስ ፈገግታ ከፊቱ ላይ አይጠፋም፡፡

‹‹እድሜ ለውይይት ክበብ፥ ዛሬማ ምናሉ ብዙ ተምረናል፡፡››

‹‹አምን፥ ወሬ የለም እንጂ ትግሉስ ተጡዋጡፎአል›› አለ ሀብቴ፡፡

‹‹የራሳችን ጠላት የሆነው ማስታወቂያ ሚኒስቴር የገባን እለት ነው፡፡››

‹‹የለም፥ የኤምባሲ ኮክቴል የቀመስን እለት ነው›› አለውና ጉደታ፥ እንደ ልማዱ በራሱ አባባል ከት ብሎ ሳቀ፡፡

ጌታቸው ድምፁን የባሰውኑ ዝቅ አድርጎ፥ ‹‹ጉዳዩ ወደ ቀልድ ዞረ እንጂ፥ ሰው የራሱ ጠላት ነው›› አሉ፥ በጋዜጠኝነት ሙያ ራሱን ያስለከፈበትን ቀን እያስታወሰ፡፡

ከኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ ወጣ፥ እህቱ ወይዘሮ አምላለ አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ዘንድ ወስደው ባስተዋወቁት በሶስተኛው ቀን ነበር ጥሩ ደመወዝ ተቆርጦለት ማስታወቂያ ሚኒስቴር የተቀጠረው፡፡ አቶ መኮንን

ሀብተ ወልድ፥ ከራጉኤል ደብተራዎች ሌላ ጋዜጠኛ የለም ብለው የሚያምኑ ቢሆኑም፥ ጌታቸው ባጭር ጊዜ ውስጥ ስራውን ተለማምዶ ባሳየው ችሎታና ብልሀነት በመገረም፥ ጋዜጠኛንና ሰላይን ለይተው አይመለከቱም ነበርና፥ ለሁለቱም ስራ ያስጠጉት ጀመር። መኮንን ሀብተ ወልድን የሚያህል፥ አድራጊ ፈጣሪ፥ ፈላጭ ቆራጭ ባሰኘው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ገብቶ የሚያዝ ሰው መጠጋቱ ባልከፋም ነበር። ግን፥ ለምን ሊያስጠጉት እንደ ፈለጉ በትክክል ባወቀ ጊዜ ነበር አዘውትሮ የመለኪያ አንገት መጨበጥ የጀመረው። እንደ እድል ሆኖ ብዙም አልቆየም። ነፃ የትምህርት እድል አግኝቶ ወደ አሜሪካ ሄደ። ሆኖም፥ ከመኮንን ሀብተ ወልድ ቢገላገልም፥ በእሳቸውና በእህቱ ምክንያት የተጠናወተው የጋዜጠኛነት ሙያ እንደዛር አድሮበት ቀረ።

‹‹አቶ ጌታቸው ያልከው እውነት ነው። አሁንም ቢሆን የራሳችን ጠላት እኛው ራሳችን ነን›› አለ ታቦር። አሳቡ ከምላሱ ስለሚቀድም አፉን መክፈት አቅቶት ሲጨነቅ ሌላውንም ያስጨንቃል።

‹‹እንዴት?››

‹‹አዎን፥ ማለቴ፥መደብ ከልጉዋም ይስባል ይባል የለ? የንኡስ ክበርቴ ባህርያችን ነው ጠላታችን።››

‹‹ምን ለማለት ፈልገህ ነው?›› አለው ጌታቸው፥ ቆጣ ብሎ።

‹‹እኔ የምለው፥ አዎን፥ የማይቁዋቁዋሙትን ሃይል ከመጋፈጥ አብሮ መለለፍ ይሻላል ለማለት ነው. . . ማለቴ፥ ዛሬ አንድ ወሬ ሰምቻለሁ።››

ታቦር ወሬ እንደማያመልጠው ያውቃልና ጉደታ ተጣድፎ፥ ‹‹ምን ወሬ ሰማህ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ከማስታወቂያ ሚኒስቴር አርባ ሰዎች ሊጋለጡ ነው እየተባለ በሰፊው ይወራል። እንደ ሰማሁት ከሆነ ሁላችንም አለንበት። ቅድም እንዳልኩ የራሳችን ጠላት እኛው ራሳችን ነን። ንቀቱን ትተን ከሰፊው ሰራተኛ ጋር በውይይት ክበቦች ውስጥ ብንካፈል ኖሮ ይህ ሁሉ አይደርስብንም ነበር። ከሰፊው ሰራተኛ ጋር ሆድና ጀርባ ሆነን የቀረነው በገዛ እጃችን ነው. . . ለራሳችንም ባይሆን፥ ብንካፈል እኮ ሰፊው ሰራተኛ በአንዳንድ ጥቅም አሳዳጅ

ግለሰቦች እየተወናበደ የተሳሳተ አቅጣጫ እንዳይዝ ለማድረግ ይቻል ነበር። ነገሩ፥ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ ሆነና ነው እንጂ. . .››

‹‹ታዲያ እንካሳ ዶሮ ሳትቀድምህ ለምን ሮጠህ ውይይት ከበብ አትባልም›› አለው ጌታቸው። የውይይት ክበብ ነገር ሲያነሱበት አይወድም።

‹‹ምንድን ናቸው ብለው ነው የሚያጋልጡን?›› ብሎ ሀብቴ ጠየቀ።

‹‹ኢ. ድ. ህ. አድርባይ. . . ቦርቡዋሪ. . . አድሃሪ. . . ወዘተ. ያልተባልነው ነገር የለም. . .››

‹‹እነማን ናቸው እንደዚህ የሚሉት?››

‹‹የመኢሶን አባሎች ነን የሚሉት ናቸዋ!›› አለ ታቦር፥ ‹‹በውይይት ክበቦችና በጋዜጠኞች ማህበር መድረኮች ላይ ዛሬ የሚጨፍሩት እነሱ ሆነዋል። የስማችን ዝርዝር ደግሞ ለማን የተሰጠ መሰላችሁ። ከመሰሪያ ቤታችን ገና ትናንት የአብዮ ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆኖ ለተመረጠው - ግን ነበር ስሙ. . . ደርቤ።››

‹‹ይሄ ደርቤ በፊት ደህና ልጅ ነበር። እሱም አብዶአል›› አለ ጉደታ።

‹‹ፍየል ከመድረስዋ ቅጠል መበጠስዋ! ገና ከመመረጡ?›› አለ ሀብቴ።

‹‹ይህ ደርቤ የሚሉት ሰው በፊት ትሁት፥ ብቸኛና ታታሪ ነበር። . .አሁን እሳት ሆኖአል። ሲናገር ሁሉ እንባ እያነቀው ነው። ካብዮት ጋር ድንገት ፍቅር የወደቀ ይመስላል። ሳያስፈጀን አንድ ነገር ብናደርግ ይሻላል።››

‹‹ምን ማድረግ ይቻላል ብለህ ነው። እኔን የሚያናድደኝ ትናንት ቀና ብለው የማያዩን እንደ ደርቤ ያሉ ሰዎች ዛሬ አድሃሪ. . . ቦርቡዋሪ አድርባይ እያሉ የሚያወርዱብን ስድብ ነው›› አለ ጉደታ፥ ብስጭት ብሎ። ‹‹ማስታወቂያ ሚኒስቴር ያለኛ የሚካሄድ ይመስላቸዋል፥ ጋዜጠኛ እንደ ሳሙና በፋብሪካ ተሰርቶ በየቀኑ ገበያ ይወጣ ይመስል።››

ጌታቸው የኮረኮሩትን ያህል ሳቀና፥ ‹‹ተሳስተዋል! እኛ ምንም አይደለንም፥ ከምኑም የለንም። አድሃሪም ተራማጅም አይደለንም። ጋዜጠኞችም አይደለንም። ምንም ምንም አይደለንም!›› ብሎ ውስኪውን አንስቶ በአንድ

ትንፋሽ ጨለጠና፥ ‹‹ይሄ ደርቤ የሚሉት ሰው እኮ አብዶአል፤ ዳሩ ይህ አብሮት ያላሳበደው የመሰሪያ ቤታችን ሰው ማን አለና›› ብሎ፥ ሌላ ውስኪ አዘዘ። በደርቤ መለወጥ እየተገረመ የአባቱን ሞት ሊበቀል ይሆናል፥ በቂም በቀል የሚያምን ሰው አደገኛ ነው ብሎ አሰበ።

መልካሙ መዳፉን አከከና ሳም ሳም አድርጎ ሌላ ውስኪ ቀዳለት። ለተቀሩትም ደገመ።

ጌታቸው ቀጠሉና፥ ‹‹ውይይት ክበብ መግባት በግድ መሆን የለበትም። እኔ አልንበረከክም። እነዚህን አናጋልጣለን ብለው የተነሱትን አፈ ጮሌዎች አንድ በአንድ ነው የምሰራላቸው፤ አይነጋ መስሎአት በቁዋት አራች ነው!›› አላቸው።

‹‹ለአለቆቻችን ሁሉ ያንተን ልብ ቢሰጣቸው ምን ነበረበት!›› አሰው ጉደታ።

‹‹ልብ የላቸውም!›› አሉና ጌታቸው፥ ‹‹ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለው ሁሉ ለአብዮቱ ሲል አይምሰልህ። ለጥቅሙ ሲል ነው። ዛሬ በአብዮት ስም ተጠቅልሎ የማይቀርብ የመርዝ አይነት የለም። ድዱን ሲመቱት ሹልክ ብሎ መጥቶ እግር ላይ ይወድቃል! አይምሰላችሁ!›› አለ ጌታቸው፥ ልቡን መታ መታ እያደረገ።

ሀብቴ ቀይ ድዱን እያሳየ፥ ‹‹እኔ የለሁበትም። ስልጣን ለሰፊው ህዝብ! አውሎ ንፋስ ሲመጣ ብልሃቱ ማጎንበስ ነው›› አለ።

‹‹አይ አቶ ጌታቸው! አንተ ኮ እልኸኛ ነህ። ድባቅ ሳትመታ አትመለስም!›› አለው ጉደታ።

ጉደታ መቼም ጥሎበት ሰውን መሸንገል ይወዳል። ከተመቸውም ሌላውን መላሪያ ከማድረግ ወደ ሁዋላ አይልም። ጌታቸውም በበኩሉ ሽንገላ አይጠላም። ስለሆነም፥ አሜን፥ አሜን የሚሉትን ሲያስጠጋ፥ አሳቡን የሚቃወሙትን ደግሞ ተከታትሎ ከማጥፋት ወደ ሁዋላ የማይል ቂመኛ ነበር። ሆኖም፥ ለሚያስጠጋቸውም ሰዎች የሚያሳየው ፍቅርና አክብሮት ዘላቂ አልነበረም። እንደ ትኩስ ድንች ነበር ሰዎችን አንስቶ የሚጥላቸው። ታዲያ፥

ጉደታ የያንዳንዱን ሰው ድክመት የማወቅ ተሰጥዎ ነበረውና፥ ጌታቸውን ባገኘው ቁጥር ሳይሸነግለው አያልፍም።

ጌታቸው ሊያስብ ቆየና፥ ‹‹አንተምኮ ሪፖርተሮች ቤታቸው ከመሄዳቸው በፊት እጅ ነስተውኝ ካልወጡ እያልክ ትቆጣ ነበር›› አለው ጉደታን።

‹‹ዛሬ አያበላም›› አለ ሀብቴ።

‹‹እሱ. . . ሆሆሆ. . . በሰላም ጡረታ እንዳይወጣ. . .›› አለ ኢዮብ። ‹‹መምሪያ ሃላፊዎቻችን. . እገሌ አድሃሪ ነው፥ ሰካራም ነው፥ ሰራ አይገባም. ማይ ፋት. . .ዘ ፓት ኮሲንግ ዘ ኬትል ብላክ. . . እያሉ ጡረታ ሲያወጡን ነው ሲሉ ሰማሁ። በስንት በኩል እንጠቃ? እኔ ግን አብዮቱ ለኛም ጭምር የመጣ መስሎኝ ነበር።››

‹‹አብዮቱ የመጣው ለጭቁኖች ነው!›› አለ ሀብቴ።

‹‹እኛ ምንድን ነን?››

‹‹ምንም አይደለንም። መደብ እንኩዋን የለንም። አቅዋምም የለንም›› አለው ሀብቴ።

‹‹ጌታቸው ነገሩ ከነከነውና፥ ‹‹አቅዋም ካልተወሰደ አገር መኖር አይቻልም ያለህ ማን ነው?›› አለ። ‹‹አየሁ፥ የሰፊውን ህዝብ ጥቅም አምኖ መቀበል አንዱ ራሱን የቻለ አቅዋም ነው። ነገር ግን ባንድ አዳር ሁሉም ኮሙኒስት መሆን አይችልም። የኮሙኒስት ፓርቲ ደግሞ በጥራት ነው እንጂ በብዛት አያምንም። እኔ የማዝነው ትናንት እልም ያሉ ነፍጠኛ፥ የዘርና የሃይማኖት ትምክህተኛ የነበሩ አንዳንድ ግለሰቦች ዛሬ ኮሙኒስት ነን እያሉ ሲደነፉ ሳይ ነው። ይህን ሳይ ኢትዮጵያዊነቴ ያስጠላኛል፥ ያመኛል፥ ያቅለሸልሸኛል።››

‹‹አየሁ፥ አቅዋም የዝምድናና የጉዋደኛነት ሀረግ ስቦ እንዲሁ በቀላሉ የሚወሰድ ጉዳይ አይደለም። የማሌ ድርጅት አባል ለመሆን አስቀድሞ ሀቀኛ ኮሙኒስት መሆን ያስፈልጋል። ኮሙኒስት ለመሆን ደግሞ ከቁስ አካላዊ ርእዮተ አለም ውጭ ያለውን እምነት ሁሉ እንደ አሮጌ ቁና አውጥቶ መጣል የመጀመሪያ ተግባር ነው። መፅሀፍ ቅዱን ለይጣንም ሊጠቅስ ይችላል። የማርክስና የሌኒን መፅሀፍ የጠቀሰ ሁሉ ኮሙኒስት አይደለም። ለማንኛውም

ነገር አወናባጅ ሁሉ እርቃኑን ወጥቶ የሚታይበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። እኛ በውሸንብር ውስጥ እንጠፋ ይሆናል። ግን ጊዜው ይደርሳል።ምናለ በሉኝ!››

ከስላሴ አካባቢ የተኩስ ዶፍ ሲወርድ ይሰማ ነበር።

‹‹ተኩሱ እየቀረበ መጣ. . . እንሂድ መሰለኝ›› አለ ኢዮብ።

መሄዱን ወዶ አልነበረም እንሂድ ያለው። ከቤቱ የበለጠ የሚጠላው ነገር አልነበረም። ለምሳና ለእራት የተጎሳቆሉ ህጻናት ፊት ማየት አስጠልቶታል። ለመሄድ የቸኮለው ጉደታና ታቦር በሱ ኪሳራ መጠጥ መደጋገማቸውን በማየቱ ነበር።

‹‹እኔስ እቆያለሁ። ከጥይቱ ይልቅ እኔን የሚያስፈራኝ ያ አፉን ከፍቶ የሚጠብቀኝ ባዶ ቤቴ ነው›› አለ ሀብቴ።

ጌታቸው፥ ‹‹አምን፥ ሞት ቦታ መርጦ አይመጣም። የመለኪያ ወገብ እንደ ጨበጡ፥ ወይም በመንገድ እየሄዱ በድንገት መሞት ይሻላል?›› ከማለቱ፥ እሜቴ - የቡና ቤቱ ባለቤት - ነጠላቸውን ከትከሻቸው ላይ ጣል አድርገው ደብረክ ደብረክ እያሉ ገቡ።

‹‹አዬ ጉድ፥ ከደንበኞቼ ሁሉ እናንተው ብቻ ቀራችሁ?›› አሉ፥ ማን ገንዘብ ከፍሎ ማን በዱቤ ለመጠጣት እንደ መጣ በልባቸው እያሰቡ።

‹‹አይዞሽ፥ ሞት ነው የሚለየን›› አላቸው፥ ጌታቸው።

‹‹ጠላትህ ይሙት!›› አሉትና፥ ወደ ሀብቴ ዘወር ብለው፥ ‹‹ማታ በህልሜ ጥጥ የመሰለ ጮማ እየቆረጥኩ ሳጎርስህ አየሁ ልጄ። ህልሜ መሬት ጠብ አይልም። ሲሳይ ነው።››

እየተንገፈገፈ ‹‹ዋጥኩት ታዲያ?›› አለ። የምግብ ነገር ሲነሳ ያንገፈግፈዋል። ሲበላ ያልበዋል። ምግብ የሚጋብዘውን ሰው እንደጠላቱ ነበር የሚቆጥረው።

‹‹እንክት አድርገህ!›› አሉትና፥ ወደ ታቦር መለስ ብለው፥ ‹‹ዛሬ ፊትህ ፊካ ብሎአል›› አሉት።

ታቦር እንደ ኪሱ ሁኔታ ነበር የአለት ጠባዩ የሚሰዋወጠው። ቀጠሉ። ‹‹ምንነው ሰሞኑን ጠፋህ?›› ብለው ጠየቁት። ምክንያቱን ሳያውቁ ቀርተው አልነበረም። በዱቤ ስለ ጠጣው መጠጥም አልነበረም። ስለሱ ጠያቂውን አያውቁም። የታቦር አለቃ እንዲያማልዱት ጠይቆአቸው ስለነበር፥ ‹‹ምንነው ልጁ፥ እያረፈድክ ስራ ትገባለህ አሉ። ለምን በጊዜ ስራ አትገባም?›› በማለት ምክር ሊሰጡት ከሞከሩ በሁዋላ ነበር ቀርቶ ላይቀር አኩርፎ የጠፋው።

በዚህ ጉዳይ እሜቴን ሊያኮርፍ የመጀመሪያ ጊዜው አልነበረም። እንደ በጋና ክረምት በየጊዜው የሚፈራረቁበት አለቆቹ፥ እሜቴ ቡና ቤት ድረደ እየመጡ፥ በጊዜ ስራ እንዲገባ ምክራቸውን እንዲሰግሱት ይጠይቁ ነበር። ታቦር ሙያተኛ ቢሆንም፥ በጊዜ ስራ መግባት አይሆንለትም ነበር። በዘነዩ ቁጥር አሞኛል፥ አሜባዬ ተነስቶብኛል፥ መኪናዬ ተበላሽቶአል፥ የፊደያባት መኪና አንድ ቀን ጎማዋ፥ ሌላ ቀን የጭስ መውጫዋ ይበላሻል እያለ ምክንያት ይደረድር ነበር። ታዲያ በዚህ የተነሳ ታቦር ሲዘገይ ስራ ጉዋደኞቹ ዛሬ ምን ምክንያት ይፈጥር ይሆን? የመኪና ጎማ? አሜባ? የጭስ መውጫ? የቤት ቡዋምቡዋ መፈንዳት? እያሉ በመወራረድ መዘባበቻ አድርገውታል።

ታቦር መልስ ስላልሰጣቸው፥ እሜቴ ወደ ሀብቴ ዘወር ብለው ‹‹እንዳልኩህ ጮማ የሲሳይ ምልክት ነው። ሎተሪ ሊደርስህ ነው መሰለኝ›› አሉት።

‹‹እውነትም!›› አለና፥ ረስቶት የነበረውን ሙሉ የሎተሪ ቲኬት ከኪሱ ፈልጎ አወጣ።

‹‹. . .እኔም ሙሉ የሎተሪ ቲኬት አለኝ። በተወለድኩበት ቀን ያልታሰበ ሰጦታ ላገኝ ነው መሰለኝ›› አለ፥ በፈረስ ፊቱ ላይ ድንገተኛ ደስታ ፈንጥቆ።

እኔም አንድ ጉዋደኛዬ ከዚች ቦርሳ ውስጥ አድርጎ ሰጠኝ ሙሉ ቲኬት አለኝ›› ብሎ፥ ታቦርም የራሱን የሎተሪ ቲኬት አወጣ።

‹‹ይግረማችሁና፥ አንድ የተቸገረ ጋዜጠኛ በሶስት ብር የሸጠልኝ ሙሉ ቲኬት እኔም አለኝ›› አለ ጉደታ ፈይሳ።

እሜቴ የሁሉንም ቲኬት ተመለከቱና፥ ‹‹እኔ ህልም ያየሁት ለሀብቴ ነው። ያገኘ እንደሆን እንድረዋለን›› አሉ።

የእህል ስም ሲያነሱበት ላብ ላብ እንደሚለው ሁሉ፥ የሚስት ነገርም ሲያነሱበት አይወድም። ሴቶችን የሚፈራው ከሩቅ ነበር። ሴቶች ሲጠጉት የሚያደርገውና የሚናገረው ነገር ስለሚጠፋው ይርበተበታል። ሆኖም በደረሰበት ሁሉ ሚስት ፈልጉልኝ እያለ የወጣትነት እድሜውን ወደ መጨረሱ ገደማ ነበር።

ጉደታ፥ ‹‹እሱኮ ያ ነገር አይሰራለትም›› አለና፥ ከት ብሎ ሳቀ።

እሜቴ፥ ‹‹እኔ ለሀብቴ ነው ህልም ያየሁት›› ሲሉ ሰምቶ ፊቱ ልውጥ አለ። የልጃገረድ ሳዱላ የመሰለችውን ከሁዋላ ያለችውን መላጣውን አከክ እያደረገ፥ ‹‹የእኔ እድል ሁልጊዜ ለምን ለሀብቴ ይሆናል?›› አለ በአሳቡ. .

. . . ከጥቂት ዓመታት በፊት እርሱ ተፃፅፎ ባገኘው የነፃ ትምህርት እድል እንዲጠቀም የተደረገው ሀብቴ ይርጉ ነበር። መቼም ሰባለስልጣኖች ማነብነብና ማጎንበስ አይሆንለትምና ታቦር እንባውን አፍስሶ ዝም አለ። እንባው በከንቱ ፈሰሶ አልቀረም። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ሌላ ነፃ ትምህርት እድል አግኝቶ ወደ አሜሪካ ሄደ። ሁለቱም የጋዜጠኛነት ትምህርታቸውን ፈፅመው ሲመለሱ ለአንድ ጋዜጣ አዘጋጅነት የተመረጠው ሀብቴ ስለነበረ ለጥቂት ወራት አለቃና ጭፍራ ሆነው ሰሩ። ያኔ ነበር ታቦር ወሽመጡ የተቆረጠው። ያኔ ነበር በጊዜ ከስራ ገበታው ላይ መገኘቱን ትቶ በግድ የለሽነት መተኛት ያመጣው። ያኔ ነበር ከወደ ውሃው ጨመር እያደረገ መውላድ የጀመረው። የደረሰበትን የብስጭት ስሜት የተረዳለት ግን አልነበረም። ሃላፊነትን መሸከም አይችልም፥ ጠጪ ነው፥ የበላዮቹን ትእዛዝ ሆነ ምክር አይቀበልም፥ በሚል ሰበብ ይባስ ብሎ እድገት እየታለፈው ሄደ፥ እርሱም በሃይል እየተበሳጨ፦

‹‹እና፥ ህልምሽ ቅዠት ነው›› አላቸው፥ እሜቴን።

እሜቴ፥ ‹‹የኔ ህልም ከመሬት ጠብ አይልም›› እንዳሉ፥ ሁለት ሰዎች ተከታትለው ገቡ። ሁለቱም ሞቅ ብሎአቸዋል። ለቤቱ እንግዳ አልነበሩም። የእሜቴ ቡና ቤት ደንበኞች ነበሩ።

ሪሀ እግራቸውን እያሳበጠ በከዘራ ተደግፈው የሚሄዱት ባሻ ትርፌ፣ የአሜቱን ቡና ቤት ካቀኑ ሰዎች አንዱ ከመሆናቸውም በላይ፣ ከተማ ከቃጥ ትርፍ ቤት ከመታወጁ በፊትም የአራት ኪሎ ሱካንዳ ቤቶች ባለቤትና የመረዳ ዳኛ ነበሩ። ሽክ ብለው ይታዩበት የነበረው ጥቁር ሱፍ ካውያ በዘቱበት ከማብለጭለጩ ሌላ ሳስቶ ክሩ መመዘዝ ጀምሮአል። ድሮ ጋቡን ከውስጣው ለማውጣት ያህል በረጅም ማንኪያ እያማሰሱ የሚጠጡት ውስኪ ቀርቶ ‹‹የአንበሳ ወተት›› እያሉ የሚያቆላምጡትን ቀንዶ መጠጣት ከያመሩ ቆይተዋል። እሱንም አጥተው በሽታው ብቻ ለመርካት ሲሉ በየቡና ቤቱ እየዞሩ ቁጭ ብለው የሚውሉበት ቀን ብዙ እየሆነ ሄዶአል። ታዲያ እየተከዙ ‹‹አህህ!›› ከማለት በስተቀር አይናገሩም።

የሞጨሞጨው አይናቸው ያለፈውን ህይወት እንጂ ያለውን እውነታ የሚመለከት አይመስልም። በአይነ ህሊናቸው የሚታያቸው በሱካንዳ ቤት ኪራይ ሂሳብ እያስወረዱ በሰላ ቢላዋ ላጥ ዋጥ የሚያደርጉት ሽንጥ - ታናሽ - ጎድን ተዳቢት - ሰብራዳ - ምላስና ሰምበር ነበር። ጮማው በአይናቸው ሲዞር፣ ምራቃቸው ጠብ ሊል ይደርሳል። ውል ሲላቸው በተወረሱት ሱካንዳ ቤቶች ደጃፍ ከዘራቸውን ይዘው እያንከሱ ይንጎራደዳሉ። ጥሩ ስጋ ሲያዩ ገብተው ዋጋውን ይጠይቃሉ። ሰሰቤቱም ሁኔታ ሳይጠይቁ አይወጡም። ተበላሽቶም ከሆነ ቁጣ ይከጅላቸዋል። ተስፋቸው ጨርሶ ስላልሞተ የተወረሱባቸውን የሱካንዳ ቤቶች ሳያዩ ውሰው አያድሩም።

‹‹ባሻ ትርፌ፣ ይጫወቱ እንጂ›› አሉዋቸው እሜቴ።

‹‹ጨዋታ ድሮ ቀረ! አህህ ብቻ ሆኖአል የኔ ጨዋታ፣ ጥሬ እንዳማረው መጋጃ! አህህን ለፈረሴ ያስተማርኩ እኔ ነኝ፤ እሱን ጥሬ እያማረው እኔን ሆድ ሲብሰኝ።››

ከባሻ ትርፌ ጋር የመጣው እንጂኔር ረታ ሙላት፣ አጫዋችም የሚያስፈልገው ሰው አይመስልም። ብቻውን ያወራል፣ እጁን እያወናጨፈ። ሲጃራ ከከንፈሩ መሃል አይለይም። አንዱ ሳያልቅ ሌላ ይቀጣጥላል። ከኪሱ እርሳስና ወረቀት አውጥቶ፣ ቁጥር ይደምራል፣ ይቀንሳል። የመንገድ ስራ ተቋዋራጭ ስለነበረ፣ ሁልጊዜ የሚያስጨንቀው ከወዛደሮች ጋር ያለው

አለመግባባትና በግል በሚያካሂደው ድርጅት ላይ በየጊዜው እየደረሰ የሚሄደው ኪሳራ ነበር። ደምሮ፥ ቀንሶ፥ ብቻውን ከራሱ ጋር አውርቶ ሲያበቃ ቀጥሎ የሚናገረውን ጋዜጠኞቹ አስቀድመው ስለሚያውቁት ተያይተው ይጠብቁት ነበር።

‹‹አዩ የኛ ጋዜጠኞች›› አሰ። ‹‹ድንቄም ጋዜጠኛ! ትርኪ ምርኪውን ከምታወሩ ስለ ሰራ ዲሲፕሊን ለምን አታስተምሩም? ሰውን ሰው ያደረገው ስራ ነው ሲባል አልሰማችሁም? ዳሩ የት ታውቁትና!››

‹‹እንጂኔር፥ ምን ጎደለ ነው የምትለው!›› አለው ጉደታ።

‹‹ምን አሙዋልታችሁ ሰርታችሁ ታውቃላችሁና? ወዛደሩ ንቃት እያለ ስራ ሲፈታ - ዝም! በስድስት ወር ውስጥ መጠናቀቅ ያለበት ስራ ሁለት አመት ሲፈጅ - ዝም! ስራው በተፈለገው ጊዜ ሳይጠናቀቅ ቀርቶ ተቁዋራጭ አሻጥር ፈፀመ ተብሎ ሲወነጀል– ዝም! የናንተ ድንፋታ የመለኪያ አንገት ስትጨብጡ ብቻ ነው!

‹‹እኔስ ግድ የለኝም። ስራዬን ዘግቼ አርፈዋለሁ። እርፍ! በቃ! ምን አዳረቀኝ! ከሙበት ሌላ ግዴታ ምን መሆኑን ከማያውቅ ሰራተኛ ጋር ለምን አዳረቃለሁ? ቆሽቴ ለምን ይድበን? ታዲያ እናንተ ጋዜጠኞች ናችሁ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎች. . .

‹‹እህህ!›› አሉ፥ ባሻ ትርፌ።

በቦታው የሉም - ባሻ ትርፌ። በህልም አለም ውስጥ የሚንሳፈፉ ይመስላሉ። ያሉበት ሁኔታ መጥፎ ቀልድ ነበር መስሉ የሚታያቸው። ለአሳቸው ሁኔታው ሁሉ ደብዛው የጠፋ አሉባልታ ሆኖ ነበር የሚታያቸው። በቦታው የሉም. .

እንጂኔር ረታ ቀጠለ፦

‹‹ወዛደሩ መብትና ግዴታን ለይቶ እንዲያውቅ አታስተምሩም። መብት! መብት! መብት ብቻ። መብት ያለ ግዴታ ትርጉም የለውም። እናንተ ጋዜጠኞች ናችሁ አገር ያጠፋችሁት። ድራሻችሁ ይጥፋና! ዳሩ ከናንተ ምን

ይጠበቃል! ሙያችሁ የሚጠይቀው ምግባር ምን እንደሆነ በአጃችሁ ያለው መሳሪያ ምን ሃይል እንዳለው የማታውቁ የአብድ ገላጋዮች ናችሁ. . .

‹‹እህህ!›› አሉ ባሻ ትርፌ።

እንጂነር ረታ ቀጠሉ፦

‹‹እኔስ ግድ የለኝም። ስራዬን ዘግቼ አርፌዋለሁ። ቆሽቴ እንደ ደበነ አይቀርም። እኩልነት ሲባል ሁሉንም ዜሮ ማድረግ ነው እንዴ? አይደለም! እኩልነት መልክ መልክ አለው። ‹‹የተካበተ ስራ›› የሚለውን የማርክስን ቲዎሪ ታውቃላችሁ? አይመስለኝም። አያችሁ ትምህርት፣ ልዩ ሙያ፣ የተካበተ ስራ ስለ ሆነ ትምህርትና ልዩ ሙያ ያላቸው ሰዎች የተሻለ ደመወዝ ይከፈላሉ። የሶሻሊዝም አላማ በእኩልነት ስም ሁሉንም ዜሮ ማድረግ ሳይሆን ከእያንዳንዱ እንደ ችታው ለእያንዳንዱ እንደ ስራው በሚል መርህ መሠረት፣ የህዝቡን ኑሮ ከፍ ማድረግ ነው። አይ የኛ ጋዜጠኖች! ይህን ይህን ብታስተምሩ ታውቁትና!. . .

‹‹እህህ›› አሉ፣ ባሻ ትርፌ።

ጌታቸው አቀማመጡን ለወጠ። ጋዜጠኞቹ ተጠቃቀሱ።

‹‹ዲስኩሩን አቁመህ ውስኪ ብትጋብዘን ጥሩ ነበር›› አለ፣ ጉደታ።

እንጂነር ረታ ቀጠሉ፦

‹‹ለምን አፊር አትጠጡም። የምትዕፉት ጋዜጣ አረቄ አረቄ ነው የሚሸተው። ‹‹ውሸጉብር›› የሚሉት ቃል ጥሩ ቃል ነው። እናንተ የውሸጉብር ኤክስፐርቶች ናችሁ። ለማንኛውም ነገር፣ ይቅርታ አድርጉልኝ። መናገር አልነበረብኝም። መናገር ምን ያደርጋል? ስራዬን ዘግቼ እርፍ! ቢቀ! ብሎ ለስራ አስኪያጁች። ሃላፊነትን አሸክሞ ዲሲፕሊን ማስከበር ለማይችለው ስራ አስኪያጅ ይብላኝልን! መጥኔውን ይስጣቸው›› አለና፣ መጠጡን አንስቶ ጨለጠ።››

‹‹በጊዜያችን፥ ትግል የህይወታችን ዋነኛው ጉዳይ ነው። መለማመድ ያለብን አይመስልህም? አለም አንድ ቦታ የቆመች አይደለችም። ለውጥ የተፈጥሮ ህግ ነው። ችግሩ የኛ አሳብ አለመለወጥ ነው›› አለው፥ ጌታቸው።

‹‹ተወው እባክህ! በኛ ላይ የማይበረታ የለም!›› አለ ታቦር።

‹‹የወዛደሩ ትርፍ ንቃት ነው። አንተ የምታስበው ብርሀን ብቻ ነው። ወዛደሩ ያሸንፋል!›› አለ ሀብቴ።

‹‹አይ ጉድ! ከስራ ስዘጋ ንቃት የት እንደሚያደርስ እናያለና!›› ከማለቱ፥ ተክዘው ‹‹እህህ›› ሲሉ የቆዩት ባሻ ትርፌ ከተቀመጡበት በድንገት ብድግ ብለው፥ የተለመደውን ሙሾአቸውን ማውረድ ጀመሩ።

‹‹ዋይ - ዋይ - ባላባት ዋይ - ዋይ! . . . ተቀበሉኝ እንጂ!›› ብለው፥ እሜቴን ነጠላ ነጥቀው ካሸረጡ በሁዋላ ‹‹በሞቴ ተቀበሉኝ!›› ብለው ‹‹ዋይ - ይ ባላባት ዋይ -›› ደረታቸውን መደለቅ ጀመሩ።

‹‹ከእንግዲህ ቀረ ሳይሰሩ መብላት!››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹የኪራይ ቤት።››

‹‹ዋይ - ወይ!››

‹‹ይህች አለም።››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹አዱኛ።››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹ወላዋይ።››

‹‹ዋይ - ዋይ!››

‹‹ዋዬ! ዋዬ! ዋዬ! ዋዬ!›› ብለው ሙሾውን በማቆም፥ ‹‹እህህ›› ካሉ ሳ፥ ስቅስቅ ብለው ማልቀስ ጀመሩ - እንደ ልማዳቸው።

የሎተሪውን ወሬ ለመስማት መልካሙ ቸኩሎ ራዲዮ ከፍቶ ነበረና የምሽቱ ዜና መተላለፍ ጀመረ። ሁሉም ጆሮአቸውን ከራዲዮው ላይ ተክለው ያዳምጡ ጀመር። መግለጫ ወይም አዋጅ፥ የተያዘ፥ የሞተ፥ የቆሰለ. . . የሚማርክ ምንም ወሬ አልነበረም።

የራዲዮ አንባቢ በመጨረሻ ‹‹የሎተሪ እጣ›› ሲል ሁሉም በይበልጥ ጆሮአቸውን አነቁ። እጣ ያላቸውን ቲኬቶች ቁጥሮች ሁለት ሁለት ጊዜ እየደጋገመ አነበበ። በመጀመሪያ ቲኬቱን ቀዶ ከወለሉ ላይ የጣለው ጌታቸው ነበር። ሌሎችም እርሱን ተከትለው አንድ በአንድ እየቀደዱ ጣሉ።

‹‹ማስተዛዘኛ እንኩዋን የለም?››

‹‹ማስተዛዘኛው ቆርጦ አቅዋም መውሰድ ነው›› አለ ሀብቱ፥ ወደ ላይ አንጋጦ ቀይ ድዱን እያሳየ።

ሁሉም ቀዳደው የጣሉትን የሎተሪ ወረቀት በበር የሚገባው ሃይለኛ ነፋስ ከወለሉ ላይ እያተራመሰ ይበትን ነበር። ሁሉም በዝምታ ተውጠው፥ እያንዳንዳቸው በአሳብ እየተጉዋዙ፥ የተቀዳደዱትን የሎተሪ ቲኬቶች በአይናቸው ሲከተሉ እንደ ቆዩ፥ መልካሙም የሎተሪ ቲኬቱን ቀዶ ጣለ። ነፋሱ ይዞት ሄደ።

ባሻ ትርፌ፥ ‹‹ሞኞች! <u>የጨዋ ልጅ እድል ካከተመ ቆይቶአል!</u>›› አሉ እየተነፋነፉ።

ጌታቸው ወደ መልካሙ ዞሮ፥ ‹‹ገብርኤልና ሰላሴዎች ከኛ የተሻለ ጉቦ የሰጣቸው አገኙ መሰለኝ! በጨረታው አልተገደዱም›› አለና፥ የውስኪ ብርጭቆውን አንስቶ፥ ‹‹ለወደፊቱ ህይወታችን! ወይስ የወደፊት ህይወት የሚባል ነገር የለም? ብሎ ቆመ።

‹‹የነገው ህይወታችን በደርቤ እጅ ነው!›› አለ ታቦር።

ጌታቸው፥ ‹‹እንግዲያውስ ለደርቤ ጤንነት!›› አለና፥ ውስኪውን ጨለጠ - እስከ መጨረሻዋ ጠብታ. . .

ምእራፍ ፲፫

"ለወይዘሮ አምሳለ ምሳለና ለአቶ ጉልላት ቀኑ ቀውጢ ሆኖባቸው ነበር። ስለ ቀበሩት መሳሪያና ስለ ደርቤ ማሰብ አቁመዋል። መነታረክና መወነጃጀልም ትተዋል። ስለ ራሳቸው ህልውናም ሆነ ስለ ችግራቸው ረስተዋል። ሁሉቱም የተጨነቁበት ጉዳይ በሂሩት መጥፋት ነበር።

ሂሩትን ፍለጋ ስልክ ያልደወሉበት የዘመድ ቤት አልነበረም። ከሂሩት የቅርብና የሩቅ ጉደኞችም መሃከል ስልክ ያልተደወለለት አልነበረም። ተያይዘው ያልደረሱበትም ሰፈር አልነበረም። ሬሳ ወድቆበታል የተባለ ሰፈር አንድም አልቀራቸውም። ከተማውን ከዳር እስከ ዳር አዳርሰውታል።

በደጀ ሰላሙ ላለፉት ታቦት ሁሉ - ገብርኤል - በአታ - ሰላሴ - ቅድስት ማርያም - መድሀኔ አለም - የካ ሚካኤል - ጨርቆስ - እስጢፋኖስ - ልደታ - ተክለሃይማኖት - ራጉኤል - ቅዱስ ዮሐንስ - ቅዱስ ጊዮርጊስ ‹‹ሂሩትን ከዚህ መለት የለወርክልኝ እንደሆን፥ ምንም ሳይነካት ያስገኘህልኝ እንደሆን›› በማለት ለንጋ - ሙክት - ጃንጥላ - ገንዘብ - ወርቅ - የጀሮአቸውን ጉትቻ - የጣታቸውን ቀለበት - የአንገታቸውን ወርቅ - አጣን - ከርቤ - መጋረጃ - ግምጃ - ጡዋፍ - ያልተሳሉት ነገር አልነበረም።

ወይዘሮ አምሳለ በየደረሱበት የወደቀ ሬሳ ገና ከሩቅ ባዩ ቁጥር፥ ‹‹እኔ አላይም! አይኔ አያይም! የኔ ፅጌ ረዳ ናት የተቀጠፈችው! አመለ ቅብጥብጥዋ! ቁንጮንጥዋ እመቤት!›› እያሉ፥ ደረት ጥሰው በመጮህ አገር ሲያስቸግሩ ነበር የዋሉት።

አቶ ጉልላትና ወይዘሮ አምሳለ በአንቱ ሲማስኑ ውለውና በከባድ ሃዘን ተውጠው ሲመለሱ፥ ጎረቤታቸው ይቀልጥ የነበረው የስርግ ዘፈን፥ ይደሰቅ የነበረው ከበሮ፥ ያስተጋባ የነበረው እልልታ፥ አንዱ ሲሰቅ ሌላው ያሰቅላል አንዲሉ፥ የህይወት ሁለት ገፅታ ሳይከሰትላቸው አልቀረም። የሰርጉ ዘፈን ምሬታቸውን በማባባሱ ሁለቱም በዝምታ ስቅስቅ ብለው ያለቅሱ ስለነበረ፥ ከቤታቸው ደጃፍ የተደረደረውን የመኪና ብዛት አላጤኑትም። ሁለቱም፥ የድሃ ስርግ መሆኑን ዘንግተው፥ መኪናዎቹ ሰርጉ ቤት የተጠሩ እንግዶች ሳይሆኑ አይቀሩም በማለት በግማሽ ልብ አስበው ነበር።

ከቤት ሲገቡ የሂሩትን መጥፋት የሰማ ዘመድ አገሣግድ ቤቱን ሞልቶ ጠበቃቸው። ከዚያማ ምኑ ቅጡ! ወይዘሮ አምላለ ለገላጋይ አስቸገረው ነበር። ሂሩት በምትቀመጥበት ወንበር ላይ፥ በምታልፍበት ኮሪደር ላይ፥ ፊትዋን በምታይበት መስተዋት ላይ እየተደፋ፥ ‹‹ቅብጥብጥዋን አመቤት አምጡልኝ፡ ፅጌ ረዳዬን! ወላጅ ይፍረደኝ!›› በማለት ሲጮሁ ሴቶቹም አሳቸውን ተከትለው ዋይታ ሲያቀልጡና ደረት ሲደልቁ፥ የጎረቤት ሰርግ ዘፈን፥ ከበሮና እልልታ ከልቅሶውና ከዋይታው ጋር እየተማታና የአድማጭን ጆሮ እየተሸማ ግራ ያጋባ ነበር። በዚህ ሁኔታ ብዙ ጊዜ ካለፈ በሁዋላ አንዳንድ ወንዶች፥ ‹‹እ በፊጠራችሁ! ልጅትዋ ምንም ሳትሆን አታሙዋርቱባት! እግዜር በስንቱ ማላዘን ይሆናል። የሰይጣንም ጆሮ አይስማው! ይልቅ የሚያሳዝነው የዘመኑ ልጆች ወላጆቻችን ይሰጋሉ፥ ይጨነቃ ብለው ባለማሰብ፥ በዋል ፈሰስ መሆናቸው ነው። በየቤቱ ስንት ጉድ አለ! አላህ ከሰው ሲጣላ አርፈዱሚ አይቆርጥም ይባላል። እናንተን ለመቅጣት የቆረጠልን አርፈዱሚ የገዛ ልጆቻችን ናቸው›› በማለት፥ እንደ ምንም አፅናንተው ዝም አሰኙአቸውና፥ እንግዶቹን እህልና ውሃ በማለት ሽር ጉድ፥ ጎንበስ ቀና፥ በየጉዋዳው ደፋ ደፋ ማለት ተጀመረ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ተሰማ ከመኝታ ቤት ውስጥ ተዘግቶ ከራሱ ጋር ይሙዋገት ነበር። ሂሩት የት እንደነበረች ያውቃል። ግን በአርሱዋ ጥልጥ ብሎ መጥፋት ምክንያት ቤቱ ውስጥ ሰሰ ደረሰው ጭንቀት ስልክ ደውሎ ሊነግራት ቢያስብም፥ ለመደወል ፈራ። ሂሩት ወደ ነበረችበት የኢ.ህ.አ.ፓ. ሀዋስ ስልክ ከደውሉ፥ በጥዋት ተነስቶ የጠፋበትን ምክንያት ማስረዳት ስለሚኖርበት፥ ራሱን አጋልጦ እህቱንም ከአደጋ ላይ ለመጣል አልፈለገም።

ለወላጆቹም ሂሩት ያለችበትን ስፍራ ገልፆ ለመናገር አልፈለገም። የኢ.ህ.አ.ፓ. ሀዋስ የት እንደሆን መጠቆም አደገኛ መሆኑን በመገንዘብ፥ አሳቡን ከአእምሮው ውስጥ አወጣ። በአሳብ ባህር ውስጥ ብቅ ጥልቅ እያለ በሚዋኝበት ጊዜ ሁሉ፥ ያለ ምንም ውጤት እያከተመች የምትሮጠዋ ደቂቃ አደጋውን እያቀረበች መሄድዋ እየተሰማው፥ ጎፈሬውን ከመንጨት፥ ጢሙን ከመጎንተል ሌላ የሚያደርገው ነገር አልነበረም። የእህቱና የራሱ ህይወት

ለአደጋ ተጋልጦ ሳለ የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት ዝም ብሎ በአሳብ መጨነቁ ነበር በደብልዮ ያስጨነቀው።

‹‹ከአደጋ ጋር ድብብቆሽ መጫወት!›› የሂሩት አባባል ትዝ ባለው ቁጥር ‹‹ጅል!›› እያለ ይሳደባል። ውስጥ ውስጡን እንደ መጋዝ ይዞ የሚገዘግዘው ግን ሌላ ነገር ነበር። ‹‹በቃ ፈሪ ነኝ!›› ብሎ ራሱን ለመታዘብ ይቃጣውና፥ ‹‹የለም ራሴንና እህቴን ከዚህ አደጋ ለማውጣት መሞከር ፈሪ አያሰኘኝም!›› ቢልም፥ ራሱን በራሱ ለማሳመን እያቃተው ከራሱ ጋር ይጣላል።

በአሳብ ሲጨነቅ ከዋለ በሁዋላ፥ የእናቱና የቤተዘመዱ ዋይታ ህሊናውን ስላስጨነቀው፥ አንድ ነገር ለማድረግ ቆረጠ። ድንገተኛ አሳብ መጣለት።ደርቤ መጥቶ ከፊቱ ተደቀነ።

ደርቤ ከነጋ እፎይ ብሎ የሚተነፍስበት የአንድ ደቂቃ ጊዜ እንኩዋን አላገኘም። በቀበሌው ቁጥጥር ስር የዋሉን ግለሰቦች ማህደር አንድ በአንድ መርምሮ ውሳኔ መስጠት፥ ጥቆማ የተደረገባቸውን ግለሰቦች ተከታትሎ ሁኔታቸውን በተጨባጭ ማጣራት፥ የቀበሌው ጥበቃ የሚጠናከርበትን መንገድ ባስቸኩዋይ መሻት፥ እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ስራዎች ከፊቱ ተደቅነው፥ መስራት ያለበት ስራ ብዙ፥ የተሰራው ጥቂት እንዲሉ፥ የሚይዘውና የሚጨብጠው ነገር ጠፍቶት ይንደፋደፍ ነበር። በዚያ ላይ፥ እግር በእግር የሚተኩ ስብሰባዎች መሳተፍ፥ የማያቁዋርጡ አቤቱታዎችን መስማትና በየደቂቃው የሚመጡትን የስልክ ጥሪዎች መቀበል ነበረበት። ስለሆነም፥ ከስራ ብዛት የተነሳ ስለ ደረሰበት የህሊና ጭንቀት ለማስታወስ ጊዜ አላገኘም። ሆኖም ከአእምሮው በስተጀርባ አንድ ነገር ሳያቁዋርጥ እንደሚጎተጉተው ይሰማው ነበር።

በተለይም ከጥዋት ጀምሮ እስከ ስምንት ሰአት ድረስ ያለውን እንደ አይኑ ብሌን የሚሳሳለትን ጊዜ ያሳለፈው በላዲሶ ቀብር ዝግጅትና በቀብሩ ስነ ስርአት ላይ ስለነበረ፥ ፋታ አላገኘም። ከቀብር ሲመለስ ከድካሙ ብዛት ሰውነቱ ዝሎ ነበር።

እንደ ደርቤ እንቅልፍ አጥቶ፥ ስራ በዝቶበት የተዳከመ አንድ የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ፥ ‹‹እስከ መቼ ድረስ ነው በዚህ ሁኔታ የምንቀጥለው?›› አለው፥ ተበሳጭቶ።

ከድካሙ ብዛት ከለውነት ወጥቷል። ላለፉት ሃያ አራት ሰአቶች ከአግሩ ያልተለዩት ሹራቦች መሸተት ጀምረዋል።

‹‹አብዮት የራስዋን ልጆች ትበላለች፥ ሲሉ አልሰማህም?›› አለው።

‹‹ማን ሊቀራት?››

ደርቤ ፈገግ ብሎ፥ ‹‹ለማቆጥቆጥና ለማበብ አብዮት የልጆችዋን ደም ትጠጣለች. . .››

‹‹ከዚህ የበለጠ ምን እናድርግ ታዲያ?››

‹‹እኛ የምንሞተው ጫማችንን እንደተጫማን ነው. . .››

‹‹የኔ እንዲያውም መሸተት ጀምሮአል።››

ደርቤ፥ ‹‹አንተም ባትለው፥ ራሱ እየተናገረ ነው›› አለውና፥ በቁምነገር፥ ‹‹የለም ጉዋድ የኔና ያንተ፥ በአጠቃላይም የኛ ትውልድ እጣ መሰዋእትነት ነው። ሌላ ተልእኮ ያለን አይመስለኝም። እንዳልኩህ መጫሚያችንን ሳናወልቅ ነው የምንሞተው። ተዝናንተው ከአብዮቱ ፍሬ በእኩልነት የሚቋደሱት ምናልባት የኛ ልጆች ወይ የልጅ ልጆቻችን ይሆናል። ታዲያ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ፥ እኔን የሚገርመኝ፥ የስልጣን ሽሚያ ገበያ እንዲህ መድራቱና የስግብግብነት ባህርይ መስፋፋቱ ነው። አየህ፥ ፊውዳላዊ ስርአትን ገርስሰው ሳያበቁ፥ እንዳለ ሊቀጥል ዝም ብሎ ማየት፥ የተገረሰሰው ስርአት እንደ ገና እንዲያቆጠቁጥ ማገዝ፥ ወይም መጋበዝ ይሆናል። እባክህ ተወኝ ጃል! ያሁኑን ከሽ ከሽ ከትግል አትቁጠረው! ከወሳኙ የትግል ደረጃ ላይ የምንደርሰው የርዮተ አለም ትንቅነቅ ስንጀምር ነው። እምነት፥ የአመለካከትና የአኗኗር ጉዳይ ነውና። ገና ለገና ጥቅሜ ተነካ ብሎ ያኮረፈውን መታገል ትግል አይምሰልህ። ቀላል ነው። ህፃን ልጅ ሲያጥቡት ያለቅስ የለ? እንደዚያ ነው ያሁኑ ትግል። የርእዮተ አለም ትግል ግን ፥ ዋዛ አይደለም። ታዲያ፥ ሁልጊዜ እንደምለው ትግሉ ከራስ መጀመር አለበት። ፅኑ እምነት የሌለው ሰው

ሌላውን ሊያሳምን አይችልም›› ካለ በሁዋላ፥ ‹‹ክነጋ እህል አልቀመስኩም! በጣም ርቦኛል›› አለው።

‹‹ወንድሜን!›› አለና፥ እፍኝ የሽንብራ ቆሎ ከኪሱ አውጥቶ ሰጠው።

‹‹ዘዴኛ ነህ ጃል! ስንቅህን ይዘህ ትዞራለህ!›› ብሎት፥ ቆሎውን እየቆረጠመ፥ ‹‹ሲርበኝ የህፃንነት ዘመኔ ትዝ ይለኝና ሆዴን ባር ባር ይለዋል። እናቴም ትዝ ትለኛለች። አንጀት ጠብ የሚል እህል እያማራት ነው ጥላኝ የሞተችው። ጠኔ በያዘኝ ቁጥር የምታደርገው ነገር ሲጠፋት፥ እቅፍ አድርጋ እንቅልፍ እስኪወስደኝ ድረስ ታባብለኝ ነበር። እንባ የሚያቀሩት አይኖችዋ ትዝ ይሉኛል። አንዳንዴ ጠኔው ብሶብኝ ሳስቸግራት እያለቀሰች ትመታኝ ነበር። እኔ ደግሞ ማልቀሴን አላቆምም። ታዲያ እብድ ሆና ከቤት ብር ብላ ትወጣለች። እኔ ደሞ ደጅ ቁጭ ብዬ እጠብቃታለሁ። በህይወት የማልቆያት ስለሚመስላት ነው መሰለኝ እየሮጠች ስትመጣ እኔም እየሮጥኩ ወደሰዋ እሄዳለሁ። አንድ ነገር ሳትይዝልኝ አትመለስም ነበር። ያንን እየተስገበገብኩ ስበላ እንባ ባቀረሩ አይኖችዋ ትክ ብላ ታየኛለች። ህይወታችን ይሄው ነበር - በየእለቱ›› አለና፥ በረጂሙ ተንፍሶ ሲያበቃ፥ ‹‹እንዲያ እንዲያ ስንል አንድ ቀን ተስቦ ያዛት። ከተጋደመችበት ዳግመኛ አልተነሳችም። ልቅሶዬ እንኩዋን ሊቀሰቅሳት አልቻለም. . .ኦህ! ይህን ሁሉ ለምን እንደማወራህ አልገባኝም። ረሀብ የሚሉት ቃል ስሜቴን ስለሚቀሰቅስብኝ ነው መሰለኝ። ግሩም ቆሎ ነው›› አለውና የቀረውን ቃመው።

እፍኝ ቆሎ ጨመረለትና፥ ‹‹እኔም እንዳንተ በስቃይ ነው እዚህ የደረስኩ። የት ወደቅ ብሎ የሚጠይቀኝ ማንም አልነበረም። ያሳለፍኩትን ስቃይ ሳስታውስ ሰው ሁሉ ያስጠላኛል›› አለው።

ደርቤ በለውዬው አባባል ተነክቶ ሲያስብ ቆየና፥ ‹‹እንዲህ አይነቱ አመለካከት ጥሩ አይደለም። ጥላቻ አላማ መሆን የለበትም። የኛ አላማ ፍቅር ነው - የሰው ልጅ ፍቅር። ጠላቶቻችን የወደቀው ስርአትና የዚያ ስርአት ቁንጮዎችና ደጋፊዎች ናቸው እንጂ ሰው ሁሉ አይደለም። አንድ ሀቀኛ አብዮተኛ ጥላቻንና ቂም በቀልን ምን ጊዜም ቢሆን አላማው ማድረግ

የለበትም ብዬ አምናለሁ። ኮሙኒስት በደፈናው የሰውን ልጅ እጠላለሁ አይልም›› አሉ፥ የእምአእላፍን አባባል እያስታወሰ።

‹‹እርግጥ ከመደብ አንፃር ጠላቱንና ወዳጁን ለይቶ ማወቅ ይኖርበታል። ይህ ደሞ ከፍተኛ ንቃተ ህሊናን የሚጠይቅ ነው። በፊውዳላዊ አስተሳሰብ የተበከለ ህሊና ይዞ እንዴት ልበልሀ በይሉኝታ፥ በውለታ፥ በግል ጥቅምና ፍላጎት፥ በዝምድና፥ በጉዋደኝነት፥ በግብረ ስጋ፥ በጉቦ በሹመት - ጀረ ስንቱ - በስልጣን ጉጉት፥ በአፈ ጮሌነት፥ በሰብቅ፥ የግል ጥቅምንና ፍላጎትን በምርጥ አብዮታዊ ቃላት ሸፋፍኖ በማወናበድ፥ ሀቀኛ የመደብ ትግል አካሄዳለሁ ማለት ዘበት ነው። ቅድም ወሳኙ ትግል ገና ነው ያልኩህ ለዚህ ነው። በማንአህሉኝነት፥ በጀብደኝነት፥ በትእቢት፥ በንቀት፥ በርካሽ ፍላጎትና በራስ ወዳድነት መንፈስ ተኮትኩቶ አድጎ ያበጠው ከበርቴ ፊውዳላዊ ህሊና ተንፍሶ ልክ መግባት አለበት። የሀቀኛ አብዮተኛ ምልክቶች ፍቅር፥ ትህትና፥ ትእግስት፥ የሰፊውን ህዝብ የበላይነት አምኖ መቀበል፥ ከግል ጥቅም የህብረተሰቡን ጥቅም ማስቀደም፥ በራስ መተማመን፥ ሀቀኛ ሂስ ለማድረግም ሆነ ለመቀበል አለመፍራት፥ ለመማርና ለማስተማር ዝግጁ መሆን፥ በአጠቃላይ የህብረተሰብአዊነት ርእዮተ አለም፥ ዲሲፕሊንና አመለካከትን ከአስተሳሰብና ከድርጊት ጋር አዋህዶ መገኘት ናቸው። እንዳልኩህ ይህ በቀላሉ ሊሆን አይችልም - በተሰይ በቢሮክራሲው አካባቢ ከራስ ጋር ከፍተኛ ትግል ማድረግን ይጠይቃል። ሀቀኛ አብዮተኛ አትስከሩ እያለ የሚሰክር፥ አታመንዝሩ እያለ የሚያመነዝር፥ የስግብግብተኝት ባህርይን እያወገዘ ራሱ የሚስገበገብ፥ በትንሹ የሚደለልና የሚታለል፥ ቆጥቡ እያለ የሚያባክን፥ ከሌሎች መስዋእትነትን እየጠየቀ ራሱ የሚሸሸ፥ ስራ ከቡርነትን እየሰፈፈ ራሱ የሚሰንፍ፥ ትህትናን፥ ትእግስትን፥ ለሰፊው ህዝብ ሃያልነት መገዛትን እያስተማረ፥ ራሱ በትእቢት የሚወጠር፥ በስመ ነፍስ የሚከንፍ፥ ሽጥ አገንድሮ የሚወጠር - ሳይሆን ለአብዮቱ አላማ ራሱን ያስገዛና አብዮቱን የህሊናው መሪ ያደረገ ብቻ ነው። የአብዮት አላማ ነፃነት፥ እኩልነት፥ ፍትህና ዲሞክራሲያዊ መብት እስከሆነ ድረስ በሱ መመራት አለበት። ትግሉ ገና ነው የምልህ ለዚህ ነው። አብዮቱ ህሊናችን መሆን አለበት›› አለውና፥ ቆሎውን ቅሞ እየቆረጠመ ስልክ ለመደወል ሲዘጋጅ፥ ሌላ የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ ገብቶ ወደ ደርቤ እየተመለከተ፥ ‹‹ሰዎች ይፈልጉሃል›› ብሎ ነገረው።

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹የምን ሰዎች?››

‹‹ጥዋት በነዓ የለቀቅካቸው ሽማግሌ ወደ ሃያ የሚጠጉ ጠብመንጃ የያዙ ሰዎች ጋር መጥተዋል።››

‹‹ምን ሊሆኑ?›› አለ፥ ከደርቤ ጋር ይጫወት የነበረው የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ ደንግጦ።

‹‹መሳሪያ ሊያስረክቡ።››

ደርቤ ሰዎቹን ለመቀበል እየተጣደፈ ወጣ። አካሄዱ ድካም የተሰማው ሰው አይነት አልነበረም።

ያስገረመው የቀበሌው የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች ያልታሰቡ ወራሪዎች በድንገት የመጡባቸው መስሎአቸው በመደናገጥ ጥግ ጥግ ይዘው በተጠንቀቅ ቆመው ማየቱ ነበር። ተኩስ ባለመክፈታቸው እድሉን አመሰገነ። መጠራጠራቸውንም አልጠላም።

ሽማግሌዎቹ ወጌፎ፥ ውጅግራ፥ አልቤን፥ ዲሞትፎርና ሌሎች አሮጌ መሳሪያዎች ይዘዋል። አንዳንዶቹ እየተወለወሉ በደንብ የተያዙ ሲሆኑ፥ አብዛኛዎቹ የዛጉ መሳሪያዎች ነበሩ። ደርቤ ፊገግ ብሎ ሁሉንም በትህትና እጅ ነሳ። የአድሜያቸውን ሁኔታ ሲመለከት አንድ አይነት የሀዘን ስሜት አድሮበት አይኖቹ እንባ እንደ ማቅረር አሉ።

ጥዋት በነዓ የለቀቃቸው ሽማግሌ ወደ ፊት ራመድ ብለው፥ ‹‹ልጄ፥ እንዳከበርከን እግዜር ያክብርልን። እንደምታየን ሁላችንም እድሜ ተጭኖናል። ካለፈው ትዝታ ሌላ ተስፋ የለንም። በየጦር ሜዳው ለአገራችን ክብር፥ ነፃነትና አንድነት ደማችንን ያፈሰስን ጀግኖች ነበርን - ዛሬ እንዲህ ጉልበታችን ዝሎ፥ ክንዳችን ተዳክሞ ብታየን። የኛ ወኔ በልጆቻችን ደም ውስጥ ሲላወስ ከማየት የበለጠ ደስታ የለንም። ታዲያ፥ ይሽውልህ ጥዋት እንደዚያ አነጠረህና ለመሳሪያዬ ደረሰን ሰጥተህ የሸኘሽኝ መሆንክን ለባልንጀሮቹ ስንግራቸው፥ ሁሉም ተገርመው፥ እንደኔው ለመሳሪያ ፍቅር ብቻ ሲሉ የደበቁትን መሳሪያ ለማስረከብ ተስማሙ። እኔም አይዞዋችሁ፥ በኔ ይሁንባችሁ ብዬ ይዣቸው መጥቻለሁ። የዚህችን ሀገር ነፃነት በነዚህ መሳሪያዎች ጠብቀናል። እንግዲህ

ከዚህ ወዲህ የናንተ ተራ ነው። የምትሉም ሁሉ ማለፊያ ነው። ነገር ግን ወዳጅ መስሎ የሚቀርበው ሁሉ ከልቡ እንዳልሆነ ማወቅ አለባችሁ። ኢትዮጵያን ሲያስቸግሩ የኖሩት ከባህር ማዶ ወዳጅ መስለው የሚመጡት ፈረንጆች ናቸው። ጠላቴንስ አውቀዋለሁ፥ ከወዳጅ ጠላት እግዜር ይጠብቀኝ ማለት ያስፈልጋል። ለዚች ሀገር ማንም አይተኛም። ሰም መሬትዋ፥ ተራራና ሸንተረርዋ፥ ሸለቆና ሜዳዋ ያጓጓሉ። ቆንጆ ሚስት ያገባና ይህችን ውብ አገር የሚያስተዳድር መስጋትና መጠራጠር እጣ ፈንታው ነው።የናንተም እጣ ፈንታ ይኸው ነው ልጄ›› አሉት።

ደርቤ በሽማግሌው ንግግር ልቡ ስለ ተነካ እንባ ይተናነቀው ነበር። እንደ ምንም ብሎ ስሜቱን በመግታት ጥርሱን ነክሶ ከእንባው ጋር እየተናነቀ ‹‹አባቶቼ፥ በራሳችሁ አነሳሽነት ዛሬ የወሰዳችሁት ርምጃ ለምትወዱዋት አገራችሁ አንድነትና ለሰፊው ጭቁን ህዝብ ለመጣው አብዮት ያላችሁን ፍቅርና ታማኝነት የሚገልፅ ነው። በሁለተኛ ደረጃ፥ በቀበሌያችሁ የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች ላይ ያሳደራችሁትን እምነት ቁልጥ አድርጎ ያሳያል። ቀበሌ ሲባል በደፈናው ሀቀኛ አብዮተኞች የተሰበሰቡበትና አብዮት የሰፈነበት አካበቢ አስመስሎው የሚናገሩ ሞልተዋል።ግን አይደለም። ቀበሌ የህብረተሰቡ አካል እንደ መሆኑ መጠን፥ በአብዮተኞች ቁጥር ፀረ-አብዮተኞችም ይገኙበታል ። ያውም ባይበዙ። ስለሆነም፥ በቀበሌ ስም የሚነግዱ፥ የሚዘርፉ፥ የግል ጥቅማቸውን ብቻ የሚያሳድዱ፥ የግለሰቦችን ቤትና ክብር የሚደፍሩ አባወራዳን በሰበብ አስባቡ አስረው ሚስቶቻቸውን የሚያመግጡ እንዳሉ ከናንተ የበለጠ የሚያውቅ የለም። ታሪኩ ተዘርዝሮ አያልቅም። ሆኖም በአብዮት ሂደት ውስጥ እንዲህ አይነቱ ክስተት፥ እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሊታይ ስለሚችል አያስገርምም። ጠላቶቻችን እነዚህን ሁኔታዎች አጋንነው በማውራት አብዮቱን ላጥላሉትና ብሎም ለመቀልበስ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። በአብዮቱ ሰፊር የተሰለፉ ሀቀኛ ጉዋዶች በሁኔታው ባይገረሙም ዝም ብለው ይመለከቱታል ማለትም አይደለም። ቀበሌዎችን ከፀረ ። አብዮተኞች ለማፅዳት እስከ እለተ ሞታቸው ይታገላሉ። ድሉም የሀቀኛ ታጋዮች ይሆናል። ስለሆነም የቀበሌ ተመራጮችና ነዋሪዎች በአንድነት ለአንድ አላማ ቆመው በመተማመንና በመከባበር የሚለሩበት ብሩህ ሁኔታ በአይነ ህሊናዬ ይታየኛል። ጊዜውም ሩቅ አይደለም። ወደዚህ ብሩህ ገፅታ

የሚሆመራው የመጀመርያው ርምጃ ዛሬ እናንተ ወሰዳችሁአል። በቶላሉ የሚገመት ርምጃ አይደለም። በዚህ ቀበሌ ታሪክ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ ይይዛል ብዙ አምናለሁ። ለመሳሪያዎቻችሁ አስፈላጊ ደረሰኝ ይሰጣችሁአል። በትረብ ጊዜ ውስጥ መሳሪዎቻችሁ እንዲመለሱላችሁ ተደርገው፥ የአብዮቱን ስፈር እንደምታጠናክሩባቸው አልጠራጠርም። አመሰግናለሁ›› ብሎ ንግግሩን እንደ ጨረሰ፥ ሁሉም ግርማ ሞገስ ባለው ሁኔታ በአንድነት እጅ ነሱ።

ደርቤ ከደስታው ብዛት የአያንዳንዳቸውን ጉንጭ ይዞ ለመሳም ከጅሎት ነበር። አንድ የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ ሲርጥ መጥቶ፥ ‹‹ስልክ ይፈልግሃል። ቡጣም አስቸኩዋይ ነው ትላለች። ሶስተኛ ጊዜ መደወልዋ ነው›› ብሎ ነገረው።

‹‹ማን ናት እስዋ?። ቆይታ ልትደውል አትችልም?››

‹‹ሂሩት ነኝ ትላለች። ቆይተሽ ደውይ ብላት አሁን ካላቀረብክልኝ ሞቼ እገኛለሁ አለችኝ። ሃይለኛ ሴት ናት።››

ደርቤ ደነገጠ። ሂሩት የሚል ስም ሲሰማ ልቡ ይደነግጣል። ሂሩት የምትባል ሌላ ሴት አያውቅም - ልቡ ውስጥ ካለችው ሌላ። ሂሩት በሚል ስም የሚጠሩ ሴቶች ሲያጋጥሙት ሁልጊዜ ከፊቱ መጥታ የምትደቀነው ሂሩት ጉልላት ብቻ ነበረች። ሂሩት - ስምዋ ራሱ ለጆሮው እንደ ረቂቅ ሙዚቃ ሆኖ ነበር የሚሰማው።

የነራ ጉዋደኞቹ ለሽማግሌዎቹ ደረሰኝ ሰጥተው በክብር እንዲሸኙዋቸው አዘዘና እየተቻኮለ ወደ ቢሮው ሄደ። ቴሌፎኑን ሲያነሳ እጁ ይንቀጠቀጥ ነበር።

‹‹ሀሎ. . .››

‹‹ደርቤ ነህ?››

‹‹ነኝ. . .››

‹‹ሂሩት ነኝ።››

‹‹አውቄአለሁ››

‹‹በምን አወቅኸኝ?››

‹‹በድምፅሽ:: ድምፅሽ የትም አይጠፋኝም:: ስንት ዘመን ስሰማው የኖርኩ ድምፅ አይደለም እንዴ? አንዳንድ ስሞችና ድምፆች ልዩ ስሜት ይሰጣሉ::››

‹‹ታዲያ ምን ነው አስጠበከኝ ልጄ? የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር መሆን ያኮራል እንዴ? በነገራችን-እንኩዋን ደስ አለህ!››

‹‹ስራ ይገፋ ነው እንጂ ምኔ አንቺ ላይ ይኮራል ብለሽ ነው ሁሉጊዜም አሽከርሽ ነኝ::››

‹‹ሁሉጊዜም ወንድምሽ ነኝ ብትለኝ ይሻላል::››

‹‹እኔ የምመርጠው አሽከርነቱን ነው፥ እንዲህ በማለቴ ሌላ ትርጉም እንዳትሰጪው:: አንቺ ሀብታም እኔ ድሃ ምን ሲሆን ወንድምና እህት እንሆናለን ማለቴ አይደለም:: ምረጥ ቢሉኝ አሽከርሽ መሆንን ነው የምመርጠው:: አሽከርሽ መሆን የበለጠ ደስታ የሚሰጠኝ ይመስለኛል›› አላት::

ዝም ብላ ስታስብ ቆይታ፥ ‹‹ብዙ ደሞዝ ካልጠየቅሽኝ ስራ ስይዝ እቀጥርሃለሁ›› አለችውና፥ ከት ብላ ሳቀች::

‹‹ደሞዝ አልጠይቅም ኧረ!››

‹‹ያለ ደሞዝማ ብዝበዛ ይሆናል!›› አለችውና፥ ‹‹እንደ ክርስቶስም በምላሌ መናገር ጀምረሃል መሰለኝ!›› በማለት፥ በአሽሙር ነካ አደረገችው::

‹‹ጠቢባን ይነባቸዋል!›› አላትና፥ መሀረብ አውጥቶ ከፊቱ ላይ የተንቸረፈፈውን ላብ ጠረገ:: እጁም ሳይቀር አልቦት ነበር::

ሂሩት በሀሳብዋ፥ ‹‹እኔ ደንቆሮ ነኝ:: እውነቱን ነው:: ስለ ራሴ ብቻ ስለማስብ ነው መሰለኝ፥ የሰው ስሜት አይገባኝም:: ግን ህይወት ተአምራዊ ነገር ናት:: አይናችን እየተገለጠ ነው የሚሄደው›› ስትል ቆየችና፥ ‹‹ለብርቱ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር›› አለችው::

‹‹አሽከርሽ መሆኔን እመርጣለሁ ብዬሽ የለም? ከቃልሽ አልወጣም፤ ጉዳዩን ንገሪኝ›› አላት::

‹‹በስልክ የሚነገር አይደለም:: ላገኝህ እፈልጋለሁ::››

‹‹መቼ?››

‹‹ከተቻለህ አሁን:: ወይም በሁዋላ:: ሱቃችንን ታውቀው የለም? እዚያ::››

‹‹እሜቴም ጥዋት ደውለውልኝ በጣም እፈልግሃለሁ ብለውኝ ነበር:: ይገርምሻል፤ እንዲት ደቂቃ እረፍት የለኝም:: ሳላስቀይማቸው አልቀረሁም:: ይሽውልሽ አሁንም ላስቸኩዋይ ጉዳይ ስብሰባ መግባቴ ነው›› አለና፥ ምን እንደምትለው ለመስማት ፈልጎ ዝም አለ::

‹‹ሂሩቴ፥ ምንነው ዝም አልሽ? ተቀየምሺኝ መሰለኝ?›› አላት::

‹‹ለምን አልቀየምም? ግን ጥፋተኛዋ እኔው ነኝ›› በል ተወው ስትል፥ አቁዋረጣትና፥ ‹‹ምን አባቴ ላድርግ ትይኛለሽ? ፋታ የለኝም እውነቴን ነው. . . እንጂ ለነገሩማ እኔም ላገኛችሁ በጣም ፈልጌ ነበር. . . አንቺንና ተስማን›› አላት::

‹‹ለምን ትፈልገናለህ?›› ብላ ጠየቀችው፥ ድምፅዋን በድንገት ከፍ አድርጋ::

‹‹የምንነጋገርበት ብርቱ ጉዳይ አለ:: እሜቴንና ጌቶችንም በጣም አፈልጋቸዋለሁ:: የጊዜ ጉዳይ ሆነብኝና ነው እንጂ::››

‹‹እኮ ለምን?››

የድምፅዋ መለወጥ ታወቀው:: ድምፅዋ ውስጥ የመደናገጥ ወይም ግራ የመጋባት ሁኔታ ይሰማ ነበር::

‹‹ምን ሆንሽ?›› ብሎ ጠየቃት::

‹‹ምን ሆንኩ?››

‹‹ድምፅሽ ተለወጠብኝ:: ድንገት ስትርቂኝም ተሰማኝ::››

‹‹መስሎህ ይሆናል::››

‹‹እሺ ማታ እንገናኝ::››

የቀይ ኮከብ ጥሪ

‹‹በስንት ሰአት?››

‹‹ሶስት ሰአት ላይ። ሱቅ ሳይሆን ቤታችሁ። ሁላችሁንም ባንድነት ላገኛችሁ እፈልጋለሁ።››

‹‹ሶስት ሰአት ላይ አይቻለኝም. . .እ. . .›› አሰችና፥ ለምን እንደማይቻላት ምክንያት ስትፈልግ ቆይታ፥ ‹‹ነፃ ርምጃ በተፋፋመበት በዛሬው ጊዜ አምሽቶ መሄድ አደገኛ ነው። አይመስልህም?››

‹‹የሚያሰጋ ነገር የለም። ለሀቀኛ አብዮተኞች ጊዜው አያሰጋም። የሰጋቱ ጊዜ አልፎአል። አሁን በማጥቃት ላይ ነን።››

‹‹አዎን ልጄ! ላንተማ ሁሉም በእጅ ሁሉም በደጅ ሆኖልሃል። ለማንኛውም ዛሬ ማታ አይመቸኝም›› አለችው።

‹‹እሺ ስብሰባውን እንደ ጨረስኩ ልደውልልሽ›› አላት። እሺ ልትለው ነበር፡ አሳብዋን ለወጠችና፥ ‹‹እኔ ሲመቸኝ እደውልልሃለሁ። አትቸገር። ቻው!›› ብላ፥ ለመመለስ እድል ሳትሰጠው ሰልኩን ዘጋችበት።

ሂሩት ስልኩን እንደ ዘጋች ወደ ላእከ ዞር ብላ፥ ‹‹ምን አንዳለኝ ሰምታችሁአል?›› አለች።

‹‹ምን አለሽ?›› አላት ተፈራ፥ ቸኩሎ።

ቀኑን ሙሉ ከነበሩበት ኪዮስክ - ከኢ.ህ.አ.ፓ. ህዋስ - የሚወጣበትን ደቂቃ በናፍቆት ይጠባበቅ ነበር። ከጥዋት ጀምሮ በሰፈሩ ከባድ አሰሳ ይካሄድ ስለነበረ መውጣት አልቻለም። ሰፈሩ አንድ በአንድ ሲታሰስ ኪዮስክዋን ዞር ብሎ የተመለከተ አልነበረም። እንደዲያውም፥ ፀሀይ ያቃጠላቸውና ሲጃራ የጠማቸው ፈታሾች እየተመላላሱ ከሱቅዋ አምቦ ውሀና ሲጃራ ሲገዙ ነበር የዋሉት። ፍተሻው ጋብ ካለ በሁዋላ በተፈራ ጎትጉዋችነት ነበር ሂሩት ወደ ደርቤ የደወለችው።

‹‹እኔን፥ ተሰማን፥ እናቴንና አባቴን - ሁላችሁንም ባንድነት በሶስት ሰአት ላይ ለማግኘት ይፈልጋል። ለምን ይሆን?›› አለች።

ላእከ እየቀለደ፥ «ቢተሰክን ሰላሳም ጉዞ ሊሰደቅ ይሆናሉ አይፈሩ አላት።

«እያደረግም ብለህ ነው? ደፋር ነው ኮ» አለው ተፈራ።

«የለም የለም፥ አለች ሂሩት፥ «ሁላችንንም ባንድ ወየመድ ሊያደሆን ነው፤ ተንኮሉ ገብቶኛል።»

ላዕከ ራሱን ነቀንቀና፥ «አትቃጠር አባክሽን» አላት፥ «አንድ ግደም የቀሀሌ ዘሀኖ የሌለውን እውቀትና ፕህብ አለው ብለሽ አትሳቢው። እንደንገራችሁኝ ከሆን ስውዱው በጎ አሰራለሁ ብሎ የተነሳ ጆል ነው። ሁላችሁንም የፈለገበት ምክንያት ለኔ ግልፅ ነው። ሊያግባባችሁ ፈልጎ ይሆናል። በእድሉ መጠቀም አለብን። እምቢ በማለትሽ ተሳስተሻል። በጣ ወየመዱ ልታስጢው ትችያለሽ። ውብ ሴት የማትፈታው ወንድ የለም - በተለይም በኛ ህብረተሰብ ውስጥ እንደ ውሻ ተከትሱሽ ባይመጣ ምናለ በይኝ።»

ወዲያውኑ ጠንሩን የተሳፈኤ እንድ ውጣት ጮኖ፥ «የተወናከረ ፈታሽ ቡድን በለፈሩ እንደ ጮኘ ተሰማርቶአል» አላቸው።

ሁሉም ተያዩ።

ላእከ የሚያፈሰውን እፀ ፋርስ በረዥሙ ማፃ አድርጎ ቁራፌን ወረወረና፥ «እነዚህ ሰዎች ዛሬ አልለተቁንም፤ ጥቃጣ ደርሶአቸው ይሆናል» አለ። ሁሉም ስራ እንዲያቆሙና መብራት አጥፍተው በተጠንቀቅ እንዲቀዩ አዘዛቸው።

ሁሉም ስራቸውን አቁመው መሳሪያቸውን መፈተሽና ማኑሪስ ጀመሩ።

«እቅጻችንን ሊያስተንዋለሱብን ነው መሰለኝ» አለች ሂሩት፥ በናፍቀት የምትጠባበቀው ከአደጋ ጋር የደብበቆሽ ጨዋታ ትዝ ብሎአት።

«አትሰጊ አሁን ይሄዳሉ። በቀን ያጡትን ቦታ በምሽት እንዴት ያገኙታል? ምዕአት ቢመጣ ይሀን ቦታ ሊያገኙት አይችሉም፤ ከሀዲ መከላላችን ካሌለ በስተቀር» አላትና፥ «በንገራችን ላይ ስለ ወንድምሽ የሰጠሽኝ መልስ አላጠገበኝም። ዋሽተሽኛል። ወንድምሽ የታመመ አልመሰለኝም። እኔ

ኢትዮጵያውያንን አላምንም ከራሴ ጀምሮ። በጭምብል (በግዕዝ) ተሸፍነን የምንኖር ህዝቦች ነን። ለሰው የምናሳየው ገፅታና እውነተኛው ባህርያችን የተለያዩ ናቸው። እንደ ተረታችን፥ ስነልሁሉችንና ንግግራችን፥ ባህርያችንም ሰምናወርቅ ነው. . .

‹‹ዘሀይ ላይ ደግሞ ክፉውና በጎውን ነገር፥ አንዱን ከሌላው ሳይተን የምናይበት መለኪያ የለንም፡ የማንኛውም ነገር መሰረታዊ መለኪያችን ምግ ጥቅማችን ነው፡ ለዚህም ነው ተንኮል የሚበዛው፥ መተማመን የሌለው የወዳጅነት ወይም የጉዋደኝነት ትርጉሙ የማይታወቀው፤ ሀሜት አሉባልታና እርስ በርስ መበላላት የሚበዛው። ኢትዮጵያውያን ስንባል የምናውቀው መርህ አንድ ብቻ ነው - የግል ጥቅም! ከራስ በላይ ነፋስ - እኔ ከሞትኩ ስርዶ አይብቀል. . . ሰውን ማመን ቀብሮ፥ ይሉታል ከንተረቱ። የሚሳዝን ነው. . .

‹‹ለግል ጥቅማችን የሚበጅ ከሆነ እንዋሻለን። ስንዋሽ ህሊናችንን ቅንጣት ታህል አይቆረቁረንም። እንዴት አድርጎ ለግል ጥቅም የተገዛ ህሊና ሊቆረቁረው ይችላል?

‹‹ለተንኮል አንመለስም። የምንሸርበው ተንኮል ጉዋደኛን፥ ወዳጅን፥ የስጋ ዘመድን ከጠላት አይለይም። ተንኮል ምቀኝነትና ቅናት ባህላችን ነው።

‹‹ምግባር የሚባለውን ነገር በአፍ ካልሆነ በቀር በተግባር አናውቀውም። በአጠቃላይ ክፉውንና በጎውን ለይቶ የሚያይ ህሊና የለንም። ያስተማረንም የለም። የተማርነው ነገር ቢኖር በአደባባይ ሰው መስሎ መታየት ነው፡ ሰው መሳይ በሽንጎ ይሉ የለም? በአደባባይ ሁሉም ጨዋ፥ ልበ ሙሉ፥ ጀግና፥ አትንኩኝ ባይ፥ ኩሩ፥ ቅን፥ በጎ አሳቢና ታማኝ፥ አስተዋይና ትሁት ነው። በአደባባይ የምናጠልቀው ጭምብል ይህ ነው። በግል ኑሮአችን ግን ከስብቅ ከምቀኝነት፥ ከተንኮል፥ ከቅናት፥ ለውሸት፥ ከአሉባልታና ከሀሜት፥ ለግል ጥቅም ለመልከስከስና ከመልፈስፈስ ከፍርሃትና ከአድር ባይነት ርቀን አንገኝም። መለያ ባህርያችን ግብዝነት ነው። የግብዝነት ጭምብል አጥልቀን ነው የምንኖረው! ያለ ጭምብል እናስቀይማለን. . .ወይም እናምራለን። አይታወቅም። ያለ ጭምብል ታይተን አናውቅማ!

‹‹የምለው ነገር ትርጉም አለው? ለምን ይህን ሁሉ እንደምለፈልፍ እኔም አልገባኝም። ለማለት የፈለግሁት. . . ምን ለማለት ነበር የፈለግሁት. . . አዎን፥ አንዱ ኢትዮጵያዊ የሚያስበውን ሌላው ሊያውቅ አይችልም ለማለት ነበር የፈለግሁት - ባጭሩ፡ ምክንያቱም ክፉና በጎን የማይለይ ሀሊና ይዋሽ አይዋሽ አይታወቅም። የኢትዮጵያዊ ባህርይ እንቆቅልሽ ነው - ፍቺ የሌለው እንቆቅልሽ ነው። እውነቱን ንገሪኝ። የት ነው ወንድምሽ?›› አለት፥ ሂሩትን።

‹‹እውነቱን ማወቅ ትፈልጋለህ? የት እንደሆነ አላውቅም። ቤት ሂዶ ይሆናል። ግን ስልክ ደውዬ ለማረጋገጥ አልፈለኩም። ብቻ እዚህ እንደማይመለስ እርግጠኛ ነኝ›› አለችው፥ ፍርጥም ብላ፡

‹‹አሁን ገባኝ። አለተሳሳትኩም። በራሱ ላይ ፈርዶአል በይኛ!››

‹‹አልገባኝም።››

‹‹ይገባሻል›› አላትና፥ ሂዶ ለአንድ ጠረንጋሎ ወጣት በጆሮው አንድ ነገር ነገረው። ወጣቱ ፊቱን በቁም ነገር አኮሳትሮ እያዳመጠ በእሺታ ራሱን ይነቀንቅ ነበር።

ሂሩት ምንም እድል ሳትሰጠው በድንገት ስልኩን ጆሮው ላይ የዘጋችበትን ምክንያት ለማሰላሰል ደርቤ ጊዜ አላገኘም። ወዲያውኑ ነበር ተጠርቶ ስብሰባ የገባው። የስብሰባው አላማ ስለ እናት አገር ጥሪ ዝግጅት ለመነጋገር ነበር። ሆኖም ስብሰባው ከተጀመረ ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ፥ ውይይቱ ፈር ለቆ ወደ ዲሞክራሲያዊ መብት ጥያቄዎች በማምራቱ፥ ስብሰባው የቡድን ስሜት ማንፀባረቂያ መድረክ ሆኖ ለገላጋይ እስከማስቸገር ደርሶ ነበር።

‹‹የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ጥያቄ የሰፊውን ህዝብ ነፃ ርምጃ ለማይናፍቅ ታቅዶ የቀረበ የቀኝ አድርባዮች ጥያቄ ስለሆነ፥ እናወግዘዋለን! ነፃ እርምጃችን በትግላችን ይቀጥላል! አድርባዮች ይጋለጣሉ!›› አሉ ከዳር የተቀመጠው ባለ አንድ አይና ሰውዬ።

‹‹ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እየተባለ ከትናንት ማታ ጀምሮ እስከሁን የሚለፈፈው ነፃ እርምጃችንን ለመግታት ብቻ ላይሆን ዲሞክራሲያዊ መብት

ለጭቁኖች አሁን፥ የሚለውን ጥያቄ ጭምር ለማፈን የታቀደ የቀልባሾች ሴራ ነው!›› አሰ፥ መሀል የተቀመጠው እጀ ቆራጣ ሰጥቆ።

ከሁሉም ፈንጠር ብሎ የተቀመጠው መዓዝ መሳይ የሁለቱን ተናጋሪች አሳብ በመደገፍ፥ «የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ጥያቄ ወቅቱን ጠብቆ የመጣ ጥያቄ አለመሆኑን በተጨባጭ ለመገንዘብ ችለናል›› አለ። ‹‹የዚህ ጥያቄ አለመሆን በተጨባጭ ለመገንዘብ ችለናል›› አለ። ‹‹የዚህ ጥያቄ አላማ ከመከላከል ወደ ማጥቃት የተሸጋገረውን የአብዮታችንን ሂደት ለመግታት ካልሆነ በቀር ሌላ ትርጉም የለውም። የሰፊው ህዝብ ጥያቄ ነፃ አርምጃ ይፋፋም! ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን፥ የሚል ነው። የወዛደሩ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ፥ ዲሞክራሲያዎ ማእከላዊነት ሊኖር አይችልም። ህልም ነው። አድርባዮችና ቀልባሾች የሚያልሙት ህልም ነው። የጥያቄው ትክክለኛ ገፅታ ይህ መሆኑ እየታወቀ፥ ዝም ብለን ማየት አንችልም። በሀቀኛው ታጋይ በገዱ ዋሲሁንና በሌሎችም ላይ የተወሰደውን እርምጃ ባንድ ድምፅ እያወገዝን፥ ሰርጎ ገብ ቀልባሾችና አድርባዮች ራሳቸውን እንዲያጋልጡ እንጋብዛለን፥›› አለ።

ሶስቱ ሰዎች እየተቀባበሉ ሲናገሩ፥ ደርቤ ሳይሸበር ዝም ብሎ ያዳምጣቸው ነበር። በእርሱ ላይ ሊሸረብ የዋለ ሴራና ተንኮል መሆኑ ገብቶታል። ተንኮሉ ከየት እንደ መነጨ ለማወቅም አልተቸገረም።

ውይይቱ እየተጋጋለ መጥቶ አየሩ ጭንቀት እየሰፈነበት መሄዱንና በያንዳንዱ የስብሰባው ተካፋይ ልብ ውስጥ ፍርሃትና ጥርጣሬ፥ የመውላወልና የመደናገጥ ሁኔታ እየሰረፀ መሄዱን በማጤን፥ ደርቤ ለመናገር ተነሳ።

‹‹የተነሳሁት በተቀነባበረ ሁኔታና በቅበብሎሽ መልክ የተሰነዘሩት ኢ-ሳይንሳዊ ሂሶች እኔን የሚመለከቱ ስለመሰለኝ ነው›› አለና ንግግሩን ጀመረ። ‹‹ቅድም ተደጋግሞ እንደ ተነገረው፥ የወዝ አደሩ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ይኑር ማለት፥ ነፃ አርምጃችንን ለመግታት የታቀደ የቀልባሾች ደባ ነው ተብሎአል። የወዛደሩ ፓርቲ እስኪፈጠር ድረስ ሰርአተ-አልበኝነት ይንገስ ካልተባለ በስተቀር የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነትን አሰራር የሚቃወም አእምሮ፥ በኔ ግምት ጤነኛ አይመስለኝም. . .

‹‹ለጊዜው የወዛደሩ ፓርቲ ባይኖርም፥ አብዮታዊ መንግስት አለ። አብዮታዊ መንግስት የለም፥ አብዮታዊ አመራር የለም የሚሉ ሰዎች ካሉ፥ አመራር የሚሰጥ አብዮታዊ መንግስት አለ ብዬ አምናለሁ። አብየቱ ማእከል አለው ብዬ አምናለሁ። ስለሆነም፥ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር በተግባር እንዲተረጎምና በነፃ እርምጃ ስም የሚፈፀመው ስርአት አልበኝነት እንዲጠፋ እታገላለሁ. . .

‹‹ጉዋዶች! የወዛደሩ ፓርቲ በሌለበት ሁኔታ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር ሊኖር አይችልም፥ የሚሉት እነማን ናቸው? በፍርሃት ተውጦ ማን እንደሆኑ፥ ለምን አላማ ተሰባስበው እንደ ተሰለፉ፥ ገሀድ ሳናወጣ ብንቀር የገዛ ሀሊናችን ይፈርድብናል። እንዲህ አይነቱን ውሸንብር የሚነዙት ለስልጣን የቁዋመጡ፥ አብዮታዊውን መንግስት በሾኬ ጠልፈው በመጣል ከሰፊው ህዝብ ትከሻ ላይ ባቁዋራጭ ወጥተው ጉብ ለማለት የሚፈልጉ ንኡስ ክበርቴዎች ናቸው። ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን፥ የሚለው አቁዋም፥ ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አሁን፥ ከሚለው ጥያቄ በይዘትም ሆነ በአላማ የሚለይበት መንገድ አይታየኝም. . .

‹‹አብዮታዊው መንግስት ጉያ ውስጥ ተሸጉጡ ሰፊውን ህዝብ አነቃለሁ፥ አደራጃለሁ እያለ በአንዳንድ ፋብሪካዎች፥ ቀበሌዎችና መንግስት መስሪያ ቤቶች አካባቢ ራሱን ለስልጣን ሲያደራጅ የቆየው ቡድን፥ ዛሬ ድርጅታዊ እብጠት ተሰምቶት፥ ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን፥ በሚል ሽፋን ስልጣን ስጡኝ፥ እያለ ሲደነፋ ያስቃል። ነገሩ የልጆች ጨዋት ሆኖ ነው የሚታየኝም. . .

‹‹እኔ ምሁር አይደለሁም። ስለ ሳይንሳዊ ሶሺያሊዝም ያለኝም እውቀት በጣም አነስተኛ ነው። ግን ደደብ አይደለሁም። በድርጅት አካባቢ ግለሰቦችን አሰባስቦ ሆያ ሆዬ በማብዛት የወዛደሩን ፓርቲ ለማስገኘት እንደማይቻል ይገባኛል። የወዛደሩ ፓርቲ ስል ላሳስታችሁ አልፈልግም. . . የሰርቶ አደሩ ፓርቲ ብል ትክክል ይመስለኛል። በኢትዮጵያ የወዛደሩ መደብ ገና እያቆጠቆጠና እያበበ በመሄድ ላይ ነው። አሁን ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ሀልውናው የተጠናከረ አይደለም። ለማንኛውም ነገር የሰርቶ አደሩን ፓርቶ

ሊመሰርቱ የሚችሉት በግንባር ቀደምትነት ታግለው፥ የሚያታግሉ፥ አመራራቸው በሰፊው ህዝብ ዘንደ ተቀባይነትንና ታዋቂነትን ያገኘ፥ አብዮቱንና የኢትዮጵያን አንድነት ለመጠበቅ ችሎታና አስተማማኝ ሃይል መሰረት ያላቸው ታጋዮች ናቸው እንጂ፥ የዚህ ድርጅት ወይም የዚያ ድርጅት የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ነን በማለት፥ በር ዘግተው ሲያወሉ የሚውሉና አጫፋሪዎቻቸውን እየላኩ ምልመላ በገፍ እንዲካሄድ የሚያደርጉ ብልጣ ብልጦች አይደሉም።

‹‹ጉዋዶች! የስልጣን ጥማቸውን ለማርካት መሳሪያ ሊያደርጉን የሚፈልጉን ቡድኖች መታገል አለብን። የሀቀኛ አብዮተኞች አይነተኛ ተግባር፥ ሀቀኛ ታጋዮች የሰርቶ አደሩን ፓርቲ እንዲያስገኙ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩላቸው መታገል ነው እንጂ፥ በቅጥረኛነት ስሜት ለቡድኖች አምባገነንነት እርስ በርስ ሽኩቻ ማካሄድ አይደለም።

‹‹አቅዋሜን ገልጫለሁ። ቤቱ ፍርዱን እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ›› ብሎ ቁጭ አለ።

ቤቱ ስሜቱን በጋለ ጭብጨባ ገለጠለት። ሶስቱ ሰዎች ግን አቀርቅረው ነበር።

‹‹ሶስቱም በራሳቸው ላይ ግለ ሂስ አካሂደው ቤቱን ይቅርታ ይጠይቁ›› የሚል አሳብ ካንዱ አባል በመቅረቡ፥ ሁሉም አሳቡን በመደገፍ እጃቸውን አወጡ።

ሶስቱም ሰዎች የተመካከሩ ይመስል፥ በአንድነት ተነስተው ከስብሰባው ለመውጣት ሲሄዱ፥ በር ላይ የቆሙት ሁለት የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች አቆሙአቸው።

የቀበሌው ሊቀ መንበር የሚሰጠው ትእዛዝ ጠፍቶት ሲያቅማማ፥ ደርቤ ሽጉጡን ላጥ አድርጎ አቀባበለና፥ ‹‹ካሁን ጀምሮ በቁጥጥር ስር ውላችሁአል። እብሪት ለማንም አይበጅም። የሰፊው ህዝብ ዲሞክራሲያዊ መብት በተግባር እየተተረጎመ ነው። የናቃችሁትም ማእከል ፍርዳችሁን ይሰጣችሁአል›› አላቸውና፥ ትጥቃቸውን አንደ በአንድ አስፈትቶ እየነዳ ይዞአቸው ወጣ።

ሶስቱንም እየነዳ ሲሄድ በአይነ ህሊናው ሌላ የትግል ግንባር ሲከፍት ይታየው ነበር። ዞር ሲል ተሰማ ጉልላትን ስላየ ተገረመና፥ ‹‹ተሰማ ምን ነው ደህና አይደለህም? ምን ታደርጋለህ እዚህ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹አንተን ነበር የምፈልገው። ከመጣሁ ቆይቻለሁ›› አለው፥ ጢሙን እየጎተተለ።

‹‹ጠብቀኝ መጣሁ›› ብሎት ሰዎቹን ተከትሎ ሄደ።

ደርቤ አልቆየም። ወዲያውኑ ነበር የተመለሰው። ተሰማ የመጣበትን ጉዳይ ለመስማት የቸኮለ መሆኑ ያስታውቃል። ተያይዘው ወደ ቢሮ ገቡ። ደርቤ እየተደናበረ ሄዶ መብራቱን አበራ። ጊዜው አልታወቀውም። ሰአቱን ተመለከተ። ከምሽቱ አንድ ሰአት ተኩል ሆኖ ነበር።

‹‹ጊዜው እንዴት ይሮጣል!›› አለ። ‹‹ጊዜ ተርፎን፥ የምናደርገውን አጥተን ሶስት ሽህ ዘመን እንዳላንቀላፋን ሁሉ፥ በድንገት ጊዜ ያጥረን ጀመር። ይገርማል! ኢትዮጵያውያን ጊዜ አጠረን ሲሉ ሰምቼ አላውቅም ነበር፡ ስለ ጊዜ ማን ደንታ ነበረው? ‹‹እሺ ነገ›› ብሄራዊ ጠባያችን ሆኖ ቆይቶ ነበር። ባሁኑ ጊዜ ነገ የሚባል ነገር የለም። ህይወት ፍጥነት ጨምራለች!›› አለውና፥ ትኩር ብሎ ሲመለከተው ከቆየ በሁዋላ፥ ‹‹ምን ሆነሃል? በጣም ትተክዛለህ። የፍርሃት መልክም ይታይብሃል›› አለው።

ተሰማ አንገቱን ቀና አድርጎ በሚንቀጠቀጥ እጁ ጢሙን እየጎነተለ፥ ‹‹ደህና ብለሃል›› አለው በጎረና ድምፅ፥ ‹‹በጣም ተክዣለሁ። ፍርሃትም አድሮብኛል። ጊዜም የለኝም። ጊዜ እየከዳኝ ነው!››

‹‹ንገረን ምን ሆነሃል?››

ሲያቅማማ ከቆየ በሁዋላ፥ ‹‹መጀመሪያ ራሴን አጋልጬ እጄን ላንተ ልሰጥ ነው የመጣሁት›› አለው።

‹‹እንዲህ አይነቱን እርምጃ የሚወስዱ ጀግኖች ናቸው። ታዲያ ለምን ፍርሃት አድሮብኛል ትላለህ?›› ብሎ አበረታታው።

‹‹ስለ ራሴ አልተቸገርኩም። ብሞትም ብኖርም ደንታ የለኝም። በደመ ነፍስ ስሜት ተነሳስቼ እዚህ ከደረስኩ በሁዋላ ተመልሼ ሄጄ ራሴን ለመግደል አስቤ ነበር። ግን ሳስበው ራሴን መግደል መፍትሄ ሆኖ አላገኘሁትም። የኔ መሞት እህቴን ከአደጋ ሊያድናት አይችልም›› አለው

‹‹ሂሩት ምን ሆናለች?›› አለ ደርቤ፥ ከተቀመጠበት ተስፈንጥሮ እየተነሳ።

‹‹ቤት እየተላቀሱ ናቸው. . .››

‹‹የት ናት እስዋ? ያዘዋት? ንገረኝ! ቅድም ደውላልኝ ነበር። ወዲውኑ ልታገኘን የፈለገችው ለካ ተቸግራ ኖሮአል! ታዲያ ለምን አልነገረችኝም? ዝም ብላ ነው ስልኩን የዘጋችብኝ።››

ተስማ ጢሙን ቀስ ብሎ እየጎነተለ፥ ‹‹ደውላልህ ነበር? ብሎ ጠየቀው። የመገረም መልክ ይታይበት ነበር።

‹‹አዎን፥ ቅድም ደውላልኝ ነበር። አሁን የት ናት?››

ተስማ በጣም ተጨንቆ ከህሊናው ጋር እንደሚሙዋገት ያስታውቅ ነበር። ከጭንቀቱ ብዛት አይኖቹ እንባ እያቀረሩ ሲሄዱ ይታዩ ነበር።

‹‹ህይወት ለስዋ የድብብቆሽ ጨዋታ መድረክ ነው። ጅል!›› አለና፥ እንባውን ዱብ ዱብ አደረገ።

‹‹የት ናት ነው የምልህ! ጊዜ የለንም። ይዘዋት ከሆነ ጊዜ አይስጡአትም ያለችበትን ቦታ ንገረኝ!›› አለው ደርቤ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

‹‹የእህቴ ህይወት ከነርሱ ህይወት በምን ይበልጣል? እህቴን ለማዳን በነርሱ ህይወት ላይ ለምን እፈርዳለሁ? ለምን? ለምን? ለምንስ መጣሁ? ራሴን ብገድል ይሻለኝ ነበር። ፈሪ ነኝ! ፈሪ ነኝ!›› እያለ ግማሽ ለራሱ ሲናገር ቆየና፥ ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ጀመረ. . .

ደርቤ ሄዶ ትከሻውን ይዞ በማባበል ሊያስታግሰው ቢሞክርም አልሆነለትም። ተስማ ህቅ እስኪለው ድረስ ነበር የሚያለቅሰው።

የያዘው አባዜ ካለፈለት በሁዋላ፥ በእጆቹ ፊቱን ሸፍኖ እንዳቀረቀረ፥ ‹‹ለምንድር ነው የምንኖረው? የህይወት ትርጉም ምንድር ነው? እንወለዳለን፥

ኣድለኛ ከሆንን እናድጋለን፥ እናረጃለን፥ እንሞታለን። ከእንስሳት የተለየ ህይወት አይደለም። ልዩነት ቢኖር የሰው ልጅ ስለ መኖር ያለው የማሰብ ፉሎታ ብቻ ነው። ማሰብ ባይኖር ኖሮ ከቱን ለበጎ ለይቶ ለማወቅ ሀሊናችን ይጨነቅም ነበር። ህይወት አጭርና ጅል ነገር ናት! ግን ታስጨንቀናለች። ጭንቀቱ መሰረት የማሰብ ችሎታችን ነው። ሴላ አይደለም። የማሰብ ሎታችን ሲቆም እፎይታ፥ ሰላም፥ ዘለአለማዊ ፀጥታ! የሰው ዘር ሞኝ ነው። ል ነው። ለሚኖረው አጭርና ጅል ህይወት፥ ገና ለገና የማሰብ ችሎታ አለኝ ሎ፥ ለእንስሳ ባህርይው የረቀቀና የላቀ ትርጉም ሊሰጠው ይሞክራል። ነቃዩ ዋነኛ ምንጭ ይኸው ነው. . .

‹‹መኖር ስቃይ ነው። ለማትረባ አጭር ህይወት ብዙ ስቃይ፥ መዋተት፥ ጨነቅ፥ መቃተት፥ መቡዋጠጥ፥ መንጠራራት፥ ትርጉሙ ምንድር ነው? ዞሮ ፡ ጥሪኝ አፈር - መቃብር! ሞት ነው ዘለአለማዊ ነገር። ሞት ውበት ነው። ው ልጅ ግብ ነው። ግን እንፈራዋለን። ተወልዶ፥ አድጎ፥ አርጅቶ መሞት ኖሩን እያወቅን ሞትን ልናመልጠው እንሞክራለን። እኖ፥ የሰው ልጅ የወል ደት ምንጩ ይኸው ነው። በፍርሃት ጥላ ስር የሚኖር ሁሉ በዚህም ሆነ ያ እብድ ነው። የያንዳንዱን ሰው የእብደት መጠን ወይም ደረጃ፥ ጠባይ፥ ርይ እንለዋለን. . .

‹‹ህይወት ቁማር ጨዋታ ቢሆንም፥ እኔ ህይወትን እንዳመጣው ተቀብዬ ጫወት አልችልም። በሴላ አነጋገር ድፍረት የለኝም። ፈሪ ነኝ። ፈሪ ሆን ኖሮ እዚህ አልመጣም ነበር።

‹‹ሂሩት ህይወትን እንዴት እንደምታይ ታውቃለህ። ለሱዋ ህይወት ህደቃ፥ የመቡዋረቂያ፥ የድብብቆሽ ጨዋታ መድረክ ነው። አደጋ ኮያትም። የአንባሳ ስሜት ነው ያላት። እንደሰዋ በሆንኩ ኖሮ!. . .

‹‹ለምን እንፈራለን? ለምን? ሰው አድሜ ምን ያህል ነው? ግፋ ቢል ቡ አያልፍም። ከዚህ ውስጥ ለላሳ ወይም አርባ አመት መቀነስ ለምን ራናል? ለምን? ጥቂት አመት በተጨማሪ ለመኖር ስንል የፍርሃት ኖ፥ ድንዝና ቅጥረኛ ሆነን እንቀራለን። በዚህ ረገድ ሁላችንም አድርባዮች

‹‹ሰው ፍርሃትን ድል አስካልነሳ ድረስ የህይወት ድንክ ነው፤ ምንጊዜም ክባርነት አይወጣም። ክብር የለውም። ሽርሙጣ ነው። እኔ ፈሪ ነኝ፥ ክብር የለኝም፥ ሽርሙጣ ነኝ። ብሞት ይሻለኝ ነበር። መሞት እፈልጋለሁ። ግደለኝ›› አለውና፥ ያውልህ አሰረኝ እንደሚል ሰው ሁለቱን እጆቹን አጣምሮ ሰጠው።

ደርቤ ትእግስቱን ጨርሶ ነበር። የሚያደርገው ነገር ጠፍቶት እጆቹን በንዴት አወናጨፈ። ዝም ብሎ ተመለከተው። ለመንጎራደድም ሞከረ። በመጨረሻ ቆም ብሎ፥ ‹‹አየህ ተሰማ›› አለው፥ ‹‹የተሰፋ መቁረጥ ስሜት ነው የሚታይብህ። እና ህይወትን አጨልመህ ለማየት ትሞክራለህ። ህይወት ግን ብሩህ ናት። የሰው ልጅ ያለ ተስፋ አይኖርም። ተስፋ የሚያደርገው ደግሞ በከንቱ አይደለም። ባለው የምርመራ ችሎታ አለምን ሊያውቃት ይችላል። አንድ ቀን ተፈጥሮን ድል ያደርጋል። የተፈጥሮን ምስጢር፥ የህይወትን ትርጉም ፈልፍሎ ያውቃል። እና፥ የሰው ልጅ ግቡ ህይወት ነው እንጂ ሞት አይደለም. . .

‹‹ግቡ ተፈጥሮን ድል አድርጎ፥ ከቁጥጥር ስር በማዋል አለማዊ ደስታን መሻት ነው። በኔ ግምት የያንዳንዱ ሰው ጠባይ የሚለካው ለሰው ልጅ ደስታ በሚያደርገው አስተዋፅኦ መስዋእትነትና አሳቢነት መጠን ነው። ምክንያቱም ማናችንም ከህብረተሰቡ የተለየ ህልውና የለንም፤ ሊኖረንም አይችልም። የሰው ልጅ የጋራ ጥረት የጋራ ህልውናውን ማወቅ፥ አውቆም ለጋራ ችግሩ መፍትሄ መሻትና የጋራ ደስታ መፍጠር ነው። በኔ ግምት የመኖር - የህይወት ትርጉሙ ይሽ ነው። የያንዳንዳችን ደስታ የሚለካው ለሰው ልጅ ደስታ በምናደርገው አስተዋፅኦ መጠን ይመስለኛል።

‹‹የምትለው ነገር ይገባኛል። ጭንቀትህም ይታየኛል። ግን ማወቅ ያለብህ አንድ ነገር አለ። የቀይ ኮከብ ጥሪ አላማ ግድ አይደለም። ሀቀኛ አብዮታውያን ካልተገደደ በስተቀር በሰው ህይወት ላይ ርምጃ አይወስዱም። ሁሉም ነገር ለሰው፥ ከሁሉም በላይ ሰው ነው፥ የሀቀኛ ታጋዮች አላማ። ስለሆነም፥ አብዮት የሚካሄደው ለሰው መሆኑን በቅድሚያ ማወቅ አለብን። አላማቸው ህይወትን መንከባከብ፥ ከሰው ልጅ ደስታ መሻት ነው። ግድያ ምንጊዜም ቢሆን አላማቸው አይደለም።›› አለው እምአእላፍ አንድ ቀን ያለውን አስታውሶ። ‹‹እና፥ የባሰ አደጋ ውስጥ ሳትወድቁ ላንጋግራችሁና የሰፊው ህዝብ ወገን

እንድትሆኑ ላግዛችሁ አስቤ ነበር። ጌቶችም የደህቁትን መሳሪያ እንዲያስረክቡና በሰላም እንዲኖሩ ለመምከር ፈልጌ ነበር። ከዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ከፍተኛ የመንፈስ ጭንቀት አሳልፌአለሁ። ሆኖም፥ አብዮቱ ሀሊናዬ እስከሆነ ድረስ ለአብዮቱ ሀልውና የማልወስደው እርምጃ የለም...

‹‹እባክህን ሂሩት ያለችበትን ንገረኝ። ህይወትዋ አደጋ ላይ ነው!›› ያለው።

‹‹ያለችበትን ቦታ እንዴት አድርጌ ልነግርህ እችላለሁ?››

‹‹ለምን አትችልም?››

‹‹ምክንያቱም የሰዋን ህይወት አድናለሁ ብዬ ሌሎቹን ለአደጋ ማጋለጥ ይሆናል።››

‹‹አላማችን ግድያ አይደለም እያልኩህ! ደም የጠማን ሰዎች አይደለንም። የኛ ጥም ፍትህ፥ እኩልነትና ነፃነት ነው።›› አለው ብስጭት ብሎ።

‹‹አዎን፥ አንተ እንዲህ ትላለህ። ግን ላእከን አታውቀውም። ሰይጣን ነው።››

‹‹ማን ነው ላእከ?››

‹‹ከሱ ጋር ናት። በዋዛ እጁን የሚሰጥ አይደለም። በህይወቱ የቆረጠ ሰው ነው። በህይወቱ የቆረጠ ስለሆነ፥ እኛ የምንወላውለው የህይወት ድንክች እንፈራለን። በፍርሃት እንታዘዘዋለን። እንደሱ ብሆን ምን ነበረበት? ግን አይደለሁም። ፈሪ ነኝ።››

‹‹ተሰማ! ፈሪ አይደለህም። በፍርሃት እንደ በግ መነዳትን ጠልተህ ነፃነትህን ለመሻት እዚህ መምጣትህ ደፋር አድራጎት ነው›› ሲል፥ ተሰማ በእምቢታ ራሱን ሲነቀንቅ ስላየው፥ ‹‹እውነቴን ነው። እኔ ላታልልህ አይደለም በእምቢታ ራሱን ሲነቀንቅ ስላየው፥ ‹‹እውነቴን ነው። እኔ ላታልልህ አይደለም ይህን የምለው። ከማታምንበት ነገር ደፍረህ መውጣት ጀግንነት ነው›› አለው።

‹‹ትናንት ማታ ለእህቴና ለተፈራ አሁን ያልከውን ስነግራቸው ነበር። ግን ራሴን ሳታልል ነው። በመሰረቱ ፈሪ ነኝ። አየሁ ፍርሃታችንን ለመሸፈን ምክንያት እንፈጥራለን።››

‹‹ግን እኮ ያልገባህ ነገር አለ ተሰማ። ላእከ ሰይጣን ነው ካልክ በየአለቱ በስንት ሰዎች ህይወት ላይ የሚፈርድ መሆኑን አትርሳ። በአደጋ ላይ ያለው የሂሩት ህይወት ብቻ አይደለም። የብዙ ንፁሃን ሰዎች ህይወትም ጭምር ነው። የምለው ይገባሃል? በዛሬው እለት ስንት የቀበሌ ጉዋዶች የወደቁ ይመስልሃል? ብዙ ናቸው። ከኛ ቀበሌም ዛሬ ጠዋት ላሊሶ የተባለ የአብዮት ጥበቃ ጉዋድ ከናንተ ቤት አጠገብ ተገድሎአል። በዚህ ቀበሌ አንድ የኢ.ህ.አ.ፓ. ህዋስ እንዳለ ደርሶበት ነበር። ባጭሩ ቀጨት። ቀበሌው በመሰየ ለባሾች ሲታሰስ ነው የዋለው። የተባለውን ህዋስ ለማግኘት ፈፅሞ አልተቻለም። የፈጠራ ወሬ ነው ብለው ትተውታል። ይህ ህዋስ ካልተደረሰበት በብዙ ሰዎች ህይወት ላይ የአደጋ ጥላ እንዳንጎበበ ይኖራል።››

‹‹ያንተም ህይወት አደጋ ላ ነው›› አለው ተሰማ፥ ‹‹ላሊሶ ዛሬ ተገድሎአል። ነገ ያንተ ተራ ላይሆን አይቀርም።››

‹‹አውቃለሁ።››

‹‹ታዲያ አትፈራም?››

‹‹ለምን አልፈራም? ግን ተልእኮ አለኝ። ካስፈለገ ሞትን ልቀበለው እችላለሁ።››

‹‹እኔም እንዳንተ የምሞትለት ተልእኮ ቢኖረኝ ደስ ይለኝ ነበር። ግን የለኝም። ባዶ ህይወት ነው የምኖረው›› አለና፥ በሀዘን ተውጦ አቀረቀረ።

‹‹የህይወት ተልእኮ ይኖርሃል። የህይወታችንን ተልእኮ ለማወቅ ጊዜ ይፈጅ ይሆናል። ተልእኮአችንን ባወቅን ጊዜ ግን፥ ህይወት ጨለማ አትሆንብንም። ትርጉም ይኖራታል። ግብዋ መቃብር አይሆንም።››

ተሰማ አንገቱን ቀና አድርጎ ደርቤን ትኩር ብሎ እየተመለከተው ‹‹ህይወትህ ለምን አደጋ ላይ እንደሆነ ታውቃለህ?›› አለው።

‹‹ግልፅ ነው›› አለ ደርቤ።

‹‹የለም ግልፅ አይደለም። ሂሩት ስለምትፈራህ ነው!!››

‹‹ለምን ትፈራኛለች?››

‹‹ስለምትወዳት። እንደምትወዳት እኔ አውቃለሁ። አድራጎትህ ሁሉ ለሰዋ ያለህን ፍቅር ቁልጭ አድርጎ ያሳየኝ ነበር። ቶሎ አንድ ትልቅ ቦታ ላይ ለመድረስ የምታደርገው ጥረት ሁሉ ለሰዋ ባለህ ምስጢራዊ ፍቅር ምክንያት መሆኑ ለኔ ስውር አይደለም። አውቃለሁ። ራስህን አለቃይተሃል። ስቃይህ ይገባኛል. . .

‹‹ግን ሂሩት ይህን ሁሉ አታውቅም ነበር። ገና ትናንት ማታ ነው ያወቀችው። እኔ ነኝ የነገርኩት። እናቱ ደነገጠች። በዚህ ላይ የኢ.ህ.አ.ፓ. ደሌዎች መሆናችንን አንተ እንደምታውቅ ስለምናውቅ ፍርሃት አደረባት። ተፈራ ደግሞ ሂሩትን እንደሚወዳት ታውቅ የለም? የምናደርገው ነገር ጠፋን። በነገራችን ላይ የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር ሆነህ መመረጥክን ወዲያውኑ ነበር የሰማነው፤ ግራ ገባን። አስገድደህ የምትወስዳት ስለ መሰላት ሂሩት በጣም ተጨነቀች። ተፈራም ሂሩትን አስገድደህ ስትወስዳት በሃሳቡ እየታው ቅናት አድሮበት ተናደደ።

‹‹ባንድ ጊዜ ዋነኛ ጠላታችን ሆነህ ታየኸን። እና ምን አደረግን መሰለህ? ልናስገድልህ ወደንን። ስህተት ነው። ባንድ ፊት ላንተ በሌላ በኩል ለእህቴ ሀሊናዬ እየተጨነቀ ነው። አእምሮዬ ልክ አይደለም።››

ደርቤ ተነሠ ዝም ብሎ ያዳምጠው ነበር። ተሰማ በሚናገርበት ጊዜ ሂሩት ከፊቱ መጥታ ትደቀን ነበር። አልፎ አልፎ የተከለከለች ፍሬ የሚል አሳብ ይመጣበት ነበር።

በረጂሙ ተነፈሰና፥ ‹‹አምን፥ እንዳልከው ጥሎብኝ እወዳታለሁ›› አለ። «የህልውናዬ ቅመም ለሱዋ ያለኝ ፍቅር ነው። ነጋም ጠባም ስለሰዋ ነበር ማልመው። በአሳቤ ከሰዋ ጋር ስነጋገር የምውልበት ቀን ነበር። ግን አሁን በጉ ፍቅር መሆኑ ገብቶኛል። አንድ እጂ ብቻውን አያጨበጭብም። ባንድ

አቅጣጫ የሆነ ፍቅርም እንደዚሁ ነው። ስቃይ ነው›› አለው፥ ፍኖት ስለ ፍቅር ያጫወተችውን አስታውሶ. . .

‹‹እና፥ መኖሬን እንኩዋን ለማታውቅ ሴት ይህን ያህል መጨነቁ ይገርማል። ምናልባትም እስዋን አግብቼ ትልቅ ሰው ለመሆን ፈልጌ ይሆናል። የጌቶቹን ልጅ አገባ፥ ትልቅ ሰው ሆነ ለመባል። ፊውዳላዊ ህሊና - አለ አይደል? ባለፈው ስርአት በዚህም በዚያም ብሎ ትልቅ ሰው ለመባል የማይንጠራራ ሰው አልነበረም። ያም ሆነይሁ፥ እወዳት ነበር። ልቤ ለሌላ ሴት ፍቅር ቦታ አልነበረውም።

‹‹ይግረምህና፥ እኔም ከትናንት ጀምሬ ስጨነቅበት የነበረ ጉዳይ ነው። ልቤ በሌላ ፍቅር መንደድ ጀምሮአል። የአብዮት ፍቅር በልቤ ውስጥ እንደ እሳት እየተቅጣጠለ ነው። አዲስ ተልእኮ፥ አዲስ ህይወት አግኝቻለሁ›› አለው፥ ፍኖት ያብዮትና ያገር ፍቅር ከሁሉም ይበልጣ ያለችውን አስታውሶ።

‹‹እና፥ ሂሩት የመጀመሪያ ፍቅሬ በመሆንዋ አልረሳትም። ለዘለአለም በልቤ ውስጥ ትኖራለች። ይህም በመሆኑ እድል አገኘሁ ብዬ ያለውዴታዋ በምንም ሁኑታ አላስገድዳትም ነበር። አውሬ አይደለሁም። ፍቅር ያለ ውዴታ እንደማይሆን አውቃለሁ። አንድ ሰው ለሌላው የስሜት ማርኪያ እቃ ሊሆን እንደማይገባው አምናለሁ።

‹‹እና፥ ግን አንድ እውነት ነገር ልንገርህ። ሂሩትን እወዳታለሁ። ይህንንም ስልህ በምወደው አብዮት ላይ ደባ እንዳትሰራ ቢቻል በምክር ለመመለስ፥ ባይቻል ግን እየወደድኩዋትም፥ ጊዜው፥ ሁኔታውና ስፍራው የሚጠይቀውን ማናቸውንም እርምጃ ልወስድባት ቆርጬ ነበር። ባንተም ላይ እንደዚሁ። አሁንም አቅዋሜ ከዚህ የተለየ አይደለም›› አለው ብስጭት ብሎ።

‹‹እና፥ ያለችበትን ቦታ ብትነግረኝ ከጥፋት ልናድናት እንችላለን። እንድትኖር ነው እኔ የምፈልገው። የሰውን ልጅ ማሰቃየትና መግደል የአብዮቱ አላማ አይደለም›› አለው።

‹‹ምን እንጠብቃለን ታዲያ? ተከተለኝ›› ብሎት ተያይዘው ወጡ።

ምእራፍ ፲፬

ደርቤ አስር ያህል የአብሮት ጥበቃ ጉዋዶችን አስከትሎ ከተሰማ ጋር ተያይዘው በወጡበት ወቅት፥ ጌታቸው የሸዋሉል ከእሚቴ ቡና ቤት ወጥቶ ቤቱ ደረሰ። ብዙ ጊዜ አብሮት የኖረው ዘበኛው የውጭውን በር በፍጥነት ከፍቶለት ከዘጋ በሁዋላ፥ ጌታቸው የመኪናውን ሞተር ሳያጠፋ ሮጦ ደረሰበት።

ጌታቸው መኪናውን አቁሞ ሊወርድ ሲል ተንደርድሮ ሄደ ያዘው። ጌታቸው እንደ መደንገጥ ብሎ፥ ‹‹ምን ሆነሃል?›› አለው።

ዘበኛውም በበኩሉ ደንግጦ ፊዞ ቀረ። ከጥቂት ጊዜ በሁዋላ ነበር ነፍስ ገዝቶ ‹‹የለም እ. . ልደግፍምት ነበር›› በማለት አድራጎቱን ለማስረዳት የሞከረው።

ጌታቸው ገባው። እንድ ብር አውጥቶ ጉርሻ ሰጠው። አልሰከረም ነበር። በዚህ ለስት ራሱን ችሎ በትክክል ሲራመድ ዘበኛው አይኑን ለማመን አቅቶት ዝም ብሎ ይመለከተው ነበር። ጌታቸው ፊዞ የቀረውን ዘበኛ ትቶ ወደ ቤቱ ገባ።

ባልዋ ያለ ዘበኛ ድጋፍ በር ከፍቶ ሲገባ በማየትዋ ትእግስትም እንግዳ ነገር ሆኖባት በመገረም ከእግር እስከ ራሱ ትመለከተው ጀመር።

እንባዋን ጠራረገችና ፈገግ ብላ፥ ‹‹አዲስ አበባን ድርቅ መታት እንዴ?›› አለችው።

‹‹አዲስ አበባን የመታት ቀይ ሽብር ነው። ቁጭ ብሎ በሰላም ለመጠጣት አልተቻለም! ምን ሆነሽ ነው ደግሞ የምታለቅሺው?››

‹‹እንኳን ቶሎ መጣህ! ሂሩት ጠፍታ ቤተሰቡ ሁሉ እየተሳቀሰ ነው። ተሰማም ቤት ውሎ ማምሻውን የሄደበት አልታወቀም።››

‹‹ሂሩት? ከቤተሰቡ ሁሉ የምወዳት እስዋን ነው። ህይወት አላት። መች ጠፋች?››

‹‹ከጥዋት ጀምሮ የለችም። እስዋን ፍለጋ ያልደረሱበት ቦታ የለም። እየተላቀሱ ናቸው።››

‹‹ያበሻ ልቅሶ መስማት አልወድም ባክሽ። ያስጠላኛል። ከመጮህ ሌላ የልባ ሀዘን የለበትም። ወዲያውኑ ደግሞ ሙት ደረቅ አይወድም በሚል ፊሊፕ ልቅሶው ወደ ድግስ ይለወጣል። ባህላችን ሁሉ በተቃርኖ የተሞላ ነው!››

‹‹ጥቁር ፈረንጅ!›› ብላ፥ እየሳሳ የሚሄደውን ጠጉርዋን ማበጠር ጀመረች። ጠጉርዋ ከመላላቱ የተነሳ የራስ ቅልዋ ይታያል።

‹‹ያበሻ ልቅሶ አልወድም። ሀዘኑ ላይ ላዩን ሆኖ ጥልቀት የለውም፥ ከጨኽት ሌላ!›› ካለ በሁዋላ፥ ‹‹ከንፈር እየመጠጡ ከመጉላላት ሌላ ምናለ! የሆድ ድርቀት ነው ትርፉ!›› አላት።

ጠጉርዋን በቁጭት ሙሾቅ አደረገችና፥ ‹‹ኢትዮጵያውያን ሆናችሁ ኢትዮጵያዊ የሆነውን ባህል ሁሉ ስትጠሉ ይገርመኛል›› ብላ በጠጉርዋ መርገፍ ተበሳጨችና፥ ‹‹ለዚህ ነው ጥቁር ፊረንጅ ያልኩህ›› አለችው።

‹‹ተቀፅላ ኢትዮጵያውያን ማለትሽ ነው?›› አላት፥ ከብዙ አመት በፊት በአዲስ ሪፖርተር መፅሄት ያወጣውን ፅሁፍ አስታውሶ። በዚያ ፅሁፍ ያስፈረው ሀሳቡ ብርንዶና ‹‹ኬክ›› በአንድ ሳህን አቅርበው ስለሚውጡና በአኑዋኑዋራቸው የለየላቸው ፌውዳሊስቶች በውጪዊ አስተሳሰባቸው ግን ስለ ምአራባውያን ፍልስፍና፥ የአኑዋኑዋር ዘይቤ፥ ስነ ፅሁፍና የፓርላማ ዲሞክራሲ በየቡና ቤቱ የቆጡን የባጡን፥ ስለሚቀባጥሩ ዘመናይ ኢትዮጵያውያን፥ ከስልጣኔ ጋር የሚያገናኛቸው ነገር ቢኖር፥ ያስሩት ክራባት ነው፥ በነገራችን ላይ የሰው ወርቅ አያደምቅም፥ የሚያብለጨልጭም ነገር ሁሉ ወርቅ አይደለም: የሁዋላ ቀርነት ትክክለኛ ትርጉም የአለምሮ ሁዋላ ቀርነት ማለት ነው›› የሚል ነበር።

ትእግስት ማበጠሪያዋን ከሶፋው ላይ ጥላ በእድዋ የሳሳውን ጠጉርዋን አስተካክላችና፥ ‹‹ተቀፅላም በለው ምን፥ ያው ጥቁር ፊረንጅ ማለት ነው›› ብላ፥ በጠጉርዋ መሳሳት በራስ ቅልዋ መታየትና በፊትዋ መጨማደድ ተበሳጭታ፥ ‹‹ያገራችንን ባህል መናቅ ራሳችንን እንደ መጥላት ይቆጠራል። ተምረናል የምትሉት አበሾች ፊረንጅም አበሻም አይደላችሁም፥ ጥቁር ፊረንጅ ናችሁ። ቆዳችሁ ጥቁር አስተሳሰባችሁ ዝንጉርጉር። ምንም ረብ የላችሁም። ረብ የሌላችሁ መሆናችሁን ስምታውቁ ራሳችሁን ትጠላላችሁ። የውስጣችሁ ባዶነት ያስጠላችሁአል። እና፥ ከእውነት ለመሸሽ ትሞክራላችሁ. . .

‹‹በመጠጥ ብቻ ማለቴ አይደለም። የውስጣችሁን ባዶነት ለመሸፈን አበሻን ፊሪ ህዝብ - እ - አዝማሪ ቆሞ፥ በለው በለው እያለ እየፎከረና እያቅራራ ናላውን አዙሮ ካላሳበደው በቀር የማይዋጋ ህዝብ. . .እ . . ተንኮለኛና ራሱን የሚወድ ህዝብ - ለራሱ ጥቅም ሲል በወንጉ ራሳ ላይ ተራምዶ የሚሄድ አይነት ህዝብ አድርጋችሁ ትመለከቱታላችሁ. . .

‹‹ግን ፊሪ ተንኮለኛ፥ ራሱን ወዳድና ስግብግብ ጉዋደኛውን እንደ ጅብ ከሁዋላ የሚበጭቅና የሚወጋ ማን ነው? ብትለኝ ተምረናል የሚሉት ጥቁር ፊረንጆች ናቸው!›› አለችው።

ጌታቸው ሲጃራ አውጥቶ አቀጣጠለ። ጉሮሮው ደርቆ ሊስነጠቅ የደረሰ መሰለው። መጠጥ አማረው። ንግግሩዋ አጥንቱ ድረስ ዘልቆ ተሰማው።

‹‹እኔም ጭምር?›› አላት::

‹‹አንተም ጭምር!›› አለችው::

ጉሮሮው ደርቆ በጣም ስላስፈለገው፥ ‹‹እዚህ ቤት የሚጠጣ ነገር አለሽ?›› ብሎ ጠየቃት. . .

ትእግስት ብልጭ ብሎባት፥ ‹‹የቡዋንቡዋ ውሃ አለልህ!›› አለችና፥ ‹‹እሱም ቢሆን ሊቆረጥ ነው›› ብላ ነገረችው፥ ስለ ቴሌፎን መብራትና ውሃ ሂሳብ የደረሱዋትን የመጨረሻ ማስጠንቀቂያዎች እያስታወሰች::

ያለባቸውን የሁለት ወር የቤት ኪራይ ውዝፍ እዳም አልረሳችም:: ወይዘሮ አምሳለ ጤፍ ባይልኩላት ኖሮ፥ ቡሀቃዋ ባዶ እንደሚሆንም ትዝ አላት:: ‹‹ብሩም መቅኖ የለው:: በዚህ ላይ የእቃ ዋጋ እሳት ሆኖአል:: የደላው ሙቅ ያኝካል አሉ:: ደግሞ መጠጥ ብሎ ነገር›› በማለት ስታስብ ቆየችና፥ ‹‹አንተ ደልቶሃል ልጄ›› አለች::

ኢኮኖሚያዊ ችግር ቤታቸውን እንደ ነቀዝ እየቦረቦረ በመሄዱ ሚስቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መነጫነጭ መጀመርዋን ሳያጤን አልቀረም:: ሞቅ ብሎኝ ብመጣ ኖሮ አትነተርከኝም ነበር ብሎ አሰበና፥ ‹‹ትንሽ መጠጥ ቤት ውስጥ ያለ መስሎኝ ነበር›› አላት::

ውስጥ ውስጡን የሚባሉት በኑሮአቸው ላይ በደረሰው የኢኮኖሚ ቀውስ ብቻ አልነበረም:: ከፉኛ ብስጭት ብላ፥ ‹‹አዎን ምን ጠፍቶ:: ባንተ ቤት ሁሉም ነገር ሞልቶአል:: ይህ ቤት እኮ ላንተ እንደ ሆቴል ቤት ነው::

‹‹ጠዋት ትወጣለህ፥ በውድቅት ትገባለህ:: ደህና ማረፊያ ሆቴል አግኝተሃል:: እኔ ደግሞ ላንተ እቃ ነኝ:: በፈለግኸው ጊዜ የምጎተት እቃ:: አንተ ምን ታደርግ:: እኔው ነኝ ራሴን በራሴ የገደልኩ:: ገረድ እንኩዋን ዛሬ መብት አግኝታለች:: እኔ ነኝ እቃ ሆኜ የቀረሁት›› አለች::

ጭላጭ ውስኪ ለመፈለግ ቡፌውን ከፈተ:: ጭላጭ ውስኪ በማግኘቱ ደስ አለው:: ጠርሙሱን አንጠፍጥፎ ቀዳና ብዙ አምቦ ውሀ ጨምሮበት የደረቀ ጉሮሮውን አረጠበና፥ ‹‹ከስንት ዘመን በፊት የረሳነውን ንትርክ አሁን መጀመርሽ ምን ይባላል?›› አላት::

‹‹አንገፈገፈኝ በቃ!›› አለችው ጆሮ በሚበጥስ ድምፅ::

‹‹ከእንግዲህ ለማዳ የቤት ውሻ ልሆንልሽ አልችልም!›› አላት ረጋ ብሎ፥ ለድምፁ የግል ጥልቀት በመስጠት::

‹‹እኔም ከተኩላ ጋር መኖር እንግዲህ በቃኝ!›› አለችና፥ ከቦርሳዋ ውስጥ ትንሽ መስተዋት አውጥታ ፊትዋን ተመለከተች። ፊትዋ አስጠላት፤ ይህችስ የማውቃት ትእግስት አይደለችም በማለት ብስጭት ብላ፥ ‹‹ዛሬ በጣም አሞኛል›› አለችው፥ መስተዋት ባየች ቁጥር ህመምዋ ይነሳባታል።

ለጌታቸው እንግዳ ነገር አልሆነበትም። ስለ ህመምዋ ላለመሰማት ወሰኖ ውስኪውን ተጎነጨ። ሶስት መቶ ስድሳ አምስት ቀን በየቀኑ ደግሞ ሃያ አራት ሰአት ሙሉ ስለ ህመምዋ ስታወራ፥ ህመምዋን ስታዳምጥ ነበር የምትኖረው። ልብዋ፥ ጨጉራዋን፥ ራስዋን፥ ኩላሊትዋን ጊዘትዋን - ከእግር ጥፍርዋ እስከ ራስ ጠጉርዋ የማያማት ነገር የለም። በሽታዋ ደግሞ እንደ አየሩ ሁኔታ በየቀኑና በየእለቱ ይለዋወጣል። ካለ ህመም ደግሞ ሌላ ወሬ የላትም። የምታወራው ወሬ ሁሉ በህመም ተጀምሮ በህመም ያልቃል። በሚያውቁዋት ሰዎች ዘንድ ትእግስተ መጣልዋ ቀርቶ ‹‹ህመምተኛዋ›› እየተባለች መጠራት ጀምራለች።

‹‹የእርድና ጣጣ!›› አለ ጌታቸው በልቡ፥ ውስኪውን እየተጎነጨ። ሲጃራውን ወደ ውስጥ በሃይል ሳበና፥ ‹‹ከኔ የምትፈልገውን ርህራሄና ፍቅር ሁሉ ልቤ ሲያንቆረቁርላት ቢችል ምን ነበረበት፥ ግን ልቤ ድንጋይ ነው! ምን ላደርግ እችላለሁ›› እያለ ሲያሰብ ቆየና፥ ‹‹በመከላችን አንድ ልጅ ቢኖረን ምን ነበረበት›› ብሎ ተመኘ። ግን አልጠላትም። ራሱን ነበር ያማረረው።

ላንዳፍታ የድሮ ውበትዋ መትቶ ከፊቱ ድቅን አለበት። የውበት ዛፍ ነበረች።

ሰው በብዛት በሚገኝበት ስፍራ መታየት መጥላት ከጀመረች ቆይታለች። ድሮ እዩኝ እዩኝ በማለት በሰዎች መካከል ስትውረገረግና ስታሸበርቅ እንዳልነበረች ሁሉ! በጠጉርዋም፥ በአለባበስዋ በፊትዋ መጨማደድና መጠባበስ የከፋት መሆንዋን ልትደብቅ አልቻለችም። የበሽታ ጭምብልዋን (ማስኩዋን) አትልቃ፥ ‹‹ተነስ እንሂድ›› አለችው።

‹‹ምን ለማድረግ? ቁጭ ብለን ከንፈራችንን ስንመጥ ለማምሽት?›› አላት።

‹‹ከቤተሰቡ መለየት የሰብንም። ተነስ እንሂድ›› አለችና የእጅ ቦርሳዋን ይዛ ብድግ አለች።

ጌታቸው ያለ ውዴታው ተከትሎአት ወጣ. . .

አራት ሲቀርብ ነበር ጌታቸውና ትእግስት የደረሱት። የድግስ ቤት መስሎ ነበር። በማንም ፊት ላይ የሀዘን ስሜት አይነበብም። ስጋው በያይነቱ ይቀርባል፥ ጥሬ ስጋ፥ ቅቅል ስጋ፥ የተጠበሰ ስጋ፥ ከትፎ፥ አልጫ ወጥ፥ ቀይ ወጥ። ጌታቸው

ተንሸገሸገ። አበሻና አውሬ አንድ ናቸው፥ ያለ ስጋ አይኖሩም፥ የሚል አሰብ መጣበት።

ወይዘሮ አምላለ መጡና፥ ‹‹መቼም እህል ደመኛ ነው። ባይሆን ይህን ጠጣ›› ብለው ቀድተው ሰጡት።

ውስኪውን ይዞ ቦታ ፈለገና ቁጭ አለ። እንዳጋጣሚ ከሚያውቃቸው ሁለት ሰዎች መሃከል ነበር የተቀመጠው። አንደኛው ሀኪም ሲሆን ሌላው ጠበቃ ነበር። ሰላምታ ከተለዋወጡ በሁዋላ፥ ‹‹ድግስ ቤት ሆኖ የለም እንዴ?›› አላቸው ጌታቸው።

‹‹ያበሻ ልማድ በየምክንያቱ ተሰባስቦ መብላት ነው። ለሽርሽር ወጣ ሲሉ አንኩዋን አገልግል አይለያቸውም። ከመብላት ሌላ ደስታ ያለ አይመስለንም። እዚሻ ከጧ ሶስት አራተኛውን የሚወጣው ለምን ይመስላችሁአል? ለምግብ ነው›› አለ አንደኛው።

‹‹ለዚያውም ስጋ ብቻ! የጠም ቀኖች ባይበዙማ ኖሮ አንድም ክብት አይተርፈንም ነበር!›› አለ ጌታቸው።

ሁለቱም ጌታቸው የሚናገረውን ለመስማት የተቸገሩ መሆናቸው ያስታውቃል። እጁ መንቀጥቀጥ የጀመረው ሀኪም ሰውነቱን ለማረጋጋት እየሞከረ ‹‹ሽሮ የሚያርባቸው ወገኖች መኖራቸውን አትርሱ። እናንተ የምታወሩት ስለ ሞጂዎችና የሞጂዎችን ጠባይ ስለ ወረሱት ወገኖች ነው›› አላቸው።

‹‹ሁሉም ካገኘ ያው ነው›› አለ ጠበቃው።

‹‹አምን›› አለ ጠበቃው፥ ‹‹ከመሬት እዋጅ ወዲህ ገበሬው ያመረተውን ራሱ መብላት ጀምሮአል። የእህል እጥረት አንዱ ምክንያት የሆነው ምን መሰላችሁ? የገበሬው ፍጆታ ነው። በአጠቃላይ ሆዳችንን እንወዳለን።

‹‹መቼ መውደድ ብቻ ሆነና! የህልውናችን ማእከልም ሆድ ነው። ሰው ሊናደድ፥ አንጀቱ ደበነ ወይም ሆዱ አረረ፣ ሲያዝን ወይም ሲጨነቅ፥ አንጀቱን ባላው፥ አንጀቱ ተላወሰ፥ ሆዱን ባርባር አለው! ከውሳኔ ሲደርስ፥ አንጀቱ ቆረጠ! ትእግስት ሲያሳይ - ሆደ ሰፊ ነው፣ ማሺንክ ሲሆን፥ ሆዱ አይገኝም፣ ሲወድ፥ ካንጀቱ ይወዳል፣ ሲጠላም እንደዚሁ! አንዱ ሌላውን ማሞንት ሳይችል፥ ሆድ ለሆድ ይተዋወቃሉ፣ ብቻ ምናለፋችሁ! ስናስብም፥ ስንወድም፥ ስንጠላም፥ ስናዝንም፥ ቂም ስንይዝም፥ ብልጥ ስንሆንም፥ ሁሉም በሆዳችን ነው!. . .››

‹‹ተረቶቻችንም ከሆድ አይርቁም። - ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል። እስቲ ጨምሩበት።››

‹‹ሆድ ሰባሰው ማጭድ አታውሰው›› አለ ሀኪሙ። ‹‹አሮ ሆዴ ተከኖ ሆዴ ፍምም አልወረደው፥ እህል እየበላ ውሃ እያበረደው!››

‹‹ዶክተር ተናደሃል መሰለኝ! ይህ ተረት በምን ትዝ አለህ ጃል?›› አለው ጠበቃው።

‹‹ምን ነው አልናደድ? ድሬሰሮች ሲፈነጩብኝ! ሀኪሞች ብጣሽ መረቀት ላይ የማይነበብ ነገር ጫር ጫር ከማድረግ ሌላ ምን ስራ አላቸው?! በማለት ማውገዝ ጀምረዋል። ተው ቻለው ሆዴ እያልኩ ነው። የሰው ሆድ ከውቅያኖስ ይሰፋል ይሉ የለ?››

‹‹ካንጀት ካለቀሱ እንባ አይገድም አይዞህ›› አለው ጠበቃው።

‹‹አንተም አትጨነቅ። አምላክ የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም። ጉሮሮ ከሆድ ጋር የተያያዘ ነው እኮ! የምትወክላቸው ፊረንጆች ሁሉ ኩባንያዎቻቸውን ዘግተው ቢጠፉ፥ ነገር ከኢትዮጵያ አይጠፋም! አንዱ ብሄራዊ ስራችን ነገር መሳንሳን ነው። ፍርድ ቤቶች አሁንም በነገረተኛ ጢም አንዳሉ ናቸው። ነገርና ነገረተኛ እስካሉ ድረስ የነገረ ፈጅ ሆድ ማሰብ የለበትም። በሆዳችን ስለምናስብ ነው እኮ ጭንቅላታችን የማይሰራው።››

‹‹ነገራችሁ አንጀቴን እያረሰው ነው›› አለ ጌታቸው።

‹‹አንጀት ይቆርጣል በል እንጂ!›› አለ ጠበቃው።

‹‹ማሰብስ የሌለበት የሀኪሞች ሆድ ነው። ሆድ ሲያውቅ ደሮ ማታ እሱ! ከነገረተኛው በሽተኛው አይደለም እንዴ የሚበልጠው? ዛሬ እኮ የአግዜር ሰላምታ ቀርቶአል። የሚቀድመው ጥያቄ፥ ያ ሀመምም እንዴት ሆነ? ተሻለውት? ተመረመሩ? ጠበል ሄዱ? የሚል ነው። እንግሊዞች ስለ አየር ጠባይ ቀኑን ሙሉ ሲወያዩ እንደሚውሉ ሁሉ፥ የኛው ሰው ቀኑን ሙሉ የሚያወራው ስለ በሽታ ነው . . .››

‹‹እዚህ ቤት ውስጥ ዞረን ብናዳምጥ፥ አርግጠኛ ነኝ፥ አብዛኛው፥ በተለይም ሌቱ፥ የሚያወራው ስለ በሽታው ነው። ሌላ ወሬ የለም! ነገረተኛ አልከው ዶክተር? በሽተኛ ነው እንጂ የሚበዛው። የግል ክሊኒክ አልከፈትክም መሰለኝ። አንጀትህ ይርስ ነበር።››

‹‹የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል!›› አለ። ‹‹ጎመን በጤና ብዬ ዘጋሁት እንጂ ነበረኝ። ይነግዳል ተብዬ በየቀኑ በድሬሰሮች ከምወነጀል መዝጋቱን መረጥኩ - ሆድና ጀርባ አታድረገኝ አሉ - ጊዜው ሁሉም ነገር ሆድና ጀርባ አድርጎታል።›› አለና እየተከዘ በሚንቀጠቀጥ እጁ ውስኪውን አንስቶ በአንድ ትንፋሽ ጨለጠ፥ ‹‹የኢትዮጵያ ሆድ ሽንጉርጉር ነው። ጋዜጠኞችንም ወልዳለች!›› አለ።

የቀይ ኮከብ ጥሪ

"እንዴት?" አለ ጌታቸው።

"እነሆድ አምላኩ - በበሉበት የሚመሁ (ቀሰ በግእድ፣ አህያ ጫኖ ይላላል) ይባላል ከንተረቱ። ሰጋዚጠናችም ቢሆን ችርጉም ይሰጣል... ሴሉ ነገሩን ሳያወጣርስ፡ ተከታታይ ተከብ መስማት ስለ ጀመረ ሁሉም ምክኑኛ ወራውን አቁሞ ያዳምጥ ነበር።

"ሆድህ ተሸበረ መሰለኝ" አለ ጌታቸው። የተናገረውን የሰማ አልነበረም። ቤቱን ፀጥታ ስለ ዋጠው፡ ጎረቤት የሚቀልጠው የሰርግ ዜፈን ፀጥታውን ጥሶ ይሰማ ጀመር...

ጌታቸው ሚስቱን በአይኑ ፈለጋት። ካንዲት ሴት ጋር አፍ ለአፍ ገጥማ ታወራለች። ሴትዮዋ የሀዘኔታ መልክ ልታሳያት ብትሞክርም፡ የትለገሰት ወሬ የለሽችት ትመስላለች። በሀመም ወሬ ይሆናል ያለለችችት ብሎ አለበና በመናደድ ፈንታ ለሚስቱ አዘነላት። ከቤት ከመውጣታቸው በፊት የተናገረችው ትዝ አለው...

ጥቁር ፈረንጅ... ከዚህም ከዚያም ያልሆናችሁ... ሬብ የሌላችሁ... ውስጠ ባዶ... ራሳችሁን ወዳድ... እና ከውነት ለመሸሽ ተፈልጋለችሁ... ታላትዋን አንድ በአንድ አስታወሰ።

"አውነት ነው" አለ። ውስጠ ባዶነቱ ታየው። "ይህን ሁሉ ዘመን... ባዶ ህይወት... ከንቱ ህይወት... አያለ ሲያስብ ግምሻውን እሜቴ ውና ቤት ውስጥ ያሳለፈው ጊዜ ትዝ አለው። እንደ ሽምበቆ ውስጡ ባዶ የሆነ ህይወት... ግን ከአንግዲህ ምን ልሆን እችላለሁ? አኔ አኔ ነኝ። ሌላ ልሆን አልችልም... ጨለማበት...

ድንገት አይጦች ጭንቅላቱ ውስጥ መሽሎክሎክ ጀመሩ። እንሰሱን ይሸትላሉ - አይጦች - ምስጦች - ባፍንጫው ቀዳዳዎች ውስጥ ይለገስጋሉ። ጭልፊቶች አይኑን በጥፍራቸው ያፈላሉ። ጉንዳኖች ነጭ አጥንቱ ላይ ይተራመሳሉ። ውሾች አንጀቱን ይጎትታሉ። ጥምብ አንሳዎች ስጋውን ይበጭቃሉ። ጉንትል - ጉትት - ቡጭት...

መላእክት ዳንኪራ ይረግጣሉ - እምቢልታ እየነፉ። ክንፎቻቸው ሲጋጩ እሳት ይወጣል። ብልጭ ቦግ እያለ። ዋሽንት - የአረኛ ዋሽንት - ለጥ ያለ ሜዳ - ሳር የለውም - ከብቶች አፈር ይግጣሉ - ጭራ - ሆታ - ብዙ ሰዎች - ራቁታቸውን - ብልታቸው ላይ ቃጭል - ራሳቸው ላይ የጸርት እሾህ...

አዲስ አበባ ይፈነዳል - እሳቱ ይንቀለቀላል - ይንቦገቦጋል - አይጦች ብዙ አይጦች ከየቤቱ ወደ መንገድ ይወጣሉ - እሳት ይነድባቸዋል - ፀጉራቸው ይቃጠላል - ቆዳቸው ይጨሳል - ሲጮ፡ ሲጥ እያሉ አውራ መንገዶችን ሞልተው ይሮጣሉ - እየነደዱ...

ሳር ቤቶች ይነዳሉ - እንደ ችቦ - ፎቆች ይደረመሳሉ - ሰማዩ ተሰንጥቆ እሳት ይተፋል - ጨረቃ ትፈነዳለች - ከዋክብት ይረግፋሉ እንደ ጤዛ. . .

ያዲስ አበባ መጠጥ ቤቶች መደርደሪያዎች ተንኮታኩተው ይወድቃሉ - የውስኪ ጠርሙስ - ያረቂ ጠርሙስ - የቢራ ጠርሙስ እንከሽከሻቸው ይወጣል። ከውስጣቸው የሚወጣው ፈሳሽ መጀመሪያ ትንሽ ጅረት - ቀጥሎ ትልቅ ወንዝ - በመጨረሻ የረጋ የደም ባህር ይሆናል - ያዲስ አበባ ሰገራዎች በሙሉ ይፈነዳሉ።

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ለሁለት ተሰንጥቆ ሲያበቃ ይደረመሳል - የማተሚያ መኪናዎች ይፈነዳሉ ንፋስ የወደሳቸው ወረቀቶች ሰማዩን ይሞሉታል - ጋዜጠኞች ከሰባተኛ ፎቅ ተወርውረው ይፈጠፈጣሉ - አንጎላቸው ከአስፋልቱ ላይ እንደ ንፍጥ ይለጠፋል። የጣንያን ሬሳ ሲቃጠል፥ ሲጋይ፥ ጭንቅላቱ አይኑ ሲፈነዳ - ፍፃሜ! የጋዜጠኛ ፍፃሜ! ወሬ የለም። የአለም ፍፃሜ! የስልጣኔ ፍፃሜ!

ቼ በለው ያገሬ አፈር። ሳጥናኤል ሽህ በክንፉ። ሽህ በጥርሱ። ሽህ በጥፍሩ። ቼ በለው ሲዘጋ የመንግስት ሰማያት በር። ቼ በለው እግዜር አኩርፎ ሊቀመጥ ዙፋኑ ላይ። ቼ በይው ያገሬ ሴት፤ ደረት ጥለሽ - ዋይ ዋይ - ውይ ውይ። ቼ በለው ያገሬ አፈር. . .

ጌታቸው ከተቀመጠበት ድንገት ብድግ ሲል አጠገቡ ተቀምጠው የነበሩት ሰዎች ደነገጡ። በቀጥታ ወደ ሚስቱ ሄዶ፥ ‹‹ተነሽ እንደንስ›› አላት። ደንግጣ ‹‹በሞትኩ ምን ማለትህ ነው?›› አለችው።

አፍራ ግራና ቀኝ ተመለከተች። ያላፈጠጠባቸው አይን በቤቱ ውስጥ አልነበረም።

‹‹እንደንስ ነው የምልሽ!››

‹‹እንዴ! የምን ጉድ ነው አሱ!›› አለችና አፍዋን ያዘች።

‹‹የሰርግ ዘፈን አይሰማሽም! ሰርግ ነው እኮ!››

‹‹ምን ማለትህ ነው ጌቱ?››

‹‹ዳንስ። የሞት ዳንስ። ዳንስ። ዳንኪራ›› አላት።

ወይዘሮ አምላለና ባለቤታቸው፥ ጠበቃውና ሀኪሙ እንዲሁም ሶስት ሌሎች ሰዎች ክብ ሰርተው ዙሪያውን ቆመው ነበር።

ሃይለኛ የራስ ምታት እንደ ያዘው ሰው ጭንቅላቱን በሁለቱም እጆቹ ጭምድድ አድርጎ ይዞ ከቆየ በሁዋላ፥ ‹‹ሁላችሁም ደንቆሮዎች ናችሁ። ጆሮአችሁ አይሰማም። ጨቨቱ አይሰማችሁም›› አለ፥ ድምፁን ከፍ አድርጎ።

አንዳንዶቹ ጌታቸው የሚሰማውን ጩኸት ለማዳመጥ ጆሮአቸውን አቁመው ነበር።

‹‹አድሃሪ! አድሃሪ! ሲሉ አልሰማችሁም! ቀበሌዎች፥ ውይይት ክበቦች ተሰብስበው አድሃሪ! አድሃሪ! ይላሉ። እንዴት ነው አድሃሪ የሚሉት። ለምን አድሃሪ ይሉኛ! እኔ ጌታቸው ነው ስሜ። አይደለም እንዴ፥ ቲጊ? እኔ አድሃሪ ነኝ እንዴ? . . .

‹‹አድሃሪ አድሃሪ እያሉ ለምን እንቅልፍ ይነሱኛል? መኝታ ቤት ድረስ እየሸቱ ቢሮዬ እየመጡ በየመንገዱ እየተከተሉኝ አድሃሪ! አድሃሪ! እያሉ ይጮሁብኛል። ነፃነት የለኝም እንዴ! በየግድግዳው ላይ፥ በየበሩ ላይ አድሃሪ! አድሃሪ! እያሉ በትልቁ በቀይ ቀለም የሚፅፉት እኔን ለመስደብ ነው? ቆይ ብቻ! ልክ አስገባቸዋለሁ - አንድ ባንድ!›› ብሎ እንደ ገና ራሱን ጭምድድ አድርጎ ሲይዝ ሀኪሙ ‹‹አይዞህ። አሁን ዝም እናሰኛቸዋለን›› እያለው ወደ ጉዋዳ ይዞት ሄደ።

ትእግስት እያለቀሰች ተከተለቻቸው። የተቀሩት በሀዘን ከንፈራቸውን ይመጡ ነበር። ሁሉም ከንፈሩን ሲመጥ ነበር የሚሰማው። ወይዘሮ አምላሉ አስር አስር ጊዜ ‹‹ጉድ ነው!›› ይሉ ነበር።

‹‹መርፌ ትወጋቸዋለህ?›› አለው ሀኪሙን ወደ ጉዋዳ ሲገቡ።

‹‹አዎን።››

‹‹እና ዝም ይላሉ?››

‹‹አዎን፥ ዝም ይላሉ።››

‹‹ሁለተኛ አድሃሪ! አድሃሪ! አይሉኝም?››

‹‹አይሉህም። ምን ቆርጦአቸው!›› አለውና፥ ሁለት ትናንሽ እንክብል መድሀኒቶች ከኪሱ አውጥቶ ሰጠውና እንዲውጥ አደረገው።

ጌታቸው መድሀኒቶቹን ከዋጠ በሁዋላ ‹‹ጩኸቱ ቆሟል እንግዲህ! አይደለም?›› አለው።

‹‹ቀጥ ብሎ።››

‹‹እና እንቅልፍ ይወስደኛል?››

‹‹ጭልጥ አድርጎ።››

ወይዘሮ አምላለ አልጋ ላይ ጋደም አለ። ሀኪሙ ወደ ትእግስት መለሰ ብሎ፥ ‹‹አይዞሽ አታልቅሺ። ምንም አይደል! የአእምሮ ጭንቀት አድሮበት ነው። እኔም አለብኝ። በዚህ መድሀኒት ነው የምኖረው። ይሻለዋል። በደህና ካሳደሩን ጠዋት አየዋለሁ›› አላት።

እንባዋን እየጠረገች፥ ‹‹ደህና የሚሆን ይመስልሃል?›› ብላ ጠየቀችው።

ጌታቸው እንደህፃን ልጅ ፊርቶ አይኖቹን ሲያቁለጨልጭ ልበ ኩሩ. . . ልበ ሙሉ. . . አትንኩኝ ባይ ባሌ እንዲህ ይሁን! ብላ አሰበችና እንደ ገና ስቅስቅ ብላ ማልቀስ ጀመረች።

‹‹በኔ ይሁንብሽ ደህና ይሆናል›› አላት ሀኪሙ።

‹‹እያየኸው! የሚናገረውን እየሰማህ?››

‹‹አእምሮውን የሳተ አይመስልሽ። አንዳንድ ተናዳጅ የሆኑ ሰዎች በጭንቀት ሁኔታ ውስጥ ለመሰራት ይቸገራሉ። የእሱም ችግር የተለየ አይመስለኝም። አይዞሽ ደህና ይሆናል።››

አላመነችውም።

ደርቤ ተኩስ እንዲከፈት ፍላጎቱ አልነበረም። በተሰማ ጠቁዋሚነት ሄደው እነሂሩት ካሉበት ኪዮስክ እንደ ደረሱ ማንም ሰው በምንም ሁኔታ ተኩስ እንዳይከፍት ጥብቅ ትእዛዝ ከሰጠ በሁዋላ ሁሉም ኪዮስኩን ከበው አደፈጡ።

የአብዮት ጠባቂ ጉዋዶች በደረታቸው ተኝተው ተገን ከያዙ በሁዋላ ከመካከላቸው አንዱ ድምፅ ማጉያ ይዞ ‹‹ሀሎ! ሀሎ! ሀሎ! እዚህ ኪዮስክ ውስጥ የምትገኙ ሰዎች! በሰላም እጃችሁን እንድትሰጡ አብዮታዊ ጥሪ እናቀርባለን›› የሚል ቃል አሰማ። እየቆየ ይህንኑ ቃል በመደጋገም ጥሪ ቢያቀርብም እድን ለመስጠት ብቅ ያለ ማንም አልነበረም።

የኪዮስኩ መብራት ድርግም ብሎ ጠፋ። በአካባቢው ያሉት ቤቶች መብራቶች አንድ በአንድ ድርግም እያሉ ሲጠፉ ይታይ ነበር። ፀጥታ፥ ፍፁም ፀጥታ ሆነ። ተሰማ እየጨመረ የሚሄደውን የልቡን ትርታ በደረቱ ተኝቶ ሲያዳምጥ ከቆየ በሁዋላ፥ ‹‹ምን የሚያደርጉ ይመስልሃል?›› አለው፥ ደርቤን።

ደርቤም የመንፈስ ርጋታ አይታይበትም። ‹‹ምን አውቃለሁ። ግን እዚሁ ከበናቸው ነው የምናድረው። በመጨረሻ መውጣታቸው አይቀርም። በየትም በኩል ሊያመልጡ አይችሉም። እጃቸውን በሰላም እንደሚሰጡ ተስፋ አደርጋለሁ።››

‹‹ላእከ ሰይጣን ነው ብየህ የለም? ቢሞት እጁን አይሰጥም።››

«ምን አይነት ሰው ነው እሱ?»

«ሰውን ቀርቶ ጥላውንም የሚጠራጠር ሰው ነው። ድሮም እንዲሁ ነበር። በዚያ ላይ ጡንቸኛ ስለሆነ ልጆች ሁሉ ይፈሩታል። እሱ ባሳደረብን ፍርሃትና በሂሩት የጀብደኝነት ስሜት ነው ተቆራኝተን የቀረነው። ወ.ወ.ኪ.ማ. ውስጥ በክብደት ማንሳት የታወቀ ነበር። እንዲህ አይምስልህ፣ በጡንቻው ሲኮራ። እንደሱ ሰውነቱን የሚወድ፣ ከራሱ ጋር ፍቅር የወደቀ ሰው አላየሁም። ታዲያ ይግረምህና ከሰው ጋር ሲደባደብ አይቼም ሰምቼም አላውቅም. . .

«አባቱ የታወቁ ክፉ ነፍጠኛ ነበሩ። ጥንት ባርያ ፈንጋይ አውሬ አዳኝ ነበሩ። በዝሆን ጥርስ ንግድ ነው የከበሩት። በጣልያን ጊዜ የጣልያኖች ቀንደኛ ባለሙዋል ነበሩ ይባላል። ሁዋላ የውስጥ አርበኛ ተብለው የፊታውራሪነት ማእርግ ተሰጣቸው። አብዮቱ ከፈነዳ ወዲህ ሸፍተው በስንት መከራ ታድነው ነው የተገደሉት። ልጁም እንዳባቱ አመፀኛ ነው። ቂም ይዞአል። ሀይለኛ ጥላቻ ያደረበት ይመስለኛል።»

«እስቲ እናያለን» አለ ደርቤ። «ከራሱ ጋር ፍቅር የወደቀ ሰው ሞትን የሚመርጥ አይመስለኝም። በጉራ ብቻ ይሆናል የሚኖረው።»

«የሰጋሁት ለሂሩት ነው» አለ ተሰማ። «ይኸኔ ምንም አደጋ አይታያት ይሆናል። ሁሉም ነገር ጨዋታ ነው የሚመስላት፣ ተፈራ ደግሞ ያሳዝነኛል። ለስዋ ሲል ነው እዚህ ጣጣ ውስጥ የገባው። ከስዋ ተለይቶ የሚኖር አይመስለውም። ያልታደለ ሰው።»

ደርቤና ተሰማ በደረታቸው ተኝተው በሚነጋገሩበት ጊዜ ላእከ ከኪዮስኩዋ ጉዋዳ እንደ ዳልጋ አንበሳ ማጅቱን አሳብጦ ይንጎራደድ ነበር። እጃቸውን አንዲሰጡ ከተጠየቁ ጊዜ እንስቶ አልተቀመጠም። ጠይም ፊቱ ላይ ሳብ ተንቸርፍፎ ይታያል።

ተፈራ እየደጋገመ፣ «የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል!» ይል ነበር። ቱ አሸቦ መስሎአል። ከንፈሩ ደርቆአል። ሰውነቱ በፍርሃት ርዶአል።

ከፍሉ ውስጥ የነበሩት ሌሎች ወጣቶችም በፍርሃት ተውጠው ነበር። ቂቶቹ እንባ አውጥተው ሲያለቅሱ፣ የተቀሩት ደግሞ የሚያደርጉት ነገር ፍቶአቸው ጠጉራቸውን ይነጨ ነበር። አንዳንዶቹ አይናቸው እስኪጎለጎል ድረስ ማፍጠጥ ሌላ ህይወት ያለቸው አይመስሉም። ሁሉም አመዳቸው ወጥቶአል።

ተፈራ እየደጋገመ፣ «የፈሩት ይሰርሳል. . .» ከማለት ሂሩት አቁዋረጠችውና፣ ቲጋ! ምን እንዳረጀ ሽክላ ያንኑ መላልሰህ ታነበንባለህ? ይልቅ ከዚህ ኖመልጥበትን ዘዴ አምጣ። ትልቁ ነገር ስለ አደጋ ማሰብ አይደለም። ቁም

ነገሩ አደጋ ሲመጣ እንዴት እንደምንቁዋቁዋመው ከማሰቡ ላይ ነው። እንወጣዋለን። ግን እንዴት እንደምንወጣው ማሰብ ለጊዜው አልቻልንም። ችግሩ እዚህ ላይ ነው›› አለችው።

ተፈራ አፉን ከፍቶ ትኩ ብሎ ለጥቂት ጊዜ ተመለከታትና፥ ‹‹የአደጋው መጠን አሁንም አልገባሽም መሰለኝ››፥ አላት ‹‹ቀልዱ አብቅቶአል፥ የኔ ውብ አልገባሽም እንጂ ከሞት ጋር እየተፋጠጥን ነው። በምትቀጥለው ሴኮንድ ወይም ደቂቃ ከዚህ አለም ላይ የለንም። ማየት፥ መስማት፥ ማሽተት፥ መዳሰስ፥ መቅመስ የለም! በድን እንሆናለን። ይታይሻል? አይታይሽም! . . .

‹‹እኔም እንዳንቺ አውር ነበርኩ። ካንቺ መለየት አቅቶኝ እንደ ጥላሽ ስከተልሽ ኖርኩ። እና ተከትዬሽ የት ደረስኩ? እዚህ። የጉዞአችን መጨረሻ ላይ ደርሰናል። መውጫ የለንም። ይግባሽ። እድሜ ላንቺ፥ መውጫ የለንም። እኔስ ከእንግዲህ ግድ የለኝም። መውጫ ካጣሁ ቆይቻሁ። ብቻ ላንቺ ይብላኝ ከእንግዲህ ድብብቆሽ ጨዋታ አብቅቶአል›› አለ።

የደም ስሮቹ ሁሉ ተገታትረው ነበር። ልቡ በአዲስ ድፍረት ተሞላ።

‹‹ለምን ወደ ሌላ ሀዋስ ደውለን እንዲደርሱልን አናደርግም? ከዚህ ለመውጣት ያለን እድል ይህ ብቻ ነው›› አለች ሂሩት፥ አንገትዋን ወደ ቀኝ መታ አድርጋ።

ላእከ ቆም አለ።

ጠጉሩን የተላጨ አንድ ወጣት የተዝረከረከውን አፍንጫውን በእጁ ጠረገና፥ ‹‹የሚያዋጣን በሰላም እጃችንን መስጠት ብቻ ነው! ቆሎ ሻጭ እናቴን ከችግር ላላወጣት መሞት አልፈልግም›› አለ።

የተቀሩትም እጅ በመስጠቱ ጉዳይ የሚስማሙ መሆናቸውን አንድ በአንደ ከገለፁ በሁዋላ፥ ላእከ ሁለት እጆቹን ወደ ሁዋላ አጣምሮ እንደ ቆመ አንገቱን ቀና ሳያደርግ፥ ‹‹እጃችሁን ብትሰጡ ለህይወታችሁ ምን ዋስትና አለ?›› አላቸው። ‹‹ምንም የለም፥ የምትሞቱበትን ቦታ ለመምረጥ ካልሆነ በስተቀር። ምርጫው ግን የቦታ ጉዳይ አይደለም። ተሰቃይቶ መሞት ወይስ በድንገት መሞት። ምርጫው እዚህ ላይ ነው።

‹‹እኔ በድንገት ቢገድሉኝ ይሻለኛል። ስቃይ አልችልም። ግን ሰዚሁ ሁሉ ያበቃን ማን ይመስላችሁአል? በጉዳዩ ላስብበት ነበር። እዚህ መሀላችን ከሀዲዎች አሉ። እነሱም እነዚህ ሁለቱ ናቸው›› ብሎ፥ ሂሩትና በተፈራ ላይ ሌባ ጣቱን ቀሰረ።

‹‹ምን ማለትህ ነው?›› አለችው ሂሩት፥ ትላልቅ አይኖችዋን አፍጥጣበት። ‹‹ፅጌረዳ ያለ እሸህ አይበቅልም። በእሸህ የታጠርሽ ፅጌረዳ ነሽ እ. . . ወንድምሽ የት ነው? አንቺስ ለደርቤ ደውለሽ በኮድ ምን እንደ ነገርሺው ማን ያውቃል? የተቀነባባረ ሴራ ነበር። አይደለም? አለበለዚያ ይህን ቦታ እንዴት ሊደርሱበት ቻሉ?›› አለና፥ ኮልት ሽጉጥ ከደረቱ መዞ ሂሩት ልብ ላይ ደገነ።

ሂሩት ፍንክች አላለችም። ቀልድ ነበር የመሰላት።

ተፈራ ዘሎ መሀላቸው ገባና፥ ‹‹እብድ አትሁን!›› አለው። ‹‹የተናገርከው ሁሉ የአጉል ጥርጣሬህ ነፀብራቅ ነው እንጂ ትርጉም የለውም። ይልቅ የእርስ በርስ ግጭቱን አቁመን ምን እንደምናደርግ በጋራ ብናስብ ይሻላል። ጊዜ የለንም። ተኩስ ከከፈቱብን በሁዋላ ምርጫ አይኖረንም።››

ላእከ በላብ ተዘፍቆ ነበር። ያፍንጫው ቀዳዳዎች እንደ ወናፍ ከፍ ዝቅ ሊሉ ይታያሉ። አይኖቹ የጋለ ብረት መስለዋል።

‹‹ተኩስ አይከፍቱም!›› አለ፦ ‹‹እጄን ለመያዝ ነው የሚፈልጉት። ገብቶኛል። አለቃይተው ሊገድሉኝ ነው ፍላጎታቸው። አይምሩኝም። ማናችንንም አይምሩም. .

‹‹የዚህ ሀዋስ አላፊና የዞኑ ኮማንደር መሆኔን አትርሳ። ቢያገኙኝ በቁመናዬ ነው ቆዳዬን የሚገፉት። እና ደግሞ ስቃይ አልችልም። ራሴን እንደማመልከው ታውቃለህ። አስቲ ይህን ሰውነት እየው። እየኝ። የአፓሉ ሰውነት ነው። ጥቁር አፓሉ!

‹‹በሰውነቴ ላይ እጃቸውን አያላርፉበትም! ከዚያ ቀድሜ ነው የምጨርሳቸው። ግን ከዚያ በፊት የውስጥ ጠላት መመታት አለበት። ከሀዲዎች፥ የባንዳዎች ሰላዮች ናችሁ ብሎ፥ በአፉ አረፋ መድፈቅ ሲጀምር፥ ተፈራ እደገኛነቱ ስለታየው ሂሩትን እየገፋ ወደ ሁዋላ አፈገፈገ።

ላእከ አውራ መስሎ ጥርሱን በመንከስ፥ ‹‹ሰላሮች! ሰላሮች! ጥቁር አፓሎ አይሞትም!›› እያለ ሲጠጋቸው፥ ተፈራ በፍጥነት ቢራታ ሽጉጥን አውጥቶ ተኮሰበት::

ላእከም አከታትሎ ተኮሰ:: ተፈራም ከመውደቁ በፊት ሁለት ጥይት አከታትሎ በደረቱ ለቀቀበት::

ሂሩት አንጀትዋን በእጆችዋ ደግፋ፥ ‹‹እኔ አላምንም! እኔ አላምንም! አምላኬ እባክህን ውሸት አድርገው!›› ስትል ከቆየች በሁዋላ፥ እጆችዋን ከሆዱዋ ላይ አንስታ ተመለከተች:: ትኩስ ደም በእጆችዋ ላይ እየተንጠባጠበ ይወርድ ነበር::

ቡልቅ ቡልቅ እያለ የሚወጣው ደም በጥቁር ሱሪዋ ላይ ኮለል ብሎ ሲወርድ አየችና፥ ‹‹መቼ ይህ ሆነና ነገሩ? ሰፈሩን ነበር እኮ በቀይ ልናጌጠው ያሰብነው:: አምላኬ ውሸት አድርገው! እውነት አይደለም:: እኔ አላምንም!›› እያለች ዘሞ ብላ ወደቀች::

ተፈራ በደሙ ውስጥ በደረቱ እየተሳበ ወደ ሂሩት ለመጠጋት የመጨረሻ ጥረት ካደረገ በሁዋላ፥ እንደ ምንም ብሎ እጅዋን ጨበጠና በደከመ ድምፅ ‹‹ሂሩት! ሂሩት!›› ብሎ ጠራት::

‹‹ተፈራ፥ እውነት ነው እንዴ? ንገረኝ!›› አለችው::

‹‹እውነት ነው ሂሩቴ:: ከሞት ጋር እየተፋጠጥን ነው:: አየዞሽ! ከጥቂተ ጊዜ በሁዋላ ሁሉም ነገር ያልፋል:: ለሚያፈቅሩን ሁሉ የሚቀረው ትዝታችን ብቻ ነው:: ከፍቅርሽ ጋር ወደ መቃብር መውረድ ደስታ ነው - ሂሩት! ሂሩት!››

‹‹ውሸት ነው በለኝ::››

‹‹እሺ ውሸት ነው:: በርቺ:: እኔም እበረታለሁ:: እኖራለሁ:: እኖራለሁ በይ›› አላት::

‹‹እኖራለሁ!››

‹‹አይዞሽ ትኖሪያለሽ:: አንድ ነገር ብቻ ልለምንሽ:: መቃብሬ ላይ አንድ ፅጌረዳ አበባ ትከይልኝ:: እንዳትጠወልግም ተንከባከቢያት:: ይህን ብቻ ነው የምጠይቀሽ:: እሺ?››

እጁን ጠበቅ አደረገችው::

ተፈራ በድንጋጤና በፍርሃት ተውጠው አፋቸውን ከፍተው ወደሚመለከቱዋቸው ወጣቶች ፊቱን አዞረና፥ ከወደቀበት በግድ ቀና ብሎ ‹‹ሁላችሁም እጃችሁን ወደ ላይ!›› አላቸው።

ታዘዙት።

‹‹ፊታችሁን ወደ ግድግዳ አዙራችሁ፥ እጃችሁን ወደ ላይ አድርጋችሁ ተጠግታችሁ ቁሙ›› አላቸው።

እንዳዘዛቸው አደረጉ . . .

ከኪዮስኩ ውስጥ ተኩስ እንደ ተሰማ፥ ‹‹ምን ሊያደርጉ ይሆን?›› በማለት ተሰማ ደርቤን ጠይቆት ነበር።

‹‹አላማቸው አልገባኝም›› አለው! ተኩሱ በርዶ ፀጥ እንዳለ። ‹‹ላእከ ለይጣን ነው ብዬሃለሁ›› አለውና አላስችል ብሎት፥ «ሂሩት! ሂሩት!» እያለ ከተኛበት ተስፈንጥሮ ተነስቶ ባዶ እጁን ወደ ኪዮስኩ ሮጠ።

‹‹ተሰማ፥ ተመለስ! ተመለስ ብዬሃለሁ!›› እያለ ቢጮህበትም ስላልሰማው ደርቤም ተነስቶ፥ ክላሺኑን ደግኖ ተከተለው።

ደርቤ ከመድረሱ በፊት ተሰማ የኪዮስኩን በር በትከሻውም በእግሩም እያለ ለብሮት ስለነበረ ተከታትለው ወደ ውስጥ ገቡ።

ወደ ውስጥ የምታስገባውን ስውር በር ተሰማ ያውቅ ነበርና በጨለማ እየተደናበረ ሄዶ ከፍቶ፥ ‹‹ሂሩት! ሂሩት! ሂሩት!›› እያለ ወደ ውስጥ ዘለቀ። ደርቤ ተከተለው።

ክፍሉ ውስጥ ብርሃን ነበር። ተሰማ ጨለማ ውስጥ ቆይቶ በድንገት ብርሃን በማየቱ ለጥቂት ጊዜ ግር ቢለውም፥ ሶስት ሰዎች ወድቀው ታዩት። እህቱ የት እንዳለች ለማወቅ ጊዜ አልፈጀበትም። ሮጦ ሂዶ ላይዋ ላይ ተደፍቶ፥ ‹‹ሂሩትዬ ጥፋተኛው እኔ ነኝ!›› እያለ ይጮህ ጀመር።

ተፈራ ሁለቱ ተከታትለው መግባታቸውን እንዳየ ሽጉጡን ጥሎ፥ የመጨረሻ ጥረት በማድረግ ወደ ሂሩት በይበልጥ ለመጠጋት ሞከረ። እጁን ወደ ሂሩት እንደ ዘረጋ፥ አንድ ጊዜ ብቻ ህቅ ብሎ ፀጥ አለ።

ደርቤ ቀይ መሀረብ ከኪሱ አውጥቶ የተፈራን ፊት ከሸፈነ በሁዋላ፥ ሂሩት ደረት ላይ ተደፍቶ የልብዋን ትርታ አዳምጦ ሲያበቃ ተሰማን የአብሮት ጥበቃ ጉዋዶችን በፍጥነት እንዲጠራ ነገረው። ተሰማ እንባውን እየረጨ ሮጦ ወጣ።

ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ተሰማና የአብሮት ጥበቃ ጓዶች ተከታትለው ሲገቡ፥ ደርቤ በግራ እጁ የሂሩትን አንገት ቀና አድርጎ ደግፎ ይዞ በቀኝ እጁ ክላሺኑን በሰዎቹ ላይ ደግኖ አገኙት።

ተሰማ እንባውን እያዘራ፥ ‹‹ህይወትዋ አለ?›› ብሎ ጠየቀው።

‹‹ትንፋሽዋ አለ›› አለውና እሱም እንባውን መርጨት ጀመረ።

‹‹ቶሎ ሆስፒታል እናድርሳት!›› አለ ተሰማ።

‹‹በምን መኪና? አለው ደርቤ።

‹‹እንግዲያውስ ቤት እንውሰዳት። ቶሎ በል!›› አለው።

ሂሩት አይኖችዋን ከፈተች። ብዥ ብሎባታል። ትኩር ብላ ደርቤን ተመለከተችው። ከንፈሮችዋን በግድ አላቃ፥ ‹‹ደርቤ ነህ?›› አለችው።

‹‹አዎን፥ ለመናገር አትሞክሪ። ደህና ትሆኛለሽ። በርቺ ብቻ›› አላት።

‹‹ስምህ ያስጠላኛል›› ብላ፥ ህይወት የሌለው ፈገግታ አሳየችው።

‹‹ሲሻልሽ ሌላ ስም ታወጪልኛለሽ። አሁን ዝም በይ ብቻ አላት።

‹‹ተፈራ ምን ነው ዝም አለ?›› ብላ ጠየቀች።

መልስ አላገኘችም። እንባዋ ኮለል ብሎ ወረደ። ቆየችና፥ በጣም በተዳከመ ድምፅ፥ ‹‹እውነት አይደለም በሉኝ. . . ፅጌረዳ አበባ. . . ፅጌረዳ አበባ›› አለችና አይኖችዋን ከደነች። ከተከደኑት አይኖችዋ ውስጥ እንባ ይፈስ ነበር።

‹‹ይህን ስፍራ ማን አሳየህ? አለችው፥ ድንገት ነፍስ በዘራ ድምፅ።

‹‹እባክሽን ለመናገር አትሞክሪ። አላት ደርቤ።

ወዲያው ተሰማ፥ ‹‹እኔ ነኝ›› አላት።

ጀርዋን ማመን አቅቶአት አይኖችዋን ከደነች። ግን፥ ዝም አላለችም። አይናችዋን በግድ ከፍታ ትኩር ብላ እያየችው፥ ‹‹አሁን የት ልትወስደኝ ነው?›› ብላ ጠየቀችው

ተሰማ ተፀፅቶ እኔ ነኝ ብዬ ባልነግራት ይሻል ኖሮአል? ብሎ አሰበ።

‹‹ቤትሽ ከዚያ በሁዋላ ሆስፒታል. . .››

‹‹አሳክመህ አድነህ ልትገድለን?››

ደርቤ በድንገት ብልጭ አለበት። ንዴት ተናነቀው። ጉሮሮው ሲደርቅ ተሰማው።

‹‹እዚህ ብትገድለኝ ይሻላል›› አለችው፥ ድክም ባለ ድምፅ።

‹‹ጉሮሮውን በትንፋሹ ጠረገና በሚንቀጠቀጥ ከንፈር፥ ‹‹አውሬሽን ፊልጊ! እኛ አውሬዎች አይደለንም። የኔ አላማ፥ እስከ ተቻለኝ ድረስ፥ እንዳንቺ ያሉትን ወደ አብዮቱ ሰፊር መመለስ ነው እንጂ መግደል አይደለም!›› አላት።

‹‹አላምንህም›› አለቸው።

‹‹እመኚኝ!›› አላት። ‹‹እኔን ባታምኚ ለሰፊው ህዝብ የመጣውን አብዮት እመኚ!››

‹‹ከአደጋ ጋር ድብ – ብ – ቆሽ መጫወት ይብቃሽ ብሎኝ ነበር ተሰማ. . .›› አለች፥ እየተዳከመ በሄደ ድምፅ።

‹‹እኔም ስልክ የደወልሽልኝ ጊዜ ከሁላችሁም ጋር መገናኘት አለብኝ ያልኩሽ ለዚሁ ነበር›› አላት።

የንብ ንግስት ስእል ትዝ አለው። ሂሩት የምትናደፍ ንብ መስላ ታየችው። ከንብ ንግስት ጋር የሚገናኝ ሰራተኛ ንብ ወዲያውኑ እንደሚሞት ድንገት ስለተከሰተለት ጡንቻው ሲወጣጠር ተሰማው።

መዳከምዋን ስላየ ከላሺኑን አንግቶ፥ ሂሩትን አቅፎ ይዞአት ተነሳ። ጥቁር ሀር ነዶ የመሰለው ረጅም ጠጉርዋ ተዘናፍሎ ወርዶ ይታይ ነበር።

ደርቤንና ተሰማን ሁለት የአብዮት ጥበቃ ጉዋዶች ብቻ ተከትለዋቸው ሲወጡ፥ ሌሎች ወደ ሁዋላ ቀሩ። ደርቤ ሂሩትን ተሸክሞ ጨለማውን እየሰነጠቀ

ወደ ቤትዋ ገሰገሰ። ኪዮስኩ ከአቶ ጉልላት ቤት እምብዛም ሩቅ አልነበረም። ደርቤ ላንዳፍታ አቶ ጉልላት ስለቀበሩዋቸው መሳሪያዎች አስታወሰ። ‹‹ነገም ሌላ ቀን ነው›› ብሎ መንገዱን ቀጠለ።

መንገዱ ባዶ ነበር። ንፋሱ ምጥ እንደ ያዛት ሴት ያቃስታል።

በከዋክብት የተከበበች ግማሽ ጨረቃ አይናፋር ልጃገረድ መስላ ብቅ ብላለች። ደርቤ ግን የታዩት፥ ጥቁር ሰማይ ላይ የተፈነጠቁ ቀይ ከዋክብት ነበሩ። ጥቁር ሰማይ - ቀይ ከዋክብት። ድንገት ቆም ብሎ የሂሩትን የልብ ትርታ አዳመጠ።

‹‹ትንፋሽዋ አለ›› አለው ተሰማ ቁርጥ ቁርጥ በሚል ትንፋሹ። ደርቤ መልስ አልሰጠውም። ፍጥነቱን ጨመረ።

እርምጃው ወዴት እንደሚመራው ሊታየው አልቻለም። ልቡ ተንሳፈፈ። ብርድ ቢሆንም አልቦታል። ላቡ በማጅር ግንዱ እየተንቆረቆረ ይወርዳል። ጀርባውን አልቦታል - ሽሚዙ ከጀርባው ጋር እስኪጣበቅ ድረስ። ብብቱን አልቦታል - እና ጡንቻዎቹ ስቃይ ይሰማቸዋል። መንገዱ ወዴት ያመራል? የሚል ጥያቄ ከእርምጃው ከትንፋሹ ጋር - ከልብ ትርታው ጋር - ስልት ይዞ ያስተጋባል - አእምሮ ውስጥ።

ጨረቃዋ ጥልቅ - ጥቁር ጉም ውስጥ። የጠቀሰችው መስለው - እኖ አስታወሰ. . . አምአላፍ በእጁ ፅፎ የሰጠውን ጥቅስ አስታወሰ. . .

Man's dearest possession is life. It is given to him but once, and he must live it so as to feel no torturing regrets for wasted years, never know the burning shame of a mean and petty past; so live that, dying, he might say: all my life all my strength were given to the finest cause in all the world, the fight for the liberation of mankind" . . . ኒኮላይ አስትሮ ቪስኪ. . .

ፈገግ አለ። በፈገግታው ውስጥ ፍኖትን አያት።

ከነአቶ ጉልላት ቤት አጠገብ ሲደርስ እንዳጋጣሚ ሆኖ ‹‹ሙሽራዬ›› የተባለው የሰርግ ዘፈን ከስፈሩ ፀጥታ በላይ ነግሶ ጨለማውን እየጣለ ደምቆ ይሰማ ነበር. . .



በሰፊ አምስት ዓመታት ሃይለ ሥላሴ እዚህ ሀገ
ከመገለጽ ችሎታ የነፈጋቸው ሰፊውን ጭንቅ ከመዘመር ሰ
ሥራዎች ነው። ሰውን ሰብዓዊ ፀባዩን ከማስጠት አንፃ ወይ
መሳሰሉ ሳይ ሰብዓዊ ሰሜት ያሸነፈ ይመስል
ከአብዛ ጉራ ፈጣሪው ሰብዓ ጋር ማለስ በዙ ሰ
የአብዮቱን ሃይሎ ከማንኛውም ሪፍ የመቻቻሪያው
መሆን ነው።

የተቋ ከአገ ጎራ ተሰይ ማሽ ባሕሪይ ገባሰ
በሥርዓቱ ሰለኑ ከማለፍ ታሪክ ይፈሞል የአብዙ
ቋርሰ የተጋሰሁት ዓለማ ሰፋፍም ለሳሳራም
ታማኝነት ሥጡ ሰማሰታረት

ከአድማስ ባሻገር የነሰኑ ደመል በተባሰ ቅ ሁሰት ለሰለዶ
በንሱ ጋርማ የፊሰራኑ የአተራክ ችሎታውን አሰመሰከራል በዚህ
ከአብ ጉራ ብሰሳችሙ የነሁት ልቦሰሱ ደግሞ በከያኒነት ሙያው
ሐውጫ ወደ ፊት እንደሚደ ብዓሰጽ ይታደል

በማንሱሳ ማሩማያ ቤት ያተመ
0113 691933

ዋጋ 7120 ብር

